ለእውነት እንቁም

(የሚሊኒየሙ መርዶ እና ብስራት)

በስሜ ታደሰ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
2004 ዓ.ም

«ማስታወሻነቱ»

የጌታን ፈቃድ በአግባቡ ልብ እልበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ አማኑኤል ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያንን፣ አስከትሎ ቤዛ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰጠኝ በዛም ተገኝቼ በመንፈሳዊ ሕይወቴ አድግ ዘንድ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን በአግባቡ እረዳ ዘንድ በዚያ መንገዱን ስላኖሩልኝ ለእነርሱ ይሁንልኝ።

ይልቁኑ፣ በቤዛ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ልዑልነት በመረዳት ተገቢ የሆኑ ተግዳሮቶችን በመቋቋም የመጽናት ምንነትን እየተማርኩ ከመዝለቅ ባሻገር በዚያች አጥቢያ ውስጥ እንዳገለግልም ሆነ እንድገለገል እግዚአብሔር ድንቅ ቸርነቱን ስለ ገለጠልኝ ዝገጅቶቼ ለማስታወሻነት ብቃት ይኖራቸዋል።

ምስጋና

‹‹በጥንትና በመካከለኛው ዘመን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› ዝግጅቴ ውስጥ ብዙ ምስጋናን ለባለቤቴ እና ለልጆቼ አድርጌ ነበር፤ ዛሬም ይኸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግና ከፍ ማለት እፈልጋለሁ፤ ወላጆቼን፣ እኅቶቼና ወንድሞቼን (አቶ ታደሰ ገብረ ክርስቶስ፣ ወ/ሮ አፀደ ማሞ ከዚያም አካሌ፣ ጽጌ፣ ሙሉ እመቤት፣ መኮንን፣ ጳውሎስ፣ ኢየሩሳሌም፣ ቅድስት፣ ገነት እና ዮሴፍ ታደሰ) የእነርሱ አሻራ በግል አኗኗሬ፣ አመለካከቴ እና እምነቴ የትልቅ ትልቁን ድርሻ ወስደዋል፤ ቸር አምላክ ለእነርሱ እንድገኝ ስላደረገኝ እርሱን በቅድሚያ አመሰግናለሁ፤ እነርሱን አስከትዬ አመሰግናቸዋለሁ።

የቤዛ ባፕቲስት ማኅበረ ምእመንን ከልቤ ዛሬም ነገም አመሰግናቸዋለሁ፤ ይመክሩኛል፣ ያደምጡኛል፤ የተሻለውም ይኽ ነው ብለው የልባቸውን ይገልጹልኛል፤ እነርሱን እንደምወዳቸው እንደ መግለጽ ደስ የሚያሰኝ እና አመሰግናችኋለሁ ማለቴን እንዲያነቡልኝ ከምፈልጋቸው ቀዳሚዎቼ አንደኛው ናቸው።

በቀደመው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዝግጅቱ የጽሑፍ ሥራውን በማረም፣ በመጻፍ ከእኔ ጋር የደከመችው ወ/ት ገነት ተክለ ማርያም ነበረች፣ ዛሬም ምስጋናዬ ይድረሳት፤ ለዚህ ዝግጅት ደግሞ ቸር አምላክ ወ/ት ጸጋ ፈቃደን ባይሰጠኝ ይህ ይነበብ ነበር ወይ ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ፣ ምላሹም በፍጹም የሚል ነው፤ አመሰግንሻለሁ።

መግቢያ

ጥድፊያ በሞላበት ዓለም ውስጥ እየኖርን ሳለ ነው፤ ሌላ ተጨማሪ ሊነበብ የሚገባውን ሥራ ወደ እናንተ ያደረስኩት፤ ገጹ ብዙ ይመስላል፤ ግና በርካታ ርእሰ ጉዳዮችን በየብቻው የሚያስተናግድ ስለ ሆነ አያሰለችም፤ ይህን ደግሞ የመረጥኩት ሆን ብዬ ነው፤ ጥቂት ማንበብ የወደደ ሁሉ ቁም ነገር አገኝበት ይሆን? ብሎ ላሰበው ቅድሚያ የመስጠት ዕድልን ለመቸር፣ እንዲሁም ከዳር ዳር እዘልቃለሁ ለሚልም ነገሮች ሁሉ ተጋምደው ወደ አንድ አቅጣጫ እየተንዘፉ እንዳላቸው እንዲረዱ መፈለጌ ዐይነተ–ብዙ ርእሰ ነገሮችን አካትቼበታለሁ።

ከዚህም የተነሣ፣ የተመጠኑ ለጥናት መነሻ የሆኑ ሥራዎችን እንዲሁም በየራሳቸው ሊቆሙ የሚችሉ ቶሎ ተነብበው ቶሎ ተጠናቅቀው ሊጠቅሙ የሚችሉ ጽሑፎችን በዝግጅቴ አካትቻለሁ። አሰነዳደሬ የይዘት ቅርርብ ያላቸውን ለማጣመር መሞከር ነው፤ እንግዲህ የንባብ ጊዜያችሁን ሳልሻማ አንብባችሁ ምላሻችሁን እሰማ ዘንድ ምኞቴ ነው።

ልብ በሉልኝ፣ አንዳንድ ጽሑፎቼ ለውይይት በቤዛ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ወይም በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዝግጅት ላይ በመቅረባቸው ለዛቸውን እንዳያጡ መጠነኛ ማሻሻያ አድርጌባቸዋለሁ። አንዳንዶች ግን ሙሉ ለሙሉ ‹‹እንደ ወረደ›› ወደ እናንተ የመጡ ስለሆኑ ‹‹የሚያነብ ሁሉ እንደ ቤሪያ ሰዎች ነገሩ እንዲህ ነውን›› እያለ ያብራራውና ያሰፋው ዘንድ እፈልጋለሁ። ይህን ቅጽ አንድ ያልኩበት ምክንያት ተከትሎ የሚመጣ ሌላ ቅጽ ሁለት አብሮት ስላለ ነው።

መልካም ንባብ

ስሜ ታደሰ

ማውጫ

1. ለእውነት እንቁም 7
2. ስመ ጥሩ ሰው 15
3. ፀረ ማርያሙ ማን ነው? 17
4. ልዑል ማን ነው? (ክፍል አንድ) 23
5. ልዑል ማን ነው? (ክፍል ሁለት) 27
6. በእውነት ላይ የተመዘዘ ሰይፍ 32
7. ማማማ፡- ሦስትዮሽ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ 35
8. ቅኝት፡- በ«ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ» መጽሐፍ ላይ .. 40
9. ቅድስት ማርያምና «ልዩ መገለጦች» 53
10. ክለኒንግ፡- «ሰው በሰው ሊፈጠር?» 61
11. ጸሎተ ገብረሐና 68
12. «ለሚመለከተው መሪ ሁሉ!» 71
13. ቅኝት- «መጽሐፍተ ኑፋቄ» በመጽሐፍ ቅዱስ ዓይን ሲታይ 79
14. አንገት የለሾቹ ሰዎች! 86
15. ያልተቀጣ ዓይን አውጣ 91
16. ምርጫችን እሑድ ለምን ሆነ? 94
17. እርቃኑን የቆመው ትውልድ 103
18. ትውፊት እና «የእኔ ድርሻ» 107
19. ግላዊ የነፍስ ነጻነት 110
20. አዲስ አበባ 117
21. ማን ይተምን? የፈጠረ 122
22. በሰውነት ቋንቋ መጠቀም 130
23. ኢትዮጵያ እና አርባ ሁለቱ ጥቅሶቿ 136
24. ለውርጃ ተጠቂዎች ምን ተስፋ አለ? 156
25. ጸምና ጿሚዎች 176
26. ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ 183
27. ውርጃስ ይቅር! 195
28. ፍልስፍና እና ፈላስፎች 210
29. ኃላፊነትና ተጠያቂነት 207
30. ትዳር እና ወሲብ 221
31. ክርስትና እና እስልምና 227
32. ጸጋ - በሰው ሁሉ አፍ ቀሎ የተገኘ ቃል 237
33. አንባቢን እና ጆን ቡንያን 247
34. ሕፃንነት. . . ጣለኝ ወይስ አወደቀኝ? 249
35. ከዚህም የሚበልጥ ታላቁ ተአምር 254

36. መከረኝነት 260
37. ላጤነት እና ዘንድሮ.....265
38. ትጭጭት እና ዘንድሮ.....270
39. የሠርጉ ማግስት ... የምስራች.....274
40. ለምን እንጽፋለን? 279
41. እንተራረም 284
42. ውርጃ = መብት ወይንስ ግድያ? 288
43. የወላጅ አባዜ! 294
44. «ጥሎሽ»ን ጣለብኝ.....299
45. ጸታዊ መፈላለግ 306
46. የሠርጋችን ክቡር እሴቶች እና «አይረቤ» ባህሎች 311
47. የጠንካራ ማኅበረሰብ መለኪያ 321
48. ለተመራቂዎች ሁሉ 324
49. ትችት- በ«መለኮታዊ ራዕይ ሲኦል ሲገለጽ» 327
50. ቀልባችን አጋንንት ላይ ያልሰፈረበት ምክንያት 336
51. ሔዋን የቀየሰችው መንገድ 343
52. የሥነ ፍጥሜው ቅኝት 348
53. ገናን አናግነው!.....355
54. «ዝምታ ወርቅ አይደለም!» 360
55. ቃሉን ማን ተጋፋው.....363
56. መግባባት የፍቅር መሠረት 366
57. 2000ም እንደ 1900!.....369
58. የቀባሪው ጣጣ 373
59. «ሶዶማዊነት» 376
60. የሴቶች ድርሻ በጎብረተሰብና በቤተ ክርስቲያን 385
61. ይሁዳ.....410
62. የሚሊኒየሙ መርዶና ብሥራት.....424

ለእውነት እንቁም

ብዙ ጊዜ የጀመርኩትን ንባብ ዳር አደርሳለሁኝ፤ አልፎ አልፎ ደግሞ ገምሼ ወይም ጀምሬ የምተውበት ወቅትም አለ። ለማቋረጤ በቂ ምክንያት አለኝ። የማነበው ጋዜጣ፣ መጽሔት ወይም መጽሐፍ ይዘቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሳይገጣጠም ሲቀር ያኔ እተወዋለሁ። መተዊ ጊዜዬን በከንቱ እንዳላባክን ይረዳኛል። አለማንበቤ የማይጠቅም ልምምድ እንዳልለማመድ፣ የማይረባና የማያዛልቅ አፈ ታሪክ ውስጥም ገብቼ እንዳልሰጥም ይረዳኛል፣ እናም ከዚህ የተነሣ ለንባቤ ማቋረጥ ምክንያት ቅቡል ነው።

በቅርቡ ከዳር ዳር በዘለቅሁበት ጽሑፍ ደስ ተሰኝቻለሁ። «ለእውነት እንቁም» ይላል፤ ጸሐፊው ፒተር ማስተርስ ናቸው። እርሳቸው «ለእውነት መቆሙ ጥንካሬን እንደሚጠይቅ እና ዋጋ እንደሚያስከፍል» ብቻ ተናግረው አላበቁም፤ ለእውነት ላለመቆም ምክንያት የሆኑትንና የሚመሳሰሉትንም ጭምር ለአንባብያኑ ገልጸዋል። እርሳቸው የሚሉት ሁሉ ስለ ተመቸኝ እናንተም ታነቡልኝ ዘንድ ጓጓሁ።

የጉጉቴን የመነሻ ድልድይ የማደርገው በ1987 ዓ.ም የሕይወት መጽሔት ቁጥር 17 ሽፋን ላይና በውስጥ ገጾቹ የሚነበበውን ከዶክተር አለማየሁ መኮንን ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ ነው።

የመጽሔቱ የፊት ሽፋን «በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ያለውን ልዩነት ለመፍታት ይቻላል ብዬ እገምታለሁ» በሚል ርእስ ደምቋል። ርእሱን ለብቻው አይቼ «እንዴት?» አልኩኝ። ለዚህ ጥያቄዬ ምላሽ ለማግኘት የውስጡን አነበብኩኝ። የዝግጅት ክፍሉ ጠያቂ፣ «ታዲያ በታቦት፣ በማርያም፣ በመላእክት አማላጅነት፣ በደኅንነት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ያለን ልዩነት እንዴት ሊታረቅ ይችላል?» በማለት ይጠይቃል። ለዚህ የዶክተሩ መልስ፣ «ልዩነታችን በትምህርትና በውይይት ይፈታል። ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ ከምንም ነገር በላይ ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ሊሰጥ ይገባዋል። ፕሮቴስታንት ብንሆን ኦርቶዶክስ እራሳችንን ለእግዚአብሔር ቃል ካስገዛን ልዩነታችን እየጠበበ ይመጣል።

ፍጹም አንድነት የምናገኘው በመንግሥተ ሰማያት ብቻ ነው» የሚል መልስን ይሏል።

ምላሹ ከፊል እውነት አለው። ከፊሉ ግን መሆን የማይችል ጉዳይ ላይ ተስፋን ብቻ ሰጥቶ አላፊ ነው። መጽሔቱ የጠየቀው ዓይነት ጥያቄ ግን በእኛ አቆጣጠር በ1986 ዓ.ም አሜሪካ ላይ በተደረገው የወንጌላውያንና የካቶሊክ ቤተ እምነቶች በጋራ ተገናኝተው ከተወያዩ በኋላ ተስማምተው የተለያዩት፣ «ካቶሊካውያንና ወንጌላውያን በእግዚአብሔር ፊት የዳኑ ስለሆኑ አንዱ ሌላውን በወንጌል ለመድረስ የሚያደርገውን ጥረት ያቁም፣ በምትኩ በጋራ ለእግዚአብሔር መንግሥት እንሥራ» በማለት ነበር። ይህ የሆነው እንደ ሌሎቹ ልዩነቶች በውይይት ጠበው ወይም አንዱ ለእግዚአብሔር ቃል ለመገዛት ፈቅዶ ሳይሆን፣ «መቻቻል» የተሻለ አማራጭ ነው በማለት እንደ ነበር ይታወሳል።

ቀደም ብሎም በእንግሊዝ አገር በ1960 እና 1970 በተካሄዱት ተመሳሳይ ጉባኤዎች ላይም ወንጌላውያንና ካቶሊካውያን ተገናኝተው በወንጌላውያኑ በዶክተር ጆን ስቶት ገላጋይነት፣ «የእንግሊዝም ሆነ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ፊት የተወደዱ ሕዝቦች ናቸው፣ እርስ በርሳችን መናቆራችንን እናቁም፣ ልዩነቶቻችን የሚያቆሙት በሰማይ ብቻ ነው፣» በማለት ነበር የቋጨት።

ለእኔ የእነዚህ መግለጫዎች በይዘት ሳይለያዩ በየጊዜው መውጣታቸው ለእውነት የመቆም ምንነትን በአግባቡ እንዳጠና አግዞኛል። በዘፍጥረት 3፡1 ዲያብሎስ ሔዋንን፣ «በእርግጥ እግዚአብሔር በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ ብሎአልን?» በማለት ነበር በሴቲቱ አዕምሮ ውስጥ መዋለልን ወይም ጥርጣሬን የዘራው። ይህ ጥያቄ አዳምንና ሔዋንን ፍጹም ለሆነው ለእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዳይገዙ ያደረገ የዲያብሎስ ፈተና ነው። ማመቻመች (*Compromise*) ምን አለበት ወደሚል አቋም በመግባት ሊቀላቀሉ የማይችሉትን ለማግኘት መሞከር ጥፋትን የሚያስከትል መሆኑን የእግዚአብሔር ሕዝብ በነበሩት በእስራኤላውያን ላይ ታይቷል። እነርሱ አትንኩ የተባሉትን ነክተዋል፤ ግደሉ የተባሉትን ምረዋል፣ ከሌሎች አትጋቡ ሲባሉ ተጋብተዋል፤ ተዋልደዋልም፣ እርምን የተቀደሰ አድርገው

ወስደዋል። ይህ ለእግዚአብሔር ቃል አለመቆምና እውነት ለሆነው አለመገዛታቸው በዘመናቸው ጥፋትን አሳጭዷቸዋል። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር በሁለቱም የኪዳናት መጻሕፍት ውስጥ ከሐሰትና ከሐሰት አሠራር ሕዝቡ እንዲለይ ይመክራል።

ይህን ምክር 1998 ዓ.ም ላይ ቆመን ስንመዝነው ጥንቃቄው እንደ ካቶሊክ ከመሳሰሉት ጋር በመሆን ማሰብን ቸል ብለን፣ «በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል በየጊዜው የሐሰት አሠራርን አዝሎ ለማቆየት የሚደረገውን ጥረት ልብ ሊሉት የተገባ ይሆናል።» በአሁኑ ወቅት ብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የክርስቶስን ትእዛዝ በሙሉነት ባለመፈጸም ተወቃሽ ናቸው። በማቴዎስ 28፡19-20 ለአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው የተግባር መመሪያ በክርስቶስ ትምህርት ወንጌልን ማብሰር፣ ማጥመቅ እና ማሳደግ (ማማማ) ነው። ይህ ኃላፊነት በብዙዎች ዘንድ ወንጌልን በማብሰር፣ ከዚያም በማጥመቅ ላይ ተገትቷል። ደቀ መዝሙር ማድረግና ማሳደግ በበርካታ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ተትቷል። የዚህ መጉደል ደግሞ የስሕተት ትምህርቶችን የመለየት አቅምን በማሳጣት ወደ ክርስቶስ ቁመት አለማደግን ያመጣል። ሕዝቡ ጨለማንና ብርሃንን፣ ርኩሱንና ቅዱሱን ሳይለዩ መዝለቅን ይጋብዛል። ይህ ደግሞ አደጋ ነው፣ ከአደጋም የከፋው የዲያብሎስ መሣሪያ ነው።

እውነትን በመረዳት ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ማደግን ያልመረጠ ጉባኤ እና ወንጌል ተበስሮለት ከጨለማ ተነጥቆና ለብርሃን በቅቶ የተጠመቀ አማኝ በቃኝ ሳይል ማደግና በአጥቢያው የማሳደግ ድርሻ ውስጥ መሳተፍ ይጠበቅበታል። ቤተ ክርስቲያኒቱም የክርስቶስን ትእዛዝ ካልፈጸመች ከእውነት ትምህርት የተነሣ የሚመጣው የመንፈስ አንድነት አይመጣም፤ በምትኩ መናቆር፣ መለያየት፣ መከፋፈል መወቃቀስና መነካከስ የሁል ጊዜ ትእይንቶች ይሆናሉ።

ይህ እንዳይሆን ግን ጽኑ መፍትሔ አለ፡- በመንታ መንገድ ላይ የሚተወውን የዲያብሎስን አሳብ መቃወም ነው። ይህ መቃወም ደግሞ መገለጽ የሚችለው ከስሕተቱ ጋር አብሮ በመኖር ሳይሆን፣ በመለየት እና በመራቅ ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ

ቆሮንቶስ 6፡14-17 «ክርስቶስ ከቤልሆር [ከሰይጣን] ጋር ምን ስምምነት አለው - ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፤ ይላል ጌታ» በማለት የጌታን መልእክትን ያበስራል፡፡ በሮሜ 16፡17፣ «ወንድሞች ሆይ፣ መለያየትን ከሚፈጥሩትና የተማራችሁትን ትምህርት በመቃወም በጕዞአችሁ መሰናክል ከሚያደርጉት እንድትጠነቀቁ አሳስባችኋለሁ፤ ከእነርሱም ራቁ፡፡» በማለት ወንድሞችን ይመክራል፡፡ ለእውነት መቆም በማሳደግ ሥራ ውስጥ ጠንካራ መሠረት መሆኑን ለመረዳት ተከታታዮቹን ተጨማሪ ጥቅሶች ልብ የሚል ልብ ይበላቸው፡፡

- «አሁን የጻፍሁላችሁ፣ «ወንድም ነኝ» እያለ ከሚሴስን ወይም ከሚስገበገብ ወይም ጣዖትን ከሚያመልክ ወይም ከሚሳደብ ወይም ከሚሰክር ወይም ከሚቀማ ጋር እንዳትተባበሩ ነው፡፡ ከእንደዚህ ዐይነቱ ሰው ጋር ምግብ እንኳ አትብሉ፡፡ . . . ክፉውን ሰው ከመካከላችሁ አስወግዱት» (1ኛ ቆሮ. 5፡11-13)፡፡
- «ነገር ግን እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን» (ገላ. 1፡8)፡፡
- «በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና ከትምህርቱ ስቶ የሚወጣ ሁሉ አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት የሚኖር ግን አብም ወልድም አለው፡፡ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ፣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤ ሰላምም አትበሉት፤ የሚቀበለው ሰው፣ የክፉ ሥራው ተ ባባሪ ይሆናልና» (2ኛ ዮሐ. 9-10)፡፡
- «እግዚአብሔርን ከማያከብር ርባናቢስ አፈ ታሪክና ከአሮጊቶች ተረታ ተረት ራቅ፤ ይልቁንም ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራስህን አሠልጥን» (1ኛ ጢሞ. 4፡7)፡፡
- «ማንም የሐሰት ትምህርት ቢያስተምር፣ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ ቃልና እውነተኛ መንፈሳዊነት ከሚያጐለብት ትምህርት ጋር የማይስማማ ቢሆን፣ ያ ሰው በትዕቢት ተወጥሮአል፤ አንዳችም አያስተውልም» (1ኛ

ጢሞ. 6:3-4)::

- «ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት አይኑራችሁ፤ ይልቁንም ግለጡት» (ኤፌ. 5:11)::

እነዚህን ሁሉ መረጃዎች ቸል በማለት ለእውነት መቆም ያልወደዱ ግን ሁሉን በማቀፍ ስም ምክንያት አለን ይላሉ::

ሁሉን ማቀፍ /ማግበስበሱን/ የሚመርጡ ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹ

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚዘራውን የሐሰት ትምህርትም ሆነ እንደ ካቶሊክ የመሳሰሉ ቤተ እምነቶችን በማቀራረብ ሁሉን በጋራ በአንድነት ለማስኬድ የሚጥሩ ግለሰቦች እና ቤተ ክርስቲያናት ለሚሉት ምክንያት አላቸው:: ከምክንያቶቻቸው ጥቂቱን ለመጠቆም ልሞክር::

ምክንያት አንድ

«ወንጌልን ለማዳረስ በጋራ መሆናችን ተገቢ ነው፣» በማለት ውጤቱን በመመልከት ላይ ያተኩራል: ጳውሎስ በሮሜ 3:8 ላይ ግን «በጎ እንዲመጣ ክፉ እንሥራ?» ይላል:: ይህ ማለት ሙሴ እግዚአብሔር «ዐለቱን በመናገር ውኃ ይወጣል» ያለውን በመጣስ ዐለቱን በበትር ሁለት ጊዜ በመምታት ውኃ እንዲፈልቅ ከማድረጉ ጋር ይያያዛል (ዘኁልቁ 20:7-21):: ውኃው በምድረ በዳ በመገኘቱና ማኅበሩም በመጠጣቱ ከጥሙ መርካቱ በውጤቱ ጥሩ ነው፤ ግና ውኃው የተገኘበት መንገድ በሙሴ የአለመታዘዝ አካሄድ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ወደሚሰጣቸው ምድር እንዳይገቡ አገዳቸው:: ልክ እንዲሁ፣ ወንጌልን ለማዳረስ በክርስቶስ እውነት ከማይመሳሰሉ ጋር በጋራ እንሁን የሚል ትብብር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: በዮሐንስ 14:15 ኢየሱስ የነገረን ቁም ነገር «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ::» የሚል ነው::

ምክንያት ሁለት

«ኢየሱስ ከሐሰት አስተማሪዎችና ከሐሰተኞች ሳይለይ አገልግሏል::» ይሄ ሌላው ምክንያት ነው:: ለዚህ ግን ልከኛው

መልስ በማቴዎስ 23፡13፣33 ያለውን ማጤን ነው። እርግጥ ነው ኢየሱስ ሐሰተኞችን አግኝቷል፣ በመካከላቸውም ተገኝቷል። ተገኝቶ ግን፣ «እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገቡ በሰዎች ላይ በሩን ስለምትዘጉባቸው ወዮላችሁ! እናንተ ራሳችሁ አትገቡም፤ መግባት የሚፈልጉትንም አታስገቡም።» እያለ ይዘልፋቸው ነበር። ይህንንም በተለያዩ አጋጣሚዎች አደረገው እንጂ፣ እነርሱን እንደሚጠቅሙ ዕቃዎች በአጠገቡ በማኖር አልተንከባከበም።

ምክንያት ሦስት

«ጳውሎስ የሐሰት መናኸሪያ የሆኑትን ቆሮንቶሳውያንና የገላትያን አብያተ ክርስቲያናት እንዲለያዩ አላዘዘም፣» የሚለው ሌላኛው አብሮ የመኖር ምክንያት ተደርጎ የሚቀርብ ነው፤ ለዚህም ደግሞ ብዙዎች ባለማስተዋል የሚያነሡት ዐብይ ጥቅስ ገላትያ 5፡13 ነው። «ወንድሞቼ ሆይ፤ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤ ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉት፤ ይልቁንም አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል።» የሚለውን በማድመቅ፣ «በፍቅር አንድ ላይ ተሳስበን ብንኖር ይሻላል፣» ይላሉ። የእግዚአብሔር ቃል ግን በገላትያ 2፡8፣9 ሆነ በ2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14 «ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ መንገድ አትጠመዱ» ማለቱን ልብ ሊሉት ይገባል።

ምክንያት አራት

«መለየትን መምረጥ ኃጢአት ነው፣» የሚል አቋም ሌላኛው ስንኩሉ ነጥብ ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡10፣ «ወንድሞች ሆይ፣ በመካከላችሁ መለያየት እንዳይኖር፣ አንድ ልብ፣ አንድ አሳብ እንዲኖራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም እንድትስማሙ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ» ይላል። ይህ ክፍል እርግጥ አንድነትን ያውጃል፤ በአንድ አሳብ በአንድ እውነት የተገዛ አንድነትን በውጤቱ ይናፍቃል፤ ይህን ለማግኘት ደግሞ ለእውነት መቆም ብቻ ማዋጣቱን ይናገራል፤ ከዚህ ውጭ ግን ለእግዚአብሔር ቃል ባለመገዛት የሚፋንነውንና የራሱን የሐሰት ሽቀጥ የሚያራግፈውን መለየት፣ ማራቅና ማስናበት ግን ኃጢአት ሳይሆን

ጽድቅ ነው።

ምክንያት አምስት

«ስንዴውና እንክርዳዱ በአንድ ላይ እንዲያበቅል ተፈቅዷል።» ይህ እውነቱን ከሐሰት ቀላቅለን በመኖር ለመዝለቅ እንደ ሌላው ሁነኛ ምክንያት ሆኖ ይቀርባል። ለዚህ ደግሞ ማቴዎስ 13:28-30 ተጠቃሽ ነው። «እንክርዳዱን ሄደን እንድንነቅለው ትፈልጋለህ?» ብለው ጠየቁት። እርሱ ግን፣ አይሆንም፤ . . . እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ» የሚለውን የኢየሱስ ክርስቶስን ምላሽ ለዚህ ሁሉን አቀፍ ጎብረት ይጠቀሙበታል። ይህ ትምህርት ግን በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊነቀፉ፣ ሊገሠጹ፣ ሊወገዱ የሚገባቸውን ሁሉ እንድትይዝ ያስረዳበት ሳይሆን፣ የዓለምን ሁኔታ ያብራራበት ገለጻ ነው። እውነተኛው የክርስቶስ ትምህርት አለ። ይህ ግን እንዳይዘልቅ ዓለም አመሳስላ ጎብረተሰቡን ለከንቱ የምታበቃበትን መንገድ የሚገልጽ መሆኑን ልብ እንበለው።

ምክንያት ስድስት

«ኢየሱስ አንድ ስለ መሆን ጸልዮአል» ሌላኛው ተገዳዳሪ ነጥብ ነው። ዮሐንስ 17:21 ለዚህ ተጠቃሽ ነው « . . . አባት ሆይ፤ አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ . . . » እጸልያለሁ። ይህን በአግባቡ ለመረዳት ዮሐንስ 17ን በዐውዳዊ ንባቡ ማጥናት የግድ ነው። ኢየሱስ በዚህ ጸሎት ልመናው ለደቀ መዛሙርቱ ነበር፤ እነርሱ ደግሞ በእግዚአብሔር የተመረጡ ደግሞም የተጠሩ ሰዎች ናቸው። እነርሱ ከክርስቶስ ሕይወትና ከቃሉ ተምረዋል። የመንፈስ አንድነት ከቃሉ የተነሣ የነበራቸው የመጀመሪያዋ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ነበሩ። እነርሱም ሁሌም ለእውነት ይቆሙ ዘንድ በቃሉ ይቀደሱ ዘንድ ጸልየዋል። ይህ ጸሎት ከእውነት የራቀ አሠራር ባለበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፣ በአንድ እውነት ላይ ለመቆም በተስማሙበት ዘንድ ዛሬም የሚፈጸም መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል።

ምክንያት ሰባት

«ስለዚህ ንቃ፤ ሊሞት የተቃረበውን የቀረውን ነገር አጽና»

(ራእይ 3፡2)። በዚህ ዝግጅት ይህን ሌላው ስንኩል ምክንያት አድርጌ እወስደዋለሁ። የዮሐንስ ራእይ የመጀመሪያ ምዕራፎች በትንሿ እስያ ለነበሩት ሰባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተላኩ የፍቅርና የግሣጼ መልእክቶች ናቸው። በተላከላቸው ሁሉ ዘንድ «ከክፉው አሠራር ራቁ፣ ተዉ፣ ተለዩ» መባላቸውን ማንም ልብ ሊለው ይገባል። ይህን ቸል በማለት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያሏትን አባላት በየምክንያቱ እያጣች ባለበት ወቅት ለእውነት እንቁም በሚል ስም በልምምጥ የቀሩትንም አባላት እንዳናጣ በመቻቻል የቀሩትን ይዘን እንኑር የሚል ነው። ይህን ግን የቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ኢየሱስ አላስተማረውም፤ አልተገበረውም።

ማጠቃለያ

የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ወንጌልን በማብሰር፣ በማጥመቅ እና በማሳደግ /ማማማ/ መገለጽ ይገባዋል። ይህ የሦስትዮሽ ሰንሰለት መሠረቱ የሚጸናው እውነት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ነው። ለእውነት መቆምን በመኖር የምንገልጽበት ሂደትም ዮሐንስ በመልእክቱ ያዘዘንን መፈጸም ነው። «በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና ከትምህርቱ ስቶ የሚወጣ ሁሉ አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት የሚኖር ግን አብም ወልድም አለው። ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ፣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤ ሰላምም አትበሉት፤ የሚቀበለው ሰው፣ የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናል» (2ኛ ዮሐ. 9-10) ይላል። ይህ እውነት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን የሚያቆም ጽኑ መሠረት ነው።

ይህን ተግባራዊ ባለማድረግ ቸል የምትል ቤተ ክርስቲያን አቋራጭ መንገድን መጠቀም አማራጭ መስሎ ይታያታል። ከዚህም የተነሣ መቻቻልን በመምረጥ በእውነት መሠረት ላይ ካልቆሙት ቤተ እምነቶች ጋር በመጣመር መሥራትን እንደ እውነተኛ ጎብረት ይቆጥራሉ። በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ከቃሉ በማፈንገጥ የሚደረጉ ልምምዶችን፣ ትምህርቶችን እና እንቅስቃሴዎችን በመታገሥ ስም፣ ሰባት እና ከዚህ በላይ ምክንያቶችን በመደርደር መግበስበስ ዋስትና እንዲመስል

ያደርጋሉ።

ይህ ግን ዲያብሎስ ሔዋንንና አዳምን በማሳት ከተጠቀመበት መንገድ ጋር ተቀራራቢ ስለሆነ፣ ሁሉም ልቡን ገዝቶ በሚያልፈው ዘመኑ ያማያልፍ ሥራን ሠርቶ ማለፍ ይጠበቅበታል። ይህም ዋጋ በሚያስከፍለው ለእውነት በመቆም ይገለጽ። ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ «ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት አይኑራችሁ፤ ይልቁን ግለጡት» (ኤፌ. 5፡11)።

ስመ ጥሩ ሰው

ይብዛም ይነስ ሁሉም ሰው ብርቱ ሰውን ይናፍቃል፣ ሁሉም ሰው ከስመ ጥር ሰው ጋር አብሮ መሆኑን ይወዳል። አዋቂዎች፣ በተለይም የታሪክ ሰዎች፣ የሚሉት የድግግም ቃል አለ። «ስመ ጥርን ሰው ያጣ ግለሰብ፣ ሕዝብም ሆነ አገር ከመውደቅ አይድንም» ይላሉ። እኔ ግን፣ «ብርቱ ስመ ጥር ሰውንም ያጣች ቤተ ክርስቲያን ትርፏን ማጉደሏ አይቀርም» እላለሁ።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ዘከረልን ከሆነ፣ ዛሬ በምድራችን ጤናማውን የወንጌል ዘር እየዘሩ ላሉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ለፍሬያማነታቸው መሠረት የጣሉላቸውን የብፁአንን ታሪክ መለስ በማለት ያሳስባችኋል፤ ከጠዋቱ ሐዋርያቱ የዓላማ ጽናታቸውን የገለጹበት የሰማዕትነት አሟሟት ድቅን እያለ ብርታት ይሆናች ኋል። ኋላም በየዘመኑ እየፈኩ ደምቀው ያለፉት ክርስቲያኖች አይዘነጉም።

ቅዱስ መጽሐፍም ሕይወታቸውን ገልጾ ያሳየንን በጌታ የበረቱ ስመ ጥር ሰዎችን ወደናቸዋልና ልጆቻችንን ሳይቀር በእነርሱ መሰየም እንወዳለን፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ዮሐንስ፣ ጳውሎስ፣ ሉቃስ፣ አስቴር፣ ሩት እያልንም እንጠራለን።

እንዲህ ማድረጋችን አንድን ነገር ነው የሚጠቁመው፣ የብርቱ ሰው፣ የስመ ጥር ሰው ጥማታችንን ያመላክታል።

ትዝ ይላችሁ ከሆነ፣ እስራኤላውያን አንድ ወቅት ላይ ስመ ጥር መሪ በማጣት ሁሉም ፋንነው ነበር፤ መሪው ብልሹ ሆኗልና ሕዝቡ ሁሉ ብልሹ ሆኖ ተራከሰ፤ እስራኤላውያኑ እንደ አንድ ሰው ሆነው

የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ መፈጸምን ተዉ፤ አጓጓዛቸው ሁሉ ከድጡ ወደ ማጡ፣ ኋላም ወደ አዘቅቱ ወረደ። የእግዚአብሔር ቃል ተረግጦ፣ የአጋንንት አሠራር ነገሠ። የአሞናውያን፣ የከነዓናውያን፣ የሂታውያን፣ የፌሪዛውያን፣ የኢያቡሳውያን፣ የፍልስጥኤማውያን አማልክት የሕዝበ እስራኤል አማልክት እስኪመስሉ ድረስ ከቤተ መቅደስ እስከ የሰዉ ጎጆ ገቡ። እነ አሼራ፣ በኣል፣ ዳጎን፣ ከሙሽ፣ ሞሌክ፣ አስታሮት የተሰኙት ጣዖታት መሥዋዕትና ካህናት እየተዘጋጁላቸው ተመለኩ።

ይህ ደግሞ የሆነው ለእግዚአብሔር የቆመና እንደ ፈቃዱ የሚመላለስ ሁነኛ ስመ ጥር ሰው በመታጣቱ ነበር።

አንድ ቀን ግን እንዲህ ሆነ። ልዑል የሆነው እግዚአብሔር አንድን ሰው ከመካከላቸው አስነሣ- ስመ ጥሩን ኢዮስያስን። የዚህ ሰው አባት በንግሥናው ዘመን ሁሉ ሕዝቡን እንዳሳተ ኖሮ ሞተ፤ አያቱም ምናሴ በእስራኤል ላይ ለ55 ዓመታት ሲነግሥ ለዐመፀኞችና ለነውረኞች ጥሩ ምሳሌ ሆኖ የጌታን ፈቃድ እንደ ሻረና እንደ ዘበተ፣ ሕዝቡን ከሕያው አምላካቸው አርቆ ሞተ። ዛሬ ግን ብላቴናው ኢዮስያስ የቀድሞ አባቱን የዳዊትን መልካም ምሳሌነት በመከተልና ለእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ታዛዥ በመሆን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ሥራ ሊሠራ ተነሣ (2ኛ ነገሥ. 22፡2)።

ሲነሣም ቀዳሚው ተግባር የጠፋውን የሕጉን መጽሐፍ አስፈልጎ ማስገኘት፣ የተገኘውንም እንዲነበብ በማድረግ ሕይወቱን መለወጥ፣ ኋላም ለሕዝቡ አስነብቦ ማብቃት ነበርና ተሳካለት፤ ስመ ጥር ያልኩት ይህ ብርቱ ሰው በዚህ ብቻ አልተገታም። በቤተ መቅደስ ተከማችተው የነበሩትና ለበኣልና ለአሼራ የሚያገለግሉትን ዕቃዎች አስወጥቶ አቃጠለ፣ በየኮረብታው የነበሩትን መሠዊያዎች አስወግዶ፣ ለእነርሱ የሚያሸበሽቡትን ካህናት አሰናበተ፣ በየአማልክቱ ስም የተዘጋጁትን «ታአምረ ዳጎን፣ ድርሳነ-በኣል፣ መልከ ሞሌክ፣» እየተባሉ የተደረሱትን የዲያብሎስ ክብር ማግኛ መጻሕፍትን አቃጠለ።

ስመ ጥር የሆነው ይህ ሰው ይህን ሁሉ ካስወገደ በኋላ በመጨረሻ በቃል ኪዳኑ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት ለአምላካቸው

ለእግዚአብሔር የፋሲካን በዓል ያከብሩ ዘንድ ሕዘቡን አዘዘ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው እርሱ ብርቱ ነው፤ ሕዝቡ ከተጣለበት አዘቀት፣ ከማጥና ከድጡ አትርፎ በተደላደለ ስፍራ የሚያቆም እርሱ ስመ ጥር ሰው ነው፡፡ እርሱን ሁሉ ሰው ይወደዋል፤ ያከብረዋልም፡፡

አዲስ ኪዳናችንም ይህን ስለ ሁላችን ሲመሰክር፣ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ፣ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ» (1ኛ ጴጥ. 2፡9-10) በማለት ይመሰክርልናል፡፡

ይህ ምስክርነት ዳግም ለተወለዱና በእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥሪ ሊድኑ ለተዘጋጁት ሁሉ ብስራት ሆኖ የሚያገለግለን እውነት ነው፡፡ አንባብያን ሆይ፣ «ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይፈለግበታል» የሚለው መለኮታዊ ቃል የሚፈጸምባቸው ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ብርቱ ሰውን፣ ስመ ጥር ሰውን በማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ወግኖ ለእግዚአብሔር የሚያበቃ ሰውን በፊታቸው በታማኝነት እንዲመላለስ ይጓጓሉ፣ ይጸልያሉ፡፡ ታዲያ ለምን እናንተ የጸሎቱ መልስ ሆናችሁ የኢዮስያስን ፈለግ አትከተሉም፡፡

ፀረ ማርያሙ ማን ነው?

አንዲት ሴት ከሕዝቡ መካከል ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፣ «አንተን ወልዳ ያጠባች እናት እንዴት የተባረከች ናት» አለች፡፡ ኢየሱስ ግን፣ «የተባረኩስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው በሥራ ላይ የሚያውሉት ናቸው» አላት (ሉቃስ 11፡27-28)፡፡

ሴቲቱ በኢየሱስ ትምህርትና ድርጊት ተደነቀች፣ የመደነቋንም መንሥሔ በእናቱ በማርያም ላይ በማድረግ፣ «እንዴት የተባረከች ናት» በማለት መሰከረች፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሴቲቱን የአድናቆት ምክንያት ቸል አለ፤ የእርሱንም ተወው፤ በምትኩ እናቱም ሆነች ሌላው ሕዝብ የተባረከ የሚሆነውም ሆነ የሚባለው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው በሥራ ላይ ያዋሉ እንደ ሆነ

መሆኑን በአንክሮ ገለጸ።

በዚህ ጽሑፍ ይህን መሠረታዊ ቃል በመግቢያነት መጠቀሜ መልእክቴን በመጨረሻ ላይ ለመደምደም የሚረዳኝ ሆኖ ስላገኘሁት ነው።

ለመሆኑ «ፀረ ማርያሙ ማን ነው?» . . . የሚለውን ጥያቄያዊ ርእሰ-ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት ማርያምን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት እንደ ተገለጸች አስቀድመን እንመልከት።

ታሪክን በጥንቃቄና በእርግጠኝነት የሚጽፈው ሉቃስ በወንጌሉ ማርያም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘች (1:30)፣ ከእግዚአብሔር የሆነውን መልእክት እሺ ብላ የምትቀበል (1:38)፣ ከሴቶች ሁሉ ይልቅ የተባረከች (1:42)፣ መድኃኒት በሆናት አምላኳ የምትደሰት (1:47)፣ ዝቅተኛ አገልጋይ መሆኗን የተረዳች (1:48)፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸሟ ትውልድ ሁሉ የተመሰገንሽ የሚሏት (1:48)፣ የሚሆኑትን ድርጊቶች እያየች የተስፋ ቃሉን መፈጸም የምታስተውልና የምትደነቅ (2:19-33)፣ ኢየሱስን ከማይቀበሉት በሚመጣባት መከራና ሞት ነዘንተኛነቷ የሚታወቀው (2:34-35) እና «ኢየሱስን አጥታው ከቤተ መቅደስ ከማግኘቷ በፊት ተጨንቃ እንደ ነበር» (2:48) ሉቃስ በወንጌሉ ገልጾታል።

ማቴዎስ በምዕራፍ 1:20-25፣ 12:46-50፤ ማርቆስ በ3:31-35 ላይ ከላይ የተነሡትን መሠረታዊ ነጥቦች በመድገም የሚያጠናክሩ ሲሆን፤ ዮሐንስ በምዕራፍ 2:3-5 ማርያም ሰዎች ኢየሱስ የሚላቸውን ብቻ እንዲፈጽሙ መምከርዋ፣ እንዲሁም በሉቃስ ጸሐፊነት በተዘጋጀው በሐዋርያት ሥራ 1:14 ላይ ማርያም ሁል ጊዜ ከክርስቲያኖች ጋር በመሆን ትጸልይ እንደ ነበር ይገልጻል።

ከላይ የተነሡት መሠረታዊ ዝርዝር መረጃዎች ማርያምን እንድናውቃት እና ስለ እርሷም በአወቅነው እንድንናገር ይረዳናል። ታዛዥ፣ ትሑት፣ አገልጋይ፣ የተመሰገነች፣ መካሪ፣ ጸላይ፣ በጌታዋ የተደገፈች እንደ ሆነች እና እንደ ነበረች መናገር፣ ማስተማርና መስበክ ማንንም ፀረ ማርያም ወይም የማርያም ጠላት አያሰኝ ውም።

ይልቁኑ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከገለጻት ውጭ በባሕሪዋና በድርጊቶቿ ላይ ጨማምሮ፣ ቀይሮ፣ ገለባብጦ የሚናገር ቢኖር ያ

ሰው ወይም ያ ቡድን የማርያምን ስምና ታሪኳን አጥፍቷልና ፀረ ማርያም ሊሰኝ ይገባዋል።

በማርቲን ሉተር የተመራው የፕሮቴስታንት የከፊል ተሐድሶ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ አንድ መቶ ዓመት ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ ታላቅ የወንጌል እንቅስቃሴ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት 1424-68 ተካሂዶ ነበር። የወንጌል መልእክተኞቹ መሪ እስጢፋኖስ ይባል ስለ ነበር፣ ተከታዮቹ ደቂቀ እስጢፋኖስ በመባል ታወቁ። እነርሱ በክርስቶስ በማመን መጽደቅን፣ እንዲሁም ለማርያምና ለመስቀል ስግደት አይገባም በማለታቸው ተወገዙ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች የተወሰነባቸውን ብይን በሚከተለው ሁኔታ ጽፈውታል።

> «በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚባሉ ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስግደት አይገባም የሚሉ መናፍቃን እንደ ተነሡ ይጽፋል። ይኸው ዜና መዋዕል እንደሚለው፣ እነዚህን መናፍቃን ንጉሡ ባሉበት ሊቃውንቱ ተከራክረው ረቷቸው። ከዚህ በኋላ እነ ደቂቀ እስጢፋኖስ ለፍርድ ቀረቡ፣ ንጉሡም ፍርዳቸውን ከምእመናን እንዲቀበሉ የተሰበሰቡትን ምእመናን ጠየቁ። ሁሉም በሞት ቅጣት እንዲቀጡ በየነባቸው። በመጨረሻም፣ አፍንጫቸውን ተፎንክው /ተቆርጠው/፣ ምላሳቸውን ተቆርጠው፣ በድንጋይ ተወግረው የካቲት ሁለት ቀን ሞቱ» በማለት ጽፏል።

«<u>በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን</u>» ታሪክ አዘጋጅ ወንድዬ አሊ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ ደቀ እስጢፋኖስ የተባሉት ተከታዮች መናፍቃን የሚል ስም ተሰጥቷቸው ከጎብ ረተሰቡ እንዲገለሉና እንዲገደሉ መደረጉን በጊዜው የወጣውን አዋጅ በመዘርዘር እንደሚከተለው አስፍሯል፦

> *«በሁለቱም ጊዜያት ድንግል የምትሆን የማርያም ምእመናን የሆናችሁ ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ! እንዲህ እላችኋለሁ ማናቸውም ሰው ሁሉ ደቀ እስጢፋኖስን የተቀበለ፣ ከእነርሱ ጋር የተባበረ፣ በቤቱ ውስጥም ያኖራቸው ወይም በቤተ ክርስቲያንና በርስቱ ምድር*

ያኖራቸው ቢገኝ ሹመት ያለው ቢሆን ከሹመቱ ይሻር፣ ቤቱም ይዘረፍ፣ ገንዘቡ ሁሉና ያለውም የምድሩ ርስት ለባዕድ ይሁን። እነዚህ ደቀ እስጢፋኖስ ለድንግል ማርያምና ለአንድ ልጅዋ መስቀል መስገድን እምቢ ያሉ ናቸውና በእውነት አይሁድ ናቸው። ከደቀ እስጢፋኖስ የሆነውን ሰው አግኝቶ ሰላምታ የሰጠው ሰው ሁሉ ዕድል ፈንታው ደቀ እስጢፋኖስን ለተቀበሉ እንደሚገባቸው ይሆናል።»

የዚህን አዋጅ ውስጣዊ ይዘት ብንፈትሽ፣ «መናፍቃን» የተሰኙት ሰዎች ፍጡር በመሆኗ ለማርያም ስግደት አይገባትም ማለታቸውን፣ ያዳነን ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ የሠራው ሥራ እንጂ፣ መስቀያው መስቀሉ እንዳልሆነ ማመናቸው ነበር። በዚያን ወቅት በእነዚህ ሰዎች ተቀጣጥሎ የነበረው የወንጌል ዜና ፈጥኖ የከሰመ የመሰለበት ድርጊት ተከታተሎ በወቅቱ በነበረው በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መቀጠሉን መጻሕፍት ያስረዱናል። ዘርዓ ያዕቆብ ንጉሥ ብቻ ሳይሆን ጸሐፊም ነበሩና በዘመነ መንግሥታቸው ማርያምን የሚመለከት በርካታ ድርሳናትና ገድላ ገድሎች እንዲጻፍላት አድርገዋል። ካጻፉት መጽሐፍ ዋንኛው «ተአምረ ማርያም» ነው። ይህ መጽሐፍ እንዲደረስ የተፈለገበት ሁነኛ ምክንያት፡- «ሰዎች ሁሉ በአዲስ ኪዳን ላይ የተገለጸችውን ማርያምን በትክክል ይወቋት» በማለት ያስተማሩትንና የተረዱትን ሰዎች በጽኑ ለመቃወም እንደ ነበረ የታሪክ መጻሕፍት ይመሰክራሉ።

በዚህ መጽሐፍ «ፀረ ማርያሙ ማን ነው?» የሚለውን በአግባቡ ለማስተናገድ ማርያም እንዴት በ«ተአምረ ማርያም» ውስጥ እንደ ተገለጸች ውሱን ምሳሌዎችን በማንሣት ዝግጅቴን አጠቃልላለሁ።

ምሳሌ 1. ተአምረ ማርያም ምዕራፍ 12፣ «ማርያም ከልጇ ጎን በፈሰሰ ደሟ እኛን ንፁሐን አደረገችን» ይላል።

ምሳሌ 2. ተአምረ ማርያም ምዕራፍ 32 በዝሙት ምክንያት ተ ይዛ በሙሴ ሕግ መሠረት በድንጋይ ልትወገር የነበረችው ሴት ለሦስት ቀን ታገሡኝ ብላ ጠየቀች፣ ወዲያውም የማርያምን ሥዕል አስመጥታ፣ «ሰዎችን ሁሉ የምታድኛቸው ሆይ፣ አድኑኝ» እያለች

በማልቀሷ ማርያም እንዳዳነቻት በመግለጽ ለቁስ ኃጢአትን ስለ መንገር ኃላፊነት ያወሳል።

ምሳሌ 3. ተአምረ ማርያም ምዕራፍ 43 ታሪኩን ከተነተነ በኋላ፣ «እመቤት ሆይ፣ ካንቺ ዘንድ ሽቶ/ፈልጎ/ የወደደውን ሁሉ ያላገኘ ማነው? ባንቺስ አምኖ ያፈረ ማን ነው? አንቺንም ለምኖ ወደ ገሃነም ያወረድሽው ማን ነው? ወደ መንግሥተ ሰማይ አገባሽው እንጂ» ይላል።

ምሳሌ 4. ተአምረ ማርያም ምዕራፍ 49 ጌታ ማርያምን፣ «በእኔ ምክንያት ከገጠሙሽ መከራዎች ከፍተኛው የትኛው ነው?» ባላት ጊዜ አምስት መከራዎቿን ትነግረዋለች። ጌታም ይህንን ከሰማላት በኋላ በእኔ «ምክንያት ያገኙሽን እነዚህን ሐዘኖችና መከራዎች ሰላመ ገብርኤልና አቡነ ዘበሰማያትን እያለ ማንም ቢጸልይ ስለ እርሷ ሲል ኃጢአቱን እንደሚያስተሰረይላት» ቃል ይገባል።

ምሳሌ 5. ተአምረ ማርያም ምዕራፍ 15፣ ማርያም በቀኝዋ ያለውን መልአክ በእጁ የያዘውን የመስቀል ጦር በመቀበል የሰውየውን ጎድን መውጋቷን ያስረዳናል። ይህ የተወጋው ሰውም ደሙ ፈስሶ መሞቱን ተአምሩ በሚገልጸው እደመድማለሁ።

እነዚህ አምስት ምሳሌዎች አንድ መቶ አሥራ አንድ ምዕራፎችን ከያዘው መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው። እስቲ በአዲስ ኪዳን የተገለጸችውን ማርያምን መለስ ብለን እናስታውሳት። እርሷ ለእውነት ታዛዥ፣ አክባሪ፣ ትሑት፣ በአገልግሎቷ የተመሰገነች፣ ችግርተኞችን መካሪ ጸላይ መሆኗን ያስገነዝበናል።

በትይዩ ደግሞ እስጢፋኖስንና ተከታዮቹን ለመቃወም የተ ዘጋጀው «ተአምረ ማርያም» በምዕራፍ 12 ማርያም የክርስቶስ ደም ተትቶ ኃጢአተኞች እርሷ በደሟ እንዳነፃች መናገሩ፤ በተአም ረ ማርያም ምዕራፍ 32 በዝሙት ከተያዘችው ሴት በመነሣት ኃጢአተኞችን እግዚአብሔር ብቻ ሊምራቸው ሲገባ እርሷ የምትምር ሆና መገኘቷ፤ በተአምረ ማርያም ምዕራፍ 43 ድነት ክርስቶስን በማመን ብቻ የሚገኝ የዘላለም ሕይወት ሆኖ ሳለ፣ በዚህ ምዕራፍ ግን ማርያምን ብቻ ማመን ወደ ገሃነም እንደማያወርድ መገለጹ፤ በተአምረ ማርያም 49 የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ወደ አብ የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ኢየሱስ መሆኑና የኃጢአት

ስርየትም በዮሐንስ 3:16 መሠረት በኢየሱስ መሆኑ ተገልጾ ሳለ፣ ተአምረ ማርያም ግን ኢየሱስ ቃሉን አፍርሶ ስለ እርሷ ጎዘን ሲል ውሳኔውን መሻሩን መግለጹ፤ በመጨረሻም፣ በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 15 ማርያም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ትሑትና አዛኝ ሴት ሆና ሳለ፣ ሰውየውን ወግታ በመግደል በወንጀለኝነት መቅረቧ በብርቱ ከሚያሳስቡት ጉዳዮች ዋንኞቹ ናቸው።

እንግዲህ ፀረ ማርያሙ ማን ነው? ታሪኳን ያዛነፈ፣ ያበላሸ፣ ያለ ስም ስም፣ ያለ ሥራ ሥራ በመስጠት የሰበካትና ያስተማረው፣ ወይስ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተገለጸላትን ማንነቷን ብቻ አምኖ የሰበከና ያስተማረ? ፍርዱን ላስተዋይ ትቼ ወደ ማጠቃለያ ጥቅሴ ሉቃስ 11:27-28 ልመለስ፦ «የተባረኩስ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ሰምተው በሥራ ላይ የሚያውሉት ናቸው።» በቃ።

ልዑል ማን ነው?

ክፍል አንድ

« . . . እግዚአብሔር ድቅድቅ ጨለማም ሳለ ጥቁር ቅንቅንን በጥቁር ዐለት ላይ የምታደርገውን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል::»

ይህን አባባል የመረጥኩት ይብዛም ይነስ ልዑል እግዚአብሔር መሆኑን ይገልጽልኝ ይሆናል ብዬ ነው:: የአማርኛ መዝገበ ቃላት ልዑል የሚለውን ቃል ሲፈታ፣ «ከፍ ያለ፣ ከሁሉ በላይ ያለ፣ ተ ለዐለ፣ ከፍ ከፍ አለ፣» በማለት ልዑል ከመታወቅ፣ ከመመርመር ከአዕምሮ በላይ ያለ እግዚአብሔር መሆኑን በገጽ 53 ከሣቱ ብርሃን ተሰማ ይደነግጋሉ:: የአማርኛ ሥነ ቃላት አዘጋጅ የሆኑት ተፈራ ወርቅ አርምዴ «ልዑል»ን «ባለማርማ፣ እጅግ የከበ ረ» በማለት ይፈቱታል:: እኒህ ፍቺዎች እንደ ተጠበቁ ሆነው፤ እግዚአብሔርን እንረዳው ዘንድ የገለጠልን ቅዱስ መጽሐፍ ልዑሉን እንዴት ገልጾት፣ እኛስ እርሱን እንዴት ተረዳነው? እኚህ የክፍል አንድ እና ሁለት ንባባችን ይሆናሉ:: አሁን ጥቂት የልዑል መገለጫ ዎችን ላነሣሣ::

* * *

መቼም «ተስማምተው በሦሩት ወንጀል ትንሣኤ የለም» እንዲሉ፣ «የዮሴፍ ወንድሞች ብላቴናውን ባሪያ» ሆኖ እንዲኖር ሸጡት:: ገዢዎቹም ዳር አገር ይዘውት ዘለቁ፣ ማንም ዱካውን ተ ከትሎ እንዳያገኘው ሆነ፤ ታናሽየው ዮሴፍ፣ ባህሉ፣ ቋንቋው፣ እምነቱ፣ ኑሮው ወዳልሆነ አገር ተሰደደ:: እነርሱ ወንጀላቸውን ከድነው አባታቸውን በደም የነከሩትን ጌጠኛ ጥብቆ «ይህ የማን ይሆንን?» አሉት:: ያዕቆብ በኀዘን ሰከረ፤ ላይጽናና በዚያው ማለ፤ አዘነ፣ አለቀሰ፣ ተሳቀቀ፣ እናም ሁሌ ሞቱንና መቃብሩን ይናፍቅ ጀመር:: እንግዲህ ሰዎቹ ታሪክን እንዲህ ሠርተው ደመደሙ::

በሌላ ጊዜ፣ በሌላ ዘመን ግን እንዲህ ሆነ፤ ቀጥሮ የማይሰጠው ራብ ሲገሰግስ ምድሪቱንና የያዕቆብን ቤተሰብ ከብቦ መግቢያ መውጪያ አሳጣ፣ ረሀብ ጸንቶ ሳለ የተስፋ ቃል ከወደ ግብፅ ተ ሰማ:- «የተትረፈረፈ እህል በዚያ አለ!» የሚለው የምሥራች ልጆቹን ወደዚያ ያስልክ ዘንድ ያዕቆብን አነሣሣው፤ ተላኩም:-

ደርሰው እየሸመቱ ሳለ ዮሴፍ ተመልክቶ አወቃቸው፤ እነርሱ ግን አላወቁትም፣ ታሪኩን ወዲያ ማዶ ጨርሰዋልና ያውቁትም ዘንድ ምንም ፈንታ አልነበራቸውም::

ዮሴፍ ግን በራብ ጠመንጃ ተሰድደው ለደረሱ ወንድሞቹ፣ «የሸጣችሁኝ ዮሴፍ እኔ ነኝ» አላቸው፤ ይህንንም ሲያብራራ፣ «ወደዚህ የላከኝ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ እናንተ አይደላችሁም:: በእርግጥ እናንተ ክፉ ነገር መክራችሁብኝ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ወደ መልካም ለወጠው» በማለት ደመደመ::

እንግዲህ ልዑል እግዚአብሔር ሆኖ ሲገኝ ሁሉንም ነገር እንደ ገዛ ፈቃዱ ተቆጣጥሮ እርሱ ለአሰበው ዓላማ ሲፈጽም፣ የዚህ ብቸኛ ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ይገለጻል::

* * *

ቀውስ ሲፈጠር የሚለየው፣ አባት ከቤተሰብ ሲለይ፣ መጋቢ ከቤተ ክርስቲያኑ ሳይኖር፣ መምህር ከትምህርት ቤት ሲጠፋ፣ የአገር መሪ አገሪቱን ድንገት ሲለቅ፣ መናወጥ ይከተላል:: ለዚህ ትኩረቴን በአገር መሪ ላይ ላድርግ:- ኢትዮጵያንም በምሳሌነት ልጠቀም:: በ1920ዎቹ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከአገር ወጡ የሚል ወሬ በሕዝቡ ዘንድ ሲሰማ ጥቂቱ «ታዛቢም የለ» ብሎ «ባንዳ» ለመሆን ፈጠነ፤ ጥቂቱ በወዳጁ ላይ ሰይፍ አነሣ፤ ጥቂቱም ዘረፋን እያካሄደ ሄደ:: ከ50 ዓመት በኋላ በ1980 ፕሬዚዳንት መንግሥቱ አገሪቱን ጥለው ጠፉ ሲባልም፣ በየከተማው ብጥብጥ እና ሕገወጥነትም ጨመረ፤ ይህ ሁሉ ግን የሆነው መሪው ካለመኖሩ ነበር::

ጥንት ዓለምን ከገዙ አገሮች አንዷ ባቢሎን ነበረች:: ገሸርውም ስመ ጥሩው ናቡከደነፆር ነበር:: ይህ ሰው አንዲትን አገር ብቻ ሳይሆን፣ አገራትን ጠቅልሎ በአግባቡ ያስተዳደረ ሰው ነበር:: ግና ንስሐ አልገባ ባለበት ጉዳይ መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ «ዛፉን ቁረጡ፣ ቅርንጫፎቹን ጨፍጭፉ፣ ቅጠሎቹን ሽምጥጡ፣ ፍሬውንም በትኑ፣ አራዊቱንም ከጥላው ሥር፣ አዕዋፍንም ከቅርንጫፎቹ ላይ አብርሩ፣ ጉቶውን ግን ተዉት» እያለ ወደ እርሱ ደረሰ::

ከዚህም የተነሣ ንጉሡ ከመንግሥቱ ተሰውሮ ወደ ጫካ ተ

ሰደደ። በዚያም ምግቡ እንደ በሬ ሣርን መጋጥ ሆኖ ጥፍሩ እንደ ሰማይ በራሪዎች ረዘመ። ጠጉሩ በቁመቱ ልክ አደገ፤ ይህም ድርጊቱ ለተከታታይ ዓመታት ዘለቀ። እንግዲህ ይህ እንዲህ ከሆነ ታላቋ የባቢሎን መንግሥት እንዴት ውላ አደረች? ሕዝቡስ ለዓመታት ያለ መሪ እንዴት ተወጡት? አገሪቱንስ ማን ገዛ? የእነዚህ ምጥን መልስ ልዑል የሆነው እግዚአብሔር የሚል ነው።

ንጉሡ ወደ አእምሮው ተመልሶ ከጫካው በወጣ ጊዜ የመጣው ወደ ዙፋኑ ነበር። በዚያም የገጠመውን ሁኔታ በአንደበቱ ሲገልጽ፣ «. . . አማካሪዎቼና መኳንንቶቼ በደስታ ተቀበሉኝ፣ ከቀደመው የበለጠ ክብር ተጨምሮልኝ በንጉሥነቴ ጸናሁ። እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ ትክክል ነው፤ መንገዱም ቅን ነው፤ በትዕ ቢት የሚመሩትንም ሁሉ ማዋረድ ይችላል» አለ። እንኪያስ እግዚአብሔር ቀውስንና ሽብርን አስወግዶ መሆን የሚገባውን ታላቅ የተባለውን የመንግሥት መዋቅር በአግባቡ የሚቆጣጠር የሚገዛም መሆኑ እንከን የለሽ ጌትነቱን ይመሰክራል፣ ይህም ልዑልነቱ ነው። እስቲ ደግሞ ተከታዮቹ ምንን ይጠቁሙ ይሆን?

«ከአገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ፤ ቢጭኑት አህያ ቢያሸክሙት ፈረስ» የሚለው አባባል በባዕድ አገር ሁሉን ሆኖ መኖርን፣ «እሺ» ባይነትን ይገልጻል። በተመሳሳዩ «አነር ነብር ነበር ከአገሩ ሳይወጣም» ሌላው ነው። በአገሩ የተከበረው ነብር ድመት ያክል ሆነ ጭራውን ያለ አገሩ ሸጎጠ፤ የሚል ትርጉም በመስጠት ለመኖር «ራስን መሸጥ» የሚል ፍቺ ይሰጠናል። ይህም የብዙዎቹ ሕይወት ነው።

አይሁዳዊው መርዶክዮስ ግን እነዚህን አባባሎች ንቋል። በባዕድ ምድር የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት ሊፈጽም በአረማውያን መካከል ተገኝቷል። «ለሚያልፍ ቀን» የሚለውን የማመቻመች መርጎ ሽሮ ለገናናው መሪ ለሃማ ስግደትን ከለከለ። በትይዩ ዓለሙ ሁሉ ለሰውየው ሰግዷል። ሐማ ለእምቢ ባዩ መርዶክዮስ ሞት አዘጋጀ፤ አሟሟቱም በስቅላት ሆኖ ዝግጅቱ ተጠናቀቀ፤ አልጫን ያለው አህያ፣ አልሸከም ያለው ፈረስ፣ አነር አልሆንም ያለው ነብር ሕይወቱ ልትሸጥ ጥቂት ቀራት።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል በዚያች የመጨረሻ አጣብቂኝ ሰዓት

ከአርጤክስስ ከንጉሡ እንቅልፍ ሸሸ፣ እናም እስኪነጋ አልያም ተናፋቂው እንቅልፍ እስኪመጣ የታሪክ ድርሳናት በጆሮው ይንቆረቆሩ ዘንድ ባለሟሎቹን ያስነበብ ጀመር። ንጉሡ ለማድመጥ ከትረካዎቹ ውስጥ እዚህ ጋ ሲደርስ የልቦናው ዓይን ነቃ፤ ጆሮውም ያደምጥ ጀመር። አስጨርሶም እንዲህ አለ፣ «እንኪያስ ንጉሡን ላተረፈው ለመርዶክዮስ ምን ተደረገለት?» ምላሹ ምንም ምንም የሚል ነበር። «ሐማን ጥሩ» ተብሎ ተጠራ። «ንጉሥ ለሚወደው እንዲህ ይደረግለታል» እያልክ በፈረሴ ላይ አኑረህ ልብሰ መንግሥቴን አልብሰህ በከተማው አግንነው» አለለት። በሃያ ሁለት ሜትር ከፍታ በተዘጋጀው የእንጨት መስቀል ሊሰቀል ያለው መርዶክዮስ ባሠቃዩ እጅ ከበረ። በዚህም ልዑል እግዚአብሔር መሆኑን ገለጸ።

ማን ያውቃል ሐማ ትእዛዙን ከንጉሡ ጆሮ እያዳመጠ በዚያ ቅጽበት፤ «እንዲህ አድርጌስ ቢሆን ኖሮ . . .» ይል ይሆናል፤ «አለመስገዱን እንዳወቅኩኝ ሳልታገሥ ከመሬት ቀላቅዬው ቢሆን ኖሮ! . . . ለአማልክቴ አሳብቄ ወገቡን አሽመድምጄ ቢሆን ኖሮ! ንጉሡ ከመጣራቱ ከደቂቃ በፊት ሰቅየው ቢሆን ኖሮ!» እነዚህ ጥቂት ኖሮዎቹ በብዙ መላዎቹ ቢተኩም፣ ልዑል የሆነው እግዚአብሔር ዕቅዱን ከመፈጸም ቸል አላለም።

* * *

«የሮጡ አመለጡ» የሚለው አነጋገር በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አለው። እርግጥም፣ ስኬታማ ሕይወት በጥረት ሊገኝ ይችላል። ይህ ማለት ግን ሁል ጊዜ ልከኛው መንገድ እርሱ ነው ማለት አይደለም።» «ምሕረት ለሮጠ ወይም ለወደደ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለወደደውና ለማረውም ይሆናል፣» ተብሎ ተጽፏል፤ ሆኗልም። ለዚህም ተጠሪ ሰው ዳዊት ነው።

ዳዊት በብልጠት የተሞላ ሰው አልነበረም፣ ምኞቱን ጠብቆ ራሱን አላኖረም፣ ለብር የሚያበቁ የዕድል በሮችን አልተጠቀመባቸውም፣ ለንግሥና የሚበቃ ሰው ሲፈለግ፣ እርሱ በዚያ አልነበረም፤ ጎልያድ ሁሉን ሲያንቀጠቅጥ፣ እርሱ ፈጥኖ አልተገኘም፤ ሳያል ሲያሳድደው፣ ከመሸሸ በቀር አልተጋፈጠም፤ እየሸሸም ጠላቱ ከእጁ ሲወድቅ አላጠቃውም፤ ከዚህ የተነሣ በእነዚህ ሁሉ

አቅም ማጣቶች ዳዊት የት ይደርስ ይሆን? በሰው አመለካከት የትም አይደርስም።

ግና አቅመ ቢስ ያሰኙት ሁሉ አስተዋጽኦ አላቸው። እርሱም ጊዜው ሲደርስ የአደባባይ ሰው እንዲሆን ለዙፋን እና ለንግሥና አጓጓዙት፣ እረኛ ንግሥናን ቢያስብ ሞኝነት ነው፤ ንጉሥነት ወደ እረኛው ሲመጣ ግን አምጪው በልዑልነቱ የሚገለጠው እግዚአብሔር ብቻ ይሆናል። ለዚህም ነው፣ «እግዚአብሔር እረኛዬ ስለሆነ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አላጣም» ያሰኘው።

እንኪያስ ልዑል ማለት በዮሴፍ ወንድሞች የተከናወነን ግፍ ለአደባባይ የሚያወጣ፣ «የዮሴፍ መገፋትን የሚክስ፣ በናቡከደርናፆር ትዕቢተኞችን ዝቅ የሚያደርግ ልክንም የሚያሳውቅ ሕዝብን ሁሉ የሚገዛ፣ በመርዶኪዮስ ከሕዝቡ ጋር የሚጸና፣ የሚያከብር፤ በዳዊት ደካማን የሚያበረታ፣ ከፍ የሚያደርግ በመሆኑ ጳውሎስ ለዘንድሮዎቹ ለእኛ እንዲህ አለ፣ «. . . እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን . . .።» በጥቁር ዐለት ላይ ያለችን የጥቁር ቅንቅን አካሄድ በድቅድቅ ጨለማ የተቆጣጠረ ጌታ፣ ለእኛ ማ ልዑልነቱ እንዴት አይደምቅ!

ልዑል ማን ነው?
ክፍል ሁለት

የርእሴን ተጠቃሽ ጥያቄ መመለስ የምችለው መግቢያዬን «በዕቁብተኞቹ» ተረት ከጀመርኩ ብቻ ነው። ተረቱ «ዝሆን፣ አንበሳ፣ አቦሸማኔ፣ ጅብ እና ምድር ዕቁብ በየወሩ ሊጠጡ ተስማሙ» ይላል። እኚህ አምስቱ ዕቁብተኞች እንዲሆኑ ያስገደዳቸው ሁሉም ሊያቋቁሙ ለፈለጉት ድርጅት ገንዘብ ስላጠራቸው ነው። የተ መኟቸው ድርጅቶች ደግሞ፦

ዝሆን፦ የፍጥነት ጨማሪና የክብደት ቀናሽ የመድኃኒት ማም ረቻን፣

አንበሳ፡- ለአንበሶች የቁጣ መንሥኤን የማወቂያ የጥናት ተቋም፣

አቦሸማኔ፡- ነብርን የመለያ አቋምና መጠን ማስፋፊያ፣

ጅብ፡- የእግር ማስረዘሚያና የሽታ ማስወገጃ ፋብሪካን፣

ምድር፡- የውኃ መጠን እንዳይጨምር የመከላከያ ተቋም ማቋቋም ነበር።

ለዚህ ደግሞ እያንዳንዳቸው በቂ ገንዘብ ስላልነበራቸው ዕቁቡን መሠረቱ። በምሥረታው የተስማሙበት የመጀመሪያው አንቀጽ፣ «ዕቁቡን ለማቋቋም አሳብ ያፈለቀው የመጀመሪያውን ክፍያ ማግኘት ይችላል።» ስለሚል፣ ሕጉን ያረቀቀው አቦ ሸማኔ የመጀመሪያው በመሆን ገንዘቡን በቀዳሚነት ሰብስቦ ወደ ቤቱ አቀና። ከዚያም «ነብርን የመለያ አቋምና መጠን ማስፋፊያ» ለሚለው ድርጅት ገንዘቡን ሳያውል በምትኩ የአራዊት ንጉሥነቱን የሚያስረዱ መግለጫዎችን በተነ፣ አስከትሎም በዕቁብተኞች ላይ አሾፈ፣ «ከእናንተም ያገኘሁት ምንም ገንዘብ የለም» በማለትም ዕቁብተኞቹን ካደ።

አቦሸማኔ ይህን መግለጫና ክህደት የፈጸመው ያዋጣኛል ባለለት በፍጥነቱ በመተማመኑ ነበር። እርሱ እንዳሳተው የዝሆን ባለህበት እርገጥ፣ የአንበሳ ግሥላነት፣ የጅብ አንካሳነት ከእርሱ አምላጭነት ጋር እንደማይገናኝ ስለ ተረዳ፣ «እግሬ አውጭኝ» ለሸሩ መፍትሔ ሆነለትና ተሰወረ። ገንዘቡን በበላ በወሩም ድንገት በቆመበት ቦታ ላይ ምድር «የበላኸውን ክፈል» አለችው ለዚህ ምላሹ ግን ቀጣይ ሸሽትን በመምረጥ አምልጦ በሌላ አገር ተገኘ፣ በዚያ ያለችው ምድር ግን ደግማ «ክፈል» አለችው። አቦሸማኔ አሁንም በመደንበር ተሯሩጦ ከዛፍ ላይ ወጣ። በዚያም ምድር «ወርደህ ክፈል» የሚለውን ጥያቄ አቀረበችለት። ወርዶም ቢሸሽ ለውጥ አልነበረም፤ ሞኙ አቦሸማኔ በግፉ የሰበሰበውን ሳይጠቀም ሸሽቶ ሳይዘልቅ እየሸሻት ባላት ምድር ላይ ሞተ ይባላል። እናም ያኔ ነው አሉ ምድርም፣ «በማን ላይ ተቀምጠህ ምድሪቱን ታማለህ» ያለችው።

መቼም ይህን የረዘመ ተረት ያቀረብኩት «ልዑል ማን ነው?» ለሚለው ጥያቄ መገጣጠሚያ እንደሚሆነኝ አስቤ ስለሆነ፣ የቀረኝን ዋና ነገር በጥቂቱ ላመላክታችሁ፡- በሰዎች ዘንድ የማይቋጭ

የመወያያ አጀንዳ ፈልግ ቢባል አንዱ «ይህችን ዓለም በልዕልና የሚቆጣጠራት ማን ነው?» «የሚለው ዐቢዩ ይሆናል። «በሁሉም አገሮች ጦርነት መፍትሔ መስሎ እያሸነፈ መጥቷል፤ ሊገታ የማይቻለው የኤድስ ወረርሽኝ ሕዝብን ጠራርጎ ዘልቋል፤ መፈንቅለ መንግሥት በዓለም ሁሉ ይድረስ የተባለ ያህል «የወቅቱ ፋሽን መስሏል»፤ የውኃ መጥለቅለቅና የምድር ነውጥ ያልሠለጠኑ የሠለጠኑ ሳይል ሁሉንም ፍርስርስ እያደረገ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለባዶነት ያበቃል . . .» ታዲያ ይህን ሁሉ ያየ ወደ ራሱ ማጠቃለያ ለመድረስ ደግሞ ይጣደፋል፣ መደምደሚያውም መቼም እግዚአብሔር የሰማዩን ግዛት ሲቆጣጠር፤ ሰይጣን ደግሞ ይህችን ዓለም እንዲቆጣጠር የሥራ ድርሻ ቢኖር ነው ብለው ግላዊ ቲዎሪ (ንድፈ-አሳብ) ይነድፋሉ። ይህ ያሰቡት ግን መልስ አይደለም፤ የነጠረን ምላሽ የሚሰጠን የእግዚአብሔር ቃል እንደ «አቦሸማኔው» አምላጭ መሳይ ግን ተያዥ ሆኖ የሰው ልጅ እንዳይቀር መምከሪ ያውን አኑሯል።

ያም «እግዚአብሔርን ለሚወዱና እንደ ፈቃዱም ለተጠሩት ሰ ዎች እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለጥቅማቸው እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን» (ሮሜ 8፡20) የሚለው የሐዋርያው ጳውሎስ ጽኑ ምክር ነው። ይህን ደግሞ የመዘዝኩት የእግዚአብሔር ልዕልነት ለዓለም ሕዝብ ሁሉ እንዲገለጽ ግድ ባለመሆኑ፣ ብዙዎች ራሳቸውን ለዚህ ዓለም ገዢ ፈቃድ በሙልዓት ስለ ሰጡ፤ ብዙዎች በራሳቸው ውሱን ዕውቀት ተገድበው ስለ ቀሩ፤ በተጨማሪ ብዙ ዎች እግዚአብሔር ራሱን ስላልገለጠላቸው ደፍረው ሊሉ የቻሉት ያዩትን፣ የሰሙትን፣ ያነበቡትን ብቻ ነው። ያ ደግሞ እግዚአብሔ ርን በሚመለከት አያዋጣም። ይልቁኑ፣ የልዕልነቱ መግለጫዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተጠሩ የእርሱ ሕዝቦች ቀዳሚዎቹ ናቸው። እነርሱ ደግሞ እንደ ሰው የበረከተ ጥያቄ ቢገጥማቸውም፤ ክስን በመመሥረት በእግዚአብሔር ላይ አይሳለቁም (ኤር. 12፡1-2)። ይልቁኑ፣ የነገሮች ሁሉ መደምደሚያ ለእግዚአብሔር ክብር እና ለጥቅማቸው እንደ ሆነ በመረዳት የተገለጠው ለሰው ጥቅም የተሰወረውም ለእግዚአብሔር ክብር በመሆኑ እርሱኑ ይታመኑታል።

ይህን ደግሞ ከተረዱት የሁለት ሰዎችን የሕይወት ጉዞ ልግለጽላችሁና የክፍል ሁለት መልእክቴን ልደምድም።

ቀዳሚ ተጠቃሹ ኃይለማርያም ሕሩይ ነው፣ ራእዩ ትልቅ «ለጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ቤተሰብ» በማለት በከተማና በገጠር ጽኑ የቤተሰብ ትምህርትን ከባለቤቱ ከየምሥራች ደሳለኝ ጋር በመሆን ይሰጣል፤ ባልና ሚስቱ የልባቸው መዝገብ ያለበት ስፍራ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማገልገል ስለሆነ ሁሌም ፈቃዱን ለመፈጸም ይታጋሉ፤ እንዲህ እየተጉ ግን አንድ ቀን እንዲህ ሆነ በጤናው ላይ ጽኑ መታወክን ያላመጣበት «ሕመም መሰል» በሽታ በቀዶ ጥገና ከወዲሁ እንዲወገድ የሐኪሞች ውሳኔ መጣ። እናም በቀኑ ወደ ሆስፒታል አመራ። ባለቤቱንም «በሞት እንኳን እግዚአብሔር ለሚያደርገው አዋቂ መሆኑን አትዘንጊ» ብሏት ገባ። የቀዶ ጥገናው ሥራ እንደ ተጀመረ ግን የኃይለማርያም የሰማይ ጥሪ አብሮ ከተፍ አለ፤ ወደ ሞቱ ተቻኮለ፣ ወደ ዕረፍቱ ገሰገሰ፣ እናም ከጌታው ጋር ብዙም ሳይቆዩ ተገናኘ።

ይህ ሰው ጌታውን በአገለገለበት ዘመን ሁሉ ከባለቤቱ ጋር ሁሌ በፍቅር የሚተሣሠረው «እግዚአብሔር በሰጠን ጊዜ እናገልግል» በማለት ነበር። ኃይለማርያም ይህን እያለ ለጊዜው ባለቤቱን፣ ልጆቹን ቃል ኪዳንና ቤዛን ተሰናበተ፤ ይህን እግዚአብሔር ባደረገ ግን ከዳር ያሉ ሰዎች ግን በእግዚአብሔር ልዑልነት ላይ የተሳከሩ ሆኑ። መንፈሳውያን ነን የሚሉት፣ «እግዚአብሔር በልጁ ላይ እንዴት ይጨክናል?» በማለት አጉተመተሙ፤ ራቅ ያሉት፣ «የአባቶቹን እምነት ስለ ሻረ ነው» ብለው መከሩ። የሕክምና ባለሙያዎች ደግሞ፣ «የእኛው ስሕተት ይሆንን?» በማለት መዘገቡ። ብቻ ሁሉም የየፊናውን እያነሣ የእግዚአብሔርን አዋቂነት፣ ቻይነትና ተገንነት ችል ብሎ ላይለውጥ የቅርብ አዳሪ እየሆነ ባለበት ቆመ። የኃይለማርያም ኑሮ ግን በሮሜ 8፡28-29 ላይ ጸንቶ ዘለቀ።

ተከታይ ተጠቃሼ ጀርመናዊቷ ቤቲ ናት። እርሷን የገጠማት «በድንገተኛ» ደራሽ የሳንባ ካንሰር መያዝ ነበር። ሐኪሞቿ ቤቲን የሳንባዋ ዕድገት እየጨመረ በመምጣቱ ይህንን ተከትሎ መተንፈስ እንደምትቸገር ነገሯት። ይህን የሰማችው ቤቲ በአልጋዋ ላይ ሆና

ወደ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰች፣ ያም ከባለቤቷ ጋር የሠርግ ቃል ኪዳናቸውን በተለዋወጡበት ቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡ ስድስት መቶ ያህል ሰዎችን በጥሪ ካርድ ለመጋበዝ ወሰነች፤ አረገችውም። እናም «አስቸኳይ ጥሪ» ባለችበት ቀንና ሰዓት ታዳሚዎች አዳራሹን ሞሉት፤ ቤቲም ከመድረኩ ብቅ አለች። ጤና እንደሌላትና እንደ ደከመች ታስታውቃለች። ቢሆንም ግን፣ ትንፋሽ እያጠራት ጥሪዋን ላከበሩላት ሰዎች እንዲህ አለች፣ «ሁላችሁም ስለ መጣችሁልኝ አመሰግናለሁ። የጠራኋችሁ በቅርብ ቀን ከዚህ ዓለም በሞት እለያችኋለሁ። ስሞት በቀብሬ ላይ ትመጡ ይሆናል፤ እንደ ሁኔታውም ላትመጡም ትችላላችሁ። ይህን ያኔ ማለት አልችልም፤ እኔ ግን ዛሬ ሁላችሁንም እሰናበታችኋለሁ። ወደ ሞት የሚያጣድፍ በሽታ ገጥሞኛል፤ ይህም የሆነው ፈጽሞ በማልገምትበት በዚህ ዓመት ነው። የዘንድሮ የእኔ ዕቅድ ልጆቼን ወደ ተሻለ ት/ቤት ማዛወር፣ የራሳችን የሆነውን ቤት መግዛት፣ ለባለቤቴ የቀደሙ ስሕተቶቼን አስወግጄ በፍቅር መኖር፣ በዚህች አጥብያ ቤተ ክርስቲያኔ ከአምናው ይልቅ በትጋት ጌታን ማገልገል ነበር። እነዚህ ነበሩ ዝግጅቶቼ። ይህ የሳንባ ካንሰር በሽታዬ ግን አሸነፈኝ፤ መሸነፌን ግን በማማረርና ተስፋ በመቁረጥ ልገልጽላችሁ አልፈልግም። በእኔ ላይ የሚፈጸመው ሁሉ ከእግዚአብሔር ልዑልነት የተነሣ ለበጎ እንደሚሆን አምኛለሁ፤ ከበጎነቱም አንዱ ለእናንተ ያደረስኩት የዛሬ ጥሪዬ ነው። አፍቃሪዎቼ ሆይ! ከእናንተ ጋር ወይ ለዘለዓለም እኖራለሁ ወይም ለዘለዓለም እለያችኋለሁ። መቼም ቢሆን በቀጣዩ የዘላለም ሕይወት መገናኘት የምንችለው በአንድ መንገድ ብቻ ነው፤ ያም ስለ እናንተ ደሙን ያፈሰሰውን ኢየሱስን እንደ እኔ ካመናችሁት። ነገ እናንተም ብትሞቱ በትንሣኤ እንገናኛለን።

«ወዳጆቼ ሆይ፣ ከሞት እንቅልፍ ስነቃ በክርስቶስ መንግሥት እንድንገናኝ ጥሪዬን እንዳከበራችሁልኝ የእርሱንም የጥሪ ቃል ተቀበሉ፣ የስንብት መልእክቴን በመስማትም ምላሽ ስጡ።» ብላ ንግግሯን አበቃች። ጥሪዋ ምላሽ አገኘ፤ ብዙዎቹ ለክርስቶስ መንግሥት በቁ፤ ከዘለዓለም ሞት አመለጡ። ቤቲ ዛሬ በአካል በዚህ ምድር የለችም። የሥራዋ ፍሬ ግን የእግዚአብሔርን

ልዑልነት በመረዳት ላይ ስለሆነ፣ ዛሬም አለ።

አሳቤን የምጠቀልለው እግዚአብሔር ሰማዩን ብቻ እንዲገዛ የተተ ወለት ሳይሆን፣ ምድርንና በውስጧ የሚከናወኑትን ሁሉ የሚያስተ ዳድር ልዑል እርሱ ብቻ መሆኑን በማብሰር ነው። ሁሉን ነገር እንደ ገዛ ፈቃዱ ያስኬዳል፣ ዓላማውን በወደደው መንገድ ዳር ያደርሳል። ይልቁኑም፣ የእርሱ በሆኑት ሕይወት ውስጥ እንደ ቃሉ ሊረዱትና ሊደገፉት ይወዳል፤ ይህንንም የተረዱ በሰላም ውለው ያድራሉ፤ ምድር አቦሸማኔውን፣ «በማን ላይ ተቀምጠህ ምድርን ታማለህ?» እንዳላቸው፣ እነርሱ አይባሉም።

በእውነት ላይ የተመዘዘ ሰይፍ

በዓለም ደምቆ የታየ ኮከብ በአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታየ። ያም ኮከብ የእንግሊዙ ጆን ዊክሊፍ ነበር። እርሱ ሰው በኦክስፎርድ በሚገኘው በባሊዬል ኮሌጅ ፕሬዚዳንት ሲሆን፣ ፕሮፌሰርነትን ያገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ የትንታኔ ጥናት ነው። ዊክሊፍ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት እየበራለት በሄደ ቁጥር «ቤተ ክርስቲያናት ነን» በሚሉት ስም የሚካሄደው ነውር አስመረረው። ሰዎች ወደ እነርሱ የመጣውን ኢየሱስን በማመን ምትክ ወደ እግዚአብሔር ደርሰናል ብለው የሚገነቡት የሐሰት ግንብ አሳሰበው፣ ጳጳሳት ገዢ፣ ምእመናን ተ ገዢ በመሆን የሚወገዙበትንና የሚገደዱበትን አካሄድ አስተዋለ።

ይህ አስተውሎ ዊክሊፍን ለአንድ ተግባር አበቃው። ያም ሕዝቡን ማመዛዘን ነሥቶ ካናወዙት ዋንኛ ምክንያቶች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለእንግሊዞቹ በማያውቁት በላቲን ቋንቋ የተተ ረጎመ መሆኑን መረዳት ነበር። ዊክሊፍ ይህን እንደ ተረዳ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ ለሕዝቡ ሊያደርስ ወስኖ ተነሣ፣ እግዚአብሔ ርም አከናወነለት። ለዘመናት በማያውቀው ቋንቋ እየተነበበለት በጨለማ ይኖር የነበረው የእንግሊዝ ሕዝብ የክርስቶስን ሥራና የብርሃኑን ውጤት በቋንቋው አየ። አይቶም ወደ እግዚአብሔር ተ መለሰ። ይህ በእንግሊዝኛ የተተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስም ቀስ

እያለ ወደ እንግሊዝ ቤተ መንግሥትም ገብቶ የሰውን ሕይወት ለወጠ። ይህም ደግሞ የታወቀው ጳጳሱ በቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ በተነገረ ጊዜ ነበር። በሰኔ 1394 የየርክ ሊቀ ጳጳስ አሩንዴል በዳግማዊ ሪቻርድ ባለቤት በንግሥት አና /Anne/ ቀብር ላይ ስለ ንግሥቲቱ እንዲህ አለ፣ «ንግሥት አና ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉመው የነበሩትን አራት ወንጌላት ከማንበቧ የተነሣ በመንፈሳዊ ሕይወቷ በእጅጉ የተመሰገነች ነበረች። እኒህ መጻሕፍት እውነተኛና ሁሉም ሊያነባቸው የተገቡ ናቸው» በማለት ቀብሩን አስፈጸመ። በዚህም የቅዱሳን መጻሕፍትን ሕይወት አዳሽነትን መሰከረ።

ከ14 ዓመታት በኋላ ግን ይኸው ሰው «ውግዝ ከመአርዮስ» የተ ሰኘውን የእርግማን ውግዘቱን ሕዝብን ሰብስቦ «. . . ከዚህ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች ወደ እንግሊዝኛም ሆነ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎም ለማንም አይፈቀድም፣ ለዚህ ሥልጣኑ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው፤ ከዚህም የተነሣ በዊክሊፍ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው እንደ እግዚአብሔር ቃል አይቆጠርም...» በማለት አጣጣለው፤ አወገዘውም።

የማጣጣሉና የማውገዙ ምክንያት አንድ ነው፤ ለእግዚአብሔር እውነት የታደሉት ብዙዎቹ ከጨለማው ግዛት ኮብልለው ለእግዚአብሔር በቅተው ነበርና ይህ ለጳጳሱ የራስ ምታት ሆነ።

እያደር ግን ውግዘቱ በብቻው በቂ ሆኖ አልተገኘምና ጆን ዊክልፍ በሞተ በ44ኛው ዓመት በ1428 ጳጳሱ ማርቲን 5ኛ ትእዛዝ አወጣ፤ የዊክሊፍ አፅሙ ከአረፈበት ወጥቶ እንዲቃጠል አዘዘ፤ እንደ ትእዛዙም ሆነ፣ አመዱም በታላቁ ወንዝ ላይ ተለቀቀ።

ጨለማውን የገለጠው ሰው ታሪክ እንዲህ ነበር። በዚህ ንባብ ዊክሊፍን በግርድፉ ላስተዋውቃችሁ ያነሣሣኝ ሌላኛው ሁነኛ ምክንያት ላቲን ለእንግሊዞች ብርሃን እንዳልሆናቸው፣ ግዕዝም ለበርካታ ኢትዮጵያውያን እንደዚያው መሆኑ እርግጥ ነው። ኢትዮጵያ ለክርስትና እምነት ገና ከጠዋቱ የተጋለጠች አገር ናት። መጋለጧ ግን መጽሐፍ ቅዱስን በሚመለከት አግባብነት ይጎድለዋል። ብዙዎች የማይረዱትን እንደ ላቲን እንዲያነቡት ተ

ደርጓል። ይህም ላለፉት በርካታ መቶ ዓመታት በሕዝቡ ዘንድ ተ
ከናውኗል። መቼም ቋንቋው ሕያው ሆኖ መልእክትን በላኪውና
በተቀባዩ ዘንድ መግባባትን ያሰፈነ ቢሆን ምንም አልነበረም።
ዋነኞቹ መልእክቱን በግዕዝ ቋንቋ ለሕዝቡ ይናገራሉ፣ ያዜማሉ፣
ይቀድሳሉ፣ ያነባሉም። ተቀባዩ ግን «እናንተን አምኜ» በሚል
መንፈስ ብቻ ደርሶ ይመለሳል፣ በቤቱም ፊደላቱን እያየ ይቆጥራል፤
ክርስቲያን እንደ ሆነም በመቁጠር ይጽናናል። የመጽናናቱ ልክኛ
ጊዜ ግን ባልሰማው፣ ባልተረዳው ቋንቋ ሳይሆን፣ ሊረዳው ወደሚቻ
ለው ቋንቋው መለስ ብሎ የእግዚአብሔርን መልእክት ሲቀበል
ነው።

በኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም አንጻር የወንጌል
መልእክት ወደሚረዱበት ቋንቋ ተመልሶ «ሕዝቡ ከኃጢአት
እሥራት ነፃ ይውጣ የሚለው» የዊክሊፍ መሰል ጉጉት በቀላሉ
መፍትሔ እያገኘ የነፃነት ጉዞን አልተጓዘም። ብዙዎቹ
ለመልእክቱ ተቀባይ የሌለው የግዕዝ ቋንቋ ወደ አማርኛ እና ወደ
ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በተመለሰ ጊዜ እልፍ አእላፋት ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት ፈልሰውና እየፈለሱ፣ ከጨለማው
ወደሚደነቀው ብርሃን ዘወር ባሉ ጊዜ ተቃውሞው ለእንግሊዞቹ
ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደ ደረሳቸው፣ እዚህም ተመሳሳይ ሆኖ
እውነተኞቹ መናፍቃን ሲሰኙና ተሰዳጅ ሲሆኑ ይታያል።
አንዳንዱም እንደ ዊክሊፍ በበድናቸው ላይ መወራረድና
ላለማስቀበር መጣር፣ ቢቀበርም ለአውሬ ለመስጠት የሚደረገው
ከጥንቱ ጋር ምስስል ኖሮታል፡-

በቅርቡ «የዘመቻ ፊልጶስ ምልምል ቅጥረኞች፣ ፀረ ማርያሞች
አታወናብዱ» በሚል በመምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን የጥላሁን
መኮንንን «መጽሐፍተ ኑፋቄ» ለመቃወም የተጻፈው መጽሐፍ ስለ
66ቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲህ ነቅፎ አስነብቧል።

«ከአውሮፓው 66 መጽሐፍ ቅዱስ የእኛ ልፋፊ ጽድቅ
ትበልጣለች፣ ምክንያቱም በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሀዱ አምላክ በማለት ጀምራ በእግዚአብሔር ስም ትጨርሳለች /
ገጽ 18/. . . የተሸቀጠ የተቀላወጠ ወንጌል ከባሕር ማዶ የመጣው
66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው እንጂ ተአምረ ማርያም አይደለም። /ገጽ

27/ መጨው የሉተር ሃይማኖትና 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው. . . /ገጽ 17/ ከብዙ በጥቂቱ።

ጎበዝ! ይህ ገለጻ በ1428 ከዚያ በፊት ጳጳስ ማርቲን 5ኛ እውነትን ላለመቀበል ካደረገው ውሳኔው ጋር አይቀራረብምን? በዚህ አያያዝ ኪዳነማርያም ጌታሁን ከማን ጋር እየተጣሉ ነው? ከእግዚአብሔር ወይስ ከጥላሁን?

ማ.ማ.ማ.

ሦስትዮሽ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ

ቶምሮስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚጠቅሙ መጻሕፍትን የሚያዘጋጁ የባኘቲስት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ናቸው። እኚህ ሰው «የቤተ ክርስቲያን ሁነኛ ተልዕኮ» የሚለው ሥራቸው ልቤን አሳርፎታልና ለዚህ ጽሑፍ ዐቢይ ምንጭ አድርጌ እጠቀምበታለሁ።

ጸሐፊው ለቤተ ክርስቲያን ሁነኛ ተልዕኮ ግልጹ መርጎ፣ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ. 28፡19-20፤ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የ1954 ዓ.ም እትም) የሚለው ትእዛዝ መሆኑን ያበሥራሉ፤ ከጥቅሱም ሊለያዩ የማይችሉ ሦስት መሠረታዊ ማዕዘናትን ያቆማሉ።

ይህ ሦስትዮሽ በብዙዎች ዘንድ «ታላቁ ተልዕኮ» በመሰኘት ይጠራል። ጂ. ደብሊው. ፖርተር 1900 ዓ.ም እንደ ባተ በጻፉት መጽሐፍ ስለዚህ ንጥጥል አልባ ስለሆነው ባለ ሦስት ዘርፍ አገልግሎት ሲጽፉ፡- «ቤተ ክርስቲያናት ሊወጡት የሚገባ ኃላፊነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ ያስቀመጠውን መለኮታዊ ትእዛዝ ማክበር ነው። ዓለምን በወንጌል የምሥራች ቃል ማብሰር /ያለ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለመቻሉን/ ከወንጌል የተነሣ ዳግም ጌታ የወለዳቸው ደግሞ በመጥለቅ ጥምቀት መተባበራቸውን

ማስገለጽ፤ እኒህ የተጠመቁም ደግሞ የጌታን ቃል እያስተማሩ እንዲኖሩበት በማገዝ ማሳደግ የክርስቶስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነኝ ያሉ ሁሉ የሚወጡት ሁነኛ ምልክት ነው። ከዚህ ውጭ ከተ ሄደ፣ ያለ ተልዕኮ፣ ለከንቱ መደራጀትን ያመጣል. . .»[1] በማለት ጽፈዋል። እንደ ፖርተር የመዝጊያ አጻጻፍ፣ ያለ ተልዕኮ ያለች «ቤተ ክርስቲያን ምን የምትፈጽመዋ ትሆን?»

አንደኛዋ፣ ከወንጌል መልእክት በፊት የኀብረተሰብ ለውጥ በማስቀደም የምትመራዋ ትሆናለች። ትኩረትዋ የተራቡትን መመገብ፣ የታረዙትን ማልበስ ነው፤ አካባቢ ወይም ተፈጥሮአዊ እንቅፋትን አስቀድሞ ማስወገድን ታስቀድማለች፤ የወንጌልን የምሥራች ለሰው ለማሰማት «አስቀድሞ ሊመቸው ይገባል» ጩኸቷ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን የተሞሉ ሆዶች በክርስቶስ ላይ መነሣታቸውን፣ ያተራረፉ ሰዎች ለእግዚአብሔር መንግሥት ጀርባቸውን መስጠታቸውን ይገልጻል። ብዙ ምግብና ልብስ የሰውን ኃጢአተኝነት ሊያስወግደው አለመቻሉን አዲስ ኪዳን ይናገራል። የሰው ሙትነት ሕያው የሚሆነው ወንጌል ሲሰበክ መንፈስ ቅዱስ አንቅቶ ሕያው ሲያደርገው ብቻ ነው፤ ያ ደግሞ ለዓለም ችግረኞች ቁሳዊ ጠቀሜታዎች ይዞ በመቅረብ፣ ለዚያም በመድከም አይመጣም።

ሁለተኛዋ፣ ሰዎች ሊደሰቱበት የሚገባቸውን አዝናኝ ዝግጅቶች በማቀናጀት የወንጌል መልእክት ከአሳሳቂ ቅመሞች ጋር ለውሶ ለማድረስ የምትጥረዋ ናት። ብዙዎች፣ በኃጢአት ተበክሎ በገዛ እጁ ለመዳን ተስፋ የሌለውን ሰው፣ በማዝናናት እንዲመቸው «ለካስ ክርስቲያን ነኝ» እንዲል ይደልሉታል፤ በአቅርቦቶቻቸው ዓለማዊ ሕይወትን የሚያዳብር ትረካንና ስሜትን አነሁልሎ አቅል የሚያሳጣ «ዘመናዊ ሙዚቃን»፣ ረብ-የለሽ ቀልዶችን፣ የእግዚአብሔር ማንነትና የሰው ምንነቱን የማይገልጽ ስብከት ቢጤ ዎችን በማዘውተር የ«ታላቁን ተልዕኮ» አካሄድ ያመቻምቻሉ። የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ግን ሰው እንዲደሰት በማድረግ ወንጌልን ማድረስ አይደለም። ወንጌል እግዚአብሔር ከፍቅሩና ከሚባላ እሳትነቱ ጋር ይገለጻል፤ ወንጌል የሰውን የኃጢአት ደንካራነት ሳያቅማማ ይገልጻል፤ ይህ በብቻው ይሠራልና።

ሦስተኛዋ፣ ራሴ ክርስቶስ ነው ያላለች ቤተ ክርስቲያን፦ የተልዕኮዋን ውጤታማነት በሰዎች የኑሮ ስኬታማነት ላይ እና እንደ አሸን ወደ ሰበካዋ በሚመጡት መጠነ ሰፊ ሕዝብ ላይ ታደርጋለች።

ይህ አካሄድ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ እየሰፋ በመሄዱ፤ የምእመኖቻቸው ቁጥር ጥቂት በሆኑ ዘንድ ጭንቀት አለ። ከዚህም የተነሣ የወንጌላቸው አጀንዳ «የቁጥር መጨመር ዘዴ» ሆኖ ይገኛል፤ እውነቱ ግን በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡6-8 ያለው ነው፣ «. . . እኔ ተክልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤ እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም። የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው፣ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል» (የ1954 እትም)። እንግዲህ እያበሰረ የሚያረዳን የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ተፈጻሚነት የሚያገኘው በእግዚአብሔር የሥራ ባለቤትነት ላይ መመካት ሲሰፋ መሆኑን ነው። ከዚህ ከወጣ ግን፣ የቁጥር መብዛት በክርስቶስ ያልሆኑትን ክርስቲያን-መሰል ሰዎችን በማጋበስ መታለል ነውና በብቻው ለዚህ መድከም ከንቱነትን ያሳጭዳል።

እንግዲህ ከላይ የተነሡት ሦስት አካሄዶች እንደ ጂ. ደብሊው. ፖርተር አተናተን እና እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ለቀደሙት ለመሰል ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት «አገልግሎታቸውን» የሚያራምዱ «ቤተ ክርስቲያናት» ሥራዎቻቸው ከጌታ ጋር አለመጣጣሙን ለአፍታ ቆም ብለው ሊመዝኑት የሚገባ ይመስላል። ይህንንም አግዝፎ ለማሳየት ወደ ሦስቱ ዋነኛ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዎች መለስ እንበል፦

ማብሰር፦ በማርቆስ 16፡15 «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ይላል። ከገለጸው የምሥራቹ የሚነገርበት ስፍራ ሙሉው የዓለም ሕዝብ ነው፤ ለዚህ ሕዝብ ደግሞ የሚነገረው ብስራት፣ «ክርስቶስ ስለ ኃጢአታቸው ሞተ፣ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ» (1ኛ ቆሮ. 15፡3-4) የሚለው መልእክት ነው። ጳውሎስ በዚህ መልእክት መርካቱን ሲገልጽ፦ «በወንጌል አላፍርምና?» (ሮሜ 1፡16) ይላል። ያለማፈሩ ምክንያት በኃጢአቱ ከእግዚአብሔር ለተለየ ሰው ዋናና ብቸኛ

መፍትሔን እግዚአብሔር ኢየሱስን በመላክ መፈጸም ነው። የወንጌል የምሥራቹ መልእክት ግልጽና አጭር ነው፤ ይህን ግን ወደ ጎን በመተው፣ ማብሰርን ሳይሆን ማርዳትን የሚይዝ፣ ደኅንነትን በሰው የድካም ውጤት እንደሚገኝ የሚገልጽ መልእክት በስመ ወንጌል ሰዎችን ለጥፋት ያበቃል። በገላትያ 1፡8-9 ጳውሎስ ስለ እነዚህ «የጥፋት ወንጌል» ባለቤቶች ሲናገር፣ እነርሱ «የክርስቶስን ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ (ናቸው) . . . ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ፤ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» ይላል።

የቤተ ክርስቲያን የሁልጊዜ ተልዕኮ ወደ ኢየሱስ አዳኝነት የጸጋን ታላቅነት በማመን ብቻ መትረፍን ለሕዝቦች ሁሉ ሳያቋርጡ መንገር ነው፤ ይህም የእያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው።

ማጥመቅ፦ ማቴዎስ 28፡19-20፣ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝ ኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ይላል። ትእዛዙ ሁለተኛዋን የቤተ ክርስቲያን ተከታይ ተልዕኮ ያሳውቃል፤ ማጥመቅን። ጥምቀት፣ የከፊል ተሐድሶ አራማጅ የሆኑ አንዳንድ የኅሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት እንደሚያደርጉት ከዘላለም ሕይወት ጋር አይገናኝም፤ በአፈጻጸም ውኃን በመርጨት አይከናወንም፤ ሕፃናትንም አይጨምርም።

አዲስ ኪዳን በግልጽ እንዳስቀመጠው፣ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛውን የውኃ ጥምቀት አግባብነት ባለው ሰው፣ በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ዳግም የተወለደውን አማኝ አጥልቆ በማጥመቅ ተልዕኮውን መፈጸም አለባት፤ ማጥመቅን። በተመለከተ ጀ. ደብሊው. ፖርተር በጽሑፋቸው ሲያሳስቡ፣ «. . . ክርስቶስ ስለ እኛ ምትክ ሆነልን፣ ግና የክርስቶስ የሆነው መለኮታዊ ትእዛዝ ምትክ-የለሽ ነው፣ ተለዋጭ/ተቀያሪ የማሻሻያ መልእክት የለውም። ይህን ብቸኛ አገልግሎት ቸል ያለች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብትኖር እርሷ ራሷን ለውርደት ያዘጋጀች ብቻ ናት፣ ክርስቶስ በእርሷ አይደለም፤ ምትክ ያልሰጠላትን ትእዛዙን

ጥሳለችና. . .»[2]

ማሳደግ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ማብሰርና ማጥመቅን በመግለጽ ያነሣው ሦስተኛው አቻ ጉዳይ በማቴዎስ 28፡19-20 እንደ ተገለጸው በማስተማር ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው። ብዙ የቀደሙት ቤተ ክርስቲያናት አብስረው ያጠምቃሉ፤ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የማስተማር ኃላፊነት ግን ችላ ይላሉ፤ ወይም ይተዉታል። ቸልታቸውና ስፍራ አለመስጠታቸው የእውነት አንድነትን በማጣት መለያየትንና ያለ እግዚአብሔር ቃል በመሆን እንደ መሳፍንት ዘመን «ሁሉም ደስ ያሰኘውን በማድረግ ውጤታማ አለመሆንን ያሰፍናል፤ በነፃነት እንድንኖር ክርስቶስ ነፃ አወጣን» (ገላ. 5፡1) የሚለው የድል መልእክትም በመክሰም ነፃ ሕይወት በእሥረኝነት እንዲተካ ያደርጋል፤ ሐዋርያው በ2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡3 ሲመክር፣ ሰዎች ንጹሑን ቃል ለመስማት አለመፈለጋቸውን፣ ለወሬ ብቻ መጎምጀታቸውን፣ የሚወዱትን ነገር የሚነግሩአቸውን ብቻ ማድነቃቸውን ያመለክታል። ይህ ዓይነት ችግር በአንድ ሁነኛ ምክንያት ብቻ ይከሰታል፤ ያም ሙሉ አሳብ /መልእክት/ ያለውን የጌታን ቃል ባለማስተማር ይመጣል።

እንግዲህ ማ.ማ.ማ. የማይነጣጠል፣ ሁሉ መተግበር ያለበት ሦስት በአንድነት ያሉ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ነው።

ቶምሮስ ይህን ተልዕኮ ለመፈጸም እግዚአብሔርን መታዘዝ ቀዳሚው ነው ይላሉ። የትእዛዙ ባለቤት፣ «የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ» (ዮሐ. 14፡15) ብሏልና፣ መታዘዝ በክርስቶስ ላልሆኑት በማሰብ ወንጌልን ለማድረስ የሚያስፈልገውን መሥዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል መዘጋጀትን ያቅፋልና።

እንግዲህ ለሁላችንም ያለኝ የማጠቃለያ መልእክት፣ «... እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያውና የተቀደሰ መሥዋዕት አድርጋችሁ ሁለንተናችሁን እንድታቀርቡ በመሐሪው በእግዚአብሔር ስም እለምናችኋለሁ፤ ይህም ማቅረብ የሚገባችሁ ቅንነት ያለው እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልግሎት ነው» [ሮሜ 12፡1 አዲስ ትርጉም (የታረመ)] ከሚለው የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ጋር መጣጣም ነው።

ለማብሰር፣ ለማጥመቅ፣ ለማስተማር[3] እንበርታ።

መረጃዎች

1. Porter J.W. *The Baptist Debt to the World*. L Wilmington. OH Baptist Heritage Press, 1991, p.10
2. Ibid. pp. 22-23
3. Tomross. *Teachings on the Local Church*. (Providence Baptist Church; 1993).

ቅኝት «በወላዲት አምላክ በኢትዮጵያ» መጽሐፍ ላይ

የመጽሐፍ አዘጋጅ፡- አለቃ አያሌው ታምሩ

የኅትመት ዘመን፡- 1970 ዓ.ም.

የገጹ መጠን፡- 78

መነሻ ቅኝት

«. . .ጊዜ ከመስታወት የሚበልጥ ነውና በጊዜ ተገኝቼ ይህን ሁሉ በማወቄና በመረዳቴ ወላዲት አምላክ በኢትዮጵያውያን ያላትን ክብር በእርስዋና በኢትዮጵያዊያን የቃል ኪዳን አንድነት በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርስዋ የተጻፈውን በመጠቅለል ሰብሰብ በማድረግ ተሰፋቸውን እንዲያውቁ በባዕድ ትምህርት የተጠለፉና የወደቁ ቢኖሩ ንስሐ እንዲገቡ ለመውደቅ የሚፍገመገሙ ቢኖሩ በመጽናት ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ኃይማኖታውያንም ለትምህርታቸው፣ ለአሳባቸው በቂ ድጋፍ እንዲያገኙ «ወላዲት አምላክ በኢትዮጵያ» የተባለውን ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ::

ማንንም ለመንቀፍ ፍላጎት የለኝም:: የእኔ ዓላማ ኢትዮጵያውን ሁሉ አገራቸው ኢትዮጵያ ከማናቸውም የዓለም አህጉር የማታንስ ይልቁንም በሃይማኖት የምትበልጥ፣ እነርሱም ከማንኛውም የዓለም ሕዝብ የማያንሱ ይልቁንም የሥነ ጽሑፍ፣ የባህል፣

የትምህርት፣ የሕግ፣ የቋንቋ፣ የፊደል፣ የእኩልነትና የባለአገርነት ነባር ታሪክ ያላቸው በመሆናቸው የሚያስመካ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነባር ታሪክ ያላቸው የማይጠፉ የሕይወት ቅርስ ባለቤትና ባለመብቶች መሆናቸውን ለማስረዳት ብቻ ነው . . .» አለቃ አያሌ ው ታምሩ፣ ገጽ 10-11::

የዝግጅቴን መክፈቻ ያደረግኩት አለቃ በመጽሐፋቸው መቅድም ላይ ያስተላለፉትን መልእክት በከፊል በመውሰድ ነው:: መልእክቱ «ወላዲት አምላክ በኢትዮጵያ» በማለት አዘጋጅተው የነበሩትን መጽሐፍ ዘልቄ እንዳየው ረድቶኛል:: ከዳር ዕዳር እያጠናሁ በከለስኩት ቁጥር በውስጡ ጠንካራ ጎኖች አግኝቼ እንደ ተ ደሰትኩበት ሁሉ፣ ጥያቄ የሚፈጥሩም ግራ-ገብ የሆኑ ማጠቃለያ ዎችን አግኝቼበት ግርምታ ይዞኛል:: አግራሞቴን በጠነከረ ሁኔታ ያደመቁብኝ ነጥቦች ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያልተገለጹ ወይም ፈጽመው የሌሉ መሠረተ እምነቶች «ማርያምን» በማስመልከት በታሪክ ስም ተቀምጠው ማግኘቴ ነው::

እርግጥ ነው፣ ኢትዮጵያ ከማንኛውም ሕዝብ የማታንስ፣ ይልቁንም ስም የሚያስጠሩ በርካታ ቅርሶች እንዳላትና ለዓለም ሥልጣኔ በር ከፋች መሆኗን አለቃ እንዳሉት እኔም እስማማለሁ::

ዳሩ ግን እምነትን ስናስብ እንዲህ አይደለም፤ ክርስትናን በአግባቡ እናጢነው ከተባለ በመቅድሙ እንደተገለጸው ሳይሆን፣ የክርስትና መሠረት የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን በመረዳትና ለእርሱም በመታዘዝ የሚሆን ሕይወት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ፣ በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ የሚመሩበት መጽሐፍ ነው::

እኔ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን አምነዋለሁ፤ ከእርሱ ያፈነገጠውን የሰው አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ ሚዛን ባለመድፋት ወደ ዘላለም ሕይወት የማያደርስ ሕያው እግዚአብሔርን የማያሳይ ነውና ቸል እለዋለሁ:: ሰዎችንም ከዚህ ይጠነቀቁ ዘንድ እመክራለሁ:: ሲያያዝ የመጣ የቅድመ-አያቶቼ እምነት ነውና እንዲሁ እነርሱን ብቻ አምኜ ልቀበል አልልም:: ይልቅስ፣ «ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እያንዳንዱ በግል በፍርድ ፊት ይቀርባል»

(ሮሜ 14:12)። ይህ ሰው በግርግር እንዳይኖር ሕያው ቃሉ ዳኛ ሆኖ በመካከል አለ፤ ከዚያም የተነሣ ነው በአለቃ አያሌው ታምሩ ዝግጅት ላይ መጽሐፉ የያዘው ጠንካራ ጎን እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ በትይዩ የእግዚአብሔርን ቃል የተጣረሱትን ነጥቦች በመቃኘት ግርድፍ ጥናቴን የማቀርበው።

«እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሰው ዘር ውጪ የሆነች ልዩ ኃይል አይደለችም፤ ከዳዊት ከአብርሃም ዘር የተወለደች ድንግል ናት ሴት እንደ መሆንዋ ታጭታለች» (ገጽ 22)።

ይህ አነጋገር ማርያምን ከሰው ዘር የተለየች አለመሆኗን ደግሞም እንደ ሴት ልጅ ወግ በድንግልናዋ ታጭታ እንደ ነበረ መግለጹ እውነት ነው። ይህችው ማርያም ጌታ ለክብሩ መርጧት ወንድ ሳታውቅ በመንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ፀንሳ መውለዷ ሌላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው። ይህን ተከትሎ «ስለዚህ ኢትዮጵያ» በማለት አለቃ አያሌው በመጽሐፉ ገጽ 25 ላይ «እመቤታችን ድንግል ማርያምን ያለ ዘርዐ ብእሲ አምላክን የወለደች የአምላክ እናት ናት ብላ ታምናለች» የሚል ድንጋጌን ያሳዩናል። እዚህ ላይ እምነትን በሚመለከት የኢትዮጵያን ሕዝብ ወክሎ «ኢትዮጵያ . . . ታምናለች» ማለቱ ልክም ባይሆን፣ ይበልጥ የሚያነጋግረን «ማርያም የወለደችው አምላክን ነው ወይስ ድካማችንን ሊያስወግድ ሰው ሆኖ የተወለደውን ኢየሱስ ነው?» ምላሹ ማርያም ሰው የሆነውን ኢየሱስን እንጂ አምላክን አልወለደችም። ለዚህም የማያሳምትን ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎችን በጥቂቱ ልግለጽ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሁለት ባሕርያት ባለቤት ነው። አምላክ ነው፣ ሰውም ነው፤ በአምላክነቱ መጀመሪያና መጨረሻ የለውም (ሮሜ 9:5)፣ ሁሉን ያውቃል (ዮሐ. 18:4)፣ በሁሉም ስፍራ ይገኛል (ማቴ. 28:20)፣ ሁሉን ይችላል (ቈላ. 1:16)። ይህም ብቻ አይደለም፣ በክርስቶስ የሆንን እግዚአብሔርን በትክክል እንድናውቀው ስለ እግዚአብሔር የነገረን እርሱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን 1:3፣ «እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ነው፣ እርሱ በባሕሪው ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ትክክል ነው» ይላል፤ ይህም ማለት ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው።

እንዲሁም ዮሐንስ 1:18፣ «እግዚአብሔርን ያየው ከቶ ማንም የለም፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ያለው አንድያ ልጁ ብቻ ገለጠው» [አዲስ ትርጉም (የታረመ)] ይላል። ይህም አምላክነቱን ያረጋግጣል። ከዚሁ ጋር በማያያዝ፣ ዮሐንስ 6:46፤ ቈላስይስ 1:17 ይመልከቱ።

ከዚህ ተነሥተን ማረጋገጥ የምንችለው ማርያም ፍጡር በመሆኗ በሁሉ ነገር ውሱን ነች። በአንድ ወቅት ከሰው ተወልዳ በአንድ ወቅት የአረፈች ናት፣ እናም እርሷ ዘላለማዊ የሆነውን፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለውን፣ ሁሉን የሚያውቀውን፣ በሁሉ ስፍራ መገኘት የሚችለውን እግዚአብሔር ወልድን ወለደች በማለት እመ አምላክ ማለቱ አግባብ አይደለም።

ግና ኢየሱስ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አስቀድሞ ያወቃቸውንና የጠራቸውን የሰው ልጆች (ሮሜ 8:29-30) በሞቱ ያድናቸው ዘንድ ሰው ሆኖ ይመጣ ዘንድ ተገባው፣ ይህንንም ፈጸመው። ይህ ማለት መለኮት ሆኖ ዘላለማዊ የሆነው ክርስቶስ በተፀነሰ ጊዜ ተጨማሪ ባሕርይ ኖረው ማለት ነው። እርሱም ሰው መሆን ነው። ማርያም ለዚህ ሰው ለሆነው ለኢየሱስ እናቱ ናት፣ አምላክ ለሆነው መለኮት ግን እናት መሆን አትችልም። እመ አምላክነት ፍጡር ለሆነችው ለማርያም ከዚህ የተነሣ አይገባም። የእግዚአብሔር ቃል በፊልጵስዩስ 2:6-11፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ በምድር ላይ ግን «ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደ ያዘ አልቈጠረውም፣ ይልቁንም ያለውን ክብር ሁሉ ትቶ እንደ ባሪያ ሆኖ ታየ» ይለናል።

እርግጥ ነው፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዓለም ላይ እየሰፋ በተናኘ ቁጥር፣ በብዙዎች ዘንድ ግርታን የፈጠረው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሁለት ባሕርይ ባለቤትነቱ ጉዳይ ነው?

ይህ ግርታ ሰዎች በገዛ አስተሳሰባቸው ላይ በመደገፍ ሊቀይጡት፣ አንዱን ከሌላው ሊለያዩት፣ አንድ ባሕርይ ብቻ ሊያደርጉት ሙከራ እንዳላቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስታውሳል። የዚህ ሁሉ ጽኑ መፍትሔ ግን የእግዚአብሔር ቃል የገለጸውን ብቻ ማመን ነው።

ቅኝቱን ልቀጥል፤ በመጽሐፉ ገጽ 23 ተራ ቁጥር 3 ኢትዮጵያ

ነቢዩ ሕዝቅኤል በትንቢቱ በምዕራፍ 44፡1-4፣ «ወደ ምሥራቅ በኩል የተዘጋ በር አሳየኝ ይህ በር አይከፈትምን? ብዬ ጠየቅሁት፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር አልፎበታልና አይከፈትም የተዘጋ ሆኖ ይኖራል አለኝ» ይላል። በዚህ መሠረት አምላክን የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን ከመፀነስዋ በፊት፣ በፀነሰች ጊዜ፣ ከፀነሰችም በኋላ፣ ከመውለድዋ በፊት፣ በወለደች ጊዜ፣ ከወለደችም በኋላ ለዘላለም ድንግል ናት ብላ ታምናለች።»

ይህ ገለጻ በርካታ ጥያቄዎችን ያነሣሣል። ከጥያቄዎቹ ጥቂቶቹ የምሥራቁ በር የት ይገኛል? በሩ ለምን ተዘጋ? ለምንስ የተዘጋውን በር አሳየው? እግዚአብሔር በምን ምክንያት የእስራኤል አምላክ ተባለ? እነዚህ በተጠቀሰው ቁጥር ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች ናቸው። ይህ የመጽሐፉ አዘጋጅ ሲፈቱት የዘጋው በር ፍቺ የማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና በመግለጽና በማሳወቅ ደምድመዋል። ልክኛው ዳኛ እግዚአብሔር አሳቡን የገለጸበት ቃሉ ነው። ትንቢተ ሕዝቅኤል 48 ምዕራፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ አጠቃላይ መልእክት የእግዚአብሔር ፍርድ በሕዝቡ ላይ ሊመጣ መቃረቡንና የኢየሩሳሌም መያዝና መፍረስ የደረሰ መሆኑን እያስጠነቀቀ፣ ቤተ መቅደሱና የእስራኤል መንግሥት ወደ ቀድሞው ሁኔታ እንደሚመለስ ሕዝቅኤል ያየው ራእይ ነበር። የዚህ ራእይ የማጠቃለያ ምዕራፍ ከ40-48 ያለው ሲሆን፣ በዚያ የቤተ መቅደስ እደሳ፣ የመሠዊያ ዝግጅት፣ የቤተ መቅደሱ አደባባይና ዋና ዋና የዙሪያው በሮች እንዴት እንዴት እንደሚታደሱ የተገለጸበት ምዕራፎች ናቸው። ከእነዚህ የአደባባይ በሮቹ አንደኛው የምሥራቁ በር ነው።

ስለዚህ በር የሚናገረው ክፍል በአለቃ አያሌው ሕዝቅኤል 44፡1-4 የተባለለት ብቻ ሳይሆን፣ በሕዝቅኤል 8፡16 የፀሐይ አምላኪዎች ተንበርክከው የሚሰግዱበት ስፍራ መሆኑ፣ በሕዝቅኤል 10፡19 ኪሩቤል ክንፎቻቸውን ዘርግተው ሲበሩ በዚያ በር ቆም ማለታቸውን፣ ከሕዝቅኤል 11፡23 ደማቅ ብርሃን በከተማይቱ በስተ ምሥራቅ ወዳለው ስፍራ መሄዱጨ በሕዝቅኤል 43፡1-2 በዚያ ደግሞ ብርሃን ከምሥራቅ ሲፈልቅ ማየቱ፣ ሕዝቅኤል 44፡1-4 ይኸው የምሥራቅ በር ተዘግቶ እንደሚቀር መግለጹ የታሪኩ ሂደት

በቁንጽልነት የማይታይ መሆኑን ያስገነዝባል።

ከዚህ በማዕከላዊነት የምንይዘው መረጃ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱንና ሕዝቡን የሚያድስበትን የወደፊት ሁኔታ የሚገልጽ መልእክት መሆኑ ነው። የተዘጋውም በር ቀድሞ ጣዖት አምላኪ ዎች በስፍራው የገነቡበት ተወግደው እግዚአብሔር ላይለያቸው ከእነርሱ ጋር ሳይወጣ ሊኖር እንዳለው የሚገልጽ እንጂ፣ ማርያምን በዚህ ስፍራ አምጥተን ሊመሳሰሉና ሊቀራረቡ የማይችሉ ገለጻዎችን በመውሰድ ማገጣጠም የመልእክቱን ዐውደ ንባባዊ ፍቺ መጣስ ነው። እንዲህ ይሁን ተብሎ ከቀጠለማ በዚያው ምዕራፍ ቁጥር 3 የሕዝቡ መሪ የተቀደሰውን የመሥዋዕት ኅብስት ለመብላት በዚያ መቀመጥ ይችላል፣ መግባትና መውጣት ይፈቀድለት የተባለለትን ምን ሊሉት ይሆን?

ከላይ እንዳነሣሁት፣ በቅኝቴ የቃሉን ዳኝነት የተማጸንኩበት ነጥብ በከፊል ከመጽሐፉ አዘጋጅ አባባል ጋር እየተስማማሁ ወደ ፍጻሜው ላይ ያነሡትን የዘላለማዊ ድንግልናን አትኩሮት መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እርሳቸው ከዳር ዳር ዘግቶ አያስቀምጥም። እርግጥ ነው፣ እኔም ቅድስት ማርያም ጌታን ከመፀነስዋ በፊት፣ በፀነሰች ጊዜ፣ ከፀነሰችም በኋላ፣ ከመውለዷ በፊት፣ በወለደች ጊዜ ድንግል ናት ብዬ አምናለሁ። ከዚያ በኋላ ባለው ቀጣይ ሕይወቷ ግን የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤዎች እንዳንስት ያስፈልጋል።

ትኩረት አንድ፦ «የዳዊት ዘር» ዮሴፍ ሆይ! እጮኛህ ማርያም የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ስለ ሆነ፣ እርስዋን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ» [ማቴ. 1:20፤ አዲስ ትርጉም (የታረመ)]። ይህ ጥቅስ በአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ ብቻ ሚስትህ ማርያም መባል የሚገባውን ቃል እጮኛህ በማለት ተተ ክቷል (ለዚህ ለውጥ የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ምላሽ ይኖረው ይሆናል)። የእኔ ትኩረት በእናት በአባቷ ቤት ሳለች ታጭታ የነበረችው ማርያም ከቤተሰቧ መለየት የምትችለው ወደ አጫት ሰው ገብታ ስትኖር ነውና ይህ መልእክት በመልአኩ ወደ እርሱ መጣ።

ትኩረት ሁለት፦ «እጮኛውን ማርያምን ወደ ቤቱ ወሰዳት።

ይሁን እንጂ፣ ልጅዋን እስከ ወለደች ድረስ አላወቃትም» (ማቴ. 1:24-25)። በዚህ ላይ እጮኛው በማለት የተተካው ሚስቱን በማለት የተጻፈው ነው። በዚህ ጥቅስ ላይ ላተኩርበት የፈለግኩበት ቃል «አላወቃትም» የሚለው ማሠሪያ ቃል ነው።

ይህ ቃል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተብሎ የሚተካ ነው። እንዲህ ከሆነም ዮሴፍ. . . ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙ ነት ካልፈጸመ፣ ኃላስ?

ትኩረት ሦስት፦ ዮሴፍና ማርያም በቤተ መቅደስ ባዩት ጊዜ ተደነቁ፤ በዚያን ጊዜ እናቱ፣ «ልጄ ምነው እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር» እኮ አለችው (ሉቃስ 2:48)። ይህ የሆነው ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ ነበር። ከዚህ የምንረዳው ማርያምና ዮሴፍ በአንድ ላይ ይኖሩ እንደ ነበር ነው። ከኖሩስ. . .?

ትኩረት አራት፦ «ኢየሱስ ለሕዝቡ ገና ሲናገር ሳለ እናቱና ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጪ ቆመው ነበር» (ማቴ. 12:46)። ይህ ቃል የተጻፈው ኢየሱስ በ30 ዓመት እድሜው አገልግሎት በጀመረበት ጊዜ ነበር። ይህ ማለት ማርያምና ዮሴፍ ለበርካታ ዓመታት አብረው በኖሩበት ጊዜ ውስጥ፦ ኢየሱስን የፈለጉት እናቱ ደግሞም ወንድሞቹ ነበሩ፣ ወንድሞቹ ለኢየሱስ ወንድም የሚሆኑት በአንድ መንገድ ነው፤ እርሱም በእናቱ የተገኙ ከሆነ ነው። በዮሴፍ በኩል ብቻ የመጡ ከሆነ፣ ከእርሱ ጋር የሥጋ ወንድምነትን ሊያገኙ አይችሉም። ምክንያቱም ኢየሱስ ያለ ወንድ ፈቃድ ወይም ያለ ዮሴፍ የተገኘ ስለሆነ። ይህ የሚጠቁመን ወንድሞቹ ከማርያም የተገኙ መሆናቸውን ነው።

ትኩረት አምስት፦ «እነዚህ ሁሉ ዘወትር ለጸሎት በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር ከእነርሱም ጋር አንዳንድ ሴቶችና የኢየሱስ እናት ማርያም እንዲሁም የኢየሱስ ወንድሞች ነበሩ» (ሐዋ. 1:14)። ይህ አገላለጽ። በእርግጥ ኢየሱስ ወንድሞች እንደ ነበሩት፣ እንዲሁም ማርያም እንደ እነርሱ በጌታ ታምና እንደ ነበረች ይጠቁማል።

እነዚህን ሁሉ ያነሣሁት በመጽሐፉ ላይ ዘላለማዊ ድንግልና የሚለው አባባል ሊታሰብበት የሚገባ በመሆኑ ነው። ዓላማዬ

አንዲት ናት፤ ዳኛችን «የጌታ ቃል ብቻ ነውና በእግዚአብሔር ሕያው ቃል ላይ ራሳችንን እንስጥ፣ ለእርሱም እንገዛ።»

ቀጣይ ቅኝት

«ከእሴይ ለዳዊት ዘር የሆኑ እያቄምና ሐና መካኖች እንደ ነበሩ ታሪክ ይናገራል ግን በያም በጸሎት በሕጉ ጸንተው ከኖሩ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነሐሴ 7 ቀን በብሥራተ መልአክ ተፀንሳ ግንቦት 1 ቀን ተ ወልዳለች» (ገጽ 42)።

«እመቤታችን ከእናት አባትዋ ቤት 3 ዓመት ኑራለች፤ በቤተ መቅደስ 12 ዓመት ቆይታለች፤ ይህም 15 ዓመት ይሆናል። በዚህ ዕድሜዋ ሊቀ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ እንደምትፀንስ ወንድ ልጅም እንደምትወልድ አበሠራት» (ገጽ 45)።

«ሄሮድስ ሊገድለው ሲያድነው በነበረበት ጊዜ ካህኑ ስምዖን አይሁድ እንደሚገድሉት ትንቢት በተናገረበት ጊዜ ለበዓል ወጥቶ ሳይመለስ በመቅረቱ፡- በደረሰባት ድንጋጤ፣ አይሁድ ሁልጊዜ ለጠላትነት ሲዘጋጁበት በመመልከትዋ፣ ኋላም ሕማሙን ስቅላቱን በማየትዋ የደረሰባት መከራና ሀዘን እጅግ በጣም ከባድና አሳዛኝ ነው። ከዚህም በቀር ጌታ ካረገ በኋላ 5 ዓመት ሙሉ ይኸው የዕለተ ስቅለቱ ሐዘን ከልብዋ ሳይወጣላት ስታዝን ስትተክዝ ኖራለች» ከዚህ በላይ በገለጥነው ሁኔታ 63 ዓመት ያህል ከኖረች በኋላ በ64ኛ ዓመትዋ ጥር 21 ቀን ዐረፈች» (ገጽ 54)።

«ሐዋርያት ተሰብስበው በተገኙበት ልጅዋ ጌታችን፣ አምላካችን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕረፍትዋ ወዳለችበት መጥቶ ነፍስዋን ከሥጋዋ ለይቶ ወደ ሰማይ ሲያሳርጋት ሥጋዋን ደግሞ ሐዋርያት በጌቴሴማኒ መቃብር አሳርፈውታል» (ገጽ 55)።

«ፍልሰታ የሚለው ቃል የእመቤታችን ሥጋ ከጌቴሴማኒ ወደ ገነት መፍለሱን ኋላም በገነት በዕፀ ሕይወት ሥር ከነበረበት መነሣቱን ለማመልከት የሚነገር ቃል ነው።» ነሐሴ 16 ቀን ጌታ መላውን ሐዋርያትን ወደ ገነት አውጥቶ በገነት በዕፀ ሕይወት ሥር ከነበረው መቃብር እመቤታችንን ነፍስዋን ከሥጋዋ አዋህዶ ትንሣኤዋንና ዕርገትዋን አሳይቶ ለዓለም ይህንኑ እንዲያስተምር አዘዛቸው» ይላል ገጽ 67-68።

ከላይ እየመጠንኩ ያስቀመጥኩት፡- የማርያምን የሕይወት ታሪክ ነው፣ እንደ መጽሐፉ አባባል «ከመፀነሷ እስከ ትንሣኤዋና ዕርገትዋ ድረስ ያለው ክንውን ምን እንደሚመስል በመፈለግ ይህንን ለቀጣዩ ጽሑፌ መግቢያ አድርጌዋለሁ፡፡

መቼም ታሪክ ጽኑ ታሪክ ሆኖ ለሕዝብ ሊናኝ የሚችለው በብዙ ምስክሮችና መረጃዎች ተረጋግጦ መቅረብ ሲችል ነው፡፡ አልያ ውዝግብ ውስጥ እና ጥርጥር ውስጥ ይከተናል፡፡ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ለዘከራቸው ነጥቦች መረጃዬ ብለው ያነሡት ምናልባት ትውፊታዊ አባባልን ካልሆነ በቀር ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ምንም መረጃ የለም፡፡ ይልቁን፣ በዝርዝር የተጠቀሱትን የማርያምን የሕይወት ታሪክ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ አንሥቷቸዋል ወይ? ብለን ብንጠይቅ፣ ስለ አንዱም ያለው ምንም ነገር የለም፣ እርሱ ካልተናገረ ደግሞ እኛ እንናገርለት ዘንድ አንችልም፤ ፍጹም ባለሥልጣን ለሆነው ቃል በመገዛት ቅድሚያ ለእርሱ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

አለቃ አያሌው በመረጃነት ባዘጋጁት መጽሐፍ ላይ፡- በማርያም የሕይወት ታሪክ ላይ ከትንቢት ውስጥ የተወሰኑትን በመመልከት፣ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያልተጣጣሙትን ጉዳዮች በማንሣት ወደ ሌሎች ተከታይ ዐቢይ ነጥቦች አብረን እንዘልቃለን፡፡

ጉዳይ አንድ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 14:3፣ «ሄጄ ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ እኔ ባለሁበት እንድትኖሩ እንደገና መጥቼ እወስዳችኋለሁ» [አዲስ ትርጉም (የታረመ)] በማለት ከአረገ በኋላ እርሱ ባለበት ቅዱሳንን ወደ ራሱ ለመውሰድ እንደሚመጣ ተናግሯል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ የሚያደርግበትን የአመጣጥ ዓይነት በ1ኛ ተሰሎንቄ 4:15፣ «ጌታ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሕያዋን ሆነን የምንቈይ የሞቱትን አንቀድምም» በማለት ገልጾታል፡፡ እግዚአብሔር ቃሉን የሚፈጽም አምላክ ነውና፣ ይህን አካሄድ ስለ ማርያም ብሎ አያፋልስም፡፡ በአለቃ በተዘጋጀው መጽሐፍ ግን ነፍስዋን ለመውሰድ ወደ ምድር እንደ መጣ ይናገራል፡፡ ጌታ ግን በመጨረሻው ዘመን በክርስቶስ የሆኑትን ለመውሰድ ዳግም ይመጣል እንጂ፣ የእናቱን ነፍስ ለመውሰድ ወደ

ምድር አይመጣም። እናም ከዚህ የተነሣ ይህ አባባል ለውዝግብ ተ ጋልጧል።

ጉዳይ ሁለት

በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:52-54፣ «የሞቱትም ሰዎች የማይጠፉ ሕያዋን ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን፣ *ይህ የሚጠፋው የማይጠፋውን ይህም የሚሞተው የማይሞተውን መልበስ አለበት።* ይህ የሚጠፋው የማይጠፋውን ይህም የሚሞተው የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ፣ «ሞት በድል ተዋጠ!» ተብሎ የተጻፈው ይፈጸማል» [አዲስ ትርጉም (የታረመ)]። ይህ ክፍል አንድን ቁም ነገር ያስጨብጣል። ዛሬ በምድር ላይ ያለን ሰዎች የሚጠፋ አካል ለብሰናል፣ በሞትም ወደ አፈር እንመለሳለን፣ የማይበሰብስ አካል የምንለብሰው ወደ ፊት በትንሣኤ ጊዜ ነው። ግና ይህን እውነት የሚቃረን ነጥብ የማርያም ታሪክ ላይ ተነሥቷል። እርሱም፣ «ጌታ መላውን ሐዋርያትን ወደ ገነት አወጣ፣ ከዚያም መለሳቸው» ይላል። ይህ ሊሆን አይችልም፤ ቢሆንማ ኖሮ ወደ ገነት በወጡ ጊዜ የማይጠፋ አካል ለብሰው ዘላለማዊ አካል ይዘው ነውና የመጡት አይሞቱም ነበር፤ ግን ሁሉም ሞተው አፈር ሆነዋል። ከዚህ የተነሣ ይህ አተራረክ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተጣርሷል።

ጉዳይ ሦስት

ማቴዎስ 28:19፣ «እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አስተምሩአቸው...» [አዲስ ትርጉም (የታረመ)]። ጌታ ሐዋርያቱን ወደ ዓለም ሁሉ የላካቸው የእርሱን ትምህርት እንዲያስተምሩና የወንጌልንም ምሥራች እንዲያውጁ ነው። ይህንንም አዘዛቸው። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ይኸው ብቻ ሆኖ ሊዘልቅ ይገባዋል። በአለቃ መጽሐፍ ግን ከዚህ ሕያው መልእክት ጋር የሚቃረን ሌላ መልእክት ለሐዋርያቱ ሲሰጥ እናገኛለን። ያም፣ «ጌታ ስለ እናቱ ትንሣኤዋንና ዕርገትዋን አሳይቶ ለዓለም ይህንኑ እንዲያስተምሩ አዘዛቸው» ይላል። ይህ አባባል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አይግባባም።

ጉዳይ አራት

ጉዳይ አራት አሳቡን በጉዳይ ሦስት ላይ ያደርጋል። ኤፌሶን 2:20፣ «በሐዋርያትና በነቢያትም መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማእዘኑም ራስ ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ሲል፣ በሐዋርያት ሥራ 2:42 ደግሞ፣ «እነርሱም የሐዋርያትን ትምህርት በመስማት፣ በኅብረት አብሮ በመኖር፣ ማዕድን አብሮ በመብላት በጸሎት ይተጉ ነበር» ይላል [አዲስ ትርጉም (የታረመ)]። እኒህ ሁለት ጥቅሶች የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን ትምህርትና የምትኖርበትን እውነት በመሠረትነት የጣሉላት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት ናቸው።

እነዚህን ሐዋርያት ነው በአለቃ አያሌው የማርያም የሕይወት ትረካ ውስጥ ሐዋርያትን ወደ ገነት መውሰድ ብቻ ሳይሆን፣ ሲመልሳቸው ለማርያም ያደረገላትን ሁሉ በዓለም እንዲያስተምሩ አዘዛቸው የተባለው። እነርሱ ግን ይህን ታዘዙ ወይ? ምላሹ አልታዘዙም ነው። ላለመታዘዛቸው መረጃው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መቼም የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት በአብዛኛው የጻፉት ሐዋርያት ናቸው። ወደ ገነት ተወሰዱ ከተባሉት ሐዋርያት ውስጥ ማቴዎስ፣ የማቴዎስ ወንጌልን፤ ዮሐንስ፣ የዮሐንስ ወንጌልን፣ 3 መልእክቶችንና ራእይን፤ ጴጥሮስ 1ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጽፈዋል። እነርሱ ግን አንድም ቦታ፣ አንድም ጊዜ ጌታ የማርያምን ነፍስና ሥጋ በተመለከተ ወደ ገነት ወስዶን ነበር፣ የሠራውንም ተአምር ለዓለም እንድናስተምር አዘዘን አላሉም። ካላሉ፣ እኛስ ምን እንላለን፣ ዝም እንጂ።

አሁን ደግሞ በቅኝት መግቢያዬ ላይ ባልኩት ሁለት ዐቢይ ነጥብ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል በማስተያየት ልመዝን፦

ቀዳሚ ዐቢይ ነጥብ፦

«በኃልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር/በማሰብ፣ በመናገር፣ በሥራ/በደል ያልተገኘባት በነፍስ በሥጋ በሕሊና ድንግል ንጽሕት መሆንዋን እናምናለን» (ገጽ 76)።

ከዚህ አባባል ጥያቄ የሚፈጥርብኝን ላመላክት። በሮሜ 5:12፣ «በአንድ ሰው (በአዳም) ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ፣

በኃጢአት ምክንያትም ሞት መጣ፤ እንዲሁም ሰው ሁሉ ኃጢአትን ስለ ሠራ ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ» ሲል፤ በሮሜ 3:23፣ «ሰ ዎች ሁሉ ኃጢአት ሠርተዋል፤ እግዚአብሔር የሰጣቸውንም ክብር አጥተዋል» ይላል። እነዚህ ጥቅሶች አስረግጠው የሚነግሩን ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ነው። ማርያምን ስናስብ ከዚህ ውጭ የሚሆንበት ምንም ምክንያት የለም። እርሷ የኃጢአት ዘር ካለባቸው ከእናትና አባቷ የተገኘች ነች፤ ከዚህም የተነሣ በሉቃስ 1:46-47 በገዛ አንደበቷ፣ «ነፍሴ ጌታን ታመሰግናለች መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ትደሰታለች» በማለት መድኃኒቴ ብላ ጌታዋን ትጠራለች። ይህም ኃጢአተኛነቷን ያረጋግጣል። ይህ ሆኖ ሳለ ግን፣ «በማሰብ፣ በመናገር፣ በሥራ በደል ያለተገኘባት» የሚለው ትምህርት እንዴት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይጣጣም?

እርግጥ፣ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የማርያም መፀነስ ተአምራዊ ነው። ይህም የሆነው እናት አባቷ መሀን ከመሆናቸው የተነሣ እግዚአብሔር በተአምር ያለ ኃጢአት እንድትወለድ አደረጋት የሚለውን ማርያማዊ አስተምህሮ ማስተ ማርን አስቀድመው ጀመሩ። የሮማ ካቶሊክም ባልተለየ መልኩ 1140 ዓ.ም ከአዳም ኃጢአት ነፃ ሆና መፀነሷንና መወለዷን አስተ ጋቡ። ይህን በጊዜ ውስጥ አንሥተው ያስተምሩት እንጂ፣ በቃል ላይ የሚታመኑት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች እንደ የቂሣሪ ያው ዩሲቢየስ /260-339/፣ አምብሮስ /339-397/፣ ቅዱስ አውግስቲን /354-430/ ያሉት ማርያም እንደ ማንኛውም የአዳም ዘር ኃጢአተኛ እንደ ሆነች አስተምረዋል።

ተከታይ ዐቢይ ነጥብ፡-

«በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኘች ለማማለድ ሥልጣን የተ ሰጣት መሆንዋን» እናምናለን (ገጽ 76)። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ «በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኘች» በሚለው እኔም እስማማበታለሁ። ያልታረቀልኝ ነጥብ እርሱን ተከትሎት የመጣው «ለማማለድ ሥልጣን ተሰጣት» የሚለው ነው። ይህ አነጋገር በምሥራቅና በምዕራብ ቤተ ክርስቲያናት ዘንድ ገናና የሆነ አስተ ምህሮ ነው፤ ብዙዎች አምነው ይቀበሉታል። ቁም ነገሩ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የመኖሩ ጉዳይ ሳይሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ስለ ማርያም የማማለድ ሥልጣን ምን የተላለፈልን መልእክት አለ? የሚለው ነው።

ከጽኑ ቃሉ ልነሣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5፣ «እግዚአብሔር አንድ ነው፤ በመካከል ሆኖ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስታርቀውም አንድ ነው፤ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» ይላል።

ሮሜ 8፡34፣ «. . . እርሱ ስለ እኛ የሞተ፣ ከሞት ተነሥቶ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ ስለ እኛም የሚማልድ ነው» ሲል፣ ዕብራውያን 7፡24-25 «ኢየሱስ ግን ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ ክህነቱ የማይለወጥ ነው። ስለዚህ እነርሱን ለመማለድ ለዘላለም እነርሱን ለመማለድ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ስለሚኖር በእርሱ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሁሉ በፍጹም ሊያድናቸው ይችላል።»

እነኚህ ተከታታይ ጥቅሶች በእርግጥ የሚናገሩት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት ነው። ምናልባት ስለ ማርያም ማማለድ አፋችንን ሞልተን የምንናገርለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቢኖር የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ሊሆን ይችላል፤ ያም በቃና የሠርግ ሥርዓት ላይ ወይን ጠጅ አለቀ፣ ማርያምም ጌታን ጠየቀችላቸው፤ ይህ የልመና ጥያቄ ማማለዷን ያሳያል፤ ይህ ግን እንደ አለቃ አያሌ ው መጽሐፍ እስከ 64ኛ ዓመትዋ ጥር 21 ቀን ድረስ የቀጠለ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ዕለት እንደ እርሳቸው ጥናት የሞተችበት ጊዜ ስለሆነ። ልክ እንዲሁ፣ ማንም በክርስቶስ ሆኖ በሕይወት ካለ ለሌ ላው ይጸልይለት /ያማልድለት/ ዘንድ ይችላል። ከዚህ ውጪ ግን መጽሐፍ ቅዱሳችን ዘላቂ የማማለድ ሥልጣንን እግዚአብሔር ለማርያም እንደ ሰጣት የሚገልጽ አንድም ጥቅስ አናገኝም።

ማጠቃለያ

በመግቢያዬ ላይ «ወላዲት አምላክ በኢትዮጵያ» የሚለው መጽሐፍ በርካታ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት ገልጫለሁ። አስከትዬ ግን የክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ሁሉ መለኪያ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ስለሆነ፣ ከዚህ ሕያው መልእክት ያፈነገጠ ምንም ዓይነት ትምህርት ሊያወያይና ሊያመካክር ይገባዋል። የዚህም ውጤቱ ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ

3:16-17 እንደተናገረው መሆን ነው፣ «ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው፣ እርሱ እውነትን ለማስተማር፣ የተሳሳቱትን ለመገሠጽ፣ ስሕተትን ለማረምና ለትክክለኛ ኑሮ የሚበጀውን መመሪያ ለመስጠት ይጠቅማል። የሚጠቅመውም የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም እንዲሆንና ማንኛውንም መልካም ሥራ ለመሥራት ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው» [አዲስ ትርጉም (የታረመ) 1997]። እንግዲህ የማጠቃለያ መልእክቱ ይኸው ነው።

ቅድስት ማርያምና «ልዩ መገለጦች»

«በመርከቡ ላይ የተጫነው ትልቅ ሳጥን መነሻውን ያደረገው ካሊፎርኒያ ሲሆን፣ መድረሻው ቫቲካን ነበር። በዚያ ደርሶ የሚቀርበው ለብፁዕ ወቅዱስ ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ ይሆናል። ይህ በፊታችው ሊቀርብ ያለው ሳጥን በየክፍለ ዓለሙ ያሉ የበርካታ አገራትን ዝርዝር ይዟል፤ በየአገራቱ ዝርዝር ውስጥ የበርካታ ግለሰቦች ፊርማ አለ፣ መጠኑም 40,383 ነው። ፊርመው የተ ስማሙበት ዐቢይ ጉዳይ፣ ጳጳሱ ሊሻር ሊለወጥ የማይችለውን ድንጋጌ የማውጣት ሥልጣኑን ይጠቀሙበት፤ በዚህም ደግሞ የአዲሱን ቀኖና፣ ይኸውም የቅድስት ድንግል ማርያም የማዳን ድርሻዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እኩል ሆኖ ለሰዎች ሁሉ የምትቆም ጠበቃ መሆኗ ይደንገግልን፣ የሚል ነበር።»

«ይህ ጥያቄ ለማርያም ብዙዎች የሰጧት ከነበረው የቀደመ ስፍራ በእጅጉ የመጠቀ ነው፤ ይህ ምጡቅ ፍላጐት ይሟላ ዘንድ ባለፉት ተከታታይ አራት ዓመታት ወደ ሊቀ ጳጳሱ ከ157 አገሮች 4,340,429 ፊርማ የታከለባቸው ጥያቄዎች ጎርፈዋል። ስሌቱ በማዕ ከላዊ አኃዝ 100,000 ደብዳቤዎች በየወሩ ቀርበዋል ማለት ነው፤ የካልካታዋ እማሆይ ቴሬዛ፣ 500 ያህል ጳጳሳት፣ 42 ካርዲናሎችና ሌሎች፣ ዋንኞቸው ዳግማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣናዊ ቃል በላይ ሊከበርና ሊጸና ይችላል የሚባለውን ቀኖና በጊዜ እንዲያጸድቁ ተማጽነዋል።»

እንዲህ የሚለውን ጽሑፍ ያነበብኩት ከኒውስ ዊክ መጽሔት ላይ ነበር። መልእክቱ አስገረመኝ፣ እናም ጻፍኩበት።

ኬኒት ሊውድዋርድ በጽሑፉ እንደ ገለጸው፣ ይህ ተማጽኖ ግቡን ከመታ ግራ ገብ የሆኑ ሦስት ለየት ያሉና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ አስተምህሮች ይወጣሉ፦

አንደኛው፦ ማርያምን በልጅዋ በተሠራው የደኅንነት ሥራ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ያደርጋታል።

ሁለተኛው፦ በክርስቶስ ሥቃይና መከራ ሊገኝ ያለው ጸጋ ዋስትና የሚኖረው በማርያም በኩል በሚደረገው የምልጃ ሥራ ይሆናል።

ሦስተኛው፦ የጸሎት ልመናዎች ተፈጻሚነት ያገኙ ዘንድ በማርያም በኩል በማለፍ ኢየሱስ ትኩረት ያደርግባቸዋል። እነዚህ ሦስቱ ማርያምን ከፍ ላለ ደረጃ ያበቋታል። ይህ ግን በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5፣ «በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» (የ1954 እትም) የሚለውን ሕያው ቃል ፈጽሞ ይጻረራል። ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር ቃል ብቸኛ ባለሥልጣንነት የሚታመኑት ክርስቲያኖች በዚህ ቀኖና እያሰቡበትና እያሳሰባቸውም የሚገኝ ሆኖአል።

ለመሆኑ በማርያም የሚደገፉትን ወደዚህ ድንጋጌ ወይም የውሳኔ ቃል ላይ እያስገሰገሰ ያደረሳቸው ምን ይሆን? ለዚህ ጥቂት ምላሽ እንዘክር፤

ዶክተር ሮበርት ሺፈር፦ ለሕዝብ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት የተሰጠውን ምላሽ በማስላት ያሉት፣ «. . .ብዙው የዓለም ሕዝብ ልቡን ከየትኛውም ዘመን ይልቅ በእነዚህ ቅርብ ዓመታት ለማርያም ሰጥቷል» የሚል ሲሆን፣ ሌሎች ካቶሊካውያን ሆነው በማርያማዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበሩት ደግሞ፣ «መንፈስ ቅዱስ ማርያምን ወደዳት፣ ቀርቦም አጫት» የሚል መልእክታቸውን አስፋፉ። ***<u>እንዲሁም</u>*** ሌሎች፣ «ሐዋን በኤድን ገነት ለእግዚአብሔር አሳብ እምቢታን ገለጸች። ማርያም ግን እግዚአብሔር ያላትን በእሽታ በመግለጽ በመታዘዟ የመዳናችን ብቸኛ ምክንያት ናት» ሲሉ፣ ***<u>ሌሎች ደግሞ፣</u>*** ወንጌላት ስለ ማርያም የተረኩት ትረካ ጥቂት ነው፤

ለምሳሌ፣ ከወንጌላት በቅድሚያ ተጻፈ የሚባለው ማርቆስ «ማርያም ልጅዋን እንደ ተረዳችው» ብቻ ገልጾ ሲያቆም፣ ማቴዎስ በድንግልና እንደ ወለደችው ዘክሮ ይተዋል፤ ትንሽ ሰፋ ያለ ዘገባ የሚገኝበት ሉቃስ ነው፤ በእርሱ ጽሑፍ ማርያም ታዛኝ፣ ትሑት፤ ጸጋን የተ ሞላች መሆኗን፣ ትውልድ ሁሉ እንግዲያመሰግናት ገለጸ፤ ዮሐንስ ደግሞ በቃና ዘገሊላ ኢየሱስ ተአምራት ያደርግ ዘንድ ምክንያት መሆኗን እንዲሁም በትረካው መጨረሻ በስቅላቱ ጊዜ በአጠገቡ የነበ ረች መሆኗን በመግለጽ ጨርሰዋል። እነዚህ ውሱን ናቸው፤ ከእነዚህ ሌላ ግን በየጊዜው ማርያምን አስመልክቶ የሚወሰኑት ውሳኔዎች፣ የሚገለጹት ራእዮች፣ የሚታዩት ሕልሞች፣ በተለያዩ አገሮች ከተለያዩ ሰዎች ጋር በአካል በመምጣት የምታስተላልፋቸው መልእክቶች እየጨመሩ መምጣት ዛሬ ላለው ማርያማዊ እንቅስቃሴ ዋነኛ መነሻ መሆናቸውን በመረጃ እየደገፉ ያቀርባሉ። አሳባቸውን መረዳት እንድንችልና ከእግዚአብሔር ሕያው ቃል ጋር ማነጻጸር እንዲቻል ከ431-1959 ዓ.ም ያሉትን ማርያም መሰል መገለጦችን በመጥቀስ በአጠገቡ ሊሆን እንደማይቻል የሚገልጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አስፍሬአለሁ። አንባቢዬ ክፍሉን በማንበብ ያረጋግጡ፤

መረጃ ከተሰኙት ክፍሎች እነሆ፡-

- **431 ዓ.ም በኤፌሶን፡-** በአሁኗ ቱርክ በተካሄደው ጉባዔ ማርያም የእግዚአብሔር እናት (እመ-አምላክ) ተብላ መጠራቷን በመስማማት ተፈጸመ (ሉቃስ 1:46-48)።

- **በ1531 በሜክሲኮ፡-** ማርያም አራት ጊዜ ልጅህን ዲጎ በመገለጽ ዲጎ ወደ ኤጲስ ቆጶስ ዘሁማርጋ በመሄድ ከሜክሲኮ ወጣ ብሎ ቤተ ክርስቲያን እንዲያሠራላት እንዲነግረው አዘዘችው ታዘዘም (1ኛ ቆሮ. 3:11)።

- **በ1830 ፓሪስ፣ ፈረንሳይ፡-** ካቲሪን በካቴድራሉ ሳለች ሁለት ጊዜ ማርያም በመገለጥ ወደ እርሷ ጸሎት ሊደረስበት የሚችል ሜዳሊያ እንዲሠራላት አዘዘች፣ እንዳለችውም ሆኖ (ተአምረኛው ሜዳሊያ) የተሰኘ መጸለያ በ1832 ተሠርቶ ተሰራጨ (ዮሐ. 14:13-14)።

- **በ1854 ጳጳስ ፒዮስ ዘጠነኛ፡-** «ማርያም ከእግዚአብሔር ልዩ

ጸጋ የተነሣና ለክርስቶስ እናት ለመሆን በመዘጋጀቷ ከአዳም ከተወ ረሰ የኃጢአት ዘር ነፃ ናት» የሚል ቀኖናን አወጡ (ሉቃስ 1፡47፤ ሮሜ 3፡11)።

- **በ1858 በፈረንሳይ ማሲቢሊ፡-** ማርያም ከየካቲት እስከ ሐምሌ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ለአሥራ ስምንት ጊዜ ተገልጻ ያለ ኃጢአት መፀነሷን አሳወቀች. . . (ሉቃስ 1፡46-55፤ ሮሜ 3፡11-23)።

- **በ1871 ፖትማን፣ ፈረንሳይ፡-** ማርያም ለአራት ልጆች ተ ገልጻ ፈረንሳይን እየተዋጉ ያሉት ወራሪዎች ከመቅረባቸው የተነሣ ይጸልዩ ዘንድ አዘዘቻው፣ በጸለዩም ጊዜ ጠላቶቻቸው ፈጥነው ተ መለሱ። ከዚህ በኋላ «የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን» የተባለ ሕንፃ በዚያ ታነጸ. . . (1ኛ ቆሮ. 3፡11)።

- **በ1879 በኖክ፣ አየርላንድ፡-** የማርያም፣ የዮሴፍ፣ የሐዋርያው ዮሐንስ፣ የበግ እና የመስቀል ምስል በመንደሪቱ ካለቸው የጸሎት ቤት በስፋት እይታ በታላቅ ብርሃን ታዩ። ይህንንም አሥራ አምስት ያህል ሰዎች በአድናቆት ተመለከቱት. . . (2ኛ ቆሮ. 11፡4)።

- **በ1917 ፖርቹጋል፡-** ዕድሜያቸው ከ7 እስከ 14 ለሚደርሱ ሦስት ልጆች ለስድስት ጊዜያት ተገልጻ፣ «ፍጹም ንጹሕ ኃጢአት የለሽ ልብ ያላት መሆኗን አዩ/ተረዱም።» ይህንኑ በ1942 በጳጳሱ ፒየስ 12ኛ ዓለም አቀፍ ደረጃ የማርያምን ልበ ንጹሕነት ገለጹ. . . (ኤር. 17፡9-10)።

- **በ1932-33 ቤልጅየም፡-** በአንድ የአትክልት ስፍራ 33 ያህል ጊዜ ተገለጸች፣ የታየቻቸውም አምስት ልጆች ዕድሜያቸው ከ9 እስከ 15 ሲሆን፣ የታየችውም ፍጹም በሆነ ልቦና ነበር (Virgin of the golden heart) (ኤር. 17፡9-10)።

- **1933 ቤልጅየም፡-** የ12 ዓመቷ ልጅ ለማሪቱ ቤኮ ስምንት ጊዜ በቤተሰቦቿ የአትክልት ስፍራ ሳለች ታየቻት፣ ታይታም (Virgin of the poor) የእምባ ጠባቂነቷንና ለድሆች፣ ለታመሙና በመከራ ላሉ አማላጅነቷን አረጋገጠችላት (ሮሜ 8፡34፤ ዕብ. 4፡14-15)።

- **1950 ሊቀ ጳጳስ ፒዮስ 12ኛ** ሊሻር በማይችል ሥልጣናዊ ቃላቸው ማርያም በነፍስና በሥጋ ወደ ሰማይ ማረጓን አሳወቁ. . . (ዮሐ. 3:13)::

- **1945-59 በአምስተርዳም፣ ኔዘርላንድ:-** ማርያም የሕዝቦች ሁሉ እመቤትነቷን በተደጋጋሚ ለኢዳ ፖርድመን ገለጠች፤ ለዓለምም ሕዝብ ሰላም ለማምጣት ቃል ገባች፣ ለኢዳም በታሪኳ ውስጥ ለጳጳስ የመጨረሻ የሆነውን ድንጋጌ ማለትም የምትቤዥ፣ መካከለኛ እና ጠበቃ መሆንዋን እንዲያሳውቅ መልእክት ሰጠችው (ዮሐ. 14:27፤ 1ኛ ጢሞ. 2:5)። እነዚህ ከፊል መረጃዎች የተ ወሰዱት (Catholic Almanac) ከተሰኘው ምንጭ ነው::

እንግዲህ በ431 በኤፌሶን ጉባዔ በእመ-አምላክነት የተገለጸችው ማርያም፣ በ1959 ለኢዳ ፕርድማን ባሳወቀችው የድንጋጌ ጥያቄ ከፊል ቅኝቱ ተጠናቋል:: አሁን የበለጠ፣ የተሻለ ንጽጽራዊ እይታ እንዲኖረን ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት እንደ ተ ገለጸች እናጢን::

ቅድመ - ልደት

መልእክተኛው ገብርኤል የንግግሩ መጀመሪያ ያደረገው ማርያም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘች መሆኗን በማሳወቅ ሲሆን፣ አስከትሎ የተናገረው ግን የመልእክቱን ዋነኛ ጭብጥ ነበር:- «ከእርሷ የሚወለደው ወንድ ልጅ ታላቅ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሚባል፣ የዳዊት ዙፋን የተሰጠው፣ በእስራኤል ላይ ለዘላለም የሚነግሥ፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የሌለው መሆኑን አበሰረ፤» (ሉቃስ 1:30-33)። ለዚህ የማርያም ምላሽ፣ «እነሆ! እኔ የጌታ አገልጋይ ነኝ፤ አንተ እንዳልክ ይሁንልኝ» የሚል የታዛዥነት መልስ ነበር:: እናም እንደ መታዘዟ ሆነ (ሉቃስ 1:38)::

ከእግዚአብሔር ለተላከው መልእክት ከመታዘዟ የተነሣ እግዚአብሔር እንዳለው ፀነሰች:: ይህ ሁኔታ በእናት በአባቷ ቤት ላለች ልጃገረድ አርግዞ መገኘት አስነዋሪና በሕጉ መሠረት አስወጋሪ ስለ ነበር፣ የእግዚአብሔር መልአክ ለእጮኛዋ ዮሴፍ የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ገልጾለት ወደ ቤቱ እንዲወስዳት ነገረው (ማቴ. 1:20)። እርሱም መልአኩ ባዘዘው መሠረት ከእርሱ ጋር ትኖር ዘንድ ወደ ቤቱ ወሰዳት (ማቴ. 1:24)። ወስዷትም አብረው

እየኖሩ ኢየሱስን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸሙም ነበር (ማቴ. 1:25)። ማርያም የእግዚአብሔር አሳብ በእርሷ ከመፈጸሙ የተነሣ ጌታዋን አመሰገነች፦ «እርሱ ዝቅተኛዋን አገልጋይ እንደ ጎበኘ፣ ከያኔም ጀምሮ ትውልድ ሁሉ የተመሰገነች እንደሚሏት ተናገረች። ***የዚህም ታላቅ ምስጢር እግዚአብሔር ለአባቶቻችን የሰጠው የተስፋ ቃል በእርሷ ከመፈጸሙ የተነሣ እንደ ሆነም አሳወቀች*** (ሉቃስ 1:46-55)።

ድኅረ - ልደት

ማርያምና ዮሴፍ ለእረኞቹ መልአኩ የነገራቸውን ሁሉ ከአንደበታቸው በሰሙ ጊዜ ተደነቁ። ለአድናቂነቱም ትኩረት ሰጥታ የሆነውን ሁሉ በልብዋ በመያዝ ታሰላስለው የነበረችው ማርያም ነበረች (ሉቃስ 2:17-19)። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሕፃኑ አደግ ብሎ ሳለ ሊሰግዱለት ***የምሥራቅ ጠቢባን መጡ፣ ባገኙአቸው ጊዜ ገጸበረከትን ለሕፃኑ አቅርበው ለእርሱም ተንበርክከው ሰገዱለት*** (ማቴ. 2:11)። ይህ ከሆነ በኋላም ማርያምን፣ ሕፃኑንና ዮሴፍን የሚያሸሽ ጉዳይ መጣ። ሄሮድስ ኢየሱስን ይገድለው ዘንድ ፈለገ፤ በዚህ የእግዚአብሔር መልአክ ዮሴፍን ይሸሽ ዘንድ ነገረው። እርሱም ታዝዞ ወደ ግብፅ ሸሸ። ኋላም እንዲሁ በእግዚአብሔር መልአክ ሕፃኑን ለመግደል የሚፈልጉት መሞታቸውን ነግሮት ይመለሱ ዘንድ አሳወቀው (ማቴ. 2:13፣ 20-21)። የመሸሹም ሆነ የመመለሱ ዋነኛ ትኩረት ከዮሴፍና ከማርያም ጋር በተያያዘ ሳይሆን፣ ስለ ሕፃኑ እንደ ሆነ ተገልጿል።

የልጅነት ጊዜ

ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ በኢየሩሳሌም በዓልን ያከብሩ ዘንድ ዮሴፍና ማርያም ይዘውት ወደዚያው ወጡ። ከክብረ በዓሉ በኋላ ሲመለሱ አብሮአቸው እንዳለ በመቁጠር ብዙ ከተጓዙ በኋላ አለመኖሩን አውቀው ተመለሱ፣ ያገኙት በቤተ መቅደስ ነበር። በዚህ ጊዜ እናቱ ማርያም፣ «ልጄ ምነው እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር» አለችው። የኢየሱስ ምላሽ ግን፣ «ልትፈልጉኝ አይገባም፤ እኔ በአባቴ ቤት መሆን እንደሚገባኝ አታውቁም ኖሮአልን» የሚል ነበር [ሉቃስ 2:42-49፤

አዲስ ትርጉም (የታረመ) 1997]::

ዘመነ አገልግሎት

ኢየሱስና ማርያም በተጠሩበት ሠርግ ተገኝተው ሳሉ የወይን ጠጅ ማለቁን እናቱ ከመስማቷ የተነሣ ወደ ኢየሱስ በመምጣት መቸገራቸውን ነገረችው፣ ለአገልጋዮቹም መለስ ብላ፣ «እርሱ የሚላችሁን አድርጉ» አለቻቸው:: ጌታም በዚያ ተአምር ፈጸመ (ዮሐ. 2:3-5)::

ማርያም እኔን ስሙኝ ሳይሆን ያለችው፣ እርሱ ብቻ ሊሰማ እንደሚገባው አሳሰበች:: ኢየሱስ አገልግሎቱን ጀምሮ በ30 ዓመት ዕድሜው በይፋ እያስተማረ ሳለ፣ «እናቱና ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው ከውጭ ቆመው ነበር» (ማቴ. 12:46-47):: እንደሚፈልጉት በነገሩት ጊዜ ወደ እነርሱ ሳይፈጥን ትልቁና ዋነኛው ጉዳይ በማስተ ማሩም የሚቀጥልበት ዐቢይ ትኩረት ከወለደችኝ እናቴም ሆነ ወንድሞቹ በላይ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚፈጽሙት ሁሉ ለእኔ እናቴም ወንድሜም ናቸው በማለት ገለጸ (ማቴ. 12:46-47፤ ማር. 3:31-35፤ ሉቃስ 8:21)::

ኢየሱስ በሌላ ስፍራ በማስተማር ላይ እያለ አንዲት ሴት ትምህርቱን አቋርጣ፣ «አንተን ወልዳ ያጠባች እናት የተባረከች ናት» በማለት ድምጽዋን ከፍ አድርጋ ጮኸች፤ እርሱ ግን ወዲያውኑ መልእክቱን ከእናቱ ወልዳ ማጥባት ላይ አንሥቶ፣ «የተ ባረኩስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው በሥራ ላይ የሚያውሉት ናቸው» አለ:: በዚያም ትምህርቱ የበረከት ዋነኛ ሕያው ቃሉን ብቻ መታዘዝ እንጂ፣ ከዚህ ያፈነገጡ ሁሉ ልክ አለመሆናቸውን ገለጸ (ሉቃስ 11:27-28)::

ቅድመ - ሞት

ኢየሱስ በሚሰቀልበት ጊዜ በአጠገቡ እናቱና የእናቱ እኅት፣ የቀለዮጳ ሚስት ማርያምና መግደላዊት ማርያም ቆመው በኀዘን ሳሉ እናቱን፣ «እናቴ ሆይ! እነሆ፣ ልጅሽ!» በማለት የሚወደውን ደቀ መዝሙር አሳያት::» ለእርሱም ደግሞ፣ «እነኋት እናትህ!» አለው፤ ደቀ መዝሙሩም ወደ ቤቱ ወሰዳት» (ዮሐ. 19:25-27):: ይህ የጌታ አደራ በጽኑ የሚያስታውሰን ቁም ነገር አለ፤ እርሱም ስምኦን በቤተ መቅደስ ሕፃኑን አቅፎ እኔን አገልጋይህን በሰላም

አሰናብተኝ ምክንያቱም ማዳንህን በዓይኔ አይቻለሁ (ሉቃስ 2:29-30) በማለት በዘመናት ሁሉ ተስፋ የተደረገበት አዳኝ መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ እናቱን ግን እንዲህ ብሏት ነበር፣ «እነሆ! ይህ ሕፃን በእስራኤል ውስጥ ለብዙዎቹ የመጥፋት፣ ለብዙዎቹ የመዳን ምክንያት ይሆናል፤ እርሱም ብዙዎች የማይቀበሉት ምልክት ይሆናል። በዚህ በብዙዎች ልብ ያለው ስውር አሳብ ይገለጣል፤ የአንቺንም ልብ የኃዘን ሰይፍ ሰንጥቆት ያልፋል» (ሉቃስ 2:34-35) በማለት የተናገረው የማርያም ዋንኛው የኀዘን ሰይፍ በግፍ በሚሰቀልበት ጊዜ በዚያ መገኘቷ ነበር፣ ከዚህም የተነሣ ከጥልቅ ኀዘኗ ያጽናናት ዘንድ ለሚወደው ደቀ መዝሙር ማርያምን አደራ አለ።

ድኅረ - ትንሣኤ

ሉቃስ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ለቴዎፍሎስ በሉቃስ 1:1-4 ሲጽፍለት፣ «በእኛ መካከል የተፈጸሙትን ነገሮች የሚገልጥ ታሪክ ከዚህ ቀደም ብዙዎች ጽፈዋል። ይህን መልእክት ለእኛ ያስተላልፉልን ከመጀመሪያው አንሥቶ የዐይን ምስክሮችና የቃሉ አገልጋዮች የነበሩት ናቸው። እንዲሁም እኔ ከመጀመሪያው አንሥቼ ሁሉን ነገር በጥንቃቄ ከመረመርኩ በኋላ ታሪኩን በቅደም ተከተል እጽፍልህ ዘንድ መልካም ሆኖ አገኘሁት። ይህንንም ማድረጌ የተማርከውን ትምህርት እውነተኛነት በደምብ እንድትረዳ ብዬ ነው» በማለት ትክክለኛውንና እርግጡን የጻፈ ሰው ነው። ሉቃስ ኢየሱስ እስኪመለስ . . . እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ በማለት አረገ ካለ በኋላ (ሐዋ. 1:8-9)፤ አስከትሎ የአሥራ አንዱን ደቀ መዛሙርት ስም ይዘረዝርና እነዚህ ሁሉ ዘወትር ለጸሎት በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር፤ ከእነርሱም ጋር አንዳንድ ሴቶችና የኢየሱስ እናት ማርያም እንዲሁም የኢየሱስ ወንድሞች ነበሩ (ዮሐ. 1:14) በማለት በዚያ በኢየሱስ አዳኝነትና ጌትነት አምነው የዳኑት በአንድ ላይ እንደ ነበሩ ያረጋግጥልናል።

ዘላለማዊ መልእክት

የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ፣ በቂ መልእክት ያለው፣ እርስ በርሱ የማይጋጭ ከመሆኑ የተነሣ፣ ስለ ማርያም በቃሉ ከተገለጸው ውጭ የወጣ እንግዳ አሳቡን ማስተናገድ አይቻልም (ገላ. 1:7-9)። ከዚህም የተነሣ፣ ለክርስቲያኖች ያለን «ዘላለማዊ መልእክት» ጴጥሮስና

ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት የተናገሩት ነው። እርሱም፣ «እናንተ ግንበኞች ንቃችሁ የጣላችሁትም ድንጋይ እርሱ ነው፤ ነገር ግን እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ። ስለዚህ መዳን ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም የለም፤ እኛ ልንድንበት የሚገባን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ስም ከእርሱ በቀር በመላው ዓለም ማንም የለም» (የሐዋ. ሥራ 4:11-12)። አሜን።

ክሎኒንግ - «ሰው በሰው ሊፈጠር?»

« . . .ኖሮፌሰር ዋልፈርድና ኖሮፌሰር ፔምብሪ የተባሉት የዘርፉ ጠበብት በክሎኒንግ... በተለያዩ ችግሮች መውለድ የማይችሉ እና እራሳቸውን መተካት የሚፈልጉ ሰዎች በዘዴው ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ከዘር ወደ ዘር የሚተላለፍ በሽታ የሚያጠቃቸው እና ልጆቻቸው የሚሞቱባቸው ቤተሰቦች ይህ ሳይንስ እያደገ ሲሄድ መፍትሔ ሊገኝላቸው ይችላል፤ በተጨማሪም በተፈጥሮም ይሁን በሰው ሠራሽ አደጋ ወይም በበሽታ ምክንያት አካላቸው ለጎደሉ ሰ ዎች ተተኪ አካል በማስገኘት ያለውን የተለዋጭ አካል ችግሮች ያቃልላል፤ በሌላ አገላለጽም፣ በክሎኒንግ ለመፈጠር የበቁ ሰዎች የኩላሊት፣ የልብ፣ የዓይን፣ የጣፊያ ችግር ላለባቸው ሰዎች እነዚህ አካላት ሊሰጡ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል . . .»

* * *

በከፊል ትንቢታዊ ገለጻ የተጀመረው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ «የሳይንስና ቴክኖሎጂ» ዓምድ ጥቅምት 26 ቀን 1990 ዓ.ም ካስነበበው ከ«ክሎኒንግ አበረታች ወይም አስፈሪ ፈጠራ» ዘገባ ነው።

* * *

ክሎኒንግ ብለው ጠርተውታል፤ የቃሉ ፍቺ የተወረሰው ከግሪክ ቋንቋ ነው። «ከዛፍ ቅርንጫፉን ብቻ በመውሰድ ሙሉ ለሙሉ/ የታቀደውን ዛፍ የሚመስል ተክልን የማስገኘት ውጤትን ያመለክታል። ክሎኒንግ ዘርን የማርባት ሥራ ነው፤ እርቢው ግን የወንዴ ሕዋስን ከሴት እንቁላል ጋር በማገናኘት የሚፈጠር ሳይሆን፣ ከአንደኛው ብቻ የዳበረ ሴል በመውሰድ የተወሰደለትን ሰው ወይም እንስሳ ማስገኘት ነው።»

ክሎኒንግ በአካላዊ ገጽታም (Physically) ሆነ በባሕርይ ውርስት (Genetically) አንድ ዓይነት የሆነን ተመሳሳይ ፍጡር ያስገኛል። በሁሉ ዘንድ እንደሚሆነው፣ በሩካቤ ግንኙነት የሚፈጠር እንስሳም ሆነ ሰው ከእናቱ እንዲሁም ከአባቱ የሚወርሰው አለው። የክሎኒንግ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከአንዱ ዛፍ የተወሰደው ቅርንጫፍ የተወሰደለትን ዛፍ መስሎ እንደ ለመለመ፣ ከአንዱ እንስሳ ወይም ሰው የተወሰደ የዳበረ ሴል የተወሰደለትን ፍጡር ሳይቀይርና ሳይለውጥ የሚያስገኝ ውጤት ነው።

ክሎኒንግ ዋንኛ የሚሆነውን ኒውክለስ በመውሰድ ሽግግር ያደርጋል፤ ኒውክለስ ደግሞ ሁሉን ያዥ የማንነት ግምጃ ቤት ነው፤ በውስጡ በራሂ (Genes)፣ ሐብለ በራሂ (Chromosomes) ይይዛል፤ እናም እርሱ ከዳበረው ሴል ተወስዶ እንዲለማ ይደ ረጋል፤ የተፈለገውም ይመጣል።

* * *

ሳይንቲስቶች ይህን አሠራር የፈለጉበትና ለእርሱም ዕ ድሜያቸውን ሙሉ በእልፍ ሙከራዎች ከሞሉበት ከዋንኛ ምክንያቶቻቸው አንዳንዶቹ፦

አንዲት ላም በክሎኒንግ ዘዴ ብትገኝ፣ እንደ ቀደሙት ላሞች ጥቂት ወተት ለግሳ አትነጥፍም፤ የወተትን ጎርፍ ታጎርፋለች፣ በትንሹ በዓመት 180,000 ሊትር ወተት ትሰጣለች፣ ሲረቡም ከበሽታ ነፃ ይሆናሉ፣ ወተታቸውም የእናት ጡትን ሙሉ በሙሉ ስለሚተካ፣ አንድ ሕፃን ከተወለደበት ሰዓት ጀምሮ ሊጠባው ይችላል። በግም ከሆነ ፀጉሩ በጥራትና በብዛት ይወጣል፣ ተሸልቶም ይበራከታል፤ ጫጩትና የዶሮ እንቁላል በመጠንም በጥራትም ዳብሮ ይፈለፈላል፤ ሰውን የሚመለከተው ደግሞ በመግቢያው ላይ ተነሥቷል። ይህ ቲዎሪ (የአሳብ ንድፍ) ከሁለት መቶ ሰባ ሰባት ጊዜ በላይ ሙከራ ተደርጎ ጤናማ በግ በማስገኘት ተጠናቀቀ፣ ይህም ያለ ወንድና የሴት ዘር ግንኙነት የተገኘችው የዶሊ ዜና ለዓለም ሲዘገብ ሰሚው ተገረመ፣ ተስፋ አደረገ፣ ደነገጠም።

መገረሙ፦ እንዴት ያለ ወንድና የሴት ዘር ግንኙነት ሕይወት ያለው ፍጡር ተገኘ በሚል ሲሆን፣

ተስፋው፦ የተሻለ ወጤት ማግኘትና ከሞት እጅ በማምለጥ ለዘለቄታው መኖር ሊቻል መሆኑ፣

ድንጋጤው፡- ዶሊን ማስገኘት የተቻለበት መንገድ ሰውንም የሚያስገኝ ከመሆኑ የተነሣ በዚህ መንገድ የተገኘው ሰው ስብእናን ያሟላ እውነተኛ ሰው ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ እናም በዚሁ ሥር የሚያወያየው አሳሳቢ ጉዳይ የክሎኒንግ የሳይንስ ውጤት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሲተያይ አፈንጋጭም መሆኑ ነው፡፡ ከፍንገጣው፡-

አንደኛው፡- እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረ፣ ክሎኒንግ ደግሞ ሰውን በራሱ አምሳል አስገኘ፡፡

ሁለተኛው፡- እግዚአብሔር ሰውን በራሱ ሉዓላዊ ፈቃድ ወደዚህ ዓለም ያመጣዋል፣ ይወስደዋልም፤ ክሎኒንግ ሰው የራሱን ጅማሬንና ፍጻሜን ያበጅለታል፡፡

ሦስተኛው፡- ኃጢአት በሩካቤ ግንኙነት በተፈጠሩ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ የወደቀ ነው፤ በክሎኒንግ ይህ ውጤት ከአንድ ሰው የዳበረ ሴል በመውሰድ አስመስሎ ማስገኘት ስለሆነ፣ ስለ ኃጢአት ያለው ምልከታ የጠፋ ነው፡፡

አራተኛው፡- እግዚአብሔር በኃጢአት ለጠፋው የሰው ልጅ መድኃኒት የሆነውን ክርስቶስን አዘጋጀ፣ እርሱም ለኃጢአተኞች ሞተ፣ እንዲህ በሞቱ የተገኘው የእርቅ የሥራ ውጤት በክሎኒንግ ዘዴ ሊፈጠሩ ላሉት የአንድ ወገን «ሰው ተብዬዎች» ውጤ ታማነቱን ያዛባል፡፡

* * *

ይህ የክሎኒንግ ዜና ወደ ሰው ጆሮ በገባ ጊዜ የአስመስሎ የማስገኘት ሙከራዎች በሚካሄድባቸው አገራት የሚኖሩ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የጀርመንና የመሰል አገሮች ሕዝቦች ተቃወሙ፤ በውጤቱም ምርምሩ በጀርመን እንዳይቀጥል ጊዜያዊ እገዳን አስከተለ፤ በአሜሪካም ፕሬዚዳንት ክሊንተን መክረው ዘክረው አስመስሎ መፍጠር ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በከፊል እንዲካሄድ ፈቀዱ፤ የሰውን ልጅ አስመስሎ ማስገኘትን ግን አገዱ፡፡

ብዙዎች ይህንን የክሊንተንን ውሳኔ «ፈጥኖ የሚሻር፣ ውሎ የማያድር ደንብ» ብለውታል፤ በአንድ ወቅት ፅንስን «በቱስት ቲዩብ ወይም በብልቃጥ» በማኖር የማስገኘት ሥራ ገሃድ በሆነ ጊዜ ተቃውሞ ሆነ፤ ጥናቱን ተግባራዊ ሊያደርግ የተነሣው የአውስትራሊያ መንግሥትም ከተቃውሞው የተነሣ በአገሩ

እንዳይፈጸም አገደ፤ ሳይንቲስቶቹ ግን ከአውስትራሊያ ወጥተው በሲንጋፖር ፈጸሙት፤ የክሎኒንግ ጠበብቶችም ልክ እንዲሁ ያሰቡትን ይፈጽሙ ይሆናል። ለዚህም ሰውን የማስገኘት ውጤትን በተከታዮች ሦስት ወራት ውስጥ ለማየት ዐቅጃለሁ የሚሉት ዶ/ር ሪቻርድ ሲድ የእውቀት ባለቤቶች ነን፣ የእግዚአብሔርን ያህል የሚመጥን ኃይል አለን፣ ሰውን አስመስሎ በማስገኘት ውጤታችን ከእግዚአብሔር ጋር መስተካከላችን ገሀድ ይሆናል፤ እኛም ሥራው በዚህ ቢታገድ በሌላ አገር ከማድረግ አንመለስም በማለት ነበር በመገናኛ ብዙኀን ያሳወቁት።

ለማንኛውም ፍርሃቱን ያጎላውን የክሎኒንግ ሙከራዎች በከፊል ልዘርዝር።

የሙከራ ዓመት	የተመራመሩት ሳይንቲስቶች	የተሞከ ረባቸው ፍጡራን	የአገኛኘቱ ዘዴ	የተገኘው ውጤት
1950	ቢሪግስና ኪንግ	እንቁራሪት	የኒውክለስ ዝውውር ከፅንስ (Embryo) ወደ እንቁላል	እንቁሪ ተገኘ፣ ሳያድግ ሞተ
1960	ጆንቢ ጎርደን	እንቁራሪት	የኒውክለስ ዝውውር ከቆዳ፣ ከጉበት፣ ከኩላሊት፣ ወደ እንቁላል	እንቁሪ ተገኘ፣ ሳያድግ ሞተ
1970	ኢመንስ	ቢራቢሮ	የኒውክለስ ዝውውር ከፅንስ ወደ እንቁላል	ዕጭ ተገኘ፣ ሳያድግ ሞተ
1984	ሚክግራንዝ እና ሶልተር	አይጠ መንጥ	የኒውክለስ ዝውውር ከፅንስ ወደ እንቁላል	ደቃቅ አይጠመንጮች ተገኙ፣ ግን ብዙ ሳይቆዩ ሞቱ
ጥቅምት 1993	ሄል እና ስቲልማን	ሰው	በሰው ሠራሽ ዘዴ ፅንስ ምስስል መንትያን እንዲያስገኝ ከሁለት የተከፈለ	የተጣበቀና ቅርጽ የለሽ ነገር ተገኘ
የካቲት 1996	በስኮትላንድ ተቋም በቡድን	በግ	የኒውክለስ ዝውውር ከፅንስ ወደ እንቁላል	ሜጋንና ሞርጋን የተባሉ ሁለት በጎች ተገኙ
ጥር 1997	በስኮትላንድ ተቋም በቡድን	በግ	የኒውክለስ ዝውውር ከበግ የተ ወሰደ ሴል ወደ እንቁላል	ዶሊ በጤናማ ሁኔታ ተገኘች
የካቲት 1997	ዶንጮልፍ እና ኦሪጋን (በአሜሪካ)	ዝንጀሮ	የኒውክለስ ዝውውር ከፅንስ ወደ እንቁላል	ሁለት ዝንጀሮ ዎች በጤናማ ሁኔታ ተገኙ

ዶሊ መስላ ከተገኘችበት በግ የዳበረ ሴል ተወስዶ ኒውክለሱ ከተ ወገደበት እንቁላል ጋር ተገናኝቶ እርባታውን ሲጨርስ ያለ ወንዱ ህዋስ (Sperm) በግ ተገኘ። ይህ ስኬታማነት በሰውም ላይ ሲካሄድ የወንዱ ሕዋስ ለእርባታው አይፈለግም። መስሎ ሊገኝ የተገባውን «ሰው» የዳበረ ሴል በመውሰዱ ብቻ እንደ በጊቱ ሰው ሊገኝ ይችላል። ይህ እንግዲህ እየተሞከረ ወይም ሊሞከር ያለው ቲዎሪ ነው።

* * *

እግዚአብሔር ግን ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው (ዘፍጥ. 5፡1-2)፤ በአፈጣጠሩም በመልኩና በምሳሌው አደረገ (ዘፍጥ. 1፡26)። ይህም ወንድና ሴት አድርጎ መፍጠሩን ያስገነዝባል። ዓላማውም ተዋልደው ምድርን ይሞሏት ዘንድ ነው (ዘፍጥ. 1፡27-28)። ከእነዚህ ጥቅሶች መለኮታዊ የሆነውን ጽኑ እውነት እንረዳለን። ያም እግዚአብሔር ቤተሰብን መሠረተ፣ ልጆችንም አስገኘ፤ ይህም ከመነሻው አዳምና ሔዋን የበኩር ልጃቸውን ቃየልን በማግኘት አረጋገጡ (ዘፍጥ. 4፡1) እንደሚል፣ «አዳም ከሚስቱ ከሔዋን ጋር ግንኙነት አደረገ፤ እርሷም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች» [አዲስ ትርጉም (የታረመ) 1997]። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ቤተሰብን፣ የወላጅና የልጅ ግንኙነትን፣ ፍቅርን፣ ኅብረትን፣ የማንነት መገኛን፣ ወዘተ. . . ሁሉ የወንድ ሕዋስ (Sperm) ከሴት እንቁላል ጋር በመገናኘት በሚፈጥረው በሰው ልጅ በኩል አደረገው፤ በዚህም ትውልድ እያለፈ ትውልድ ተተካ፤ ይተካልም።

የእግዚአብሔር ቃል ሰውን ከሌሎች እንደለየውም ሲገልጽ፣ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታትን ሁሉ ያለ እርሱ እስትንፋስ አስገኛቸው፤ «ሰውን ከዐፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም ሕይወትን የሚሰጥ እስትንፋስ «አፍ» አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ፍጡር ሆነ» (ዘፍጥ. 2፡7)። ይህ ብቻ አይደለም፣ እያንዳንዱ ሰው መንፈስ፣ ነፍስ፣ ሥጋ አለው (1ኛ ተሰ. 5፡23፤ ዕብ. 4፡12-13)። እንስሳትና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ግን የዚህ ክብር ባለቤቶች አይደሉም። ከዚህ የተነሣ የክሎኒንግ መዘዝ የሚያስከትለው ውስብስብ ጣጣ ከሌሎች ፍጥረታት ይልቅ ለሰው ልጅ የከበደ ነው።

በአንድ ወቅት ስለ መጪው ዘመን ስጋቱን አልበርት አንስታይን ሲናገር፣ «ዓለም አግባብነት በጎደላቸው ሳይንሳዊ ውጤቶች ልትጠፋ ትችላለች» አለ። የዛሬውን ሰውን የአስመስሎ የማስገኘት ክሎኒንግ መተንበዩ ይሆን?

በያዝነውም ዓመት ደግሞ ዶ/ር ሲ. ሲ. ፖዳህም፣ «የሰውን ልጅ በክሎኒንግ ዘዴ አስመስሎ መፍጠር አግባብ አይደለም፤ እርግጥ ሥጋዊ ቁመና ያለው «ሰው መሳይ» ተንቀሳቃሽ ይገኝ ይሆናል፣ ግና እውቀት፣ ስሜት፣ ፈቃድ፣ ባሕሪ፣ ፀባይ፣ የመንፈሳዊ የሕይወት አቅጣጫም ሆነ በድርጊቱ የተጠያቂነትን አእምሮ የማያስገኝለት የክሎኒንግ አካሄድ ግን አይሆኑ መሆን ነው» በማለት ሰግተዋል።

የኖቤል ተሸላሚው ጆሴፍ ሮትብልትም፣ «ሰው በሕይወት ይጫወታል፤ የክሎኒንግ የሳይንስ ውጤት ስብእናን በማዋረድ ለዓለም አቀፍ ጥፋት ምክንያት ይሆናል» በማለት አስጠንቅቀዋል።

የቫቲካን መንፈሳዊ መምህራንም፣ «ክሎኒንግ የጋብቻ ክቡርነትን ያቃልላል፣ የሰዎችን እኩልነት ይጻረራል፣ ሕፃን ሁሉ አባት እናት ይኖሩት ዘንድ መብቱ መሆኑን ይቃወማል፣ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ መሆንን ይሸሻል» በማለት አውግዘዋል።

እንግዲህ ለሔዋን ያለመታዘዝ መንሥዔ በዲያብሎስ የቀረበላት አስጎምጂ መሰል የሆነ ፈተና እንደ ነበረ አይዘነጋም፡- «እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑና ደጉን ከክፉ ለይታችሁ እንደምታወቁ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ነው . . .» አላት (ዘፍጥ. 3፡4-5)። እርሷም አመነች፤ ታዘዘችም። ዛሬም የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ቃል በመጣስ ራሱ ፈጣሪ መሆንን የተመኘ ይመስላል - በክሎኒንግ።

እግዚአብሔር ግን አለ... «አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና . . .» (ገላ. 6፡7፤ የ1954 እትም)።

መረጃ ጽሑፎች

1. አዲስ ዘመን፣ «***ክሎኒንግ - አበረታች ወይስ አስፈሪ ፈጠራ?***» ጥቅምት 26 ቀን 1990 ዓ.ም
2. Facts and Faith, To Clone or Not to Clone by Hugn Foss.

3. Light of Life, Cloning Glory, June 97.
4. Light of Life. Folly of Dolly by P. Abraham.
5. Will Dolly in the Clones by Elizabeth Penisi.
6. Advantage of Knowing Nature's Secrets by Milke Fzunz bller.
7. Financial Times, "Outcry as Doctor says He will Create Human Clone" Jan. 8,1998.
8. The Economist, Fear of Cloning. January 17th 1998.

ተጨማሪ ማብራሪያ

በራሂ፡- በሐብለ በራሂ ላይ የሚገኝ የአንድን ዕፅ ወይም እንስሳ ወይም ሕዋስ ባሕርይ የሚወስን ትንሽ የሐብለ በራሂ ክፍል ነው።

እንቁሪ፡- የእንቁራሪትና የጉርጥ እጭ ኖሮት ግን የፊት እግሮቹ ከመውጣታቸው በፊት ያለ ደረጃ ነው።

ፅንስ፡- የሚለው ቃል (Embryo) **የሚለውን ይገልጻል፤ በፍቺውም በመጀመሪያዎቹ የእድገት ደረጃዎች ላይ ያለ እንጭጭ እንስሳ በተለይም ከእንቁላል ከመፈልፈሉና የቅርጽ ለውጥ ከመካሄዱ በፊት ያለ ደረጃ ነው።**

ዝውውር ወደ እንቁላል ሴል፡- ከእንቁላል ያለው ኒውክለስ ሙሉ ለሙሉ ሊወገድ ነው።

(የሠንጠረዡ ዓመተ ምሕረቶች አቆጣጠር እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር ነው።)

ጸሎተ ገብረሐና

የአለቃ ገብረሐና የሰርክ ጸሎት፤ «ጥቅም የማያስገኝ ሹመትና ያለድካም የተገኘ ዝና አትስጠኝ» የሚል ነበር። የዚህን አባባል መንሥኤ የሚያጠናው ጎበዝ፤ ገብረሃና «ለምን ይህን ልመና ለእግዚሔራቸው ቅድሚያ ሰጡ» አለ። ለዚህ ያገኘው «የይባላል» የቅብብሎሽ መልስ በዘመናቸው ሹመት በሹመት ሆነው ግን

የሚበሉት አጥተው በረሃብ ከሞቱት ወዳጃቸው የተነሣ መሆኑን ተረዳ፣ ተሿሚው ተሾሙ እንጂ ከሹመቱ ጋር ርስት አልተሰጣቸውም፤ ገንዘብ አልተለገሣቸውም። ዘላቂ ወርሐዊ ቀለብም አልተሰፈረላቸውም፤ ብቻ እንደ «ጎልያድ» የሚያስፈራና የሚያስደገድግ ሹመት ይዘው የቀደመ ጥሪታቸውን እየበሉ ቁጭ አሉ፤ ጨረሱትም። እናም ተቸገርኩ እንዳይሉ ሹመታቸው ከላባ መቅለሉን የሚረዳላቸው አላገኙም። ብቻ ሁሌ ተጣጥበው ይወጣሉ፣ ከየሰውም ገበናቸውን የማይሸፍን የከበሬታ ሰላምታ ሰብስበው ባዶአቸውን ይመለሳሉ። ይህ ምልልስ «ተራ ሥራ» የሚሉትን እንኳ አላሠራ ብሎ ቀፈደዳቸው፤ በውጤቱም «ያለ ቀናቸው» አብቃቃቸው። አለቃም ከዚህ ስሚ በኋላ በረከት አስከትሎ ያልመጣውን ሹመት ጠሉት፣ ፈሩትም፣ ወደ እርሳቸውም ሌጣውን እንዳይመጣ የልመና ጥሪያቸውን ለእግዜር ያስደምጡ ጀመር።

«ያለ ድካም የተገኘን ዝና አትስጠኝ» ለማለት ያበቃቸው ገጠመኝ ግን ለየት ይላል፤ ሰውየው ጀግና ነው፤ የዚህን የጀግንነት ዝናውን በገዛ አፉ ሁሉ ያወራል፤ እርሱ ሲያወራ ሕዝቡ ሲያስተጋባ ገድሉ ለዓለሙ ሁሉ ተሰማ፤ አለቃም አመኑበት፤ ባመኑበት በዓመቱ የጦርነት ወሬ በዛ፤ ሳይከራርምም ነጋሪት ተጎሰመ፣ በሕዝቡም ዘንድ ግርግር ሆኖ ፍርሃት ነገሠ። ፍርሃት ይኑር እንጂ ተስፋ ከጎን አለ የዝነኛው ሰው ጀግንነት፤ እንዳሉትም ጀግናው ቀድሞ ወጣ፣ ተከተሉትም፤ ተኩስም ተሰማ፤ ጦርነትም ሆነ። ጀግናው ግን ቆሞ ቀረ፤ ጅብራ ሆኖ በቆመበት ያልሸሸ ብቸኛ ሰው ተገኝቷልና «ለምን እንዳልሸሸ ተጠየቀ፣ ለጥያቄው መልስ አልሰጠም፤ የእርሱ ቀዳሚ ጥያቄ፣ «ካዘናችሁልኝ ሱሪዬን ቀይሩልኝ» የሚል ነበር። ሰውዬው በድንጋጤ፣ ስቶ ነበር፣ በክፉ ሽታ ተሞልቶ ሁለንተናው ከላይ እስከ ታች በክቶ ነበር፤ ርሶ።

ከዚያ ሰው ወዲህ ነው አሉ የአለቃ ጸሎት፣ «ያለ ድካም የተገኘ ዝና አትስጠኝ» የሆነው። እናም ከያኔ ጀምሮ ነው፣ «ሳይገድሉ ጎፈሬ፣ ሳያጣሩ ወሬ» የተሰኘው ብሂል የተጀመረው። ገድል ገድል የሚሆነው ዝናም ዝና ሆኖ ክብር የሚሆነው በእውነት ላይ የተመሠረተ ሲሆንና በእሳት ተፈትኖ ሲያልፍ ብቻ ነው።

ከአለቃ ዘወር ልበልና ውጤታማ የሆነውንና በእውነት ላይ የቆመውን ከረምረም ያለውን ዝና ደግሞ ልንገራችሁ። ሩዋጨን አበበ ቢቂላን፤ አበበ ኢትዮጵያን ያገነነ ብርቱ ሰው ነው፤ ሮጦ ዓለምን አሸነፈ። ያውም ሁለት ጊዜ፤ ይህ የድል ሰው ዛሬ በሕይወት የለም፤ የማሸነፉ ታሪክ ግን አለ፤ ራጮች ዛሬም ይሮጣሉ፡- ኢትዮጵያውያን ያሸንፋሉ፤ ይሸነፋሉም። በድግግም በተ ሸነፉበት ወቅት ባለፈው ዝና ይጽናናሉ፤ የኋልዮሽ ታሪክን ጠቅሰው ይበረታታሉ፤ «እኛ በባዶ እግራችን ሮጠን አሸንፈናል፤ የአቤ ድል እኮ ለዘለዓለም አይረሳም» ይላሉ። በዚህ ይበረታታሉ፣ ሽምግለውም ራሳቸውን ይደልላሉ፤ ግን. . .ግን. . . እንዲህ ከሚጽናኑ ቢያለቅሱ አይሻልም፣ ቢጸጸቱ. . . ጥሎን የሄደ ድል ለዛሬ አይሆንም። ይልቅ ደካማ ጎንን አርሞ ስሕተትን አንጥሮ አውጥቶ ለመሻሻል ለማሸነፍ መዘጋጀቱ ብልህነት ነው።»

እንግዲህ አሳቤን በመጠቅለል በየአንቀጹ ያኖርኩትን ነጥብ ልሰበስብ። ለሞት የሚያበቃን የግብዝነት ሹመት ይዞ ክርስቲያን ሳይሆን ክርስቲያን ተብሎ መጠራት፤ አልያም ባልተፈተሸ ዝና ታምኖ መቀመጥም ሆነ ያለፈን ዝና እንደ ዛሬ ቆጥሮ መዝናናት ዋጋ ቢስ ነው፤ ዋጋ የሚያስገኘው ውጤቱ በእጁ ሲያዝ ብቻ ነው፤ ፍሬው ሲጎመራ።

ይህ ውጤት ደግሞ የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የዘወትር ቋንቋ ነው፤ ፍሬያማነት ውጤታማነት አሌ የማይሰኝ የእግዚአብሔ ር ፈቃድ ነው። የምእመናን የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት በጅምላ ሳይሆን በተናጠል ተፈትኖ ሲያመረቃ፣ የወንጌል ዘርን የመዝራት ኃላፊነትም በጅምላ ብቻ ሳይሆን በተናጥል ተወጥቶ የቁጥር መጠን ሲጨምር፣ ይህ ውጤት ነው።

ግና እንዲሁ «የገሃነም ደጆች የማይቋቋሟትን የቤተ ክርስቲያን ጅማሬን መጥምቁ ዮሐንስ አደረጀው» ማለቱ፣ ዝናችን ከሰማየ ሰማይ ወዲህ የደረሰ ነው ብሎ ማግነኑም ሆነ፤ የቀደሙትን የክርስቲያኖች ገድል አንሥቶ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አልቀዋል ብሎ የዛሬን ውጤት-አልባነት በሁለት ሺው የደም ታሪክ ቢዘክሩት ለቤተ ክርስቲያን የዕለት ሲሳይ አይሆንም። ይህ በትግሉ ሜዳ ላይ መቀየሪያ ሱሪ ሊያስጠልቅ ስለሚያስችል ትክክለኛውን ውጤ

ታማኝት ማጤንና መመዘን ግድ ነው። ለምን? ቢሉ ሮጠው የሚያሸንፉ አበበ ቢቂላዎች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና።

«ለሚመለከተው መሪ ሁሉ»

የዶ/ር ቢንያሚን ዮሴፍ ትምህርት ነበር ለነገሩ ትኩረት እንድሰጥ ያስገደደኝ፤ በመማር ላይ የነበርኩት ኮርስ አመራር (Leadership) ይሰኛል። ከአስተማሪዬ ብርታት የተነሣ ወይም ዛሬ የብዙ ቤተ ክርስቲያናት መሪዎች ያላቸውን ችግር ከመመልከት ብቻ ትምህርቱን ወደድኩት። «በሽታውን የደበቀ (ያላወቀ) መድኃኒት አያገኝም (የለውም)» የሚለው ተረት ከእኛ ዘንድ እንዲወገድ በማሰብ፤ «ለሚመለከተው መሪ ሁሉ» ብዬ ልጽፍ ተነሣሣሁ።

የዚህ ጽሑፍ መንሥኤ አሁንም መምህሬ ነው። ጥናታዊ ጽሑፍ እንድናቀርብ አዘዘን፤ የእኔ የጽሑፍ ርእስ፣ «የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የተለመዱ ችግሮች» (Common Leadership Problems in Evangelical Churches) የሚል ነበር። ለጽሑፌ የሚያስፈልገኝን መረጃ ለመሰብሰብ ከቤተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር መገናኘት፣ ምእመናንን ማነጋገር፣ «የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የመሪዎች ኮንፈረንስ» ላይ ተገኝቶ በውይይት ጊዜያት የተነሡትን የመሪዎች ችግር ማጤንና በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተጻፉ መጻሕፍትን በመመልከት «የጋራ ችግሮቻችን ምን ምን እንደ ሆኑ» ለመጠቆም ፈለግኩኝ። አባቶችም እንዳሉት፣ «ታመን ከመማቀቃችን በፊት አስቀድመን እንድንጠነቀቅ» መፍትሔም በእግ ረ መንገዴ ጠቀስኩኝ፤ ሁሉንም ባይሆን ዋና ዋናውን።

«አሥር አባረው አንድ ካልያዙት» የመሪ ዓይነቶች ልጀምራ፤ ሁሉን መሆን ፈልገዋል፤ ሆነውማል። ኘሮግራም ይመራሉ፣ ይሰበስባሉ፣ ያስተምራሉ፣ ይጎበኛሉ፣ ያማክራሉ፣ ያስተዳድራሉ፣ የሠርግና የቀብር ሥርዓት ያስፈጽማሉ፣ ወዘተ. . .። እነዚህ ከእንግዲህ በራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከወኑ ናቸው።

ወጣ ብለው ደግሞ በሁለትና ሦስት ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ውስጥ የቦርድ አባል ወይም ሰብሳቢ ይሆናሉ፤ የሆኑም አሉ። ግና እነዚህን ሁሉ ጀምረዋቸዋል እንጂ ዳር አላደረሷቸውም፤ ሁሉም ውስጥ ባክነዋልና ግብ አልመቱም። ያገለገሉ መሰላቸው እንጂ ወደ ማንም አልደረሱም፤ ሁሉን ነካኩ እንጂ አልጨረሱም። ከዚህም የተነሣ አሥሩን በአንዱ አባሮ አንዱንም እንዳልያዘው እረኛ ተመሰሉ፤ እንዲህ መሳይ በርካታ መሪዎች አሉን።

ከላይ ላወሳኋቸው ችግሮች ሁለት ሦስት ምክንያት ቀርበውለታል። <u>አንዱ</u>፣ ያለ እነርሱ ቤተ ክርስቲያን ህልውና እንደሌላት የሚቆጥሩ መሆናቸው ነው። አንዲት ሰንበት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ባይገኙ ሁሉ ነገር ይመሰቃቀላል በሚል ስጋት ይዋጣሉ። ይህን ስጋት ለመቀነስ ሲሉም ነው ነገራትን ሁሉ በእነርሱ ዙሪያ የሚያሰባስቡት።

<u>ሁለተኛው ምክንያት</u> የራስን ድርሻ በትክክል አለማወቅ ነው። በመሪነት ቦታ ያሉ «በሁሉም ውስጥ አለንበት» ማለት አይችሉም። በውሱን (Specific) ኃላፊነት ውስጥ ብቻ ራሳቸውን ማስገዛትና ለዚያም ኃላፊነት ተጠያቂ መሆን አለባቸው።

<u>ሦስተኛው ምክንያት</u>፣ የአገልግሎት ዘመናቸውን (ዕድሜያቸውን) የሚያሳጥረውን ነገር አለማስተዋል ነው። ማገልግል፣ ማገልገል፣. . . ብቻ የሚል ገናና አሳብ በብዙ መሪዎች ዘንድ ተንሠራፍቷል። ይህ ደግሞ እነርሱ ሲያልፉ ወይም ሲያቆሙ «ማን ተተኪ አለኝን» ከቁጥር አያስገባም። ዕረፍት የሚባል በእነኚህ ዘንድ ስለሌለ የጤና ቀውስ፣ የአዕምሮ አለመረጋጋትና የስሜት መ ረበሽ ችግር ይገጥማቸዋል፤ የገጠማቸውም አሉ። ከሳምንት፤ ከወርና ከዓመት ላይ የተወሰነ ቀን (ቀናት) ማረፍ ግዴታ ነው- መለኮታዊም ፈቃድ ነው።

ቀደም ሲል ለጠቃቀስኳቸው ችግሮች አንዱ ዐቢይ መፍትሔ፤ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት የማያሻማና ግልጽ ዓላማ ይዞ መነሣት ነው። ይህም ዓላማ ውሱን ግብ (Specific goal) እንዲኖረው መወጠንና ዓላማውን ለውጤት ለማብቃት የሥራ ቅደም ተከተል መንደፍ፣ በጊዜ ውስጥ ለታለመው ግብ መብቃት አሌ አይሰኝም ይሆናልና።

በየትምህርት ቤቶች ሕንፃ ላይ ተሸልሞ በተጻፈው አነጋገር ልቀጥል፤ «ካልተሳፈሩበት ቶሎ ተሸቀዳድሞ፣ ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ» - ተማሪዎች በሚያልፈው ጊዜ እንዲጠቀሙበት አሳሳቢ አባባል ነው። አባባሉ በቤተ ክርስቲያንም ሁሉንም ምእመን አስታዋሽ ሊሆን ይገባል፤ ይልቁኑ ለመሪዎቹ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ወቅት ላይ በሉቃስ 13:31-33፣ ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋልና ሸሽ የሚል መልእክትን ፈሪሳውያን ይዘውለት መጡ፤ እርሱ ግን «ዛሬና ነገ አጋንንትን አስወጣለሁ፤ በሽተኞችን እፈውሳለሁ፤ በሦስተኛ ቀንም ሥራዬን እጨርሳለሁ» (ቀ.አ.) አላቸው። በጊዜ ውስጥ ሊፈጽማቸው ያቀዳቸው ሥራዎች ነበሩትና ነው፤ ይህን ያለው እንዳለውም ያቀደውን በጊዜ ውስጥ አደረገ። እንግዲያስ ከመሪዎች ሁሉ የሚጠበቀው ይኸው ነው። ደግሞም፤ «ይህ ዘመን ክፉ ስለሆነ በማናቸውም አጋጣሚ ጊዜ ተጠቀሙ» (ኤፌ. 5:16፣ ቀ.አ.) ተብሏል። እውነታው ይህ ይሁን እንጂ፣ የብዙ መሪዎች የጊዜ አጠቃቀም ቅድም ከተባለው ነገር ጋር ይቃረናል። ለዚህም ሁለትና ሦስት ምክንያቶች አሉ።

<u>አንደኛው</u>፣ በእጃችን ላይ የተገኘው ዛሬን በመዘንጋት ከነገ ጀምሮ ተግባራዊ እናደርጋለን፣ አባባል መስፋትና መንሰራፋት ነው። በርካታ መሪዎች ውጥናቸው ግብ ሳይመታ ሲቀር (ጊዜን ሳይጠቀሙ) እንግዲህ ይህ ዓመት አልፏል፣ በመጪው ዓመት ግን ይህንና ያን እናደርጋለን፣ ጌታም ዳግም ይጎበኘናል ይላሉ። ነገር ግን ያም ቀን፣ ያም ወር፣ ያም ዓመት መጥቶ ሲያልፍና ደግመው ደጋግመው እናደርጋለን ቢሉ፣ «በጊዜ የማይጠቀም ራሱን መምራት የማይችል ሰው ነው» የሚለው አባባል ይፈጸምብናል። «ነገ የሚያመጣውን አታውቅምና. . .» ዛሬ ወይም አሁን የተባለበትም ምክንያት ለዚሁ ነው።

<u>ሁለተኛው</u>፣ ትልም ተግባርን (ሥራን) ለሰዎች ባለማከፋፈል ምክንያት የሚከሠት የጊዜ ብክነት ነው። አንድ ዕቅድን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከግብ የማድረሻው ስልት ሥራ ለሰዎች ማከፋፈል ነው። መሪዎች ሰዎችን ለሥራ አሳታፊዎች መሆን አለባቸው።

ሦስተኛው፣ ረብ (ጥቅም) ያለውን ሥራና አላስፈላጊውን ያለመለየት ችግር ነው። በአጭርና በረዥም ጊዜ ውስጥ ዋናና

መለስተኛ ወይም ከፍተኛና ዝቅተኛ ተግባሮችን መንደፍና በንድፉም መሠረት ውጥኑን መተግበር ተገቢ ሆኖ ሳለ፣ በአብዛኛው ግብታውያን ሆነናል። ትልቁን ከትንሹ መለየት እጅግ አስፈላጊ ነው። ቀዳማዊውንና ተከታዩን ማወቅ ያስችለናልና።

«የአለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» ዓይነት መሪዎችን ሥራ ደግሞ ከገባኝና ካየሁት በመነሣት ልቀጥል፤ ሮሜ 12:8 እንደሚገባ ማስተዳደር አስፈላጊ መሆኑን ሲያስገነዝብ፣ «. . . በትጋት እናስተዳድር» ይላል (ቀ.አ.)። ግን ትጉሕ አስተዳዳሪነት በአብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ታይቷል ወይ? አልታየም ነው መልሱ፤ ለአንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ጥያቄ ቀርቦለት በሰጠው ምላሽ ልዝለቅበት። «በየእሑድ አምልኮ ቤተ ክርስቲያን ትገኛለህ?» . . . «አልገኝም»። ለምን? «. . . ኘሮግራሙ ድግግሞሽ ይበዛበታል፣ አዲስ ነገር አላገኝም፣ ከዕቅዴ ውጪ ያልጠበቅኩትን ገንዘብ ያስወጡኛል፣ በቤተ ክርስቲያኔ ተሳታፊ አልተደረግኩም፣ የአምልኮው ጊዜ ሥርዓት ያጣ ይሆንብኛል፣ ወዘተ. . .» መልሶቹ ነበሩ። እውነት አለው። መራቅ አቅቷቸው፣ ግን ሁሉን ታግሠው የተቀመጡትም ቢሆን እንደ ሰውየው መልሳቸው ተቀራራቢ ነው። የዚህ ምክንያቱ ብዙ ነው። ዐቢዩ ችግር ስሜት ብቻ የሚያደርሱ ኘሮግራሞችን በተደጋጋሚ ማዘጋጀትና ምእመናን ዘላቂና አንድ ወጥ (Consistance) ክርስቲያናዊ አመለካከትና ጠባይ እንዲያፈሩ የሚያግዝ ትምህርታዊ ኘሮግራም አለማዘጋጀት ነው። በየጊዜው የሚዘጋጁ ኮንፈረንሶች ቋሚ ለውጥ እንደማያመጡ የተገነዘቡ መሪዎች ስንት እንደ ሆኑ ባላውቅም፣ ጊዜያዊ ኘሮግራሞች ጊዜያዊ ለውጥ ብቻ እንዳላቸው ሊታወቅ ይገባል።

መሪዎች በሳምንት ወይም በአሥራ አምስት ቀን እየተሰበሰቡ ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው ጉዳይ መነጋገራቸው አልቀረም፤ አጀንዳዎቻቸው ግን ብዙውን ጊዜ ተቀራራቢ ወይም አንድ ዓይነት ናቸው፤ ለተከታዩ ሳምንት ከመካከላቸው የመልእክት ጊዜውን ማን ያዘ፣ ይህ አጀንዳ ለቀጣዩ የስብሰባ ቀን ይተላለፍ፣ . . .ሁሉ ንግግርና ውሳኔ ነው። «እንዴት ግን ወደ ዐቀድነው ግብ እንደርሳለን?» የተረሳ ጉዳይ ነው። የእነዚህን ዓይነት መሪዎች አጀንዳ ለማሻሻል

ወይም ለመቀየር መፍትሔው አንድ ነው፤ ጌታ እንዳለ «ማርታ፣ ማርታ፣ አንቺ በብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፤ ትታወኪያለሽም፤ ነገር ግን ተፈላጊው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ማርያም የሚሻለውን ነገር መርጣለች፤ እርሱንም ከእርስዋ የሚወስድባት ማንም የለም» (ሉቃስ 10፡41-42፣ ቀ.አ.) የሚለውን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ለቀዳሚውና ለዋነኛው ነገር ትኩረት መስጠት፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደራዊ ቅርጽ በሚገባ ማደራጀትና በትጋት መምራት፣ ማኅበረ ምእመናኑን መመገብ፣ መጠበቅና ማስተሳሰር፣ እንዲሁም በክርስቶሳዊ ምሳሌነት በአግባቡ መምራት ከብዙ ተፈላጊዎቹ መካከል ዋንኞዎቹ ናቸው።

መቼም የማነሣቸው ችግሮች አንዱ በአንዱ ውስጥ እየተደበቀ መነሣቱ አልቀረም፤ ተቀራራቢ ችግር ፈጥሬ ከሆነ ይቅርታ እጠይቃለሁ፣ ተጠላልፎብኝ ነውና። አሁንም «የራሷ እያረረባት የጎረቤት አማሰለች» ዓይነት መሪዎችን አብረን እንቃኝ፤ የያዙትን የመሪነት ስፍራ ቀደም ብዬ እንደ ገለጽኩት መልቀቅ አይፈልጉም፣ አያስቡበትምም፤ እንደ ሙሴ ተተኪ የማዘጋጀት ራእይ የላቸውም፤ ብቻ እንመራለን፣ ዛሬም እኛው ነን ይላሉ። ግን ለቤተ ክርስቲያናቸው መንጋ አይጠነቀቁም። መንጋውን የሚመግቡት የላቸውም፣ ቢኖራቸውም ልብ አይሞላም። ከዚህም የተነሣ መንጋው ተንከራታች ሆኖ ይዞራል፤ የሚጥመውን ወይም የመሰለውን ምግብ እስኪያገኝ ድረስ። መቼም በየከተሞቻችን ብዙ ምግብ ቤቶች እንዳሉ ታውቁ የለ። ተመጋቢው ሰው ጥሩ የሚለውን ምግብ እስኪያገኝ ድረስ ምግብ ቤቶችን መጎብኘቱ አይቀርም። ልክ እንዲሁ፣ በቤታቸው የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ ምግብ የተነፈጉም «ቅልውጥ» ይጀምራሉ። በየሄዱበት የተገኘውን መመገብ ምን ያህል የአመለካከት (የእምነት) ልዩነት እንደሚያመጣ መገመት አያዳግትም። ለአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «የአንድ ልብ» አምልኮና አገልግሎት መጥፋት ትልቁ ምክንያት ይሄው ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የበላይ ባለሥልጣንነት (Absolute Authority) ቸል በማለት፤ ከእርሱ በመቀነስ ወይም በመጨመር፣ በማሻሻል ወይም ያለ ቃሉ መሪነት በማስተማር ብዙ ተንከራታች ምእመናንን የሚጎዱ ሰባኪዎችና

አስተማሪዎች እንዳሉ መዘንጋት ወይም መካድ አይገባም። ውጥንቅጡ የወጣ መረዳትና ልምምድ መያዝ የራስንም ሆነ የሌላውን ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ እምነት እንደሚያናጋ መታወቅ አለበት።

አያሌ ቤተ ክርስቲያኖች የገጠማቸው ችግር (ግንጥልጥሎሽ) ይህ የመረዳት ወይም የልምምድ ቀውስ መሆኑን አሌ የሚል አይኖርም፣ ዋሽተሃል የሚል ካለ ከእኔ ጋር ሳይሆን ካቀረብኩት እውነታ ጋር መካካድን መርጧል።

ለዚህ ውድቀት በውል የሚጠቀሱ ምክንያቶች አሉ። <u>የመጀመሪያው</u>፣ እግዚአብሔር እንድናገለግላቸውና እንድንመራቸው የሰጠንን ሕዝብ ተግቶ አለመመገብ፣ አለመጠበቅና አለመንከባከብ ነው። ብዙ መሪዎች አገልጋይ ሳይሆን፣ አለቃ መሆንን ነው የሚፈልጉት። ከዚህ ይልቅ መሪዎች እንደ ግሩም የምግብ ባለሙያ ሴት ሊሆኑ ይገባል። ይህ ደግሞ አለቅነትን ሳይሆን፣ አገልጋይነትን ይጠይቃል። <u>ሌላው ውድቀት</u> የአርአያዊነት መጥፋት ነው። ክርስቶሳዊ ምሳሌነት የመሪዎች ትልቁ ባሕርይ መሆን አለበት። ያለበለዚያ ተተኪም ሆነ ተከታይ አይኖርም።

መገምገምንና መገምገምን የማይወዱ መሪዎች መብዛት ሌላው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችግር ነው። እግዚአብሔር በስድስት ቀናት የፈጠራቸውን ፍጥረታት ከተመለከተ በኋላ «ሁሉም መልካም ነበር» አለ። ሥራውን ወደ ኋላ ተመልሶ ተመለከተ፤ ገመገመ። ሐዋርያው ጳውሎስ እንኳን «በከንቱ ሮጬ እንዳይሆን» እናንተ የቤተ ክርስቲያን አዕማዳን ነገሬን ተመልከቱ ያለውን ማጤን አስፈላጊ ነው። ዕቅዶች ግብ መድረሳቸውንና አለመድረሳቸውን መመዘን የግድ ያሻል። አልያ ከንቱነትን ማጨድ ነው። በበርካታ መሪዎች ዘንድ የሚታይ አስተዛዛቢ ነገር መገምገምን - መገምገምን መንቀፍና መጥላት መከሠቱ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ያህል አባላት እንዳሏትና ኑሮአቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ አይጥሩም። የገቢ-ወጪያቸው ሥርዓት ደንብ-አልባ ሲሆን ግድ የላቸውም። ብቻ ነገር ሁሉ በነሲብ ይነገራል፤ «ሁሌ ጌታ ይ ረዳናል ወይም ረዳን» የዘወትር የመጽናኛ ቃል ነው፤ በስንፍና መጽናናት፤ የብዙ መሪዎች ችግር አለማወቅ አይደለም፤ ስንፍና

እንጂ::

ውሱን ትልም የውጤታማነት መሠረት ነው:: ግምገማ ደግሞ ግራ-ቀኙን እንድናይ ይረዳናል፤ ትርፍና ኪሣራችንን ያስለየናል:: ችግሩ የት አካባቢ እንደ ሆነ ይጠቁመናል:: እርግጥ ነው፣ የተወሰነ ዕቅድ ለመንደፍና የዕቅዱን ተግባራዊነት ለመገምገም ቀንና ሌሊት መሥራትን ስለሚጠይቅ አድካሚ ነው:: ግን ደግሞ የሥራ መሠረት ነውና መሆን አለበት፤ በግድም ቢሆን ከዚህ ድካም በቀላሉ ለመገላገል የሚወዱ ቸልተኛ መሪዎች ያለ ዕቅድና ግምገማ መኖር ይመርጣሉ:: እንዲህ መሰሎቹ «የሚያስተዳደር በትጋት ያስተዳድር» (ሮሜ 12:8) የሚለውን፣ «የሚያስተዳድር በስንፍና ያስተዳድር» በሚለው የተኩ ናቸው:: ይህን ነገር በ1994 ዓ.ም ገጠመኜ ላስረዳ፣ በዕቅድ እናውጣ ድርድር ላይ ድንገት «የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በመጪው ዓመት ከ50,000 በላይ ይሆናሉ» በማለት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌ በጽኑነት አበሰረ፤ «እንዴት እንዴት» ሲባል፣ «ጌታ ብሏል፣ አሳይቶኛል» ነበር መልሱ:: እንግዲህ 1994 ነው ብያችኋለሁ፤ አምናን ዘንድሮ ላይ ቆመን የቤተ ክርስቲያኒቷን ምእመናን ስንቆጥር አራት ሺህ ያህል ናት:: ከቀድሞው (ከ1994 ዓ.ምቱ) ልዩነት ቢኖር የ500 ምእመናን ጭማሪ ነው:: 45,000ው የት ቀሩ? ዕቅድን ምክንያታዊ ካለማድረግ፤ አዎን አዎን፤ አሜን፣ አሜን በማለት የመጣ ችግር ነው:: አቅምን፣ ችሎታንና አካባቢን ካለማገናዘብ የተከሰተ ስሕተት ነው:: ነገሩ መንፈሳዊነት መስሎን ይሆናል፤ ግን አይደለም፤ ግብታዊነት እንጂ:: መሪዎች በዚህ መሰል «ራእይ» ይደለላሉ:: የተባለው ነገር ከእግዚአብሔር ይሁን አይሁንም፤ ለአንድ ውጥን፣ አስፈላጊ ነገሮችን አሰባስቦ ለውጥኑ ተግባራዊነት እስካልተንቀሳቀሱ ድረስ ውጤት ሊመጣ ከቶ አይችልም:: ከአቅማችን በላይ እንድንፈተን የማይፈቅድ እግዚአብሔር፣ እኛነታችንንና ውስንነታችንን ስለሚያውቅ፣ ከአቅማችን በላይ ራእይ አያሸክመንም::

መሪዎች በአግባቡ ቢጠቀሙት በረከትን ባይጠቀሙት ግን ጥፋትን ስለሚያስከትለው አንድ ልበል፤ ስለ ገንዘብ:: በቃለ እግዚአብሔር ምንነት ተገቢ ስፍራን ይዞ በመልካም መንገድ እንዲያገለግል ቢደረግ፤ ብር (ገንዘብ) ለእግዚአብሔር መንግሥት

ማስፋፊያ ዋነኛ መሣሪያ ነው። በተቃራኒው፣ በመሪዎች በአጓጉል መንገድ ከተያዘ መጠፋፊያ ይሆናል። ጌታ ኢየሱስ ሲመክር፣ «መዝገብ በምድር አይሁንላችሁ፣ በሰማይ እንጂ» አለ። አስከትሎም፣ «ማንም ለገንዘብም ለእግዚአብሔርም እኩል ልቡን ሰጥቶ ማገልገል አይችልም» አለ። ሁለት ጌቶች ለአንድ ሎሌ አስቸጋሪ ስለሆኑ። ቅድሚያ መስጠት፣ ምርጫም ማድረግ ግድ መሆኑ ነው። ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከ«በጀት» እና ከ«ሂሳብ» አያያዝ ጋር ያላቸው ትውውቅ ደካማ ነው፤ ወይም ዕውቀት የላቸውም። «ቤተ ክርስቲያን በእምነት ብቻ ትመራ፣» ከሚል አጉል መንፈሳዊነት ጋር በመጣበቅ ራሳቸውን ፈተና ላይ ይጥላሉ። በዚህም ብዙዎች መልካም ምስክርነታቸውን አጥተዋል። «ራስን በራስ መጣል» ማለት ይህ ነው። በጥሩና በመደበኛ የገንዘብ አያያዝ መጠቀም ሲቻል፣ ለምን የውድቀት መንገድ እንደሚመቻች አይገባኝም። አሁንም ቢሆን ከጥፋት መጠበቂያ ዘዴ ካልተቀየሰ፣ ነገ ደግሞ ብዙዎች ሊወድቁ ይችላሉ። ዛሬና ትላንትና ብዙዎች ወድቀዋልና። ካለፈ ነገር መማር የብልህ መሪ መለያ ይመስለኛል።

ወደ ነገሬ ፍጻሜ ልሂድና፤ «የእግዚአብሔርን ቤት ከሠራሁ፣ የእኔን ደግሞ እርሱ ይሠራልኛል» በሚለው ነገሬን ላሳርግ። ከዚህ የእምነት አነጋገር ጋር ጠብ የለኝም፤ እስማማበታለሁ። እኔ ግን የራሳቸውን ቤት እያፈረሱ፣ እግዚአብሔር ቤቴን ይሠራልኛል ከሚሉት ጋር አልወግንም። አያሌ መሪዎች ትዳር መሥርተው ልጆች አፍርተዋል። ይሁንና፣ ሚስት የባሏን ፍቅር በተግባር ማየት ናፍቃ፣ ልጆችም የአባትን ምክርና አለኝታ ሳያገኙ እንዲያው ቀርተዋል። የአባትነት ፍቅራቸውን ለሚስትና ለልጅ ነፍገው፣ የክርስቶስን ፍቅር እንሰብካለን የሚሉ ምንኛ ያሳዝኑ? ብዙዎቹ ግን የፍቅር ንፉጋን ናቸው። ማለዳ ከቤት ወጥቶ እኩለ ሌሊት ወደ ቤት መመለስ የወትሮ ተግባር ነው። እንዲህ ዓይነቱ ዕለታዊ ተግባር ስውር ወይም ግልጥ ምሬትን ከቤተሰቦቻቸው ማመንጨቱ አይቀርም። ቆይቶ ደግሞ ሰላም ያናጋል፤ በምትኩም ቅሬታ ያነግሣል። ሚስቶችም፣ «እኛን ሳይሆን፣ አገልግሎቶቻቸውን ነው ያገቡት» ማለት ይጀምራሉ፤ ያሉም አይጠፉም። እውን አንድ መሪ ለቤተሰቡ ሳያስብ ውጤታማ አገልጋይ ይሆናልን? ፈጽሞ

አይሆንም፤ መስሎት እንጂ::

ጽሑፌን ስጀምር ምን ምሳሌ እንዳነሣሁ አትርሱብኝ፣ «በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አያገኝም» ብዬ ነበር:: ለምን ታዲያ የበሽታችንን ዋነኛ ጉዳይ ገልጠን ለመድኃኒት አናበቃውም፤ እንፈውስ የለ::

ቅኝት

«መጻሕፍተ ኑፋቄ በመጽሐፍ ቅዱስ ዓይን ሲታይ»

የመጽሐፉ አዘጋጅ:- ጥላሁን መኮንን

የኅትመት ዘመን:- 1991 ዓ.ም

የገጽ መጠን 135

የኅትመት ቦታ:- አፍሪካ ማተሚያ ቤት::

ጥላሁን መኮንንን አላውቃቸውም:: ስለ ጻፉት መጽሐፍ የሰማሁት አንብበው ካደነቁት ሰዎች ነው:: አልዘገየሁም፤ ገዝቼ ንባቤን አደረስኩ፤ ደጋገምኩትም:: የመድገሜ ምክንያት የሰከነ እይታ እንዲኖረኝ ነበር፤ እናም ያስተዋልኩትን በቅኝት ደረጃ ለማስተዋወቅ ተነሣሁ::

ጸሐፊው ጥላሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያነጻጸሩ የፈተሹዋቸው የመነሻ መጻሕፍት:-

1. ተአምረ ማርያም
2. ገድለ ተክለሃይማት
3. ገድለ ክርስቶስ ሳምራ እና
4. ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው::

በዚህ ጽሑፍ በጸሐፊው የተሰጠውን ተአምረ ማርያምን፣ ከአቅርቦቱ አኳያ እመለከተዋለሁ:: ይህን እንዳደርግ የገፋፋኝ ደግሞ «በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን» የሚለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመጽሐፉ ገጽ 25 መነሻ ላይ:-

«ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ [1434-68] ንጉሥ ብቻ ሳይሆኑ በገዳም የኖሩ ጸሐፊም ነበሩና ራሳቸው እየጻፉና ሌሎችን እያጻፉ

በዘመነ መንግሥታቸው ለማርያም፣ ለመስቀልና ለሥዕል መስገድ እንደሚገባ የሚናገሩ በርካታ መጻሕፍት እንዲበዙ አድርገዋል። ተዓቅቦ ምስጢር፣ መጽሐፈ ብርሃን፤ ተአምረ ማርያም፤ ርቱዓ ሃይማኖት፤ ጦማረ ትስብእት፣ መጽሐፈ ምዕላድ፣ አርጋነ ድንግል፣ ዘለፋ እስጢፋ . . . እና ሌሎችም የተጻፉትና ተተርጉመው የተሰናዱት በዚህ ጊዜ ነው» ይላል።

ይህ አባባል የጫረብኝ መሠረታዊ ጥያቄ፣ እኒህን ሁሉ ዘርዓ ያዕቆብ ለምን አጻፉ? «ሕዝበ ክርስቲያኑ» እኒህ መጻሕፍት እዚሁ በአገራችን መደረሳቸውን ያውቃሉ ወይ? እውነትስ በመጻሕፍተ ኑፋቄ መጽሐፍ ጀርባ አብርሃም ግርማ የተባሉት ሰው ስለ መጽሐፉ በሰጡት አስተያየት ላይ፡-

«መቼም አውቆ የተኛ. . . እንደሚባለው ካልሆነ በስተቀር ይህንን መጽሐፍ አንብቦ ለእነዚህ ድርሰቶች ጥብቅና የሚቆም አይኖርም። ይህ መጽሐፍ ለዘመናት «በእኛ ተዉት» ብለው የሕያው የእግዚአብሔርን ልጅ የኢየሱስን መድኃኒዓለምነት ከሕዝቡ ልብ አውጥተው በደል የፈጸሙትን ገድላ ገድሎች በገሃድ ያሳየ እውነተኛውን የመዳኛ መንገድ የጠቆመ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ስለዚህ በማስተዋልና እውነትን በመሻት ለሚያነበው እንደሚጠቀምበት አምናለሁ።»

...እንዳሉት ዓይነትስ ይሆኑ ወይ? እኒሁ ጥያቄዎች ሆነውብኝ ወደ መጽሐፉ ዘልቄ ተደንቄአለሁ፤ እንናተም እኒህ አባባሎች ምን ያህል እውነት እንደ ሆኑ «መጻሕፍተ ኑፋቄ» ከተሰኘው መጽሐፍ ተአምረ ማርያምን ብቻ አለፍ አለፍ ብዬ በንጽጽር አስተዋውቃለሁ፤ ዳኝነቱን ደግሞ ለአንባቢያን ትቼዋለሁ።

ተአምረ ማርያም እንዲህ ይላል	አጠያያቂ አሳቦች	መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል
«ጌታችን እጅዋን ይዞ በፍቅር ተቀበላት፣ እናቴ ሆይ፣ መጣሽን እያለ በጌትነቱ ዙፋን ላይ አውጥቶ በቀኙ አስቀመጣት» ... (ተአምረ 12:16፣ ገጽ 24)	በዙፋኑ ላይ የተ ቀመጠው ብቻውን ገዢ የሆነው የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱም ደግሞ በቀኙ ያስቀመጠውም ማርያምን ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።	የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፣ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ፣ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ (ዕብ. 1:3፤ ዮሐንስ ራእይ 7:10፤ ድ.ት.)
ወዳጆቿ የምትሆኑ ደስ ይበላችሁ፤ ይህንን ድንቅ ኪዳን ቸርነትን በኅነትን ሁሉ የያዘ ጌታ በሰማይና በምድር ያሉ ሁሉ ስሟን በመጥራት ይድኑ ዘንድ የሰጣትን ድንቅ የሆነን መሐላ ታዩ ዘንድ ኑ... (ተአምረ 12:46፣ ገጽ 25)	የጠፋው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኝ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እርሱን አምኖ እና ጠርቶ ሰው ከዘላለም ጥፋት ይድናል እንጂ፣ የማርያምን ስም በመጥራት ደኅንነት የለም።	መዳን በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተ ሰጠ ስም [ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር] ከሰማይ በታች የለምና (ሐዋ. 4:12)።
ከንጉሥ ልጅዋ ጎን በፈሰሰ ደሟ ንጹሐን አድርጋ እንደ ስሟ ትርጓሜ ወደ ልጅዋ ባሮች አባቶቻችንን በፍጹምነት መርታ ታድርሰን (ተአም ረ 12:54፣ ገጽ 27)።	ለመስቀል ሞት አበቃው፤ ከዚህ የተነሣ በደሙ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንድናለን እንጂ፣ ማርያም በልጅዋ ደም አታድንም።	በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ጠብቁአት (ሐዋ. 20:28፤ ሮሜ 5:9፤ ድ.ት.)።
በአንቺ አምኖ ያፈረ ማን ነው? አንቺን ለምኖ ወደ ገሃነም ያወረድሽው ማን ነው? ወደ መንግሥተ ሰማያ አገባሽው እንጂ.... (ተአምረ 43:24-25፣ ገጽ 39)	ሊታመን የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡ የፍርድ ባለቤትም እርሱ ነው። ሰው ከገሃነም የሚተርፈው ማርያምን አምኖ ሳይሆን፣ ክርስቶስን ታምኖ ነው።	እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም (ዮሐ. 14:6፤ ድ.ት.)።

ሰይጣን ትጋታቸውን አይቶ ተፈታተናቸው ምድጃቸውንም አፍርሶ አፈር ሞላው... ምግባቸውን የሚያበስሉበትን ባጡ ጊዜ ድንቅ ተአምራት ወደምታደርገው በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ወደ ጸናችው እመቤታችን ለመኑ፤ ልመናቸውን ተቀብላ ምድጃችሁን ያፈረሰ ሰይጣን ነውና እንደ ባሪያ አሥራ ሁለት ዓመት ይገዛላችሁ አለቻቸው። ከእንግዲህ ወዲህ አትዘኑ ከልጁ ከባሕሪው በተገኘ ሥልጣን ሰይጣንን ትገዙት ዘንድ ስለ እናንተ ለምኜዋለሁና አለቻቸው። (ተአምረ 51:3-8፣ ገጽ 52)	ተአምሩ ይህን እንደ መነሻ ያደረገበት ስፍራ በግብፅ ካሉ አውራጃዎች ባንዱ የመነኮሳት ገዳም ውስጥ ነው። ትረካው ጥያቄ ውስጥ ያዘፈቀው ሰይጣን ሰው አካል ወይም ሰው የሚመስል ሳይሆን፣ መንፈስ እና በመላእክት ደረጃ የተገለጸ ፍጡር ነው። እንደ ተራ ወንጀለኛ ታስሮ፣ የሰው አገልጋይ አይሆንም - ያውም ለአሥራ ሁለት ዓመታት። በተጨማሪም ማርያም በጸሎቷ እንደ እግዚአብሔር አሳብ ያልሆነ «የልመና መልስን» ሰጠች ማለት አደናጋሪ ነው። የሰይጣንን ሥራ ያሸነፈው ክርስቶስ በመስቀል ሥራው ብቻ ነው።	ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ... (ሉቃስ 14:6፤ ድ.ት) እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል. . . (ያዕ. 4:7፤ ድ.ት) ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና (1ኛ ጴጥ. 5:8፤ ድ.ት.) ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና። ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ (1ኛ ዮሐ. 3:8፤ ድ.ት)
...እርሱም እኔ ሰይጣን ነኝ ሲል መለሰለት . . . ነጋዴውም ልትረዳኝ ይቻልሃል በማለት ማለደው። ሰይጣንም ነገሬን ብትቀበለኝስ ባለ ዘመንህ ሁሉ እንደ ቀድሞ ፍጹም ባለጸጋ ትሆናለህ. . . በደረቱ ያለውን ውሰድ አለው። ለዚያም ነጋዴ ክንዱን አወጣና የለዘቡ ሁለት አናቁ ሰጠው፣ ነጋዴውም ከደስታው የተነሣ ምን ላድርግልህ ብሎ የውለታ ካሳ	- የሚተረክለት ነጋዴ ጥብርያዶስ የሚባል ሰው ነው። ኑሮው የተመሠረተው ቅፍጥ በሚባል አገር ነው። ሀብታምና ባለጸጋ ነበር፣ ግን ደኸየ። ለዚህ ሰው መፍትሔን የሚሰጥ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ፣ ሰይጣን መፍትሔን አዘጋጅ ሆኖ ተገኘ። - ባለጠጋውም «ሰይጣን ነኝ» ብሎ ሲነግረው መደንገጥና መሸሽ ሲገባው እንደ አብሮ አደጉ ሰላማዊ	- ዲያብሎስ ኢየሱስ. . . የዓለምን መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፡- «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ አሰጥሃለሁ አለው። ያን ጊዜ ኢየሱስም፡- «ሂድ፣ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና» አለው (ማቴ. 4:8-10፤ ድ.ት.)። «እግዚአብሔር ሰጠ፣

ጠየቀው። ይህን ጊዜ ሰይጣን 1ኛ) ክርስቶስን ካድ፤ 2ኛ) ክርስትናህን እርገም፤ 3ኛ) ጥምቀትህን አቃልል፤ 4ኛ) የሱራፌልና የኪሩቤልን መኖር ካድ፤ 5ኛ) አምላክን የወለደች እመቤታችንን ማርያምን ካድ አለው። ነጋዴው . . . እመቤቴ ማርያምን አልክድም እንጂ፣ ክርስቶስንም እክዳለሁ፣ ክርስትናዬንም ጥያለሁ፣ ጥምቀቴንም አቃልያለሁ፣ ሱራፌልና ኪሩቤል የሚባል ነገር አላውቅም አለ። ሰይጣንም ማርያምን ካልካድህ የምሠራው አይ ረባህም ብሎ ከሱ ተሰውሮ ትቶት ሄደ። እመቤታችንም ልጄ ሆይ፣ የዚህን ኃጥእ ምስኪን ሰው ኃጢአቱን ይቅር ትለው ዘንድ እለምንሃለሁ አለችው። ጌታም. . . ክዶኛል ይቅር አልለውም አላት . . . ልጄ ሆይ ይቅር ትለው ዘንድ እለምንሃለሁ በጡቴም እማጸንሃለሁ እያለች መሪር ልቅሶን በፊቱ አለቀሰች። (ተአምረ 110:2-16)	ውይይት ማካሄዳቸው የሰይጣንን ባሕርይ ቀይሮታል። ሌላው በት ረካው ላይ ግር የሚለው ክርስቶስ ተካደ፤ መካዱ ግን ምንም ችግር ሳይፈጥር የማርያም አለመካድ ሰይጣንን አስቆጥቶት አስኬደው። በዚህም ገለጻ ማርያም ልቃ ክርስቶስ ዝቅ ማለቱ በግልጽ ይታያል። - ደግሞም የበረከት ምንጭ በእግዚአብሔር እጅ ሳይሆን፣ በማርያም እጅ መሆኑን በማሳወቅ መተረኩ አደናጋሪ አድርጎታል። ከዚህም በላይ፡- ጌታ ይቅር ባይ እንዳልሆነ አድርጐ መሳሉና በጌታ ፊት እንባዎች ሁሉ በሚወገዱበት ስፍራ የማርያም ልቅሶና መማጸን ተአምርነቱን ሸሮታል።	እግዚአብሔርም ነግ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን (ኢዮብ 1:21፤ ድ.ት.)። ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ፣ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ (ማቴ. 10:32፤ ድ.ት)። ኢየሱስ ሲናገር፣ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፡- የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው። እርሱ ግን፡- አዎን፣ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው አለ (ሉቃስ 11:27-28፤ ድ.ት)። . . .እንባን ሁሉ ከዓይናቸው ይጠርጋል ሞት ወይም ኀዘን ወይም ለቅሶ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም (ራእይ 2:14)።

እንግዲህ በሠንጠረዡ ላይ እንደ ተመለከታችሁ፣ ጥላሁን ከአዘጋጁት መጽሐፍ አንድ አራተኛውን ወስጄ ከእርሱም ለግንዛቤ እንዲረዳ ብቻ የተወሰኑ ነጥቦችን ማንሣቴን ልብ በሉልኝ። አስከትዬም ለመጽሐፉ የተሰጠውን ስያሜ ብቁነት ለግንዛቤ ላብቃ። ስያሜው «መጻሕፍተ ኑፋቄ . . .» የሚል ነው። በጎብረተሰባችን ዘንድ ኑፋቄ፣ መናፍቅ፣ መናፍቅነት የሚሉት መጠሪያዎች ተ ደጋግመው ሲነገሩ ይስተዋላሉ። ፍቺው ከሊቃውንቱ መዝገበ ቃላት ሲፈተሽ ደስታ ተክለወልድ በገጽ 794 ላይ ኑፋቄ (መናፍቅን)፡- «ሃይማኖተ ግማሽ፤» ሲሉት፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የተሰኘው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ በገጽ 110 ላይ «ከእውነተኛ ሃይማኖት መውጣት፤ በፈጣሪ በእግዚአብሔር የማያምን፣ ይልቁንም የኢየሱስ መድኃኒትነት፣ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወትነት የማያምን የሚክድ» ብሎ ይፈታዋል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ደግሞ በገጽ 646 ላይ፡- «የሚጠራጠር፤ የሚያጠራጥር፤ ጠርጣሪ፤ አጠራጣሪ፤ ሃይማኖቱ ንጹሕ ያልሆነ ምሉእና ፍጹም ትክክል የአይደለ፤ መንፈቅን አምኖ መንፈቁን የሚክድ» በማለት ኑፋቄንና መናፍቅነትን ይፈታሉ።

የሊቃውንቱ አተረጓጐም ትክክልና ተገቢ ነው። በገለጻቸው እንከን ከሌለው እውነት ሸርፎ፣ ቆርሶና ገምሶ የሚያስተላልፍ ሁሉ በኑፋቄነት ተጠርቷል። እውነትና ሙሉ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ከቃሉ የወጣ፣ ያፈነገጠና ያጐደለ ትምህርት እርሱ ኑፋቄ ነው። ይህ ደግሞ ያሳስታል፣ ጥርጥር ውስጥ ይከታል፣ ከእውነትም ያርቃል። ሐዋርያው ጳውሎስ ኑፋቄ ወይም መናፍቃን ሊባሉ ስለ ተገባቸው ሲናገር፣ «እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» (ገላ. 1፡6-8፤ ድ.ት.) በማለት እግዚአብሔር ስለ ደኅንነት ለሰው ልጅ የገለጸውን የምሥራች የማይለወጥ፣ የማይጨመርበትና የማይቀነስለት መሆኑን አሳየን። ከቃሉ ያፈነገጠ ትምህርት ሁሉ ጎዶሎና የተሸቀጠ በመሆኑ፣ ይህን የመሰለውን ጽሑፍ ኑፋቄ ብሎ መጥራቱ ተገቢ ይሆናል። ደግሞም ጸሐፊው መጽሐፉን

«በመጽሐፍ ቅዱስ ዓይን ሲታይ» በማለት ስላነጻጸሩት፣ ተገቢ ርእስ መሆኑን አስተውያለሁ።

ተአምረ ማርያም በእግዚአብሔር መንፈስ በተደረሱት ቅዱሳት መጻሕፍት ሲፈተሽ አልተጣጣመም። ከዚህም የተነሣ፣ እኒህን የመሰለ የደራሲውን ቀሪ ሥራዎችን ለአንባቢያን ትቼ፣ ሊታረሙ ይገባቸዋል የምላቸውን ጥቂት ነጥቦች በማንሣት ቅኝቴን ልጠቅልል።

ለምሳሌ፣ በመቅድመ ተአምር ቁጥር 7 ላይ ይገኛል የተባለውና «ፍጥረት ሁሉ እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠረ፤ አዳምና ሔዋን እመቤታችን ከእነርሱ ልትወለድ ተፈጠሩ፤» በማለት አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑና ፍጥረታትን እንዲገዙ መሆኑን ገልጾ፤ መመስገን የእግዚአብሔር ድርሻ እንጂ የማርያም አለመሆኑን ሊገልጽ የተገባው ክፍል ጥቅስ በትክክል አልተገለጸም።

ሌላው ነጥቤ ተአምረ ማርያም አንድ መቶ አሥራ አንድ ምዕራፎችን ይዞ በ589 ያህል ገጾች የተካተተ የግእዝ-አማርኛ ሥራ ነው። ይህም ሰፊ ጽሑፍ መሆኑን ያሳየናል። ጸሐፊው «ድንግል ማርያም በተአምረ ማርያም» በማለት በሠሩት ሥራ ውስጥ ሊነሡ የሚገባቸውንና ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር የተጣረሱ ትረካዎችን ሳያነሡ አልፈዋቸዋል። አንደ እኔ ምልከታ ባይታለፍ መልካም ነበር የምላቸውን ጥቂት ክፍሎች እስኪ ላስታውስ፡- ተአምረ ማርያም ምዕራፍ 7 የማርያም ትንሣኤና የደቀ መዛሙርቱም እርሷን ለማየት ወደ እግዚአብሔር ማረጋቸው . . . ተዝካሯን ሲፈጽሙ ኃጢአታቸው ሊደመሰስላቸው፤ እሳቱንም ፈጽሞ እንዳያዩ መወሰኑ፤ በምዕራፍ 26 ደግሞ ስለ ማርያም ብቻ በመቀደስ የኖረውን ቁስ ባለጸጋው «ደም ትፋ» ብሎ ስለ ሰደበው፤ ባለጸጋው ማታውኑ ደም ተፍቶ መሞቱን ከዘረዘረ በኋላ፣ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ኃጢአቱ አይሰረይለትም የተባለለት ቃል ለዚህ መሆኑን ይገልጻል። በምዕራፍ 109ም ሰርጊስና አብርስቅላ በባልና ሚስትነት ሊኖሩ ጀምረው ግን የሩካቤ ሥጋ ሳይፈጽሙ ለመኖር ወሰኑ። ውሳኔያቸውንም አጽንተ ው ለዓመታት ኖረው አንድ ቀን ግን ሰርጊዮስ (ባልየው)፡- የግብ

ረ ሥጋ ግንኙነት ካልፈጸምን በማለት ሚስቱን አስጨንቆ፣ ልጅ መ ረገዙን፤ ኋላም ሰይጣን የተወለደውን ልጅ ለመግደል ወደ ሲያል ይዞት ሲወርድ ማርያም ልጁን ይዛ እንደ ወጣች ይተርካል።

እኒህን የመሳሰሉ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተጣረሱ ትረካዎች ሳይወቀሱ ተትተዋል። ቢታከሉ ኖሮ ግን በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ሚካኤል ዘ እስጢፋኖስ «የክርስቶስ የክብሩ እውቀት ብርሃን እንዲያበራልን ለዘመናት የሕዝቡን አሳብ አሳውሮ የነበረው የዚህ ዓለም አምላክ በዚህች መጽሐፍ ምስጢር ተገለጠበት፤ ሥራውም ፈረሰበት። ለምድራችንም ነጻ መውጣት እንዲሆን አስቦ ይህችን መጽሐፍ የሰጠን እግዚአብሔር ይመስገን። እኔም የነጻነት መጽሐፍ ብያታለሁ።» ያለው ይበልጥ ጉልህ ይሆን ነበር።

አንገት የለሾቹ ሰዎች

ጥናታዊው ጽሑፍ የዝግጅቱ መጀመሪያ ያደረገው ምሳሌን ነው፤ አይጥን። ብዙዎች አይጥን በቅርብም ሆነ በርቀት ስትንቀሳቀስ ሲያዩ ይደነግጣሉ፣ ይጮኃሉ፣ ይዘላሉ። ይህ እንዲህ መሆኑ በብዙዎች ዘንድ የሚደጋገም ሁኔታ ነው፤ ይላል ጽሑፉ። ዳሩ ግን ማን ያውቃል እኚህ ተጨናቂዎች አንድ ሌላ ቀን አንገት የሌላት አይጥ በፊታቸው ብትሄድ ምላሻቸው ምን ይሆን? ብዙዎች እንደሚስማሙበትና እኔም እንደምገምተው፣ በላብ መዘፈቅ የስሜታቸው መገለጫ ይሆናል።

አባቶች እንደሚሉት፣ «ጉድ ሳይመጣ መስከረም አይጠባምና» የዘንድሮዎቹ የቴክሳስ ዩኒቨርስቲ ምሁራን አንገት-የለሽ አይጦችን አምርተዋል፤ እነርሱ ያደረጉት እንዲህ ነው፤ በመጀመሪያ ራስ ሊሆን የሚቻለውን ትክክለኛ ጂን ለማወቅ ጣሩ፣ አገኙም፤ ከዚያም በሺህ ከሚቆጠሩ የአይጥ ፅንሶች ውስጥ እነዚያን ጂኖች በማስወገድ ፅንሱ እንዲቀጥል አደረጉ፤ ከሺዎቹ ብዙዎቹ አለቁ፤ አራቱ ግን እስከ ውልደት ቀን ደረሱ፤ ከአራቱ ደግሞ አንዲቱ በሰላም ያለ አፍ፣ ያለ ጆሮና ያለ ራስ ተወለደች፤ ተንቀሳቅሳ ብዙም ሳትቆይ

ሞተች::

ምሁራኑ ለምን ይሆን እንዲህ መመራመሩን ያዘለቁት? ከአይጥ ጋር ውሎ ማደሩን፣ አብሮ መክረሙን ያስወደዳቸው ምን ይሆን? እርግጡ፣ አይጥን መወደድ መጥላትም ሳይሆን፣ አይጥን ራስ - የለሽ አድርጎ ማስገኘት ውጤታማ ከሆነ፣ ያንን ውጤት ይዞ ራስ የሌለው ሰው ማምጣት ቀጣዩ ተስፋ ይሆናል፤ እናም የሙከራው ግብ አይጥ ሳይሆን፣ «አንገት-የለሽ ሰው» ማምረት ነው::

ይህ መጪ ሰው ራስ የሌለው ቢሆንም፣ በሕይወት ማቆየት ይቻላል፤ ሰው ሠራሽ የማቆያ ዘዴ በመጠቀም ልቡ ቀጥ እንዳትል ጥረት ይደረግለታል:: «የተጣረሰት ሰው» የሰውነቱ ክፍሎች እንዳስፈላጊነታቸው እየተመነዘሩ ለአካል ክፍል ፈላጊዎች መተኪያ ይሆናሉ - እየተቆራረጡ፣ እየተከፋፈሉ፣ እየተበለቱም::

በፒርስተን ዩኒቨርስቲ የሞለኪዩለር ሥነ ሕይወት (Molecular Biologist) ሳይንቲስት የሆኑት ሊሲልቨር «እንዲህ ዓይነት ራስ-የለሽ ሰው ማስገኘት የእውቀት ድላችን ነው፣ የተመረተውን አእምሮ- የለሽ ሰው እንደ ልባችን ለፈለግነው ጉዳይ ብንጠቀምበት ሃይማኖታውያን፣ ፖለቲካውያን እና የፍልስፍና ጠበብቶች ሊከሱን፣ ሊወቅሱን አይችሉም:: አለመቻላቸውን ምርቱ በራሱ መብቱን ሊያስከብር የሚችል አይደለምና፣ ሰዎችም እከሌ ነው ብለው ጥበቅና አይቆሙለትም» ይላሉ::

ይህን ንግግራቸውን በርካታ የጂኔትክ አጥኚ ዩኒቨርስቲዎች ይስማሙበታል፤ ሁሉም:- ራስ የለሽ «ሰውን ማምረት ለሁሉም ይበጃል» ባይ ናቸው፣ «ተወጋጅ የአካል ክፍሎች አካል ማግኘ ታቸውን የመሰለ፣ ምን እረፍት አለ?» ይላሉ::

ሊሲልቨር ሥራቸውን ግልጥልጥ አድርገው የጻፉበት «የቀድሞዋን የኤድን ገነትን እናስገኝ» የሚለው መጽሐፋቸው ሳይንቲስቱ እግዚአብሔር ቀድሞ ሰውን እንደ ራሱ አምሳል በዚህ ፈጥሮት ነበር፣ ዛሬ እኛ ሰውን እንደ እኛ አምሳል በዚያችው ኤድን እናስገኛለን» ይላሉ:: ይህን የሚደግፈው ሼር ቤከር እምነቱን በጽሑፍ ሲያብራራ፣ «የሊሲልቨር መጽሐፍ ምክንያታዊ፣ ተአማኒ፣ የብሩህ ተስፋ መንሥኤ በመሆን በዓለም ላይ ያለነውን አስደምሞናል» ብለውላቸዋል::

ሊሲልቨር እንደሚተነትኑት፣ «ይህ የጥናት ውጤት የገንዘብ አቅም ያለው ማንም ሀብታም ሊጠቀምበት ይችላል» በማለት ውጤቱን የገበያ ጉዳይ አድርገውታል።

የዚህን የጥናት አካሔድ ጋዜጠኞች ወደ ሊሲልቨር በመቅረብ «በመጪው ዓመታት የሰው ሞት ያበቃ እና ዘላለማዊ መሆን ይችል ይሆን?» የሚለውን ቀዳሚ ጥያቄ አድርጎላቸው፣ «ግባችን እርሱ ነው፣ ያለጥርጥር ሞትን ድል እንነሣለን» የሚል ሆነ።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ፣ «እግዚአብሔር ብቻ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይ» መሆኑን ያስተምራል። ሊሲልቨር ደግሞ፣ «ሰው የማያውቀው፣ እንዳያውቀው ሊደረግ የሚገባም ምንም ነገር ሊኖር አይችልም» በማለት ያደፋፍራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብቻ ዘላለማዊ መሆኑን አስረግጦ ያስተምራል፤ እኛም ከክርስቶስ የትንሣኤ ኃይል የተነሣ ሕያዋን እንደምንሆን ይገልጻል። ሊሲልቨር ግን በምጥቀ ሥልጣኔ ዘላለማዊነት የግላችን ይሆናል ይላሉ።

የሊሲልቨርንና የአጋሮቹን የሙያ ውጤት ከምኞታቸው ጋር ላዘግይና የእግዚአብሔር ቃል ስለ ራስ የገለጸውን እውነት እንመዝን፣

እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን የሁሉ ራስ አደረገው በማለት ክርስቶስ፣ በሰው፣ በፍጥረት፣ በሉሲፈር እና በቤተ ክርስቲያን ላይ ራስ እንዲሆን ማድረጉን በኤፌሶን 1:22 ላይ ይገልጻል። እግዚአብሔር ዔድንን እንዳቀዳትና እንዳሰባት ለሰው ልጅ ጥቅም አዘጋጃት፣ ግና ዲያብሎስ ሰውን ሸነገለ፣ ለሰው ራስ የሆነለትን እግዚአብሔርን በሚያጓጓ ቃል አታለለ፣ «ብትበሉ እንደ እርሱ እንደምትሆኑ አውቆ ነው» ባላቸው ጊዜ አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ጠረጠሩት፣ ዲያብሎስንም አመኑ፣ እናም ታከውት በኃጢአት ወደቁ፣ በውጤቱም ከእግዚአብሔር ተለይተው ካለዋኝኛው ቀሩ። ያለ ራስ ሆነው ከእግዚአብሔርና ከዔድን ገነት ተለዩ፣ በትይዩ ተለይተው ወደ ሰይጣን ቀረቡ፣ የፈቃዱ ፍጹም ተገዥ በመሆን የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር አሳብ እጅጉን እየራቀ የገዛ ፈቃዱን የሚያመልክበትንና የሚታመንበትን ያዙ።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በአንድ ወቅት እንዲህ ሆኖ ነበር።

እግዚአብሔር በትዕቢት እንደ ልቡ ለሆነው ለጢሮስ ንጉሥ በነብዩ በኩል ተከታዩን መልእክት ላከለት፡- «ልብህ ስለ ታበየ እኔ አምላክ ነኝ በባሕሩ መካከል በአማልክት ዙፋን ላይ እቀመጣለሁ ብለሃል፣ ምንም እንኳ አንተ በአሳብህ አምላክ ነኝ ብትል ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም። ከዳንኤል ይበልጥ ጥበበኛ የሆንክ ይመስልሃል፤ ምንም ምሥጢር እንደማይሰወርብህም ታስባለህ፤ በእርግጥም በብልኀትህ ብዙ ሀብት አግኝተሃል፣ በግምጃ ቤትህም ብዙ ወርቅና ብር አግበስብሰሃል። በንግድ ሥራም ባሳየኸው ታላቅ ብልኀት ብዙ ሀብት አግኝተሃል፤ ከሀብትህም ብዛት የተነሣ ኵራት ተሰምቶሃል» (ሕዝ. 28፡2-5፤ ቀ.ኢ.)።

በራስ - የለሽ የገበያ ምርትም ላይ ያለው ዘላቂ አመለካከት ተመሳሳይ ነው፣ በፍጥረቱና በኃጢአቱ የተገደበ የሰው ልጅ እንደ እግዚአብሔር ፍጹም እውቀት፣ ፍጹም ኃይል፣ ችሎታና ሙሉነት የለውም፣ አይኖረውም። ይህን ጎደሎነት ችል ብሎ ራሱን እንደ አምላክ የመቁጠር አካሄድ ሥልጣኔን ለመሰይጠን እንዳዋለው ያሳስባል።

አንድ ነገር ብዬ ይበልጥ የሚያሳስበውንና ሊስተዋል በሚገባ ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርጌ ልደምድም። በጽሑፉ መነሻ ላይ ድንገት አይጥን ማየት አስበረገገ፤ ይልቁኑ አንገት - የለሽ አይጥ ሆኖ ሲገኝ መደንበር ነበር ትርፉ። የሰው ራስ - የለሽ ሲታይ ደግሞ የሁለንተናችን መንዘፍዘፍ አይቀሬ ቢሆንም፣ ግና በየአውራው መንገድ ላይ የሚጓዘው ጤነኛ መሰል ሰው፣ ውስጠኛው ማንነቱ ሲፈተሽ ያለ ራስ ሆኖ መገኘቱ የሚገርም ይሆናል።

እግዚአብሔር ስለ ሰው ልጅ ሲናገር፣ «ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ሠርተዋል፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውንም ክብር አጥተዋል» ይላል፣ ኃጢአት ሰው እግዚአብሔርን በትክክል እንዳይረዳ፣ የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ሁሉ በሙልዓት እንዳያስተውል አድርጎ ከእግዚአብሔር ፈጽም አርቆታል፣ ከዚህም የተነሣ ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ በፊት ለሰው ልጅ በዔድን ገነት የሰጠውን ክብር አጥቶአል። ይህም ዋናው የሰው ልጅ ሁሉ ጉድለት ነው። ይህን ጐዶሎነት እግዚአብሔር ኢየሱስን በመላክ ዓለም በልጁ አምኖ ሙሉ እንዲሆንና ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ሰላምን ያደርግ

ዘንድ ወድዶ፣ «በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፣ በእርሱ የማያምን ግን በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ ገና ድሮ ተ ፈርዶበታል» (ዮሐ. 3፡16-18) በማለት ያመኑት በእግዚአብሔር ተ ደግፈው፣ ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ጋር በመገናኘት ሙሉ ሰው መሆናቸውን፣ ያላመኑበት ግን ዋንኛውን አጥተዋልና በሥጋዊ ሕይወት ቢንቀሳቀሱም ከእግዚአብሔር ቁጣ አይተርፉምና በውስጣዊ ማንነታቸው «ራስ - የለሽ» ሰዎች ሆነዋል።

እንግዲህ በውጤቱ የቱ ያስፈራል? አንገት-የለሽ አይጥ? ወይም «አንገት-የለሹ ሰው» ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ጋር ያለተገናኘው «ራስ - የለሹ ሰው»?

ማመሳከሪያ መረጃዎች

1. Ready for the Future. The Back To God Hour Publishers.
2. Headless Humans by L. Silver.
3. Remaking Eden by L. Silver.
4. Ready to Rebuild by. Jccl Prince.

ያልተቀጣ ዓይን አወጣ

ሰዎች ሁሉ ሊከተሏቸው የሚገባቸው ምግባራት የታወቁ ናቸው፤ በመለኮታዊ የሥነ ምግባር መስፈርቶች ላይ ተዘርዝረው ታውቀዋልና። ከዚሁ ጐን ለጐን፣ በጐ ውጤት የሚያስገኙ ባህላዊ ክስተቶችም አንዱ ማኅበረሰብ በማኅበረሰብነቱና በግላዊ ሕይወቱ እንዴት መመላለስ እንዳለበት ያሳውቁታል፣ ያስገነዝቡታል፣ እንዲሆኑትም ያመላክቱታል።

እንግዲያስ ማኅበረሰብ ሊሆን ለሚገባው የበጐ ሥነ ምግባር ውጤት ሁነኛ አመላካቾች እነማን ይሁኑ ተብሎ ቢጠየቅ፣ ምላሹ ክርስቲያኖች ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ «ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው. . . ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም. . .» በማለት ጸልዮአል (ዮሐንስ 17፣6፣15፤ ድ.ት)። ይህን የጸለየበት ዋንኛ ምክንያት በዓለም ወይም በኅብረተሰቡ መካከል የሚገኙት ክርስቲያኖች በኑሯቸውና በምግባራቸው፣ በአካሄዳቸውም ሁሉ ጨው ሆነው እንዲያጣፍጡ፣ እንዲሁም ብርሃን ሆነው ጨለማውን ዓለም መግለጣቸው እውን እንዲሆን ነው።

ጸሎቱ ምላሽ እንዳለው ማወቅ የሚቻለው እያንዳንዱ ዳግም የተ ወለደ አማኝ በጐ የሆነው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በሕይወቱ ሲገለጥ ነው። እንግዲህ ወደ ቁም ነገሩ ራመድ ልበልና አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ ሊገለጥ የተገቡት በጐ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባሮች ሳይገለጡ ቢቀሩ ሕይወትና ምግባሩ ጨውነቱንና ብርሃንነቱን ሳይሆን፣ አልጫነቱንና ጨለማነቱን የሚያገኙ ቢሆን፣ ይህን ችግር በምን ይፈቱታል? ምላሹ በጳውሎስ ወደ የጢሞቴዎስ መልእክት ላይ ይገኛል፤ «. . . በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው...» (1ኛ ጢሞ. 3፡15፤ ድ.ት.) በማለት አንድ ክርስቲያን ሊያውቀው የሚገባውን መሠረታዊ ቁም ነገሮች ያስረዳል። ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያንና በወገኖቹ መካከል ሊመላለስ ጤናማነት የጐደለው፣ የጨለመና በነውር የተነቀፈ ሕይወት ቢኖረው፣ የጌታ ድንጋጌ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን፣ መገሠጽ፣ መቅጣትና

ማስወገድ እንደ ሆነ ከሕያው ቃሉ መረዳት ይቻላል።

እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በነውሩ የሚመላለስን ሰው አክብሮ አያውቅም፤ ይቀጣዋል፣ ሲቀጣውም በቅጣቱ ሌሎች እግዚአብሔርን እንዲፈሩ፣ ቤተ ክርስቲያንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድትመላለስና ተቀጭው እንዲታረም በመሻት ነው። እናም ይህ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አጥፊ ሳይቀጣና ሳይገሠጽ ቢቀር፣ ነውር በዝቶ የቤተ ክርስቲያን የሕይወት መሠረትነት ይጠፋል፣ ያልተ ቀጣም ዓይን ማውጣቱን ያዘልቃል።

ይህ ግን እንዳይሆን፣ ብሉይ ኪዳን አካንንና ጥፋቱን ይገልጽልናል፤ በውጤቱም ማኅበሩን አውኳልና እርሱና ቤተሰቡ ለድንጋይ ወገራ ተዳርገዋል፣ ካህኑ ኤሊና ልጆቹም በነውር ሥራ ቸልተኝነትና መተባበር አጓጉል ሞት ተከሥቷል፤ በእነርሱ መዘዝ ይመለክበት የነበረው የእግዚአብሔር ቤት ፈርሷል።

በአዲስ ኪዳን የሸማግር ዘመንም በሐዋርያት ሥራ ላይ ሐናንያና ሰጲራ በሥነ ምግባር ጥፋታቸው ለሞት በቅተዋል፣ ጳውሎስ በነውራቸው ደንድነው ያለ ንስሐ ሕይወታቸውን ሊመሩ የሚወዱትን ቤተ ክርስቲያን ከመካከል እንድታስወግድ አጥብቆ ያዛል። ይህ ብቻ አይደለም፣ ጳውሎስ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በማጣት በክፉ መንገድ የሚዘልቁትን አንዳንዶች በሥጋቸው እንዲሠቃዩ ለዲያብሎስ አሳልፎ እስኪሰጣቸው ድረስ ደነገገ፣ አንዳንዶችም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ነን እያሉ በዐመፅ የሚደነድኑትን በተገለጸው የእርምት ደረጃ መሠረት በመጠቀም ሰውየው አግባብነት በጐደለው ሥነ ምግባር ከመመላለሱ የተነሣ የተጐዳው ወንድም በግል ጉዳዩን በማነጋገር መርዳት፤ ይዜ መፍትሔ ተጐጂው ተበዳዩ ከሌላ ሰው ጋር በመሆን አጓጉል የሆነውን ያንን ሰው በማነጋገር ያው ሰው ከክፉ መንገዱ አልመለስም ካለ ቤተ ክርስቲያን አነጋግራው በጐ ሥነ ምግባር ላለማሳየት ከወሰነና ለንስሐ ልቡን ከዘጋ በአደባባይ ከዚህ ሰው ጋር ማንም እንዳያብር በመግለጽ ማስወገድን ቤተ ክርስቲያን እንድትለማመድ ያበረታታል። የዚህም በጐ ውጤት ለዓለም ብርሃን እንሆን ዘንድ እንድንበቃ የጌታ አሳብ ነው።

መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ሰበከ፣ ንስሐ መግባት

ብቻ አልነበረም፣ የንስሐ ፍሬም ማፍራታቸው ወሳኝ መሆኑን ገለጸ። ይህንን ሲያስተምር ትልቅ ትንሽ፣ ደሀ ሀብታም፣ ያልተማረ የተማረ. . . አላለም ሁሉንም በአደባባይ ገሠጸ፣ አላመቻመቸም።

ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረታትን ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ዘመኑ ሲያጠራት ከገለጸው ትምህርት ዋንኛው ጥራት እንጂ ብዛት ዋጋ እንደሌለው ማሳየት ነበር፣ በጠባቡ ደጃፍ ለመግባት መታገልን እንጂ በሰፊው በጅምላ ያለ እንቅፋት መጓዝን አላስተማረም። በአንድ ወቅት ጌታን ብዙዎች ይከተሉት ነበር፣ አንድ ቀን ግን ሊከተሉት አቃታቸው፣ ተመለሱም፣ እርሱም የተቀሩትን ዘወር ብሎ፣ «እናንተስ ልትሄዱ ትወዳላችሁን. . .» ነበር ጥያቄው። ለዚህ መሻቱ፤ ንጽሕና፣ መልካም ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር ነበር።

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በቤተ ክርስቲያን ገንኖ ይወጣ ዘንድ መሪዎቹ ትልቅ ስፍራ አላቸው፤ የተሰጣቸውን ድርሻ ሳይፈጽሙ ሁሉ መረን ወጥቶ ስድነት፣ ልቅነት በቦታው ቢተካ የቤቱ ጠባቂ ዎች ከቅጣት አይተርፉም። ለዚህም በመረጃነት ነቢዩ ሳሙኤል፣ ንጉሡ ሳኦል፣ ካህኑ ኤሊ ተጠቃሾች ናቸው።

ቤተ ክርስቲያን የእውነት ዓምድ ሆና በብርሃንነትና በጨውነት ዓለምን ለማጣፈጥ የተለየች ከሆነች፣ በመካከሏ የሚሆነውን አጥርታ ለማየት ትገደዳለች፤ ስታጠራ ጽኑ መሆን ግዴታዋ ነው። አንዳንዱ ሰባኪዎችና መሪዎች ኃጢአትን ባለመገሠጽ፣ ሰዎችን ወደ ንስሐ ባለመምራት ዝም ብለው መስበክን ይመርጣሉ። ለምን ቢሉ የአሥራት የገቢ እጥረት ሊገጥም መቻሉን፣ የወዳጆች ፊት መንሣት መከተሉን፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት የመቅረትና የመጥፋት አደጋ ሊኖር እንደሚችል በማሰብ መሸቀጥን ዋነኛ መተዳደሪያ ያደርጋሉ። እንደዚህ ዓይነት መሪዎች ሳይቀጡ አይቀሩም፣ እንደዚህ ዓይነት አስተማሪዎችም የተማሪዎች ፍርድን ለራሳቸው ያከማቻሉ።

ይልቁኑ ሊያደርጉትና ሊሆኑት የሚገባው እንዲህ ነው። ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡6 (ድ.ት.) «. . . ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን?» በማለት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የተሠራውን ነውር ሚስት አግብቶ የተቀመጠ አለ እርሱን አስወግዱት ይላቸዋል፣ እርሱን ለዚህ ያበቃው ጥቂቱን እርሾውን

ቸል ስላላችሁለት ነውና። ማብራራቱን በማዝለቅ ማንም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን በሕይወቱ ካላስመሰከረ ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ ይላቸዋል፤ እውነትም ነው።

ልንሆነው የሚገባውን ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የጌታ ቃል ገልጾልናል። ሆነው መገኘታችን የጌታ ፈቃድ ነው፤ አለመኖር ግን ቅጣትን እንደሚያስከትል አስተውለናል። የጽሑፌ ፍጻሜ «ያልተ ቀጣ ዓይን አወጣ» እንዳይሆን፣ «ወንድሞች ሆይ፣ ከአፋ እንደተ ቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን. . . በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችን የማይታዘዝ ማንም ቢኖር፣ ይህን ተ መልከቱት፣ ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር አትተባበሩ። ነገር ግን እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ እንደ ጠላት አትቍጠሩት» (2ኛ ተሰ. 3፡6፣14፣15፤ ድ.ት.)። በጽኑ ልናስብበት ይገባል።

እንግዲህ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ስናጤን፣ ኢየሱስ «ከዓለም፣ ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገልጥሁላቸው» ያለውን አለመዘንጋት ወሳኝ ነው። በጌታ የሆንን እኛን ጌታ ከዓለም ሆነን፣ በኀብረተሰቡ መካከል ተገኝተን፣ የእያንዳንዳችን ድርሻ ብርሃንነትና ጨውነት ብቻ ነው። የእውነት ዓምድና መሠረት በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሥነ ምግባራቸውን በጌታ ቃል በተገለጸው እውነት የተገራና የታገዘ ሆኖ መገኘቱን ማየት የሁሉ ድርሻ ነው፤ ያኔ ነው ቤተ ክርስቲያን የምታድገው፣ የወንጌል ተልዕኮዋንም የምትፈጽመው።

ምርጫችን እሑድ ለምን ሆነ?

የዘጸአት ምዕራፍ ሃያ የሚያስተዋውቀን አሥሩን ትእዛዛት ነው። በዚህ ጽሑፍ በብዙዎች ዘንድ በየጊዜው ድንግርግር የሚፈጠርበትን ሰንበትን በተመለከተ የተሰጠውን አራተኛ ትእዛዝ እናጠናለን። መጽሐፍ እንደሚል፣ «የሰንበትን ቀን አክብር፣ ቀድሰውም፣ ሥራህን ሁሉ የምታከናውንባቸው ስድስት ቀኖች አሉልህ፤ ሰባተኛ

ው ቀን ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር የዕረፍት ቀን ነው፤ በዚያን ቀን. . .» (ቁ. 8-11፣ ቀ.አ) በማለት ቃሉ ቀኑ የተፈለገበትን ምክንያትና በቀኑ ሊከወኑ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን በመዘርዘር ይገልጻል።

መቼም ቢሆን በቋሚ መርጎነት ለሰዎች የተላለፈ የእግዚአብሔር አሳብ ሊሻሻል፣ ሊቀየር፣ ወይም ሊሻር አይችልም፤ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በጽኑነት ይዘልቃል፤ ግን ደግሞ ሰንበትን አስመልክቶ በአስተምህሮ ጥንታዊነቷን እንደ ጠበቀች ያለችዋ የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን፣ ሰንበት የሚለውን ቃል ትታ የጌታ ቀን ብላ ቀይራዋለች፤ ቅዳሜንም ትታ በእሑድ ጌታዋን ታከብራለች። ለምን ይሆን? በትይዩው ደግሞ ብዙ በርካታ መጻሕፍትን በሰንበት ላይ የጻፉ የሰባተኛዋ ቀን አክባሪ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሜ እንደ ጥንቱ ሊከበር፣ ዕለቱም «ሰንበት» እንደ ተባለ እንዲዘልቅ አጠንክረው በማስተማር ቃሉን ሳያሻሽሉ፣ ሳይቀይሩ ወይ ሳይሸሩ እስካሁን ያዘከራቸው ምን ይሆን? ለሁሉም መልስ አለው።

አንደኛው የመለኪያ መንገድ፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በማደግ ላይ በነበረችበት ሁለትና ሦስት ምእተ ዓመታት ውስጥ የነበሩ የሥነ መለኮት መምህራንና የእምነት አባቶች የጊዜውን እውን ታሪክ እንዴት አስቀምጠውት ነበር በማለት የኋልዮሽ የታሪክ መዘክሮችን መመርመር ነው።

ሁለተኛው የመለኪያ መንገድ፣ ቃሉ ቃሉን እንዴት እንዳብራራው በአግባቡ መረዳት ነው። መቼም አንዲት ነጠላ ጥቅስ ነጥሎ መክነፍ ለማንም አይጠቅምም። የትኛውም አስተምህሮ በሙሉው የመጽሐፍ ቅዱስ የድግግም አሳብ መደገፉ ግዴታ ነውና ቃሉን በማብራራት ወደ ጽኑ መፍትሔ እንዘልቃለን።

1. ምስክረ-ታሪክ

ናንዶር የተሰኘው ታዋቂ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ እሑድ መከበር ለምን እንደ ተጀመረ ሲናገር፣

> «...አይሁዶች የአይሁድነት አርማችን ሰንበትን መጠበቅ ነው ብለው ራሳቸውን ከቅዳሜት ጋር አስማሙ፤ ክርስቲያን መሆንን ሳይሆን አይሁዳዊ እንደ ሆኑ መኖርን ፈለጉ።

ከዚህም የተነሣ ከአይሁዶች ለመለየትና የክርስቲያኖች የድል እና የአዲስ ሕይወት ማብሰሪያ የክርስቶስ ትንሣኤ በእሑድ ስለ ተከናወነ፣ መሠረታችንና መልእክታችን እሑድ ሆነልን፤ ክርስቶስም የክርስትና ብቸኛ ማዕከልነቱን እሑድ ላይ ገለጸ፤ ስለዚህም ከቅዳሜ ይልቅ እሑድን እናከብራለን»

ብሎ ይጽፋል። ይህን የታሪክ መዘክር ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባቶችም አጽንተውታል። ቀደም ብሎ በሰማዕትነትን ወደ ጌታ የተሰበሰበው ጀስቲን በ150 ዓ.ም ላይ፣

«. . .እሑድ ዕለት በየቦታው ያሉ አማኞች ከያሉበት ተሰብስበው ወደ አንዱ የመሰብሰቢያ ስፍራ ይመጣሉ፤ በዚያም ሐዋርያት ያስተምሩት የነበሩትን ትምህርት ያደምጡ እንዲሁም የነቢያት መጻሕፍት ለረዥም ሰዓታት ይነበብላቸው ነበር» በማለት ጽፏል።

ከ260-340 ዓ.ም የኖረው ዩሲብየስ ደግሞ፣

«...ጉባዔ በክርስቲያኖች የተጀመረው በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነበር። በእነርሱ አጠራር «የጌታ ቀን» ይሉታል፤ እሑድን መሆኑ ነው፤ በዚያን ቀን ጌታቸውን ያመልካሉ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበቡ ይሰብካሉ፣ የጌታ እራትንም በዕለቱ ይወስዱ ነበር...»

በማለት የእሑድን ጥንታዊነት በጽሑፍ ገልጧል።

በ200 ዓ.ም ላይ በተርቱሊያን የተጻፈውን መረጃ ደግሞ እንደ ማጠቃለያ አድርጌ ልውሰደው።

«. . .የጌታ ቀን ለቤተ ክርስቲያን ያላት ብቸኛ የማምለኪያ ዕለቷ ነው፤ ከእሑድ እንጂ ከሰንበት ቅዳሜት ጋር ምንም ወዳጅነት አልነበረንም...» በማለት እነዚህ ሁሉ ገና ከጠዋቱ ታሪካዊ መረጃን ዘክረውናልና፤ የሰባተኛው ቀን ወይም የቅዳሜት አክባሪዎች ግን፣ «እሑድ ለመከበር ምክንያት የሆነው ኮንስታንታይን ወይም ደግሞ በትረ-ሥልጣኑን ጨብጠዋለሁ በማለት ጳጳሱ የደነገጉት ነው» በማለት መከላከያ ለመስጠት ይሞክራሉ። ልኩ ግን ከላይ የተነሡት መረጃዎች ሁሉ ከኮንስታንታይን ቀድመው የነበሩና ጳጳሳዊ አመራር ከመጀመሩ በፊት የነበሩ ጥንታዊያን መሆናቸውን ዘንግተውታል።

2. ምስክረ-ቃለ እግዚአብሔር

ወደ ሁለተኛው የመረጃ ሰነድ ስንዘልቅ ቃሉን እናገኛለን፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተችዋ ቤተ ክርስቲያን እድገት ማሳየቷን የምናውቀው የሐዋርያት ሥራን ስናጠና ነው፤ በዚህ መጽሐፍ በአሥራ አምስተኛው ምዕራፍ ላይ ለቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች ገጠሙ፡፡ ግጥሚያው በአክራሪ ክርስቲያን አይሁዶችና በአሕዛብ ክርስቲያኖች መካከል ነበር፡፡ ከፊሎች የቀደሙት ሕግጋትና መመሪያዎች በማደግ ላይ ባለችው ቤተ ክርስቲያን አማኞች ላይ ሥራ ላይ መዋል አለባቸው ብለው ሲሞግቱ፣ የተቀሩት ደግሞ በፍጹም በምንም ልንታገትና ልንገታ አይገባም፤ ጸጋው አድኖናል የወቅቱ ሙግት ነበር፡፡ ለዚህ ውዝግብ መፍትሔ አልታጣም፣ ከአይሁድ የሆነው ጴጥሮስ «ታዲያ፣ አባቶቻችንም ሆኑ እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በአማኞች ጫንቃ ላይ በመጫን ለምን አሁን እግዚአብሔርን ትፈታተኑትላችሁ? እኛም የምንድነው ልክ እንደ እነርሱ በጌታ ኢየሱስ ጸጋ መሆኑን እናምናለን» (ቁ. 10፣11 - ቀ.አ.)፡፡ ይህ የጊዜ ው መሪ ቁርጠኛ ቃል ሆነ፡፡ ጴጥሮስ፣ አስፈላጊ ከሆነ ሊጠበቁ የሚገባቸው ትእዛዛት ካሉም በማለት ከቁጥር 19-20 ያሉትን ጠቅሶ ቅዳሜትን ወይም ሰንበትን እንዲጠብቁ ሳያዛቸው ወይም ሳይደነግግላቸው ቀረ፤ አንዳንዶች ጴጥሮስ እርሱን ያልጠቀሰው ምናልባት «በጊዜው ሰንበትን ከአሕዛብ ወገን የነበሩት ክርስቲያኖች ይጠብቁት ስለ ነበረ ችግር ሆኖ አልቀረበም» የሚል ግምት ይፈጠርባችሁ እንዳይሆን፤ ለእርሱም አስተማማኝ መልስ ከቃሉ አለ፡፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20፡7፣ «ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን... ተሰበሰብን» ሲል፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1 እና 2፣ «በየሳምንቱ እሑድ ከእናንተ እያንዳንዱ...» በማለት በእሑድ በጌታ ቀን አምልኮን አማኞች ያደርጉ እንደ ነበር ያጸኑናልና፤ ስለዚህ፣ የጴ ጥሮስ ምላሽ ቅዳሜትን በመተው እንደ ሆነ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ግን ማን ያውቃል እንዲህ የሚል ሌላ ጥያቄ ተከታትሎ ሊመጣ ይችላል፡- በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የት ጋ ነው ቅዳሜ ወደ እሑድ ተቀየረ ተብሎ የተጻፈው? መልሱ አንድም ቦታ አልተጻፈም ነው፡፡ የተጻፈውስ ያው ሰንበት ሰባተኛው ቀን መሆኑ ብቻ ነው፡፡

እንደገናም እንዲህ ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል፦ በአዲስ ኪዳን በየትኛው መጽሐፍ ነው የሳምንቱን የመጀመሪያ ቀን አክብሩ የሚል ቃል የተጻፈው? ለዚህም ምላሹ አንዱም ጋ አልተጻፈም የሚል ነው። ግን እንዲህ የጠየቁ በምላሹ እንዲህ ሊጠየቁ ይችላሉ፣ «በአዲስ ኪዳን ውስጥ የቱ ጋ ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት ቅዳሜትን /ሰንበትን/ እንዲጠብቁ ወይም እንዲያከብሩ አዘዙ?» ምላሹ አንድም ቦታ አልጠቀሰም፣ አላስተማሩምም። ይልቅስ፣ ታዋቂው ዶክተር ቶሪ ሰንበትን አስመልክቶ ያሉትን ለማብራሪያነት ልጠቀምበት፣ «አዲስ ኪዳን ሁሉንም ትእዛዛት በብሉይ ኪዳን ከነበራቸው አጠቃቀም በጠነከረ መልኩ ጸንተው ተግባራዊ እንዲሆኑ አጽንቶ፣ ሳያጸናው ሳያነሣሣው የተወው ግን ከአሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ሰንበትን ብቻ ነው፣» በማለት ለመረጃ የሚከተሉትን ጥቅሶች ዘክረዋል፦ ሮሜ 13፡8-10፤ ኤፌሶን 6፡1፣2፤ ያዕቆብ 5፡12 እና 1ኛ ዮሐንስ 5፡21። እነኚህ ሁሉ ቅዳሜት ክርስቲያኖችን ሊያስራቸው እንዳልተገባ ያበስራሉ።

3. ምስክረ ቤተኛ

ዲ. ኤም. ካንራይት ለበርካታ ዓመታት የሰባተኛ ቀን /ቅዳሜት/ አክባሪ ነበሩ። ኋላ ላይ ግን ቃሉን ቃሉ ሲፈታላቸው፣ ከነበሩበት ባንነው ኮበለሉ። አስከትዬ የእርሳቸውን «ማን ይመስክር? የነበረ፤ ማን ያርዳ? የቀበረ» እንዲሉ ሰውየው ያስነበቡትን አንብቡልኝ፤

> «ለሃያ ስምንት ዓመታት ሰንበትን ጠበቅኩኝ፤ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ደቀ መዛሙርት ሰንበትን እንዲጠብቁ አደረግሁ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ በጥቅስ፣ ፊደል በፊደል፣ መስመር በመስመር በጥንቃቄ ከሃያ ጊዜ በላይ አነበብኩ፣ ሰንበትን አስመልክቶ ለሚነሡ ጥያቄዎች ሁሉ አጥጋቢ መልሶችን እኔ ይገፍ ሌሎችንም አስያዝኩ፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥንታዊ ወጥ ጽሑፎችና በርካታ ትርጉሞችን አጠናሁ፤ የሰዋስው ጥናትን፣ መድበለ ቃላትን፣ የመዝገብ አስተያየቶችን፣ የቃላት መፍቻን በአግባቡ አጠናሁ፣ እስከ ጥጉም ለመድረስ እንደ እኔ የሰንበት አክባሪዎችንም ሆነ የጌታ ቀን /እሑድ/ አክባሪዎችን የውዝግብ እሰጥ አገባ መረመርኩ። የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶችንም ሥራ ፈተሽኩኝ። በውጤቱም በርካታ መጻሕፍትን በሰንበት /

ቀዳሚት/ ላይ ጻፍኩኝ። አንባቢዎቼም ረኩባቸው፤ ዳሩ ግን በፍጻሜው እንዲሁ ሆነብኝ። ቃሉንም ሆነ የተቀሩት መረጃዎች ሁሉ ቀዳሚትን እንድንጠብቅ የሚያደርገን ሆኖ አላገኘሁትም» የሚለውን ቃላቸውን ሰጡ።

4. ምስክረ አዲስ ኪዳን

የካንራይት ምስክርነት ይህ ሆነ፤ የጌታ ቃል ግን ጠንካራ ተጨማሪ መረጃ ገና አለው። ሰንበት ለአዲስ ኪዳን አማኞች ያልተደነገገ ስለ መሆኑ የጳውሎስን መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች አሥራ አራተኛውን ምዕራፍ ይመልከቱ፣ «... አንዱ ቀን ከሌላው ቀን ይበልጥ ክቡር ነው ብሎ የሚያስብ ይኖር ይሆናል፤ ሌላው ደግሞ ቀኖቹ ሁሉ እኩል ክብር አላቸው እንጂ፣ በቀኖች መካከል ልዩነት የለም ብሎ ያስባል» በማለት ትንተና ይሰጣል። ይህንኑ በማጐልበት ራሱ ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች ሲጽፍ፣ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ፣ በዓላትን ወይም የወር መባቻን፣ ወይም ሰንበትን በማክበር ምክንያት ማንም አይፍረድባችሁ። እነዚህ ሁሉ ወደፊት ይመጡ ለነበሩት ነገሮች እንደ ጥላ ናቸው፤ እውነቱ የሚገኘው ግን በክርስቶስ ነው» (ቈላ. 2:16-17) በማለት የክርስትና ማዕከል ክርስቶስ እና የክርስቶስ ሥራ መሆኑን በመነሻው አበሰረ።

ለመሆኑ ሰንበት ከአሥርቱ ትእዛዛት በፊት የነበረ መሆኑን ያውቃሉ? እርሱ ብቻ አይደለም፣ ግዝረትም ጥንታዊነት አለው። እነዚህ ሁለቱ ከሙሴ በፊት ነበሩ። ለምን? ቢሉ ከአብርሃምና ከአብርሃም ዘር ሐረግ በተያያዘ ጉዳይ ለምልክትነት ተሰጥተው ነበርና።

በዘፍጥረት 17:9-10፣ 12-13 ግዝረትን አስመልክቶ፣ «... አንተና ከአንተም በኋላ የሚመጣው ዘርህ ከእኔ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን ከትውልድ እስከ ትውልድ ጠብቁ... የምትጠብቁት... በመካከላችሁ ያሉት ወንዶች ሁሉ መገረዝ አለባቸው... በስምንተኛው ቀን ይገረዝ። ቃል ኪዳኔ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር የሚኖር መሆኑን የሚያሳይ የሥጋ ምልክት እንዲሆን እያንዳንዱ ወንድ ይገረዝ።» ይህ ለአብርሃም ዘር ብቻ ለእስራኤላውያኑ የተሰጠ የቃል ኪዳን ምልክት ሆነ፣ ለሌላ ለማንም አልተደነገገም። ድንጋጌው እንደ

ዘዳግም 10:16፤ 30:6 መሠረት እስራኤላውያን ልበ ደንዳናነትንና እልኸኛነትን አስወግደው ለጌታ ክብር እንዲውሉ ማብቃት ነው። በአዲስ ኪዳን በገላትያ 6:15 እና ቄላ. 2:11 በብሉይ ኪዳን በስምንተኛው ቀን መገረዝ የአሮጌው ተፈጥሮ ውክልና መሆኑ ተገልጿል። ዛሬ ግን አዲስ ኪዳን በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ወይም በስምንተኛው ቀን ከኢየሱስ ትንሣኤ የተነሣ «... ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም፤ ምክንያቱም መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ምንም አይጠቅምም የሚጠቅመውስ አዲስ ፍጥረት መሆን ነው...» ተበሰረ። አስከትሎም፣ «... ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን ተገርዛችኋል ይህም መገረዛችሁ ኃጢአተኛውን ሥጋ ለማስወገድ በክርስቶስ የተደረገ ነው እንጂ ሰው ሠራሽ መገረዝ አይደለም...» በማለት የብሉይ ኪዳን ግዝረት ቢያስፈልግም፣ ለእስራኤላውያን እንጂ በክርስቶስ ለታመንን ለእኛ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ልክ እንዲሁም ሰንበትም ተመሳሳይ ግጥምጥሞሽ አለው። ለእስራኤላውያን የዘለቄታ ምልክት ሆኖ ተሰጠ፤ በዘፍጥረት 31:12-17 እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው፣ «ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው የእረፍት ቀን አድርጌ የመረጥሁትን ሰንበትን ጠብቁ... ይህ በእኔና በእናንተ መካከል ጸንቶ የሚኖር ምልክት ነው... የእስራኤል ሕዝብ ይህን ቀን ጸንቶ የሚኖር የቃል ኪዳን ምልክት አድርገው ይጠብቁት እርሱም በእኔና በእስራኤል ሕዝብ መካከል ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ምልክት ይሁን... ከሥራዬ ያረፍኩበት ዕለት ነውና።» ይህ ትእዛዝ እግዚአብሔር ሰንበትን ከእስራኤላውያን ጋር እንዳስተሳሰረው ወይም እንዳቆራኘው ያረጋግጣል። ትሥሥሩን ግን ከእስራኤል ዐመፀኝነት የተነሣ እርሷን በመተው በቤተ ክርስቲያን በኩል ሥራውን ሲቀጥል ሰንበትን መጠበቅ ተፈላጊነቱን አጣ። ለምን? ቢሉ ቤተ ክርስቲያን፣ እስራኤላዊ፣ ግሪካዊ (አሕዛብ)፣ አገልጋይ፣ ጌታ፣ ወንድ፣ ሴት፣ ሳትል ሁሉንም የምታገለግል ሆነች (ገላ. 3:28)። አሕዛብም ለእስራኤላውያን በተሰጡ መርኖዎች መገዛት ቀረላቸው፤ ይህም ሐዋርያት በሐዋርያት ሥራ 15:28-29 ሰንበትን ትተው ውሳኔዎችን እንዲያሳልፉ ሆኑ።

5. ምስክረ በዓለ ኀምሣ

የፋሲካንና የቂጣ በዓልን አንሥቼ እንዴት የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን ለእሑድ ለጌታ ዕለት እንደ በቃች መረጃ ልጨምር፣ ያው ቃሉ ቃሉን ተርጉሞ፤ ዘሌዋውያን 23:9-21 ይመልከቱ::

«...የመጀመሪያውን ነዶ ለካህኑ ትሰጡታላችሁ፤ እግዚአብሔር ይቀበላችሁ ዘንድ ካህኑ ነዶውን ወደ ላይና ወደ ታች በመወዝወዝ ለእግዚአብሔር ልዩ መባ አድርጎ ያቀርባል፤ ካህኑም እርሱን ማቅረብ ያለበት <u>ከሰንበት ቀጥሎ በሚውለው ቀን ነው</u>... ልዩ መባ አድርገህ ካመጣህበት ሰንበት ማግሥት ጀምሮ ሰባት ሳምንት ቁጠር <u>ከሰባተኛው ሰንበት በኋላ በሃምሳኛው ቀን</u> እንደገና የአዲስ እህል ቁርባን ለእግዚአብሔር ታቀርባለህ... አዲስ መከር ለእግዚአብሔር የበኩራት መባ ሆኖ ይቅረብ... <u>በዚያን ቀን ለአምልኮ ተሰብሰቡ</u>::»

የተሰመረባቸውን ዓረፍተ ነገሮች መለስ ብሎ ማጤን ግድ ነው:: ሕዝቡ የነዶአቸውን መጀመሪያ ለእግዚአብሔር ነበር የሚያቀርቡት፤ ካህኑም ነዶአቸውን ይዞ የሚቀርበው በሰንበት / በቅዳሜ/ ማግሥት ነበር-እሑድ:: ይህም ከቀረበ በኋላ ከሰባተኛው ሰንበት በኋላ በማግሥቱ በሃምሣኛው ቀን፣ እሑድ ማለት ነው፣ የአዲስ የእህል ቁርባን ለእግዚአብሔር ያቀርባል፤ እናም በዚሁ ዕለት ሕዝብ ሁሉ ለአምልኮ ይሰበሰባል /በሰንበት ማግሥት/ በእሑድ:: ብሉይ ኪዳን የፋሲካንና የቂጣን በዓልን እንዲህ ነው ያሰፈረው:: በአዲስ ኪዳንም ፋሲካን ስናስብ በእሑድ ዕለት «ክርስቶስ ለሞቱት ከሞት የመነሣት የመጀመሪያ ምሳሌ ሆኖ በእርግጥ ከሞት ተነሥቷል» ይለናል (1ኛ ቆሮ. 15:20)::
እንግዲያስ በዚህ እሑድ /የሰንበት ማግሥት/ በአዲስ ኪዳን ላይ ምን ምን ነገሮች በዋናነት ተዘከሩ? ሴቶች ወደ ጌታ መቃብር ሄዱ፤ ኢየሱስ ሞትን ድል ነስቶ ተነሣ፤ አሮጌው ነገር ሁሉ አልፎ በአዲስ ሕይወት ተተካና ሁሉም አዲስ ሆነ፤ ይህ ብቻ አይደለም እሑድ ዕለት የሚውለው፤ በዘሌዋውያን መጽሐፍ የተገለጸው የበዓለ ሃምሳን አከባበር በአዲስ ኪዳን ላይ በዋናነት ተዘክሮ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ ይነሣል:: በዕለቱ ታላቅ ተአምር ሆነ፤ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት፣ እርሱ ሲመጣ ስለ እኔ ይነግራችኋል (ዮሐ.

16:15)፣ ያስተማርኳችሁንም ሁሉ ያስታውሳችኋል የተባለለት እርሱ መጣ። መጥቶም ማቴዎስ 28:19-20 እና ሐዋርያት ሥራ 1:8ን ተግባራዊ ሊያስደርግ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ሊያድር፣ ሊያትም፣ በእሑድ ዕለት የአሠራር ለውጥ ሆነ፤ እርሱ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድም ሰዎችን ያስረዳል የተባለለት ነውና ለቤተ ክርስቲያን ዋንኛ ሲሆን፤ ሥራውን እሑድ ዕለት ገለጠ፣ በበዓለ ሃምሣ። እኛም የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ የተሻለ አጽናኝ የለንምና የአዲስ ሕይወት ጅማሬ በሆነው እሑድ ልክ በብሉይ ኪዳን በዘሌዋውያን 23:2 መሠረት በዚያን ቀን ለአምልኮ ተሰበሰብን፤ እየተሰበሰብንም ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰንበትን አስመልክቶ ሲናገር፣ «ሰንበት ለሰው ተሠራ» አለ። ይህም ማለት ለሰው ዘር ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ያመለክታል። በስድስቱ ቀናት ጥሮ ግሮ ለፍቶ ከርሞ በአንደኛው ቀን ግን አካላዊ ዕረፍቱንና መንፈሣዊ ኅብረቱን በተመለከተ «እርፍ» ይልበት ዘንድ ፈቀደ። ይህንንም ሰንበት እስራኤላውያን ከመምጣታቸው በፊት ለሰው መበጀቱ ላይ ተመርኩዞ አስተማረ (በዘፍጥ. 2:3)። ይህም ለሰው ልጅ ጥቅም ይውል ዘንድ ነው፤ ዛሬ በዓለም ላይ ያሉ ሠራተኞች ከሳምንቱ በአንዱ ቀን ያርፋሉ፤ ይህም ጌታ እንዳለው ሰንበት ለሰው ጥቅም መሆኑን ያሳውቃል። ጌታ በነበረበት ዘመን ግን፣ «ሰው ለሰንበት የተፈጠረ እንጂ ሰንበት ለሰው የተሠራ» አይመስልም ነበር። በዚህ ዘመን ደግሞ በቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ የጌታ ቀን ወይም እሑድ ቀደም ብሎ እንደተዘረዘረው ለአምልኮ የመሰብሰቢያ፣ በኅብረት የመጸለይና የጌታ እራትን የመውሰጃና ክርስቲያናዊ ኅብረትን የመፈጸሚያ ቀን መሆኑ ቀርቶ በብዙዎች ዘንድ እሑድ የስፖርት ቀናችን፣ የመዝናኛ ዕለታችን፣ የእድርና የእቁብ መሰብሰቢያችን፣ የርቀት ጉዞ መጀመሪያችን ወይም ሠርተን ጥቂት ገንዘብ ማግኛ ሁነኛ ሲሳያችን እየሆነ መምጣቱ ሳያስደነግጥ አልቀረም።

አንድሩ የተባሉ መጋቢ በዚህ ጉዳይ ሰግተው እንዲህ አሉ፣ «አሮን የሕዝቡን ጥያቄ በመቀበል «ነገ ለእግዚአብሔር ክብረ በዓል ይደረጋል» በማለት አሳውቆ... ሕዝቡ የግብጣ ዝግጅቱን አጠናቆ ተሳከረ፣ ሊዘፍንም ሊዝናናም ተነሣ፣ በወርቅ ጥጃቸው ዙሪያ

እያሸበሸቡ (ዘጸአ. 32) ፎለሉ። ይህም እግዚአብሔር ካቀደው አሳብ ፈጽሞ የራቀ ነበርና ቅጣትን አስከተለ። እናም አማኞች በጌታ ቀን ከጌታ የበለጠ ነገር ባይኖራቸው የተሻለ ነው» በማለት ስጋታዊ ማስጠንቀቂያቸውን አሳውቀዋል።

ዶ/ር አር. ኤ. ቶሪም፣ «በጌታ ቀን በቤተ ክርስቲያን በመገኘት የሐዋርያት ትምህርትን በማድመጥ በኅብረት እንጀራ በመቁረስ፣ በጸሎትና በወንድማማቻዊ ኅብረት ማሳለፉ አንዳንዶች እንደሚሉት በሕግ ሥር መሆን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን መልካም ዕድል ተጠቃሚ መሆን ነው። ሰው መንፈስና ነፍስ እስካለው ድረስ መታደስ፣ ከጌታ ጋር የሰመረ ኅብረት መፍጠርና በእርሱ በማረፍ ጌታን ማገልገል አለበት። ይህንንም በስፋት የሚጠቀምበት ቀን እሑድ ነው፤ አልያም፣ የመንፈሣዊ ሕይወት ድህነቱን ያሳድጋል» በማለት የጆሮ ያለው ይስማን መልእክት አስተላልፈዋል።

እኔም ደግሞ፣ የምታድግ ቤተ ክርስቲያን አባላቷ ሁሉ በጌታ ቀን በኅብረት ለመሆን ወደው በመሰብሰባቸውና የጌታንም ፈቃድ ሲፈጽሙ በመታየታቸው ትታወቃለች እላለሁ። እናንተስ ምን ትላላችሁ?

«እርቃኑን የቆመው ትውልድ»

ለዚህ ጽሑፍ መነሻዬ፣ «አንብቡኝ» የሚለው ርእስ ነው- «ውስጡ የተዘረፈበት ትውልድ» ይላል። ጽሑፉን ያገኘሁት በቁጥር 35 ሕይወት መጽሔት የፊት ሽፋን ላይ ነው፤ ጸሐፊው ምን ሊል ይሆን? እንዴትስ ሊሆን ይችላል? ሕሊናዬ ገና ጽሑፉን ሲያየው የሞገቱት ጥያቄዎች ናቸው።

ደራሲ አማረ ማሞ፡- ማራኪ ርእስ እንደ ቀይ የትራፊክ መብራት ይመስላል ይላሉ፤ መብራቱ የሚፈጥን መኪናን ያስቆማል፣ እንዲሁ ያየሁት ርእስ አስቁሞ ገላልጬ እንዳነበው አስገደደኝ፤ ዘልቄም መልእክቱን ተረዳሁት፤ ጥሩ ነበር፤ እንዳንጓጓኝ ግን እፎይታን አልሰጠኝም፤ አላረካኝም።

እናም ያለመርካቴን ምክንያት ከኅብረተሰቡ አኳያ ይህንን

ትውልድ በመጠኑ ልቃኘው ፈለግሁ።

ትውልድ እንደ ሰንሰለት እየተያያዘ የሚቀጥል ሕዝብ ነው። በሩጫ ሜዳ ላይ እንደሚታየው የዱላ ቅብብልም ሊቀበል ተዘጋጅቶ ላለው ዱላውን የያዘው፣ ሊይዝ እተዘጋጀው ጋ ደርሶ የሚያቀብለው የቅብብል ጨዋታ ነው። እናም ስለ ዛሬው ትውልድ ለማውራት የቀደመውንና ሊመጣ ያለውን አገናኝቶ ማዋቀር ይገባል።

አያይዞም ትውልድን መዝረፍ ካለ ዘራፊ አለ። ዘራፊ ካለም የሚዘረፍ ዋንኛ ነገር አለ ማለት ነው።

ትውልድ በትውፊቶች ክምችት፣ በትምህርት ክትትል፣ በመንፈሳዊ እውቀትና በአጠቃላይ ግንኙነቶች ይገነባል። በውስጡ የሚሠርጸውን የማንነት ምንነት ጠብ ጠብ እያለ ዓለትን ሊሸረሽር እንደ በቃው ውኃ እነዚህም ከውልደት ዘመኑ ጀምሮ ይዘልቁበታል፣ ይኖሩበታል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ጎብረተሰቡ ሊኖረው የሚገባው ተቀባይነት ያለው አመለካከትና የሕይወት አቅጣጫዎች በአልባሌ ነገሮች ከተተ ኩ ወይም ከተወገዱ ዝርፊያ ተካሄደ ማለት ይቻላል። ለአባባሌ መጠነኛ ገለጻ ልስጥ፡-

ለዚህም ከመደበኛ የትምህርት ዘርፍ አልፈው የሚመጡትን እንቃኝ። እንደ ዋንኛ ሳይንሳዊ ግኝት ተቆጥሮ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ከምናየው የሥነ ሕይወት ዘርፍ ውስጥ ዝግመተ- ለውጥ ዋንኛው ነው። ዳርዊን የሰው ልጅን የአመጣጥ መለኮታዊ ድርሻ በመሻር፣ ያለ እግዚአብሔር መገኙቱን የሚያረዳው ትምህርት ነው። ይሄ ጥናት ትውልዱ ያለ እግዚአብሔር መቆም እንደሚችል፣ የእግዚአብሔር መኖርም አላስፈላጊ እንደ ሆነ፣ ሰውም ተጠያቂ ሊሆን አለመቻሉን ለግንዛቤ ያበቃል። በዚህም ኃጢአትና በኃጢአት መጠየቅ ትርጉም- አልባ ሆነዋል። ይህ ጤናማነት የጎደለው በንድፈ አሳብ ደረጃ ያለውና መሰል ትምህርቶች ትውልዱ ከእግዚአብሔር ላይ ዓይኑን አንሥቶ በሌላ መደገፍን በማላመዱ የመዘረፉ አንዱ ምልክት ነው።

አስከትለን በመንፈሳዊ ጉዳይም ላይ ቅኝት እናድርግ። ብዙ ሕዝብ ስለ እምነቱ ምላሽ እንዲሰጥ ሲጠየቅ የሚያጣቅሰው በራስ

በመተማመን ልኩ ይሄ ነው የሚል ጽኑ መልስ ሳይሆን፣ «ያባት የናቱ ሃይማኖት» የሚል አይደለም? እርግጥ ፈቅ አለማለት ተገቢ የሚሆንበት ጊዜ አለ። እርሱም በእውነት የያዝኩት በመቆም እውነትን ይዞ የተቀባበሉት በትር ከሆነ ምላሹ ተገቢ ነው፤ አልያ ግን፣ «የክርስትና እምነት ተከታዮች ነን፣ በዚህም ሺህ ዓመት አስቆጥረናል» የሚለው ንግግር እኔ ማን ነኝ? እግዚአብሔር ከእኔ የሚጠብቀው ምንድን ነው? ለሰዎች ጥቅም የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ምላሽ አለው? የተሰኙትን መሠረታዊ ጥያቄዎች መመለስን አልቻለም። ይልቁኑ፣ ትውልዱ የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት ሳይሆን፣ መደብደብን፤ እግዚአብሔር ያለውን ሳይሆን፣ ወግን በመከተል የመዝለቅ ቀናዊነትን ያደላድላል፤ ይህ ደግሞ የሚያሳየው ሌላውን የመዘረፍ ገጽታ ነው።

በማኅበራዊ የሕይወት ጉዳይም ላይ አጽንኦት ከሰጠን በመላው ዓለም እየተናኘ በአገራችንም ዋንኛ ከተሞችና በጎበረተሰቡ ውስጥ የተከበሩ ቤተሰባዊ ጉዳዮች ተራቁተው ለአደባባይ ቆመዋል፤ ሲቆሙም ልክኛ እንደ ሆኑ በጎ ትርጓሜና ሳይንሳዊ ትንታኔ እየተሰጣቸው ነው። ለምሳሌ፣ ውርጃ «ግድያ ሳይሆን፣ ያልተፈለገን ጽንስ ማስወገድ» ሲሆን፣ በጥቅሙም «በምድር ሕይወቱ በጉስቁልና ሊኖር ያለውን ከማምጣት መሸኘት፣ ከትዳር ውጭ በመጸነሱ ለተጋቢዎቹ መጪ ሕይወት ደንቃራ የሚሆነውን ከማምጣት ማስቀረት» እንደ «ጽድቅ» ይቆጠራል፤ ሽልም በማሕፀን እስካለ ሙሉ ስብእና የለውም የሚለው አሳቤም በተቀባዮቹ ዘንድ ተወዳጁ ነጥብ ነው። በእነዚህ አስተያየቶች መሠረት፣ «ጽንስን ማጨናገፍ የማያስፈልግ ጥርስን ነቅሎ ከመጣል እኩል እየሆነ መጥቷል።» ይህም ሂደት እንደ ሌላው የትውልድ ዝርፊያ ይቆጠራል።

በትይዩም የሰዶማዊነት መስፋፋት፣ የወንድ ከወንድ፣ የሴት ከሴት የተራክቦ ግንኙነት ለመፈጸም መዳፈር ሳይንሳዊና ቅቡልነት የጎደለው መንፈሳዊ ትንታኔ ተሰጥቶት በዚሁ ትውልድ ተናኝቷል። ከሳይንሱ ምልከታ ዋንኛው የሴት ሆርሞን የበዛባቸው ወንዶች ሴታዊ ባሕሪን ስለሚያበዙ፣ እንደ ወንድ ሳይሆን እንደ ሴት ሆነው እራሳቸውን ያስገዛሉ፤ ከዚህም የተነሣ ወንዱ በራሱ «ሴት

ሆኗልና» ለወንዱ እንደ ሚስት ሆኖ ሊያገለግል ይፈቅዳል፤ እናም ትውልዱ ይሄን መከልከል ተገቢ አይደለም ይላል። ጥቅስንም አለሰፈሩ ሊጠቅሱ የሚወዱ «መንፈሳዊያን ነን» የሚሉቱም ዳዊት በዮናታን ፍቅር ሰክሮ «ከሴት ፍቅር ይልቅ ፍቅርህ ለእኔ ግሩም ነበር» (2ኛ ሳሙ. 1፡27) የሚለውን ጥቅስ በመውሰድ ከጠዋቱ የነበራቸው ግንኙነት «ሶደማዊ» ነበር ይላሉ፣ ከዚህም ተነሥተው የባልና ሚስትን ግንኙነት ያረክሱታል፤ ይህም ሌላው ትውልድን መዝርፍ ነው።

በቅርቡም በዐውደ ትንቢት ጋዜጣ ላይ የተዘከረው የክሎኒንግ ሳይንሳዊ ውጤትም በትውልድ ዝርፊያ ውስጥ ይካተታል፤ ክሎኒንግ ሰውን እንደ ችግኝ፣ የማፊያ ዘዴ ነው። ያለ ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሰውን ለማስገኘት ወይም ለማባዛት ይጥራል፤ የጥናቱ ዋንኛ አቀንቃኝ ዶ/ር ሪቻርድ ሲድ፣ «ይህን በማስገኘት ከእግዚአብሔር ጋር መተካከላችንን» እናስመሰክራለን ብለዋል። ይህ ዘመቻ እግዚአብሔርን በማውጣት በራስ መመካትን ያራምዳል፤ ይህም ትውልድን መዝረፍ ነው።

በመጨረሻም፣ የትውልድ ዝርፊያ ሊታይ ያለበትን አስደንጋጭ ክልል በማንሣት ልደምድም- የዓለምንና የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናትን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን አስተማረ፣ እንዲህም አለ፣ «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ... ትውልዱን አጣፍጡት፤ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ... ጨለማውን ግለጡት» በማለት የክርስቲያኖችን ድርሻ አሳየ። ሊሆን የሚገባው የክርስቲያናት ኃላፊነት ይኸው ነው፤ ይኸን ደግሞ ለመፈጸም ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ሆኖ መገዛት፣ ያንንም ማስተላለፍ ግዴታ ነው። ብዙዎች ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት ግን ሊቤዥ የሚገባውን ትውልድ ባለመድረስ በየራሳቸው ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች እየፈጠሩ ነው፤ እርሱም ለተገለጠውና ለተጻፈው ለእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ አለመገዛት ነው፤ ይልቁኑ፣ በምትኩ በስሜቶቻቸው ላይ በመደገፍ መመራትና መምራትን ያዘወትራሉ፣ ይኽ አስጊው ነው።

አስጊነቱ ክርስቲያኖችን በቀጥታ መመልከቱ፣ ምልከታውም እየተዘረፈ ያለውን ትውልድ ሊደርሱለት የሚችሉት ቀዳሚ

ባለአደራዎች እነርሱ መሆናቸው ነው፤ አስቀድሞ እራሳቸውን በማ
ረም እየተራቀተ ያለውን ትውልድ በእግዚአብሔር ቃል ሊመሩት፣
ሊሞሉት ይገባል፣ ወንጌል መፍትሔው ነው፤ ይኽ ትውልድ
የእግዚአብሔር አሳብ በሕይወቱ ምን እንደ ሆነ አላወቀም፤ ያውቅ
ዘንድ ያስፈልጋል። በዘላለም ዕቅድ ውስጥ ላሉት ሊደርስ
የሚገባውን የምስራች ቃል ይዞ መቅረብ የሁላችንም ኃላፊነት
ነው።

«ይልቁኑ ብዙ ከተሰጠው ሰው ብዙ ይፈልግበታል፤ ብዙ
ዐደራም ከተሰጠው ሰው፣ ብዙ ይጠበቅበታል» (ሉቃስ 12:48፣
ቀ.አ.) የጌታ ማሳሰቢያ ነው። ብዙ የሰበሰባችሁ በመራቆት ላይ
ያለውን ትውልድ ድረሱት፤ በመግቢያዬ ላይ ትኩረቴን ሳበው
ያልኩት ርእስ «ውስጡ የተዘረፈበት ትውልድ» የሚል ነበር፣ እኔ
ግን ለዘከርኩት ቅኝታዊ ማሳሰቢያ «እርቃኑን የቆመው ትውልድ»
ልለው ፈልጌያለሁ። እርቃኑን ደግሞ ከቆመ፣ በወንጌል ደርሰን
ከእግዚአብሔር የሆነውን ልብስ እናልብሰው።

ትውፊት እና «የእኔ ድርሻ»

ብዙ መልካምና ክፉ ነገሮች ከእጃችን ላይ ያረፉት በአንድ
መንገድ ነው- በቅብብሎሽ።

በዚህም መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተቀብለን
የምናቀብለው ባህላችንን ነው። ባህል ኑሮ ነው፤ ማንነት።
አኗኗራችን የተቀየሰበት ወይም የጠፋበት፣ አስተሳሰባችን የለዘበበት
ወይም የከረረበት፣ የነገ ዕይታችን ግልጽ ያለበት ወይም የደነዘበት
የውጤት መነሻ ባሕል ነው።

ትውፊት ደግሞ የዚህ አካል ነው። አንዳንዶች ትውፊትን ሥነ-
ቃል ይሉታል፤ በትርጉሙ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመዝገበ
ቃሉ ላይ እንዲህ ያብራሩታል፣ «... ልማድ፣ ትምህርት፣ ወግ፣ ታሪ
ክ፣ ሃይማኖት፣ ሥርዓት ከጥንት ከአበው ሲያያዝ ሲወርድ ቃላት
በቃል ሲነገር የመጣ» (ገጽ 396)። በዚህ ፍቺ ውስጥ ሊሰመርበት
የሚገባው «ቃል በቃል ሲነገር የመጣ» የሚለው ነው። ትውፊት

ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ተላላፊዎቹ ምሳሌዎች፣ አባባሎች፣ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ እንካ ሰላንቲያዎች፣ ቀልዶች፣ ዘፈኖች፣ መዝሙሮች፣ ስሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሁሉ የዚህ ክፋይ ናቸው።

እነዚህን ነው እንግዲህ በዚህ ጽሑፍ በመነካካት፣ «የእኔስ ድርሻ» በማለት ለመጻፍ የፈለግኩት። መቼም አንድ ነገር ቃል በቃል ተላለፈ ሲባል መነሻው ከየት ይሆን ብሎ ማሰብ ግድ ነው። ለዚህ ይረዳኝ ዘንድ ራሳችሁን የዛሬ ሰው አድርጉና ወደ ኋላ፦ አባት፣ አያት፣ ቅድመ - አያት፣ ቅም አያት፣ ሽማት፣ ምዝላት፣ እንጅላት በማለት የተቀባበልናቸውን ሁሉ ነገሮች በየዘርፋቸው ለአፍታ እዩ። ከዚያም በስሞችና ባሉን ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ አተኩሩ። ስሞቻችን ምን ፍችን በውስጣቸው ይዘዋል፤ በእልፍ ምሳሌያዊ አባባሎቻችን ውስጥሳ ስንቱ፦ ቅርባችንን አሳይተውን እነርሱው ሰፍተው እሩቁን አስመለከቱን? አይሁዳውያን በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ተስፋ፣ መደገፍ፣ መዳኘት፣ መደመጥና፣ ጥንካሬ የሚገልጹት በስሞቻቸው ላይ ነው። እስቲ በዕብራይስጥ እግዚአብሔር የሚል ፍቺን የያዘው «ኤል» በስርወ ቃሉ ፊት እና ኋላ በመምጣት እንዴት የእግዚአብሔር ማንነት እንደ ተገለጸበት ልብ በሉ።

ኤል ሻዳይ	እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።
ኤል ኤዜር	እግዚአብሔር ረዳቴ ነው።
ኤል ያስ	እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው።
ኤል ሳህ	**እግዚአብሔር** መድኃኒቴ ነው።
ኤል ሳቤት	**እግዚአብሔር** ኪዳኔ ነው።
አማኑ **ኤል**	እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው።
ዳን **ኤል**	**እግዚአብሔር** ዳኛዬ ነው።
ሳሙ **ኤል**	እግዚአብሔር ይሰማኛል።
ሕዝቅ **ኤል**	**እግዚአብሔር** ያጠነክራል።
ሚካ **ኤል**	እንደ **እግዚአብሔር** ያለ ማን ነው?

እነዚህ ከላይ በምሳሌነት የተነሡት ስሞች በትርጉም ውክልናቸው ሕያው እግዚአብሔርን በትክክል በመግለጽ

የአስታዋሽነትን፣ የመጽናናትንና የመጽናትን ሕይወት ይቸሩናል። የየስሞቹም ድምር ፍቺ «ልዑል እግዚአብሔር ብቻ» መሆኑን ያስተምራሉ።

ይህ በአይሁዳውያኑ ዘንድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ምሥጢርን አዝሎ እየተላለፈ የመጣው ስም በኢትዮጵያውያኑ ዘንድም በተ መሳሳይ መልኩ ሲዘልቅ ይታያል፦

እስቲ እነዚህን ስሞች ልብ ይበሉ፡

ያለው ላይቀር - የእግዚአብሔርን ታማኝነት
ማን ያዘዋል - የእግዚአብሔርን ልዑልነት
ምን ተስኖት - የእግዚአብሔርን ቻይነት
ማን ተጋፍቶት - የእግዚአብሔርን ታላቅነት
ማን አክሎህ - የእግዚአብሔርን በላይነት. . . ያሳያሉ።

እነዚህን የመሰሉ ስሞች ናቸው፣ ወላጅ ለልጅ እየሰየመ ሕያው እግዚአብሔርን የሚተርክበትና «እርሱ ራሱን ያለ ምስክር አለመተ ዉን» የሚገልጹበት የቃል በቃል በጎ ርክክብን በመሆን የሚያገለግሉት።

ልክ እንዲሁም በመኖር እየተፈተሹ በልክነት ያለፉ ምሳሌያዊ ንግግሮችም የትውፊት ሀብቶቻችን ሆነው የእግዚአብሔርን ማንነት ይገልጹ ዘንድ የደረጁ አባባሎች አሉን። እስቲ ተከታዮችን ልብ ይበሉ፦

- እግዚአብሔር ሲጥል እናት አታነሣም = (የእግዚአብሔር አሳብ አለመለወጡን)
- ለምን ላለው ስልቻውን፣ ጫን ላለው ኮርቻውን አይነሣውም = (የእግዚአብሔር አቅራቢነት)
- ላይሞት ይፈራል፣ ላይድን ይሸሻል = (የእግዚአብሔርን ቅድመ - ውሳኔ)
- ሰው ያስባል፣ እግዚአብሔር ይፈጽማል = (የእግዚአብሔርን አድራጊነት)
- በማን ላይ ተቀምጠሽ እግዜርን ታሚያለሽ = (የእግዚአብሔ ርን ሰሚነት)
- በእግዜር ቢቆጡ በጨለማ ቢያፈጡ ምን ያምጡ =

(የእግዚአብሔርን ልዑልነት)

- ተሸፋፍነው ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ = (የእግዚአብሔርን አዋቂነት)
- አንተ አብጀው አስቤም አልፈጀው = (የእግዚአብሔርን ፈጻሚነት)።

እንግዲህ በስሞች ዙሪያና በምሳሌዎቻችን ዙሪያ እግዚአብሔር ከተገለጠ በፍቺው መደነቅ ብቻ ሳይሆን፣ ለትርጉሙ መታዘዝ ልከኛው መርጎ ይመስለኛል። በእኔ እምነት ከትውፊት በጎ በጎውን እንዲህ እያሸጋገሩ ተጠቃሚ መሆን ደግ ነው።

ግላዊ የነፍስ ነጻነት

በነገራችን ላይ «ፍጹም» የሆነች ቤተ ክርስቲያን በስተማችን አለችን? ምላሹ እንጃ! ወይም የለችም ነው። ይህ ማለት ግን ለተ ገለጠው ለእግዚአብሔር ቃል በመገዛት በዚያም አስተምህሮ በመመራትና በመኖር የምትገለገል የተሻለች ቤተ ክርስቲያን የለችም ማለት አይደለም። ከሌሎች መሻል በምን በምን ከተሰኘ? ለስን ያሉትን አሥር ያህል አዲስ ኪዳናዊ መለያዎችዋን ልጠቁም፣ ሁሌ በክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስነት ላይ ትደገፋለች (ቈላ. 1:18)። በመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ ባለሥልጣንነት ላይ ትንተ ራሰሳለች (2ኛ ጢሞ. 3:15-17)። ሁሌ ድነው በተጠመቁት አማኞች ብቻ መያዟን ታስተውላለች (ሐዋ. 2:4-47)። ሁሉን በወንድማማችነት የሚይዝ ማኅበረ ምእመናዊ አስተዳደር እንዳላት ታምናለች (ማቴ. 20:24-28)። በመንግሥት ጉዳይ ውስጥ ፖለቲካዊ አቋም ይዛ ጣልቃ ባለመግባት ትጸናለች (ማቴ. 22:21)። እያንዳንዱ አማኝ ካህን መሆኑን ታጸናለች (1ኛ ጴጥ. 2:1-9)። የቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ ሉዓላዊነት በማንም አይደፈሬ መሆኑን ታደምቃለች (ማቴ. 18:15-17)። በተልዕኮዋም ወንጌልን በማድረስ አገልግሎት ላይ ታተኩራለች (ማቴ. 28:16-29)። መስተዳድሯ

በእግዚአብሔር ቃል መሠረትነት በተሾሙ መጋቢዎች እና ዲያቆናቱ መመራቱን አጥብቃ ታምናለች (1ኛ ጢሞ. 3፡1-3)። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትነት ያላቸው ሥርዓቶቿ በውሃ ጥምቀት እና የጌታ ራት መከበራቸውን ታስታውቃለች (ማቴ. 28፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 11-25)። የሰው የግላዊ የነፍስ ነጻነት ሊከበር እንደሚገባውም ታምናለች (ሮሜ 14፡5፣12)።

ርእሴ በዚሁ የጽሑፍ መግቢያ መጨረሻ ላይ በጠቀስኩት፤ «በግላዊ የነፍስ ነጻነት» ላይ አጽንኦት ይሰጣል። መቼም ሰውን ስናስበው የነፍስ፣ የመንፈስ እና የሥጋ የቅንጅት ውጤት መሆኑ ይታወሳል። መጽሐፍ ቅዱስ «መንፈሳችሁ ነፍሳችሁ፣ አካላችሁ በሙሉ... ያለነቀፋ ተጠብቆ ይኑር» ይላል (1ኛ ተሰ. 5፡23፤ ቀ.አ.)። ይህንኑ ዕብራውያን 4፡12ም ያጸናዋል። ከሦስቱ አንዱ ወይም ሁለቱ የዛሬ ጉዳያችን ነው። «ነፍስ» የሰው የስሜቱ፣ የፈቃዱና የዕውቀቱ መግለጫ ነች። ከዚህም የተነሣ ስለ ነፍስ ነጻነት መናገር ተገቢ ነው።

ነጻነት ማለት፡- ከምርኮኝነት መላቀቅ፣ ከእሥር ቤት መፈታት፣ ከባርነት ዕዳ መገላገል፣ ከአምባገነን ገዥ መለየት የሚለው ይህ አንደኛው «የነጻነት» ፍቺ ነው። በትይዩ ማኅበረሰብ ወይም መንግሥት በስምምነትና በጋራ ላጸደቀው ሕግና ደንብ በአግባቡ መገዛትም «ነጻነት» ሊሰኝ ይችላል። ሦስተኛው የነጻነት ፍቺ ያለተ ጽዕኖ አንድ ሰው እርሱ እንደ ተረዳው፤ እንደ ገመተውና እንዳመነበት ይሆነኛል ብሎ የሚወስነውን ውሳኔና ድርጊት መቀበልም «ነጻነት» ተብሎ ይጠራል።

ተፈላጊው ፍቺ የበስተመጨረሻው ነው። ክርስቲያኖች ግላዊ ነጻነት ሲሉ ይህንኑ ፍች ማጉላታቸው ነው። በተለያዩ ወቅቶች በጅምላ በሰው ልጆች ላይ የተፈጸሙ ተጽዕኖዎች እንደ ነበሩ ይታወቃል። ለምሳሌ፣ የሮማን ካቶሊክ ለተሐድሶ ልትጋለጥ እንደሚገባ በማጤን ከማርቲን ሉተር ብቅ ባለ ጊዜ ተከትሎ

የሆነው በእርሱና በተከታዮቹ ላይ ተጽዕኖና ጫና መጣል ነበር። «ካቶሊክን ያስደፈሩ ይደፈሩ፣ የዜግነት መብታቸውን ይጡ፣ ይሰደዱ፣ አለያም ካቶሊክ ሆነው ይቅሩ!» የሚል ትእዛዝ ወጣ። በፈቃደኝነት ላይ ሳይሆን፣ በግዴታ ላይ ዒላማዎቹ አነጣጠሩ። በሌ ላ ጊዜ ደግሞ የካልቪንን የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥትን የትስስር የጋብቻ ውሳኔ የሚቃወሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ለዘብጥያ በቁ፤ ኋላ ደግሞ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የእንግሊዝ አማኞች በመሰል ጉዳይ ለግዞት በቁ። በቅርቡም ኮሚኒስቶች በግላዊ የነፍስ ነጻነት ላይ ጣልቃ ገብነትን ተያያዙት፤ «የእኔን እመን፤ ቀድሞ ያመንከውን ካድ» በስፋት ተናኘ። እኒህን በመሰሉ ፈቃደኝነትን ያልተከተሉ ድንጋጌዎችን ወደ ጎን በመተው ያለ ተጽዕኖ ሰው በግላዊ ስሜቱ፣ ፈቃድና እውቀቱ ተመርቶ የሚሄድበት መንገድ ግላዊ የነፍስ ነጻነት ይሰኛል።

ይህን ነጻነት መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 14፡5-12 ላይ፣ «... እንዲሁም አንዱ ቀን ከሌላው ቀን ይበልጥ ክቡር ነው ብሎ የሚያስብ ይኖር ይሆናል፤ ሌላው ደግሞ ቀኖቹ ሁሉ እኩል ክብር አላቸው እንጂ በቀኖቹ መካከል ልዩነት የለም ብሎ ያስባል። እንግዲህ ይህን በመሳሰለው ነገር እያንዳንዱ የራሱ አስተሳሰብ ሊኖ ረው ይችላል...» ዳሩ ግን እያንዳንዱ ሰው ከልቡ ያመነበትን ያድርግ። ...ስለዚህ እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን መልስ እንሰጣለን» (ቀ.አ.) ይላል። ይህ ክፍል ማንም ሰው በሌ ላው ላይ የማሳመን አስገዳጅነትም ሆነ የመንቀፍ መብት እንደሌ ለው ይጠቁማል። መንቀፍና ማስገደድ ስሕተት የሆነው ማንም የሰውን ልብ የመለወጥ አቅምም ሆነ ድርሻ ስለሌለው ነው። የእግዚአብሔር የሆነውን የሚገልጽና የሚያሳይ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የሰው ድርሻው ማሳየት ነው፣ ክርስቲያኖች እምነታቸውን አስፈራርተው፣ አስበርግገው ወይም ዝተው፣ አሊያም ተ ለማምጠውና ደጅ ጠንተው ክርስቶስን ወደ ሰዎች ለማምጣት የየሰውን በር አይቆረቁሩም፤ በውድቅት ሌሊት ጥሩንባም እየነፉ

«ቀኑ ደርሷል» በማለት አያውኩም፤ ከመንገድም ጠልፈው «እውነት እኛ ጋ ብቻ ነው፤ የሌላው ሐሰት ነው» አይሉም፤ ጥበብ በተሞላበት ማራኪ ንግግርም ሊያሳምኑ አይጥሩም። ይህ ማለት ግን እውነት የሆነውን ብቸኛውን የመዳን መንገድ አይገልጡትም፣ አያስተምሩትም ማለት ግን አይደለም፤ ያስተምሩታል። የትምህርታቸውን ፍሬ ግን ወደ እውነት ለሚያደርሰው ለመንፈስ ቅዱስ ነው የሚተዉት፤ የእርሱ ፈቃድ ያይላልና። እናም ሰው አጥርቶ የሚያስበው፣ ቀናውንም መንገድ የሚይዘው ያለግፊት እግዚአብሔር ሲገለጽለትና ለዚያም ካበቃው ቅጽበት እንደሚጀመር ያምናሉ።

ጳውሎስ በሮሜ አሥራ አራት መልእክቱ ላይ ሁለት ሰዎች ስለ ቀናት ጽኑ አስተሳሰብ ኖሮአቸው፣ እነዚህ ሰዎች የተረዱት መ ረዳት ሊታረቅ ወይም ሊቻቻል አልቻለም። አንደኛው፣ «ለተለየ ቀን ክብርና ሞገስ ይገባል» ይላል፤ ሌላኛው፣ «ቀን ሁሉ ያው አንድ ነው፣ ለተለየ ቀን ከበሬታ መስጠት ነውር ነው» ብሎ ያስተ ምራል። ይህን ጊዜ ጳውሎስ መፍትሔ ብሎ እነዚህን ሁለት ሰ ዎች ከአሥር ቤት ይውረዱ፣ ከቤተ ክርስቲያን ይታገዱ አላለም። በምትኩ እውቀት የነፍስ የመገለጫ አንደኛው መንገድ ነውና ማብራሪያቸውንና ውሳኔአቸውን አከበረው። እንዲያውም፣ «እያንዳንዱ ሰው ከልቡ ያመነበትን ያድርግ» ብሎ ደመደመ። ጳውሎስ ለዚህ የዝምታ ውሳኔው ጽኑ ምክንያት አለው። እርሱንም በዚያው ምዕራፍ በቁጥር 12 አነሣው። ማንም ሰው ከዕለታት አንድ ቀን «እውቀቴ ውሳኔዬ ነው» ብሎ ለኖረለት አቋም ምላሽ ይሰጥበታል፤ ይህም ምላሽ በምድር ላይ ለሚገኝ ጽኑ አማኝ ወይም አንቱ ለሚሰኝ ሰው አይደለም፣ ምላሽ የሚሰጠው ለሕያው እግዚአብሔር ነው፤ «... እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን መልስ እንሰጣለን» ይላልና። ይኸው እውነት በ2ኛ ቆሮንቶስ 5:10 ደግሞ ተደገመ፤ የዚህን የግላዊ የነፍስ ነጻነት ርእሰ ጉዳይ አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኢየሩሳሌ

ም ባለቀሰላት ድርጊት እንየው (ሉቃስ 13፡34-35)። እርሱ እምባውን ያፈሰሰው ዕዳቸውን አልተቀበሉምና ነው፤ ግና የማዙፍ ዓለማት ፈጣሪ እርሱ ነው። እመኑኝ ብሎ ለማስገደድ ከልካይ የሌ ለበት፣ ከፈለገ የሰማይ ሠራዊቱን አስልፎ ያምኑበት ዘንድ ለማድ ረግ ችሎታው አለው። ዳሩ ግን ሁሉንም አላደረገውም። እርሱ ሕይወትን አቀረበላቸው፣ ተቃወሙት፤ ድርሻው ጥፋቷን እያመለከተ ማልቀስ ሆነ።

የሳምራዊቷ ጉዳይም ይኸው ነበር፤ በውኃው ጉድጓድ አጠገብ አገኛት፣ በዚያም የዘላለምን ሕይወት አቀረበላት እንጂ፣ «የምልሽን እመኚ» አላላትም። «ካላመንሺኝ ዛሬ ወደ ሲኦል ትወርጂያለሽ» የሚል ተጽዕኖም አላደረገም፤ ሴቲቱ ግን የሚገርመው ያለ ምንም፣ ያለማንም ተጽዕኖ በእርሱ አመነች (ዮሐ. 41፡1-49)።

ሮሜ አሥራ አራትን የመሰለ አማኝ በአማኝ ላይ ተጽዕኖ አድርጎ ወደ ራሱ አቋም በግድ ሊያመጣው እንዳይገባ የሚገልጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ልጨምር። ጥንት ገና ከጠዋቱ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ግልጽ የሆነ መመሪያ ሊበሉት ባላቸውና በሌላው የዛፍ ፍሬ ላይ ሰጣቸው። እርሱ ሊበሉት ስለማይገባው ፍሬ ገልጾ ወዲያውኑ ተሳስተው ወይም ተጠራጥረው እንዳይበሉት ለማድረግ ጠባቂ ዘብ አላቆመላቸውም። ሌላው ቀርቶ ሊበሉት ወደ አፋቸው ሲያስጠጉት አልተከላከለም፤ አለመከልከሉ አቅም አጥቶ ወይም ሊያግዳቸውና ከመንገዱም ሊያስቀራቸው ተ ስኖት አይደለም፤ ግላዊ የነፍስ ነጻነታቸውን አክብሮላቸው እንጂ። እነርሱ ነጻነታቸውን ተጠቀሙ፣ ኋላ ላይ በእግዚአብሔር ፊት ቀ ረቡ፣ ለተጠየቁትም ጥያቄ ምላሽ ሰጥተው፣ ዋጋቸውን ተቀበሉ።

ታላላቅ የወንጌል ገድሎችን በምናነብበትና በምናይበትም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ «ከማንኛችን ጋር ይሂድ?» በሚለው ጥያቄ ጳውሎስና በርናባስ በዮሐንስ ማርቆስ ላይ የአሳብ ልዩነት ገጠማቸው። አንዱ አንዱን ለማስረዳት ሙከራ ተደረገ።

ግን አልቀጠለም። አማራጩ አንዱ በአንዱ ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ከማሳመን ጥልቅ መለያየት የተሻለ ሆነ። ሁለቱም የየራሳቸውን መንገድ በተለያየ አቅጣጫ አስምረው ለወንጌል ሥራ ዘመቱ። ፍሬያማም ሆኑ (ሐዋ. 15:36-41)።

በስተመጨረሻ፣ የሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያንን መልእክት እናጢነው። በዚያ ኢየሱስ ክርስቶስ ከበራፍ ቆሞ ሲያንኳኳ ይታያል። የምዕራፉ ዐውድ እንደሚያስረዳው፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያለ ጌታዋ ድጋፍ በራሷ ልትኖር እንደምትችል በማመን፣ ኢየሱስን አራቀች። እርሱ ደግሞ አብሯት መሆን ፈለገ፣ ለዚህም ትሕትናን ተሞልቶ፣ በርጋታ በሩን ያንኳኳል። ግን እኮ እርሱ ፈጣሪ ነው፤ ሁሉን ማድረግ ይችላል። «ሰብሮ ገብቶ» ኃይሉን አሳይቶ ሊገሥጻቸው ይችላል። ይህን ግን አላደረገም። ለምን? ቢሉ የራሱን ፈቃድ በእነርሱ ላይ ለመጣል አልፈለገም። እርሱ የግላዊ የነፍስ ነጻነት አክባሪ ነው።

እንግዲህ ከላይ የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስናጤን፣ «ግላዊ የነፍስ ነጻነት» እውነት የሆነ ጉዳይ እንደ ሆነ ልናጤን ይገባል። ቢሆንም ግን፣ ሦስት ያህል ገደቦች እንዳሉት አይዘነጋም። አንደኛው ገደብ፣ የራስን ነጻነት በማስከበር ሂደት ውስጥ የሌላው ነጻነት እንዳይደፈር የመጠንቀቅ ገደብ ነው። የትኛ ዋም ቤተ ክርስቲያን የጆሮ ታምቡር ሊበጥስ የሚችልን የድምፅ ማጉያ በጣራዋ ላይ ሰቅላ ትምህርቶችዋን ስሙልኝ በማለት የሌ ሎችን መብት አታቃውስም፤ በኖረችበት ዙሪያ የመኖሪያ ቤቶችም ካሉ በመጮህ በጉዳዩ የማይመለከታቸውን ሌሊት ከእንቅልፍ፣ ቀንም ከጉዳዮቻቸው አታስተጓጉልም። ይህ የነጻነት ገደብ ነው።

ሁለተኛው ገደብ፣ ሰው ሁሉ የነፍስ ነጻነት አለው ማለት አማኝ የፈለገውን ለማድረግ ተፈቅዶለታል ማለት አይደለም። የሮሜ አሥራ አራት ሁነኛ መልእክት፣ «አማኝ ሁሉ ለሌላው ወንድም መሰናክል እንዳይሆን ሊጠነቀቅ ይገባል» የሚል ነው።

ሦስተኛው ገደብ፣ የነፍስ ነፃነት የእግዚአብሔርን ቃል ለመጣስ ወይም ለመተላለፍ የፈቃድ ወረቀት ማለት አይደለም። አንድ አማኝ ከአመነ በኋላ ተጠምቆ ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል ወይም ሳይጠመቅ አለመቀላቀል ለግሉ የተተወለት ነጻነቱ ነው። ይህ ግን ላለመጠመቅ ነጻነቱን የሰጠኝ «የእግዚአብሔር ቃል ነው» ማለት አይችልም፤ ይልቁኑ፣ ባለመጠመቁ ተጠያቂው «እኔው ራሴ ነኝ» ማለቱ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳችን «ሰውን በኃይል አስገድዱ» የሚል ትምህርትን አላስተማረም፤ «አስፈራርታችሁም አሳምኑት» ብሎ አላዘዘንም። ይህም ሲባል ስለ ሰው ግድ የሌላችሁ ሁኑ የሚል ትምህርት ይዟል ማለትም አይደለም። ልክ አይደለም ብለን በቃሉ ያነጠርነውን የኃጢአት ወይም ሊሆን የሚገባውን ብቸኛ እውነት ለሰው ልጆች ሁሉ በማሳየት ኃላፊነታችንን ልንወጣ ግድ ነው። ጌታ እናደርገው ዘንድ ከገለጻቸው መርኖች ጥቂቶቹን ልጠቅስ፦ የሕይወትን እውነተኛ መንገድ ሊያውቅ ይገባል ብለን ላሰብንለት ሰው አስቀድመን እንጸልይለት፣ አግባብነት ያለውን ክርስቲያናዊ ሕይወት በመኖር እናሳየው፤ ጓደኛም በመሆን አቅም በፈቀደው ሁሉ በመርዳት፣ የቃለ እግዚአብሔር እውነትን በመግለጽ እንማርከው። በርእሰ ጉዳዩ ላይ የሚስማሙ ጽሑፎችን በመስጠት እንርዳው። በጉዳዩ ዋንኛነት ላይ አጽንኦት በመስጠት ያስበው ዘንድ እንርዳው፣ ይህ ድርሻችን ነው። በዚህ ያለግዳጅ በሚደረገው «የክርስቶስ አምባሳደርነት» አገልግሎት ላይ ጌታም የራሱን ድርሻ ይፈጽማል።

አዲስ አበባ

ከከተማም ርእሰ መዲናችንን አዲስ አበባን ይመለከታል። እንዲህም ቢሆን ፈጥኜ ወደ ጉዳዩ ዘው አልልም፣ መንደርደሪያዬን አስተዋውቃችኋል።

መነሻዬ ቁጥር ነው- ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት፤ ይህ የቁጥር መጠን ከዘፍጥረት የመነሺያ ምዕራፎች በመጀመር እስከ ራእይ ዮሐንስ ዳርቻ ድረስ የተጠቀሱትን ከተሞች ያስታውቃል፤ መጽሐፍ ቅዱስ በበጎም ይሁን በክፉ በዚህ ያህል ቁጥር ከተማ፣ ከተሜ፣ ከተሞች እያለ ዘልቋል። ምሳሌ ይሆነኝ ዘንድ አለፍ አለፍ እያልኩ ጥቂት ልዘክር።

ዘፍጥ. 4:17 - ቃየል **ከተማን** መሠረተ፣ በልጁም ስም «ሄኖክ» ብሎ ጠራው።

ዘፀአ. 1:11 - የብዙ ነገር ማከማቻ የሆኑትን... **ከተሞች** ለፈርዖን ሠሩ።

ዘዳግ. 3:5 - **ከተሞቹ** ከፍ ያለ ቁመት ባላቸው ቅጥሮች የተ መሸጉ ነበሩ።

ዘዳግ. 6:10 - ብዙ ሀብት የሞላባቸውን ታላላቅ **ከተሞች** ይሰጣችኋል።

ኤር. 29:7 - **ለከተሞቹ** እድገት መልካም ነገር አድርጉ፣ ስለ እነርሱም ወደ እኔ ጸልዩ።

ማቴ. 2:23 - ኢየሱስ... እዚያ በደረሰ ጊዜ መኖሪያውን በናዝሬት **ከተማ** አደረገ።

ማቴ. 8:34 - **የከተማው** ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን ለማየት ወጡ።

ማቴ. 21:10 - «ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ የከተማው ሰዎች በሙሉ «ይህ ማን ነው?» በማለት ታወኩ። ሕዝቡም «ይህ በገሊላ ምድር ከምትገኝ ከናዝሬት **ከተማ** የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው» አሉ።

ሉቃስ 19:41 - ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም **ከተማ** ቀርቦ **ከተ ማይቱን** በተመለከተ ጊዜ አለቀሰላት።

❁ ❁ ❁

በእነኚህ ጠቋሚ ጥቅሶች የምንጨብጠው በምድር ላይ የመጀመሪያዋ ከተማ በቃየል የተመሠረተች እና ስሟም ሄኖክ መባሉንና ከዚያም እያደገ ሲመጣ ከተማ የብዙ ነገር መገኛ፣ በአግባቡ በነጻነት የተመሸጉ፣ የብዙ ሀብት መገኛዎችና የሰዎች ተከማችቶ የመኖሪያ ክልል መሆናቸውን ነው። ለእነዚያም ከተሞች እድገት መጠበብና መልካም ማድረግ፣ ስለ እነርሱም መጸለይ የእግዚአብሔር አሳብ መሆኑ ተጠቁሟል። ከእነዚህም ከተሞች በአንዷ በናዝሬት ኢየሱስ መሪውን በዚያ ሊያደርግ መምረጡ፣ ኋላም የከተሞች ሁሉ ቁንጮ ወደ ሆነችው ኢየሩሳሌም ሲደርስ ስለ ከተማዋ ነዋሪዎች ማልቀሱን ቀደም ያሉት ጥቅሶች ይጠቁሙናል።

ለምን ይሆን ኢየሱስ ግን ከተማይቱን ተመልክቶ ያለቀሰው? በእምነት የዚህ ምላሽ ከተማን ከተማ ሊያሰኙ የሚችሉ ነገሮች ለኢየሩሳሌም ቢኖራትም፣ ውስጣዊ ገበና መንፈሳዊነትን በተመለከተ ሕይወት የማይሰጥ መሆኑ አሳዝኖት ነው እንባውን ያፈሰሰው። ኢየሩሳሌም፦ የሕዝብ አስተዳደር ማዕከል፣ የትምህርት መገኛ፣ የመንገዶች መነሻ፣ የመረጃዎች መፈተሻ፣ የንግድ መናኸሪያ፣ የኢንዱስትሪ መስፋፊያ፣ የመከላከያ መገንቢያ፣ የጎብኚ መከማቻያ፣ የእምነት መመንጪያ፣ የባህል ሙዚየም ነበረች። እነዚህ ሁሉ የዘመኑ የሥልጣኔ ፈርጦች በመሆናቸው፣ ኢየሩሳሌም በተጠናከረ ሁኔታ ሁሉንም አሰባስባለች። ዜጎቿ ኢየሱስን አውቀውት፣ አምነውትና ታርቀውት በእርሱ የነበረውን መልካም ዜና ከዚያው ጀምሮ ለዓለም በማድረስ ኃላፊነታቸውን ይወጡ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። ነገር ግን አዳኙን የገዛ ወገኖቹ ሳይቀበሉት ቀሩ። የከተማው ኗሪዎቹ «ይባስ ብለው» ሊያስወግዱት፣ ሊሰቅሉት ወሰኑ፣ ያኔ ነው ኢየሱስ ያለቀሰው። መልካሙን ዜና ያደርሱበት ዘንድ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ ስለ ተቃወሙ አዘነ፤ አለማመን ስለ ሰፈነባቸው አነባ፤ ለዘላለምም ሕይወት የመጨረሻ የሆነውን ሁነኛ የእግዚአብሔር መፍትሔን ኢየሱስን ሊያውቁት ሲችሉ ገለል በማድረጋቸውና በማንገዋለላቸው አዘነ።

ከዚህ ከጥንቷ የኢየሩሌም ከተማ ፊቴን ዘወር አድርጌ ወደ መነሻዬ ወደ እኛይቱ «አዲስ አበባ» ስመለስ፣ በአንድ ወቅት ደራሲ

ሀዲስ አለማየሁ ስለ ከተማዋ በወንጀለኛው ዳኛ መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ አስፍረዋል፡፡

«...አዲስ ከተማ በኢትዮጵያ ከሚሠራውና ከሚፈራውም ሌላ ኬላ እየሰበረ ቀረጥ ሳይከፈልበት ከሚገባው የውጭ አገር ዕቃ ላብዛኛው መደብር ስለ ሆነች፣ የአዲስ አበባ ወይዛዝርትና መኳንንት፣ ሽማግሌና ባልቴት፣ ወጣቶችና ሕፃናቶች የውጪ አገር እቃ በርካሽ ለመግዛት እዚያ መሄድ አለባቸው፡፡ አዲስ ከተማ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስ እንዲሁም የዘመናዊት ኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና የሥራ ፍሬዋ ባንድ ላይ የሚታዩባት ስለ ሆነች፣ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ከልዩ ልዩ አገር በብዛት የሚመጡ አገር ጎብኚዎች እዚያ መሄድ አለባቸው፡፡ አዲስ ከተማ ገጠሬው በየክፍሉ ያፈራውን ጭናም ሆነ ተሸክሞ እየመጣ ለከተሜው ቸርቻሪ የሚሸጥበት ስለ ሆነች፣ ከየአቅጣጫው የሚመጣው ገጠሬ ሁሉ እዚያ መሄድ አለበት፡፡ አዲስ ከተማ ተሸካሚው ተሸክሞ፣ ደላላው ደልሎ፣ አታላዩ አታሎ፣ ለማኙ ለምኖ፣ ሌባው ሰርቆ የዕለት እራቱን የሚያገኝባት ስለ ሆነች፣ ሁሉም እዚያ መሄድ አለበት!...» (ወንጀለኛው ዳኛ፣ ገጽ 89፣ 1974 ዓ.ም)፡፡

የደራሲው ገጸ ባህሪ በአዲስ አበባዋ አዲስ ከተማ ላይ የጦፈ ንግድ መኖር፣ የታሪክና የቅርስ መናኸሪያነቷን፣ የጎብኚዎች የመጠራሪያ ስፍራነቷን፣ የገጠር ኗሪዎች የገባ ወጣ ስፍራ መሆኗን፣ እድሜውን ለአንድ ቀንም ቢሆን ሊያራዝም የወደደ በዚያ ሆኖ ደጅ የጠናባት ከተማ አዲስ አበባ መሆኗን ገለጹ፡፡ እናም እርሳቸው የፈጣን የሕይወት እንቅስቃሴ ማዕከልነቷን አስ ረግጠዋል፡፡ እኔ ደግሞ አንድ እርምጃ ከእርሳቸው ልዝለቅና የአዲስ አበባን ወቅታዊ ሁኔታ በየዘርፉ በግርድፉ አነሣለሁ፤ ስጨርስም «በክርስቶስ የሆንን የከተማ ክርስቲያኖች ምን እንጠብቃለን?» እላለሁ፡፡ በፍጻሜዬም ለእማኝነት ጳውሎስ በከተሞች ላይ እንዴት ውጤታማ እንደ ሆነ አበስራለሁ፡፡

በየአሥር ዓመቱ የሚደረገው የመላው ኢትዮጵያ የሕዝብ ቆጠራ የቅርቡን የአዲስ አበባን ዘገባ በመያዝ ለአደባባይ ቀርቧል፤ በውስጡ

- የሕዝቧን ብዛት፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ሃይማኖት፣ የውልደት መጠን፣ የሞት መጠን፣ ፍልሰት፣ ትምህርት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የሥራ፣ የኢንዱስትሪ፣ የቤት ብዛት፣ ወዘተ. . . ዘርዝሯል። እኔ በከተማ ለወንጌል ሥራ ብናውቃቸው ይጠቅሙናል ከምላቸው አንዱን ብቻ አነሣለሁ።

ሃይማኖትን በተመለከተ የከተሜው 82 በመቶ የኦርቶዶክስ ተከታይ ሲሆኑ፣ 12.7 በመቶ ሙስሊም ነው፣ ፕሮቴስታንት 3.9 በመቶ ሲሆኑ፣ 0.8 በመቶው ካቶሊክ ነው፤ ከዚህ ውጭ ያሉት 0.6 በመቶን ይይዛሉ።

ትምህርትን በተመለከተ ከከተማው አጠቃላይ ኗሪዎች ውስጥ በእድሜ አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ካሉት ሕዝቦች ውስጥ ከወንዶቹ 89 በመቶ፣ ከሴቶቹ 76 በመቶው በተለያየ ደረጃ ውስጥ በማለፍ በትምህርት ዓለም ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

70 በመቶው የሬዲዮ ተጠቃሚ፣ 16 በመቶው የቴሌቪዥን፣ 18 በመቶ የስልክ ተጠቃሚዎች ናቸው። በመጨረሻም፣ የአማካይ የአንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ እድሜ ወንድ ከሆነ 57 ሲሆን፣ የሴት ደግሞ 60 ዓመት ተሰልቶለታል።

ይህቺ ከሦስት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርባት የአዲስ አበባ ከተማ ይህን ያህል የሕዝብ ክምችት እንዲኖራት ያበቃት፦ ሀዲስ አለማየሁ እንደ ገለጹት የምቹና የፈጣን የሕይወት እንቅስቃሴ ማዕከልነቷ ዋንኛው ነው። በእርሷ ከሚገኘው በርካታ የሚነበብ የምስራች ቃልን ማጣጣም አያቅተውም። ከኗሪዎቹ ብዙው አቅሙ በፈቀደለት መጠን ተምሯል፤ አንብቧልና የሚነበብ የምስራች ቃልን ማጣጣም አያቅተውም፤ ከኗሪዎቹ በርካታው ለመገናኛ ብዙኃን ተጋልጧል፤ የዜና ስርጭቶች ፈጥነው ለዓይኖቹና ለጆሮዎቹ ይደርሱለታልና በሰከነ ሁኔታ የተዘጋጀውን የወንጌል መልእክት ለመስማት አይሣነውም። በቅርቡ በተደረገው ጥናት ከአዲስ አበባ ነዋሪ ውስጥ ሦስት አራተኛው በተለያየ ምክንያት በፍልሰት የሰረጉ ናቸው። ይህ ደግሞ ወዳጆቻቸው በሩቅ አሉና የከተማዋን እንቅስቃሴና መልእክት በየምክንያቱ ወደ ወጡበት የማድረስ ዕድላቸው ሰፊ ነው፣ እናም ወንጌል በአግባቡ በአዲስ አበባ ከተዘራ ተላላፊ የመሆን ዕድሉ እሙን ነው። በተለይም በመዲናችን

የተመሰቃቀለው የኑሮ ሁኔታ ጎብረተሰቡን ወደ ጥፋት ጎዳና እየመራው ይታያል። ፊት ለፊት ከሚታዩት ያማሩት ፎቆች ጀርባ የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናትና የሴተኛ አዳሪዎችን የዘቀጠን ሕይወት ወደ እውነት ጎዳና መምራት የእኛው ድርሻ ነው።

መቼም ከኗሪው ምን ያህል በጌታ በሆነው የወንጌል የምስራቹ ቃል ባለአደራ እንደ ሆነ ከላይ በተዘገበው ቁጥር ግልጽ ብሏል።

አዲስ አበባ እንደ ጥንቷ ኢየሩሳሌም የሁሉ ነገር ማዕከል ናት፤ ለሁሉ ነገር ምቹ ስፍራ ናትና ኢየሱስ ክርስቶስን መላው ኢትዮጵያ እንዲሰማው ከተማዋን በእኛ በኩል ይፈልጋታል።

ጳውሎስ እድሜውን ሁሉ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ በመሄድ ዘለቀው። እርሱ ከመጀመሪያው ወንጌላዊ ጉዞው ጀምሮ እስከ እልፈቱ አንዲም ከከተማ አልታጣም፤ የየከተሞቹን ምኩራቦች በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነትና አዳኝነት አጥለቀለቀ፤ አንጾኪያ፣ ገላትያ፣ ኤፌሶን፣ አቴና፣ ቆሮንቶስ፣ ወዘተ... በጉዞው ተዳሰሱ። በዚያም ዘሩን ዘራ። ጳውሎስ ዛሬ በእጃችን የደረሰውን ታላቅ ምሥጢር በዚህ መልኩ አደረሰ። ይህ ለአዲስ አበባም እውነት ነው።

በጥንቷ ኢየሩሳሌም በበዓለ ሃምሳ ላይ ለመገኘት ከተለያዩ ክፍሎች የመጡት በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በዚያን ዕለት የጴጥሮስን ስብከት አድምጠው የኢየሱስ ክርስቶስን የአዳኝነት ሥራ ተረዱ፤ በውጤቱም ያኔ ንስሐ ገብተው ክርስቲያኖች ሆኑ፤ እነርሱው በዓሉ ሲያልቅ ከዚያች ከተማ ተነሥተው ወደ መጡበት ተመመሙና፣ እናም በደረሱበት በሌላ ከተማ ሁሉ ወንጌልን ዘሩ፣ አበቀሉም።

አዲስ አበባ ዓመቱ ተጠብቆ የሚከበር ዓመታዊ በዓል የላትም። ግን «የገሃነም ደጆች ሊቋቋሟቸው የማይችሉ ቤተ ክርስቲያናት» አሏት፤ እነርሱ ኃላፊነታቸውን ተወጥተው የሚናኝ የምስራችን መልእክት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተላልፉ ዘንድ ግድ ነው። ሳጠቃልል፣ አዲስ አበባ ብዙ የተቀበለች ከተማ መሆኗን፣ ለመቀበሏ ምሳሌ ላንሣና ልሰናበት፡- ይህቺ አዲስ አበባ ወደ መላው ኢትዮጵያ የሚዘልቁ ዋና መንገዶች፣ ወደ ዓለም ሁሉ የሚበሩ በርካታ የአየር መንገዶች፣ ለአገሪቱ ሁሉ የሚደርስ የዜና

ማሠራጫ፣ ጽሑፎች ታትመው ይናኙና ይነበቡ ዘንድ የሚያስችል አቅም፣ ከዓለም ኅብረተሰብ ጋር የሚገናኙ የውጭ ድርጅቶችና ኤ ምባሲዎች፣ የከፍተኛ የትምህርት ማዕከላት በአግባቡ የበረከቱባት እና የመላው ኅብረተሰብ የዘር፣ የቋንቋ የነገድ ባለቤቶች ሁሉ ተ ሰበሰበው የሚኖሩበት ከተማ ናት።

አዲስ አበባ ከእዚህ ሁሉ በላይ፣ በመንፈስ ቅዱስ አመላካችነት ኃጢአተኝነታቸውን ተረድተው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝነት አምነው የዳኑ ክርስቲያኖች ያሉባትም ከተማ ናት። እነርሱ አዲስ አበባ የተቀበለቻቸውን ብዙ በጎ ነገሮች ተጠቅመው በከተማው የወንጌልን ዘር ይዘሩበት ዘንድ ግድ ነው።

ማን ይተምን? የፈጠረ

አዶልፍ ሂትለር በጊዜው የተነሣበት ሁነኛ ዓላማ ዘረኝነት ነበር። «የጀርመኖች ደም፡- ንጹሕ፣ ክቡርና ከሰው ዘር ሁሉ በላጭ ነው» አለ። ይህንንም ለማሳየት ጀርመኖችን አሞካሸቶ ቀሪውን የዓለም ሕዝብ አጥላላ።

❁ ❁ ❁

ኢየሱስ ወደ እርሱ መጥቶለት ክርስቲያን የሆነ ወጣት በቅርቡ ቀን ሞተ። «እንግዳ ነኝ እኔ ስኖር በዚች ዓለም» ተዘምሮለት ተቀበ ረ። ኋላ ግን «ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የእናት አባቱን እምነት ክዷልና ሊቀበር አይገባውም» የሚል ዐመጽ በተከታዩ ቀን ተነሣ። አነሣሾቹ በድኑን ከመቃብር አውጥተው አቃጠሉት። በነበልባሉም ውስጥ፣ «የዚህ ዓይነቱ ወደፊትም ቀባሪ ይጣ» ተብሎ ተወገዘ።

❁ ❁ ❁

ወንጌልን እየሰበክን ነው ያሉ አንዳንድ ሚሲዮናውያን ደግሞ፣ «ጥቁሮች የክርስቶስን አዳኝነት ሰምተው ከእግዚአብሔር የዘለዓለም ዕቅድ ጋር መገናኘት አስፈላጊያቸው አይደለም» ብለው ሰብከ። ለዚህም ዐቢይ ምክንያታቸው፣ «ጥቁሮች» እንደ እንሰሳ የሚድን ነፍስ የላቸውም» የሚል ነበር።

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ሰፋና ጎላ ብሎ ብዙዎች ተዘፍቀውበት የሚታየው ሰው በሀብቱ፣ በሥልጣኑ፣ በእውቀቱ፣ በአለባበሱና በዕድሜው በውጫዊ ሰውነቱ እና በመሳሰለው ላይ በመመሥረት የማቅረብና የማግሸሽ፣ የማክበርና የመናቅ ልምድም አለ። ለእኔ እኒህ ከላይ ያነሣኋቸው አራት ያህል ምሳሌዎች ሰዎች ስለ ሰው ያላቸውን የተዛነፈ አስተሳሰብ ይገልጹልኛል።

ሁሉም የሰውን ማንነትና የእግዚአብሔርን ድርሻ ረስተዋል። እንዲህ እንዲያምኑና እንዲያስቡ ግን ያስገደዷቸው ምክንያቶች አሉ። የቅርቡ ሪደር ዳይጀስት «. . .ሰው ተገነጣጥሎ የሚሸጥ ቢሆን ገበያ ላይ የሚያወጣው ዋጋ ሃያ አንድ የኢትዮጵያ ብር ብቻ መሆኑን» ጽፏል።

የ1996ቱ የባፕቲስት ቻሌንጅ ደግሞ፣ «በማሕጸን ያለ ፅንስ ሰውን ከንስር ጋር አወዳድሯል። ንስሩ ከፅንቁላሉ ገና አልተ ፈለፈለም፣ ሕፃኑም በእናቱ ማሕፀን አለ። በእነዚህ ላይ አንድ ግለሰብ የመግደል እርምጃ ቢወስድ፣ የቅጣት ተመኑ ንስሩን ለገደለው ሠላሳ ሦስት ሺህ የኢትዮጵያ ብር እና የአንድ ዓመት እሥር። ሰው ያጠፋውን ደግሞ ያለ ቅጣት በመተው በምትኩ ለአስወራጁ ክፍያ እንደሚፈጸምለት ያብራራል። እንግዲህ ይህ ለሰው ልጅ ተመኑ መሆኑ ነው።

የቅርቡ ሪደር ዳይጀስት ሰውን ካለው ንጥረ ነገሮቹ አኳያ ተምኗል። አንድ ሰው ሊኖረው የተገባውን ሆርሞኖች፣ ፕሮቲኖች፣ ወዘተ... ሠርቶ ለማዘጋጀት አርባ ሁለት ሺህ ትሪሊዮን የኢትዮጵያ ብር ያስፈልጋል። ትሪሊዮን በቁጥር መጠኑ ከቢሊዮን በልጦ የሚገኝ ነው። እንግዲህ አንድን ሰው ለወግ ለማብቃት ይህን ያህል ብር ያስፈልጋል። ይህም «ሰው ለሰው ሕይወትን መስጠት» ቢችል በማለት የተተመነ ነው።

ለመሆኑስ በእግዚአብሔር አኳያስ የሰው ልጅ ተመኑ ይህን ያህል ነው? ለመተመን ሊተምን የሚችል አመለካከትና አስተሳሰብ ሰው ሊኖረው ይገባል። ይህን በአግባቡ ለመረዳት የሰው ልጆችና እግዚአብሔር የነደፏቸውን ሦስት እሳቤዎችን ላመልክት። ይህን ማድረጌም የቀደሙትን ማብራሪያዎች የደካማነት ምንጭ ለማሳየት

ስለሚረዳኝ ነው።

አንደኛው እሳቤ፦ የሰው ዝግመታዊ ለውጥ ነው (Atheistic evolution)። ይህ ሁሉም ነገር ከድንገተኛ አጋጣሚ፣ ከኢምንት ደረጃ በመነሣት ቀስ በቀስ ወደ ውስብስብና ዕድገቱ ከፍ ወዳለ ደረጃ መሄዱን ያስረዳል፤ ሰውንም እንዲሁ ከኢምንት መነሻ በመነሣት ለዛሬው መብቃቱን ያብራራል። በዚህ ንድፈ አሳብ ተከታዮች ዘንድ ሰው ከማንኛውም ነባራዊ ነገሮች ጋር ዋጋው እኩል ነው።

ሁለተኛው እሳቤ፦ በመለኮት የመጣ የሰው ዝግመታዊ ለውጥ ነው (Theistic evolution)። እግዚአብሔር ዓለማትንና በውስጧ ያሉትን በስድስቱ ቀናት ውስጥ አልፈጠራቸውም። ይልቁኑ፣ ሁሉን ነገር ከኢምንት መጠን በመጀመር ቀስ በቀስ ለዚህ ለዛሬው ወግ አበቃቸው ይላል። ይህ እሳቤ ከመጀመሪያው ንድፈ አሳብ ጋር ይቀራረባል።

***ሦስተኛው እሳቤ የስድስቱ ቀናት የፍጥረት ታሪክ ነው* (Six day creation)።** ሰው በቀጥታ የእግዚአብሔር የእጅ ሥራ ውጤት መሆኑን ይተነትናል። በዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፎች የተ ዘገበው መረጃ እንዳለ መቀመጡን ያምናል። ሁሉንም ነገር በስድስቱ ቀናት ውስጥ በቅደም ተከተሉ መገኘታቸውን ይዘክራል። እንግዲህ በአንደኛውና በሁለተኛው እሳቤ የተዋጠ የትኛውም ሰው ስለ ሰው ያለው ግምት ደብዛዛ ነው። ሦስተኛው ግን እውነተኛ መሠረት ነው። ይህ መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ሰውን እንዴት እንደ ገለጸው ካብራራሁ በኋላ መለስ እላለሁ። ለዚህም የማጠንጠኛ ጥቅሴ «የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው ሥጋዊ ግን ከእግዚአብሔ ር መንፈስ የሚሰጠውን ስጦታ መቀበል አይችልም፤ የስጦታው ታላቅነት የሚመረመረው በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት ስለ ሆነ ሊያስተውለው አይችልም፤ እንዲያውም ይህ ለእርሱ ሞኝነት መስሎ ይታየዋል» (1ኛ ቆሮ. 2:4፤ ቀ.አ.)። «. . . ገና ሥጋውያን ናችሁ. . . [የእግዚአብሔር ሰዎች መሆናችሁ ቀርቶ] ሥጋውያን ሰ ዎች መሆናችሁ አይደለምን?» (1ኛ ቆሮ. 3:3፤ ቀ.አ.)። «. . . የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው ግን ሁሉን ነገር መመርመር

ይችላል፤ እርሱ ግን በማንም አይመረመርም» (1ኛ ቆሮ. 2፡15፤ ቀ.ሉ.)። እነዚህ ጥቅሶች የሰው ልጆችን በሦስት ይፈርጇቸዋል።

አንደኛው ፍጥረታዊ ሰው ነው። እነዚህ ክርስቶስን በማመን ለእግዚአብሔር ልጅነት አልበቁም። ሁለት ጊዜ ሊወለዱ ሲገባ በመጀመሪያው ልደት ላይ ብቻ ቀርተዋል፤ ከዚህም የተነሣ ፍጥረታዊ ተብለዋል። እነርሱ በጎ ነገር ማድረግ ቢችሉም፣ ዕለት በዕለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ግን አይችሉም። ፍጥረታዊው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘውን ድልድይ አልተጠቀመበትም። የእርሱ የሆኑትን ሌሎች መንገዶች ተጠቅሞ እግዚአብሔርን ማስደሰት ደግሞ አይችልም። በዮሐንስ 5፡42 ኢየሱስ ክርስቶስ እናንተ የእግዚአብሔር ፍቅር በራሳችሁ የሌላችሁ መሆናችሁን ዐውቃለሁ አለ። ጳውሎስም ይህን ዓይነቱን ሰው፤ በሮሜ 7፡18 ላይ ሲገልጸው፣ «በእኔ ወይም በእኔ *ሥጋዊ* ባሕርይ ምንም መልካም ነገር እንደ ሌለ ዐውቃለሁ፤ መልካም ነገር የማድረግ ፍላጎት ቢኖረኝም እንኳ ያን መልካም ነገር የማድረግ ችሎታ የለኝም» በማለት አብራርቷል። ከዚህም የተነሣ ይህ መቼም ቢሆን ሰው ስለ ራሱ እና ስለ ሰው ያለው ግምት ትክክለኛ አይሆንም።

***ሁለተኛው ሥጋዊ* ሰው ነው።** ይህ ሰው የሁለት ልደት ባለቤት ነው። ከእናቱ ከአባቱ ተወልዷልና ከእግዚአብሔርም የተወለደ ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 3፡3 እንደ ገለጸው፣ «. . . አሁንም ገና *ሥጋውያን* ናችሁ፤ እርስ በርሳችሁ ስለምትቀናኑና ስለምትከራከሩ *ሥጋውያን* መሆናችሁ አይደለምን? የእግዚአብሔር ሰዎች መሆናችሁ ቀርቶ የዓለም ሰዎች መሆናችሁ አይደለምን?» ብሏል። *ሥጋዊ* ክርስቲያን ሁሌ ይህ ዓለም ባወጣውና በሚመራበት መርኅ ራሱን የሚያስገዛ ነው። ክርስቲያን ነው፤ ነገር ግን ክርስቶስ እንደ ኖረው ለመኖር ያልፈቀደ ሰው ነው። የእርሱም አተማመን ከፍጥረታዊው ሰው ብዙ አይርቅም።

***ሦስተኛው መንፈሳዊ* ሰው ነው።** ኑሮውና ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ነው። ሁሌ በቀናው መንገድ በመሄድ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ይሆናል። ለነገራት ሁሉ

መመዘኛው በቃሉ የተገለጸው እግዚአብሔርና ሥራው ናቸው። ይህ ሰው፣ የክርስቶስ የሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ሊኖሩት የሚገባውን ሕይወት በመመላለስና ዕለት በዕለት ወደ እግዚአብሔር በመጠጋት የፈቃዱ ተገዢ ይሆናል። የእርሱ መለኪያው ቃሉና እግዚአብሔር ብቻ ናቸው።

እንግዲህ ስለ ሰው በማሰብ የሰውን እሴት ማውጣት የሚችለው ማን ነው? ከላይ እንደ ተነሣው የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሣል የተፈጠረ ስለሆነ ማመዛዘን፣ ማስተዋልና መወሰን ሀብቶቹ ናቸው። ዛሬ ላይ ግን እነዚህ ንብረቶች ፍጹማን ወይም ነጻ አይደሉም። በላያቸው ላይ የደረሰ ብክለት አለ። በኃጢአት ንጽሕናቸውን አጥተዋል። ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር እስካልታረቀ ድረስ መንፈሰ - ሙት ነው። መንፈሰ ሙት ስለሆነ ደግሞ የእግዚአብሔር የሆነውን እውነት አይረዳም። መረዳትና ማመዛዘን የሚሞክረው አእምሯዊ አስተሳሰቡ ነው።

ተፈጥሮአዊ ሰው እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ወደ አሰበለት ወደ ቀድሞው አሳብ መመለስ እንዲችል እግዚአብሔር እስካልረዳው ድረስ በራሱ ጥናታዊ ቀመር ስለሌለው፣ የሚሰጠው ተመን ፍጹምነት የለውም። ከዚህም የተነሣ በየዘመናቱ የኖሩ ፈላስፎች፣ ሳይንቲስቶች እና አዋቂዎች ሁሉ የድካም ውጤታቸውን ከመነሻ እውነት ጋር ያስተያዩት ዘንድ ግድ ነው። አሊያ ተዛብቶ የሚያጠፋ አመለካከትን ማንገሥ ብቻ ሥራቸው ይሆናል።

በሁለተኝነት የተነሡት ሰዎች እግዚአብሔር ለሰው ያለውን አሳብና ውሣኔ ይረዱ ዘንድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች የተመቻቹላቸው ናቸው፤ ወደ እነርሱ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታቸው ምትክ እንደ ሆነላቸው በማመን በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀዋል። በውጤቱም ለዘላለም የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ግንኙነት ጀምረዋል። ግና ጅምራቸውን ለማሳደግ ፈቃደኝነታቸው ደካማ ነው። ሁሌ ለኃጢአት ባሕሪያቸው መገዛትን ይመርጣሉ። እግዚአብሔር ስለ ሰውና ስለ ራሣቸው ያለውን ዘላለማዊ ዕቅድ ለመፈጸም አይተ

ጉም። ባለመትጋታቸው የተነሣ ብዙውን ጊዜ የመጀመሪያዎቹ ተ
ፈጥሮአዊ ሰዎች የሚያንጸባርቁትን አመለካከትና አስተሳሰብ
ለማንጸባረቅ ምቹ ናቸው። ከዚህም የተነሣ ለሰው ተመኑ ምን እንደ
ሆነ ቢያውቁትም፣ አይታዘዙለትም።

ሦስተኞቹ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ካስተማረው
ትምህርት ውስጥ «ቃሉን ሰምቶ የሚታዘዘው (የሚያደርገው) ቤ
ቱን በዐለት ላይ የሠራውን ልባም ሰው ይመስላል» ያለላቸው
ናቸው። ኢየሱስንና ትምህርቱን በፍጹምነት ያምናሉ፣
ይታዘዙታልም። ሁልጊዜ ሕይወታቸውን ከሕያው ቃሉ ጋር
አጣጥመው እየፈተሹና እያመዛዘኑ ይኖራሉ። ሕግጋት ሁሉ የተ
ጠቃለሉበትን ሁለቱን ወርቃማ አዋጆች በሙሉ ልባቸው
ያፈቅሩዋቸዋል። አስቀድመው እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍሳቸው
በፍጹም ኃይላቸውና በፍጹም ልባቸው ይወዱታል። በውጤቱም፣
ሰውን እንደ ራሳቸው አድርገው ያፈቅራሉ። በዚህ የተነሣ ስለ ሰው
ያላቸው ተመንም እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን ተመን መረዳትና
መሆን ብቻ ነው።

እግዚአብሔር የሰውን ሥራ፣ አጥንቱንና ደሙን ለያይቶ የሰው
ዋጋው ሃያ አንድ የኢትዮጵያ ብር ነው አይልም። ወይም ደግሞ
ለመኖር የሚያበቁትን ሆርሞኖች፣ ኢንዛይሞችና ፕሮቲኖች፣ . . .
ወዘተ አደርጅቶ ሰውን በአርባ ሁለት ሺ ትሪሊዮን የኢትዮጵያ ብር
አይተምነውም። ወይም ከአሜሪካውኑ የንስር ዋጋ ጋር አያወዳድ
ረውም።

ይልቁኑ፣ በአምሣሉ ለፈጠረው ሰው የእግዚአብሔር ተመን
ጳውሎስን፣ «ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን» ያሰኘ
ለት ክርስቶስ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ስለ ወደደን አንድ ልጁን
ሰጠን። ልጁም ለዚህ ታዘዘ።

ከእግዚአብሔር ፍጹም ተለይቶ ለነበረው፣ ምንም የተስፋ
ጭላንጭል ሳይኖረው አዘቅት ውስጥ ለወደቀ፣ የሰው ልጅ ይህ
ሆነለት። እግዚአብሔር የሰውን ተመን የላከው በአንድያ ልጁ
ሕይወት ነው።

እንኪያስ ሰውን ሰው ያሰኘው ሥራው፣ ሃይማኖቱ፣ ዘሩ፣ ቋንቋው፣ ብልጽግናው፣ ዕድሜው፣ ቀለሙ አለመሆኑ ተበሰረ። በመነሻዬ ላይ ስለ ሰው አመጣጥ ያለውን ዕሳቤ ለመግለጽ እንደ ሞከርኩት የዝግመተ ለውጥ አመጣጥ አማንያን ሁሉ ነገር በቀስ በቀስ የለውጥ ሂደት መጣ የሚሉለት ሰው በእነርሱ ዘንድ በሕይወት ሊኖር የሚያስችለውን ነገር ካጣ ትቢያ በመሆን ለሌላ ቅርጸ-አካል መነሻ የሆነ ከንቱ ፍጡር ነው። በዚህ እሳቤ መሠረት የሰው ተመኑ የተሻለ እንሰሳነት እንጂ ክቡር ፍጡርነት አይደለም።

የመለኮታዊ ዝግመት ለውጥ አማንያንም ሰው ሰውነቱ ዛሬም ገና አልተጠናቀቀም። ሂደቱን ያልጨረሰ ነው። ይህንንም ያደረገው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን በእሳቤያቸው ስለሚገልጹ፣ ለሰው ልከኛ ዋጋ ለመስጠት ለእነርሱ ጊዜው ገና ነው።

ይልቅ፣ የስድስተኛው ቀን ተሠሪ እና ተፈጣሪነቱን በአግባቡ የገለጸልን መጽሐፍ ቅዱስ ሰው በእግዚአብሔር አምሣል፣ የመፈጠሩ ሁነኛ ምክንያት ለራሱ ለእግዚአብሔር ክብር መሆኑን፣ በውጤቱም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን በማድረግ በአምስቱ ቀናት የተፈጠሩትን ፍጥረቶች ለእርሱ ጥቅም ያውላቸው ዘንድ ለኃላፊነት የበቃው ሰው መሆን ገልጿል። «ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ቢሆንም እግዚአብሔር እውነተኛ ነውና» (ሮሜ 3፡4፤ ቀ.አ.) በሚለው በዚህ እውነት ልንያያዝ ይገባል።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተናገረው፣ «እውነቱን የተረዱ እውነት ነጻ ያወጣቸዋል።» ያም ስለ ሰው የተገለጸው እውነት ከራሳችንም ሆነ ከሰዎች የሚጠበቀውን ገልጾልናል።

ለእዚህ እውነታ የታዘዙ የአዶልፍ ሂትለርን የዘረኝነት በትር አያነሡም፣ እውነትን የተረዱ አንዱን ብሔር ከሌላው ለማላቅ ሚዛን አያሠሩም። «አንቱ» የተሰኘ ሃይማኖትም ለእግዚአብሔር ልጅነት አያበቃም። እንደ አጓጉሉ ሚስዮናውያንም ጥቁር የሚድን ነፍስ የለውምና ወንጌልን አይሰማ አይሉም። በምትኩስ እውነትን አውቀዋልና ነጻ ወጥተው ነጻ ያወጡበታል። ቅንነታችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቢ እናድርግ፣ ማን ያውቃል? ክርስቶስ ድምጹን ሊሰሙ ላሉት በጎቹ እንደ ሞተላቸው ግምት ውስጥ ሳይከቱ የተ

ጠሩትን፣ ክርስቲያኖች በመካከላቸው ሊኖር የሚገባውን ኅብረት በዘር፣ በቋንቋ፣ በትምህርት፣ በሀብት፣ በጸጋ ስጦታዎች፣ በመንፈሳዊነት፣ ወዘተ...ከፍና ዝቅ በማድረግ የሰው ዋጋው ይዋዥቅ ይሆንን? እንዲህ ከሆነ፣ ጨውና ብርሃንነታችንን አጥንተናል ማለት ነው።

ይልቁንም፣ ክርስቲያኖች እርስ በርሳችን በሀብትም ሆነ በኑሮ ደረጃ፣ በሥልጣንና በእውቀት ወይም በሌላ ይመስሉናል የምንላቸውን እያቀረብን ሌላውን ገሸሽ በማድረግ የምንፈጽማቸውን ጥፋቶች ልብ እንበል።

«አንደኛው በጣቱ የወርቅ ቀለበት ያደረገና የሚያምር ጌጠኛ ልብስ የለበሰ ሀብታም ነው፤ ሌላው ያደፈ አሮጌ ልብስ የለበሰ ድኻ ነው፤ የሚያምር ጌጠኛ ልብስ የለበሰውን ሰው በማክበር፣ በዚህ በመልካሙ ቦታ ተቀመጥ» ትሉታላችሁ። ድኻውን ግን፣ «አንተስ እዚያ ቁም፣ ወይም በእግሬ ሥር ተቀመጥ» ትሉታላችሁ፤ ታዲያ፣ በዚህ ዐይነት በመካከላችሁ ልዩነት እንደምታደርጉና የአድልዎ ፍርድ እንደምትፈርዱ አይታያችሁንም? . . . እግዚአብሔር በእምነት ባለጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድኾች አልመረጠምን? እናንተ ግን ድኾችን ትንቃላችሁ. . .» (ያዕቆብ 2፡2-5፤ ቀ.አ.) በማለት ያስጠነቀቀውን፣ ጆሮ ያለው ሁሉ ይስማው።

ኢየሱስ በጎሊናቸው ውስጥ ታትሞ እንዲቀር የወደደውን የሰውን ተመን ለአድማጮቹ ሲያስተዋውቅ ሕይወታችሁና መላ ሰውነታችሁ ከሚበላና ከሚለበስ ነገር ይበልጣሉ /ሕያው ቃል/ . . . እስቲ በሰማይ የሚበሩትን ወፎች ተመልከቱ፤ እነርሱ አይዘሩም አያጭዱም፣ በጎተራ አይከቱም ነገር ግን የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል፤ ታዲያ እናንተ ከወፎች እጅግ ትበልጡ የለምን?» አለ (ማቴ. 6፡25-26)። ትክክለኛው የሰዎች መለኪያ መነሻው እግዚአብሔር ያዘጋጀው መለኪያ ነው። ይኸውም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ክብር ሕይወት ነው።

ዋቢ መጻሕፍት

1 Willmington's Complete Guide to Bible Knowledge, Introduction to Theology.

2. The Baptist Challenge, April 1996 Vol. XXXVI. No. 4 Which is More Valuable?

3. Reader Digest, April 2003

4. ዘረኝነትን የሚያስፋፉ ቀልዶች ከሕዝብ የተሰበሰቡ።

በሰውነት ቋንቋ መጠቀም

ያየሁት ሰባኪ ዐይናማ መሆኑን የተረዳሁት ንግግሩን በጸሎት ዘግቶ ከመድረኩ ሲወርድ ነበር፤ ሲያጠናቅቅ ያለ መሪ ተራምዶ ከስፍራው ያለምንም ችግር ተቀመጠ። ቆሞ ሳለ ግን ለአንዲት ቅጽበት ዐይኑም መጽሐፉም አልተገለጡም ነበር። እርግጥ፣ ሰባኪው ሊጠቀሱ የተገባቸውን ሁሉ በየስፍራቸው አንሥቷል። ይህም ቢሆን፣ መሠረታዊው ጉዳይ ከእግዚአብሔር የተሰጡት ዓይኖቹ ሳይንቀሳቀሱ በመቅረታቸውና ሕዝቡን ባለመቃኘታቸው መልእክቱ ያለ ጥርጥር ፈዟል።

አንድ ዕለት የገጠሙኝ ዘማሪዎች ደግሞ፣ ደመቅ አድርገው «ልዑል አንተ ብቻ» በማለት ሽብሸባና ጭብጨባ አከሉበት። ስንኙን በማለት ይቀድም የነበረው መሪ የሕዝቡን ዓይን አስጨፍኖ በጸሎት መንፈስ አምልኩ አለ። በዚህም፣ የእኛን ተመልካች ዓይን አስጨለመው፤ እኛም ታዛቺ ሆነን በሬዲዮ የሚተላለፍ የመሰለውን መዝሙር ያለ እይታ ሰማነው። እናም ካለመተያየታችን የተነሣ የመዝሙሩ መልእክት ተዳከመ።

ወደ ሌላው ሰባኪ መለስ ልበልና የመግቢያ ማግባቢያዬን ጽሑፌን ልደምድም። ስብከቱን «ተነሡ!» በሚል «ወታደራዊ» ትእዛዝ ጀመረ፤ ተነሣን። ጸልዮ ደግሞ እንድንቀመጥ አዘዘን፣ ተ

ቀመጥን፣ ከዚያም ተናገረን።

በንግግሩ ሁሉ ከመቆሙ ሌላ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አላደረገም፤ የንግግሩ መልእክት ሙሉ እንዲሆን የፊት ገጽታውንና የድምጽ አወራረዱን ለአፍታም አልቀየረም። ከሰውነቱ አፉ ብቻ ይናገር ስለ ነበር ተንቀሳቅሷል። ቀሪው ግን «እንደ ጅብራ» ቆሞ ቀረ። ከዚህም የተነሣ መልእክቱን ሰበከ ሳይሆን፣ አነበበው ሊባል ተገባው።

* * *

እንግዲህ ከላይ ያነሣኋቸውን ገጠመኞች ሊተዉ ይገባቸዋል ልል ነው። ማረሚያቸውም በዕይታ የሚተላለፉ መልእክተኞች ናቸውና የተሻለ እንዲያግባቡ አጃቢያቸውን አንነጥል፡- እነርሱም አግባብነት ያላቸው የሰውነት እንቅስቃሴዎች ናቸው - «የሰውነት ቋንቋ»። ዐይኖቻችን ተገልጠው እንደ መልእክቱ ይዘት ሲጣቀሱ፣ ሲፈዙ፣ ሲያስጠነቅቁ ሲታይ፣ ግንባራቸው ሲዘረጋ፣ ሲሸበሸብ፣ እጆቻችን ሲዘረጉና ሲታጠፉ፣ ጣቶቻችን ሲያመላክቱና ሲያስጠነቅቁ፣ ድምፃችንም ሲምዘገዘግ፣ ዝግ ሲል፣ ሲያስደነግጥ፣ ሲያባብል መልእክቱ ጉልበተኛ ይሆናል።

መቼም ሰውን ከሌላው ሕያው ፍጥረት የለየው ዋንኛ ነገር በአንደበቱ መናገሩ ነው። የሚሰማና የሚናገር፣ የሚጽፍና የሚያነብ ባለበት ሁሉ የአንደበት ቋንቋ መልእክት በመሆን በላኪና በተቀባይ መካከል ተገኝቶ መንፈሳዊውንና ቁሳዊውን ነባራዊ ክስተት በመግለጹ ቋንቋ የሰው ግላዊ ሀብት ነው። ይህንንም ስንል የማሰብ ችሎታውንና የመሥራት አቅሙን አልዘነጋነውም።

በአኳያው ግን በአብዛኛው በቋንቋ እየታገዙና በከፊል ራሱን ችሎ በመቆም በሁለት ሰዎች ወይም በብዙ መካከል ተገኝቶ ለሰው ልጅ እንደ «መግባቢያ» ከሚያግዘው «ከንግግር-አልባ የመግባቢያ ዘዴ ዎች» አንዱ «የሰውነት ቋንቋ» ነው። እኔም በዚህ ጽሑፍ ለማስተዋወቅና ለጥናት ለመጋበዝ እንዲያግዝ በማለት ለመነሻነት አቅርቤ ዋለሁ።

ሰዎች «በሰውነት ቋንቋ» (Body language) መግባባት መቼ

ጀመሩ? ለሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ ባይኖርም፣ መግባቢያው የዕድሜ ባለጠጋ መሆኑ ግን ተረጋግጦአል። አገልግሎቱ በሳይንሳዊ መንገድ ሥራዬ ተብሎ መተንተን የጀመረበት ጊዜ ግን እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከ1970 ዓ.ም በኋላ ነው። የዚህ ጥናት ውጤትም በብዙዎች ዘንድ ሊጠና የተገባው ተወዳጅ ዘርፍ አስደርጎታል። እንደ አጥኚዎቹ አተነባበይ፣ «ወደፊት እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ ሊሰጥ ይገባል» ብለዋል። እርስዎም አባባላቸውን ለማረጋገጥ ጎብረተሰቡን እንደ ሀብትዎ ቆጥረው የራስዎንም የሰውነት አቋምና እንቅስቃሴውን በማስተዋል ምን ያህል ሊያግዝ መቻሉን ከዛሬ ጀምረው ማጥናት ይችላሉ።

በጥናትዎ ውስጥ ግን አጀማመርዎ የሰውነት ቋንቋ (Body language) «አብሮን የሚወለድ? ወይስ በዘር የሚወረስ? ወይስ የምንማረው? ወይስ ባህላዊ ነው?» የሚል ጥያቄን መልስ ለማግኘት በመጣር ባይሆን ይመረጣል። የዚህ ምክንያቱ፣ «ቁርጥ ያለ መልስ የለውም» የሚል ነው።

ለምሳሌ፣ ሕፃናት ሲወለዱ የእናታቸውን ጡት ለመጥባት ፈጥነው መጀመራቸውን ስንመለከት፣ ከማን ተማሩ? ብንል ማየት የተሣነው ሕፃንስ የሚመለከተው ምንም ሳይኖር ለሚያስፈልገው ጉዳይ ፈገግታን እንዴት በፊቱ አሳየ? አብሮት የተወለደ የንግግር አልባ የሰውነት መግባቢያው ነው ሊያሰኝን የሚያስችል ይመስላል።

አጣምረን ስንቀመጥ በአጠማመራችን የግራው እግር በቀኙ ላይ ነው የሚውል? ወይስ የቀኙ በግራው? ለዚህ ጥያቄ ብዙ ሰዎች ሁኔታውን ነቃ ብለው አሁን ካልሞከሩት በቀር ይሄ ነው ማለት ያስቸግራቸዋል። ሆኖም ግን፣ ሁኔታው በብዙዎች ዘንድ ሳይቀየርና ሳይሻሻል በተመሳሳይ ሁኔታ ሲከናወን ይገኛልና ለልጅ ልጅ የሚሻገር ነው የሚለውም ሳያስኬድ አይቀርም።

በተጨማሪም፣ አስተውላችሁት ከሆነ ወንዶች ኮታቸውን ለመልበስ ሲጀምሩ አብዛኛዎቹ የቀኝ ክንዳቸውን አስቀድመው ሌላውን ያስከትላሉ። በሴቶች ግን እንዲህ አይደለም። የግራ ክንዳቸውን ወደ ኮቱ እጅጌ አስቀድመው ይልካሉ። ይህ እንግዲህ

በማየት መለመዱን አስከትሎ ባህላዊ ሆኖ ይሆናል።

«የሰውነት ቋንቋ» (Body language) አብዛኞቹ በሁሉ ዘንድ በተ መሳሳይነት አንድን ትርጉም ብቻ በየአገሩ ሊሰጡ ሲችሉ፣ በአንጻሩም ከአገር አገር፣ ከባህል ባህል የተለያየ ትርጉም በአንዱ «የሰውነት ቋንቋ» ሊታይ መቻሉን ማወቅ ሌላው አስፈላጊ ነገር ነው። ለምሳሌ፣ በመላው ዓለም የሰዎች ሁሉ ደስተኝነት በፈገግታ መገለጽ፣ ሲያዝኑና ሲከፉ ፊታቸው መደበቡ በሁሉ ዘንድ ትክክል ሲሆን፣ የራስ ላይ ታች ንቅናቄም ለአወንታ፣ የግራ ቀኙም ለአሉታ መዋሉ በማግባቢያነቱ በአንዳንዶች ዘንድ እያሻማ መሆኑን ልብ ማለት ተገቢ ነው።

አሻሚውና በብዙ ሊያሳስበን የሚገባው «የሰውነት ቋንቋ» (Body language) በአንድ አገር የነበረውን ትርጉም አጥቶ በሌላ አገር ሌላ ፍቺ ሲይዝ መገኘቱ ነው። አውራ ጣትን ምሳሌ አድርገን እናስተ ውለው።

አውራ ጣት በአውስትራሊያና በኒውዚላንድ የሚሰጠው ፍቺ ሁለት ነው። አንዱ ጋ የ«አምን፣ ይሁን» ሲሆን፣ ሌላው ዘንድ ግን «አስነዋሪ ስድብን» ያመለክታል።

እንግዲህ «የሰውነት ቋንቋ» (Body language)ን በአግባቡ ለመጠቀምና ከሰዎች ጋር በሚኖር ግንኙነት የተዋጣ አገልግሎት ለመስጠት ከአገር አገር ያለውን ልዩነት ማስተዋሉ ባለመግባባት ከመራራቅ ስለሚያድን አገሩን ለቅቆ ባህሉና ሕዝቡ ወዳልሆነ ስፍራ ለሚሄድ ሰው፣ «በሮም ስትቆይ እንደ ሮማውያኑ አድርግ» የሚለውን አነጋገር ማስተዋሉ ጥሩ ነው።

«የሰውነት ቋንቋ» (Body language) ከንግግር ቋንቋ ጋር የሚመሳሰል አንድ ዋንኛ ጠባይ እንዳለው ማወቅ መግባባትን በማገዝ ከስሕተት የምንወገድበትን ፍንጭ ሊያሳየን ይችላል።

የንግግር ቋንቋ የራሱ ቃል፣ ሐረግ፣ ዐረፍተ ነገር እና ሥርዓት አለው። በቋንቋው ውስጥ ቃል ብቻውን ለማግባባት ፋይዳ የለውም። ሐረግ ዐረፍተ ነገርን ማስከተል አለበት። በጽሑፍ ሲሆንም፣ ሥርዓተ ነጥብን መጨመር ተገቢ ነው። የሰውነት

ቋንቋም ልክ እንዲሁ ነው። በአንድ ውሱን የሰውነት እንቅስቃሴ ብቻ በቂ ትርጉም መስጠት አይቻልም፣ ልክ እንደ ቃል። ቢሰጥ እንኳን አሻሚነቱ ይበዛል። ስለዚህ፣ ዐረፍተ ነገር ሆኖ ፍቺውን እንድናገኝ፣ ክትትል አጃቢ እንቀስቃሴን ከሁኔታው ጋር አብሮ ማጤን ያስፈልጋል። ለምሳሌ፣ በአውቶቡስ የመጠበቂያ ስፍራ (ፌርማታ) አንድ ሰው ሰውነቱን ሰብሰብ አድርጎ እጆቹን በደረቱ ላይ፣ እግሮቹንም በማጣመር ካፊያውን በመሸሽ ምሶሶውን ተደግፎ ቢታይ፣ «ብርድ ይዞታል ወይም አውቶቡስ ይጠብቃል» ብትሉ፣ ግምታችሁ በአብዛኛው ትክክለኛ ነው። ግን ሕዝብ ባለበት ቦታ በአንድ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ያን መሳይ ሰው ፈንጠር ብሎ በዚህ መልኩ ብታዩት፣ ሰውየው በመደረግ ላይ ያለውን ሁኔታ የሚቀበል መንፈስ እንደሌለው ሊያስገነዝባችሁ ይችላል።

ይህን «የሰውነት ቋንቋ» (Body language)ን ባልተለመደ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ቢሞከር የማሳጣትና የማደናገርንም ፍቺ ሊሰጥ ይችላል። ለምሳሌ፣ ውሸተኞችን እንመልከት፡-

በጥናት እንደተገለጸው፣ መልእክትን በትክክል የሚያስተላልፈው ውስጣዊ አእምሮአችን «መልእክትን» ወዲያው በትክክለኛው ገጽታው ስለሚያስተላልፍ፣ ሰውነታችን በአንደበታችን ላይ በመነገር ካለው ውሸት ጋር ሲያጋጨን ይገኛል። ውሸታሞች ልክ መዋሸት እንደ ጀመሩ የተክለ ሰውነታቸው እንቅስቃሴ ሊቃረናቸው ይጀምራል።

«እየዋሸኝ ነው» የሚያሰኝ ላብ ችፍ ይላል፣ ወይም ከንፈር ይንቀጠቀጣል፣ ወይም ቃል ይሰባብራል፣ ወይም ደግሞ ግንባር ዘርጋ ኮምተር ሲል ይታያል። ለዚህም ነው የራሳቸው ያልሆነ ባሕርይ ተላብሰው የሚተውኑት ተዋንያን፣ የገበያ አስተዋዋቂዎችና በመሰል የሥራ ዘርፍ የሚገኙ ባለሙዎች ራሳቸውን ለማሳመን ወደ ሕዝቡ ፊት ከመቅረባቸው በፊት የድግግም ልምምድን የሚያደርጉት።

«የሰውነት ቋንቋ»ን አገልግሎት ስፋትና ጥበት ደግሞ በጋራ

ለማየት እንሞክር፡- ጓደኛ ከጓደኛ ወይም አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር በሚያደርገው መግባባት ሰፊ ትውውቅ ካላቸው በርካታ የሰውነት ቋንቋን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ሕዝብ በበዛበት ቦታ ግን በቁጥር ሊሆን ወይም ጭራሽ ላይኖር ይችላል።

ለምሳሌ፣ በተጨናነቀ አውቶቡስ ውስጥ የማታውቀውን ሰው ማናገር ቀርቶ ድንገት የምታውቀውን እንኳ ብታይ «እኔም አለሁ» ለማለት ትጠቅሰው ካልሆነ በቀር ከዚህ ያለፈ አይባልም፣ በዙሪ ያሀም ያሉትን በዓይኔ እየዞርኩ ልመልከታቸው ብለህ አትደፍርም። በአሳንሰር (ሊፍት) ውስጥ ወደ ፎቅ ለመውጣት ወይም ለመውረድ ብለህ ብትገኝ በውስጡ ያሉትን የማታውቃቸውን ሰዎች ማየት ትተህ እይታህ ምናልባት በስንተኛው ፎቅ ላይ መድረስህን ከሚያሳየው ቁጥር ላይ ማንጋጠጥ ብቻ ይሆናል። እንግዲያስ የሰውነት ቋንቋ ብዙ ሕዝብ ባለበት፣ በማትተዋወቅበት ስፍራ ሊቀንስ ወይም ከእነጭራሹ ላይኖርም ይችላል ማለት ነው።

በእጅ መዳፍ አቀማመጥ ስለ «ሰውነት ቋንቋ» (Body language) የተጀመረውን የመነሻ አሳብ በመመልከት ጽሑፉን ልጨርስ። በታሪክ ውስጥ መዳፍን በፊት ለፊቱ ዘርግቶ ማቅረብም ሆነ ማሳየት የእውነተኛነትን፣ የታዛዥነትንና የወዳጅነትን ትርጉም ይይዛል። ብዙ ቃለ መሃላዎች መዳፍን በልብ ላይ በማድረግ ሲገልጹ፣ ለምስክርነቱም የቆመ ሰው መዳፉን ወደ ዳኛው መልሶ ቃል ሲሰጥ ተስተውሏል። መጽሐፍ ቅዱስንም በግራ እጅ በመያዝ የቀኙን እጅ መዳፍ በላዩ በማድረግ እውነተኛነቱን ያስመሰክርበታል። መዳፍ ለግልጽነት እንደ መዋሉ፣ ለአሸናፊነት እና ለማስጠንቀቂያ በግልብጡ ሲያገለግልም ተስተውሏል። እንግዲያስ የሰውነት ቋንቋ የማግባባት አቅም ካለው፣ በእነዚህ ንግግር - አልባ በሆኑ መግባቢያ ዎች ሁሉ ላይ ጥናትን በማድረግ የተሻለ ግንኙነት ሊመሠረት ይችላል እላለሁኝ። በተለይም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአገልጋዮችና በተገልጋዩ ግንኙነት ላይ በሚያስከትለው በጎ ውጤት ወንጌልን በግልጽነት በማድረስ አቅሙ አጋዥነቱ ብዙ መሆኑን ልብ የሚል ልብ ይበለው።

መረጃ መጻሕፍት

1. Allan Peace, Body Language: How to Read Other Thoughts by Their Gestures, Camel Publishing Company, 1980.
2. Burgoon Saine, The Unspoken Dialogue. An Introduction to Non - verbal Communication, Houghton Company, 2001.
3. Wall Work, J. E. Language and People. New York Press, 1988.
4. Engel F. James, How to Communicate The Gospel Effectively. AC Press, 1988.
5. Egan Gerard, Jnkr Personal Living, Bayola University and Chicago, 1990.
6. Weinberg Sanford B. Group Communication, U.S.A. Press, 1981.

«ኢትዮጵያ እና አርባ ሁለቱ ጥቅሶቿ»

ድሮ ድሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ስሞች ሁሉ የተባ ረኩና የተቀደሱ ይመስሉኝ ነበር፤ ኋላ ላይ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አማኑኤል እንዳለ ሁሉ ሳጥናኤልም መኖሩን፣ እግዚአብሔ ር እንዳለ ሁሉ ዲያብሎስም መኖሩን ልብ አልኩኝ፡፡ የአገራት ስሞችን በሚመለከት ኢትዮጵያ 42 ያህል ጊዜ በመጠቀሷ ስገረም፣ በትይዩ ግብፅም የኢትዮጵያን አምስት እጥፍ ማስቆጠሯን አስተ ዋልኩ፤ ይልቁኑ እስራኤል ስሟ ከዳር ዳር ተነሥቶ አገኘሁ፡፡

በዛሬ ግርድፉ አሳቤ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመገኘቱ አንባቢና ሰሚ ያለው መረዳት ምን ይመስላል? የሚለውን ላጣቀም ፈልጌያለሁ፡፡

በ1990 ዓ.ም መነሻ ላይ አንድ «የበቁ» ባህታዊ፣ «እግዚአብሔ ር ኢትዮጵያን ብቻ ይወዳታል፤ በዓለም መጨረሻ ሌሎቹን ሁሉ ሲያጠፋ የሚያተርፋት እርሷን ብቻ ነው፣ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ ተስፋ ተገብቶላታል» በሚል

መልእክታቸው ተከታያቸው መብዛቱን አስታውሳለሁ። በ1993 ዓ.ም በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ የመሪዎች ስብሰባ ላይ ደግሞ ሰባኪው፣ «ኢትዮጵያ፡- ዓለምን ሁሉ በወንጌል ለመድ ረስ የእግዚአብሔር ብቸኛ ገጸበረከት ናት፣ የዚህም መረጃው ስሟ በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ተነሥቷል» ማለታቸውን ልብ እላለሁ። በቅርቡ በ1995 ዓ.ም የሥራ ባህላችን ሙትነት እየተ ገለጸ፣ ስንፍናችን፡- በአገር አቀፍ ደረጃ በታታሪነቷ እስካልተለወጠ ወዮልን የሚል ማብራሪያ እየተሰጠ ሳለ፣ ተወያዮች ጎራ ከፍለው የየራሳቸውን ለማጠናከር «ኢትዮጵያ» የሚለውን ስም እያነሡ ብዙ ብለዋል።

ለጎራ መከፈሉ ግን መንሥኤው ለዛሬዋ ኢትዮጵያ ድህነት ቀዳሚ ተጠያቂዎቹ መንፈሳውያን አባቶች ናቸው የሚል ፍልቅቅ አሳብ በመነሣቱ ነበር። አንሺው፡- ገበሬው ለሺህ ዓመታት በቀሳውስቱ እየተወገዘ እንዳይሠራ ተደርጓል፣ ከ365 ቀናት በዓላትን ያልያዘችና ያልደረበች ከአንድ ቀን በቀር ምንም የለም፣ እግዚአብሔ ር ግን ለፈጠረው ሰው የሰጠው ቀዳሚ ትእዛዝ አለመሥራትን ወይም በበዓላት ስም መቦዘንን ሳይሆን፣ «በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ» (ዘፍጥ. 3፡19፤ ድ.ት.) የሚለውን ነው። አዲስ ኪዳንም ሊሠራ የማይወድ አይብላ (2ኛ ተሰ. 3፡10) በማለቱ፣ የእግዚአብሔ ር ሕዝብ ነኝ የሚል በክርስትና ስም የተጠራ ሁሉ በመሥራት መበርታት አለበት። ይህ ግን በተግባር እንደ ታየው፣ ተ ደማጭ የሆኑ መንፈሳውያን አላስተማሩም፣ ሠርተውም አላሳዩም በተባለ ጊዜ እንደ ነበር ልብ እላለሁ።

ለዚህ ንጡር የመፍትሔ አሳብ የተሰጠው ምላሽ አበረታችም ተ ቃዋሚም ነበር።

ተቃዋሚዎች በጋራ የተስማሙት፣ እግዚአብሔር ከኢትዮጵያ ጋር ጉዳዩን አልጨረሰም፤ እርሱ ራሱ የልመና እጆቻችን በጥጋብ ይተካዋል፤ ስማችን በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ ተነሥቷል እና የሚል ነበር።

ግና የኢትዮጵያ ስም የተነሣባቸውን ቦታዎች አይተን፣ የተ

መኩባት እርሷ በምን በምን ጉዳዮች ላይ መጽሐፍ እንዳነሣት አጢነን ማጠቃለያ ብንሰጥ፣ ለተሻለ መፍትሔ የምንነሣሣ ይመስለኛል። ከዚህም የተነሣ እስቲ ተከታዩን ሠንጠረዥና እና ማጠቃለያዬን አይተው የሚሉትን ይበሉኝ።

	ኢትዮጵያን ጠቃሽ ጥቅስና ንባቡ	አጠቃላይ መልእክቱ	ተፈላጊው ቁም ነገር
ዘፍጥ. 2:13	... የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል።	በዘፍጥ. 2:8-17 ላይ ያተኩራል፤ በኤድን ገነት እግዚአብሔር የፈጠረውን ሰው አኖረ፤ በዚያ ግን ወደ አራት አቅጣጫዎች የሚፈስ ወንዝ አለ፤ ከወንዞቹ አንዱ ኢትዮጵያ በተሰኘችው ምድር ዙሪያ ይፈሳል።	የኢትዮጵያ ስም የተነበበት ብቸኛ ምክንያት ግዮን የተባለው ወንዝ የሚያካልልበትን ለመግለጽ ብቻ ነው።
2ኛ ነገሥ. 19:9	... እርሱም፦ የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሊወጋህ መጥቶአል የሚል ወሬ በሰማ ጊዜ ደግሞ ወደ ሕዝቅያስ መልእክተኞችን ላከ፤	2ኛ ነገሥ. 19:1-37 ባለው ላይ ያተኩራል፤ እስራኤል በአሦር ጦር ልትወረር በሆነበት ወቅት ሕዝቅያስን በማገዝ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከጦኑ ቆሞለት እንደ ነበር ያስገነዝባል።	ኢትዮጵያ በጦር ኃይል እገዛ በማድረግ የአሦርን ጦር ለመውጋት መነሣቷን ያመለክታል።
አስ. 1:1	በአርጤክስስም ዘመን እንዲህ ሆነ፤ ይህም አርጤክስ ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሀያ ሰባት አገሮች ላይ ነገሠ።	አስቴር 1:1-22 አርጤክስስ ቤተ መንግሥቱን በሱሳ ከተማ አድርጎ ቢቀመጥም፤ የግዛቱ ክልል ግን መቶ ሀያ ሰባት አገሮችን በመግዛት ላይ ያተኮረ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለውን የመንግሥት ግዛት (ወሰን) ከጫፍ ጫፍ ሲያነሣ ኢትዮጵያ የአንዱ ጫፍ ሆና መነሣቷን ይገልጻል።	የኢትዮጵያ ተነሺነት የተፈለገው የግዛት ድንበርን ለማንሣት 127 አገሮችን በመጥቀስ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለውን ለማሳየት እንዲያግዝ ነው።

አስ. 8፡9	መርዶክዮስም ስለ አይሁድ እንዳዘዘው ሁሉ ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሀያ ሰባቱ አገሮች ላሉ ሹማምትና አለቆች አዛውንትም ለእያንዳንዱም ሕዝብ እንደ ቋንቋው . . . ተጻፈ።	አይሁዳውያን በሀማ አማካይነት ሊጠፉ የታወጀውን ትእዛዝ መርዶክዮስ በሌላ የመታደግ አዋጅ በመቀየሩ ይህ የምስራች ለአይሁዳውያን ሁሉ እንዲዳረስ በመፈለጉ መልእክቱ በ127ቱ አገሮቹ መላኩን ከዚህም የተነሣ ኢትዮጵያ በአስቴር 1:1 መሠረት መነሣቷን ይገልጻል።	በግዛቱ ካሉት አገሮች ኢትዮጵያ አንዷ ብትሆንም፣ በዚህ ክፍል ግን ስለ ኢትዮጵያ ለመዘከር ሳይሆን፣ በአገሪቱ ባሉት አይሁዳውያን ላይ ብቻ ያተኮረ ነው።
ኢዮብ 28፡18-19	...የጥበብ ዋጋ ከቀይ ዕንቁ ይልቅ ይበልጣል። የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን አይተካከላትም፣ በጥሩም ወርቅ አትገመትም።	ጸሐፊው የጥበብን ምንነት ለመግለጽ የተጠቀመበት የንጽጽር ዘይቤ በኢትዮጵያ ከሚገኘው የከበረ ማዕድን ጋር ማመሳሰል ነው፤ ከዚህም የተነሣ የማዕድኑ መገኛ አገር የት መሆኑን ለመግለጽ የተፈለገ ነው።	የከበሩ ድንጋዮች በብዙ ድካም እንደሚገኙ ኢዮብ 28 ካብራራ በኋላ፣ የመልእክቱን ጭብጥ ግን በቁጥር 28 ላይ ያደርጋል። «እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው፤ ከክፋትም መራቅ ማስተዋል ነው» በማለት ትኩረቱ ኢትዮጵያ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ጥበብ መሆኑን የሚገልጽ ነው።

መዝ 68:31	ሰልፍን የሚወድዱትን አሕዛብን በትናቸው። መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።	መዝ. 68:1-35 ያለው ገለጻ በእግዚአብሔር ላይ የሚዘባበቱ ሁሉ እንደ ተበተኑና እንደ ጠፉ ከገለጸ በኋላ፣ እስራኤልን ደግሞ የሚቋቋሙና የሚገዳደሩ ሁሉ እንደሚቀጡ ይዘረዝራል። በዚህም አካሄድ ቁጥር 31 በግብጽ ተቋቋሚዎችም ሆኑ ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር አሸናፊነት የተነሣ ድል ተነሥተው እጃቸውን እንደሚሰጡ በማመልከት የምድር ነገሥታት ሁሉ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ ቁጥር 32 ያሳያል።	የኢትዮጵያ ተነሺነት በእግዚአብሔር ኃይል እንደምትንበረከክ ገላጭ እንጂ ከበረከት ጋር ወይም እግዚአብሔርን ሊያውቅ ከተዘጋጀ ሕዝብ ማንነት ጋር በተያያዘ አልተነሣም። (የዚህን ክፍል ሰፊ ማብራሪያ በማጠቃለያው ላይ ይመልከቱ።)
መዝ. 87:3-4	የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፣ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል። የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁ፤ እነሆ፣ ፍስጥኤ ማውያን፣ ጢሮስም የኢትዮጵያም ሕዝብ እነዚህ በዚያ ተወለዱ።	መዝ. 87:1-7 የመልእክቱ መነሻ ለእስራኤል መገኛ የሆነውን ያዕቆብን በማንሣትና የሕዝቡ ከተማ በሆነችው በጽዮን መወለድ የሚያኮራ መሆኑን ይዘክራል፤ ኢትዮጵያንም ከፍልስጥኤምና ከጢሮስ ጋር አብሮ በመቁጠር ይጠራታል።	የኢትዮጵያ ተነሺነት ከባቢሎን፣ ከፍልስጥኤምና ከጢሮስ እንደ አንድ የአሕዛብ ምድር ተደርጎ ከመቆጠር ባሻገር ሌላ ተጨማሪ መኩሪያ ያልተነሣላት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

ኢሳ. 18:1	በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላለች፣ ክንፍ ያላቸው መርከቦች ላሉባት፣ መልእክተኞችን በባሕር ላይ የደንገል መርከቦችንም በውኃ ላይ ለምትልክ ምድር ወዮላት!	ኢሳ. 18:1-17 ክንፍ ያላቸው (መርከቦች ጦረኞች ወራሪዎች) የሚገለጹበት ዘይቤ ነው። በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ እነዚህ ወራሪዎች መኖራቸውን በማመልከት እነርሱ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ቢነሡ እንደሚጠፉ የሚያስጠነቅቅ መልእክትን ይዟል።	በዚህ ክፍል ኢትዮጵያም ሆነ ከወንዞቿ ማዶ ያሉ ሕዝቦች፣ ወራሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ ጥፋት ሊመጣባቸው እንዳለ የተጻፈ መልእክት ነው።
ኢሳ. 20:3-5	እግዚአብሔርም አለ፦ ባሪያዬ ኢሳይያስ በግብጽና በኢትዮጵያ ላይ ሦስት ዓመት ለምልክትና ለተአምራት ሊሆን ራቁቱንና ባዶ እግሩን እንደ ሄደ፣ እንዲሁ የአሦር ንጉሥ፣ የግብጽንና የኢትዮጵያን ምርኮ፣ ጕበዛዝቱንና ሽማግሌ ዎቹን፣ ራቁታቸውንና ባዶ እግራቸውን አድርጎ ገላቸውንም ገልጦ፣ ለግብጽ ጕስቁልና ይነዳቸዋል። እነርሱም ከተስፋቸው ከኢትዮጵያ፣ ከትምክሕታቸውም ከግብጽ የተነሣ ይፈራሉ፣ ያፍሩማል።	ኢሳ. 20:1-6 የአሦር ንጉሥ እስራኤልን ያንቀጠቀጠ መንግሥት ነው፤ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ከዚህ ግፊት የተነሣ በግብጽ እና በኢትዮጵያ ለመደገፍ እራሱን አዘጋጅቶ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ኢሳይያስን በማስነሣት ለሦስት ዓመት በግብጽና በኢትዮጵያ ራቁቱን ሆኖ በባዶ እግሩ እንዲመላለስ ያዘ ረዋል፤ በዚህም ሕዝቅያስ በኢትዮጵያ እና በግብጽ መመካት ዋጋቢስ መሆኑን በማስረዳት በኢትዮጵያና በግብጽ የተመኩ ሊሰደዱና ሊያፍሩ እንደሚችሉ የሚያስረዳ ገለጻ	በዚህ ጥቅስ ኢትዮጵያ በበጎ አትገለጽም፤ ተስፋ ቢያደርጉባት፣ የምታዋርድ፣ ቢደገፉባት የምታገል አገር ልትሆን ስለምትችል፣ እስራኤል የቅርብ ሩቅ በሆኑት በግብጽም ሆነ በኢትዮጵያ እንዲያምፁ ያስ ረዳል።

ኢሳ. 37፡9	. . . እርሱም የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሊዋጋህ መጥቶአል የሚል ወሬ ሰማ፡፡	ኢሳ. 37፡1-38 የእስራኤል ንጉሥ ሕዝቅያስ የአሦር ጦር ጥቃትና ወረራ የሰፋ መሆኑን ባስተዋለ ጊዜ ወደ ነቢዩ ኢሳይያስ መልእክተኞችን ላከ፤ የኢትዮጵያ ንጉሥ ደግሞ ለሕዝቅያስ ያግዝ ዘንድ ጦሩን በማምጣት ላይ እንደ ነበር የጦሩ አዛዥ ሰናክሬም መስማቱን ይዘ ረዝራል፡፡	የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ የሶሪያን ጦር በመውጋት ሕዝቅያስን ለማገዝ መነሣቱን ይገልጻል፤ እግዚአብሔር ግን የኢትዮጵያ እገዛ ስለ ኖረ ሳይሆን፣ የአሦር ንጉሥ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ተሳለቀ ብቻ እንደሚያጠፋው በነቢዩ መልእክትን የላከበት ጭብጥ
ኢሳ. 43፡3	እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኃኒትህ ነኝ፤ ግብጽን ለአንተ ቤዛ አድርጌ፣ ኢትዮጵያንና ሳባንም ለአንተ ፋንታ ሰጥቻለሁ፡፡	ኢሳ. 43፡1-28 እግዚአብሔር ያዕቆብን (እስራኤልን) በአጽንኦት የሚመክረው መልእክት (በቁ. 5) «እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ»፣ (በቁ. 15) «ቅዱሳችሁ የእስራኤል ፈጣሪ ንጉሣችሁ፣ እግዚአብሔር እኔ ነኝ» በማለት ብርቱ መመኪያ እርሱ ብቻ መሆኑን የሚገልጽበት ምዕራፍ ነው፡፡	በዚህ ስፍራ ግብጽንና ኢትዮጵያን ማንሣት የተፈለገበት ዐቢይ ምክንያት እግዚአብሔር ለእስራኤል እንክብካቤን ማድረጉን ከገለጸበት ሥራው አንዱ እነዚህን ሕዝቦች ስለ እነርሱ ተላልፈው እንደ ተሰጡ የገለጸበት ጭብጥ ነው፡፡ በቁ. 4፣ «ስለምወዳችሁ ሕይወታችሁን ለማዳን ሕዝቦችንና መንግሥታትን አሳልፌ እሰጣለሁ

ኢሳ. 45:14	እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል፦ የግብጽ ድካምና የኢትዮጵያ ንግድ ቁመተ ረጅሞችም የሳባ ሰዎች ወደ አንተ ያልፋሉ፤ ለአንተም ይሆናሉ፤ እጀቻቸውም ታሥረው ይከተሉሃል፤ በፊትህም ያልፋሉ፣ ለአንተም እየሰገዱ፦ በእውነት እግዚአብሔር በአንተ አለ፣ ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም ብለው ይለምኑሃል።	ኢሳ. 45:1-25 እግዚአብሔር ልዑል መሆኑን ምዕራፉ በስፋት ይተነትናል። እርሱ ብቻ እግዚአብሔር እንደ ሆነና ከእርሱ ሌላ አምላክ አለ መኖሩን እያረጋገጠ (ቁ. 18)፣ በንጽጽሩ ከእስራኤል ውጭ የሆኑት አሕዛብ ግን ጣዖት ሠሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ (ቁ. 16) ሊያፍሩ እና ሊዋረዱ እንደሚገባቸው ያብራራል፣ በዚህም ከሚዋረዱት ውስጥ በስም ተጠሪዎቹ ግብፅ፣ ኢትዮጵያ፣ ሳባን በማንሣት፣ እነርሱም ከመዋረዳቸው የተነሣ እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን ማመናቸውን ይገልጻል (ቁ. 14)።	ኢትዮጵያ፣ ግብጽ እና ሳባ በቅጣት ውስጥ እንደሚያልፉ፣ ሕያው እግዚአብሔርን ሳይሆን፣ በሌሎች አማልክት ሥር የነበሩ መሆናቸውን፣ ኋላም እግዚአብሔርን በማወቅ ተገዥ ሊሆኑ መቻላቸውን በመግለጽ ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሳባ በቅጣት ወደ ሕያው እግዚአብሔር ሊመጡ እንደሚችሉ ይጠቁማል፡
ሕዝ. 29:10	ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ... እነሆ፣ በአንተና በወንዞችህ ላይ ነኝ፣ የግብጽንም ምድር ከሚግዶል ጀምሮ እስከ ሴዌኔና እስከ ኢትዮጵያ ዳርቻ ድረስ ውድማና ባድማ አደርጋታለሁ።	ሕዝ. 29:1-21 ዝርዝር እግዚአብሔር በሕዝቅያስ በኩል ስለ ግብጽ ወቅታዊና የወደፊት ዕድል ፈንታዋ ምን ሊሆን እንደሚችል ትንቢት ያናገረበት ምዕራፍ ነው። በትንቢቱ ግብጽ እንደምትፈራርስ፣ ኃያልነቷም ተዋርዶ እንደ ድሮም የምታፈራ አገር አለመሆኗን ይናገራል፤ በዚህ ጥፋትም የክልሏ ድንበር ኢትዮጵያን ሊጨምር እንደሚችል ያመለክታል።	ኢትዮጵያ በግብጽ የኃያልነት ዘመን ወቅት በግብጽ ሥር ሆና አልያም እግዚአብሔር በትንቢቱ ፈራርሰው ባድማ በመሆን ከሚቀጡት አገሮች ሌላኛዋ ኢትዮጵያ መሆኗን የገለጸበት ስለሆነ፣ በዚህ ክፍል ኢትዮጵያ በበጐ የተነሣች አገር አትሆንም።

ሕዝ. 30፡4-5፣9	ሰይፍ በግብጽ ላይ ይመጣል፤ ሁከትም በኢትዮጵያ ይሆናል፤ የተገደሉትም በግብፅ ውስጥ ይወድቃሉ፣ ብዛትዋንም ይወስዳሉ፣ መሠረትዋም ይፈርሳል፣ ኢትዮጵያና ፉጥ ሉድም የተ ደባለቀም ሕዝብ ሁሉ ኩብም ቃል ኪዳንም የገባችው ምድር ልጆች ከእነርሱ ጋር በሰይፍ ይወድቃሉ። . . . በዚያ ቀን መልእክተኞች ተ ዘልለው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን ለማስፈራራት ከፊቴ በመርከብ ይወጣሉ እንደ ግብፅም ቀን ሁከት ይሆንባቸዋል፤	ሕዝ. 30፡1-26 የእግዚአብሔር ቃል ወደ ነቢዩ በመምጣት የዋይታ ቀን ከፊታቸው እንደሚመጣ፣ በዚህም ጊዜ ዋንኛው ተቀጪ በሀብታ፣ በጦሯ እና በአማልክታ ተደግፋ የነበ ረችውን ግብጽ በሰይፍ ተሸናፊ ልትሆን እንደሚገባት ይገልጻል፤ አያይዞም በአንድ እንደ ተጠመዱ ወይም እንደ ተባበሩ የሚቆጠሩት ኢትዮጵያ፣ ፉጥ፣ ሉድና መላው ዐ ረብና ሊብያ በአንድነት መጥፋታቸውን ይተነብያል።	ኢትዮጵያ በዚህ ገለጻ ተጠቃሽነቷ ሰላማዊ በሆነ ትንታኔ ሳይሆን፣ ሁከት (ጭንቀት) በዚያን ጊዜ እንደሚሆንባት፣ በተጨማሪም በሰይፍ እንደሚወድቁ ያስረዳል።
ሕዝ. 38፡5-6	. . . ፋርስንና ኢትዮጵያን፣ ፉጥንም ከእነርሱ ጋር ጋሻና የራስ ቍርን የለበሱትን ሁሉ፣ ጋሜርንና ጭፍሮቹን ሁሉ፣ በሰሜን ዳርቻም ያለውን የቴርጋማን ቤ ትና ጭፍሮቹን ሁሉ፣ ብዙዎችንም ሕዝቦች ከአንተ ጋር አወጣለሁ።	ሕዝ. 38፡1-32 እግዚአብሔር በነቢዩ አማካይነት በጎግ ላይ ትንቢትን ይናገራል፤ ጎግ በኃያልነት ተነሥቶ በሰላም የተቀመጠውን የእስራኤልን ሕዝብ ሊያጠፋ ይመጣል፤ በዚህ ወቅት ከጐኑ የሚቆሙለትና በአንድ ሆነው ከሚነሡለት አገራት ውስጥ ፋርስ፣ ኢትዮጵያና ፉጥ የመሳሰሉት ይገኙ በታል፤ እግዚአብሔር ግን በቁጥር 18 ጎግ የእስራኤልን ምድር ሲወጋ ብርቱ ቁጣው በእርሱ ላይ ሆኖ እንደሚነሣ ይተነብያል።	ኢትዮጵያ የእስራኤል ጠላት ሆኖ ሊነሣ ላለው ከጎግ ጋር ተባባሪ መሆኗን ይጠቁማል፤ በውጤቱም አጠቃላይ ቅጣትን እግዚአብሔር በጎግ ላይ በማድ ረጉ የእግዚአብሔ ር ታላቅነትና ቅድስና ይታያል፤ በሕዝቦች ሁሉ ፊት ማንነቱን በመግለጹ ተገዥ ይሆናሉ (ቁ. 23)።

ናሆም 3:9-10	. . . ኢትዮጵያና ግብጽ የማይቆጠር ኃይልዋ ነበሩ ፉጥና ልብያ ረዳቶችዋ ነበሩ። እርስዋ ግን ተማርካ ፈለሰች፣ ሕፃናቶችዋ በመንገድ ሁሉ ራስ ላይ ተ ፈጠፈጡ።	ናሆም 3:1-19 በስፋት የደም ከተማ ስለሆነችው ነነዌ ይዘረዝራል፤ በማጠቃለያው ደግሞ፣ የአሦር ንጉሥ ሆይ! እ ረኞችህ አንቀላፉ፣ መኳንንትህ ዐርፈው ተ ኙ ሕዝብህ ሰብሳቢ አጥተው በተራራ ላይ ተ በትነዋል (ቁ. 18) በማለት ለነነዌ እና ለአሦር የተያያዘ ጥፋትን ያትታል። በዚህ ውስጥ ደግሞ ኢትዮጵያና ግብጽ የነነዌያውያን ጉልበት ሆነው እንደ ነበር፣ ግን በአጠቃላይ እንደ ተዋ ረዱ የሚያስረዳ ንባብ ነው።	የኢትዮጵያ ተ ጠቃሽነት በዘመኑ ከኃያላኑ ጋር ልትሰለፍ ብቃቱ ያላት አገር ትመስላለች። ያ ኃይልና ጉልበት ግን ከእርሷ በበለጠ ለማገዝ ተባባሪ ብትሆንም፣ እንዳልተጠቀመች የሚገልጥ ጭብጥ አለው።
ሶፎንያስ 3:10	. . . ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ፣ የተ በተኑት ሴቶች ልጆቼ ቍርባኔን ያመጡልኛል።	ሶፎንያስ 3:1-20 የኢየሩሳሌም የወደፊት ዕጣ የተዘረዘረበት ምዕ ራፍ ነው። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ባለመታመኑ። ሹሞቹ እና ነቢያቱ ትዕቢተ ኞችና አታላዮች ከመሆናቸው የተነሣ የእግዚአብሔር መዓት እንደሚፈላባት ይገልጻል። በዚህ ውስጥ ግን ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እና የሚማልዱ እንዳሉ ይገልጻል።	ከኢትዮጵያ ወንዞቿ ማዶ ስላሉት ሕዝቦች በተገለጸው ማብራሪያ፣ በዚያ ያሉት ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩና የሚማልዱ ከመሆናቸው የተነሣ እስራኤ ልን ያስቀናሉ።

ከ1-17 ያሉት ጥቅሶች በቀጥታ ኢትዮጵያ የሚል መጠሪያ ያለው አገርን የማያመለክቱ መልእክቶች መሆናቸውን ልብ በሉ።			
ሐዋ. 8:27	እነሆም፣ ሀንደኬ የተ ባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደ ረባ የነበ ረ በገንዘብዋ ም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር።	ሐዋ. 8:1-40 ከዚህ ገለጻው ውስጥ የኢትዮጵያን ሰው ታሪክ የሚያካትተው ከቁ. 26-40 የሚገ ኘው ነው። ንጉሡ ሀንደኬ በወቅቱ እንደ ቅዱስ ይታይ ስለ ነበር፣ እናቱ የመንግሥቱን አስተ ዳደር ታከናውን ነበረ፤ ከዚህም ደግሞ የተነሣ ሀንደኬ እንደ ማዕ ረግ ስም ይጠራል። በዚያን ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው የኢትዮጵያ ሰው ከአሕዛብ ወደ ይሁዲነት የገባ ወይም ተበትነው ካሉት አይሁዶች አንዱ ሊሆን ይችላል። ይህ ሰው ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ሰማ፣ አምኖ ተጠመቀ፣ ወንጌልንም በየከተማው እየሰበከ መመለሱን ይገልጻል።	ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራው የጊዜው የግዛት ክልል ከላይኛ ው ዓባይ ጀምሮ እስከ ካርቱም ድረስ ያለውን የኑብያ ምድር የሚያጠቃልል ነው። በዚህ ገለጻ የኢትዮጵያ መነሣት የክርስቶስ የአዳኝነት ዜና በጃንደረባው አማካኝነት የመጣበትን የምስራች የሚያሳውቅ ነው።
ዘፀአ. 12:1	ሙሴም ኢትዮጵያይ ቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይ ቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ።	ዘፀአ. 12:1-16 ዝርዝሩ እንደሚገልጸው፣ የማርያምና የአሮን በሙሴ ላይ መናገር አንደኛው ምክንያት ኢትዮጵያዊቱን በማግባቱ ሲሆን፣ የዚህም መነሻ ኩሽ የካም ልጅ ሆኖ በደቡብ የዐባይ ሸለቆ ወደ ደቡባዊው ጫፍ ክልል ይኖር የነበረ ሕዝብ ነው (ዘፍጥ. 10:6-7)። ይህ የኩሽ አገርም ኢትዮጵያ ተብሎ ይጠራ ነበር። ማርያምና አሮን ኢትዮጵያዊት የሚለውን ቃል መጠቀማቸው ወገኖቿን ምድያማውያንን በንቀት መናገራቸውን ሲያመላክት፣ ሌ ላው የተቆጡት ኢትዮጵያዊ በማግባቱ ሳይሆን፣ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙ ነት ስለ ነበረው፣ ቀንተውበት ሊሆን ይችላል።	ኢትዮጵያዊቱ በማለቱ ሴቲቱ ሙሴ ወዳለበት ሀገር መጥታ ወይም እርሱ ወደምትገኝበት ደርሶ ሳይወስዳት አይቀርም። በዚህ ቦታ ኢትዮጵያ የተ ጠቀሰችው የሴቲቱን መገኛ ወይም የምን አገር ሰው መሆኗን ለመግለጽ ብቻ ነው።

2ኛ ዜና 14:9-13	ኢትዮጵያዊውም ዝሪ አንድ ሚሊዮን ሰ ዎችና ሦስት መቶ ሰረገሎች ይዞ ወጣባቸው ... አሳም፣ አቤቱ፣ በብዙም ሆነ በጥቂቱ ማዳን አይሳንህም፤ አቤ ቱ... አድነን እግዚአብሔርም በአሳና በይሁዳ ፊት አትዮጵያውያንን መታ፣ ኢትዮጵያውያን ም ሸሹ። አሳም ከእነርሱ ጋር ሕዝብም እስከ ጌራራ ድረስ አሳደዱአቸው፤ ኢትዮጵያውያን ም ፈጽመው እስኪጠፉ ድረስ	የ2ኛ ዜና 14:1-15 ገለጻ ከይሁዳ ንጉሦች መካከል አሳ ቅንና በእግዚአብሔር ፊት መልካሙን በማድረግ ሕዝቡን ያስተዳደረ ንጉሥ ነው፤ የባዕዳን መሠዊያ ዎችንና ማምለኪያዎችን ሁሉ በማፈራረስ ሁሉም እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ ያዘዘና የመራ ንጉሥ ነበር። በዘመኑም የተዋጋው አልነበ ረም። ይህን እየፈጸመ ሳለ ግን ኢትዮጵያዊው ዝሪ ከአንድ ሚሊዮን ጦሩ ጋር ሊወረው መጣ፤ አሳ ይህን ባወቀ ጊዜ ከመዋጋት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ እግዚአብሔርም የኢትዮጵያን ጦር ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ፣ ብዙ ምርኮን ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸውን ይገልጻል።	ኢትዮጵያዊው ዝሪ የተባለው ሰው ኑብያዊው በመባል ይታወቃል፣ አንዳንዶች የግብፅ ንጉሥ ሳይሆንም አይቀርም ይላሉ፤ ጭብጡ ግን እርሱና ተከታዮቹ ኢትዮጵያውያንን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ በተደገፉት በንጉሥ አሳ እና በሠራዊቱ ተሸንፈው መጥፋታቸውን ከመግለጽ ባሻገር፣ ለመዋጋት ያልተነሣሡትን ሕዝቦች በግፍ ለማጥፋት ከመነሣት አኳያ የኢትዮጵያ ትዕቢትን የሚጠቁም ነው።
ኤር. 13:23	በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?	በኤር. 13:1-27 እግዚአብሔ ር ስለ እስራኤልና ስለ ይሁዳ ሲናገር፣ የይሁዳን ትዕቢት እና የኢየሩሳሌምን እብሪት አጠፋለሁ በማለት ለቅጣቱ መንሥኤው ክፉ ማድረግ ለመዳችሁ፣ ከዚህም የተነሣ መልካምን መፈጸም አልቻ ላችሁም (ቁ. 23)፣ ይህም በንጽጽር የኢትዮጵያዊ መልኩ እና የነብር ዝንጉርጉርነት እንደ ማይለወጥ አትለወጡም ይላቸዋል።	በዕብራይስጡ መጽሐፍ ኢትዮጵያዊ የሚለውን ኩሻዊ ይለዋል። በዚህ ክፍል የኢትዮጵያ መልክ ሊቀየር እንደማይችል እናንተ ም ከክፋታችሁም መለወጥ አትችሉም ለማለት የተጠቀሰ አባባል ነው።

ኤር. 38፡7-12	በንጉሡም ቤት የነበረው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርምያስን በጕድጓድ ውስጥ እንዳኖሩት ሰማ . . . ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌክን ከአንተ ጋር ሠላሳ ሰዎች ከዚህ ውሰድ ... ብሎ አዘዘው... ኢትዮጵያዊውም አቤሜሌክ ኤርምያስን፡- ይህን አሮጌ ጨርቅና እላቂውን ልብስ ... አድርግ ... አለው።	ኤር. 38፡1-28፣ ኤርምያስ በኢየሩሳሌም ላይ ትንቢትን ተናገረ። ይህች ከተማ በእርግጥ ለባቢሎን ንጉሥ ሠራዊት አልፋ ትሰጣለች፣ እርሱም ይይዛታል በማለቱ፣ መኳንንቱ በዚህ ተበሳጭተው ነቢዩን በጥልቅ የውኃ ጕድጓድ ውስጥ አስጣሉት። ይህን ተግባራቸውን ንጉሡ በመስማቱ ኢትዮጵያዊውን ሹም አቤሜሌክን በመላክ ኤርምያስ ከተጣለበት ጕድጓድ እንዲወጣ ያስደርገዋል።	በኢየሩሳሌም የተገኘው ኢትዮጵያዊ አቤሜሌክ ተብሎ የተጠራው ሰው ለኤርምያስ ያሳየው ቸርነት በእግዚአብሔር ላይ መታመኑን ይገልጻል። እግዚአብሔርም መልካም አድርጎለታል (39፡15-18)። ይህ ኢትዮጵያዊ የተባለው ሰው ከላይኛው አባይ አካባቢ ይኖር የነበረ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።
2ኛ ዜና 12፡2-4	. . . የግብጽ ንጉሥ ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ ዘመተ፤ ከግብጽ አብረውት የመጡትን አሥራ ሁለት ሺህ ሠረገላዎች፣ ስድሳ ሺህ ፈረሰኞችና ስፍር ቁጥር የሌላቸውን የሊብያ፣ የሱኪሲምና የኢትዮጵያ ወታደሮችን ይዞ የተመሸጉትን የይሁዳ ከተሞች በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ እስከ ኢየሩሳሌም ዘለቀ (ከአ.መ.ት. የተወሰደ)።	2ኛ ዜና 12፡1-16፣ ሮብዓም መንግሥቱን ካደላደለ በኋላ እርሱም ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ሕግ ተዉ ናቁም፤ እግዚአብሔርን ከመበደላቸው የተነሣ የግብጽ ንጉሥ የጦር አጋሮቹን በአንድነት አደራጅቶ ወረራ አካሂዶ የቤተ መቅደሱን ንብረት ሁሉ ዘርፎ መውሰዱን፣ ከዚህም የተነሣ ሮብዓም ራሱን አዋርዶ በመገኘቱ እግዚአብሔር ምሕረት እንዳደረገለት ይገልጻል።	ኢትዮጵያና ተጠቃሾቹ አገሮች በግብጽ ንጉሥ ሥር ሆነው ለጦር ስለ ወጡ በኃይልና በጉልበት ከእርሱ ያነሱ ግን ከእርሱ ዓላማ ጋር ለመተባበር የተዘጋጁ ሕዝቦች መሆናቸውን ሲጠቁም፣ በተጨማሪም በመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ከኢየሩሳሌም ዙሪያ ያሉ ሆነው እግዚአብሔር እስራኤላውያን ባመፁ ጊዜ እንደ በትር ይጠቀምባቸው እንደ ነበር ያስረዳል።

2ኛ ዜና 16:8	... ኢትዮጵያውያንና የልብያ ሰዎች እጅግ ብዙ ሰረገሎችና ፈረሰኞች የነበሩአቸው እጅግ ታላቅ ጭፍራ አልነበሩምን? በእግዚአብሔር ስለ ታመንህ በእጅህ አሳልፎ ሰጣቸው።	2ኛ ዜና 16:1-14፤ አሳ በይሁዳ ነግሦ ሳለ የእስራኤልን ንጉሥ ባኦስ ሊወጋው ሲመጣ አሳ እንደ ቀድሞው በእግዚአብሔር መታመኑን ትቶ የሦሪያ ንጉሥ ወልደአዶር ይረዳው ዘንድ መልእክተኛን ላከ። በመልእክቱም ከባኦስ ጋር ያለውን ውል አስቀድሞ እንዲያፈርስ ስጦታን ላከለት። በዚህ ተግባሩ እግዚአብሔር በባለ ራእዩ አናኒ በኩል በአምላክህ በእግዚአብሔር ታምነህ በነበረበት ወቅት ኃያል ሠራዊት የነበረችውንና የኢትዮጵያንና የሊብያን ጦር በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼህ ነበር፤ ዛሬ ግን በእኔ ስላልታመንህ፣ ጦርነቱ ለአንተ አይደለም ይለዋል።	ኢትዮጵያ እና ልብያ በዚህ ቦታ ላይ የተነሡት አሳን ይወጉ ዘንድ ተሰብስበው በመጡ ጊዜ እንደ ተዋረዱ ለመግለጽ ነው። ከዚህ ገለጻ ልንገነዘብ የሚገባው የኢትዮጵያን ጦረኛ መሆንና በአንድ ወቅት ከጉልበተኞች ተራ የቆመች አገር እንደ ነበረች ነው።
2ኛ ዜና 21:16-17	እግዚአብሔርም በፍልስጥኤማውያንና በኢትዮጵያ አጠገብ የሚኖሩትን የዓረባውያንን መንፈስ በኢዮራም ላይ አስነሣ። ወደ ይሁዳም ወጡ፣ አፈረሱአትም፣ የንጉሡንም ቤት ዕቃ ሁሉ ወንዶች ልጆቹንም ሴቶች ልጆችንም ማረኩ፤	2ኛ ዜና 21:1-20፤ ኢዮራም በኢየሩሳሌም እንዲነግሥ ወንድሞቹንና የእስራኤልን አለቆች ገደለ፤ የአባቶቹንም አምላክ ተወ። በዚህ ወቅት ነቢዩ ኤልያስ አንተ በአባትህ በኢዮሣፍጥ ወይም በይሁዳ ንጉሥ በአሳ መንገድ ስላልሄድህ ከግፍ የተነሣ በመቅሠፍት ትሞታለህ ሲል ይነግረዋል። ለዚህ ደግሞ ከፍልስጤማውያንና ከኢትዮጵያውያን አጠገብ የሚኖሩ ዓረቦችን በኢዮራም ላይ በጠላትነት እንደሚያስነሣበት የሚገልጽ ትንቢትን አዝሏል።	ኢትዮጵያን ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ አጠገብ የሚኖሩትን የዓረባውያንን መንፈስ ማስነሣቱን መናገሩ፣ ጉዳዩ በቀጥታ ኢትዮጵያን የሚመለከት ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ተጠቃሽነት ለስፍራ መለያ ወይም የዓረባውያንን መኖር ለመግለጽ ተፈልጎ የተነሣ ነው።

ኤር. 46:9-10	ፈረሶች ሆይ፣ ውጡ፣ ሰ ረገሎችም ሆይ፣ ንጮዱ፣ ጋሻም የሚያነግቡ የኢትዮጵያና የፉጥ ኃያላን፣ ቀስትንም ይዘው የሚስቡ የሉድ ኃያላን ይውጡ። ያ ቀን ጠላቶቹን የሚበቀልበት የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር የበቀል ቀን ነው።	ኤር. 46:1-28፣ የእግዚአብሔ ር ማዕከላዊ መልእክት በቴብስ አምላክ ላይ፣ በአሞን ላይ፣ በፈርዖን ላይ፣ በግብጽና በአማልዕክቷ ላይ፤ በነገሥታቷም ላይ እንዲሁም በፈርዖን የሚታመኑት ላይ ቅጣት አመጣለሁ (ቁ. 25) በማለት በራሳቸው ተደግፈው የኖሩትን በእስራኤል ላይ ጠላት የነበሩትን እንደሚቀጣ ደጋግሞ ይናገራል። በዚህም ምዕራፍ በስፋት የተገለጸችው አገር ግብጽ እና ቅጣቷ ነው። እግዚአብሔር ኃያል ከሆነችው ከግብጽ ጋር አብረው መመኪያ ሆነው የኖሩትም የኢትዮጵያ እና የፉጥ ኃያላንም በቅጣቱ ሥር መሆናቸውን ይዘረዝራል።	ኢትዮጵያ በዚህ ቦታ የተጠቀሰችው ለግብፅ ሠራዊት ቅጥረኛ በመሆን የጦር ሠራዊቷን ያጮለበቱ ከመሆናቸው የተነሣ ቅጣቱ በባቢሎናውያን አማካኝነት በሁሉም ላይ እንደሚሆን ያ ረጋግጣል። በቁጥር 28 መሠረት፣ እግዚአብሔር ሁሉን ቀጥቶ ሲያጠፋ የገዛ ሕዝቡን ግን ቢቀጣቸውም ፈጽሞ እንደማያጠፋቸው ያ ረጋግጣል።
ዳን. 11:43	በወርቅና በብርም መዝገብ ላይ በከበረችም በግብጽ ዕቃ ሁሉ ላይ ይሠለጥናል፣ የልብያና የኢትዮጵያ ሰ ዎችም ይከተ ሉታል።	ዳን. 11:1-45፣ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ንጉሥ እንደሚነሣ ዳንኤል ይናገራል። ይህ ንጉሥ በእግዚአብሔር ላይ ተ ሰምቶ የማይታወቅ ስድብን ይሳደባል፣ በባዕድ አምላክ ርዳታ ጽኑ ምሽጎችን ይዋጋል፤ ለእርሱም የሚገዙትን ያከብራቸዋል። ይህ ንጉሥ ሌላ ተቋቋሚ ሲመጣበት እንዳለ ባወቀ ጊዜ እርሱን ለመቋቋም የሚያደርገው ወራሪ የግብጽ፣ የልብያ እና የኢትዮጵያ ሰዎች ሁሉ ይገዙለታል።	ኢትዮጵያ የተነሣችበት ይህ ታሪክ በዘመን ፍጻሜ ላይ የሚሆነውን ጦርነት ሳያመለክት አይቀርም፤ በዚያ ጊዜ ኢትዮጵያም ሆነች ግብጽ ልብያም ጭምር በእግዚአብሔ ር ላይ ለተነሣው ክፉ ገዥ ተገዥ መሆናቸውን ያረዳል።

አሞፅ 9:7	የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር።	አሞፅ 9:1-15፣ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚያጠፋ የሚገልጽበት ምዕራፍ ነው። በዚህ ጥፋት ውስጥ ክፉኛ የሚቀጡት በሕዝቡ መካከል ሆነው ክፋ ነገር አያጋጥመንም፣ ወይም አይደርስብንም በማለት በኃጢአታቸው የከረሙና ሌሎችን ከሕያው እግዚአብሔር የሚያርቁት በሰይፍ እንደ ሆኑ ያረጋግጣል።	ኢትዮጵያ ለንጽጽር ያገዝ ዘንድ በዚህ ስፍራ ተጠርታለች፤ እስራኤላውያንን እናንተ እኮ እንደ ኢትዮጵያውያን ናችሁ ተብለዋል። ይህ መልእክት ኢትዮጵያን ከትዕቢታና ከትምክህተ ኝነታ ጋር ያነረጻጸረ ነው።
ሶፎ. 2:12	እናንተም ኢትዮጵያውያን ደግሞ፣ በሰይፌ ትገደላላችሁ።	ሶፎ. 2:1-15፣ ነቢዩ በእግዚአብሔር የሚቀጡትንና የሚጠፉትን ሕዝቦች ይዘ ረዝራል። ፍልስጥኤምን ፍጹም አጠፋሻለሁ፣ ከነዋሪዎችም የሚተርፍ የለም (ቁ. 5)፤ ሞዓብንና የአሞንን ደግሞ ሞዓብ እንደ ሰዶም፣ አሞናውያን እንደ ገሞራ ዐረም እንደ ዋጠው ቦታና እንደ ጨው ጉድጓድ ለዘላለም የጠፉ ይሆናሉ (ቁ. 9)፣ አሦርን በተመለከተ አጠፋታለሁ፣ ነነዌን ባድማ በማድረግ ደ ረቅ ምድረ በዳ እንደሚያ ደርጋት ይናገራል (ቁ. 13) ፤ ኢትዮጵያንም በሚመለከት በቁጥር 12 በሰይፉ መገደላቸውን የሚያስረዳ ምዕራፍ ነው።	የኢትዮጵያ ተጠቃሽነት ከተነሡት አገራት ሲተ ያይ፣ በጦርነት የታወቁ ከመሆን ባሻገር፣ የእስራኤል ጠላት ሆነው በድግግም ተነሥተ ዋል።

ማጠቃለያ

በሠንጠረዥ ውስጥ፣ ከአርባ ሁለቱ ጥቅሶች ሃያ ዘጠኙን ነው የጠቀስኩት የተቀሩት አሥራ ሦስቱ በይዘት እና በታሪክ በተጠቀሱት ውስጥ ያለምንም ለውጥ የተነሡ በመሆናቸው ትቻቸዋለሁ። እንግዲህ ያነበባችሁት ኢትዮጵያ-ጠቃሽ ክፍሎች አብዛኞቹ ወይም ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ኢትያጵያን እንደ አንድ በዓለም ውስጥ እንዳለች አገር እንጂ፣ የተለየችና ለእርሷ ብቻ ተቆንጥሮ ከእግዚአብሔር የተሰጣት ተስፋም ሆነ ቃል ኪዳን እንደ ነበር አያመላክትም። ይልቅስ፣ በበረከት ሳይሆን፣ በጥፋት-ነክ ጉዳይ፤ በሰላም ሳይሆን፣ በጦርነት ላይ፤ በማሸነፍ ሳይሆን፣ በመሸነፍ (በመማረክ) መልእክት ላይ፣ ለመሠራት ሳይሆን በቅጣት ያለፈበትን ታሪክ መዘከሩን ልብ የሚል ልብ ሊለው ይገባል።

ይህን ደግሞ ማለቴ ለአንድ ጉዳይ ነው። እኔም ኢትዮጵያዊ በመሆኔ ደስ ይለኛል። የበለጠ እርካታዬ ግን «ስማችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል» በሚል ሰበብ ጥረን ግረን አገራችንን ከማሳደግ ተለይተን በአፍቅሮተ-ኢትዮጵያ ብቻ ኋላ ቀር (ጅራት) ሆነን የሚያስቀረንን አመለካከት ወይም እምነት በእውነት ተክተን ስንኖር ማየት ነው።

እግዚአብሔር በላከልን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥሪ ታምነን ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም እንድንኖር ጠርቶናል።

በመጨረሻም፣ በብዙዎች ዘንድ እጅግ ታዋቂ የሆነውን ጥቅስ በመውሰድ አጭር ትንተና እሰጣለሁ። ጥቅሱ መዝሙር 68:31 ነው፡- «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።» አንድ ወዳጄ ይህ ጥቅስ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ፓስፖርት ላይ ተጽፎ እንደ ነበር ሲያጫውተኝ፣ ነገሩ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ታሪክ እንዳለው ተገነዘብሁ። ለመሆኑ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ማለት ምን ማለት ነው? ጥያቄውን ያነሣሁት ያለ ምክንያት አይደለም። ጥያቄ ያመራምራል፣ ነገሮችን በደፈናው ከመቀበል ይልቅ በምክንያት እንድንቀበል ያግዘናል፤ ሌሎች በደፈናው ያስተጋቡትን እኛም እንዳናስተጋባ ያዝ ያደርገናል። ብዙዎች ይህን ጥቅስ የሚጠቅሱት ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደችና የተባረከች አገር

መሆኗን ለማሳየት ነው፤ ሌሎች አገሮች እስከነ መኖሩ ሲረሱት ኢትዮጵያ እንዳወቀችው ለመግለጽ ነው። ከዚህም የተነሣ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደችና የተባረከች አገር መሆኗን ከማሳየትም በላይ፣ ኢትዮጵያ ቀን የወጣላት፣ በአምላክ የተመረቀች አገር ተደርጋ ትዘከራለች። መቼም ኢትዮጵያ እንዲህ ያለች ምስጉን አገር ብትሆን ማንም አይጠላም። እግዚአብሔር ቢወዳትና ቢባርካትም ማንም ቅር አይለኝም። ይህ ግን ምኞት ነው። መዝሙር 68፡31ን በመጥቀስ ለኢትዮጵያ እንዲህ የመሰሉ ነገሮችን መመኘት አይቻልም። ምክንያቱም ልክ እንደ ጉም መሠረት-የለሽ ምኞት ነው፤ አለ ስንለው የለም። ያም ሆነ ይህ፣ መዝሙር 68፡31 የሚናገረው ስለ ምንድን ነው?

ይህ መዝሙር የሚገኘው በሁለተኛው መጽሐፍ ውስጥ ነው። መጽሐፈ መዝሙር አምስት ዐብይ መጻሕፍት አሉት። አንደኛው መጽሐፍ ከመዝሙር 1-41፣ ሁለተኛው መጽሐፍ ከመዝሙር 42-72፣ ሦስተኛው መጽሐፍ ከመዝሙር 73-89፣ አራተኛው መጽሐፍ ከመዝሙር 90-106፣ አምስተኛው መጽሐፍ ከመዝሙር 107-150 ድረስ ያለው ነው። የሁለተኛው መጽሐፍ ዋነኛ አትኩሮት እግዚአብሔር ሕዝቡን ይመሠርታል፣ ይጠብቃል በሚለው ላይ ሲሆን፣ መዝሙሮቹ፣ በአንድም በሌላ መንገድ፣ የሚያንጸባርቱት ይሄንኑ አሳብ ነው። ወደ መዝሙር 68፡31 ስንመጣ፣ ይህ መዝሙር የሚናገረው እግዚአብሔር ለእስራኤል ስላደረገው በጎነት ነው።

በመጀመሪያ፣ መዝሙረኛው እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተሟጋች እንደ ሆነ ይገልጻል (ቁ. 1-6)። ተሟጋች የተገለጸልን ግን እንደ ጠበቃ ሳይሆን፣ እንደ አርበኛ ነው። ሕዝቡን ነጻ የሚያወጣው ከጠላቶቻቸው ጋር ተዋግቶ ነው። በመቀጠል፣ የሕዝቡ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ብርቱ አምላክ እንደ ሆነ ይናገራል (ቁ. 7-10)።

ለሕዝቡ የሚሟገተው አምላክ ሕዝቡን ለመታደግ ሲመጣ በፊቱ ሊቆም የሚችል ማንም የለም። ምድር እንኳ ከግርማው የተነሣ ትርበደበዳለች። ከዚያም መዝሙረኛው ወደ ኋላ በመመራት እግዚአብሔር በቀደመው ዘመን ለሕዝቡ ያደረገውን ቸርነት ይተርካል (ቁ. 11-14)። ቀጥሎም እግዚአብሔር ጽዮንን እንደ መረጠና

በመካከሏም እንደሚኖር ይናገራል (ቁ. 15-18)። ጽዮንን ማደሪያው ሲያደርግ ወደ እርሷ የገባው ክንደ-ድል አድራጊ አርበኛ ነው። በቁጥር 19-23 ላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ብርታት የሕዝቡ መዳን እስኪፈጸም ድረስ በታሪካቸው ሁሉ የሚቀጥል መሆኑን ይገልጻል። በቁጥር 24-27 ላይ ያ ድል አድራጊው አምላክ ወደ ቤተ መቅደሱ በመገሥገሥ ላይ እንደ ሆነ ይተርካል። ከዚያም እግዚአብሔር ዘወትር ሕዝቡን የሚያስጨንቁ ጠላቶቻቸውን ድል ማድረጉን እንዲቀጥል ጸሎትና አቤቱታ ሲቀርብ እናያለን (ቁ. 28-31)። በመጨረሻም፣ የዓለም መንግሥታት ሁሉ ወደ ሰማየ ሰማያት ለወጣውና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ መኖሪያውን ላደረገው ለእስራኤል አምላክ ምስጋና እንዲያቀርቡ ጥሪ ሲደረግ እናነባለን (ቁ. 32-35)። እንግዲህ፣ «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» (ቁ. 31) የሚለው ሐረግ የሚገኘው በዚህ ዐምድ ውስጥ በመሆኑ፣ ነገሩን ከላይና ከታች ከተነገሩት አሳቦች ጋር ማዛመድ የግድ አስፈላጊ ነው። ጥቅሱን በዐውዱ መሠ ረት ካላየነው፣ እኛ የምንፈልገውን ሊልልን ይችላል። ቀደም ሲል ስለ ቁጥር 28-31 እንደ ገለጽነው፣ ይህ ምንባብ የሚናገረው እግዚአብሔር እንደ ቀድሞው ዘመን ሁሉ አሁንም ብርቱ ክንዱን እንዲያሳይና ማንነቱን ያላወቁ ሁሉ ሳይወዱ በግዳቸው እንዲያውቁ የሚጠይቅ ነው። ግብጽና ኢትዮጵያ ማንነቱን አላወቁም። ግብጽ የሕዝቡ ጠላት ናት፤ ሕዝቡን ያሳደደችና ያስጨነቀች ናት። እግዚአብሔር ግን ካሳዳጅዋና ካስጨናቂዋ ጠላት ሕዝቡን ነጻ አወጣ። ኢትዮጵያም ብትሆን የእስራኤል አምላክ ማን እንደ ሆነ ያልሰማች ናት። በቁጥር 30 ላይ እነዚህ ሁለት ሕዝቦች ከዱር አራዊት ጋር ተነጻጽረዋል። አራዊትና ኮርማዎች የሚወክሉት ጨቋኝ፣ አዋኪና አጥፊ ሕዝቦችን ነው። የእነዚህ ሕዝቦች ክፉ ተ ግባር ማክተም አለበት። ጦርነትን የሚወዱ ሕዝቦች መንኮታኮት አለባቸው። ግብጽ ለጌታ መገዛት አለባት፣ ኢትዮጵያም ለእስራኤል አምላክ ስጦታ በማምጣት ማንነቱን መገንዘብ አለባት (ኢሳ. 18፡1-19፣ 15፡20፡1-6)። እጅን ወደ ላይ መዘርጋት የሚያመላክተው መሸነፍን፣ ድል መነሣትንና ለአሸናፊውና ለድል አድራጊው መገዛትን ነው (ኢሳ. 19፡21፤ 45፡14)። ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ሲባል፣ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔ

ር ትሰግዳለች፣ ማንነቱን ተገንዝባ በፊቱ ትደፋለች ማለት ነው። ኢትዮጵያ እጆቿን የምትዘረጋው ምልስ ስለ ሆነች አይደለም፤ ልትቋቋመው የማትችለው ባላጋራ ስለ ገጠማት ነው። ያላት አማራጭ ራሷን ማስገዛት ብቻ ስለ ሆነ፣ ሳትወድ በግዷ የተ ባለችውን አደረገች።

ለውርጃ ተጠቂዎች ምን ተስፋ አለ?

ውርጃን የፈጸሙ ሴቶችን ምስክርነት መስማት መልካም ነው። መልካምነቱ ደግሞ ሁለት ነው። አንደኛው፣ ውርጃን ያልፈጸሙ ሴቶች ቁም ነገርን ይገበያሉ□□፤ ምክንያቱንና የሚያስከትለውን ውጤት በማወቅ ይነቃሉ፤ ይህም ውርጃን ለፈጸሙ ሴቶች ርኅራኄን ኀዘኔታንና እርዳታን ላለመንፈግ ያነሣሣቸዋል፤ ሁለተኛው ውርጃን በመፈጸማቸው በዙሪያቸው ያለው ኅብረተሰብ ድንጋይ አንሥቶ በላያቸው ላይ ሊጭነው ያለውን የማዋረጃ የአስተሳሰብ ጫና ለማስጣልና ለማሻርም ጥረት ማድግ እንዳለባቸው ያስገነዝባቸዋል። ከዚህም የተነሣ፣ ታዳሚያን ሁሉ በዚህ ተካፋይ እንድትሆኑ በሴቶች ላይ የሆኑትን እዘክራለሁ፦

(መዋረድን ፈራሁት... ሜሮን፣ እድሜ 18)

ከፍቅር የተነሣ የተፈጠረውን ሕፃን ለመጠበቅ ፈለግሁኝ፣ ሌላው ቢቀር ወልጄው ለጉዲፈቻ እሰጠዋለሁ ብዬ ወሰንኩ፤ ግን በዙሪ ያዬ ያሉ ሁሉ «አሳቀፋት» እያሉ ዘጠኝ ወር ሙሉ መጠቋቆማቸውን ሳስብ ደነገጥኩ። ወላጆቼ ደግሞ ቢሰሙ እንዴት አድርገው እንደሚያዋርዱኝ ከወዲሁ አረጋገጥኩ። በየቀኑ የክፍል ጓደኞቼ ለወራት የሚነጋገሩበት ርእሳቸው መሆኔን አወቅሁኝ። እነዚህ ሁሉ ለጉዲፈቻ እስክሰጠው አላስቆይ አሉኝ፣ እናም ልጄን ገደልኩት።

(የወደደኝ ፊት ነሣኝ... መአዛ፣ እድሜ 16)

«አበድኩልሽ» ይለኝ የነበረው ጓደኛዬ ማርገዜን እንዳወቀ አንቋሸሸኝ፣ ዓይንሽን አልየው አለኝ። በእርሱ ፊት መንሣት ዓለሙ ሁሉ እንደ ከዳኝ አረጋገጥኩ። ብቸኛ ፍጡር ሆኜ ቀረሁ። አልኮል

መጠጣት ጀመርኩኝ። ሀሽሽ መውሰድ የዘወትር ሥራዬ ሆነ። ተቀባይነት ያጣች ነፍሴ ፅንሱን ካስወገድኩ ወዲህ በእነዚህ ውስጥ ተከለለች።

(የሸመገለው ምሥጢር... ደጅይጥኑ፣ እድሜ 95)

ለመጋቢዬ ዝሙት መፈጸሜን ነግሬው ነበር። እርሱም በዚህ ጉዳይ ላይ ንስሐ እንድገባ መከረኝ። ውርጃ መፈጸሜን ግን አልነገርኩትም። ላለፉት 50 ዓመታት ባልተናገርኩት በዚህ ጉዳይ ላይ ዕረፍት አላገኘሁም። ጭንቅላቴ ዛሬም «አንቺ ነፍሰ ገዳይ» እያለ ይነርተኛል።

(ብቸኝነት አይኖርም ነበር፡- ፍሬ ሰላም፣ እድሜ 72)

በ1952 ዓ.ም ውርጃውን እንደ ፈጸምኩ ከሰውዬው ጋር የነበረኝ ወዳጅነቴም ተሰረዘ። ጎሊናዬ ከትቦ የያዘልኝ ተነሣሽ ጥያቄ፣ «ፍቅራችሁን ላታድሱ፣ ልጅሽንም ማጣትሽ» የሚል ሆነ። መቼም ልጄን ገደልኩ አልልም፣ አረድኳት እንጂ። ዛሬ በሕይወት ብትኖርልኝ እኮ 50 ዓመት ይሞላት ነበር፤ ለእኔም ብቸኝነት አይኖርም ነበር።

(ይቅርታን ለራሴ ነፈግሁት፡- ትዕግሥት)

ደግሜ ውርጃን እንደ ፈጸምኩ ቀድሞ የነበረኝ የፍቅር ግንኙነት ከስሞ ባለቤቴን ጠላሁት። እንደቀድሞው የሚለኝን፣ የሚመክረኝን ሁሉ መስማት አቆምኩ። ድሮ የነበረ ሳቁ ዛሬ ሊገኝ የማይችል ተረት ሆኖ ቁጭ አለ። ተከታዮቹን አሥር ዓመቶች ዝምታና ቁዘማ አጣደፉኝ። ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ተወስጄ ተመረመርኩ፣ ለውጥ አልመጣም። በምናቤ ከፎቅ መወርወር ይመጣብኛል፣ መታነቅ ይታየኛል። ሦስቱ ልጆቼ ተጨንቀው ሲጠጉኝ እገፈትራቸዋለሁ፤ ለአንድ አፍታ «እወዳችኋለሁ» ልላቸው አልቻልኩኝም። የዚህ ሁሉ አለመቻሌ ዋንኛ ምሥጢር «እግዚአብሔርም እንኳ ይቅር እንደማይለኝ ማመኔ ነበር።» በፈጠርኩት የራሴ ምክንያት የመጀመሪያ ልጄን ገደልኩ፤ አላርም ብሎኝ በመጨረሻ ላይ የፀነስኳትንም ገደልኩ፤ ከስሕተቴ እስካልተማርኩ ድረስ ማን ይምረኛል? ይህ ጭንቅ ሆኖ ከረመ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ግን ቢጤ ዎቼን አገኘኋቸው። እነርሱ በነጻነት ይመካከራሉ፤ ዳር ሆኜ ሰማኋቸው፤ ቀስ እያልኩ ወንበሬን፣ ጆሮዬን፣ ልቤንም ወደ እነርሱ አስጠጋሁት፤ ለካስ ዛሬም የጌታ ልጅ ነኝ... ለካስ ይቅር ተብያለሁ፡-

የዛን ምሽት ፈውስ ሀ ብሎ ጀመረልኝ።

(ወደ ኋላስ አልመለስም... ሜሪ)

የአሥራ ሦስት ዓመት ሕፃን ሳለች ነው ወላጆቿ የተፋቱት። ለፍች ያበቃቸው ደግሞ ልቅነታቸው ነው። ባለጌ አባትና እናት አሳድገዋታል። ይህ ምሳሌነት የጎደለው ሕይወታቸው ቀጣይ ሕይወቷን አናጋው፤ እናቷ ባሏን ከተለየችው በኋላማ ለየላትና የማንም ሆና ቀረች።» ሜሪ የዚህ መፍትሔው ተለይቼ በመውጣት ራስን መቻል ብላ አሰበች፤ በ15 ዓመቷም ለአንዱ ፀነሰች፣ መፀነሷን ደግሞ ለማረጋገጥ የሄደችበት «የቤተሰብ የምጣኔ ማዕከል ክሊኒክ»፣ «ኑሮ መሮሽ ያመጣሽው ፅንሱ መውረድ አለበት» አላት። ልጅቷ ግን፣ «ይህማ! ግድያ ነው» በማለት ተቃወመች። ክሊኒኩን ትታ ሊረዱኝ ይችላሉ በሚል እምነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደች፤ ደርሳም ታሪኳን ለመጋቢው ዘከዘከችለት፤ እርሱም፣ «ልጅ ነሽ፣ ልጅ ነሽ፣ በማለት ከመሳቢያው 150 ብር አውጥቶ ወደ ክሊኒኩ እንድትመለስ ነገራት፤ ሜሪ ተገረመች፤ ቆም ብላ «አትግደሉ የሚለው እግዚአብሔር እንደኔት ውርጃን ይፈቅዳል?» ብላ እያጉተመተመች መንገዷን ቀጠለች። ክሊኒኩም ከመድረሷ በፊት፣ «ልጄ ወንድ ይሆን ሴት ባላውቅም አብረን እንድንኖር ግን እፈልግ ነበር፤ ይህንን ግን ሐኪሙም እግዚአብሔርም አልፈቀዱትም» ብላው ገባች፤ እናም ፅንሱ ተወገደ፣ ተገደለ።

የሜሪ ሕይወት ተወሳሰበ፤ በየምክንያቱም አራት ጊዜ ውርጃ ፈጸመች፤ በመጨረሻ ያስረገዛት ለልጇ አባት ለእርሷም ባል ለመሆን ቃል ገብቶላት አብረው መኖር ጀመሩ፤ ነዋሪዎቹ ከጊዜ በኋላ ክርስቲያን ሆኑ፤ የክርስቶስን ፍቅር በመረዳት የጎበረተሰቡ አቅርቦትና መተሳሰብ ከመጨመሩ የተነሣ፣ የሜሪ «የወንጀለኝነት ስሜት» ተሸረሸረ። ዛሬ «ፅንስን ማስወረድ የሚያስከትለውን አደጋ» በሚያስተምር ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ ትሠራለች።

(ወላጅ አልባዋ፣ ባል አልባዋ፣ ልጅ አልባዋ ኮሊ)

ወላጆቹ ከሚጠሉት ጐረምሳ ጋር በ18 ዓመቱ ቀበጥኩኝ፤ ቅብጠቱ ውስጥ አረግዛለሁ የሚለው ጥርጥሬ ተረሳ። ብቻ በኬሚስትሪ የላብራቶሪ ክፍል ውስጥ ሳለሁ ጓደኞቹ የወደዱት ጠረን እኔን አቅለሸለሸኝ፤ ጓደኛዬም በወቅቱ ነገሬን ተረድታ ወደ ቤተ

ሰባቸው ሐኪም ላከችኝ። ሐኪሙ ማርገዜን አውቆ በካርድ ላይ ጫር ጫር አድርጐ ወደ ሌላው ክሊኒክ መራኝ። በሄድኩበት የገጠመችኝ ነርስ፣ «ሕክምናው ቀላል ነው፣ ሳምንት ይህን ያህል ብር ይዘሽ ነይ» ብላ መለሰችኝ። ለእኔ ግን ማስወረድ ጎሊናዬ አልተቀበለውም። ከዚህም የተነሣ ሴቷ መምህሬን አማከርኳት። «እኔ ብዙ ጊዜ ያደረግኩት ስለሆነ አሳብ አይግባሽ። አሁን ላይ ደም ስለሆነ ይጠርጉልሻል» አለችኝ። እኔ ግን ይህንንም ለመታዘዝ አልፈለግኩም፤ ብቻ ሞጋች ጎሊናዬ ወደ አንዲት መነኩሴ እንዳዘግም አስገደደኝ። ወጣቷ መነኩሴ፣ «ፈጽሞ እንዳታደርጊው፤ ይህ መግደል ነው» ብላ አወገዘችኝ። ውግዘቷ ግን አልዘገየም፤ እንደዚያም ቢሆን ግን፣ «የተሻለው አማራጭ ውርጃው ሳይሆን ይቀራል ብለሽ ነው?» አለችኝ። በዚህ ሰዓት በእውነት ግራ ተጋባሁ። እናም ሄጄ ያን የሚያቀብጠኝን ጓደኛዬን አረዳሁት። እርሱም፣ «የተለየ ነገር አልልሽም» በማለቱ ጭንቀቴ በዛ፤ በመጨረሻም፣ የመጨረሻ ሙከራዬን አደረግሁኝ።

የገጠመኝን ሁሉ ወላጆቼ ጋ ደርሼ እየተበሳጨሁ አወራሁኝ። አባቴ ግን፣ «ቤቴ የዲቃላ መሰብሰቢያ አይሆንም፤ ከቻልሽ አስወግጂው፣ እምቢ ካልሽ ወደ ቤት አትመለሽ» አለኝ። አይገርማችሁም? ያወራኋቸው ሁሉ፣ «ኮሊን አብደሻል እንዴ? ልጅ ለማቀፍ ጊዜሽ አይደለም፤ ወጣት ነሽ እኮ፤ ወጪውን ገምቺ እንጂ፣ ልጅን ከማሳደግ ሕንፃ መሥራት ይቀላል፤ ከቤተሰብ ተለይተሽ ብቻሽን ልታደርጊው አትችይም።» ይህ ሁሉ ክምር ምክር አንድ ቀን ከማስጨነግፈበት አልጋ ላይ ጋደም አስደረገኝ። ደጅ የተጠናበትም ፅንስ ተወገደ። የውርጃው ጉዳይ ግን እንደ መከሩኝ ችግሩ ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም። ይልቅስ፣ የተዛዘለ መከራን ጫነብኝ። ባሌ ባልጋችን ላይ ከሌላ መተኛት ጀመረ። በዚህ በድርጊቱ ስነጫነጭ፣ በደረቱ ላይ ጨቤ ሰንዝሮ «አርድሻለሁ» የሁልጊዜ ቋንቋው ሆነ፣ በዚህም ተፋታን። ድርጊቱ የምንም ነገር ባለቤት ሳያደርገኝ ቀረ፤ የማልክደው ቀሪ ነገር አለኝ ብል ሁለት ልጆች ስለ ነበሩኝ በእነርሱ እጽናናለሁ።

ለዚህ ዝግጅት መንደርደሪያ ከዚህ በፊታችን የቆሙት የእነዚህ ሴቶች ምስክርነት በቂ ነው። በመግቢያው ላይ እንዳልኩት፣ ሁለት ቁም ነገርን ማንም ይጠብቃል። ለችግሩ ተካፋዮች አዛኝነት፣ ለራስ

ጥንቁቅነት፣ እንዲሁም ጎብረተሰቡ ተቀባይና አጋር እንዲሆን የማድ ረግ ጥረት ጭብጦቹ ይሆናሉ።

ይህ ግን ውጤታማ እንዲሆን ጥርጊያው በአግባቡ መጠረግ አለበት ከመንገዱ እንቅፋት አንዱ ደግሞ ፈሪነት ነው። ውርጃ አደጋ መሆኑን መግለጽ በየሰበቡ ይፈራል፤ ፈሪዎች ደግሞ ሽሽታቸውን ከሚገልጹበት ጥቂቶቹን እነሆ፦

ሀ. ተጨማሪ ኃላፊነት ለመውሰድ ጊዜም የለኝ። («በሕይወት ኑሩ» ቀዳሚ መልእክት መሆኑን በመፍራት።)

ለ. የማያዛልቅ ውዝግብ ውስጥ መግባት አልፈልግም። (ኢየሱስ ኃጢአተኞች መሀል ተገኝቶ ኃጢአተኛውን ማዳኑን ችል በማለት።)

ሐ. ብሰብክበት ጉዳዩ የሚነካቸው *አቤተ ክርስቲያን ለቅቀው ይሄዳሉ። (እውነት ሊያጸናቸው መቻሉን በመርሳት።)*

መ. ቤተ ክርስቲያኔ በአመለካከት መከፋፈሏን ማየት አልፈልግም። (ኢየሱስ ልከፍል መጣሁ ያለውን በመርሳት፣ ሉቃስ 12፡51።)

ሠ. ውርጃ ፖለቲካዊ አጀንዳ ነው። (ፖለቲከኞቹ ደግሞ የውርጃ አጀንዳ የቤተ ክርስቲያን ነው ማለታቸውን በመዘንጋት።)

ረ. ስለ ውርጃ ዝርዝር ትምህርት ለመስጠት እውቀቱም የለኝም። (የሕይወት መነሻ ከእግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ በቂ መሆኑን ባለማስተዋል።)

ሰ. ውርጃን መስማት የሰው ጆሮ ሰልችቷል። (ይህ ፍርሀት ከወለዳቸው ላቅ ያለ ነው። የውርጃን መንሥኤና ውጤቱን፣ ጉዳቱንና ውስብስብ ችግሮቹን ያልተረዳው ሕዝብ ብዙ ነው። «ውርጃ ግድያ ነው»፤ አልያም፣ «ውርጃ ዕረፍት ነው» ከሚሉት ተ ጻራሪ መልእክቶች ያለፈ መረዳት ሰፊው ሕዝብ የለውም። ውርጃ ግን በሰው ላይ የሚያደርሰው አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ እና መንፈሳዊ ችግሮቹ በቀላሉ የሚቀረፍ አይደለም። እናትንም ልጅንም ለማዳን የሚደረግ ጥረት በቀላሉ፣ «ትቀበላለህ ተቀበል። ትሰሚያለሽ ስሚ» ተብሎ የሚታለፍ አይደለም።)

እነዚህ ከሀ እስከ ሰ ብሩህ ተስፋን አጨላሚ ጋሬጣዎችን አስቀድሞ በድፍረት መጫማት ቀጣዩን ጉዞ አመቺ ሊያደርገው ይችላል።

ዝምታ መዳብ ነው

አንድ ሊስተዋል የሚገባው ዐቢይ ቁም ነገር አለ፤ ማንም ውርጃን በተመለከተ መስበክም ሆነ መጻፍ አይወድም። ያለመውደዱ ምክንያት ብዙ ቢነገርበት ውርጃን በፈጸሙት ዘንድ ጽኑ ጉዳትን ሊያመጣ ይችላል፤ በተጨማሪም፣ በዚህ ርእስ ብዙ ቢዘከር ደግሞ የውድቀትን ዘር ማጨድ ብቻ ስለሚሆን፣ አጀንዳውን አለማንሣት ይሻላል በማለት አይጽፉም፣ አይናገሩምም። እውነቱ ግን መስበክ ማስተማርና መጻፍ ብቻ ነው። ዝምታው እልቂትን እንጂ፣ ሕይወትን አልዘራም። እንግዲያስ ሊሆኑ ከሚችሉ መሠረታዊ ተግባሮች ውስጥ አንዱ ውርጃን የፈጸሙ ሴቶች እና በውርጃ መንሥኤ የተጎዱ ወንዶችን ቀጣይ ሕይወት የለመለመ እንዲሆን መርዳት ነው።

ሴቶች ፅንሳቸውን ለማስወረድ ያስገደዳቸው ምክንያት ምን ይሆን? ይህን በአግባቡ መመለስ ነው። በምላሹ የሆኑትን፣ የማያውቁትንና የሚገምቱትን ሁሉ በማካተት የጋራ የሆነውን የሕይወት ገጠመኞችን እንዲያደምጡ ማድረግ ተገቢ ነው። ይህ ደግሞ ጣጣው ተሰብሮ ወይም እየተሰበረ ያለውን በማስተካከል ነጻነትን ከእግዚአብሔር መግባባትንም ከጎበረተሰቡ ጋር ያስደርጋል። ጐን ለጐንም ይህ ጥረት በሰባኪው ወይም በሚመለከተው አገልጋይ ለጉባኤው በተዘረዘረ ቁጥር፦

1. ሴቶች ከሁኔታዎች አስገዳጅነት የተነሣ ወደ ውርጃ እንደሚመጡ፣
2. ውርጃን ከፈጸሙ በኋላ ጥርጥር፣ ፍርሀትና ወንጀለኝነት በሁሉም ዘንድ መኖሩን፣
3. ሰዎች ሊረዷቸው፣ በፍቅርና በይቅርታ ዐይን እንዲታዩ በሁሉም ዘንድ «ተፈዋሽ» ልብ እንዲያገኙ መንገዳቸውን ይጠቁማል፤ መፍትሔውም ስለ ችግሩ መናገር፣ ማስተማርና፣ መረዳት ብቻ ነው።

ይህ ደግሞ በማንም ዘንድ የጀንበር ዝግጅት ሳይሆን፣ ያላሰለሰ ጥረት ከወዲሁ መኖሩን ይረዱታል። ይህም ጥረት ጅማሬው መታየት ያለበት በቤተ ክርስቲያን ነው፤ በክርስቲያኖች ዘንድ ጥናቶች ስሌቱን እንዳስቀመጡት፣ ውርጃን ከፈጸሙ መቶ ሴቶች ሰባዎቹ በፈጸሙት ድርጊት ወንጀለኝነት የሚሰማቸው ሆነው

ሁሉም ስለ ድርጊታቸው ሲጠየቁ ምላሻቸው፤ «ውርጃ መፈጸም» እንደ ትክክለኛ ድርጊት አልቆጥረውም፤ ይጸጽተኛል» የሚል ነው።

ምናልባትም ስለ ውርጃ ያለን እይታ የተለያየ ሆኖ እንኳን ቢገኝም፣ የሰውን ልጅ ለማገዝ የጋራ የሆነ የጸና አቋም ሊኖረን ይገባል። የጥናት ውጤቶች ውርጃን በመፈጸማቸው የሚከተላቸው ጉዳት የከፋ መሆኑን በዚህ ውስጥ ያላለፉም ሊጠነቀቁ እንደሚገባቸው ማስረዳቱ፦

1. በየጊዜው ውርጃን በተመለከተ ለማዘንም ሆነ ለመርዳት የማጎበ ረ ምእመኑ ቁጥር ይጨምራል።
2. ዝምታ ብቸኛ ሀብታችን ነው ያሉ ተጎጂዎች ቁጥራቸው እየቀነሰ በመምጣት ለመናገር በመብቃት ይበዛሉ።
3. የመተው፣ የመካድ የመናቅ ሥነ ልቦናዊ ሕይወት ፈጣን ምላሽን በማሳደግ ይዘልቃል።
4. በራስ መተማመንን በውስጣቸው እንዲዳብር በማድረግ ለተሻለ ሕይወት ያበቃሉ።
5. የራስን ኃላፊነት በአግባቡ በመረዳት ሰላምን ከእግዚአብሔር ጋር በመፍጠር ማደግን፤ ለሌሎችም ረጂ ልብን በመያዝ መዝለቅ የሚያስችልን በውርጃ ተጠቂ ሴቶችን ለመፈወስ ይ ረዳል።

ሴት-ተኮር እውነት

ሁላችንም በቀላሉ የምንገነዘበው እውነት አለ። በእግዚአብሔር ሥርዓት ሕግ ውስጥ በማጎፀን ላደረው ሕፃን መጋቢዋ እናቱ ብቻ ናት፤ ይህ ደግሞ እናቲቱን በተፈለገው መንገድ ሁሉም መርዳት ሕፃኑንም መርዳት ይሆናል፣ እግዚአብሔር የእናትንና የልጅን ግን ኙነት አዝልቆና አጥልቆ አደራጀ። ይህ አዘላለቅ እርስ በርሱ ተ ሣሥሮ አንዱ በአንዱ ላይ ስለሚደጋገፍ፣ ያንዱ በመልካም ሁኔታ ላይ መገኘት ለሌላው ደህንነትን፣ ያንዱ መጎዳት ሌላውም የጉዳት አሻራን ትቶ ያልፋል። ከዚህም የተነሣ፤ «ማንም እናቲቱን ሳይረዳ ሕፃኑን ሊረዳ እንደማይችል፣ ማንም ሕፃኑን ሲያስወግድ እናቱንም እንዳስወገደ መረዳት አለበት።»

ለዚህ እውነታ እማኝነት ከ20,000 በላይ ፅንስ ያስወረዱት ዶክተ ር ጆሊየስ ፎጄል እንዲህ ይላሉ፣ የትኛዋም ሴት ፅንሱ ሊወገድ

በዝግጅት ላይ ሳለ መረበሽና ድርጊቱን ያለመቀበል፣ ንጭንጭን ታሳያለች። ይህ ደግሞ ዘርን፣ እድሜን፣ ትምህርትንና የኑሮ ዳራን ሳይለይ መከወኑን ተረድቼያለሁ፤ ይህም ውርጃ በልጅና በእናት ሕይወት ውስጥ የነበረውን ፍጹማዊ ትስስር የሚያፈርስ ኃይል መሆኑን አስገንዝቦኛል፣ የፈረሰውን ማንነት ደግሞ ከእናቲቱ ሕይወት ላይ መልሶ ለመገንባት የማይቻልና ውስብስብ ችግር ፈጣሪ መሆኑን ከገጠመኞቼ አስተውያለሁ (Coleman McCarthy, "A Psychological View of Abortion):: የዶክተሩ የተግባር እማኝነት ብዙዎችን ሊያነቃ የሚችል ነው። እናትንና ልጅን በአንድ ላይ በመጠበቅ ኃላፊነትን መወጣት ተገቢ ነው።

ለነፍሰጡር የተገባ ርኅራኄ

በማኅበራዊ ሕይወታችን ውስጥ በተደጋጋሚ ከምናያቸው በጎ ምግባሮች ውስጥ አንዱ ለእርጉዞች የሚደረገው የርኅራኄ ትሕትና ነው። «ቅድሚያ ለእነርሱን» የሚታይ ክስተት ነው። ይልቁኑ፣ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናት የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን ስለምታምን፣ ክርስቲያን ሁሉ ስጦታውን በአግባቡ ለአደባባይ እንዲበቃ ማገዝ ይኖርበታል። «እርጉዝን ያቅፉ ይደግፉን» የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገራችንም ከዚህ ጋር የተገናዘበ ነው።

በመሠረቱ፣ ለነፍሰጡር የተገባው ያ ርኅራኄ መነሻ እግዚአብሔር ነው፤ የትኛውም እርግዝና የትኛውም ሕፃን የመለኮት ስጦታ ነው፤ የስጦታው አመጣጥ በትዳር ሕይወት ውስጥ፣ በዝሙት ወይም በመደፈር መንገድ ሊመጣ ይችላል፤ ሁሉም የአመጣጥ መንገዶች ግን ስጦታነቱን ከፍና ዝቅ አያደርጉትም፣ በጉዞ ላይ ላለው መጪ ሕፃን፡- በወላጅ አጋሮቻቸው መካከል መፋቀርን፣ መተሳሰብን፣ መደጋገፍንና በእግዚአብሔር ላይ መታመንን አብልጦ ስለሚያስገኝ፣ ለነፍሰጡሯ መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

ወደዚህ ዓለም እየመጣ ያለው ሕፃን ከዝሙት የተነሣ የተገኘ ቢሆን እንኳ፣ ሕፃኑ ለመቀጣጫ የተገኘ ሳይሆን፣ የዝሙት መግቻ ፈውስ ሊሆን ስለሚችል፣ አርግዞ መታየት ለማፈሪያ ሳይሆን፣ ወልዶ የመሳሚያ መንገዱ እንደ ሆነ በመረዳት ርኅራኄን ማዝለቅ ተገቢ ነው።

ለአስወረደች ሴት የተገባ ርኅራኄ

ውርጃን ከፈጸሙ መቶ ሴቶች ውስጥ ሰባው ባደረጉት የሚጸጸቱ ሆነዋል። ይህ ኀዘን በኅሊናቸው ውስጥ ተደብቆ ባለበት ሁኔታ ላይ ኅብረተሰቡ በተጨማሪ «ልጇን ገዳይ» በማለት ቢጠቋቆም፣ አንዲትን ሴት ፈጽሞ ሊኅዳት ይችላል። ከዚህም የተነሣ «ፈራጅ ሆኖ መሰየም» ፈውስን ሳይሆን፣ ጥፋትን ያመጣል። በምትኩ ቃላችንን ብቻ ሳይሆን፣ የፍቅር ልባችንንም ውርጃን ለፈጸሙ ሴቶች ማድረስ ተገቢ ነው።

በተጻራሪው ግን «ኃጢአተኛው» የሚለውን ለማጽናት ብቻ የሚቆም የኅብረተሰቡ ክፍል ቢኖር፣ ወደ ኢየሱስ በዝሙት ምክንያት ተይዛ የቀረበችውን ሴት ታሪክ ሊገነዘቡት ይገባል። ሴቲቱ በደል መፈጸሟን አልካደችም፤ ያሻሯጀም ፍርድ ይገባታል፣ በድንጋይ ትወገርልን በማለት አንድ ወጥ ዓላማ ሥር ተሳስረው መቆማቸው አልቀረም። የኢየሱስ ምላሽ «ቅዱሳን» ሆነው ላቀረቧት፣ «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት ይውገራት» የሚል ነበር። የፍርድ ውሳኔው እያንዳንዱ ነውረኛ መሆኑን አረጋገጠ። ከእርሷ ያልተሻለ በመሆኑም፣ በደለኝነቱን እየተረዳ ተሰወረ። ኋላም ብቻዋን ለቀረችው ሴት፣ «ደግመሽ ኃጢአትን አትሥሪ» በማለት በሕይወቷ ተስፋንና መጽናናትን ዘራባት። ይህ ቁም ነገር «ልጇን ገዳይ» በማለት ከመሞገት በመታቀብ ራስንና ዙሪያውን በማጤን ላስወረደች ሴት ርኅራኄን ማጽናት ተገቢ መሆኑን ያስገነዝበናል። እስቲ ደግሞ ተከታዮቹን ለፈውስ የሚያበቁ ተስፋዎችን ጨምረን በጋራ እንመልከት።

የዐይናችንን ምሰሶ ማስወገድ

ውርጃ የፈጽሙትን ሰዎች ለማገዝ ከመነሣት በፊት ራስን ማገዝ ይገባል። ደካማ መሆናችንን ማመን፣ በምንወቀስበት ወይም በሌላ ኃጢአት ውስጥ የትም፣ መቼም ቢሆን ልንገኝ እንደምንችል መገንዘብ፣ ውርጃን የፈጸሙት ሰዎች ልክ እንደኛው ሰዎች መሆናቸውን ማወቅ፤ ቀዳሚው ግላዊው ሥራ ነው። ውርጃ በፈጸሙበት ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ከማውጣታችን በፊት በገዛ ዓይናችን መሀል የተገደገደውን ምሰሶ ታግሎ ማስወገድ ተገቢ ነው።

ዶክተር ዴቪድ ራርዶን ለብዙ ዓመታት የደከሙበትን ጽንስን የመታደግ ጥናት ዛሬ ላይ ለውጠውታል፤ ለዚህ ደግሞ ምክንያታቸውን ሲገልጹም፣ «ትኩረቴ ውርጃን በሚፈጸሙ ሴቶች ላይ አልነበረም፣ እነርሱ ዐዋቂዎች ስለሆኑ ለሚያደርጉት ነገር ተጠያቂዎች እንደ ሆኑ ከሥራ መነሻዬ በፊት አምኜላቸዋለሁ፤ ሕፃናቱ ግን በዝምታ የሚያልቁ ሆነዋል። አይሟገቱም፤ አይከላከሉም፤ ብቻ መሞት ነው። እኔ ለእነዚህ የአቅሜን አደርጋለሁ ብዬ ስለ እነርሱ ማጥናት፣ መጻፍ፣ መመርመሬን አሳደግኩ። ይህ ጥረት ግን እናትየዋን ችል በማለት ሊዘልቅልኝ አልቻለም፤ አዋቂ ናት ያልኳትን ሴት ጉዳት በየዘርፉ ስቃኝ ለእርሷም ራራኹኝ፤ በሙያዬም ማድረግ ያለብኝን ሁሉ ለመፈጸም ተነሣሣሁ፤ እናም ዛሬ ውርጃን ለፈጸሙ ሴቶች የማገዝ ልቡ አለኝ፤ ሁሌም የሚደርስባቸውን ሰቆቃ ለመቅረፍ መጣርን መርጫለሁ (David C. Reardon. *The Jericho Plan)*

ዘመድ ከዘመዱ

በውርጃ ሕይወት ውስጥ ያለፉ ሴቶች ያለዘመድ የቀሩ አይደሉም፤ እኅት ወንድም፣ እናትና አባት ሊኖራቸው ይችላሉ፤ እነዚህ ደግሞ የቅርብ ሰዎችና የዕለት ተዕለት ተገናኞች ናቸው፤ ብዙ የሚያወሩት፣ የሚማከሩት፣ የሚቀላለዱበትም ጉዳይ አያጡም፤ የውርጃ ተጠቂ የሆነችውን ዘመዳቸውን ሰምተው እንዳልሰሙ በመምሰል በፊቷ «በጉዳዩ ብንነጋገር እንጎዳታለን፤ ፍቅሯንም እናጣለን» በማለት ችል ቢሉ፣ ይህ አፍን የሚያሸብብን□ የአንነካካት እርምጃ ሊያመጣ የሚችለው ፍሬ ምንም ነው፤ ይልቅስ ውርጃን የምክራቸው፣ የወሬያቸው አንደኛው የሕይወት ጉዳይ አድርገው ቢጫወቱት፣ ተጠቂዋ ትሰማለች፣ በጎ በሆኑ አሳቦቻ ቸውም ተስፋን ትዘራለች፣ ቀስ ብላ ልትናገር ትደፋፈራለች፣ በቤተ ሰብ በኩል የሚመጣውም ተስፋ ሴቲቱን ያበረታል፣ እናም «ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ» በመባል ብቻ ሳይሆን፣ በመሆን ይገለጣል።

ተስፋ መቁረጥ ባለበት ቦታ እምነት አይኖርም

ውርጃ ራስን ከማፍረስ ጋር በመያያዙ፣ የሴቶች ተስፋ ሙጥጥ ብሎ ይጠፋል፤ ቀድሞ በእግዚአብሔር የተደገፉ እንደ ነበሩ የሚያሳይ ምልክት ይታጣል፤ በቀደመው ብርሃን ላይ ድቅድቅ

ጨለማ ይተካበታል። ይህም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጸውና የተሰጠውን የተስፋ ቃል ያጠፋል፤ የእግዚአብሔር ቃል በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ሊኖር የተገባውን ተስፋ፣ ጥበቃና ዓላማ ስለ ገለጠ፣ ይህን ማጣትና መርሳት ለውርጃ ተጠቂ ዎች ጨለማን ጋባዥ ይሆናል፤ ይህን ግን ማሸነፍ የሚቻለው እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ በመረዳት ጽኑ እምነት በቦታው ሲተካ ነው።

ናዚዎች አይሁዳውያንን ለመፍጀት የየራሳቸውን የጥፋት ዘዴ ተጠቅመዋል፤ ተስፋ ለቆረጡት ረጋፊዎች፡- ሁለት ክፉ ምርጫዎችን ያቀርቡላቸዋል፣ «መቀላት ወይስ እግርን መቆረጥ።» ረጋፊዎች ብዙዎቹ እግራችን ይቆረጥ በሚለው ተስማምተው ይቆ ረጣሉ፤ በሌላው ጊዜ ደግሞ ሌላ ምርጫ ይቀርብላቸዋል፣ «መቃጠል፣ ወይስ ዐይንን ማጣት።» ብዙዎቹ ዓይንን ማጣትን ይመርጣሉ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሌላ ምርጫ ይቀርባል፣ «መቀላት ወይስ ከገደል አፋፍ መገፍተር?» ብዙዎቹ «ከገደል አፋፍ መገፍትርን» ይመርጣሉ። ይህ ሁሉ ግን ከመሞት መሰንበትን ያሳሰበ ካልሆነ በቀር የተሻለ አማራጭ ሆኖ አይደለም።

ሞት ዞሮ ዞሮ መምጣቱ አልቀረም። ናዚዎቹ ግን ፈቅደው እንዳለቁ መርጠው እንደ ሞቱ ይጽፉባቸዋል። (Bauman Modernity and the Holocaust) እንደ ቡማን ገለጻ፣ ብዙ ጊዜ ተስፋ በቆረጠ ሰው ሕይወት ውስጥ የሚወስደው ውሳኔ ከድጡ ወደ ማጡ የሚዘልቅ ነው። ተስፋ ማጣት ውሳኔን አያጠራም፤ ናዚዎች አይሁዶች ፈቅደው እንዲያልቁ አመቻችተዋል። የውርጃም የውሳኔ ሂደት የሚያፈርሳቸውን ባለማስተዋል በራሳቸው ላይ እንዲፈጽሙ ያደርጋል። ውርጃ፣ የተሻሉ የመሰሉ አማራጮች ቀርበው ቢሆን፣ አማራጫቹ ግን ክፉዎች ናቸው። እናም የምትኩ ውሳኔ በእግዚአብሔር በመታመን በሕይወት ለመኖር መታገል ነው።

ዲያብሎስና ኢየሱስ

ከውርጃ በፊት ኢየሱስ፣ «ተይ ይቅርብሽ» ይላል፣ «ሕይወት የአንቺ ነው፤ የበዛ ሰላም የአንቺ ነው» ይላል። ዲያብሎስ ደግሞ፣ «ጊዜውን ተጠቀሚበት፣ ሌላ ምንም አማራጭ የለሽም፤ አንዴ በችግሩ ውስጥ ገብተሻልና አስወግጂው፣» በማለት እያዋዛ

ይመክራል። ከውርጃው በኋላ ደግሞ ኢየሱስ፣ «አሁንም ወደ እኔ ነይ፣ ሸክምሽንም አሸክሚኝ» በማለት ይጣራል፤ ዲያብሎስ ደግሞ፣ «አንቺ ነፍሰ ገዳይ ለልጅሽ አልሆንሽም» በማለት በንስሐ የማይጠራ ኃጢአት መሥራቷን ያውጃል። ስለ ነገም፣ «ጀምረሽዋል፣ ደጋግመሽ ደጋግመሽ ቢለይልሽ ይሻላል» በጆሮዋ እንዲሰማ ያደርጋል፤ በዚህ ደግሞ ሦስት ያህል ፍላጎቷ ይሟላሉ፦

1. ሊፈታ የማይችል የእንቆቅልሽ ሕይወት ይፈጥራል።

2 በኃጢአት መክረምን በመፍትሔነት ያቀርባል።

3 በእግዚአብሔር መታመንን አውጥቶ ጥርጣሬን ይሞላል።

በኢየሱስ ዘንድ ግን፣ ውርጃን ጨምሮ፣ ይቅር የማይባል ኃጢአት የለም። ኃጢአትን በመናዘዝ የኢየሱስ ደም የማያነጻው ብርቱ ድካም የለምና፤ አስተውሉ፦ ማስወረድ በእግዚአብሔር ያለ መታመን ምልክት ነው፤ ማርገዝ ፍቅርን እግዚአብሔር የሚያሳድግበት መንገዱ ነው፤ ይህንንም መቃወም ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር አለመገጣጠም ነው፤ በማኅፀን ያደረውን ሕፃን ባለመቀበል መጽናት ስጦታውን መናቅ ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሌላም ስጦታን ከውርጃ በኋላ ያቀርባል- «ይቅር ብዬሻለሁ።» ይህ ስጦታው ፈውስን ያስከትላልና የዲያብሎስን አሳብ ያፈርሳል።

ውርጃ ሊያስከትል የሚችለው ጣጣ

በጨነገፉ ሕፃናት ቀጣይ ሕይወት ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ዝምታን የመረጠ ይመስላል፤ ሰው ግን የተባለላቸው ግልጽ ነገር ስላልኖረ በሚል የራሱን ቀመር አበጅቷል፤ ሊሆን ይችላል? ወይም እርግጡ ይኸው ነው በማለት ያስተምራል፤ ያምንበታልም። ጽንስን ያስወረዱ ሴቶች ራሳቸውን በሚመለከት ተስፋን ሊያሳድጉ የመቻሉ ሁኔታ በተመቻቸላቸው ቁጥር ከጎሊናቸው ተደብቆ የሚያስጨንቃቸው ሌላኛው ጎን የልጃቸው ዕጣ ፈንታ በሰማይ ምን ይሆናል? የሚለው አንዱ ሲሆን፣ በትይዩም ሕፃኑ በመጪው ዘመን በእናቱ ላይ ሊወስድ ይችላል ተብሎ የሚታመነው ትንቢታዊ ንግርትም አሳሳቢ ነው። ውስን ተገዳዳሪ ነጥቦችን በማንሣት ተሸናፊነታቸውን አብረን እንመልከት።

ሀ. ለመንግሥተ ሰማይ መብቃት በሕፃንነት በሚወሰድ የውኃ ጥምቀት ወይም መረጨት ከመሆኑ የተነሣ፣ ልጁ ለዚህ

ባለመብቃቱ ለገሀነም አብቅቼዋለሁ።

ለ. የደኅንነት ብቸኛ መንገድ በክርስቶስ ማመን ሆኖ ሳለ፣ የእኔ ሕፃን ግን ጊዜው ደርሶ ለማመን እንዳይበቃ በማድረጌ ለዝንተ ዓለም አጥቼዋለሁ።

ሐ. የአካሌ ክፋይ ላይ ጨክኜ ያስወገድኩት ከመነሻው በእግዚአብሔር ሳይመረጥ በመቅረቱ ነው፤ ይህ ደግሞ ልጁን እንዳላየውና በእግዚአብሔር እንዳማርር አድርጎኛል።

እነዚህ በሕፃኑ ዕጣ ክፍል ላይ ከሚያነጋግሩት ጥቂቱ ሲሆኑ፣ ልጁ በገነት ወይም በገሀነም መግቢያ ላይ ተገኝቶ በእናቱ ላይ ሊወስድ ይችላል ከሚባለው ትውፊት ዝክሮች ውስጥ ጥቂቶቹ፦

ሀ. የእናቱ ጭካኔ የከፋ መሆኑን ለማሳወቅ በገሀነም ሳለችም የገዛ ልጇ እሳቱን በሰባት እጥፍ እያቀጣጠለ ሌትና ቀን ማገዶ በማቅረብ እግዚአብሔርን ያገለግላል።

ለ. እግዚአብሔር ንስሐዋን ተቀብሎ ከኃጢአቷ ያነፃት እናት በሞተች ጊዜ በሰላም ወደ ማረፊያ ስፍራዋ ደርሳ ልትገባ ይገባታል። ይህ ግን ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚያባርሯት አሉ፣ በምድር የሕይወቷ ዘመን ያስጨነገፈቻቸው ሁሉ በዚያ ተገኝተው ይከሰክሷታል።

ሐ. እናትና ልጅ ለገነት በቅተው ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር መኖር የሚቻልበት መንገድ ሊኖር ይችላል፤ በኑሮአቸው ውስጥ ግን ልጇ ትልቅ ሰው ሆኖ እናቱ ስለምታገኘው፣ ዓይኑን ማየት በመፍራት በተያዩ ቁጥር መሳቀቅ ይበዛበታል።

መ. እግዚአብሔር ውርጃን የፈጸመችን ሴት የሚሰጣት ልጆች ሁሉ ዐመፀኞች ይሆናሉ፤ የሁልጊዜ ድርጊታቸውም፣ «ምን አለ በገደለን?» በማለት ያስወረደችው ያመጣባት ፍርድ መሆኑን ታውቃለች።

ከላይ የተዘረዘሩት ሰባት የዘወትር ምሬቶች በእናቲቱ ላይ ያልተ ቋረጠ ተጽዕኖ በማድረስ አለመረጋጋትን ሊያመጣባት እንደሚያስችል ይገመታል፤ እነዚህን ግን በአግባቡ መፈተሹ ዕረፍትንና ነጻነትን ሊያመጣ ስለሚያስችል፣ ጥቂት እንበልላቸው፦

ሀ. የሕፃናት የውኃ ጥምቀት የመነሻ መንደርደሪያን በብዙዎች

ዘንድ ያገኘው ኒቆዲሞስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ ዳግም ስለ መወለድ ኢየሱስን በጠየቀ ጊዜ፣ «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገባ ተነግሮታል»፣ በዚህም ውኃ የመዳኛ ቅድመ - መጠይቅ ሆኗል የሚል ነው። ይህም ግን መረዳት ለሚችለው ትልቅ ሰው የተነገረ መሆኑ፣ በጌታ ጎን ከተሰቀለው አንዱ ያለ ውኃ ጥምቀት ለእግዚአብሔር መንግሥት መብቃቱን በመረዳት፣ እንዲሁም ዳግም ለመወለድ ውኃና መንፈስ በዐውዱ መሠረት የሚሰጡት ፍቺ ከዚህ የሕፃናት ጥምቀት ጋር የማይያያዝ በመሆኑ፣ የትኛዋም ውርጃ የፈጸመች እናት በዚህ ወንጀለኛ አትሆንም።

ለ. የመዳኛ መንገድ ያለ ጥርጥር አንድ ነው፤ ያም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ ሕይወት ነው፤ ይህ ግን ተግባራዊ መሆን የሚችልበት ብቸኛ መንገድ የክርስቶስን የደኅንነት ሥራ የሚገልጸውን የወንጌልን መልእክት በመስማት ጆሮው የተከፈተለት ሰው ምላሽ ሊሰጥ ሲችል ነው። በማኅፀን ውስጥ ያሉ ፅንሶች ይህን በመስማት፣ ጆሮዎቻቸውን እግዚአብሔር ከፍቶ ይድናሉ ለማለት የሚያበቃ መረጃ ምንም የለም፤ መኖሩ ደግሞ በፅንስ ደረጃ ያሉትንም የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን፣ ተወልደውም በማደግ ላይ ላሉት ሕፃናት ሞት በመወራረድ የሚደረስበት ምንም ዓይነት ማጠቃለያ አይኖርም፤ ከዚህ የተነሣ አንዲት እናት በጉዳዩ ልትጨነቅ አይገባትም።

ሐ. አስቀድሞ ልጁ ለገሀነም ስለ ተወሰነበት መቼም ቢሆን አለ ማየቱ ያሳዝነኛል፤ የሚለውን መረዳት፣ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ ጋር የተሳሰረ መሆኑ አይዘነጋም፤ እግዚአብሔርን የሰው ልጆች በተመቻቸውና በሚፈልጉት መንገድና ምኞት ሊመሩትና ሊያስወስኑት አይችሉም። እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነት ጽኑ ሆኖ የሚገኘው የገዛ ፈቃዱን የመፈጸም ብቃት ያለው በመሆኑ ነው። ከዚህም የተነሣ በኃጢአት የረከሰ የሰው ልጅ ለምን ይህን አደረግህ? በማለት ሊሞግተው አይችልም። ምርጫ ከእግዚአብሔር ዘንድ በየዘርፉ መገለጡን የእግዚአብሔር ቃል ሳያሻማ ያስረዳል፤ ግና ውርጃን በልጇ በፈጸመች ልጅ ዕጣ ፈንታ ላይ ቅድመ -

ውሳኔው ቅልብጭ ብሎ አልተጻፈም። ከዚህም የተነሣ ለአንድ እውነት የመደምደሚያ መገለጫን ከራሳችን ተጠያቂያዊ አካሄድ በመሄድ ብቻ፣ «ይህ ለዚህ ከሆነ፣ ለዚህም ያው ነው» ብሎ መጠቅለል፤ በእግዚአብሔር ቦታ ላይ ለመቀመጥ መዳዳትን ያመለክታል። እናም «ቁርጤን አውቄዋለሁ» በሚል የፍጻሜ ድንበር ላይ ሆኖ መቆዘም የዕለት እንጀራ ሊሆን አይገባም። ይልቅስ፣ ተከታዮቹ የጌታን ንግግሮች ልብ ይበሉ፦ «ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፣ ደቀ መዛሙርቱ ይህን ባዩ ጊዜ ሰዎቹን ተቈጡአቸው። ኢየሱስ ግን ሕፃናትን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አለ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ስለ ሆነች ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፣ አትከልክሏቸው። በእውነት እላችኋለሁ! የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን ያልተቀበላት ሰው አይገባባትም» (ሉቃስ 18፡15-17)።

«በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ «በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው? ሲሉ ጠየቁት። ኢየሱስም አንድ ሕፃን ጠርቶ በመካከለቸው አቆመ፤ እንዲህም አለ፣ «በእውነት እላችኋለሁ፦ ካልተለወጣችሁና እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማይ ከቶ አትገቡም» (ማቴ. 18□፡1-2)። እነዚህን መሰል የእግዚአብሔር ቃሎች በዕንስ ውስጥ ስላሉት ያሉት ነገር ባይኖርም፣ ተስፋው ግን አራዝመው ጠሪዎች ናቸው።

> እናቲቱን በመጪው ዘመን ስለሚቋቋመው ተገዳዳሪ ውራጅ ሕፃንም ከተነገሩት ራስ-መቺ ትውፊታዊ ንግግሮች ጥቂቱን በማለት የእነርሱን የእሥር ሰንሰለትነትን ደግሞ እንበጥስ፦

ሀ. በገሀነም ያለውን እሳት በሰባት እጥፉ በማንደድ ሁሌ ማገዶ አቅራቢ የመሆኑ ትውልዳዊ ንግግር «አፈ ታሪክ» ነው፤ አፈ ታሪክ መነሻው ብዙ ጊዜ እውነት ሊሆን ይችላል፤ በዚያ እውነት ላይ ተጨማሪና ተቀናሽ ተረቶች ታጅለውበት ከእግዚአብሔር እንደ መጣ መልእክት ያደርጉታል ይህም እንዲሁ ነው፤ የገሀነም መኖርና ለፍርድ የተገቡት መቃጠላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፤ ተጨማሪ

ው ጉዳይ ግን ለኃጢአት የወጣለት ደረጃ፣ የማገዶ አቅርቦቱ፣ የልጁ እናቱን የማቃጠል አገልግሎቱ ሐሰት ነው። የእግዚአብሔር ቃል፣ «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል» ነው የሚለው። እናም ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው (ሮሜ 3፡23፤ ድ.ት)። ዐቢዩ ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት ነው፤ ይህ ደግሞ መፍትሔ አለው፤ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ይሆናል፤ በእግዚአብሔር ፊት መስረቅ ከመግደል፣ መዋሸት ከመዘሞት ጋር ያላቸው ዋጋ እኩል ነው፤ ውርጃም ከሌላው በልጦ ለሰባት እጥፍ ንዳድ ምክንያት አይሆንም፤ ውርጃን የፈጸመች ሴት በክርስቶስ በመሆን ኃጢአትዋን ብትናዘዝ፣ የኢየሱስ የመስቀል ላይ ሥራ ፈጽሞ ያነጻታል (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)። ከዚህም የተነሣ፣ በገሃነም ደጃፍ አገልጋይ ሆነ የተባለው ሰው ይህን መብት እግዚአብሔር አይሰጠውም።

ለ. እግዚአብሔር የማራትን ሴት፡- ልጆቿ በመከላከል ያባርሯታል የሚለው የሸመገለ የቅብብል ትውፊት ደግሞ፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ራሱን ሊመሠርት የሚያስችለው መነሻዊ ፍንጭ የለውም፤ ይልቅስ፣ የእግዚአብሔር ምክር፣ «ልጆቼ ሆይ! ይህን የምጽፍላችሁ ኃጢአት እንዳትሠሩ ብዬ ነው፤ ነገር ግን ማንም ሰው ኃጢአት ቢሠራ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እርሱም ኃ□ጢአታችን ይደመስሳል። የእኛ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን፣ የዓለሙም ሁሉ ኃጢአት የሚደመሰሰው በእርሱ ነው» (1ኛ ዮሐ. 2፡1-2፤ ቀ.ድ.) የሚለው ጽኑ ምክር በእግዚአብሔር ይቅር ባይነት ላይ ሻሪ ወይም ጣልቃ ገብ አለመኖሩን ያበሥራል፤ በሰማይ ኃጢአትም ሆነ ኃጢአተኛ የለም፤ ከዚህ የተነሣ፣ ከትንሣኤ በኋላ ለገነት የበቁትን ሊከለክሉ የሚችሉ ኃይሎች ባለመኖራቸው፣ ውርጃን የፈጸመች ሴት በመጪው የሕይወቷ ጉዳይ ላይ ከእግዚአብሔር በቀር የሚመለከተው ማንም የለም።

ሐ. በገነት የተገናኙት እናትና ልጅ፡- በልጁ ትልቅ መሆን የተነሣ እናቱ የፈጸመችበትን በማስታወስ ትሸማቀቃለች፤ የሚለው ትውፊታዊ ቅብብል መነሻው፣ ኢየሱስ እኔም በአባቴ ፊት አፍርባቸዋለሁ (ሉቃስ 12፡8-9 እና 1ኛ ቆሮ. 3፡14) ሊሆን

እንደሚችል ይገመታል።□ ሥራው በእሳት ተቃጥሎ የተ ደመሰሰበት ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንደማያፍር በመናገሩ፣ ይህን በእናቲቱ ሕይወት ላይ ለመተግበር ይሞክራል። ይህ ትውፊት ግን የራሱ የሆነ ችግር አለው። ሉቃስ ማፈርን የገለጸበት ታሪክ ስለ ክርስቶስ በድፍረት ስላለመመስከር የሚሆን ጉዳይ ሲሆን፣ የጳውሎስ የቆሮንቶስ መልእክት የክርስቲያኖች ሁሉ ሥራ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚመዘን የገለጸበት እንጂ፣ የልጁ አዋቂ ሆኖ በዚያ በመገኘት እናቱን ለማሳቀቅ ምክንያት አይሆንም። ይልቅስ፣ እግዚአብሔር ራሱ «ከእነርሱ ጋር ይሆናል፤ አምላካቸውም ይሆናል፤ እንባን ሁሉ ከዓይናቸው ላይ ይጠርጋል፣ የቀድሞው ሥርዓት ስላለፈ ሞት ወይም ኀዘን ወይም ለቅሶ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም» (ራእይ 21፡3-4፤ ቀ.አ.) ስላለ፣ ውርጃን የፈጸመች ሴት ተስፋዋ በጌታ ፊት መጽናት ነው።

መ. ውርጃን ከፈጸመች በኋላ የወለደቻቸው ልጆቿ ዐመፀኛ በመሆን ያሠቃዩዋታል፤ የሚለው የሰባክያን ንግግር፣ «ሰው ሁሉ የዘራውን ያጭዳል» የሚል መነሻ ቢኖረውም፣ በብቻው መውሰድ ሙሉ መልእክትን አያመጣም። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በግሉ ይጠይቀዋል፤ የአንዱ በረከት ለሌላው፣ የወላጅ በደል ወደ ልጅ መተላለፉን አያስረዳም፣ ኖኅ፣ ዳንኤልና ኢዮብ በውስጥዋ ቢገ ኙ እንኳ በደግነታቸው ማትረፍ የሚችሉት የራሳቸውን ሕይወት ብቻ ነው (ሕዝ. 14፡14፣ ቀ.አ) «ወላጆች ጐምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፣ ነገር ግን፣ የልጆቻቸውን ጥርስ አጠረሰ» (ሕዝ. 18፡2) በማለት ከወላጅ የተነሣ ቅጣት ወደ ልጅ እንደ ተሻጋገረ የሚናገሩትን ደካሞች እግዚአብሔር እንዳይናገሩ፣ እንዲያቆሙም አዟል። በሮሜ 14፡12፣ «እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን መልስ እንሰጣለን» በማለቱም፣ እያንዳንዱ ሰው የነፍስ ወከፍ ተጠያቂነት እንጂ፣ ከወላጅ ወደ ልጅ ትልልፍ አለመሆኑን አስረድቷል፣ ከዚህም የተነሣ፣ ውርጃን የፈጸመች ልጆቿ እንደ አጋጣሚ ዐመፀኛ ሆነው ቢገኙ፣ አስተዳደግ፣ አካባቢያዊ ተጽዕኖ ወይም መሰል ጉዳዮች ያመጡት እንጂ፣ ልትቀጣበት፣ ልትሰቀ-ቅበትና እግዚአብሔር እንዳደረገው ሊወሰድ አይገባም፤ በትይዩው እኩ፡- ውርጃን የፈጸሙ ወላጆች የተመሰገኑ ልጆች ኖረዋቸው የመገ

ኘቱ እውነታስ ይህን እምነት ከንቱ አያደርገውምን?

የፈውስ መዋጮ ለውርጃ ተጠቂዎች

- ፈጥናችሁ አትፍረዱ፤ ይፈረድባችኋልና።
- የገዛ ኃጢአቱን ማየት የተሣነው ሰው ሁሌም የሚያየው የሌላውን ድካም ነው።
- ፍርሀትና ተስፋ መቁረጥ የከፋ ውሳኔን ለማስወሰድ ፈጣኖች ናቸው።
- አዛኝ ሰው ኃጢአትን ይጠላል፤ ኃጢአተኛውን ግን ይወደዋል።
- ለማገዝ የሚወዱ በብዙ ቁጥር የውርጃ ውሳኔዎች ይቀንሳሉ።
- ውርጃን በፈጸመች በዓመቱ የፀነሰች ሴት «የለመደች» ተብላ ልትወገዝ አይገባም።
- ውርጃን ለመግታት የተነሡ ሰዎች በፍቅር ዙፋን ላይ እንጂ፣ በፍርድ ወንበር ላይ አይቀመጡም።
- ፅንሶቹ ነገን እንደሚያጨልሙ ቢቆጠሩም እንኳ፣ የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸው አይዘንጋ።
- የእግዚአብሔር ይቅርታ ፈጣን ነው፤ የሰውን አእምሮ ማፅዳት ግን ዓመታትን ይፈጃል።
- የወዳጃችን ሞት በእንባ ታጥቦ ሊጸዳ ይችላል፤ በውርጃ ከታጣው ሕፃን ሞት ለማገገም ግን ጊዜ ይወስዳል።
- ውርጃን በመፈጸም የዓለሙ ብቸኛ «እኔ ነኝ»□ ብሎ መቁጠር «ዕድሜን ያሳጥራል።»□

ባል ሆይ!... ሚስት ሆይ...!

ባል ሆይ!

እስቲ ልጠይቅህ፤ ሌሊት ሚስትህ ትቀስቅስህና፣ «የምትወስድብኝን እርምጃ ባልረዳውም፣ ከመጋባታችን በፊት ሁለት ጊዜ ውርጃ ፈጽሜ ነበር፤ አንድ ጊዜ በገዛ ወንድሜ በመደፈር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ያገባኛል ብዬ ተስፋ ያደረግሁት ሰው በከዳኝ ወቅት መፍትሔ ነው ብዬ ውርጃን መረጥኩ። ይህ ደግሞ ለአንተም ለሌላውም የደበቅኩት ብቸኛ ምሥጢሬ ነው» በማለት ትነግርሃለች። በዚህ ወቅት አንተ መስማት ከጀመርክበት ሰከንድ እስከ ጨ

ረሰችበት ሰዓት የነበረህ ስሜት ምን ዐይነት ነበር፡- «አንቺ ሽርሙጣ፣ ውጪልኝ» ለማለት መቃረብ፣ ወይስ ሌላውንም ተጨማሪ ችግሯን ለመካፈል በጉጉት መዘጋጀት

ሚስት ሆይ!

እስቲ ልጠይቅሽ፤ ባልሽ፣ «እኔ እኮ የመጀመሪያዋን የፍቅር ጓደኛዬን ውርጃ እንድትፈጽም በማድረጌ እስከ ዛሬ ድረስ ይጸጽተኛ ል። ሌላው ቀርቶ ከአንቺ ጋር ተስማምተን ጽንሱን ለማስወገድ የጋራ ጥረት ማድረጋችንን ሳስታውስ ጎሊናዬ እረፍት ያጣል። በቅርቡም. . .» እያለ ቢቀጥል፣ በጩኸትሽ፣ «ልሰማው አልፈልግም!» ነው የምትዪው፣ ወይስ በጸጥታ አድምጠሽው ልት ረጂው መላ ትፈልጊያለሽ?

ልከኛው የባሎችም ሆነ የሚስቶች አቋም ዘላቂ ዕብደት ወይም አለመረጋጋት ሊሆን፣ አልያም፣ «እርሺው፣ እርሳው» በመባባል የሚገታ ጉዳይ አይሆንም። ርእሰ ነገሩ ስሜትን ሊነካ፣ ፍቅርንም ሊሸረሽር ስለሚችል፣ ረጋ ብለን ራሳችንን መጠየቅ ሊኖርብን ነው። ያለኝ ልብ ሊምር ወይስ ሊገድል የሚችል ነው? ብለን ማጣራት አለብን። የማጣራቱ ዘመቻ ደግሞ ማን ያውቃል ሚስትህ ለመናገር ባመቻቸሃት ቁጥር ሌላም ሌላም እየነገረችህ የዛሬ ወርም ያለ ዕቅዷ እንደ መጣ የቆጠረችውን ፅንስ ሳታማክርህ ማስጨንገፏን ታረዳህ ይሆናል። በአንዳሩ፣ ባልም የቅርጽ ለውጥ ካልሆነ በቀር፣ በይዘት የሚመሳሰል የተከደነ ተወንጃይ ሕይወቱን ሊያወራሽ ይችላል። *በዚህ ሁሉ ሐቀኛው ምላሽ ምን ይሆን?* ዛሬ የሚደረገው ውሳኔ የየራሳችሁን ትክክለኛ መንፈሳዊ አቋምና መረዳትን ያንጸባርቃል። ምሕረትንና ፍቅርን በመለገስ ቀጣዩን የአጋርን ሕይወት በማቅናት ሰፊ ሥራን ከውድቀት መጀመር፣ አልያም በእንባ፣ በቁጣና በዛቻ ተሞልቶ «ይቅርታ ለምኔን» ዋስ መጥራት፤ «ለየልንን» በማራመድ ጥፋትን፣ ሞትንና መለያየትን እማኝ መጥራት።

ሰው መሆን አለና፣ በዚህ ውስጥ የተቀላቀለ የውሳኔ ሂደትም ሊገጥም ይችላል። ፈውስን ለማፍጠን ግን የተሻለው ማበዱ ሳይሆን፣ ጉዳዩ በጊዜው ይቅር ለማለት እንኳን ከብዶ ቢገኝ፣ ሊረዳ ወደሚችል እግዚአብሔር በመጸለይ ሰላምን ከአጋርህ፣ እረፍትንም ከእግዚአብሔር መለመኑ ተመራጭ ነው። በትይዩ፣ ይቅርታን

ላለማድረግ ምርጫን ማድረግ ደግሞ በውጤቱ ጥፋትን ብቻ የሚያመጣ መንገድ መሆኑን ውሎ አድሮም ቢሆን መረዳት አይቀሬው ነው።

ኢየሱስ ጸሎትን ባስተማረ ጊዜ፣ «የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን» (ማቴ. 6:15፤ 18:35) ማለቱን አለመዘንጋትና በመስቀል ላይ ሳለም ለሚበድሉት፣ «አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» (ሉቃስ 23:34) ብሎ መጸለዩን በማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ በመኖሩ ማመን ግድ ነው። እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ (ዮሐ. 15:12) የሚለው መልእክትም ጥልቀቱ በዚህ ላይ ይለካል።

ይህንን የጠላ የናቀና ፈራጅ ብቻ ሆኖ የተሰየመ ሰው ግን በእጁ ያለውን ፈውስ አርቋልና ሞት በገዛ እጁ ላይ ይሆናል።

ሊዘነጋ የማይገባው እውነት

በመከራችን የሚያጽናናን እግዚአብሔር ዛሬም በሥራ ላይ ነው። «የምሕረት አባትና መጽናናትን ሁሉ ለሚሰጥ እንዲሁም ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አባት ለሆነው ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን። እኛ ከእግዚአብሔር በምናገኘው መጽናናት በመከራ ላይ ያሉትን ሁሉ ማጽናናት እንድንችል እግዚአብሔር እኛን በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል» (2ኛ ቆሮ. 1:3-4)። ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር ውርጃን እንድንፈጽም ከጎናችን አይቆምም፣ በፈጸምነው አሰቃቂ ድርጊት ግን እያስተማረ፣ እያጽናናም ሊያሳድገን ዝግጁነቱ አልቀረም።

ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቃወማል፤ ኃጢአተኛውን ግን ይወዳል፤ መውደዱ ሰዎች በንስሐ ወደ እግዚአብሔር በመምጣት ሰላምን እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታንም በማዘጋጀት ይገለጻል። በዚህ ምጥን ጽሑፍ ውርጃን ለመፈጸም የሚያስገድዱ በቂ የሚመስሉ ምክንያቶች እንዳሉ አልተዘነጋም፦

- ከትዳር ውጭ የመጣ ልጅ «ዲቃላ» የመባሉ ፍርሐት፣
- በትዳር ውስጥ የመጣ ፅንስ ማሳደግ በሚያስችል አቅም ላይ አለመሆን፣

- በማኅፀን ያለው ሕፃን አካለ ስንኩል - መሆኑ መታወቁ፣
- የጓደኛ፣ የባል፣ የወላጆችና የሐኪም የምክር ግፊት፣
- ፅንሱ በኤድስ በመጠቃቱ ወላጅ - አልባ ልጅ መገኘቱ፣
- በመደፈር የመጣ ፅንስ አባት - የለሽ መሆኑ፣ እና የመሳሰሉት ውርጃዎችን ለማስፈጸም እንደ ምክንያት ይሆናሉ፤ ግና እነዚህን ከመሰሉ ምክንያቶች ባሻገር ውርጃን የፈጸመች ሴት ከሥነ ልቦናዊ ቀውስ ጀምሮ በተለያዩ በሽታዎች በመጠቃት ተጐጂ ልትሆን መቻሏ፣ የእግዚአብሔር የሆነው ፍጹም ሕግ መጣሱ፣ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ሊያኖር የገባውን ተስፋና መጽናናት ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ሲሆን፣ በግድያ ተገብቶታል ውስጥ አለመሳተፍን ማብራራት ደግሞ የሁላችንም የፍቅር አገልግሎት ሊሆን ይገባዋል። ይህንንም በመፈጸም ድምጿን ከፍ አድርጋ ማሰማት የሚገባት የክርስቶስ የሆነችው ሕያው ቤተ ክርስቲያን ናት።

ጾምና ጿሚዎች

የጾም ትክክለኛ ፍቺ «ለተወሰኑ ሰዓታት ወይም ቀናት ከምግብና ከመጠጥ መታቀብ» ማለት ነው። ከዚህም በመነሣት፣ መጾም ባለመመገብና ባለመጠጣት ይገለጻል። የዚህን ሥርዓት ወይም አካሄድ አስፈላጊነት ለመግለጽ በተለያዩ ጊዜያት የተነሡ የወንጌል አስተማሪዎች የየራሳቸውን ገለጻ በየድርሳናቸው ላይ ከትበው ለአንባቢው ትተዋል።

የሦስት ያህሉን ድርሳናት ስንፈትሽ ስለ መጾም ያሉት እንዲህ ነበር፦ ማቲው ሄንሪ (Matthew Henry)፣ «ጾም ሊተገበር የሚገባው በክርስቲያኖች ዘንድ መሆኑን ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል» በማለት ጽፏል። የቅድስና ወንጌል ሰባኪ የሆነው ጆን ዌስሊ (John Wesley)፣ «ትሕትናንና ቅድስናን የተሞላ ሕይወት ለመኖርና ከእግዚአብሔር ጋር በመቀራረብ ግላዊ ግንኙነት ለማዳበር ተፈላጊው ጾም ነው» በማለት ይዘክራል። ማርቲን ሉተር (Martin Luther) የከፊል ተሐድሶ አንቀሳቃሽ የነበረውም፣

«የክርስቶስ ሁነኛ ዓላማ ጾምን ማዋረድ፣ መናናቅና ማስወገድ አይደለም፤ ይልቅስ፣ ጾም በጂሚዎች እና በአጽዋሚዎች ዘንድ ተ ዛብቶ ነበርና ይህን ለማስተካከል እርምጃ ወስዷል። ክርስቶስ ጾምን ወደ ትክክለኛው ዓላማ በማድረሱም ክርስቲያኖች እንዲጾሙ መሠ ረትን ጥሏል» በማለት ጽፏል።

እነዚህ በክርስቶስ የሆኑ ክርስቲያኖች በተለያዩ ወቅቶች በጻፉት የጾም መርኅ የአሳብ ስምምነትን ይዘዋል። እነዚሁ ሰዎች አስከትለው ያስተማሩት ለመጾም የተፈለገበት ሁነኛ ምክንያትን መተንተን ነው። ካሉት በጥቂቱ እነሆ፣ በጾም የተፈጸመ ጸሎት ባልተከፈለ ልብ ወደ እግዚአብሔር ያደርሳል፤ ጾም አስፈላጊ የሆኑ ወሳኝ ምሪቶችን ከእግዚአብሔር ያስገኛል፤ ጾም በእግዚአብሔር ጸጋ ዕለት ዕለት ለማደግ ይረዳል፤ ጾም የፈዘዘና አቅም ያጣ እምነታችንን ያሳድጋል፤ ጾም በአጋንንት ዐሠራር ምሥጢር ላይ ገናና ያደርጋል፣ ጾም የወንጌልን መልእክት በግልጽ ያሰብካል፣ ጾም በርካታ የውስጥ ደዌዎችን መቋቋም ያስችላል፤ ጾም አዳማዊ በሆነው ሥጋዊ ባሕርይ ላይ ያነግሣል፣ የተለያዩ ፈተናዎችንም ለማሸነፍ ጾም ይረዳል በማለት የተዘረዘሩትን የተቀሩትን በጋዜጦቻ ቸው፣ በመጽሔቶቻቸው፣ በመጽሐፎቻቸውና፣ በስብከተ ወንጌል የመስበኪያ ስፍራዎች ሁሉ ላይ ብዕራቸውን አንሥተው፣ ድምጻቸውንም ከፍ አድርገው ያሄም አስተምረዋል፣ ዘንድሮም እንዲሁ ይጽፋሉ፣ ይሰብካሉም።

ሉቃስ በወንጌልም ሆነ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ መግቢያ ላይ እንደ ገለጸው፣ «ሁሉን ነገር በጥንቃቄ መርምሮ እርግጡን ብቻ ጽፏል።» ልክ እንደ እርሱ፣ ጥንቃቄን የተሞላ ምላሽን ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ እኛም እንተንትን።

ጾምና ጾመኞች፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በርካታ ስፍራዎች መከናወናቸውን ጥቂት ናሙናዎችን በመውሰድ መግለጽ ይቻላል። ነህምያ፡- ሕዝቡ ስለ ኃጢአታቸው መጸጸት፣ ማቅ ለብሰውና ትቢያ ነስንሰው እንዲጾሙ (ነህ. 9:1) መመሪያን ሰጥቷል፤ በአስቴር ዘመን ይሁዳዊ ሁሉ ባለበት እንዲገደል ትእዛዝ መውጣቱ ግልጽ ነው፤ ዳንኤል የወገኖቹን በደል በመናዘዝ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩንና መጾሙን፣ (ዳንኤል 9:3) እንዲሁም ዳዊት ሌሎች

በሕመም በተሠቃዩ ጊዜ እናቱ የሞተችበት ያህል በማዘን መጾሙን ከቅዱሳት መጻሕፍት እናነብባለን።

እነዚህና ሌሎችም ከመጾም ጋር የተገናኙ ክንውኖች ግን ከመሪ ዎቹ አልያም ከግለሰቡ ፍላጎትና መመሪያ የተነሣ በፈቃዳቸው የፈጸሙት እንደ ሆነ ማስተዋል ተገቢ ነው። ይህም ጾሙ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ሆኖ ለዘላቂነት በተሰጠ ጸኑ መመሪያ እንዳልተደነገገ ግልጽ ነው። እርግጥ፣ ከላይ በተጠቀሱት በሁሉም ላይ የምናገኘው የጋራ ነጥብ በኃጢአት የመጣን ጣጣ ለማስወገድ ሳይሆን፣ ለመቅረፍ የተፈጸሙ መሆናቸውን ነው።

ከእነዚህ ይልቅ ግን ሚዛን ደፊው የጾም ድንጋጌያዊ ትእዛዝና አፈጻጸሙ የተገለጠበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአንድ ስፍራ ብቻ እንደሚገኝ እንመልከት። ለዚህም ዘሌዋውያን 16፡29-34 መነሻችን ይሆናል፦

«ሰባተኛ ወር በገባ በዐሥረኛው ቀን እስራኤላውያንና በእነርሱ መካከል የሚኖሩ መጻተኞች ራሳቸውን ማዋረድ አለባቸው፣ በዚያን ቀን ምንም ሥራ አይሠሩበትም። በዚያን ዕለት ንጹሐን እንድትሆኑ፣ የኃጢአት ማስተሰረይ ይደረግላችኋል፤ . . . በዓመት አንድ ጊዜ የእስራኤላውያን ኃጢአት ሁሉ ማስተሰረይ የዘለዓለም ሥርዓት ይሆናል።» (አ.መ.ት) በማለት የዘሌዋውያን ጸሐፊ ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የጾምን ብቸኛ ምክንያት ሳያሻማ፣ ሳያደናግርም ያስተላልፋል።

በዚህ በአሁኑ ተጠቃሽ ክፍል የመጾሚያ ቀንና ወር በትክክል ይታወቃል፤ የጾም ምክንያቱም ለኃጢአት ስርየት መሆኑ ተገልጿል። ይህን ክፍል ሁላችንም በአግባቡ መረዳታችን ተገቢ ስለሆነ፣ ጥቂት ብርሃን በድንጋጌው ላይ እናብራበት፦ ኃጢአት በአዳም በኩል ወደ ዓለም በመግባቱ፣ ሁሉ በኃጢአት ተበከለ፤ ሁሉም ከእግዚአብሔር ላይገናኝ ተለያየ፤ የሰው ዘር በራሱ ጥረትና ድካም ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ቢመኝና ቢደክምም፣ ሁሉ ከንቱ ሆነው እንዲቀሩ እግዚአብሔር ራሱ ለእስራኤላውያን ተስፋን የሞላበት የሽክም ማቅለያ መንገድ ዘረጋላቸው። ያም የኃጢአት ሸክማቸውን ያቃልሉ ዘንድ በዓመት አንድ ቀን በሊቀ ካህኑ በኩል የኃጢአት ስርየት እንዲፈጸም ማድረግ ነው። በዛን ቀን ሕዝቡ ስለ

ኃጢአት እንዲያዝንና እንዲጸጸት ታዘዘ፤ ለስርየትም የንጹሕ እንስሳ ደምን ይዞ መቅረብ ግድ ሆነ። ለዚያም ዝግጅት መጾም ተገቢው መስፈርት ሆኖ ተሰጠ። ይህንንም በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን በዓመት አንድ ቀን በመጾም እንዲታዘዙ እግዚአብሔር ደነገገ።

ይህ አደራረግ ግን ዳግመኛ ላይፈጸም የተሻረበት ታላቅ ሥራ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሥራው ተከናውኗል። መጥምቁ ዮሐንስ ለብዙዎች መዳን ምክንያት የሚሆነው ጌታ መምጣቱን እንደ ተረዳ፣ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ እርሱ ነው በማለት የብሥራት ወንጌል በአዲስ ኪዳን መግቢያ ላይ አወጀ። ዓለም፡- በእግዚአብሔር አብ የተላከው ኢየሱስ የሰዎችን ኃጢአት ተሸክሞ በማያዳግም ሁኔታ መሥዋዕት ለመሆን ንጹሕ የፋሲካ በግ ሆኖ በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ። አንገትን አስደፍቶ ለነበረው ለሰዎች ልጆች ኃጢአት ፍጹም የሆነው ዋጋን በመክፈል መሥዋዕትነቱን በትንሣኤው ደምድሞ ተልዕኮውን በመፈጸም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተገኘ። በዚህም በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ስለ እኛ በመቆም ጠበቃና አማላጅ ሆነ። መፍትሔ-የለሽ ሆኖ በከንቱ ጥረትና በጥርጣሬ የተሞላውን የሰውን ሕይወት ወደ ሰዎች በመድረስ ከእስራታቸው በመፍታታ የክርስቶስ የሆኑ ሁሉ በነጻነት እንዲመላለሱ አደረገ። ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «በነጻነት እንድንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን» በማለት የአዲስ ኪዳንን ዘላቂ የሕይወት ኑሮ የእርሱ በሆኑት ሁሉ ዘንድ መስፈኑን በሮሜ መልእክቱ ጽፏል።

እንግዲህ የዘሌዋውያን በጾምና፣ በንዘን በመዋጥ ለኃጢአት መተከዝ በክርስቶስ ሥራ ተለወጠ። ጉድለት በሙላት፣ ሽንፈት በማሸነፍ፣ ኀዘን በደስታ፣ ባርነት በነጻነት መተካትን ክርስቶስ ስለ እኛ ብሎ ካደረገ፣ የጾም ተፈላጊነቱ ፈዘዘ፣ ደነዘ፣ ተሻረ፣ ቀረም ማለት ይቻላል። ይህ ግን የበለጠ ግልጽ ሆኖ የሚገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጾም ለጠያቂዎቹ በሰጠው ማብራሪያ ይሆናል (ሉቃስ 5:33-39 ይመልከቱ)።

በትምህርቱ እና በተግባሩ እንከን በመፈለግ ሊያጠምዱት ሁሉ የሚያደቡ እንቅፋቶች በጌታ ዘንድ ነበሩ፣ ፈሪሳውያን፣ የሕግ መምህራኑ፣ ሰዱቃውያንና ሄሮድሳውያኑ ይህን በመፈጸም ተግተ

ዋል። እናም አንድ ቀን ጾምን በሚመለከት ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠየቁት፤ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ይጾማሉ ይጸልያሉ፤ የፈሪሳውያንም ደቀ መዛሙርት ይጾማሉ፣ ይጸልያሉ፣ የአንተ ግን ሁልጊዜ የሚበሉት እና የሚጠጡት ከምን የተነሣ ነው? በማለት ለምን አይጾሙም የሚል ጥያቄ አነሡ።

የኢየሱስ ምላሽ ማርቲን ሉተር እንዳለው፡- «ኢየሱስ ጾምን አልከለከለም፤ ይልቅስ ወደ ትክክለኛው ዓላማና ግብ አመጣው፣» በማለት ዛሬም መጾም አስፈላጊ እንደ ሆነ በመግለጽ አልመለሰም። ይልቅስ፣ የኪዳናት ለውጥ ሊመጣ እንዳለ፣ አሮጌው በአዲሱ እንደሚተካና እንደሚቀየር በማብራራት ዘለቀ።

ያለው እንዲህ ነው፡- በእስራኤላውያን ዘንድ እንደ ሰዎች ድንጋጌ ሰኞና ሐሙስ ሁልጊዜ ከጀምበር መውጣት እስከ መጥለቅ ከምግብና ከመጠጥ በመታቀብ መጾማቸው ተግባራዊ የማይሆንበት ወቅት የሚኖረው ተፋቃሪዎች ሲሞሽሩ ነው በማለት አስረዳ። ሙሽራ ባለበት ሁሉ መዜሞችና ቤተሰቦች ሁሉ መጾም እንደማይገደዱ ሁሉ፣ የእኔ ደቀ መዛሙርት የማይጾሙት እኔ ሙሽራው በመካከላቸው እስካለሁ ድረስ ሊደሰቱ ይገባል፤ ከምግብና ከመጠጥም ሊርቁ አይገባም በማለት፣ የደስታቸው ዋንኛ ምንጭ አብሮአቸው እስካለ ጾምም በእነርሱ ዘንድ ሊገኝ እንደማይገባው ገለጸ።

እርግጥ፣ አጭር ጊዜ ይመጣል፣ ያም ለጊዜው ሙሽራው ከእነርሱ ይለያል፤ ያኔ ይጾማሉ አላቸው። ይህ አጭር ጊዜ የእርሱ ለሆኑት የመስቀልን ሞት የሚጓዙበት፣ ኃጢአታቸውንም ተሸክሞ ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ የሚታረድበት የሞት ወቅት ነበር። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ በኀዘንና በድንጋጤ ተውጠ ተለይተዋል። ኋላ ግን በሞቱና በትንሣዔው ብሥራት ደሙንም በእግዚአብሔር ፊት ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ በማቅረብ የነጻነትንና የድልን ብሥራት አከናውኖ ሙሽራው ተመልሶ ከእነርሱና ከአማኞች ሁሉ ጋር ሆኗል።

ይህንንም በማቴዎስ 28፡19-20፣ «እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ» በማለቱ፣ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ከ14-16 እንደተናገረው፣ ለዘላለም ከአማኞቹ ሁሉ ጋር በመንፈስ ቅዱስ

መሆኑን ማብሰሩና ሆኖ መገኘቱ፣ የያኔው ለጥቂት ጊዜ መለየቱ ባለመለየት መገለጹን ያስረዳል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ኋላ ላይ ሊመጣ የሚችለውን የድል ሥራ ሲገልጽ ማንም የቀደመውን አካሄድ ከአዲሱ የነጻነት መንገድ ጋር እንዳያቀላቅለው ብርቱ ማስጠንቀቂያ በመስጠት አብራርቶ ደምድሟል።

ድምዳሜው እንዲህ ነበር፦ ልብሱ አርጅቶ ቢነትብና ሊቀደድ ቢቀርብ ማንም እንደ መፍትሔ ቆጥሮ ከአዲሱ ጨርቅ በመቁረጥ በአሮጌው ላይ ቢጥፍ፣ አሮጌው አርጅቶ በመድከሙ አዲሱም አዲስ ሆኖ በመጠንከሩ እርስ በርሳቸው ሊዘላለቁ አይችሉም። አዲሱ ለአሮጌው ፍጹም አለመስማማቱን ይገልጻል (ሉቃስ 5፡36)። ልክ እንዲሁ፣ ሌላ ተመጣኝ ማብራሪያን ሲያስከትል፦ ወይን ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀምጦበት የነበረ የቀድሞ አቁማዳ በዘመኑ በገባበት የወይን ጠጅ መብላላት ተስፋፍቶና ተወጥሮ ካበቃለት፣ ሁሌም ይዞ ሊቆይ የሚችለው ቀድሞ በውስጡ እንዲገኝ የተገባውን የወይን ጠጅ ብቻ ነው። እንዲህ ከሆነ፣ በቀድሞው አቁማዳ (በአሮጌው) የቀደመውን የወይን ጠጅ አስይዞ ማኖር የተሻለ ነው። ከዚህ በተቃራኒው ግን፣ ተስፋፍቶ ተለጥጦ መጠኑን በጨረሰ አሮጌ አቁማዳ አዲስ የሚፈላ የሚብላላ ጉልበት ያለው የወይን ጠጅ እንዲቀመጥበት ቢደረግ፣ ሊመጣ የሚችል አንድ ሁነኛ ጣጣ ይኖራል፣ ያም አዲሱ በአሮጌው ውስጥ እየፈላ መጠኑ ሲጨምርና ሲስፋፋ፣ አቁማዳው ተጨማሪ የመስፋት አቅም ስለሌለው ይፈነዳል፤ በፈነዳም ጊዜ አዲሱ የወይን ጠጅ ይፈሳል አላቸው።

እንግዲህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማመሳሰሉ ዋነኛ ምሥጢር አዲስ የሆነውን ልብስም ሆነ አዲሱ የወይን ጠጅ በአሮጌው ላይ ሊካተቱ ፍጹም አይገባም የሚል ነው። በአጭሩ፣ አሮጌው የቀደመውን ኪዳን ያመለክታል፣ ያም የሕግ ሥርዓቶችን፣ የመሥዋዕት አቀራረብን፣ የክህነት አገልግሎትንና በአጠቃላይ ሕግን ባለመፈጸም ከውድድር የሚወጡትን የሚኮንን ነው። ያ ግን በክርስቶስ ሥራ ፍጹም ተቀይሮ አዲስ ልብስ፣ አዲስ የወይን ጠጅ ቀርቧል፤ እርሱም የኢየሱስ ለአንዱና ለመጨረሻ የመሥዋዕትነት በግ ሆኖ የቀረበበት የትንሣኤ መንገድ ነው። ያ ሥራ ሕያው ነው፣ ያ መንገድ አዲስ ነው፣ ከአሮጌው ኪዳን ጋር አይጣጣምምና

አዲስ ኪዳን የሆነ ኪዳን ነው። ከዚህም ኪዳን የተነሣ ማንኛውም ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በድፍረት መቅረብ ይችላል። ያኔ ግን እንዲህ አልነበረም። ኢየሱስ ለተጠየቀው ጥያቄ በሰጠው ምላሽ የትናንቱን የጸም ሁኔታና እርሱ በነበረበት ያለውን በመተንተን መጪው ወቅት አዲሱን ጎዳና ተከታይ ሊሆን መግባቱን ያበሥራል።

በመጨረሻ፣ ሕግና ጸጋ ሊቀራረቡ የማይችሉ መሆናቸውን፤ አይሁዳዊ ሥርዓቶች ከክርስቲያናዊ የሕይወት እርምጃ ጋር ሊቃየጡ አለመገበታቸውን፤ በዙሪያችን ያሉ ጾም-ተኮር ስብከቶችና ትምህርቶች በአግባቡ ሊፈተሹ መገባቱን እያሳሰብን፣ አልፎ አልፎ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጾምን ያመላከቱ ጥቅሶች ግን አንድም ፈሪ ሳውያንና የቀድሞ የሕግ መምሕራን ከዘረጉት ተጨማሪ የቀጠኑ የገዛ አሳቦች የተነሡ የመጡ መሆናቸውን፤ አልያም አዲስ ኪዳን ገዝፎ በሁሉ ዘንድ ሙሉ የሆነ መረዳትን ባላመጣባቸው ሰዎችና አካባቢዎች የቀድሞው የኪዳን መስተዳደር ጥላውን ስላጠላ መጾማቸውን፣ መጾም ከተለያዩ ችግሮች የተነሣ ምግብ ለማግኘት ካለመቻል እህልና ውኃ ማጣትን በመግለጽ የተጻፉ መሆናቸውን በመገንዘብ ዋንኛ ወደ ሆነው አዲስ የሕይወት መንገድ መመለስ ለሁሉም የሚበጅ ይሆናል።

የአዲስ ኪዳን የሕይወት ተካፋዮች መንፈሳዊ ሕይወትን ሊ ረዱ የሚገባቸው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረው ጨለማውን ዓለም ብርሃን ማድረግ ክፉ አሠራሩንም በመግለጽ መኖር፣ እንዲሁም ለተበላሸውና ለተግማማው ዓለም ጨው በመሆን ማዳንና ማጣም የክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ሲሆን፣ ያም የክርስቶስን ተልዕኮ በመፈጸምና እግዚአብሔርን መስሎ በመኖር ይገለጣል፣ ይህን ሳይኖሩ መጾም የተለየ ጉልበት ሊያመጣ እንደ ሚችል ቢገመት፣ ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች የሰጣቸውን ቃል በማወቅ ደግሞም በማመን መረታት የተገባ ይሆናል፦

> «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ፣ በዓላትን ወይም የወር መባቻን፣ ወይም ሰንበትን በማክበር ምክንያት ማንም አይፍረድባችሁ። እነዚህ ሁሉ ወደፊት ይመጡ ለነበሩት ነገሮች እንደ ጥላ ናቸው፤ እውነቱ ግን የሚገኘ

ው በክርስቶስ ነው. . . ከክርስቶስ ጋር ሞታችሁ ከዚህ ዓለም መሠረታዊ ሥርዓቶች የተለያችሁ ከሆናችሁ ታዲያ፣ እንዳልተለያችሁ ዓይነት ሆናችሁ ስለ ምን እንደዚህ ላሉት ትእዛዞች ትገዛላችሁ፤ ትእዛዞቹም፣ «አትያዝ፣ አትቅመስ፣ አትንካ!» የሚሉ ናቸው። እነዚህ ሁሉ በሰው ሠራሽ ትእዛዝና ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ስለ ሆኑ ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ ለመጥፋት የተወሰኑ ናቸው። እነዚህ ትእዛዞች ከገዛ ፈቃድ በመነጨ አምልኮና በአጉል ትሕትና፣ ሰውነትንም ከማጕሳቆል ላይ ስለሚያተ ኵር ጥበብ ያላቸው ይመስሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ሥጋዊ ስሜትን በመቈጣጠር ረገድ ዋጋቢሶች ናቸው (ቈላ. 2፡12-23) በማለት የተገለጠውን እውነት ገልጦ ያበቃል።

«እንግዲህ በዓልን ሽሮ የከበረ፣ ጦምን ገድፎ የወፈረ የለም» የሚለውን ብሂል ምን ይዋጠው።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ

በበኩሌ «ድሮን አፍቃሪ ዘንድሮን ደግሞ አንኳሳሽ አይደለሁም። የዚህም ሁነኛ ምክንያቴ በአምሳሉ እግዚአብሔር የፈጠረው የሰው ልጅ በየዘመኑ የተመሰገኑ ሥራዎችን ለራሱ፣ ለኅብረተሰቡና ለመንግሥት ሊሠራ መቻሉ ደግሞም መሥራቱ አሌ አይሰኝም፤ በትይዩ ይህ የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ረክሷል፣ በኖረበት በየትኛውም ዘመን ጥፋትን፣ ክፋትን፣ ሞትን በራሱም በሕዝብም ላይ ሊያደርስ እንደ ቻለ፤ እንደሚችልም እሙን ነው።

ከዚህም የተነሣ ቶማስ አርጋው «አሲዳም ዘመን» ብሎ በጻፈው ጽሑፍ ላይ የሚገኙትን የመምሬን ገለጻ አላወድስም «... እርሳቸው»፣... «ይሁና ምን ይደረግ የአሥር ሳንቲም አረንቻታ ሁለት ብር ሲገባ፣ የውኃ ጣሙ ከድሮው ቢቀየር ምን ያስደንቃል? የተሟጠጠ ገፊ ጊዜ መሆኑ የሚታወቀው ሕፃናቱ ትናንት

ተወልደው በማግሥቱ ገርጅፈው ይሞታሉ፤ ሽንት ቤቱን ዛሬ ቆፍረውት ነገ ይሞላል፤ ቅቤውን ሲያነጥሩት ሽታ የለው፣ ቢበሉት አይጥም፣ ቢያስቀምጡት ውሎ አያድር...» እያሉ አፍቃሪ ድሮነታቸውን ተአማኒነት በጎደለው በጎነቱ ብቻ ላይ መሥርተው ብዙ ይዘረዝራሉ፤ ይህ ድርሳን ግን አያዋጣም::

ምናልባት ከፊል እውነት አለው የምልበት የኪዳነ ማርያም ጌታሁን «ጥንታዊው የቆሎ ተማሪ» መጽሐፍ በገለጻው፣ መግቢያ

«የጥንት ተማሪ ምግቡ ስብቅ፣ መቋሚያው ሽንበቆ
የዛሬ ተማሪ ምግቡ አልጫ፣ ዱላው በጡጫ::
የጥንት ተማሪ ቁርሱ ጸሎት፣ ያውም በቁመት
የዛሬ ተማሪ ቁርሱ ብስኩት፣ ያውም በወተት::
የጥንት ተማሪ ቀጋ ለቀጋ፣
የዛሬ ተማሪ አልጋ ለአልጋ::» (በ1954 ዓ.ም ታተመ)

እያለ ድሮና ዘንድሮ በተማሪ ሕይወት ላይ የተወው አሻራ ያኔ ችግር አሁን ደግሞ ሙሉ በሙሉ ምኞት መሆኑን መተንተኑ ነው::

ደራሲያኑ ቶማስ እና ኪዳነ ማርያም ሊያዩ በወደዱት አቅጣጫ ጽፈዋል:: እኛ በአግባቡ «በቆሎ ከጸደቀው» ሰው ጋር ግን አገባብነት ያለውን ዳኝነት እንድንይዝ በግርድፉ ልዘክርላቸው የምፈልገው ሰው አለኝ:: ገብረሕይወት ባይከዳኝ ይባላሉ:: ትውልዳቸው በትግራይ አድዋ ሲሆን፣ የተወለዱት በ1885 ዓ.ም ነው:: ብዙዎች የአገር እና የውጭ የታሪክ ዘጋቢዎች ስለ ገብረሕይወት ሲተርኩ፣ «እግዚአብሔር በሰጠው ጥቂት ዘመኑ ትውልድ ሁሉ የሚጠቀምበትን መሠረት ለአገሩ የተወ አዋቂ» በማለት ጽፈውላቸዋል፤ ይህን ያስባላቸው ሞታቸው በ1918 ዓ.ም በ33 ዓመታቸው ስለ ነበር ነው::

ዘውዱ አምበሉ በቅርቡ በአዲስ አድማስ ጽሑፉ «በፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንታኔያቸው፣ በታሪክ አዋቂነታቸው፣ እንዲሁም በአፍሪካ የመጀመሪያው የጥገኝነት ጽንሰ አሳብ (Dependency Theo-

ry) ጀማሪነታቸው እኚህ ሰው እንደ ሆኑ በመግለጽ ታሪክን ሊያዘቅጡ ያላቸውን ምሁራን በአግባቡ እንዲዳኙ ለዋቢነት ይጠ ራቸዋል።

እኔም እኚህ ሰው «ትውልድ ሁሉ» ከሚዘክርላቸው ሥራዎቻቸው ውስጥ የተወሰኑትን ነቅሼ በተለይ ለታሪክ፣ ለክርስትና ዕድገት እና ለአገር ያደረጉትን አስተዋጽኦ እገልጻለሁ።

እንዲህ መጥኜም ለመግለጽ የረዳኝን ቀዳሚ መጽሐፍ በ1904 ዓ.ም «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በማለት ለመጻፍ ስላበቋቸው ሰው ራሳቸው ገብረ ሕይወት ሲጽፉ፡-

ይድረስ
ካቶ ጳውሎስ *መናመኖ*

ወዳጄ ሆይ፣

እነሆ፣ ከእግዚአብሔር በታች ባንተ ደግነት ከሞት ዳንሁኝ። በብርቱ ታምሜ ተስፋ ቆርጬ በምጥዋ በአስፔዳሌ ወድቄ ሳለሁ በገንዘብህ አገዝኸኝ፣ ለቸሩ ደጃዝማች ገብረሥላሴ በመንገርህም የበለጠ የደግነት ሥራ አደረግህልኝ። እነሆም፣ ላገራችን ጥቅም ይሆናል ስል ይህንን ትንሽ ቃል ለመጻፍ በቃሁ። የተመሰገነልኝም እንደ ሆነ ምስጋናው ላንተ ነው፤ ለእኔ ዕድሜ እንደ ሰጠህልኝ አምላክ ረጅም ዕድሜ ይስጥህ። /ገጽ 2/

ደግነትህን እስከ ሞት ድረስ ለማይረሳ
ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ

ጳውሎስ *መናመኖ* የገብረሕይወት ጤና እንዲሻል ምክንያት በመሆን በፈረንሳይኛና በአማርኛ እንዲዘጋጅ ምክንያት ለሆነው ለዚህ መጽሐፍ በማብቃታቸው በእርግጥም የሚመሰገኑ ናቸው። ይበልጥ ግን አምላክ ረጅም ዕድሜ ይስጥህ የሚለው ጸሎት ተሰሚ ሆኖ ከገብረ ሕይወት ሞት በኋላ በእጃቸው ተጽፎ ግን ለጎትመት ስላላበቁት «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» መጽሐፉ እንዲታተም ወደ ልዑሉ የቀረቡ እርሳቸው ለመሆናቸው በመጽሐፉ

መግቢያ ላይ ጳውሎስ መናመኖ እንዲህ ይላሉ፡-

ይድረስ፣

ለልዑል ጌታዬ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን፣ መድኃኔ ዓለም ጤና ይስጥልኝ ብዬ እጅ እነሣለሁ. . . ነጋድራስ ገብረ ሕይወት በትምህርቱና በዕውቀቱ በጣም የተመሰገነ ነበረ፤ በታዘዘውም ሥራ ላይ በጣም ትጉሕ እንደ ነበረ ጌታዬ ልዑልነታቸውም ያውቁታል፤ ነገር ግን በሰው ላይ ሞትን የሚያህል ዕዳ አለና. . . ነጋድራስ ገብረ ሕይወት በ31 ዓመቱ ሞተ።

ልዑል ሆይ፣

የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ስሙ እንዳይጠፋ ማሰብዎንማ በገንዘብዎ ልጁን ከትምህርት ቤት አግብተው በማስተማርዎ ተረድተነዋል። ደግሞም ልጁን ቢያስተምሩለት ጥቅሙ ለልጁ ብቻ ነው። ይህን መጽሐፉን ቢያሳትሙለት ግን አስቀድሞ ለስሙ መታሰቢያ ይሆናል፣ ቀጥሎም ለመንግሥትዎና ለሕዝብዎ ሁሉ ትልቅ ጥቅም የሚያስገኝ ነውና ለማሳተሙ ፈቃድዎ እንዲሆን አጥብቄ እለምንዎታለሁ።

መስከረም 8 ቀን 1914 ዓ.ም

ፈቃደኛዎና ታዛዥዎ ጳውሎስ መናመኖ. . . /ገጽ 9-10/

/ከመንግሥትና ከሕዝብ አስተዳደር፣ ታተመ በ1916 ዓ.ም. በንግድ ማተሚያ ቤት/

እኒህ ሰው ለአልጋ ወራሹ ባቀረቡት ልመና መሠረት ልዑሉ ከሁለት ዓመት በኋላ መጽሐፉ ታትሞ እንዲወጣ አደረጉ። የገብረ ሕይወት ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወትም «የንግሥት አዜብ ታሪካዊ ጉዞ» በማለት በቲያትር መልክ ባቀረቡት የ1951 ዓ.ም መጽሐፋቸው ብዙዎች እንደሚስማሙበት «ዓሣ አጥማጅ» በማለት ተሳታፊ ያደረጉት ገጸ ባሕርይ «የአባታቸውን የሕይወት ሂደትና አመለካከት» እንደሚገልጽ ይገመታል። ከመጽሐፉ ጠቃሚ የሆኑት ሁለቱ እንዲህ ይነበባሉ፡-

አምላኬ ሆይ! ሦስት ጊዜ መረቤን ወደ ባሕር ጣልሁ።

እንደምታውቀው፣ በመጀመሪያ ጊዜ የሞተ አህያ ግንባር አጠ መድሁ፤ በሁለተኛ ጊዜ አመድና ግብስባሶ የሞላበት ማሰሮ በመረቤ ተይዞ ከባሕር ወጣ፤ በሦስተኛው ጊዜ፣ ስብርባሪ ገልና የሐረግ ብጥስጣሽ ነው የተጎተተልኝ። እማጸንሃለሁ። ሕያው አምላክ ልመናዬን ስማኝ። አምላክ አማልክት ለለመኑህ መታደግ የአምላክነትህ ግብር ነው። (ገጽ 7)

ዓሣ አጥማጁ ገብረ ሕይወት በዚህ የልጃቸው ገለጻ ላይ በዘመናቸው ስኬትን ሳይሆን፣ ውጤት-አልባነትን በየሙከራዎቻቸው ሁሉ ላይ መታየቱ፤ የወቅቱ አስተዳዳሪዎችና የቅርባቸው ሰዎች «እንደ ጉድ» እንደ ቆጠሯቸው ያመለክታል፦ እንደ ፍቅር እስከ መቃብሩ «ጉዱ ካሣ»።

በሌላው ገጽ ዓሣ አጥማጁ ለንጉሥ ሰለሞን፣ ለልዑላኑ እና ለባሕር ሰገድም ይህን ይላቸዋል፦

«በግርግር አልበላ፣ በሽክምም አልብስ፣ በገንቦ አልጠጣ፣ ከአንዲት ክፍል መኖሪያ ቤት አላልፍ፣ ከአንድ ሰው መኝታ አልጋ አልተርፍ፣ ፍጡር የሚመኘውን ሁሉ ብጠይቅ እኔ የምገለገልበት በመጠኑ ነው . . . በችሎታዬና በተፈጥሮዬ መጠን አስፈላጊውን ሁሉ ሰጥተኸኛል። ከአስፈላጊው በላይ መጠየቅ ኃጢአት ነው፤ ትርፍ ኃብት አይጠቅመኝም፤ ባለ ትርፍ ኃብት መሆን ትርፉ ኃብቱን መጠበቅ ነው። (ገጽ 55)

በማለቱ ባላምባራስ አሸብር የአባታቸውን የሕይወት ዓላማ በአግባቡ እንደ ገለጹ ይገመታል። እንግዲህ ከተለያየ አቅጣጫ የወጣቱ ገብረ ሕይወትን ዕድሜ፣ አስተዳደግ፤ አስተሳሰብና ዕውቅና መጠቋቆም ከተቻለ፣ አስቀድሜ እየነቀስኩ ጥቂት ጥቂት ልበል ወደ አልኳቸው፣ የታሪክ፣ የክርስትና ዕድገት እና የአገር አስተዋጽኦቻቸው ዘወር ልበል፦

ታሪክ-ነክ

ገብረ ሕይወት፣ ታሪክን ማን ያጥናው? ማንስ ይጻፈው? እንዴትስ ይተግበር? በተሰኙት ዋንኛ ጉዳዮች ላይ በ1904 ዓ.ም

መጽሐፋቸው እንዲህ ይላሉ፦

> ታሪክን መማር ለሁሉ ሰው ይበጃል፤ ለቤተ መንግሥት መኮንን ግን የግድ ያስፈልገዋል፤... ስሕተትንና በጎነትን አይቶ ለመግሥቱና ላገሩ የሚበጀውን ያውቅ ዘንድ ማወቅ አለበት... ይህ የታሪክ ትምህርት ግን የሚጠቅመው እውነተኛ የታሪክ ትምህርት ሲሆን ነው። እውነተኛውንም ታሪክ ለመጻፍ ቀላል ነገር አይደለም። የሚከተሉት ሦስት የእግዚአብሔር ስጦታዎች ያስፈልጋሉ። መጀመሪያ፣ ተመልካች ልቦና የተደረገውን ለማስተዋል፤ ሁለተኛ፣ የማያደላ አእምሮ በተደረገው ለመፍረድ፤ ሦስተኛ፣ የጠራ የቋንቋ አገባብ የተመለከቱትንና የፈረዱትን ለማስታወቅ ይረዳል... ያገራችን የታሪክ ጸሐፊዎች ግን በነዚህ ነገሮች ላይ ኃጢአት ይሠራሉ፤ በትልቁ ነገር ፈንታ ትንሹን ይመለከታሉ፤ ለእውነት መፍረድንም ትተው በአድልዎ ልባቸውን ያጠብባሉ፤ አጻጻፋቸውም ድብልቅልቅ እየሆነ ለአንባቢው አይገባም... (አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ፣ ገጽ 3)

የገብረ ሕይወት የታሪክ መልእክት የዛሬ 90 ዓመት ላይ እንደ ሳቸው ቆመን ዘንድሮም (ይህ ጽሑፍ በተዘጋጀበት ጊዜ) በሺህ 998 ላይም ሆነን የምንረዳው የታሪክ እይታ ተቀራራቢ ወይም እውነት ሆኖ መገኘቱ ነው። ይልቁንም፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ምን ያህል የተዛባ እንደ ሆነ መረዳት አያዳግትም። ትልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ተዘንግቶ ወይ ተሸሮ ገድላ ገድሎች፣ መልካ መልኮች እና ድርሳናት ሰፊውን ስፍራ ይዘው ሕዝቡን ሲመሩ ሲታይ፤ በወንጌላውያኑም ዘንድ ሚሲዮናዊ ላምቤ የቃለ ሕይወት ሰው ነው? ወይስ የመካነ ኢየሱስ? ምላሽን ለመስጠት ሁለቱም ቤተ እምነቶች የየራሳቸውን በማለታቸው ታሪክ እየተዛነፈ መሆኑን መረዳት የግድና የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ገብረ ሕይወት ትክክለኛ መረጃን ባለማሳወቅ ሊመጣ የቻለውን ጦስ እንዲህ ያመለክታሉ፦

«አንድ ልበ ብሩህ ያበሻ ሰው መሬት ትዞራለች? ብሎ ቢያስተምር አሁን በቅርቡ በሐረርጌ በዳኛ ተይዞ አልነበረምን? አሁንስ በ1900 ዓ.ም አንድ ሰው የተዋህዶን ሃይማኖት ቢነቅፍ አዲስ አበባ ገበያ ላይ በደንጊያ አልተቀጠቀጠምን» (አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ፣ ገጽ 12፣) በማለት ታሪክን አጥበው በወገናዊነት ሊተረጉሙ የወደዱ ያስከተሉትን ያለማወቅ ጥፋት በመግለጽ ከጠዋቱ «ጆሮ ያለው ይስማኝን» ያሳስቡበታል።

እምነት-ነክ

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ እምነትን በተመለከተ ጎብረተሰቡ እርስ በርስ ሊተያይ የሚችልበትን መሠረታዊ ቁም ነገሮችን አስተላልፈዋል። ይህንንም የአጤ ምኒሊክ የግዛት ዘመነ መንግሥት ሊፈጽመው ካልቻለ፣ የአልጋ ወራሻቸው ልጅ ኢያሱ እንዲፈጽሙት በማሳሰብ አሥር ጽኑ መልእክቶችን ጽፈዋል። በዚህ ዝግጅት ሁሉንም ማንሣት ተገቢ ስላልሆነ፣ የመጨረሻውን ብቻ አመለክታለሁ፤ እንዲህ ይላል፦

> መንግሥታችንም እንድትቀና የሚከተሉት አሥር ነገሮች በቶሎ ቢፈጸሙ ማለፊያ ነበር... አሥረኛ፣ የሃይማኖት አርነት ይታወጅ። የሃይማኖት አርነት ጥቅም መሆኑን የማያውቅ ብዙ ሰው ይኖራል። ስለዚህ የሚከተለውን ብናስተውል ደግ ነው። ያገራችን ሰው የተዋሕዶ ሃይማኖት ከሁሉ ሃይማኖት ይበልጣል ብሎ ያምናል፤ በልጦ ግን ምን ረባን? ማን አወቀው? ሃይማኖታቸውን ለሕዝቡ ሊገልጹለት አሳብ የላቸውም። ስለዚህ ሕዝቡ እንኳን ተዋህዶ ማለት ምንድር እንደ ሆነ ሊለይ ቀርቶ የክርስቲያን ሃይማኖት አውራ መሠረት የሆነውን የወንጌልን ቃል አያውቅም። ስለዚህ አጉል ቀረ፤ የሃይማኖት አርነት እስኪታወጅ ድረስም አጓጉል ይቀራል» ይላሉ (አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ፣ ገጽ 23)።

ይህ ገለጻ የክርስትና እምነት በማወቅ፣ በመረዳት እና በማመን በሰው ሕይወት ውስጥ በፈቃደኝነት ሊፈጸም የሚገባው እንጂ፣

በተቃራኒው «እንዲህ ነኝ» ብቻ በማለት ሲጠየቁበት ምንም ምላሽ ሊሰጡለት የማይችሉ ሆኖ መገኘት እንዳይደለ ያስረዳል። ይህ መሆኑ ግን እንደ ገብረ ሕይወት የሃይማኖት አርነት ያለመታወጅ ውጤት ነው። ጸሐፊው ማብራሪያቸውን ሲያክሉ፦

> «...ለዚህም ነገር ምስክር በሀማሴን እናገኛለን። በዱሮ ዘመን በዚያች አገር ብዙ ቄሶች ሃይማኖታቸውን ሳያውቁ ይኖሩ ነበሩ። ፕሮቴስታንቶችና ካቶሊኮች ከመጡ ወዲህ ግን ትልቁም ትንሹም የወንጌልን ቃል አውቆ በትርጉሙ ይከራከራል፤ ካህናቱም በል አምጣ! ቢበዛባቸው ያስተምሩ ጀመሩ። በዚህ ምክንያት የሃይማኖት አርነት ቢታወጅ ሃይማኖት ይታወቃል እንጂ አይጠፋም።» (አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ፣ ገጽ 24)

ገብረ ሕይወት «ከመጠምጠም መማር ይቅደምን» በሥራ ላይ ለማዋል፣ ቀሳውስቱ በተግባራዊ ፈተና ውስጥ ሊያልፉ ይገባቸዋል ይላሉ። ይህም ግልጽ ሆኖ ሊወጣ የሚችለው፣ የመጠየቅና የመማር ነጻነት በአግባቡ ሥራ ላይ ሲውል ይሆናል።

ለክርስትና እምነት አስተማሪ የሆኑት የሀማሴን ቄሶች አለማወቃቸውን ተረድተው በወንጌል ራብተኛ የሆነውን ሕዝብ ሊደርሱት የቻሉት በአገሪቱ የክርስትና እምነት ውስጥ የሚገኙት የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ቤተ እምነቶች በመካከላችው ተገኝተው እውቀታቸውን ገለጹ፣ የእነርሱ አስተምህሮ ሕዝቡ ቀድሞ ካመነው ጋር እየተጋጨ አስቸገረ። ለዚህ መፍትሔን የፈለገው ወደ እምነት አባቶች በመሄድ ጠየቀ። ይህ ያመጣው ውጤት የቄሶች አለማወቅ ወደ ዕውቀት እንዲሻገር በሩን ከፈተ። ሁሉም ለወንጌል ትምህርት ራሱን አዘጋጀ፣ ለመወያየት፣ ለመግባባት፣ ለመተዋወቅም ሁነኛው መንገድ «እያንዳንዱ በእግዚአብሔር ፊት ለሠራው ሥራ ምላሽ እንደሚሰጥ በመገንዘብ» አገራዊ ወይም ባንዲራዊ ከማድረግ ግላዊ በማድረግ መቆም እውነት መሆኑን ተረዳ። ይህም የሃይማኖት አርነት ሆነ፤ ውጤቱም መጠፋፋት ሳይሆን፣ መማማር በመሆን

ሃይማኖት ጸና እንጂ አልጠፋም።

ገብረሕይወት እምነትን በሚመለከት ስላለው ድንቁርናም ሲጽፉ፡-

«...ደግሞም በአገራችን አንድ ድንቁርና ነገር አለ። ሃይማኖቱ ተዋህዶ ያልሆነ ሰው ሁሉ እንደ ርኩስ ይቆጠራል። ይህም እጅግ ያስቃል፣ አእምሮ የሌለው ሕዝብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሳያውቅ የእግዚአብሔር ጠበቃ ሊሆን ይወዳል። ሃይማኖት የልብ ነገር ነው፣ ስለዚህ ሰማያዊው ንጉሥ እንጂ የዚህ ዓለም ንጉሥ አይቆጣጠረውም። ወንጌል፣ የቄሳርን ለቄሳር ስጡ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ያለውም በዚሁ ቢተረጎም ለመንግሥታችን ሳይበጅ አይቀርም» (አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ፣ ገጽ 24)።

ነጋድራስ «ድንቁርና» ያሉት የሃይማኖት አመለካከት ዛሬም በእውነትነቱ ጥላውን እንደ ጣለ ማረጋገጥ ይቻላል። ብዙዎች መንግሥትንና ቤተ ክርስቲያንን በማጋባት የቤተ ክርስቲያንን ፈቃድ መንግሥት እንዲያስፈጽም በማድረግ በኢትዮጵያ ብዙ ትውልድና ብዙ መንግሥት ተቀያይሯል። ዛሬም ከተዋህዶ እምነት ውጭ የሆነ ዜጋ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ክርስቲያናዊ እምነቱን ባስተማረ፣ ባመነና በተገበረ ቁጥር ገብረሕይወት እንዳሉት እንደ «ርኩስ» ተቆጥሮ ከጎብረተሰቡ እንዲገለል ይሞከራል፤ ከዕድር እንዲወጣ ይታደማል፤ ቀብሩ እንዳይፈጸም ይሜራል፤ ይህ ግን የእግዚአብሔርን ለቄሣር፣ የቄሣርንም ለእግዚአብሔር እንደ መስጠት ነው። ሃይማኖት አገር ሁሉ በመመሪያ የሚቀበለው ሕይወት ሳይሆን፣ ገብረ ሕይወት እንዳሉት «የልብ ነገር ነው»፣ ግላዊም ነው። ይልቁኑ፣ ለክርስትና መስፋፋት ሁነኛ መፍትሔው ሰዎች ሁሉ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመልሰው እንዲያነቡ እንዲረዱ ያለ ተጽዕኖ የወንጌልን ምሥጢር በመረዳት ክርስቶስ እንዲያገኟቸው መርዳት ነው።

አገር-ነክ

ገብረ ሕይወት አገር አፍቃሪ ብቻ ሳይሆኑ፣ የአገር ዕድገት መሠረት ምን ሊሆን እንደሚገባው የመንግሥትም መኖር ድርሻው በሥራው እንዲገለጥ በተለይ «በመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» መጽሐፋቸው አሳውቀዋል። ለዚህም የጀርመኑ ሊቅ አስቴር ሰሞሎ በልጅነት ዕድሜያቸው ያሳደረውን ትምህርት እንዲህ በማለት ይጽፋሉ፦

> «...እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ሰው ሁሉ አጥቅቶ ለብቻው እንዲኖር ይወዳል። መንግሥት ግን በግዛቱ ውስጥ የሚኖሩትን ኃይለኞች ሁሉ እርስ በርሳቸው እንዲተናፈፉ የግድ ይላቸዋል። መንግሥት ጥረቱ ሕዝቡን ሁሉ አስማምቶ በመካከላቸው ሰላም ለማድረግ ነው...»፣ (መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር፣ ገጽ 13)

በዚህም እምነታቸው መሠረት የመንግሥት መኖር ለአንድ አገር አስፈላጊ ነው። ተግባሩም ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 13፡1-4 ካለው መርኅ ጋር የሚሄድ ነው፤ ከዚህም የተነሣ እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ መንግሥትም ሕዝቡን በሐቅ እንዲያገለግል ጽሑፋቸው ያመለክታል።

ስለ አገር ብልጽግና መሠረቱ ታታሪነት መሆኑን ሲያብራሩ፣ የገብረ ጉንዳንንና የንብን ጎብረት በማንሣት ነው፤

> «ዕውቀት የሌለው ሰው የዝሆንን ቁመትና መብረቅ ሲያይ የትልቅም ነጎድጓድ ጩኸት ሲሰማ የፈጣሪውን ሥራ ያደንቀዋል። አስተዋይ የሆነ ሃይማኖተኛው ግን የንብንና የጉንዳንን ትጋት፣ የሥራቸውንም ትክክልነት፣ የሥርዓታቸውን ማማር አይቶ በዚህ ዓለም ፍጥረት ይገረማል፤ ከመብረቅና ከነጎድጓድ ኃይልም ይልቅ የንብንና የጉንዳንን ተአምር ለፈጠረው የበለጠ ምስጋና ሆኖ ይታየዋል። እነዚህንም ሰለሞን በመጽሐፈ ምሳሌ 6:6፤ 30:25 አብራርቶታል... የአንድ አገር ሕዝብም ይበለጽግ

ዘንድ እንዲህ ይሆን ዘንድ ይገባል። (መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር፣ ገጽ 147-8)

በማለት የሰው ታታሪነቱ ከሚገለጽበት አንዱ ዋንኛው መሬት» መሆኗን ያስረዳሉ፦

መሬት ማናቸውንም ነገር ብትሰጥ በብድር ነው፤ ብድሩን ካልመለሱላት እንደ ባንኮች ሁሉ ታስቸግራለች። በአይሁድና በክርስትና የሃይማኖት መጽሐፍ እንደምናየው... «ጥረህ ግረህ በግንባርህ ወዝ ብላ»ም ሆነ፣ «መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ» የተባለለት ሰው መሬትን ይንከባከባት ዘንድ ይገባል። (መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር፣ ገጽ 69)

ገብረ ሕይወት የመሬትን አበዳሪነት ከባንክ ጋር ማነጻጸራቸው፣ ሕዝብ እንጀራውን በመሬት ላይ በሠራው መጠን እንደሚያገኝ ሁሉ፣ ኑሮውን ላደረጀች መሬት ደግሞ ያላትን ንጥረ ነገር በመጠ በቅ፣ በመተካት፣ በመንከባከብ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ መገባቱን ያስረዳሉ።

ነጋድራስ ስለ አንድ አገር ኢኮኖሚ ማደግ መሠረት ጣይ ነው ብለው ስለሚያምኑበት የባንክ አገልግሎት ሲጽፉም፣ ዓይነተ ብዙ ባንኮች መኖራቸው ተገቢ ነው ይላሉ፣ ይህም በገዛ ዘመናቸው ሳይሆን በመቅረቱ አጤ ምኒልክ ቢያርሙት በማለት ተከታዩን አስተያየት ጽፈዋል፦

ዛሬ በኢትዮጵያ የቆመው «ባንክ አፍ አቢሲኒያ» ከቆመበት ቀን ጀምሮ እስከ አምሳ ዓመት ድረስ በኢትዮጵያ ሌላ ባንክ እንዳይቆም ውል ተቀብሏል። ከዚህ ቀደም እንደ ተረዳነው ግን ማናቸውም ነገር በጥቂቶች ሰዎች እጅ ገብቶ ሞኖፖል ሲሆን ለሕዝቡም ለመንግሥቱም ጉዳት ነው። ለአፄ ምኒልክ አንድ ሰው መጥቶ በአገርዎ ከእኔ በቀር ሌላ ሰው እንዳያርስ... ወይም እኔን ሳይጠይቅ በየቤቱ ማንም ወጥ እየሠራ እንዳይበላ ፈቃድ ይስጡኝ ብሎ ለምኗቸው

ቢሆን፣ የሚናገራቸው ቃል ምንም ቢያምር፣ የሚሰጣቸው ተስፋ ምንም ትልቅ ቢሆን፣ ያለጥርጥር ይቆጡት ነበር» (መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር፣ ገጽ 140)::

ይህን ሲሉ አጤ ምኒልክ የዕውቀት ባሕሪ በሌላቸው ሰዎች ቃል ተታለው ይህን እንደ ፈጸሙ በመናገር ሲሆን፣ ለአንድ አገር ዕድገት የተለያዩ ባንኮች ተወዳዳሪዎች ሆነው ሕዝቡን ቢያገለግሉ የተሻለ ውጤት ሊኖር እንደሚችል ያኔ አሳስበዋል::

እንግዲህ በመግቢያዬ ያነሣሁትን መንደርደሪያዬን መልሼ ላንሣና መልእክቴን ልጠቅልል፤ በበኩሌ ድሮን አፍቃሪ አይደለሁም:: ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «የኋላዬን እየረሳሁ የፊቴን ለመያዝ እዘረጋለሁ» በማለቱ ምርጡ ሁሉ ድሮ ነበር ብዬ በትዝታ አልቆምም:: ይህ ዛሬን እንዳላይ፣ ለነገም የተሻለ ሥራ መሥራት እንዳለብኝ ሳያሳየኝ ያዘናጋኛል:: ዘንድሮንም አንኳሳሽ አለመሆኔ እንደ ቶማስና እንደ ኪዳነ ማርያም ገለጻ ሳይሆን፣ የምኖርበት ዘንድሮ ልሠራበት የሚያስችል ድንቅ ሀብቶች አሉት፣ ውጤታማ የሆኑ ሌሎች ገብረ ሕይወቶች ዛሬም እንዳሉ በማወቄ ትውልዴን አልረግምም::

ይልቅስ፣ እግዚአብሔር የሰጠኝ የምድር ላይ የዕድሜዬ ተመኑ አይታወቅም:: እንደ ገብረ ሕይወት አጭር የመሰለ ዕድሜ ግን ብዙ የተሠራበት፣ በውጤቱም 1998 ዓ.ም ላይ ቆሜ ልሠራው የቻልኩለት ሥራ መኖሩን ከተረዳሁ፣ ሁላችን በሚያልፍ ዘመናችን የማያልፍን ሥራ ሠርተን እንድናልፍ ያሳስበኛል፤ ያሳስቡናል::

ይልቁኑ፣ በክርስቶስ ለሆንን ደግሞ እንደ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት የጥሩ ዜጋን ኃላፊነት ለአገር ከመወጣት ባሻገር የሚበልጥ ሥራ አለብን፣ እርሱም በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለየውንና በእግዚአብሔር ጉዳይ ምንም ተስፋ የሌለውን የሰው ልጅ በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ እያለፈ ባለው ዘመን ሊሠራ ያለው የማያልፍ ሥራ ነው::

መረጃዎች

1. **አሲዳም ዘመን፣** በቶማስ አርጋው::
2. **ጥንታዊው የቆሌ ተማሪ፣** በኪዳነ ማርያም ጌታሁን /አባ/ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1954 ዓ.ም::
3. **የታሪክ ስላቅ፣** በዘውዱ አምበሉ /አዲስ አድማስ/::
4. **የንግሥት አዜብ ታሪካዊ ጉዞ፣** በአሸብር ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ 1904 ዓ.ም.::
5. **አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ፣** ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ 1904 ዓ.ም::
6. **መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር፣** በገብረ ሕይወት ባይከዳኝ /ነጋድራስ/፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1916 ዓ.ም::
7. **የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ፣** በአየለ ዘውገ /መስከረም መጽሔት/::

«ውርጃስ ይቅር»

«ሌላ የተሻለ አማራጭ ስለሌለኝ ፅንሱን ለማቋረጥ ወሰንኩኝ::»

ኤልሳቤጥ ጀንዊይ

«ማርገዜን እንዳወቅሁ ከማስወረድ በቀር የተለየ አሳብ ወደ ጎሊናዬም አልመጣም፤ ለዚህም ሁነኛው ምክንያት ትምህርቴን ገና አልጨረስኩም ነበር::» ሮማ ሳየር

«እኔና ባለቤቴ ሌትና ቀን ሠርተንም ቋታችን አልሞላም፤ በዚህ ላይ ሚስቴ አረገዘች፤ ከዚህ የበለጠ የከፋ ሁኔታ ምን ሊገጥመን ይችላል? ፅንሱ መውረድ አለበት ብለን ወሰንን::» ኬይ በይል

* * *

የአንዱ ሲያልቅ ሌላው እየተተካ ይህንን የመሳሰሉ የሕይወት ገጠመኞች የያዘ «ትልቅ መጽሐፍ» ተገኘ:: የመጽሐፉ ርእስ *"The*

Choices We Made" ወይም «የታመንበት ምርጫ» ተብሎ ተጠ ርቷል። መልእክቱ እርስ በርሱ ሲተሣሠር «ፅንስን ማቋረጥ /ማስወረድ/ ምርጫም ብቻ ሳይሆን፣ ለኑሮ ስኬት ሊሆን የተገባው ቅመም ነው» የሚል ነው።

* * *

ዊፒ ጎልድበርግ መፀነሷን እንዳወቀች ከማንም ጋር ሳትማከር ፅንሷን አቋረጠች። ይህችው ልጅ ከዘጠኝ ወር በኋላ እንደገና አረገዘች፤ በዚህ ወቅት የብቻ ውሳኔዋን ትታ የሆነውን ለእናቷ በማጫወት ምን ማድረግ እንዳለባት ጠየቀች። የእናትየዋ ምላሽ፣ «ጎልድበርግ ገና ልጅ ነሽ፤ ከፊትሽ ብሩህ ተስፋ አለ፤ ያንን ደግሞ ያለምንም ጫና ስትፈጽሚው ማየትን እፈልጋለሁ፤ ከዚህም የተነሣ ቀሪ መፍትሔው ውርጃ ነው» አለች፤ ልጅቱም ታዘዘች።

* * *

በአሜሪካ የቴሌቪዥን ሰሌዳ ላይ ሁሌ የምትታየው ባርባራ፣ «አፈናጥሮ መጣል ሳለ ጭንቀትን ለገጠመኝ ፅንስ አልጋብዝለትም፤ ይህን ባላደርግና ባዘገየው ለሕዝብ ደስታ መሆን አልችልም፤ በተክለ ሰውነቴም ላይ የቅርጽ ለውጥን ያመጣብኛል» ማለቷን የዘገበላት መጽሐፍ ድርጊቱን በፈጸመች በሁለተኛው ዓመት የገጠ ማትን ሌላ እርግዝና ለማስወረድ ምክንያቱን የምታደርገው ባለቤቷን ነው። «ባሌ ሌላ ልጅ አይፈልግም፣ እርሱን ደስ እንዲለው ፅንሱን አቋረጥኩት» ማለቷም ተከትቧል።

* * *

ተዋናይ ፖሊ በርገን ለዶክተሯ ያለችው አጭር መልእክት፣ «ፅንሱ የሕይወቴን አቅጣጫ ያጠፋዋልና አስወግድልኝ። በዚህ ልታግዘኝ ካልቻልክ የራሴን ርምጃ እወስዳለሁ» ነበር። መቼም እነዚህን የመሰሉትን ታሪኮች እያነበበ ዳር የደረሰ አንባቢ፣ «እርግጥም ፅንስን ከማቋረጥ /ከማስወረድ/ በቀር ሌላ አማራጭ የለም» ወደሚል ብቸኛ መፍትሔ መድረሱ አይቀሬ ይሆናል።

* * *

የሴቶችን መብት ለማስከበር ተፈጥሬያለሁ የምትለዋ ክርስቲን ግርሚባል ደግሞ፣ «ካንደበቴ የማልለየው ቃሌ 'ፅንስን ማቋረጥ የማንም መብት ሳይሆን፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነችው የሴቷ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ስናገር ውርጃ ሕይወትን መታደጊያ እንጂ ማጥፊያ አለመሆኑን አምኛለሁ፣ ለምንፈጽመውም ድርጊት ከማንም ጋር ለድርድር አንቀርብም፣ እናም ይህንኑ አናገራለሁ፤ እጽፋለሁም፡፡» ስትል፤ ግሬስ ፖሊ ደግሞ፣ «እኔ የተገኘሁበት ይህ ትውልድ ወሲባዊ ግንኙነት የነጻነት ሕይወት መገለጫ መሆኑን ማወቅ አለበት፡፡ ልጆችም በዚህ ልምምድ ውስጥ ገብተው እርግዝና ሊከሠት ቢችል፣ ተፈላጊው ጉዳይ «ይወገድልኛል» ወደሚለው ፈጣን እርምጃ መምጣት ብቻ ነው፣» በማለት የወሲብ ነጻነትንና ፅንስን የማቋረጥ /ውርጃ/ የተፈላጊነት ብስራተ መርዶን አስደምጣለች፡፡

* * *

አኒ አንከር «የሚያማልለው እውነቴ» ባለችው ሥራዋ ላይ «ተፈጥሮአችንን ዓለም በሙሉ ሊረዳልን ይገባል፡፡ ቄሶቹ ሆኑ ሼኮቹ ራሷን ትግዛ እያሉ የሚያላዝኑለት ሰበካ ተዓማኒነት የለውም፡፡ ሴት ልጅ ወዳ ሳይሆን እድሜዋ ነው ፍላጎትን በውስጧ ዘርቶ ወደ ወሲብ እንድትደርስ የሚያደርጋት፡፡ እርሷ ይህን ባታደርግ ሕይወቷ በመረበሽ እና «ለጎበረተሰቡ የማትጠቅም ዕቃ» በሚል መንፈስ ይጠቃል፡፡ ታዲያ ተዳፍኖ እየተቀጣጠለ ያለን ስሜት እስከ ጋብቻሽ ቀን አቀዝቅዝሮው ተብላ ብትመከር ያስኬዳልን?» በማለት ጊዜያዊ የሆነ ብሕትውና አያዋጣም በማለት ነጻነትን ማወጅ ይሻላል ትላለች፡፡

* * *

እርግጥ ነው፣ አኒ እና መሰሎቿ ለባርነት ከሚዳርግ ፅንስ ተላቅቆ ነጻነትን በራስ መወሰን አማራጭ-የለሽ መሆኑን ሊገልጹት በወደዱት መንገድ ሁሉ አብራርተውታል፡፡ ከዚሁ ሁሉ የነጠረ ከመሰለ አሳብና ጥናት ባሻገር ግን የእግዚአብሔር ቃል አለ፡፡

እርሱም ደግሞ፣ «ለሰው ቀና የምትመስል መንገድ አለች ፍፃሜዋ ግን ሞት ነው» (መጽሐፈ ምሳሌ) በማለት ሁሉም ቆም ብለው የጠቢቡን ምክር እንዲያስቡት ይጋብዛል። ያሉት ሁሉ እንዳሉት ብቸኛው መፍትሔ ፅንስን ማቋረጥ (ውርጃ) ሳይሆን፣ የተሻለን ነገር ይነግረናልና፣ እርሱን በጥቂት በጥቂቱ እናጢነው። ለዚህም ደግሞ መንደርደሪያዬ ተከታዮቹ ጥቅሶች ናቸው፦

> «. . . ለኃጢአት ብትታዘዙ ሞትን ለሚያመጣባችሁ ኃጢአት አገልጋዮች ትሆናላችሁ፤ ለእግዚአብሔር ብትታዘዙ ግን ጽድቅ ታገኛላችሁ።» (ሮሜ 6፡16)
>
> «እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፤ ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው. . . ወልድ ነጻ ካወጣችሁ በእርግጥ ነጻ ትሆናላችሁ. . . » (ዮሐ. 8፡34 እና 36) ይሉናል።

* * *

ሰውን ባሪያ አድርጎ ሊገዛው የሚችለው ኃጢአት ነው። ይህ «ባሪያ» ሰው ስለ ብዙ ነጻነቶች ጮክ ብሎ ሊያወራና ሊጽፍ ችሏል። ግን ባሪያ ከሆነለት ኃጢአት ነጻ ስላልወጣ፣ የነጻነት የመብት ክርክሩ ሚዛን ደፊ አይሆንለትም። ይልቅ፣ የነጻነት ዲስኩሩን በነጻነት መናገር የሚችለው ሙሉ ነጻነትን ሲያገኝ ብቻ ነው፤ ይህም አዲስ ሕይወትን ከክርስቶስ በማግኘት ይገለጣል። ቃለ እግዚአብሔሩ የሚለው ይህን ነው።

* * *

ምንጊዜም ሰዎች ባርነታቸው ለሰይጣንና ለኃጢአት ከሆነ፣ የእነርሱኑ ፈቃድ በመፈጸም ሕይወታቸውን ይመራሉ። በትይዩው፣ ተገዥነታቸው ለእግዚአብሔርና ለቅድስና ከሆነ፣ የእግዚአብሔር የሆነውን አሳብ በመፈጸም ይተጋሉ።

መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ማመንና መገዛት ባለበት ኑሮ ውስጥ የሰው ሕይወት ክቡር ነው። ሰውን እግዚአብሔር በራሱ አምሳል ነው የፈጠረው (ዘፍጥ. 1፡27)። ይህን የፈጠረውንም ሰው ሕይወት ማንም እንዳይቀጥፈው አትግደል (ዘፀአ. 20፡13) በማለት

መለኮታዊ መመሪያን ሰጠበት። አንዳንድ ሰዎች ግን አፈንግጠው በእግዚአበሔር ቃል ፅንስን ማቋረጥ ኃጢአት ነው ብሎ የተናገረበት ምንም ስፍራ ስለሌለ፣ ተቃዋሚዎች «ዝም ይበሉን» ይላሉ። «አትግደል» ግን ያላስተዋሉት አሻሚ ያልሆነ ዋንኛ መመሪያ ነው።

እግዚአብሔር በሚገዛቸው ሰዎች ዘንድ ወሲባዊ ጉዳይም የተቀደሰ ነው፤ የዕብራውያኑ ጸሐፊ፣ «ጋብቻ በሁሉ ዘንድ የተከበረ ይሁን፣ ባልና ሚስት ታማኝነትን በማጉደል ጋብቻን አያርክሱ፣ ምክንያቱም ሴሰኞችንና አመንዝሮችን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» (ዕብ. 13፡4) ይላል። ፅንስን የማቋረጥ መሠረታዊ መነሻ ሊከሠት የሚችለው አንድም ባለመተማመን የመጣን ጣጣ ለመቅረፍ፣ አለያም በራስ ላይ ብቻ በመደገፍ፣ ወይም በሌላ ሁኔኛ ምክንያት የተነሣ ከተደነገገለት የተቀደሰ ዖታዊ ግንኙነት በመውጣት በሚመጣ ጣጣ ነው። ዳሩ ግን፣ ሊታወቅ የሚገባው ዋና ጉዳይ የዖታዊ ግንኙነት ውጤቱ በቅድስናና በጥንቃቄቄ የሚስተናገድ መሆኑን መረዳት ነው።

መቼም ኃጢአት ባሪያ አድርጎ የገዛቸው ሰዎች ዘላቂ የሕይወት ዕቅዳቸው ያለ መደናቀፍ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ። ከዚህም የተነሣ የኑሮ እንቅፋት የተሰኘው ፅንስ ሲከሠት ከኑሮ መደላደል የሚበልጥ ስለሌለ፣ ፅንሱን ለማስወገድ አያመነቱም፤ ተገዝተውለታልና ያከብሩታል። አኒ አንሰር በዲስኩሯ ሁሌ የምታነሣው፣ «ወሲብ ከጋብቻ በኋላ በማለት የሚያስተምሩ ሁሉ የአስተሳሰብ ቀርፋፎች ናቸው። ወሲብ በአሰኘ ጊዜ፣ በተፈለገው ቦታ፣ ከሚመቸው ሰው ጋር መፈጸም ይገባዋል፣ መዝናናት ሕይወትን እንደሚያድስ፣ ይህም እንዲሁ ነው» በማለት፣ ገደብ የለሽ መረንነትን ለሰው ሁሉ አድርሳለች።

አኒ መዝናናትን በኃጢአት ባርነት ውስጥ ሆና ስለ ገለጠችው፣ ተሳስታለች፤ ከልከኛው እውነት ጋር አልተግባባችምና ሁሉን አዛንፋለች። ይልቅስ፣ እያለፍኩ የማነሣውን ዘላቂ እውነት ላጠ

ንክር፡-

> «ዕንስ ማቋረጥ ለሴት ልጅ ነጻነትን አያስገኝም፣ በምትኩ የወንጀለኝነትን ስሜት በየቀኑ፣ የጤና ስንኩልነትን እያደር የሚያመጣ የሕይወት ጣጣ ነው፡፡ ውርጃ ቤተሰባዊ ግንኙነትን፣ ማኅበራዊ ሕይወትንና ሥነ ልቦናዊ ቀውስን በመፍጠር ወደ መፍትሔ - የለሽ ችግር ያደርሳል፡፡»

ይህን ያሉት ለበርካታ ዓመታት ውርጃ የሚፈጸሙ ሴቶችን ሕይወት ያጠኑት ሻረን ሳምሶን ናቸው፡፡ የእኚህ ሴት ዋንኛው የማስረጃ ጥቅሳቸው 2ኛ ጴጥሮስ 2፡19 ነው፡፡ «ሰዎች ‘ነጻ ትወጣላችሁ’ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል፡፡ ሰው ሲሸነፍ ላሸናፊው ባሪያ ሆኖ ስለሚገዛ፣ እነርሱም ራሳቸው የኃጢአት ባሪያዎች ናቸው፡፡» የሚለው የጴጥሮስ ቃል አጽንኦት በመስጠት ይናገሩታል፡፡ ኃጢአትም በቋንቋ የአጠቃቀም ቅለት አይቀልም፤ የውርጃን ግድያነት ዕንስን መቋረጥ በሚል የረገበ አባባል ቢጠ ቀሙበት እንኳን ከእሥረኝነት ነጻ አይሆኑም፣ በማለት ሻረን ይናገራሉ፡፡

የሐሰት ተስፋም ጽኑ አለመሆኑን ለማየት ዘንድሮን ከጥንቱ ዓለም ጋር ማስተያየት መልካም ነው፡፡ ሥልጣኔ መሻሻልን ያመጣ መስሎ ግን አላመጣም፤ ያለ ውስጣዊ ድል ቅርጻዊ ለውጥ ማድረግ ዘንድሮም ባርነትን «ዓለሙ ሁሉ ተቀብሎታል» በሚል ሕዝባዊ ስሜት እያሳተ እንደ ሆነ በተከታዩ ነጥብ መመልከት ይቻላል፡፡

* * *

የጥንት ሰዎች ታሪክ በሚነበብበት ጊዜ የአንባቢን ስሜት የሚጨፈግጉ የነበሩ የያኔው የብዙዎች ድርጊት፡- ለአማልክቶቻቸው ክብር ሲሉ ሕፃናትን መሥዋዕት እያደረጉ መገበራቸው እና የሰው ልጅ ሰውን የመብላት ታሪኮች ይሰቀጥጣሉ፡፡ ይህ በ1998 ዓ.ም ወይም 2006 (እ.ኤ.አ) ተፈጻሚ አይሆንም፤ ሊፈጸም ቢችል እንኳ ውግዘቱና ሰልፉ የበረታ መሆኑ አይቀርም፡፡

የዘመኑ የውርጃ አራማጅ ታሪክ ግን «መከላከል ፍጹም የማይችሉትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፅንሶችን ይገድላሉ»፤ ግድያውም መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው ለወላጆች ክብር፣ ለግል ደኅንነት፣ ለኅብረተሰብ አለኝታነት ተብሎ ነው። እናስ ለውጡ ምኑ ጋ ነው?

ይህ የኃጢአት ባርነት ለዘለቄታው ተስፋፍቶ ዳር ሳናደርሰው አንመለስም የሚሉት «የማስወረድ መብታችን ነው ባለቤቶች» ግባቸው በፅንስ መቋረጥ ስም ግድያውን የሕግ ጥላ ለመስጠት በየሸንጎው መወዛገብ የዘወትር ሥራቸው ሆኗል። በዚህ ተስፋ የሚሰጥ በሚመስለው ጉዳያቸው የኅዳና ተዳዳሪው ቁጥር ይቀንሳል፣ የተመጠነ ቤተሰብ ይኖራል፤ ድኽነት ከእኛ ይርቃል፣ ተገድደው በመደፈር የፀነሱ ነጻ ይሆናሉ፣ የሴት መብት ይከበራል ይሉለታል። ይህ ግን «እኔ ከሞትኩኝ» ያቀፈ መብት-የለሽ የሚመስለውን ፅንስ በመግደል የመኖር ምኞት ነው።

* * *

ማን ያውቃል ንባቤን እያዘለቃችሁት ካላችሁት ሰዎች ጥቂቶቻችሁ እኮ ፅንስን ለማስወረድ የጎሊና ሙግት የያዛችሁ ትሆኑ ይሆናል፤ አልያም ውርጃን አላስፈላጊ ነገርን በቀላሉ ማስወገድ ስለሆነ ለተቸገሩ ሁሉ «መውረድ» አለበት የሚለው አንደበታሁ የሚቀላችሁ ወንዶች ወይም ባሎች ትኖሩ ይሆናል፤ ወይም «ከራስ በላይ ነፋስ» ዋንኛ መፈክራቸው ሆኖ ፅንሱም፣ ሴቲቱም፣ እግዚአብሔርም ግምት ውስጥ ሳይገቡ፣ ብቸኛው አማራጭ ውርጃ ብቻ ነው ለሚለው የግድ የኃጢአት ባሪያ የሆናችሁ ትሆኑ ይሆናል። እኔ ግን ሌላውን ብቸኛ ምትክ - የለሽ መፍትሔን ቆም ብላችሁ እንድታስቡ ጋበዝኳችሁ፡- ወደ ሰዎች እግዚአብሔር የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሕይወታችሁ ተስፋን፣ ደኅንነትንና ነፃነትን ሊሰጣችሁ በአጠገባችሁ እርሱ አለ። ለእርሱ መገዛት ከኃጢአት ባርነት ነጻ አውጥቶ ሕይወትን ይዘራል። የዘላለምን ሕይወት በግላችሁ፤ ሊቀጭ ላለው ፅንስ ዳግም በምድር

ላይ መኖርን ይለማሳል፤ መውለድ «መውረድ ወይም መዋረድ» አይደለም፤ ተወላጁን ልጅ ለማሳደግ እግዚአብሔር ራሱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የተወለደው ሕፃን አብሮ እንዲኖር ባይፈልግ የተሻለ ሌላም መፍትሔ አለ። በመሀንነት በመኖር የልጅ ጥማት ላላቸው ሰዎች በ«ጉዲፈቻነት» መስጠትም አንድ የሕይወት ማትረፊያ ነው።

እንኪያስ፣ «አትግደልን» በጽናት ለማምለጥ ነጻነትን ሊያውጅ በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ታምነን እንታዘዝ።

ፍልስፍና እና ፈላስፎች

«. . . ኤፒኮሮሶችና እስቶይኮች የተባሉ ፈላስፎችም ወደ እርሱ እየመጡ ይከራከሩ ነበር። አንዳንዶቹ፣ «ይህ ለፍላፊ ምን ማለት ይፈልጋል?» ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ፣ «ስለ አዳዲስ አማልክት የሚናገር ይመስላል» ይሉ ነበር፤ ይህንንም ያሉበት ምክንያት ጳውሎስ የኢየሱስንና የትንሣኤውን መልካም ዜና ስላበሠረ ነው። ስለዚህ፣ ጳውሎስን ይዘው አርዮስፋጎስ በተባለው ስፍራ ወደሚሰበሰበው ጉባኤ አመጡትና እንዲህ አሉት፣ «ይህ አንተ የምታስተምረው አዲስ ትምህርት ምን እንደ ሆነ ማወቅ እንችላለንን? አንዳንድ እንግዳ ነገሮችን አስተምረኸናል፣ ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ምን እንደ ሆኑ ማወቅ እንፈልጋለን። ይህን ያሉት የአቴና ነዋሪዎችና በአቴና የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ አዲስ ነገር በመናገርና በመስማት ብቻ ጊዜያቸውን ማሳለፍ ይወድዱ ስለ ነበረ ነው» (ሐዋ. 17፡18-21)።

«. . . በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ በሰው ሠራሽ ወግና በዓለማዊ ተራ ሥርዓት ላይ በተመሠረተ በፍልስፍና ከንቱ ሽንገላ ማንም እንዳያጠምዳችሁ ተጠንቀቁ. . . » (ቈላ. 2፡8)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት ስፍራዎች ብቻ ስለ ፈላስፎችና

ስለ ፍልስፍና ይናገራሉ። የሁለቱም ዋነኛ ጥቅስ አዲስ ኪዳን ነው፤ ቀዳሚው፣ ነገርን ሁሉ በጥንቃቄ ከሚጽፈው ከሉቃስ የተገኘ ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ ሁለገብ እውቀት ከኖረው ከጳውሎስ የተጻፈው መልእክት ነው፤ በዚህ ዝግጅት እነርሱኑ ነው መነሻ ያደረግኩት።

ቀዳሚው ስፍራ አዲስ ነገር በመጣ ቁጥር ስለዚያ ምንነትና ማንነት ሊረዱ ዝግጁ የሆኑትን ፈላስፎች አንሥቷል፤ በጊዜው ከነበራቸው እይታ ወጣ ያለው እንግዳ ነገር የኢየሱስ እና የትንሣኤው ዜና ነበር። ይህን ለማወቅ ጓጉ፤ ጉጉታቸውንም ወደ ጳውሎስ በመመላለስ የአቴና ፈላስፎቹ ሞገቱ።

ተከታይ ክፍለ ጥቅስ፣ ፍልስፍናን ለሁለት ከፍሎ በአንደኛው ላይ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ገለጸ፤ በእውነት ላይ ሳይመሠረት፣ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ የሚሆን ወግና ሥርዓት በባሕሪው እውነት መስሎ ያስታል፣ በማታለልም እምነትንና ተግባርን ያዛባሉ። ጳውሎስ ይህን አሳች ትምህርት አታላይነት የተሞላው ፍልስፍና ብሎ ጠራው።

* * *

መቼም አንድ ቃል በጊዜ ውስጥ ቀድሞ የያዘውን ፍቺ ያሰፋል፤ አልያም ያጠባል፤ ከዚህም የተነሣ ፍልስፍና ለሚለው ቃል ሥሪቱ የግሪክ ቋንቋ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ፍቺው ፊልዮሶፊያ ከተገኘበት ሁለት ቃል የወጣ ነው፤ ፊሎስ፡- ወዳጅ፣ ጓደኛ ማለት ሲሆን፣ ሶፊያ ደግሞ ጥበብ ነው። ድምር ፍቺ፡- የጥበብ ፍቅር ሊሆን ይችላል። ይህን ጥበብ የሚኖሩበትና የሚያፈቅሩት ደግሞ ፈላስፎች /ፊሎሶፈርስ/ ይባላሉ። ዛሬ ላይ ቆመን ትርጉሙን ስንፈትሽ ጠቦ ሳይሆን፣ ሰፍቶ ይገኛል፤ አሰፋፉም አዋቂ ተመራማሪ፣ ባለፈውና በሚመጣው ነገር ላይ ጽኑ አሳብ መስጠት የሚችል የሚልን ትርጉም በመያዝ፣ በዘርፈ ብዙ የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ የሚገኝ ቅመም ተደርጎ ይወሰዳል።

እኔ በዚህ አተረጓጎም ቅር ሳልሰኝ፣ ግና በክርስቶስ ትምህርት ላይ ያልተመሠረቱ በቅጡ ሊጤኑ የሚገባቸውን ፍልስፍና-ነክ

ጉዳዮችን «ጠይቀውን መልስ እንዳናጣና በከንቱነት የተሞሉ እሳቤዎችም ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ» አንድ ርእሰ ጉዳይ ብቻ በማንሣት የአቅሜን እሞክራለሁ። አካሄዴ ስለ እግዚአብሔር መኖርና እርሱ ከፍጥረቱ ጋር ስላለው መስተጋብር /ግንኙነት/ የተባሉትን ብቻ ይመለከታል።

ከዚህ ከተነሡት የተለያዩ ምልከታዎች ውስጥ አንዱ ቴዩዝም በመባል ይታወቃል። የእምነት መሠረቱ የብሉይና የሀዲስ መጻሕፍት ሳይሆኑ፣ ተፈጥሮን በመመልከት መወሰን ነው። እሳቤው ዓለሙ በእግዚአብሔር የተፈጠረ መሆኑን ያምናል። አናክሳጎሪስ የጥንቱ የግሪክ ፈላስፋ ዓለሙን እንዲህ የሠራና ያስጌጠ ታላቅ ባለ አእምሮ አለ ይላል። የዚህን ሰው ፈለግ ጓላ ላይ የተከታተሉት ሶቅራጥስ፣ ፕላቶ እና አርስቶትል ናቸው። እነዚህ ሰዎች «እግዚአብሔር፣ ከዓለሙ ውጭ የሆነ አንድ ልዩ ባሕርይ ነው» ይላሉ። አሳባቸውን ሲያብራሩም፣ «ማንኛውም የሚነቃነቅ /ተነቃናቂ/ የግድ አንድ የሚነቀንቀው /ነቅናቂ/ ሊኖረው ያስፈልጋል፤ ያለ ነቅናቂ /ያለ ምክንያት/ ተነቅናቂ /ውጤት/ ሊገኝ አይችልምና» በማለት የዓለም ሥርዓቱ ሁሉ በእግዚአብሔር መካሄዱን ያሳውቃሉ።

ቴዩዝም ሌላው እሳቤ /ንድፈ ሀሳብ/ ነው። የእግዚአብሔርን መኖር እንደ ቴዩዝም ይቀበላል። ይህኛው የሚለው፣ እግዚአብሔር ለዓለም የሚያስፈልገውን ሕግና ሥርዓት አበጅቶ ከፈጠረ በኋላ በገዛ ራሱ እንዲተዳደር ትቶታል። ከዚህም የተነሣ ከዓለም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም ይላል።

ትምህርቱ ቢጠሩት፣ ቢለምኑት አለመስማቱን፤ በዓለም ለተፈጠሩት ነውጦች፣ መጥለቅለቆች፣ በተለያዩ ልምላሜዎችና በረከቶች ለእግዚአብሔር ጉዳዩ እንዳልሆኑ ያብራራል። ከዚህም የተነሣ ዓለም በእግዚአብሔር እንደ ተረሣና እንደማይታወቅ እየገለጸ፣ የሚሆኑትን አስደናቂ ትንግርቶችም በተአምር ስም መጥራት አላስፈላጊ መሆኑን ይተነትናል።

ፓንቴይዝም ደግሞ ሦስተኛው እሳቤ ነው። እግዚአብሔርንና ፍጥረቱን እንዲህ ይገልጸዋል፦

> «እግዚአብሔርና ዓለም አንድ ናቸው፤ እርሱ ከዓለሙ ውጭ ወይም የተለየ ሆኖ ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፣ ከውጭም ሆኖ በዓለሙ ላይ የሚሠራ አይደለም። ይልቁኑ፣ በዓለም ውስጥ አድሮ ዓለሙን የሚያሠራ አንድ ኃይል ነው። ከዚህም የተነሣ በዚህ ዓለም ለሚደረገው ሁሉ ነገር ምክንያቱ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ እንደ ባዕድ አይቆጠርም፤ እርሱን የምናገኘው በዓለሙ ውስጥ ነው። ዓለሙም የእግዚአብሔር መልክ ነው በማለት እምነቱን ይገልጻል። «አንድ ዘር ከመሬት ላይ ወድቆ ባለበት ተገቢው የልምላሜ ጊዜ ሲደርስ፣ የተዳፈነው ውስጠኛ ፍሬ ከውስጡ እንደሚወጣ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም በዓለሙ ውስጥ እንዲሁ ነው፤ ፍሬውና ቅጠሎቹ ከዚያች ከመሬት ከወደቀችው ዘር እንደ ወጡ፣ እግዚአብሔር ከራሱ አመንጭቶ በመፍጠር ራሱ ተመልሶ በእርሱ በኩል ሆኖ ይገለጻል።» በማለትም ይመስሉታል።

ፓኑኔቴይዝም ሌላው እሳቤ ነው። ይህ ከቀደመው የሚለየው በጥቂት ነው፤ የፊተኛው እግዚአብሔርና ዓለሙን እንደ አንድ አድርጎ የሚያስብና እግዚአብሔርን በዓለሙ ውስጥ አኑሮ ማናቸውንም ድርጊት በእርሱ ውስጣዊ ምክንያትነት የሚሳካ መሆኑን ሲያስተምር፤ ይህ ግን፣ እግዚአብሔርና ዓለሙ ያው ናቸው የሚለውን ባይደግፍም። እንደ ቴይዝምና ዴዩዝም ሁለቱን ለየራሳቸው አድርጎ አራርቆ አይይዛቸውም። ዓለምን ከእግዚአብሔር በጣም ሳይለይ፣ ልክ ብርሃን ከፀሐይ እንደሚወጣ (እንደሚፈልቅ)፣ ዓለሙም ከእግዚአብሔር የወጣ ክፋይ ወይም ቁራሽ ነው በማለት ያስተምራል (ዘፍጥ. 1፡1፤ ዕብ. 11፡3)፤ ቈላ. 2፡9፤ ዕብ. 1፡1-3፤ ኢሳ. 44፡24)።

በዚህ አስተያየት የመጨረሻ አድርጌ የምወስደው *ኤቲዩዝምን* ነው። ይኸኛው የእግዚአብሔርን መኖር አይቀበልም። ዓለም በገዛ

ራሱ እንደ ተገኘ ያምናል። የማንኛውንም ነገር ሕልውና በስሜት ሕዋሶቻችን ብቻ እንገነዘበዋለን፤ ከዚያ የወጣ ምንም ነገር የለም፣ በማለት ያስተምራል።

ፈላስፋዎቹ ይህን አመለካከት ሲያራምዱ ሁሌ እያነሡ የሚያቀነቅኑለት ከመረጃ ተብዬዎቹ መካከል አንዱ ገዥዎች ሕዝብን አስፈራርተው ለመግዛት እንዲያመቻቸው ሆን ብለው ያደረጁት መሆኑን፣ ቀሳውስት የሕዝብ ሰላም እንዲጠበቅና የራሳቸው መተዳደሪያ እንዳይጓደል በማሰብ የፈጠሩት፣ አልያም ፍርሀት የፈጠረው እምነት ነው በማለት በዓለም ውስጥ ሰው ተቋቁሞ ሊያቆመው የማይችለውን አደጋ መብረቅ፣ ማዕበል፣ እሳት፣ ነውጥ፣ መጥለቅለቅ የመሳሰሉ ከግምቱ በላይ ስለሆኑ፣ እነርሱን የፈጠረ አምላክ አለ በማለት ያምን ጀመር እንጂ፣ ይህ ዓለም ያለ ፈጣሪ ያለ ነው ይላሉ።

እንግዲህ ከላይ የተዘከሩትን አምስት ያህል ምልከታዎችን ሰብሰብ አድርጌ ልቋጨው። መቼም ሰውን ሁሉ ስናስብ በአንድ ሊፈረጅ የሚገባበት ስፍራ አለው-ኃጢአተኝነት። በአዳምና ሔዋን የአለመታዘዝ ውጤት በእነርሱና በዝርያዎቻቸው ሁሉ ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ለይቶታል፣ ተለየም ሲባል የእግዚአብሔርን ማወቅና የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ሁሉ አጥርቶ እንዳይረዳ በኃጢአት ተበክሏል ማለት ነው፤ በመንፈሱ፣ በነፍሱ በሥጋው ረክሷልና። ይህም እውነት መሆኑን የምንረዳው እግዚአብሔር በቃሉ፣ «አንድ እንኳ ጻድቅ ሰው የለም፤ . . . አስተዋይ የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ አንድም የለም። ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤ ተሳስተዋል» (ሮሜ 3፡11-12) በማለት ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን እንደማይፈራ ያስረዳል። ይህም የሆነው «በበደላቸውና በኃጢአታቸው ምክንያት የሞቱ ናቸውና» በማለት ኤፌሶን 2:1 ላይም ያሳውቃል። ኃጢአት ሰውን ሙት አድርጎታል፤ ይህም ማለት እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር አይረዳም ማለት ነው።

ከዚህ የምንረዳው ከላይ የተነሡት አምስት ትንተናዎች ወደ እግዚአብሔር መቅረብን ሳይሆን፣ መሸሽን የሚያውቀው ሰው ባለው አእምሮ ብቻ ተወስኖ የተነተነው መሆኑን ያሳውቀናል። እርግጥ ነው፣ እንደ ኤቲዩዝም እግዚአብሔር የለም ብሎ ከማለት፣ የተቀሩትን የተሻለ አድርጎ በመቁጠር፣ ይልቁኑም፣ ቴዩዝም ዓለም በእርሱ ተፈጠረ ስላለ ብልጫ ያለው እሳቤ ተደርጎ ሊዘከር ይችል ይሆናል።

ሁሉንም ግን በእግዚአብሔር ቃል አኳያ ከክርስቶስ ከሆነው ትምህርት በመነሣት ቢጤኑ ጳውሎስ እንዳለው፣ ሰው ሠራሽ ወግነታቸው፣ ዳግምታ አሣችነታቸው ፍንትው ብሎ ሊታይ ይችላል። ይህን አባባል በጥቂቱ ላብራራ። የመነሻው እሳቤ ቴዩዝም ፈጣሪ እንዳለ ከተፈጠረው በመነሣት ገለጸልን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ቃል የተገለጸውን እግዚአብሔርን እና የፍጥረቱን ዓላማ አልተረዳውም። ከዚህም የተነሣ ፍሬያማ ለመሆን በመዝሙር (19)፡1-2፤ ሮሜ 1፡21፤ ኢዮብ 38 ላይ ሊደግፍ ይገባዋል።

ዴዩዝም በአስተሳሰብ ሥራቱ እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ መተዉን ነው የሚናገረው። ቃሉ ግን፣ መተዉን ሳይሆን፣ በፈጠራቸው እና በሰው አካሄድ ሁሉ ተመልካችና አዘጋጅ መሆኑን ያበስራል። ለዚህም እውነተኝነት መዝሙር (139):1-12፤ መዝሙር (124)፤ ዳንኤል 4፡35-37፤ ማቴዎስ 6፡25-33፤ ኢሳይያስ 45፡5-7፣ 9-12 በቅጡ ማንበቡ ይበጃል።

ፓንቴዩዝም እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ አድሮ ዓለሙን የሚሠራ ኃይል ነው የሚለው ትምህርት ሲፈተሽ ሐፀፁ ግልጽ ነው። እርሱም እግዚአብሔር በኢሳያስ 45፡12፣ «ምድርን የፈጠርኩና ሰውንም ፈጥሬ በእርስዋ እንዲኖር ያደረግኹ እኔ ነኝ፤ ሰማያትን በኀይሌ የዘረጋሁና ሠራዊቶቻቸውንም የምቈጣጠረው እኔ ነኝ» እያለ፣ እግዚአብሔር የፍጥረቱ ገዥና አስተዳዳሪ እንጂ በዓለም ውስጥ ያለ፣ አብሮ-በቀል አለመሆኑን ይገልጻል።

ለተጨማሪ ድጋፍም ኢሳይያስ 44:24፤ ሐዋርያት 17:22-30ን ማጤን መልካም ነው::

በአራተኛው እይታ ከፓንቴዩዝም አካሄድ ዓለሙ ከእግዚአብሔር ተቆርጦ እንደ ወጣ መረዳት ማለት እግዚአብሔር ራሱን ችሎ ሁሉን ካለመኖር ወደ መኖር እንዳስገኘ ሳይሆን፣ የእርሱ ሕልውና ተካፋይ መሆኑ፤ «ፈጠረ» የሚለውን ታላቅነቱን እንደ ሻረ ያሳስባል:: እግዚአብሔር ከውስጡ ዓለማትንና በውስጣቸው ያለውን ማስገኘት ሳይሆን፣ ከምንም ነገር (ከባዶ) እግዚአብሔር ሁሉን ወደ ሕልውና እንዳመጣ ይነግረናል:: ለዚህም መደገፊያው ዕብራውያን 1:1-3፤ ዘፍጥረት 1:1፤ ዕብራውያን 11:3፤ ቈላስይስ 2:9 ይሆናሉ::

በመጨረሻው እይታም፣ በእግዚአብሔር አለመኖር የሚታመነው እሳቤና ሁነኛ ምክንያቱ ብሎ የሚያነሣቸው ነጥቦች ያሉት ቢመስልም፣ አለ ብለው ከሚታመኑትም የተለየ አይሆኑም:: «አለ» ማለታቸው እርሱን በትክክል እስካላወቁና ኃጢአተኝነታቸው ከእግዚአብሔር የለያቸው በመሆኑ የተሻለ የሚመስል ግን ያልተሻለ እሳቤ ባለቤቶች ሆነዋል፣ ከዚህም የተነሣ ኤቲዩዝም በቅጡ ለማየት ሮሜ 1:20-21፤ ኢዮብ 38:1-41ን ማገናዘብ ተገቢ ነው::

በማጠቃለያም፣ በክርስቶስ ከሆኑና በክርስቶስ ትምህርት በቃሉ ለሚደገፉ ሁሉ ፍልስፍናን ማጤን የሚከብድ ጉዳይ አይደለም:: ከዚህ በወጣ አካሄድ ግን ሕያው ቃሉን ለመሸቀጥ፣ እምነታችንና ተግባራችንን ለማዛባት የሚያመቻቹ ከሆኑ፣ ሁሌ ቆም ብሎ መፈተሽ ተገቢ ነው:: ቀደም ተብሎ ለመጠቆም እንደ ታሰበው፣ ብዙዎቹ በየእሳቤዎቹ ሥር ተጠልለው ለመኖር ራሳቸውን ሰጥተዋል:: በክርስቶስ የሆኑ ክርስቲያኖች ግን ይህን በማስተዋል፣ እግዚአብሔር ለእርሱ ክብር ያዘጋጃቸውን ምርኮ ያደርጉ ዘንድ ወንጌልን ወደ እነርሱ ይዘው ሊወጡ ይገባል::

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1:21-25 እንዲህ አለን፣ እንግዲህ ባለን እንመራ::

«የዚህ ዓለም ሰዎች በገዛ ጥበባቸው እግዚአብሔርን ማወቅ እንዳይችሉ እግዚአብሔር በጥበቡ ዘጋባቸው፤ ነገር ግን እንደ ሞኝነት በሚቈጠረው እኛ በምናስተምረው ወንጌል የሚያምኑትን ለማዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖአል። መቼም አይሁድ ተአምር ማየትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎች ደግሞ ጥበብን ይሻሉ። እኛ ግን ክርስቶስ ስለ እኛ መሰቀሉን እናስተምራለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናከያ ነው፤ ለግሪክ ሰዎች ደግሞ ሞኝነት ነው። ለተጠሩት ግን ለአይሁድ ሆነ ለግሪክ ሰዎች ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። የእግዚአብሔር ሞኝነት ነው ተብሎ የሚታሰበው ነገር ከሰው ጥበብ ይበልጣል፤ የእግዚአብሔር ደካማነት ነው ተብሎ የሚታሰበውም ነገር ከሰው ኀይል ይበልጣል።»

መረጃ መጻሕፍት

1. **የፍልስፍና ትምህርት፣ ቅጽ 1 እና ቅጽ 2፣ በየማነ ገብረ ማርያም፣ 1955 ዓ.ም፣ በብርሃንና ሰላም በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ።**
2. Three Types of Religious Philosophy, Gordon H. Clark, 1973.
3. A Christian Philosophy & Education, Gordon H. Clark, 1946.
4. Education, Christianity & the State, J. Gresham Machen.
5. The Philosophy & Science and Belief in God, Gordon H. Clark.

ኃላፊነትና ተጠያቂነት

ይህን ጽሑፍ ሳዘጋጅ ከጐኔ የቆሙልኝ አጋሮቼ የሳውዘርን ባኝ ቲስቶቹ ሀንድሪክስ እና ሀውስ ሆልደር ናቸው። እነዚህ ጥምሮች ንጹሐን አስተምህሮ በአገባቡ ለሰዎች በማድረስ የታመኑ መሆናቸውን ከመጻሕፍታቸው ስለ ተረዳሁኝ፣ መረጥኩዋቸው። ከዚህም የተነሣ ሁላችን ልንረዳው የተገባውን ኃላፊነት፣ ደግሞም ተጠያቂነትን መጥኜ አቀርባለሁ።

* * *

ምዕራፍ አንድ

እንግዲህ የሚከተሉትን ጥቅሶች ልብ የሚል ልብ ይበላቸው፦ ማቴዎስ 4፡18-22፤ 1፡1-15፤ ማርቆስ 1፡16-2፣ ሉቃስ 6፡12-16። ቃሉ እንዳስረዳን፣ ኢየሱስ ለማስተማርና ለማገልገል የነበረው ዓመት ሦስት ዓመት ከጥቂት ወር ብቻ ነበር፤ መቼም ምንም ጥቂት ቢሆን፣ እርሱኑ መሻማት ግድ ነበር። እናም ኢየሱስ ለመስቀል ሞት ከመብቃቱ በፊት ዓለምን ሁሉ ከአብ ዘንድ ይዞ በመጣው መልእክቱ ሊያጥለቀልቀው ይገባል። በምትኩ ግን ራሱን ሊገልጥላቸው የሰነበተውና ሰማያዊ የሆነውን ጽኑ እውነት ሊያብራራ የከረመው ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ብቻ ነበር። ኢየሱስ ለእነዚህ ሰፊ ትዕግሥት፣ ብዙ ቸርነት፣ ብዙ ድካምን ደክሞ ተልዕኮውን ደመደመ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ያደረገበትን ምክንያት እስቲ ከደቀ መዝሙርነት ዳህራዊ ፍቺ በመነሣት እናጢን፦ የግሪክ ቃሉ «Manthanein» ሲሆን፣ የዚህ ግሥ ፍቺ ተግቶ መማር የሚለውን ትርጉም ያመጣል፣ ይህ ትጋተ ትምህርት በግሪኮች ዘንድ የሚካሄዳው ሊማር የወደደ ተማሪ ዕውቀቱን በአግባቡ ሊያሠርጽ ይችላል ወደ ተባለው ታዋቂ መምህር በመሄድ ያዳምጣል፣ ይጠይቃል፣ ይወያያል። መምህሩም ያደምጣል፣ ይጠይቃል፣ ይወያያል። ከዚህም የተነሣ ቅብብሉ ሁለቱን ወገን በእውቀት ያስደንቃል፣ እናም መድረኩ የዚህንም የዚያኛውንም ዓለም ምሥጢር የሚተነትኑበት ስፍራ ነው። ይህ አደራረግ በኢየሱስና በደቀ መዛሙርቱ ዘንድ ተግባራዊ ሆኗል። ዕ

ብራውያኑም ቢሆኑ ገና ከጠዋቱ ለልጆቻቸው አልተኙም፣ ሊያስተምር ወደ ተገባው ሰው በመላክ ከለጋ ዕድሜያቸው ጀምሮ የሕግን መጻሕፍትንና ተጨማሪ ተፈላጊ ሥርዓቶችን በመማር ማደግ ነበረባቸው።

ኢየሱስ ሲመጣ ግን የትኛውንም የኋላ መነሻ ሳይሸር ዘላቂ ውጤትን በሚያመጣው ላይ ተጋ። በጥቂት ብዙ ማምረት፣ ከጥቂት ጋር አብሮ መክረም፣ የሚታወቀውን፣ ሊታወቅ የተገባውን ሌላው ቀርቶ የተዘነጋውንም ጭምር በማብራራት ትምህርቱን በመኖር መግለጽ ተፈላጊው ሆነለት፤ ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ ከአሥራ ሁለት ሰዎች ጋር ውሎ አደረ።

ይህም ግን ቀሪዎቹን ተወ፣ ችል አለ ማለት አለመሆኑን ልብ ይበሉ። ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል ሲመላለስ መምህር (ረቢ) እየተባለ (ማር. 9:5፤ 1:51፤ 11:21፤ 14:45) ሥልጠናዊ ትምህርቱን አድምጠውለታል፤ እርሱም መምህር ነበረና በየምኩራቦቻቸው ሕዝቡን አስተምሯል፤ መጠየቅ በፈለጉ ጊዜ ሁሉ ይጠየቃል፣ መልስ ይሰጣል፣ እንደየ አቅማቸውም ምሳሌዎችን በማምጣት አጣጥሞ ይናገራል።

* * *

ይህ ረቢ፣ ከሕጋውያኑ መምህራን የተገደበውን ጣስ አድርጎ በልከኛው አሳብ ሲመራም ታይቷል። በመምህራኑ ዘንድ በወቅቱ ከሴት ጋር ተገናኝቶ ምሥጢርን መግለጽ ቀርቶ በቅርብ ርቀት መተላለፍም እንኳ ነውር ነበር። ኢየሱስ ግን ከሳምራዊቷ ውኃ ቀጂ ጋር ቀርቦ ተነጋገረ፣ አስተማረም። ለመምህራኑ ሕፃናት በሩቅ ይሆኑ ዘንድ ግድ ነበር። ኢየሱስ ግን ሕፃናቱን በእቅፉ አድርጎ ከባቢዎቹን አስተምሯል። የተመሰገኑ የተባለላቸው ረቢዎች ከተጻፈው ባህላዊ ትርጓሜ እልፍ አይሉም፣ ኢየሱስ ግን ወደ ምንጩ እየደረሰ ገልጧል።

ይህንንም አሥራ ሁለቱ ያዩ ዘንድ በቅርቡ ነበሩ። እነርሱ እኒህንም የፈለጋቸውና ከያሉበት የጠራቸውም እርሱ መሆኑ አይዘነጋ። ለዚህ ጥሪው እምብየው ያለ አንድም ከመካከላቸው አልነበረም። ኢየሱስ አብራችሁኝ ሁኑ ሲል፣ የተመቸኝና ስመ ጥር የሆንኩኝ ነኝ አላለም፤ ይልቅስ፣ ቀበሮዎች ዋሻ እንዳላቸው፣

ወፎቹም ጎጆ እንዳላቸው ሁሉ፣ የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት እንደሌለው (ማቴ. 8፡2) እያሳወቃቸው ሳለ፣ ከአሥራ ሁለቱ አንዱም አባቴን ቀብሬ ልመለስ (ሉቃስ 59-62) በማለት እርፍን ይዞ ወደ ኋላ እንደሚያይ ገበሬ አልሆኑም፤ ይህም የደቀ መዛሙርት ሁነኛ መለኪያ ሆኖ ተቆጠረ።

* * *

በኢየሱስ ዘንድ ውጤት-የለሽ ሥራ አልነበረም፣ ደቀ መዛሙርቱን ሲጠራቸው ዓሣን ሳይሆን፣ ሰዎችን አጥማጅ አደርጋችኋለሁ (ማር. 1፡17) የሚለው ውጤት ከወዲሁ ነበረው፤ በአጠማመዱም ከተወገዙ ኃጢአተኞች ጋር አብሮ መብላት (ማር. 2፡15)፣ የተራቡ ጎስቋሎችን መመገብ (ማር. 6፡34)፣ የአሕዛብ ወገን የሆነች ሴትን መቀበል (ማር. 7፡31) በጠመዳው ውስጥ የሚካተት የሕይወቱ ገለጻ ሆነው ለተከታዮቹ ታዩ፣ ይህም በግብነቱ ተመዘነ።

* * *

ኢየሱስ በአሥራ ሁለቱ ላይ ካተኮረበት ምክንያት ሌላኛው ብስለተ-ዕውቀት እንዲሰፍንም ነበር፤ በማርቆስ 4፡11 እንዳለው፣ «የእግዚአብሔር መንግሥትን ምሥጢር የማወቅ ችሎታ እናንተ አላችሁ፤ ሌሎቹ ግን የላቸውም» የማለቱ እማኝነት ያልጠየቁትን ነገሮች አስተምሮ፣ የጠየቁትን አብራርቶ፣ መልሶ መላልሶ እንዳስተማረ ያስረዳልና፣ አሥራ ሁለቱ ብስሎች ነበሩ።

* * *

በጥሪው የተካተቱት እነዚህኞቹ ሰዎች የኑሮ ዳህራቸው አንቱ የሚሰኝ አልነበረም። ኢየሱስ የኢየሩሳሌምን ምርጦች አጋዥር ሳያደረግ፣ በምትኩ ቀረጥ ሰብሳቢዎችን፣ ቀናተኞችን፣ ዓሣ አጥማጆቹን አሰባስቦ ለአንድ ዓለማ ሊያጸናቸው ወደደ። ሰዎቹ እንደ መልካቸው በሁሉ ነገራቸው የተለያዩ ነበሩ፤ ሌላው ቀርቶ ከወንድማማቾችም ውስጥ የአንዱ ስብዕና ከአንዱ ፍጹም ተራርቋል፤ ጴጥሮስና እንድርያስ ለዚህ ምሳሌ ናቸው። ጴጥሮስ ፈጣን ተናጋሪ ግን ደግሞ ከድርጊቱ ጋር ያልተጣጣመ ሰው ነበር። ለዚህም አምናለሁ ብሎ የካደ፤ ሆንኩኝ ብሎ ያልሆነ ነበር። የእናቱ ልጅ እንድርያስ ግን የዚህ ተቃራኒ ነበር፤ ድምፁ አይሰማም፣ የተ

ጻፈለት ምንም የለም፣ ዝምተኛ ግን አድራጊ ሰው ነበር፤ በዮሐንስ 6፡1፣14፣ ለ5,000 ሰዎች መመገብ መንሥኤው እርሱ ነበር፤ እንጀራና ዓሣ ይዞ የነበረውን ልጅ ማግኘት የቻለውም ሆነ ያገኘ ውንም ያስተዋወቀው እርሱ ነበር።

* * *

በወንድማማቾቹ በያዕቆብና በዮሐንስ ደግሞ ለየት ያለ ጉዳይ አለ፤ ሁለቱም የነጎድጓድ ልጆች ተብለዋል፣ ትዕግሥት-የለሽ ስለሆኑ፤ ሰማርያ ኢየሱስንና እነርሱን አላስተናግድ ብትል፣ ሕዝቡን ለእሳተ-ገሞራ ተመኙት (ሉቃስ 9፡54)። እነዚህ ኢየሱስን ተጠግተው ምሥጢር ሲያካፍሉትም በግራና በቀኝህ እንቀመጥ (ማር. 1፡37) የሚል ነበር። መቼም ወሬ አይደበቅምና፣ ልመናቸው ወደ ተቀሩት በደረሰ ጊዜ አብዮትን በመካከላቸው ቀሰቀሰ፣ አስቆጣቸው። እንዲህም ሆኖ ግን፣ የገዘፈ ጠንካራ ጎን ነበራቸው። ዮሐንስ የኢየሱስ የቀረበ ሰው፣ የተጠጋው ወዳጅ፣ የአራተኛው ወንጌልም ጸሐፊ ነበር፤ በሞቱ ሰዓት ለእናቱ አደራ ተቀባይ መሆን የቻለ ብቸኛ ደቀ መዝሙሩ እርሱ ነበር (ዮሐ. 19፡27)። ያዕቆብም ከአሥራ ሁለቱ የመጀመሪያው ሰማዕት ሆኖ ጌታን ለማክበር በሞቱ የተፈራረመ ጽኑ ሰው ነበር (ሐዋ. 12፡1-2)።

ማቴዎስና የቀናተኛው ስምዖን የኑሮ አቅጣጫቸው ሲመዘን ደግሞ፣ ማቴዎስ ለሮማውያን ታማኝ በመሆን ቀረጥን ከወገኖቹ እየሰበሰበ ገንዘብን ለገዥዎቹ የሚያደርስ ነበር። በዚህም ከእስራኤል ጠላቶች ጋር ተባብሯል። ስምዖን ቀናተኛው ደግሞ ቀናተኛነቱ እስራኤልን የሚያሰጨንቁትን ሮማውያንን መበቀል ነበር፣ መቃወምና በደፈጣ ማጥቃት፤ ኢየሱስ ግን በአንድ ላይ ቢገናኙ ይተራረዱ ይሆናል የተባሉትን ሰዎች በጥላው ሥር አደረጋቸው።

* * *

ፊልጶስ እና ይሁዳ የመማር ዳተኞች ነበሩ፤ ኢየሱስ በማስተማር ደክሞላቸዋል፦ ምሥጢርንም ገልጾላቸዋል፤ አወቁ ነቁ የተባለላቸው «ጌታ ሆይ፣ አብን አሳየንና ይበቃናል» (ዮሐ. 14፡8) የሚል ጨቅላ ጥያቄ አስጠይቋቸዋል፣ ለዚህ የኢየሱስ ምላሽ እስከ ዛሬ አብሬ ከእናንተ ጋር ስኖር ፊልጶስ ይህን አልተረዳህምን (ዮሐ. 14፡9) የሚል ነበር። ያስቆሮቱ ያልሆነው ይሁዳም ከዚህ ሰው ብዙ

አልተለየም፤ ኢየሱስን ጠየቀው፣ እርሱም በቀላል መንገድ ተከታይ መሆን የሚቻልበትን አሳየው፣ «አንተ ራስህን ለእኛ ብቻ ለምን ታስተዋውቃለህ፣ ለዓለሙ ሁሉ ራስህን ለምን አትገልጥም?» (ዮሐ. 14:22) አለው። ይህም ሊረከብ ያለውን ኃላፊነት በአንዴ ተገላግሎ ሊቀመጥ እንዳለው ይጠቁማል።

* * *

በናትናኤልና በቶማስ የተገኘው ሕፀፅ ደግሞ ለየት ያለ ነበር፤ በለስ ዛፍ ሥር ሆኖ መጽሐፉን ሲያጠና ፊልጶስ ብሥራትን ይዞለት ከተፍ አለ፤ የምሥራች የተባለው ግን ለናትናኤል የመርዶ ያህል ነበር። «ከናዝሬት ምን መልካም ነገር ሊመጣ ይችላል?» (ዮሐ. 1:46)፤ ይህ እውነትነት ያለው ምላሽ ነበር፤ በናዝሬት ክፋዎች ስለ በዙ፣ ክፉት የሚስተናገድበት ከተማ ነበር፤ በጎ ወጣበት ተብሎ ስሙ የሚጠራ አንድም ሰው የለበትም። ከዚህም የተነሣ ያውም መሢህ ከረከሰችው ምድር ይመጣል ብሎ መገመት አይጠበቅም። በዚህ አቅጣጫ የሚገኘው ሌላው ሰው ነገን አጨልሞ በማሰብ እውቅ ነበር፣ በኢየሱስ የፍጻሜ አገልግሎት ላይ መልእክት ወደ እነርሱ መጣ፦ «የምትወደው አልዓዛር ሞቷል» የሚል። ይህን መልእክት ቶማስ በበጎ አልተቀበለው፣ እነርሱን ጭምር የሚያስጨርሰ ጦስ ሊያመጣ እንደሚችል ከወዲሁ አረጋገጠ። ከዚህም የተነሣ ብድግ ብሎ፦ «እንግዲህ እንሂድና እንሰቅ» (ዮሐ. 11:16) በማለት አመለከተ። በእነዚህም የሚታየውን ስብዕና ኢየሱስ አውቆ ያዘው፤ አስተዳደራቸውም።

* * *

ያስቆሮቱ ይሁዳ እና ትንሹ በመባል የሚታወቀው ያዕቆብ፣ የመጨረሻዎቹ ናቸው። ዛሬ ብዙዎች ይሁዳን ሁሌ በሚተቹበት መንገድ ላይ ባልቆም የተሻለ ነው፤ ገንዘብ «አፍቃሪው» የሚለውን። መቼም ቢሆን ይሁዳ በከረጢቱ ጌታውን ሊሸጥበት ከተ ስማማበት ብር ይልቅ ውስጥ ያለው ገንዘብ ሳይበልጥ አይቀርም። ከዚህም የተነሣ፣ ለይሁዳ 3 ብር ብርቁ አልነበረም። ይልቅስ፣ ይሁዳ ኢየሱስን ከሮማውያን ነፃ ሊያወጣ የመጣ ጀግና መሆኑ ይታያል እያለ ተስፋ ሳያደርግ አልቀረም። የኢየሱስ የዘወትር ትምህርት ግን «ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ ለሚያሳድዷችሁ ጸልዩ፤» ስለ ሆነበት፣ ይሁዳ መደናገር ውስጥ ገባ። ለዚህ ደግሞ መፍትሔ

ው፣ እርሱን አሳልፎ በመስጠት፣ «በእኔስ ከመጣ» ከሚል ተ ከላካይነት የተነሣ ሰይፉን ይዞ ነጻ ሊያወጣ እንደሚችል ያጤነ፣ የተገነዘበ ይመስላል። እናም ለምኞቱ ሸጠው። ኢየሱስ ግን ይህን በሰይፍ ሳይሆን፣ እጁን በመስጠት እነርሱን ሸንቶ አበቃ። ይሁዳ ይህን ሲያይ ከግምቱ በላይ ሆነበት፣ ምክንያት የሆነውንም ብር ወርውሮ ራሱን ለማጥፋት ተቻኮለ። ትንሹ ያዕቆብ ትንሽ የሚለውን ቅጥያ ያገኘው አጭር ስለሆነ ነው ብለው የሚተቹ ምሁራን አሉ፣ ሊሆን ይችላል።

* * *

በዚህም በዚያም፣ ኢየሱስ የጠራቸው እኒህ ሰዎች መጠነ-ሰፊ ልዩነት ነበራቸው፤ ዓሣ አጥማጅ ከቀረጥ ሰብሳቢ፤ ቀናተኛ ከዝግመተኛ፤ ደግ አሳቢ ከክፉ ጠሪ ጋር ተሰባጥረው የተገኙበት ጉባኤ ነበር፤ ይህም ልክ እንደ ዘንድሮዎቹ እንደ እኛ ማለት ነው፣ እንደ እኔ እና እንደ እናንተ።

* * *

ምዕራፍ ሁለት

«ለእናንተ የመንግሥተ ሰማይን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአች ኋል» (ማቴ. 13፡11)። «የእናንተ ዓይኖች ስለሚያዩ ጆሮዎቻችሁም ስለሚሰሙ የተባረኩ ናቸው» (ማቴ. 13፡16)።

እነዚህ ቀዳሚ ጥቅሶች ኃላፊነትን ከተጠያቂነት ጋር እያጣጣሙ የሚሉት አሏቸው፣ ማርቆስ በመጽሐፉ ምዕራፍ 3፡14 ላይ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ አሥራ ሁለቱን ሾማቸው በማለት፡- የጥሪው ይዘት ስለ እርሱ ቃላዊ እውቀት እንዲኖራቸው ብቻ ሳይሆን፣ እንዲኖሩት፣ እንዲለማመዱት፣ ዘርፈ-ብዙ ሕይወቱን ገልጦ አሳያቸው፡- ከእራት ተነሣ መጐናጸፊያውን አስቀመጠ፣ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ፣ ከዚያም በመታጠቢያው ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታጠቀው ፎጣ ያብስ ጀመር (ዮሐ. 13፡4-5)። ይህን ልብ እንበለው፣ የሁሉ ድርጊት ባለቤት ራሱ ነበር፤ ይህንንም ደቀ መዛሙርቱ ያዩት ነበር፤ በማየት ሕይወት ሲደረጅ፣ ሲቀረጽም፣ እኔ እንዲህ ነኝ ወይም ልትሆኑ የሚገባው ይህ ነው ብሎ ከሚሰጥ ስብከት ይልቅ ኑሮው፣ በሕይወታቸው ተተክሎ ይቀር ነበር።

* * *

በዕብራዊያኑ ዘንድ እንዲደገም እንዲሰለስ ይደረግ የነበረውን ጸሎት እና ዓይነቱን ኢየሱስ አላስባለም፤ ግን ፈንጠር ብሎ ይጸልይ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ ከአባቱ ጋር እየተገናኘ መሆኑን አስተዋሉ። ይህም በተደጋጋሚ ጊዜ የጸሎት አስፈላጊነትን አመኑበት፣ ከዚህም የተነሣ ሊጠየቅ የተገባውን ጥያቄ ይዘው ጸሎቱን እንደ ጨረሰ፡- ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ «ጌታ ሆይ፣ መጸለይን አስተምረን» (ሉቃስ 11፡1) አሉት፤ በሕይወቱ የሚጠበቅባቸውን የሚያሳይ ሆነላቸው።

ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር አስተምሯል፤ ገለጻና ስብከትም በየጊዜው አስደምጧል፤ ከዚህ አልፈው ግን ደቀ መዛሙርቱ የእግዚአብሔርን ማንነት በእርሱ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ አግኝተውታል፤ ከመሐከላቸው አንዱ «አብን አሳየን» ብሎ ሲጠይቀው፣ «እኔን ያየ፣ አብን አየ» (ዮሐ. 14፡8-9) በማለት ነው ያብራራው።

ኢየሱስ መምህርም የመምህሩም መጽሐፍ ነው፤ «ቀንበሬን ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ» (ማቴ. 11፡29) ሲል፤ የመማሪያውን መጽሐፍ ራሱን አደረገው። ትምህርቱ ከመኖር እንደማይነጠል ገለጸ፤ «እኔ መንገድ እውነትና ሕይወትም ነኝ።» በመንገድ ላይ መገኘት፡- ከኢየሱስ ጋር መገናኘት፤ ተከትሎም በእውነት ላይ በመቆም ሕይወት የተትረፈረፈ መሆን እንደሚገባው (ዮሐ. 14፡6) አበክሮ ወደ ኋላ ላይ ግራ ለገባው የቶማስ ጥያቄ መልስ ሰጠ፤ ይህም ከዘርፈ ብዙ ሕይወት ጥቂቱ ነው።

ተራና ምንም የሌለው ከሚመስለው የአኗኗር ስልትም፣ ኢየሱስ ለተልዕኮ በሚያዘጋጃቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ አሻራውን አኑሯል። እነርሱ የቅርባቸውን አፈር፣ የቅርባቸውን ዘር፣ ወይም ሕንፃ የወትሮው ነው ብለው ቸል አሉት፡- እርሱ ግን «እነዚህን ታላላቅ ሕንፃዎች ታያላችሁን?» (ማር. 13፡2) በማለት ትኩረትን ሳበ፤ አስከትሎም፣ «አንዱ ድንጋይ በሌላው ላይ እንደ ሆነ አይቀርም፣ ሁሉም ፈራሽ ነው፤» በማለት በከተማው ውስጥ ያሉት ነገራት ሁሉ ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር ሊገጣጠሙ እንደሚችሉ ተራ በሚመስለው ጉዳይ ላይ ገለጸው። በዮሐንስ 4፡35

ላይ፣ ወቅቱን ጠብቆ በሚዘራውና በሚበቀለው አዝመራ ላይ ተመርኩዞ ደቀ መዛሙርቱን፣ «እነሆ፣ አዝመራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና ብላችሁ ማሳውን ተመልከቱ» በማለት ከቅርቡ ያስተምራቸዋል፤ የማቴዎስ 13፡3ቱም እንዲሁ ነው፣ «አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ...» እያለ የወቅቱን ገበሬ፣ የአፈሩን ዐይነት፣ የዘሩን ሁኔታ ከሁሉም መረዳታቸው ባሻገር ቁም ነገርን በሕይወታቸው አጠራቀመ። አንድ ልጇን በሞት አጥታ ለቀብሩ በአጀብ ሲጓዙ ቆም አድርጎ ሕይወት ሰጥቶ አስረከበ። እጅ ሰላላውን ሰው በሕዝቡ መካከል አስቁሞ ፈወሰ። እያስደነቀ፣ እያስገረመ፣ እያስተማረ በእጥረቱ ጋርዶት አልታየው ያለውን፣ ኢየሱስ ከዛፍ ላይ ወጥቶ የነበረውን ዘኬዎስን «ና ውረድ» እያለ፣ ሕያው ዘርን ከተግባር ጋር ሲገልጽ፣ የሆነው ሁሉ የእግረ መንገድ ወይም የአጋጣሚ ይመስላል፤ በደቀ መዛሙርቱ የሕይወት ሕንፃ ላይ ግን ይህ ሁሉ ትርጉም ነበረው።

ምዕራፍ ሦስት

«ግልገሎቼን አሰማራ... ጠቦቶቼን ጠብቅ፣... በጎቼን መግብ...» (ዮሐ. 21፡15-17)። ይህ ጥቅስ ለእኛ የደረሰው ከኢየሱስ እና ከጴጥሮስ የአሳብ ልውውጥ የተነሣ ነው። ይዘቱ መንጋን በመሰብሰብ ላይ ያተኩራል፤ እግዚአብሔር በመንፈስ ሙት የሆነውን ሰው አንቅቶ ለእምነትም ሆነ ለንስሐ ሲያበቃው፣ ነቂው ሰው ወደ መንፈሳዊው ዓለም ሀ ብሎ ተቀላቅሏል። ይህም ሰው ከትንሽ ወደ ትልቅ፣ ከጥቂት ወደ ብዙ፣ ከእንጭጭነት ወደ ብስለት ይጓዝ ዘንድ ይገባል። አዲስ ኪዳን በወንጌሉ ከግልገል ወደ ጠቦት፣ ከጠቦትነት ወደ ሙሉ በግነት መድረስ እንዳለ በምሳሌ ይዘክራል። መልእክቱ በሌላው ገጽታ ሕጻናቱን፣ «የቃሉን ወተት ተመኙ»፤ እያደጉ ያሉትን ደግሞ «ጠንካራ ምግብ ይመግባቸዋል» በማለት ይዘቱ አንድ የሆነ ቁም ነገርን ያስጨብጣል። ከዚህም የተነሣ፣ ክርስቶስ ያገኛቸውን ሁሉ በአግባቡ መንከባከብ ዋነኛ ጉዳዩ ነው። ይህም እንክብካቤ ሁሌም ሁለት ገጽታን ይይዛል፤ ትሑትነት፣ አዛኝነት፣ አፍቃሪ ሆኖ ሁሌ እንክብካቤ ለሚሹ አብሮ መገኘት አንዱ ሲሆን፤ ሌላኛው እነርሱን ማስተዳደር ነው። መቼም ቢሆን ወደ ሰዎች በቀጥታ ለመድረስ ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብና እውቀት

ያስፈልጋል። እነዚህን ሁሉ አጣምሮ ሁልጊዜም በአግባቡ በማደርጀት ተንከባካቢውን ማሳደግ የማስተዳደር ሁለተኛው ገጽታ ነው።

ዮሐንስ 21:1-22

የዚህ ክፍል መቼት ሰባት ያህሉ ደቀ መዛሙርቱ በኢየሱስ ስቅለት በማግስቱ የተገኙበት ክፍል የባሕር ዳርቻ ነው፤ ምሽቱን ሁሉ በዚያ ሆነው ዓሣን ለማጥመድ ይጥሩ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ያለውን የተልዕኮ ርክክብ በእጃቸው በሦስቱ የዓመታት ውስጥ አድርሷቸው ሳለ እንዴት በዚህ ተገኙ? ይህን አጠያየቅ ከመላው ጋር በግርድፉ ለመመለስ መሞከር ተገቢ ነው።

መላ አንድ፦ የተገኙበት ስፍራ ከመነሻው ኢየሱስ ያገኛቸውን የቀድሞ የሕይወት ገጽታን የሚገልጽ ስለሆነ የሚያሳየው፤ «አሳማ ወደ ትፋቱ፣ አህያም ወደ አመድ» እንደሚሉት ሆነው ይሆናል።

መላ ሁለት፦ ለመኖር ምግብ የግድ ነው፤ ከዚህም የተነሣ ደቀ መዛሙርቱ የምግብ እጥረት ገጥሟቸዋል፣ ተርበዋል፤ ይህንንም ያለ ገንዘብ ወጪ ቶሎ አግኝተው ወደሚያስታግስላቸው ስፍራ መሄዳቸው ይሆናል።

መላ ሦስት፦ የትንሣኤው ኃይል ይገለጽ ዘንድ፣ ኢየሱስ በዚያ ተገኝቶ ያበሥራቸው ዘንድ ተገብቷል፤ ይህም የመኖር ገጽታን በመጠቀም የተስፋውን ጽኑነት ሊያዘልቃቸው የፈለገው ስፍራ ይህ ስለሆነ ይሆናል።

በዚህ ባሕር ላይ የተገኙት ሰባቱ ሰዎች፦ ጴጥሮስ፣ ቶማስ፣ ናትናኤል፣ የዘብድዮስ ሁለት ልጆች እና ሌሎቹ ሁለት ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ። እነዚህ ወደ ገሊላ ተመልሰው በጥብርያዶስ የነበሩት ዓሣን ለማግኘት ሌሊቱን ሁሉ በዚያ ሲደክሙ ነበር። መቼም እንደ እኔ ከሦስቱ መላዎች ሐቀኛ ይሆን ዘንድ አቅም ያለው የትንሣኤውን ኃይል በመገለጥ ቀጣዩ ኃላፊነት ይዘልቅ ዘንድ የደቀ መዛሙርቱም የኢየሱስም መገኘት አስፈላጊ ሆኗል የሚለው ነው። ለዚህም ማስረገጫው ደከሙ፣ ተራቡ ግን አንድ ዓሣ መያዝ አልተቻሉም፤ ያላስተዋሉት መካከላቸው የተገኘው ሰው ለጠየቃቸው ጥያቄ የመለሱት ምላሽ «ለፍቶ መና» የሚል ነበርና።

እንግዳው ግን የመጣያ አቅጣጫን አሳያቸው፣ ለመመሪያው ይሆናል-አይሆንም፣ እሺ-እምቢ የሚል ውዝግብ አንዱም አላነሣም፣ ብቻ ታዘዙ። በውጤቱም የዘረጉት መረብ በዓሣ ተሞላና ለሸክምም ለመጐተትም አስቸገረ። ይህ ድርጊት ለደቀ መዛሙርት ኢየሱስ የጠራቸውን ያንን ወቅት ሊያስታውስ፣ ሊያገናዝብም ያስችላል። ከሦስት ዓመት በፊት መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አይታልና፣ «በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደረጋች ኋለሁ» (ማር. 1፡17) ብሏቸው ነበር። እናም ያኔም አሁንም ጴጥሮስና እንድርያስ ለዚህ እማኝነት ዋንኞቹ ሆነዋል።

* * *

በዚህ የዓሣ አፈሳ ዮሐንስ እንግዳው ኢየሱስ መሆኑን ተገነዘበ፤ መረዳቱን ለሌላው መግለጽ እንደ ጀመረ፤ እርምጃ በመውሰድ ቀዳሚ የነበረው ሰው ጴጥሮስ ሆነ። ይህ ሰው ለጠመዳ ይረዳው ዘንድ ራቁቱን ነበርና ወዲያው ልብሱን ታጥቆ ወደ ባሕሩ ራሱን ጣለ። የተቀሩት ደግሞ ከዚህ ትዕይንት ራቅ ብለው ካሉበት ዓሣ የሞላውን መረብ እየሳቡ በጀልባ ያወጡ ነበር።

* * *

እንግዲያስ የዮሐንስ *21* መግለጫ የትንሣኤው ጌታ ኢየሱስ መንፈስ አለመሆኑን፣ ዛሬም በአካል ያለው መሆኑን፣ አብሮአቸው መመገብ መቻሉን፣ በስቅለቱም የተወጋበትን እጁንና ጐኑን ማቅ ረቡና ማሳየቱ የእነርሱ የሰው አጥማጅነት ፍሬያማ እንዲሆን የገለጸበት ድርጊት ነበር።

* * *

ልብ እንበለው... መረብን ያጨናነቀ ግን ያልተቀደደ፣ የሞላ ግን ያልተዘረገፈው፣ የዓሣ ክምሩ ብዛት በቦታው ተገኝቶ በነበረው ደቀ መዝሙር በዮሐንስ ሲቆጠር ስሌቱ አንድ መቶ ሃምሳ ሦስት ነበር። ለዚህ እውቅ ቁጥር ምክንያት ይኼ ነው ብሎ መናገር ያዳግት ይሆናል፤ የወንጌላትን መልእክት እርስ በርሱ ገማምደው አንድ ገመድ ሊያወጡ የቻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ግን የሚሉት አለ። ዓሣዎቹ በዚያን ዘመን የነበሩትን የዓሣ ዘሮች ሁሉ ሊወክሉ የተገኙ ናቸው፤ ይህም የወንጌልን ዓለም አቀፋዊ ባሕርይን

በመያዝ፣ ለሁሉም የሰው ዘር ውክልና ያላቸውን ሁሉ ያቀፈ ድርጊት ነው ይላሉ። እርግጥ፣ ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለሙ ሁሉ የተላኩ ሰዎች መሆናቸው ይስተዋላል።

የቤተ ክርስቲያንም በር ለሁሉም ክፍት ነው፣ የክርስቶስም ፍቅር ለሁሉ ደራሽ ነው፤ ይህም በተሰጠ ኃላፊነት ተጠያቂነትን መወጣት የሚያስችለውን የኢየሱስን ትምህርት ለማሳረጊያነት ያበቃዋል።

* * *

ምሳ ከበሉ በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?» አለው፤ ከእነኚህ ማለቱ ከዓሣዎቹ ወይም ከዓሣ ማጥመድ ሙያው፣ ወይም ለማጥመድ ከሚረዱት ቁሳቁሶች፣ አልያም ከተቀሩት ደቀ መዛሙርት ይልቅ ማለቱ ሊሆን ይችላል። ብቻ ኢየሱስ ተመሳሳይ ጥያቄን ሦስት ጊዜ ጠየቀው፤ በሦስቱም ላይ የጴጥሮስ ምላሽ አበላልጦ መናገር ሳይሆን፣ «አዎን ጌታ ሆይ፣ እንድወድህ ታውቃለህ» የሚል ነበር። የጌታም ድርሻ ኃላፊነትን በላዩ ላይ በፍቅር ማጽናት ነበር። ግልገሎችን ማሰማራት፣ ጠቦቶችን መጠበቅ፣ በጎችን መመገብ ዘላቂ ሥራው እንደ ሆነ አበሰረው። ከጥቂት ቀን ቀድሞ ጴጥሮስ ተፈቃሪውን ብቸኛውን ኢየሱስ ሦስት ጊዜ፣ «ይህን ሰው አላውቀውም» ብሎ መካዱን አልዘነጋም።

* * *

ይህ የፍቅርና የኃላፊነት ፍሰት የሚተወው አሻራ አንድን ነገር ነው። ቀድሞ ወድቆ የታየው እርሱ ነውና ጴጥሮስ ከዚያ ኋላ ሰ ዎች ደካማ መሆናቸውን እንዲገነዘብ ረድቶታል። ይህ ሰው ጠንካሮችን ሳይሆን፣ ልፍስፍሶችን ሊያገለግል ነው፤ እንደ እርሱ ከሃዲ የሆኑትን፣ እንደ እርሱ ኃጢአታቸውን ሳያስተውሉ፣ ያለ ንስሐ ሊመላለሱ የሚችሉትን ለንስሐ ሊያቀና እንዳለው ሊያይ ነው፤ ሊኖርበት። እንዲህ ዐይነት ሰው ደግሞ ከኢየሱስ ተምሯልና አጥፊዎችን ሊያጠፋ አይነሣም፤ ደካሞችን ሊተች አይወድም፤ ጎደሎ ጎናቸውን ብቻ አጉልቶ የራሱን ጽድቅም ሊገነባ አይነሣም። ኢየሱስ «ትወደኛለህን?» ብሎ ወደ እርሱ ተጠግቶ ፍቅሩን ዳግመኛ ገልጾ የሥራው አጋር እንዳደረገው ሁሉ፣ ከዚህ በኋላ ሥራው

ግልገሎቹን፣ ጠቦቶቹንም ሆነ በጎቹን በዚህ ሕይወት መቅረጽ ይሆናል።

የኢየሱስ ፍቅር የኃላፊነት እና የተጠያቂነት ምንጭ ነውና ወደ ማጠቃለያ ነጥቦቹ ልምጣ። ኃላፊነት እና ተጠያቂነት በጴጥሮስ እና በኢየሱስ ቃለ ምልልስ ውስጥ ያለው አደራ ዛሬም አለ፣ የይቅርታ ልብ እና መታደስ። ይህ ደግሞ ወገኖች ባሉት ቦታ ሁሉ ይፈጠራል፤ መፍትሔውም ቀዳሚው እውነት ነው ።

አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የኃጢአት ነቁጣ የታየበትን ወንድም አውጥተው ለጅብ ሊሰጡት ይጣደፉ ይሆናል፤ ባይጥሉት ደግሞ የወትሮውን ሰላምታ፣ ፈገግታ እና እንክብካቤ ሊነፍጉት ይችሉ ይሆናል፤ «ቅመሰው፣ ይሰማህ» በሚል መንፈስ አልያም ጸጋውን ማስተማሩን፣ መምራቱ፣ ቡድኑን ማዘመሩን ሊያቅቡት በመምከር የሚያቀኑት ይመስላቸዋል። ይህ ግን ፍቅር ስለ ጐደለውና መሰባሰብን ስለ ሰረዘ፣ ፍሬ የለውም። የኢየሱስ ይቅር ባይነት እየተራገመ አላውቀውም ላለው ጴጥሮስ የደረሰለት ፍቅር ብቻ ለተጠያቂነት ምላሽ ይሆናል።

የተገለጸ ፍቅር ባለበት ነውር እየቀነሰ ይሄዳል። መተሳሰብ ባለበት መታዘዝና መከባበር እየበረከተ ይመጣል። በሕይወት የታየ፣ በኑሮ የተመሰከረ ሕያው ወንጌል ሰዎችን ማጥመድ ያስችላል። ያኔ ደግሞ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሆነው ይተገበራሉ። ኃላፊነት ባለበት ተጠያቂነት አለ፣ ተጠያቂነት ባለበትም ኃላፊነት አለ። መወለዱም መጠራቱም ለዚሁ ነው።

ትዳር እና ወሲብ

እኔ እና ሴልዋን ሁስ ተቀራራቢ አቋም አለን። ስለ ፍቅር፣ ስለ ትጭጭት፣ ስለ ጋብቻም ሆነ በትዳር ውስጥ ሊከወኑ ስለሚችሉ ነባራዊ ክስተቶች የምናስበው አንድ ነው። በዚህ መልእክቱ ቀዳሚ የማደርገው በጋብቻ ውስጥ ሊከወን ስለተገባው ወሲብ ነው።

ወሲብ፣ ዖታዊ ተራክቦ፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም ተ

ቀራራቢ ስያሜን ስለሚይዘው የሕይወት ሂደት መልእክት አለኝ። የመልእክቱ ምክንያት ደግሞ የተሰወረ የችግር መንሥኤ በብዙዎች ዘንድ የሚከሠትበት ክልል ይኸው መሆኑን በማመኔ ነው። በትዳር ውስጥ ያሉ ባልና ሚስት የትጭጭታቸው ጣራ በጋብቻ ጥምረተ ሥጋ ይጀምራል፤ ይህ ጅምር «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን» (ዕብ. 13:4) በሚለው መለኮታዊ መርኅ ይመራ ዘንድ ይገባዋል።

በአንድ የጋብቻ ኮንፍራንስ ላይ ሴለዊን ሁስ፣ «ስለ ወሲብ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን» በሚል አነጋገራቸው፤ አብዛኛው ታዳሚዎቻቸው ሁሉ ተደናግጠው፣ ማፈራቸውን ያስታውሳሉ። እኔም ካልተጣጣሙ ቢፋቱስ ብዬ ፍቺን ሳይሆን ጥምረትን አዝላቂ አሳቤን በወሲብ ላይ አመላክቼ በመጻፌ-ሰዎች ሁሉ መከፋታቸውን አስተውላለሁ።

የፍርሐቱ እና የሥጋቱ ጠንካራ መንሥኤ «ዝምታ ወርቅ ነው» በሚለው አባባል ከመታሠር የተነሣ የመጣ ጣጣ መሆኑን ልብ እላለሁ። «ዝም አይነቅዝም»፤ «ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም» በገነነበት አገር እና ቤተ ክርስቲያን ጽኑ መፍትሔ ሳይገለጥ በመዳፈን፣ በትዳር ላይ መከራን ሊያመጣ እንደሚችል ልብ የሚል ልብ እንዲለው የተመጠኑ ነጥቦችን አነሣለሁ።

አንዲት የሴልዋን ሁስ ተመካሪ በትዳሯ ላይ ያንዣበበውን ሥጋት አውርታ እንደ ጨረሰች፣ ሁስ፣ «ወሲብን መብራት ሳለ ትፈጽማላችሁን? ወይስ...» ብለው ጠየቋት፤ ምላሿ «ወሲብማ ምን ጊዜም በጨለማ ሊፈጸም ይገባዋል፣ ሌላው ቢቀር በዚህ ጊዜ ለእግዚአብሔር ተጋልጬ በብርሃን ልታየው ፈጽሞ አልፈልግም» የሚል ምላሽ ሰጠች። ይህን እምነት ብዙዎች ይጋሩታል፣ «ልክ ነዋ!» ብለውም ይስማሚታል። ይህ ግንዛቤ በሰፋበት ስፍራ ችግር መኖሩ አይቀሬ ነው።

ይልቁኑ፣ ወሲብን በሚመለከት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተባሉትም በዘመናቸው የጻፏቸውንም ከግምት ማግባት ይኖርብናል። አሪገን ኃጢአት ከገባ ወዲህ አዳም ስለ ወሲብ ተረዳ እንጂ፣ ከውድቀት በፊት እንደዚህ ዓይነት ጣጣ አልነበረም ይላል። ጀሮምም ወንድ ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው፤ ትዳር ጸሎትን

በማድከም መንፈሳዊነትን ዝቅ በማድረጉ አሉታዊው ተጽዕኖው ብዙ ነው በማለት ደርሷል። እኒህንና መሰል በታሪክ ውስጥ የተ ፈጸሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ አመለካከቶች ዛሬ ላይ ዳብረውና ነግሠው በትዳር ውስጥ ሊተኩሩ የሚገባቸውን ጽኑ እውነቶች እንዲሸሹ ወይም ኖረው እንደሌሉ እንዲቆጠሩ ምክንያት ሆነዋል።

እግዚአብሔር ግን ከጠዋቱ፣ «ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጠ ረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው እግዚአብሔርም ባረካቸው ... ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት... አላቸው» (ዘፍጥ. 1፡27-28)። ከዚህ በመነሣት፣ ከውድቀት በፊት ትዳር መኖሩ፣ መዋለድም በበ ረከትነቱ መታዘዙን፣ መባዛትም ከወሲብ ውጤቶች አንዱ መሆኑን እንገንዘብ።

ይህንን ሀቅ አቶ ዳታን ወዳጆ *በዘላቂ ትዳር*፣ አቶ ሣህለ ጥላሁን *ጋብቻችሁ* በሚል ድርሰታቸው፣ ቲም ላሄይም *"How to be Happy through Marriage"* በሚል ድርሳናቸው በጋራ የመሠከሩት፣ በወሲብ ጉዳይ ላይ የዕውቀት ማነስ አለ፣ ይህ ደግሞ አደጋን ይጋብዛል በማለት መረጃዎቻቸውን አደልበዋል።

ከመረጃዎቹ ተጠቃሽ ከሚሆኑት ጥቂቶቹ ሚስቱን እርቃኗን ለማየት የማይፈልግ፣ በፍቅር ጨዋታ ጊዜ «ቀስቃሽ» አካላት መኖራቸውን ያልተረዳ፣ መጥፎ ጠረን ግንኙነትን እንደሚያዳክም ያልተገነዘበ ባል የመኖሩን ያህል፣ የወር አባባ የመምጪያና መሄጃ ወቅቶች የስሜት መረበሽን እንደሚያስከትሉ ያልተረዳች፣ በከፊል እርቃንነት ወይም ገላን ገላጭ ስስ ልብሶች የወንድን ስሜት መቀስቀሱን ያልተገነዘበች፣ በግንኙነት ወቅት መርካት ድርሻዋ መሆኑን የማታወቅ ሚስት መኖሯን ማነሣሣቱ ተገቢ ይመስለኛል።

እነዚህን ተጠቃሾች በአግባቡ አለመረዳት ደግሞ ችግር ጠሪ ነው። እስቲ ሁለት ሦስት የችግር ናሙናዎችን ከነመፍትሔዎቻ ቸው ዘክሬ ቀሪውን እናንተው ትማከሩበት ዘንድ ለእናንተው ልተ ው።

ናሙና ቁጥር አንድ

ባልና ሚስቱ ልጆችን አፍርተዋል፣ በፍቅርም ተሣሥረው ይኖራሉ፤ በዚህ መኖር ውስጥ ለሚፈጸሙ የወሲብ ግንኙነቶች ግን

ሚስት ደስተኛ ሆና አታውቅም፣ ደስታ ያጣችው ከባለቤቷ የአፍ ጠረን መከርፋት የተነሣ ነው። አፉ በድን በውስጡ ያለ ያህል ይሸታል፤ ይህ ክርፋት የስከነ የፍቅር ጊዜን ከምትወደው ባሏ ጋር አላመጣም። ይህን ችግር አትናገርም፣ ግን ትነጫነጫለች። የጋራ ስኬታማ ፍቅርን ትመኛለች፣ ያንን ግን ሁለቱም አይተውት አያውቁም። ከስድስት የትዳር ዓመታት በኋላ ግን ሚስት ችግሩን ለጋብቻ አማካሪ አደረሰች። ችግሩ በጋራ ይፈታ ዘንድ ባል ታዳሚ ሆኖ በጋራ ተወያዩ። በውጤቱ ባል የአፉ ጠረን መከርፋት መንሥኤ የሆነውን ያውቅ ዘንድ ውሎውን ከሐኪሞች ጋር አደረገ። ለሽታው መንሥኤው አንዲት መንጋጋ ነበረች። ይህ ጥርስ በስብሶ መፈራረስ ይዟል፤ እርሱ በሐኪሙ ተነቀለ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ክርፋቱ ከተበላሸው ጥርሱ ጋር ባልን ትቶ ሄደ። ከዚያ በኋላ ስላላቸው ግንኙነት ባልና ሚስቱ ሲመሰክሩ፣ «በእውነትም የእግዚአብሔር የሆነውን ስጦታ በአግባቡ ሳንጠቀምባቸው ያለፉት ዓመታት ይቆጨናል» የሚል ነበር።

ናሙና ቁጥር ሁለት

ባልና ሚስቱ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ገና ዳዴ እያሉ ነው፤ ዓመት አልሞላቸውም። የባል የዘወትር የፍቅር መግለጫ «በእውነት፣ ሁሌም እውድሻለሁ» የሚል ቃል መቸር ነው፤ በዚህ አገላለጽ ሚስቱ ሁሌም ደስ ይላታል፤ በደስታዋ ላይ ግን ጎዘን ገብቶአል፤ ያም ባል በመሸ ቁጥር ወሲብ መፈጸምን ይፈልጋል፤ መፈለግ ብቻ አይደለም ይፈጽማልም። ይህ ሰው ግላዊ እርካታን ካገኘ በኋላ ቶሎ በመነሣት ቴሌቪዥን ይከታተላል፣ መጽሐፉን ያነብባል። ይህ የድግግም ድርጊቱ ዛሬ ላይ ትካዜን አኑሯል። የሚስት ሰቆቃ ለባል ሳይደርስ ለወንድሟ በመድረሱ እኔም መስማት ቻልኩ። በእኔ አቅም መፍትሔ አለኝ እላለሁ። በወንድና በሴት መካከል የወሲብ ዝግጅት ይለያያል፤ የወንድ ፈጣን ነው፤ ለተግባር ይጣደፋል፣ ቶሎም ይተነፍሳል፤ የሴት ልጅ ዝግጅት የወንዱን ችኮላ አይወድም፣ ጥቂት ዘግይቶ ከጣራው ይደርሳል። ይህን ግን ይጣጣም ዘንድ ኃላፊነቱ ለወንድ የተተወ ነው፤ ሚስትን በፍቅር ጉዳይ ከጠዋቱ ማዘጋጀት መፍትሔን ያመጣል። በመኝታ ወቅት የፍቅር ቃላትና የሙቀተ-ፈንጠዝያ ንኪኪ በቀዳሚነት

ይጠበቃል። ከዚህ ክንዋኔ በኋላ መቀራራቡ ይደምቃል። ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን ሴትን እንደ ዕቃ የሚያስቆጥር የድፍረት ሥራ ሆኖ መቀራረብን ሳይሆን መራቅን፣ መፈቀርን ሳይሆን መጠላላትን ያመጣል፤ «እወድሻለሁ» የሚስትን የፍቅር መብት በመጠበቅ ሊገለጽ ይገባዋል።

ናሙና ቁጥር ሦስት

ባልና ሚስቱ አንድ ወንድ ልጅ አላቸው። በትዳር አራት ዓመታትን አሳልፈዋል። በወሲብ ወቅት ባል ትኩረት ያልሰጣቸው የግድ የለሽነት ተግባራት አሉት። ጥርሶቹ ጽዳት አያውቁም፣ እግሩ ይሸታል፣ ላባም ነው፤ ጥቂት ሙቀት ሰውነቱን ያቀልጠዋል፤ ጢሙን አይላጭም፤ እኒህን ሁሉ እንደ ያዘ አብሮአት ይተኛል። እኒህን ያስተካክልላት ዘንድ በእርጋታ ነግራዋለች። በልምምጥ ዓይንም እባክህ ብላዋለች። ባል ደስ ባይሰኝም ፈቃደኛ ነው፤ ፈቃዱ ግን እሺ አደርገዋለሁ ከማለት አላለፈም። ነገም ጥርሱ፣ እግሩ፣ ብብቱ፣ ጢሙም ያው ነው፤ ይሸታሉ፤ ይሻክራሉ። ሚስቱ ዛሬ ለሌላ ልጅ እየተዘጋጀች ነው፤ በዚህ ዝግጅት ውስጥ እርሷ ልጆችን አተረፈች እንጂ ፍቅርን አላሳደገችም። ከጋብቻቸው ቀን አንሥቶ እስከ ዛሬ በመኝታ ቤቷ ክፉ ሽታ ያልጠፋበት በመሆኑ እግዚአብሔር በትዳር ውስጥ ባዘጋጀው የወሲብ ስጦታ ውስጥ ተደስታ አታውቅም። እንደ እኔ ትዳሩን ለመታደግ መፍትሔው ቁርጠኝነት ነው፤ ቁርጠኝነት ለንጽሕና፤ ጥርስ ብሩሽ፣ ወይም መፋቂያ፣ ጢሙን መላጫ ወይም ማለስለሻ፣ የእግር ላብ ማድረቂያ ወይም በየዕለቱ እጥበት፣ ሽቶ ወይም ዶደራንትን ለመጠቀም መወሰን አስፈላጊ ነው። ይህን ታዝዞ ሚስቱን ለማስደሰት ያልተ ዘጋጀ ባል ደስታን በሙልአት እንዳጣ እና እንዳሳጣ ይኖራል።

እነዚህ በቅደም ተከተል ያነሣሣኋቸው የግንኙነት ችግሮች ሊታ ረሙ እንደሚችሉ ጽኑ እምነት አለኝ፤ ለማስተካከል የሚወስደው እርምጃ ችግሩን ማወቅን ከዚያም መፍትሔዎቹን ሳይውሉ ሳያድሩ መተግበር ነው። በትይዩ ግን ክትትልንና ጊዜን ጠያቂ የሆኑ የወሲብ ጉዳዮችም መኖራቸውን ልብ ብንል ጥሩ ነው። አሁንም ባሎች ላይ ሊገጥም ከሚችለው ሁለቱን ልዘክር፦

አንደኛው፣ የባሎች ጊዜ ቀድሞ መርጨት ነው። ለወሲብ ጽኑ ጉጉት ያደረበት ባል አካሉ በደም ተሞልቶ ይወጠራል፤ ውጥረቱን ከሚስቱ የመርኪያ ጊዜ ጋር ለማጣጣም ሳይበቃ ወይም ከግንኙነት በፊት ዘሩን ይረጫል፤ አልያም የግንኙነት የመነሻ ደቂቃዎች ላይ ፈቃደኝነቱን ጥሶ ይፈሳል። ይህ ክስተት ባልንም ሆነ ሚስትን አያስደስትም፤ የግንኙነት ጣራ ምሉዕነት ሊኖረው የሚገባውን የጥምረት ሂደት ያዛባ ስለሆነ በወንዱ በኩል ያለመብቃት ስሜትን፣ በሴቲቱም በኩል የፍቅር መቋረጥን በማስከተል ግርታን ያመጣል። ይህም ግን የመፍትሔ ተስፋ አለው፤ ግልጽነትና ቀና ውይይት የማሸነፊያው ጅማሬ ነው። ያለ ጊዜው የሚሆን እፎይታ ጊዜው ረዝሞ አግባባዊ ዖታዊ ግንኙነትን ለመፍጠር ባልና ሚስት ኃላፊነት አለባቸው፤ በጋራ የስጦታ ጉዳይ ላይ «የእርሱ ወይም የእርሷ ችግር ነው» ተብሎ አይቆምም።

የጠቢቡ ሰለሞን የመኃልይ መኃልይው «ግራው ከራሴ በታች ናት፣ ቀኙም ታቅፈኛለች» (2፡6) የመነሻ ተግባር ሊሆን የሚችል ይመስለኛል። ባል በዚህ አስተቃቀፍ ለሚስቱ ያለውን ፍቅር በቃል ይገለጽላት ዘንድ ያወያያት፣ ያማክራት ዘንድ ይመቻል። በዚህ ቃል ልውውጥ ሰውነት ቢሞቅ ቢወጠር ለግንኙት ባለመቸኮል መዘግየትን መምረጥ እና ይህን በድግግም በስምምነት ማድረግ በጐ ውጤትን ያስከትላል፣ የደም ሥሮች ጠንካራ ሆነው ተፋጥነው እንዳይፈቱ ያግዛል። በተመሳሳዩም፣ ሚስት በሚሆነው ሁሉ ብርታትን በመስጠት፣ ተስፋን በመሙላት፣ ሊስተካከል መቻሉን በማብሰር ለባሏ ያላትን ለመስጠት የተግባር ሰው ከሆነች መፍትሔ ው በቅርቡ የሚገኝ ይሆናል። በንጽጽሩ፣ ባልም እየጨመረ ሊመጣ ያለውን የባለቤቱን የፍቅር ስሜት ለመቀት ፈንጠዝያ ምክንያት በሚሆኑ የፍቅር ቃላትንና ንኪኪን በመጠቀም በጋራ ዕረፍትን ማምጣት መቻሉን ልብ ሊሉት ይገባል።

ሁለተኛው፣ በባሎች ዘንድ ሊከሠት የሚችል ችግር ስንፈተ ወሲብ ሊሆን ይችላል። የወንድ ብልት የመወጠር አቅም ሳይኖረው እንደ ተልፈሰፈሰ ሊቀር ይችላል። ይህ ሁኔታ ሊፈጠር ከሚችልባቸው መንሥኤዎች ጥቂቱ የሥራ ጫና፣ ጭንቀትና በአእምሮ አለመረጋጋት በዘላቂነት በሚኖርበት ጊዜ ይከሠታል።

ከዚህም ሌላ፣ ከሴት ጋር የሚደረግ ግንኙነትን በማቀብ በገዛ ዘዴ ዘርን በማስፈሰስ የተለያዩ ሙከራዎችን በማድረግ የከረመ ባል ለስንፈተ ወሲብ ይጋለጣል። ባልና ሚስት በትዳር ሕይወታቸው ይህ ሲከሰት ትዕግሥት ተጠሪ ሊሆን ይገባዋል። የሚስት ትይዩ ድርሻ በዚህም ሁኔታ ውስጥ እንደምትወደው የሚያበስር ቃሏን በተ ግባር ማጽናቱ መፍትሔን ለመጋበዝ ፈጣን የውጤት ድርሻ አለው። ባልና ሚስት ዘርፈ ብዙ በሆኑ ጉዳዮቻቸው ሁሉ ሰፊ ውይይትን በማድረግ መዝለቁ ይህ ችግሩን ሊቀርፍ አስቻይ ነው።

ሳጠቃልል፣ በዚህ ጽሑፍ ልል የምፈልገው ቁም ነገር አንድን ጭብጥ ብቻ ነው። ብዙዎች በትዳራቸው የሚገጥሙአቸውን ችግር ተብዬዎች የሚያያይዙት ከበርካታ ሌሎች የችግር መንሥኤ ከሚመስሉ ግን ካልሆኑ ገጽታዎች ላይ ነው። በወሲባዊ ጉዳይ ላይ ሊነሡ የሚችሉትን አብዛኞቹ ሊናገሯቸውና ሊወያዩባቸው አይፈልጉም፤ «ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም»ን ወይም «ዝምታ ወርቅ ነው» በሚለው ዝግ ምሳሌ የብዙዎች ትዳር ተዳፍኗል፤ ሕይወት ይዘራበት ዘንድ ሲገባው በሞት ውስጥ አድሯል። በትዳር ውስጥ የሚፈጸም ወሲብ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ባለመ ረዳት መከራረም ጎጆን አጨልሞ ለማያስፈልግ ውዝግብ፣ ጥላቻ እና ፍቺ በማድረስ ሰንካላነትን በሁሉ አቅጣጫ አሳይቷል። እናም እኔም ሆንኩ *(Marriage as God Intended)* ደራሲ ሴልዋን ሁስ በጋራ የታመንበት እውነት፡- እግዚአብሔር ያጣመረውን ችግር አይለየውም የሚል ነው።

ክርስትና እና እስልምና

«ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ የለውም፤ ወልድን የሚያምን ሁሉ አብም አለው» (*1ኛ ዮሐንስ 2:23*)።

ርእሴን እንዲህ ያልኩት በዓለም ላይ በመገለጽ ክርስትና ቀድሞ እስልምና ኋላ ላይ የመጣ ስለሆነ ነው። እነዚህ ሁለት ሃይማኖቶች በዓለም ላይ ካሉት ከ6 ቢሊዮን ሰዎች ብዙዎቹ የተከማቹባቸው የእምነት ዘርፎች ናቸው። የየቁጥራቸው የትየለሌ በመሆን

ክርስትና እንደ ቀድሞው ቀዳሚውን ስፍራ ሲይዝ፣ እስልምና በዓለም ላይ ካሉት ሃይማኖቶች ውስጥ የሁለተኛነቱን ድርሻ ይወስዳል።

እርግጥ፣ የየቁጥሩ ብርካቴ በውስጡ ያሉትን ተከታዮች ለሃይማኖታቸው ቀናኢነታቸውን ወይም አምነውበት መከተላቸውን አያረጋግጥም። እንዲያውም ቢሆን ግን፣ በዓለም ላይ ብዙ ተከታይ እንዲሁም ጠንካራ የእምነት እንቅስቃሴ ከሚካሄድባቸው ሃይማኖቶች አብዛኛዎቹ አሁንም እነርሱው ናቸው።

እነዚህ ሃይማኖቶች ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ የነበራቸው የአማኝ ብዛት፣ ተከታዮቻቸው ያላቸው ወኔያዊ ስሜት፣ በታሪክ ውስጥ ተገጣጥመው ያሳለፏቸው ግጭቶች እና ጦርነቶች ብዙ ስለሆኑ፣ ማንም በስማ በለው ብቻ ብድግ እያለ የሚዘልፋቸው አይሆኑም፤ ሆኖ ቢገኝ ግን መቀያየምን፣ መጠላላትን፣ መወጋጋትን ያመጣል። ይልቅስ፣ ክርስትና እና እስልምና በአንድ የሚፈረጁበት ርእሰ ጉዳዮች አሏቸው፤ የሚለያዩባቸው መሠረታዊ መለያያዎችም እንዲሁ አሏቸው። እነርሱን በማወቅ፣ ያንንም በመረዳት በአግባቡ ለመግባባት የዚህ ጽሑፍ ዓላማዬ ይሆንልኛል።

ስለዚህ ደግሞ የመስከረም አንድ መንደርደሪያውን ያቀብለኛል። በአሜሪካ ለተፈጸመው ጥቃት በርካታ ጥያቄዎች ተነሡ፤ ምላሽ አለን የሚሉ ምሁራንና መንፈሳውያን ሰዎች በየጊዜው መልስ ሊሰጡ ሞከሩ፤ የእነርሱ ቃለ ምልልስና መግለጫም የዚህ ጽሑፍ ሥራ መነሻ ነው። አንዳንዶች የእስልምና መሥራች የሆኑት ነቢዩ መሐመድም ሆነ የክርስትና መሠረት ጣይ ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርታቸው ያስጨበጡት ቁም ነገር የጋራቸው ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር የሚደርሱበትን መንገድ ነው፤ የዚህም ወጤት ደግሞ ልዩነትን ለማግነን ሳይሆን፣ ለማቀራረብ ረጂ ነው ሲሉ፣ በትይዩ ደግሞ በዋሽንግተን የብሔራዊው ካቴድራል ኃላፊ ናታን ባክስተር ጥቃቱን በተመለከተ ለተሰበሰበው ጉባኤ፣ «የአብርሃም አምላክ፣ የመሐመድ አምላክ፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሆይ፣ ጸሎታችንን ስማልን» በማለት ጸልየው ሕዝቡን አሜን አሰኝተው ወደ መቀመጫቸው ተመልሰዋል። ክርስቲያኖችንም ሆነ ሙስሊሞችን በጋራ ለመያዝ የጣረ ልመና ነው፤ አጢኖ ላየው

ሁለቱንም የለያየ ተሰሚ ያልሆነም ጸሎት ሊሆን ይችላል።

ለአለያዩ ደግሞ በቂ ምክንያት ያለ ይመስለኛል። መቼም ቢሆን ሐቀኛ ሙስሊም እግዚአብሔር የኢየሱስ አባት እንደማይሆን ያምናል፤ ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆኑንና የዓለም ገዢ መሆን እንደማይችልም ይረዳሉ፣ ለዚህ ደግሞ ነቢዩ ይህን ኑፋቄ እምነት የሚያስተናግዱ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ አፋቸውን ከፍተ ዋልና ኃጢአተኞች ሆነው እንደ ቀሩ አስተምረዋል። በትይዩም ሐቀኛ ክርስቲያን የነብዩን እግዚአብሔር ከራሱ እግዚአብሔር ጋር አንድ ነው ብሎ አይቀበልም። አስተምህሮተ ሥላሴ የእምነቱ መሠረት መሆኑን ስለሚያምን፣ የኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅነት በሙሉ ልቡ ይቀበላል።

በዚህ ዝግጅት እኔ እንደ አመቻማቹ ናታን ባክስተር ሁለቱን አቅፋለሁ ብለው ሁለቱንም ግራ የሚያጋቡበትን ዐይነት የአመለካከት እርምጃን አልራመድም። በምትኩ ግን ሁለቱም ሃይማኖቶች ሳይዘላለፋ፣ ሳይገዳደሉ ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር ሁሉም ማሰብ መርጎ ሆኖ እንዲገኝ ለእውቀት የሚያግዙ የጋራ ነጥቦችንና የተናጠል የመለያያ ጉዳዮችን አሳያለሁ። ለዚህ ደግሞ መንደርደሪ ያዬ የጋራ ሀብቶቻቸውን አስቀድሞ ማሳየት ነው።

ሁለቱም ሃይማኖቶች የጣዖት አምልኮን ይቃወማሉ፤ ሁለቱም አንድ አምላክን ብቻ ይቀበላሉ፤ ሁለቱም በሁሉም ውስጥ አምላክነት በከፊል ወይም በሙልዓት ይገኛል የሚለውን ትምህርት ይጸየፋሉ፤ ሁለቱም ሁሉን የሚገዛው አምላ ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ጅማሬና ፍጻሜ የሌለው መሆኑን ያምናሉ።

ክርስትናም ሆነ እስልምና ፍጥረት በዝግመተ-ለውጥ ወይም በአቦሰጥ በአጋጣሚ እንደ መጡ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር እንደ ተገኙ ያምናሉ። ማኅበራዊ ሕይወትንም አስመልክቶ በሁለቱም ዘንድ ተመሳሳይ የሆኑ የጋራ አቋሞች አሏቸው። የ «World» መጽሔት አዘጋጅ ማርሺን አላሲሲ በጥናቱ እንደ ዘገበው፣ «እስልምና ግብረ ሰዶማዊነትን እና ውርጃን አጥብቆ ይቃወማል፤ በሥራ መስኮቻቸውም ታማኝነት የኑሮ መሠረት መሆኑንን በማመናቸው የሚዛን ላይ ስርቆት፣ የሜትር ላይ ቅንጣቢ፣ «ፎርጅድ» የሆኑ የግብይት አቅርቦቶችን ለገበያ አያቀርቡም፤

በእነዚህም ከክርስትና መሠረተ እምነት ጋር አንድ ነው» ብሎ ጽፏል።

እንደዚህም ቢሆን ግን የሚለያዩበት መሠረታዊ ነጥቦች አሏቸው። በእግዚአብሔር ጉዳይ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት፣ እንዲሁም የዘላለም ሕይወት የማግኛ መንገድ ላይ ሃይማኖቶቹ ይራራቃሉ፤ ላይገናኙም ይለያያሉ።

እግዚአብሔር

በቅርቡ በአንድ ዩኒቨርስቲ የተገኙ ሙስሊም ለተማሪዎቹ ስለ እምነታቸው መግለጫ ሰጡ። በርካታ ክርስቲያኖችን እንደሚያስተናግድ ከሚታመንበት ከዚህ ተቋም በርካታ አድማጮች ለሙስሊሙ አድናቆታቸውን ቸሩ። እስከ ዛሬ ድረስ እንደ ተለያየን ቆጥረን መራራቃችን ተገቢ አልነበረም። ሙስሊሞች በቀን አምስት ጊዜ ጸሎት የሚያደርሱለት አምላክ በምሕረት የተሞላ፣ ድንቅ ጌታ፣ እንዲሁም እኛ ዛሬ የምናገለግለው ራሱ ነው ወደሚል ድምዳሜ ደርሰዋል። ግና ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች የሚያመልኩት እግዚአብሔር አንድ አይደለምና የተማሪዎቹ ማጠቃለያ ትክክል አይደለም። ክርስትና እግዚአብሔር በመለኮት አንድ በአካል ግን ሦስት መሆኑን ያምናል-አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ። ይህም እምነት ለክርስቲያኖች ሦስት እግዚአብሔር እንዳለቸው አያመለክትም።

እስልምና ግን በአንድ እግዚአብሔር ቢያምንም፣ ክርስቲያኖች የሚያመልኩትን ግን አይደለም። ነቢዩ መሐመድ ከሚቃወሙት ዐቢይ ጉዳይ አንዱ የኢየሱስን የዘላለም የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ነው። ይልቁኑ፣ እግዚአብሔር ነው የሚለው አስተምህሮ አላህን መስደብ ነው ይሉለታል። እስልምና መንፈስ ቅዱስንም ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አይመለከትም። ይህንን የሚያራምዱትንም በቁርዓን 5:72-75 እንደ ተጻፈው የገሀነም ፍርድ ይገባቸዋል። አንድ የሙስሊም ጸሐፊ አስተምህሮተ ሥላሴ አላህን ከኢየሱስ ጋር እኩል ስለሚያደርግ፣ ተከታዮቹ ፍርድ ሥር ናቸው በማለቱ ያተተበትን ሰነድ ለዓለም በትኗል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ነቢዩ መሐመድ እግዚአብሔር ያለለት

ምንም የለም፤ ስለ ኢየሱስ ግን እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ በኃያል ቃል ሁሉን ደግፎ ይዟል (ዕብ. 1:3) ተብሎ ተጽፎለታል፤ ይህ መለያ ነው።

ይህን በመረዳት አንድነትን ወይም መመሳሰልን የሚያበስሩ አስተማሪዎች እና ጸሐፊዎች ቢኖሩ፣ ማለታቸው ፖለቲካዊ ይዘት ላለው ጉዳይ ማራመጃ ሊያገለግል ካልረዳ በቀር፣ ኢየሱስን ያላካተተ ምንም ዐይነት ክርስቲያን - መሰል ትምህርትም ሆነ ጸሎት እርባና ቢስ ነው።

በ2002 መስከረም (እ.ኤ.አ) መጨረሻ ላይ በያንኬ ስታዲየም በሽብርተኞች ስላለቁት ሰዎች በተካሄደው የሃይማኖት መሪዎች የጸሎት ጉባኤ ላይ ብዙ ክርስቲያኖች በጸሎቶቻቸው የኢየሱስ እንደ ሆኑ አልገለጹም፤ በኢየሱስ ስም ብለውም ጸሎታቸውን አላሳ ረጉም። ይልቁኑ፣ ለማርያም ታላቅ ምስጋና በዝማሬ ቀርቦ ‘‘Ave Maria’’ እየተባለ፣ በትይዩ ግን ክርስቶስን ያገነነ አንድም ቃል አልነበረም። ይብሱኑ፣ ደምዳሚው ቁስ፣ «የሰላም ልዕልት ማርያም ሆይ፣ ስለ እኛ ጸልዪልን» በማለት ነው የጨረሱት። እኛ ከክርስቲያኑ ጐራ እንዳሉ ራሳቸውን ያስቆጠሩት ሰው ስለ ክርስቶስ ግን ማንሣትን አልፈለጉም።

በዚያው በጆማ ስብሰባ ግን ተረኛው ሙስሊም እየደጋገመ መሐመድ የአላህ ነቢይ ነው ‘‘Mohammad is the Prophet of Allah’’ ይል ነበር። ይህን ለማለቱ ቅንጣት ሥጋት አልነበረውም፤ ድፍረቱና እምነቱ የሚገርም ነው፤ ከሽብሩ ተካፋዮች ከፊሎቹ ሙስሊሞች መሆናቸው እየታወቀ፣ ሳይሰጋ ማወጅ በእውነትም ያስገርማል። በንጽጽሩ ግን፣ የክርስቲያኑ ጎብረተሰብና መሪዎቹ በኢየሱስ ላይ ገለልተኛ መሆናቸው አሳሳቢ ነው። እንደ ክርስቲያን ጸሎት ሊሰማ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር አብ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ በተቀረበ ጊዜ ነው፤ በዚህ ያልተባበረ እምነት ሁሉ ወደ የየራሱ መታመኛ ጸልዮአልና መልእክት የተላከለት እግዚአብሔር የተለያየ ሆኗል።

ኢየሱስ ክርስቶስ

ሙስሊሞች ኢየሱስ በተአምር ድንግል ከሆነች ሴት መወለዱን

ያምናሉ፤ የተወለደው ኢየሱስ ነቢይ መሆኑንም ይቀበላሉ፤ በተ
ወሰነ ደረጃም ኢየሱስ መሢሕ መሆኑን ይረዳሉ፣ የማይጥማቸው
የእግዚአብሔር ልጅነቱ ደግሞም መለኮታዊ ባሕርይ ያለው መሆኑን
መስማት ነው።።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለ መሆኑ
ከኢየሱስም ሆነ ከደቀ መዛሙርቱ ያገኘውን መረጃ ሁሉ ተጽፎ ተ
ቀምጧል።። ሙስሊሞች ይህን በተመለከተ የሚሉት አለ።። ያም
መጽሐፍ ቅዱስ በረጅም የጊዜ ሂደት ውስጥ ተቀይጧል፤ ተዛብቷ
ል፤ ከዚህም የተነሣ ኢየሱስን በተመለከተ የመጨረሻው መተ
ማመኛ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ቁርዐን ብቻ ነው ይላሉ።።

እስቲ ልብ እንበል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እኮ ኢየሱስን
በግላቸው ያውቁት የነበሩ ናቸው፣ የእርሱን ድርጊትና ትምህርት
በዓይናቸውና በጆሮአቸው የቀሰሙ ናቸው።። እነርሱ ደግሞ ያዩትንና
የሰሙትን ኖረው የጻፉ ናቸው።።

ነቢዩ መሐመድ ግን ይህ ከሆነ ከ600 ዓመታት በኋላ የመጡ
ናቸው፤ ኢየሱስን ፈጽመው አያውቁትም፣ አላዩትም፤ እንግዲያስ
በቅርቡ የነበሩ ይታመኑ ወይም ያልነበሩ ይገምቱ።።

ሐዋርያው ዮሐንስ ከተቀሩት ሐዋርያት ሁሉ በተሻለ ሁኔታ
ለኢየሱስ የቀረበ ሰው ነበር።። ይህ ሰው ኢየሱስ እኔና አብ አንድ
ነን በማለቱ ያኔም ጠላቶቹ እግዚአብሔርን እንደ ተሳደበ ቆጥረው
ወነጀሉት (አንተ እኮ ሰው ብቻ ነህ) አሉት (ዮሐ. 10፡30-33)።።

«አይሁድም ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም ስለ ስድብህ።።»
ኢየሱስ ግን ክሱን ሙታንን በማስነሣት፣ አምልኮን በመቀበል ሻ
ረባቸው።። ቶማስም «ጌታዬ አምላኬም» በማለት መሰከረ (ዮሐ.
20፡28)።። ዮሐንስ የመጽሐፉን ዓላማም ሲገልጽ፣ «ኢየሱስ እርሱ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም
በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል» (ዮሐ. 20፡31)
ነበር ያለው።። ጥንትም ሆነ ዘንድሮ ብዙዎች ኢየሱስ የእግዚአብሔ
ር ልጅ መሆኑን ያምናሉ።። በዮሐንስ ዘመን ኢየሱስ በማስተማሩ
እና በርኅራኄው የበረታ የታሪክ ሰው እንጂ፣ እንደ ማንኛችንም
ሰው ነው ያሉ አሉ፤ ልክ ከልደቱ ከ600 ዓመታት በኋላ ነቢዩ
መሐመድ እንደ ገለጹት።። ኢየሱስን ሰው ብቻ አድርጎ መረዳት ግን

መናፍቅነት መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል፣ «እውነትን የምታውቁ ስለ ሆናችሁ፣ ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታወቁ እንጂ እውነትን ስለማታውቁ አልጽፍላችሁም። ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም» (1ኛ ዮሐ. 2:21-23፤ ድ.ት.) በማለት አረጋግጧል። እንግዲያስ ኢየሱስን ከእግዚአብሔር አሳንሶ ማሰብም ሆነ ማመን የሐሰተኛው ክርስቶስ ፈለግ ተከታይ መሆን ነው።

የዘላለም ሕይወት

«ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል» (1ኛ ዮሐ. 4:15፤ ድ.ት)።

«እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ፣ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም» (1ኛ ዮሐ. 5:11-12፤ ድ.ት)።

«የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቦናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፣ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» (1ኛ ዮሐ. 5:20-21፤ ድ.ት)።

ክርስትና ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን፣ ሞቱ እና ትንሣኤ ውም የምሕረት ማግኛ እና የዘላለም ሕይወት ዋስትና መሆኑን ያምናል። የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት በኃጢአት ለረከሰው የሰው ልጅ ምትክ መሆኑን፣ ትንሣኤውም በእርሱ ይታመኑ ዘንድ ለረዳቸው ከሞት ወደ ዘላለም ሕይወት መሸጋገሪያ መሆኑን ያበስራል። ድነትም ያለ ድካም እግዚአብሔር በክርስቶስ በሠራው ሥራ ለሰዎች የመጣ ጸጋ መሆኑን ያምናል።

እስልምና ግን እንዲህ አይደለም። አንድ ሙስሊም እንደ ጻፈው፣ እስልምና ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን፣ እግዚአብሔርም ኢየሱስን ለሰዎች ስለ ኃጢአታቸው እንደ ላከው አያምንም በማለት

ዝርዝር ድርሳን ደርሷል። በሐተታውም፣ ኢየሱስ በመሠረቱ አልሞተም፤ ጠላቶቹ ያዝን ብለው የሰቀሉት ሌላን ሰው ነው፣ ኢየሱስ ግን በዚያን ሰዓት ወደ ሰማይ ዐርጓል፣ ከዚህም የተነሣ ስለ ኃጢአት ሞተ፣ ሞትንም አሸነፈ የሚባለው የተረት ተረት ነው ብሎታል።

ይህ ትምህርቱ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ይጣረሳል። ጳውሎስ፣ «ነገር ግን ገና ኃጢአኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል» (ሮሜ 5፡8) በማለት ያስተምራል። እስልምና የዘላለም ሕይወት ማግኘው መልካም ሰው ሆኖ መገኘት ነው፣ ሰው በመልካም ሥራው ቢተጋ ይድናል ይላል። ይህ ግን ሰው ሁሉ በኃጢአቱ እንዳለ አለመቀበል ነው። ክርስትና ሰው በኃጢአት መጸነሱንም ሆነ መወለዱን ያምናል፤ ክርስትና የእምነት አባቶችም እንኳን በኃጢአት ውስጥ እንደ ነበሩ ያረጋግጣል። ኖኅ በስካሩ (ዘፍጥ. 9፡21)፣ አብርሃም በውሸቱ (ዘፍጥ. 20፡2)፣ ዳዊት በዝሙቱና በግድያው (2ኛ ሳሙ. 11) ሁሌ ይነሣሉ። እስልምና ግን እኒህን ነቢያት በኃጢአት አይወቅስም።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሰውን ባሕርይ ሲገልጽ ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት በኃጢአት የወደቁ እና ራሳቸውን ማዳን የማይችሉ እንደ ነበሩ ገልጿል። የዘላለም ሕይወት ምሥጢራቸውም በጐ ሥራቸው ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ መታመናቸው ብቻ መሆኑን አስ ረድቷል።

እስልምና ለዘላለም ሕይወት መሠረቱ አምስቱ ዐምዶች ናቸው ይላል። እነርሱም፡-

1. ነቢዩ መሐመድ ከሆነለት ከአንዱ አላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም።
2. በቀን አምስት ጊዜ ጸሎት ማድረስ።
3. ለድሆች መመጽወት።
4. በየዓመቱ በረመዳን ወቅት መጾም።
5. ከተቻለ እስልምና ወደተመሠረተበት መካ በመሄድ እና በቁርአን የተደነገጉትን ደንቦች በመታዘዘዝ የዘላለም

ሕይወት ይገኛል ይላሉ።

በመሠረቱ፣ እስልምና ሰው በኃጢአት ይወለዳል ብሎ ስለማያምን፣ የመዳን አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ የለም። በምትኩ ግን፣ ለመንግሥተ ሰማይ ለመብቃት በእስልምና የተደነገጉትን ቀኖናዎች በታማኝነት መታዘዝ በቂ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ትእዛዛትን መፈጸም እግዚአብሔርን የማፍቀር መገለጫ፣ የመታዘዝም መሠረት መሆኑን እንጂ፣ የዘላለም ሕይወት ማግኛ መሆኑን አያስረዳም። ድነትን፣ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» (ኤፌ 2፡8-9) በማለት ያጸናል።

ፍቅር

ፍቅርን በተመለከተ ኢየሱስን እና ነቢዩ መሐመድን በማነጻጸር ማመላከቱ በቂ መረጃ ሊሆን ስለሚችል፣ በእነርሱ ላይ ይተኮር።

መጽሐፍ ቅዱስ በዝሙት ላይ የተያዘች ሴት ታሪክን ይነግረናል። ያዥዎቿ ወደ ኢየሱስ አምጥተዋት በሕጉ መሠረት በድንጋይ ተወግራ ትሙት የሚል ሙግት አነሡ። በዚህ ጊዜ የኢየሱስ ምላሽ «እኔም አልፈርድብሽም፣ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ» (ዮሐንስ 8፡11) በማለት ነበር ፍቅሩን የገለጸላት። በዝሙት ምክንያት የጸነሰችው ሴት ወደ ነቢዩ መሐመድ በመጣች ጊዜ የነቢዩ ትእዛዝ ሴቲቱ እስክትወልድ ድረስ ጥሩ መስተንግዶ ተደርጎላት፣ ከወለደች በኋላ በድንጋይ ተወግራ ትሙት የሚል ነበር፤ ሆኗልም።

ኢየሱስ ስለ ኃጢአተኞች በመሞት ፍቅርን ገለጸ። ነቢዩ መሐመድ ኃጢአተኛውን በመግደል መፍትሔ መስጠትን መረጡ። ክርስቶስ በመሞት ፍቅርን ገለጸ፣ ተከታዮቹም ክርስትና እየተስፋፋ በነበረበት የመጀመሪያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት የኢየሱስን የፍቅር ወንጌል በየአገሩ እየገለጹ፣ ተሰደዱ፣ ተገደሉ፤ ይህንንም በውዴታ እንጂ በማስገደድ አልፈጸሙም። የእስልምና መነሻ ጉዞ ደግሞ በሰላም ለእስልምና እጅ መስጠት ስለሆነ፣ በአንገት ላይ ሰይፍን በማሳረፍ ማስለም ዋንኛው መርኅ ሆነ፤ በዚህም የጦርነት ዘመቻ

መላውን አረብ ተቆጣጠረ። ይህ ግን ሁሉ የክርስትና እምነት ተከታይ በታሪኩ ሁሉ ሰላማዊ ነበር የሚል ማጠቃለያን አያመጣም። ብዙ የመስቀል ጦርነቶች ከክርስትና የፍቅር ዓላማ ውጭ ተካሂደዋል። በትይዩም፣ ሁሉ ሙስሊምም ጦርነት ናፋቂ፣ ግድያን መፍትሔ አድርጎ ወሳጅ እንዳልሆነም ልብ ማለቱ ተገቢ ነው፣ ግና የየእምነቶቹ መሠረት ይህን ይዟል። ፍቅር በመሞት፣ ፍቅር በመግደል።

የንስሐ ምዕራፍ ተብሎ በሚጠራው (አልተወሳህ) ክፍል 10 ቁጥር 5፣ «የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛ ችሁባቸው ሥፍራ ግደሉዋቸው፤ ያዟቸውም ክበቧቸውም።» (Then, when the sacred month's have passed, slay the idolaters wherever you find them, and take them (captive) and besiege them) Surahlx Al-mhadinah ይላል።

አጋሪዎች የተሰኙት ይሁዶችና ክርስቲያኖች ወይም ከእስልምና ወደ ክርስትና የተመለሱ ሰዎች፣ ወይም ሙስሊም ያልሆኑትን ሁሉ ሊጠቀልል ይችላል። ይህን ደግሞ ግልጽ የሚያደርግልን የቁርአን ክፍል፣ ከዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 29 ላይ የሚገኘው ነው። «ከነዚህ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨ ረሻው ቀን የማያምኑትን አላህና መልእክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትንም እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው።» (Fight against such of those who have been given the scripture as believe not in Allah nor the last day and forbid not that which Allah hath forbidden by his messenger, and follow not the religion of truth, until they pay the tribute readily, being brought low.) surah ix Al- mandinah በማለቱ አጠቃላይ ነጥብ መውሰድ ይቻላል።

በተጨማሪም፣ ጋብቻንና የቤተሰብ ተቋምን በሚመለከት ክርስትና እና እስልምና ለየቅል ናቸው። ኢየሱስ ፍቺን ኮነነ። ጋብቻም የእድሜ ልክ መሆኑን አስተማረ። «እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው... ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን

ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል» (ማቴ. 19፡3-9) አለ።

ዘላቂውን የባልና ሚስትን ግንኙነትም አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ ባል ሚስቱን እስከ ሞት ድረስ እንዲወዳት አዘዘ (ኤፌ. 5፡25)። በእስልምና ሕግ ውስጥ ግን ባል ሚስቱን እንዲቀጣ፣ እስከ አራት ሴቶች እንዲያገባ፣ የሚፈታም ከሆነ፣ ልጆቹን ለራሱ አስቀርቶ እንዲያባርራት ይፈቅዳል።

እነዚህን ነጥቦች ሳነሣሣ በሁለቱ የሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ጥላቻን ለመፍጠር ወይም ደግሞ በታሪክ ውስጥ የሆኑትን ያለመግባባትና የውጊያ ዘመኖች ዛሬም ግምት እንዲገቡ ለማድረግ አይደለም። የክርስትና ፈርጥ፣ በክርስቶስ የተሠራው ሰዎችን የመውደድ ሥራ፣ ለሁሉ ግልጽ ሆኖ እንዲታይ ነው። ሰዎች ሁሉ የሰላምንና የፍቅርን መሠረት በመግባባት ሊረዱት ይገባል። በተጨማሪም፣ አላህ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እንዳልሆነ መረዳትም ሌላው ነጥብ ነው። እነዚህን በአግባቡ መረዳት ተቀራርቦ ለመወያየትም ሆነ ለመመካከር ይረዳል።

አንባቢዬ ሆይ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ለምን ለአፍታም ቢሆን አታስበውም? እርሱ ስለ አንተ ሞተ፤ ሞትንም አሸንፎ ተነሣ፣ ብታምነው የዘላለም ሕይወት የአንተው ነው።

ጸጋ በሰው ሁሉ አፍ ቀልሎ የተገኘ ቃል

በአብያተ ክርስቲያን ዙሪያ ቃሉ ሳይጠራ ውሎ የማያድረው ጸጋ ነው። ሁሉም፦ የእስትንፋሱን ያህል፦ «በጸጋው ነው የቆምኩት»፣ «ጸጋው ነው ያዳነኝ»፣ «ጸጋው ይበቃኛል»፣ «ጸጋው ባይኖርማ...»፣ «በጸጋ ላይ ጸጋ»፣ «የወንጌሉ ጸጋ»፣ «የጸጋውም ወንጌል» የሚሉት ጸጋ-አቀፍ አባባሎች ትናንትም ዛሬም፣ ሁሌም ሲባሉ ይሰማሉ፤ ከዚህም የተነሣ ጸጋ የቤተ ክርስቲያናት መለያ ሆኗል።

ይሁዳ መጽሐፍ 3 ሦስት ላይ፣ «ወዳጆቼ ሆይ! ስለ ጋራ

ደህንነታችን ልጽፍላችሁ በብርቱ ፈልጌ ነበር፤ አሁንም በማያዳግም ሁኔታ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለ ተሰጠው እምነት በብርቱ እንድትጋደሉ ለመምከር ልጽፍላችሁ ግድ ሆነብኝ» በማለት በዘመኑ እየሰረጉ የገቡትን የስሕተት ትምህርቶችንና ልምምዶቻ ቸውን ለማስወገድ አንባቢዎቹን ስለ ተሰጣቸው እምነት በብርቱ እንዲጋደሉ የተጠንቀቁ መልእክቱን ያደረሰው ከጅማሬው በአንደኛ ው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር።

ዛሬ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ የእግዚአብሔር አሳብ ሳይቀየር ያው ይሁዳ ምክሩን ለእኛው ይለግሰናል፣ ለዚህ ትውልድ ዘመነኞች። እኔ ምክሩን ልታዘዝ ስለ ወሰንኩ፣ እናንተን አንባቢ ወዳጆቼን ላነሣሣ ፈለግኩኝ፤ ትኩረቴ ባንድ ነጥብ ላይ ይጸናል፦ እርሱም ጸጋን በአንደበታችን ላይ መላልሰን ከማለታችን ባሻገር ዘልቀን የጸጋን ምንነት በሙልዐት ተረድተን ይሆንን? የሚል ነው፣ ፍላጎቱ ይህን ብቻ ለማመላከት ነውና አብረን እናንብብ። ጸጋን ቅዱሳት መጻሕፍት በስምምነት የሚፈቱበት ፍቺ፦

> «ምሕረት የማይገባው ሰው እግዚአብሔር በቸርነቱ የማ ረበት፣ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ሰውን ገንዘቡ ያደረገበት፣ ከሰው ማንነት የተነሣ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔርነቱ የመነጨበት፣ ሰው ሳይለምን፣ ሳይደክም፣ ወደ ሰው የደ ረሰ፣ ይሁንልህ ያለለትን ላይመልሰው ያጸናበት ስጦታ ጸጋ ተብሎ ተጠርቷል። ይህም ጎልቶ፣ ፈክቶ፣ የተገለጸው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ በሠራው ሥራ ሲሆን፣ ይህንን ሥራ በሰው ሕይወት ውስጥ ለውጤት ያበቃው መንፈስ ቅዱስ ነው።»

ከፍቺው የጸጋን ምንነት ለመነሻ ያህል እንዲህ ስንመለከት፣ አያይዘን ደግሞ እንዴት ጸጋን ገልጸውት እንደ ነበር መጥነን እንግለጽ፦

ማንም ሰው የራሱን ቅድመ-አሳብ (preconceived prejudice) ወይም ግላዊ እምነቱን ይዞ ንባቤን እያነበበ የሚተረጉምብኝ ካልሆነ በቀር፣ የጸጋን መልእክት ኢየሱስና ሁሉም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ሰብከውታል፣ አስተምረውም ጽፈውበታል። ይህ ደግሞ የአዲስ ኪዳን አጠቃላይ መልእክት ጸጋ ብቻ መሆኑን አብስሯል።

የወንጌል ማዕከላዊ ጭብጥ፣ «የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ፣ የከበረ ደሙንም ደካሞችና ተስፋ ቢሶች ለሆኑ ኃጢአተኞች አፈሰሰ፤ እኒህም ኃጢአተኞች በየገዛ ዘመናቸው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከኃጢአት ባርነት ይላቀቃሉ፤ ይህም የሚሆነው የምስራቹን ቃል ሰምተው መንፈስ ቅዱስ እንዲጸጸቱ ስለ ኃጢአታቸው ሲወቅሳቸው ነው::» የሚለው ዋንኛውና ብቸኛው መልእክቱ ነው::

ይህ ደግሞ የተገለጠበት ቀዳሚ ወንጌል የማቴዎስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው፤ «እርስዋም ወንድ ልጅ ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ስለሚያድን ስሙን ኢየሱስ ትለዋለች» (ማቴ. 1:21) በማለት ያበሥራል፤ በዚህም የተስፋ ቃል ኢየሱስ የራሱን ሕዝብ ሊያድን እንደሚመጣ ያሳውቃል:: በሉቃስ 2:34ም ስምዖን ከባረካቸው በኋላ በተለይ የሕፃኑን እናት ማርያምን እንዲህ አላት፣ «እነሆ፣ ይህ ሕፃን በእስራኤል ውስጥ ለብዙዎቹ የመጥፋት ለብዙዎቹ ግን የመዳን ምክንያት ይሆናል፤ እርሱም ብዙዎች የማይቀበሉት ምልክት ይሆናል:: ይህ የጸጋ ምንነት ለብዙዎቹ ግን የመዳን ምክንያት ይሆናል» በማለቱ ሊድኑ የተገባቸው በእግዚአብሔር ለኢየሱስ እንደ ተሰጡ ወይም እንደ ታወቁ ያ ረጋግጣል::

በዚሁ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 11:25-27 ኢየሱስ ጸጋን ሲገልጸው የእግዚአብሔር መለኮታዊ እጅ የሚያርፍበት ሁነኛ መለያ ያደርገዋል፤ «የሰማይና የምድር ጌታ የሆንህ አባት ሆይ! ይህንን ነገር ከጥበበኞችና ከአዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥክላቸው አመሰግንሃለሁ:: አባቴ ሆይ! ይህን ለማድረግ የአንተ በጎ ፈቃድ ሆኖአል:: አባቴ ሁሉን ነገር ሰጥቶኛል ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ ማንም የለም እንዲሁም ከወልድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም፤ ማንም ወልድ ሊገልጥለት ካልፈቀደለት በቀር አብን ሊያውቅ አይችልም» በማለት ጸጋ የእግዚአብሔር የልዕ ልናው ብቸኛ መገለጥ መሆኑን ያስተምራል::

ከእነዚህም ሌላ ኢየሱስ ክርስቶስ የጸጋን አስተምህሮ የገለጸበትን እውነት በአግባቡ ያስተላለፈልን ወንጌላዊው ዮሐንስ በምዕራፍ 6 ላይ ኢየሱስ 5000 ሰዎች በማብላቱ፣ ብዙ ሕዝብ ከመጥገቡ የተነሣ ተ

ከትለውት ነበር። ሕዝቡ የኢየሱስ መንፈሳዊ ትምህርት ሳይሆን የሆድ ጥያቄያቸው ምላሽ ማግኘት ብቻ ነበር እንዲከተሉት ያደ ረጋቸው። በዚህ ወቅት ኢየሱስ ከሰማይ የተላከ እውነተኛ እንጀራ መሆኑን ነገራቸው፤ ላመኑበት ሕይወትን ሊሰጥ ከእግዚአብሔር እንደ ተላከ አሳወቃቸው። «አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል ወደ እኔ የሚመጣውንም ወደ ውጪ አላባርርም፣ ምክንያቱም እኔ ከሰማይ የወረድኩት የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ እንጂ የራሴን ፈቃድ ለማድረግ አይደለም፤ የላከኝ ፈቃድ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ ሳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣ ነው» (ዮሐንስ 6፡37-39)። የጥሪው ባለቤት ስላልሆኑ ሰዎች ደግሞ ሲናገር፡- «እነዚህ እግዚአብሔርን ለመረዳትም ሆነ የእግዚአብሔር ለመሆን ምንም ዓይነት አቅም የላቸውም» በማለት፣ «የላከኝ አብ የሳበው ካልሆነ በቀር ወደ እኔ መምጣት የሚችል ማንም የለም» በማለት በትምህርቱ ዘለቀ (ዮሐንስ 6፡44)።

የሐዋርያት ሥራንና የአዲስ ኪዳን መልእክቶችን ብንዳስስ ጸጋን የገለጹበት መግለጫ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ጋር የሚስማማ ነው። ጥቂቱን እነሆ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ በአንጾኪያ ላሉት ክርስቶስን በሰበከላቸው ጊዜ ተቃውመውት ነበር፤ እርሱ ግን ያንኑ ወንጌል ተስፋ የሌላቸው ወደ መሰሉት አሕዛብ ዞሮ ሰበከው የሰሙት ደግሞ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሊሠራ ያለውን አይተ ው ተደነቁ፤ መደነቅ ብቻ አይደለም ጸሐፊው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 13፡48 ላይ እንደ ገለጸው፣ «አሕዛብ ሰምተው ደስ አላቸው የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ፣ ለዘላለም ሕይወትም የተዘጋጁ ሁሉ አመኑ» አላቸው፤ ይህም የእግዚአብሔር ቅድመ-ውሳኔና ዝግጅቱን በጸጋ ሊድኑ ባሉት ላይ እንደ ሆነ ያበስራል።

አሥራ አራቱን የጳውሎስ የአዲስ ኪዳን መልእክቶችን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ላይ ተደግፎ የጻፈው ጳውሎስም የጸጋን ምንነት በአግባቡ በማስተዋወቅ ዋነኛ ተጠሪ ለመሆን በቅቷል። ለዚህ ደግሞ ሮሜ ምዕራፍ ዘጠኝ አልያም ኤፌሶን ምዕራፍ አንድን መመልከቱ በቂ ነው፤ እኒህ ምዕራፎች ጸጋ ሰው ሊቋቋመው የማይችለው ብቸኛው የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ያስረዳሉ።

ያዕቆብ በምዕራፍ 2፡5 ላይም «የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ!

ስሙ እግዚአብሔር በእምነት ሀብታሞች እንዲሆኑና ለሚወዱት ተስፋ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?» በማለት የእግዚአብሔር ጸጋ ምንነት በምርጫው ላይ መመርኮዙን ያስተምራል።

ጴጥሮስ በቀዳሚ መልእክቱ ላይ፣ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደ ሚያስደንቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ» (1ኛ ጴጥ. 2፡9) በማለት ጸጋን በምርጫው ውሳኔና በጥሪው ድንቅነት ላይ ይመሠርታል።

ሐዋርያው ዮሐንስም 1ኛ ዮሐንስ 4፡19 ላይ፣ «እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላፈቀረን እኛም እናፈቅረዋለን» በማለት ከእግዚአብሔር ለመወለድ ዋነኛ ምክንያትና የመዳን መንስኤ የሆነው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ ይገልጻል።

እኒህ እንግዲህ የሚጠቁሙን ቁም ነገር ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋርያቱ ገና ከጅምሩ ጸጋን በአግባቡ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያናት እንዲረዱት ማስተማራቸውን ነው። ርእሴ ይበልጡኑ ተግባራዊ እንዲሆንልኝ በየዘመኑ የእግዚአብሔርን ሥራ ገልጠው ያለፉትን የወንጌሉ አገልጋዮች ጸጋ እንዴት እንደ ገለጹት አሁንም መጥኜ በማስረዳት እደመድማለሁ፡-

ታዲያ እነዚህን ሰዎች ሳነሣሣ አንባቢው እነርሱን ከአዲስ ኪዳን ጽኑ የጸጋ መልእክት ጋር የተወዳደሩ ወይም ለእግዚአብሔር ቃል ማጽኛ ለማድረግ ለማካካሻ እንዳቀረብኳቸው አድርጎ እንዳይቆጥርብኝ ከወዲሁ አሳስባለሁ።

እነርሱን የፈለግኩት ከሁለኛው ደረጃ ሊነሡ ከሚገባቸው የታሪክ እማኞች ውስጥ በማድረግ ከጥንት ጀምሮ የጸጋን ምንነት የተረዱ ሰዎች ያሉበት እውነት ዛሬም ይህን ያስተዋሉ ሌሎች ሰዎች ቢገኙ እንደ ተሳሳተ ትምህርት፤ አሊያም እንደ እንግዳ እውነት ሊቆጠር አለመገባቱን እንደሚያስረዱ እማኞች አድርጌ ስላመንኩባቸው ነው፤ እንደ አሜሪካዊው መጋቢ ቶም ሮስ እኔም የማነሣቸው ከዚሁ ዓላማ አኳያ ብቻ ነው።

በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ፔላጂየስ (Pelagius) የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ጸጋ በመካድ የራሱን ትምህርት አስተማረ፤ ዴቪድ እስቲል

ባስተማረው ላይ እንዲህ ብሎ ጽፎበታል፡-

> «ፔላጅየስ፡- የሰው ልጅ ባሕርይ በኃጢአት አለመበከሉን አስተማረ፤ የአዳም ኃጢአት በመተላለፍ በሰው ሁሉ ዘንድ በመድረስ ሁሉን የሚበክል ሳይሆን፣ የኃጢአት ጣጣ ራሱን አዳምን በተናጠል የሚያስጠይቅ ነው አለ፤ ስለሚወለዱም ሕፃናት ሲናገር፡- ሕፃናት ልክ አዳም ከውድቀት በፊት በነበረው የንጽሕና ደረጃ የሚገኙ ፍጥረቶች ናቸው። ማንም ሰው የፍጹም ነጻ ፈቃድ ባለቤት ስለሆነ፣ በዘመኑ ለሚያጠፋቸው ጥፋቶች የወንጌልን ስብከት በመሰማት ሊያምንና የእግዚአብሔርን ሕግጋት ያለ ችግር ሊፈጽም የሚችል ነው» አለ።

የካቶሊክ የሥነ መለኮት መምህር የሆነው አውግስቲን (Augustine) ግን የፔላጅየስን ትምህርት፡- «ከእውነቱ የራቀ መናፍቅነት» መሆኑን አስተማረ፤ በትንታኔውም፣ «ሁሉም ሰው በኃጢአት ምክንያት ለእግዚአብሔር በየትኛውም መንገድ በገዛ ፈቃዱ ምላሽ አይሰጥም፤ ይህም የሆነው በመንፈሱ ሙት በመሆኑ ነው፤ ሙትነቱ ከእግዚአብሔር የተለየ አድርጐታል፣» በማለት አጠንክሮ አስተማረ። ሰዎች ለደኅንነት ቢበቁም ለዚህ የበቁት እንደ ፔላጅየስ ከራሳቸው ነጻ ፈቃድ የተነሣ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ነጻ ጸጋ የተነሣ መሆኑን አበክሮ በሰው ዘር ሁሉ ኃጢአት መኖሩን አሳሰበ።

ከፔላጅየስ በኋላም የተነሣ ሌላ የሐሰት ትምህርት ነበር። የዚህ ደግሞ አብቃይ ሲሳን (Cassian) ይባላል፤ ይህ ሰው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዘራው የደኅንነት የሥነ መለኮት አቅጣጫ ከፊል ፔላጂየስ (Semi-Pelagianism) እየተባለ ይጠራል። ትምህርቱ ከፊል ከአውጉስቲን፣ ከፊል ደግሞ ከፔላጂየስ ተወስዶ የተቀየጠ ነው። ሲሳን የሚለው እንዲህ ነው።

> «የአዳም መተላለፍ ኃጢአት በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ተላልፏል መተላለፉም ያመጣው ጣጣ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ክብር እንዲጎድላቸው ማድረግ ነው፤» ካለ በኋላ፣ «ዓለም አቀፋዊ ጸጋ ለሰው ሁሉ ተዘጋጅቷል፣ ያንንም ያለምንም መከልከል እያንዳንዱ ሰው በነፃ ፈቃድ በመጠቀምና ግላዊ ውሳኔ በማድረግ ደህንነትን

የራሱ ሊያደርገው ይችላል» ይላል። ይህንን ግን የኘሮቴስታንት ከፊል ተሐድሶ አራማጅ ከሆኑት ብዙዎቹ ከመንገዱ የወጣ ዋንኛ ስሕተት በማለት ጠርተውታል፡- ለዚህም

ጄ. አይ ፓከር (J. I. Packer) እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡-

> በተሐድሶ ዘመን የነበሩት የኘሮቴስታንት መሪ የሥነ መለኮት አዋቂዎች እርስ በርሳቸው እዚህ ግባ በማይሉት የልዩነት አሳብ ላይ የቆሙ ቢሆንም፣ ካንድ መሠረታዊ እውነት ላይ ግን ሁሉም በጋራ እንደ አንድ ሰው ሆነው ቆመዋል፤ ያም፡- ኃጢአት ሰውን አቅመ ቢስ አድርጎ ካሸመደመደው፣ ለመዳን ከእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ በቀር ምንም ተስፋ የለውም በሚለው እውነት አልተለያዩም፡- ክርስትና የመዋጀት፣ በእግዚአብሔር የመቀደስ ውጤት እንጂ፣ በራስ ውሳኔ እና መልካምነት ሊሆን የማይችል ሕይወት ነው፣» በማለትም ተንትነዋል ይላሉ።

ፓከር በተሐድሶ ዘመን የነበሩት እንኳ ለእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ በአንድ ቆመው እንደ ነበር ሁሉ፣ በየዘመኑ ታማኝ ቅሬቶች ሆነው ያለፉ ባኘቲስቶችም የቤተ ክርስቲያን ጸጋን በመግለጽና በመኖር ለመቆማቸው ታሪክ ጸሐፊው ጃሬል (W. A. Jarrell) እንዲህ ከትበዋል፡-

> «በእግዚአብሔር ምርጫ በማመን፡- ይህንን አስተምህሮ ደፍረው በመስበክ ባኘቲስቶች ቀዳሚ ናቸው። ብዙ የመድረክ ስብከቶቻቸው ሮሜ ምዕራፍ ዘጠኝን ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር አጣጥመው ማቅረብ ነበር፤ በሁኔታዎችም ላይ ያልተመሠረተውን የእግዚአብሔርን የቅድመ-ውሳኔ ድንጋጌን እግዚአብሔርን የማመስገኛ በራቸው አድርገው ይሰብኩ ነበር»[3] ይላሉ።

ጃሬል እንዲህ ላሉላቸው ወገኖች፡- ሳሙኤል ሞላንድም አጠቃላይ የታሪክ ጉዞአቸውን እንደሚከተለው ተንትነዋል፤

> ከሐዋርያት በኋላ የእነርሱን ፈለግ ተከትለው ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ እንዴት እንደ ሆነ የሚያስተምሩና የሚሰብኩ ጥቂት ታማኝ አገልጋዮች ነበሩ፤ የእነርሱ መልእክተኞች እስከዚህ ዘመን እየሰበኩ ያደረሱት መልእክት እግዚአብሔር

ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ መረጠን፤ የፍቅሩም ወደር-የለሽነት በኃጢአት ፍጹም ምውት የሆነው (totally deprived) ሰው ለመዳን በምሕረቱ መወሰኑ ነው፤ የተመረጡትም ከገዛ ከእምነታቸው፣ ከበጎ ተግባራቸው፣ አልያም ከቅድስናቸው የተነሣ ሳይሆን፣ ከእርሱነቱ የተነሣ በጸጋው ስለ ሆነላቸው፣ እነርሱ በማመስገን መኖር ድርሻቸው ሆኖ ይኖራሉ። ይህንን የጸጋ ሥራም በመግለጣቸው እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ላይ የተቃዋሚዎቻቸውን የግፍ መከራ እየተቀበሉ አሉ።»[4] ብሎላቸዋል።

ሜኖ ሳይመንስ (Menno Simons) በገዛ ዘመኑም በጸጋው ተደግፈው የጸጋን ምንነት ከእግዚአብሔር የተነሣ ስለ ተረዱት ሕዝቦች ሲጽፉ፦

«ኦ ጌታ በዘላለማዊ ፍቅርህ ወደድከን፤ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት መረጥከን፤ ያለነቀፋ አቁመህ በፊትህ ቅዱስ አደረግከን፤ ይህንንም በማድረግ ምሕረትን በእኛ ላይ ገለጽክ፤ ታማኙ አገልጋይህ ጳውሎስ የአንተ ድርሻ የሆነውን የመምረጥን ጉዳይ እያነጻጸረ ሲገልጥም፣ ኤሳውን፣ ፈርዖንን፣ እና እስራኤልን እያነሣ አስተማረን፣ ይህንን ደግሞ ያደረገው ከእኛ የተነሣ ታከናውናለህ እንዳንል፦ መመኪያችን አንተን ብቻ አድርገህ፣ አንተን እንድናከብር ስለሆነ፣ በእውነት እናመሰግንሃለን»[5] ይላሉ ሲል ዘርዝሯል።

ከዚህ ግርድፍ ዝግጅቱ የመጨረሻ የማደርገው እማኜ ሲ. ኤች. ስፐርጀን (C. H. Spurgeon) ይሆናል፤ ይህ የእግዚአብሔር ሰው የጸጋን ምጡቅነት አስፋፍቶ ሲያብራራ ያለው እንዲህ ነው፦

ሲ. ኤች. ስፐርጀን የካቶሊካውያኑና የኦርቶዶክሳውያኑ የመነሻ መናፍቅነት በማያሻማው በእግዚአብሔር መልእክቱ ላይ መጨመር መቀነሣቸው ነው፤ የእግዚአብሔር የሆነውን መዋጀት ለመቀበል ሲቸገሩ ይመቻቸው ዘንድ እንደ ራሳቸው መረዳት የሰውን ሥራ በክርስቶስ ያለቀ ሥራ ላይ ለጠፉ፣ ይህ ነው ከመስመሩ ውጪ ያስባላቸው፤ ስጦታ የሆነው ጸጋ ግራ የገባቸው ለመቀበል እንኳ እጅ እንዳላቸው እስከማይገነዘቡ ድረስ ማስተዋል ተሣናቸው፤ እኔ ግን

በዘመኑ አጠራር ካልቪኒስቱ ቢሉኝም ተቀብዬው ለመጠራት ዝግጁ ሆኛለሁ፣ ጸጋ «ካልቪንዝም» ወንጌል የአንድ እውነት ሦስት መጠሪያዎች ሆነውልኝ እግዚአብሔር መረጠኝ፤ አሳቡን ላይቀይር አጸናኝ፤ ጥሪዬ ለዘለዓለም ነው፤ ይህን እየሰበክሁ እሞታለሁ፤ ለዘላለም ሕይወት የተ ዘጋጁትም በስብከቱ ቀን መጠራታቸውን ያጸናሉ፤ ከዚህም የተነሣ ሁሌ ጸጋውን እየገለጽኩ እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ እናገራለሁ። የዘወትር ንግግሬ ነበር» ይላል።

ስፐርጅን በእውነት ላይ ቆሞ፣ ላይሸቅጥ በጽናት ጸጋን ገልጦ እንዳገለገለ ሁሉ፤ የመናፍቅነት እርሾ በአንዳንዶች ዘንድ ሰርጎም እንደ ነበር ጆን ሪሲንገር (John Reisinger) በመጽሐፍ ቅዱስ የመጥምቃውያን ጎብረት (Bible Baptist Fellowship) ውስጥ ታዋቂ ሰባኪ የነበረውን የነኡል ስሚዝ (Noel Smith)ን ትምህርት ተጠንቀቁ በማለት እንዲህ ያስተዋውቅበታል፦

«በቃሉ የተገለጸውን እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እግዚአብሔ ር ያለውን እንደሚፈጽም አምናለሁ ማለት ነው።» ይላል ስሚዝ፤ አስከትሎም፣ «እኔ በስብከቴ ሁሉ ሰዎችን ሁሉ እግዚአብሔር ያድናል፤ ብዬ አስተምራለሁ፤ ለዚህም መሠረቴ ሥላሴ በጋራ ሆነው የተስማሙበትን ብይን እንደሚጠብቁ ስለማምን ነው፤ መቼም ቢሆን ሰዎች ሁሉ እንዳይጠፉ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ የጸና ጉዳይ ነው፤ ከዚህም የተነሣ የሥላሴ የዘወትር ተ ግባር እድሜ፣ ፊት፣ ቀለም ሳይለዩ ሁሉም ይድናሉ፤ የክርስቶስ ሞት ለሁሉም ሕይወት ይሆናል፤ እንዲህማ ካልሆነ በሦስትነት አንድነት የተላለፈ የእግዚአብሔርን ውሳኔ ራሱ እግዚአብሔር ሻ ረው እንደ ማለት ነው፤ ምናልባት ኃጢአተኞች ወደ ገሀነም ቢወርዱ፣ የመውረዳቸው መንሥኤ የእግዚአብሔርን ጥረት ሁሉ በማበላሸታቸው እግዚአብሔር ሊያተርፋቸው አልቻለም።» በማለት፣ የእግዚአብሔርን ልዑልነት፣ አዋቂነትና ቻይነቱን በትምህርቱ እንደሚፈታተን ተሰምሮበታል፤ ስሚዝ ምሕረት እግዚአብሔር ለወደደው ማድረጉን ረስቶ የጣረ፣ የጋረ ሊያገኘው እንደሚችል ይተርታል። ይህ ግን የጸጋ የመግለጫ ትምህርት አይደለም፣ ማከፋፊያ እንጂ።

እንግዲህ ለመዋያያ መነሻነት ያዘጋጀሁትን ይህን ጽሑፍ የምደመድመው እንዲህ ብዬ ነው፤ የክርስቶስ እንደ መሆኔ መጠን፣ እውነትን እናገራለሁ እንጂ አልዋሽም፤ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ጎሊናዬም እንደማልዋሽ ይመሰክርልኛል. . . ርብቃ የነገድ አባታችን ከሆነው ከይስሐቅ መንታ ልጆችን በፀነሰች ጊዜ የእግዚአብሔር ምርጫ በሥራ ሳይሆን በጥሪ መሆኑን ለመግለጥ ሁለቱ ልጆች ከመወለዳቸውና ክፉ ደግ ከማድረጋቸው በፊት እግዚአብሔር ርብቃን፣ «ታላቁ ለታናሹ ተገዢ ይሆናል» አላት። ይህም ያዕቆብን ወደድሁ ዔሳውን ግን ጠላሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። እንግዲህ ምን እንላለን? እግዚአብሔር ያዳላል ማለት እንችላለንን? እግዚአብሔር ምሕረት ነው. . . (ሮሜ 9:1፣10-17)። ይህንን ያለው ደግሞ እግዚአብሔር ነው።[8] እንግዲህ እንደ መነሻ ትርጉሙ የእግዚአብሔርን ጸጋ አንቀበል ብንል፣ «አንተ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ምን መብት አለህ? የሸክላ ዕቃ ሠሪውን ለምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ሊለው ይችላለን? ሸክላ ሠሪ ከአንድ ዓይነት የሸክላ ዕቃ አንድን ዕቃ ለክብር ሌላውንም ዕቃ ለውርደት አድርጎ ለመሥራት መብት የለውምን» (ሮሜ 9:20-21) በማለት ይጠይቃል፤ ምላሻቸው ምን ይሆን? ጸጋ በአፋችን ላይ ብቻ የሚንከባለል ተራ ቃል ከሆነ፣ በዚህ እውነት ላይ ተቃዋሚ በመሆን መነሣት አይቀሬ ነው፤ ተስማሚ ከሆኑ ደግሞ፣ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ጭብጥ ግቡን መታ ማለት ነው።

ዋቢ መጻሕፍት

1. Steel, David N. and Thomas, Curtis C. *The Five Points of Calvinism,* (Philadelphia, PA: The Presbyterian Reformed Publishing Co. 1979), p.20.
2. Ibid,p.21.
3. Jorrell, W. A. *Baptist Church Perpetuity* (Dallas, TX 1894), p. 139.
4. Moreland, Sauer, *The Churches of the Valley of Piemont* (For Smith, AR. Franklin Printing Co.1955), p. 113.
5. Simons, Menno, *The Complete Writings of Menno Simons*

(Scottsdale, AZ: Herald Press, 1956), p.76.

6. Spurgeon C. H. *The Early Years* (London: The Banner of Truth Trust, 1962), p.108.
7. Resinger, John, *The Sound & Grace.* February,1990,p.9.
8. Tomross, *The Abonded Truth.*

አንባቢያን እና ጆን ቡንያን

በአዛውንቱ ዳኛ ፊት የቆመው እስረኛ ጆን ቡንያን ይባላል። ይህንን ሰው፣ «ባለፈው ምሽት በገበሬው ቤት ስትሰብክ መያዝህን ታውቃለህ? ይህ ደግሞ የመንግሥትን ሕግ መተላለፍ ነው፣ ይህንን ታምናለህን?» የሚል ጥያቄ ከዳኛው ቀረበለት። ቡንያን ራሱን በመነቅነቅ፣ «ትክክል» የሚል ምልክት አሳለፈ። ይህን ለማለት ያስደፈረው የ1660ው የእንግሊዝ ሕግ ማንም «ከንጉሡ ፈቃድ ሳያገኝ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳያስተምር፤ ስብከትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ይፈጸማል» የሚል ትእዛዝ መውጣቱን ያውቅ ነበር።

ሕጉን የሚያስፈጽሙት ዳኛም፣ «ጆን ቡንያን ለሦስት ወር ዘብጥያ እንድትወርድ ወስኛለሁ፣» በማለት የፍርድ ትእዛዛቸውን ሰጡ። ቡንያን ለመጀመሪያ ጊዜ በእስር ቤት ማደርን ሀ ብሎ ጀመረ። ይህ ሰው የክርስቶስ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ አንደበቱ ለአፍታም አልተገታም፣ የቤት ቁሳቁሶችን በሚበይድበት፣ በመኖሪያ አካባቢው፣ ከመንገድ ተጓዦቹ ጋር፣ ለቀዬው ገበሬዎች ሁሉ፣ «እግዚአብሔር ንስሐ ገብታችሁ ትድኑ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስን ለእናንተ አሳልፎ ሰጥቷል፣ ብታምኑበት የኃጢአት ይቅርታንና የዘለዓለም ሕይወትን አሁን ታገኛላችሁ» ይላቸው ነበር።

ይህ ቃሉ የእስር ቤት በራፍን ከረገጠበት ቀን ጀምሮም አልቆመም። የተወሰነበትን ሦስት ወራት በዚያ ቀዝቃዛና ጨለማ

ክፍል ሆኖ መሰከረ። ዘጠና ቀናቱን ጨርሶ በፈረዱበት ዳኛ ፊት ሲቆምም፣ «ቡንያን ከአንደበትህ ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር፣ ኃጢአት» የምትላቸውን ሁሉ ትንፍሽ እንዳትል። በዚህ እዘልቅበታለሁ ካልክ፣ ሌላ ብይን ይጠብቅሃል» የሚል ቁጡኛ መልእክት ከዳኛው ወጣ። ቡንያን ይህን እየሰማ ወደ ሕሊናው ምስኪኗ ባለቤቱ መጣችበት፣ ዓይነ ሥውሯ ልጁ ከተፍ አለች፣ የተቀሩት ሦስቱ ልጆቹ ተከታትለው ታዩት። ቡንያንም በዘብጥያ የሚከርም ከሆነ፣ ለሚስቱና፣ ለልጆቹ ምንም የተወላቸው መተዳደሪያ ስለሌለው፣ ተጨነቀ። እኒህ ሁሉ በቅጽበት እየመጡበት ሳለ፣ የተከበረው ፍርድ ቤት «የተባልከውን ሰምተህልን አለው።»

«ንጉሡ መስበክ እንደሌለብኝ ያወጡትን ሕግ ዛሬም አውቃለሁ። እግዚአብሔር ግን ዛሬም ስበክ ያለኝን ትእዛዝ አላነሣም፤ ከዚህም የተነሣ የንጉሡን ሕግ ከማክበር የእግዚአብሔርን ብፈጽም እመርጣለሁ» በማለት መለሰ።

ይህም ምላሹ የዘወትር ሆኖ በዳኛው ፊት በየሦስት ወሩ መቅረብ ልማዱ ሆነ፣ ይህም የእስራት ዘመኑን አሥራ ሁለት ዓመት አደረሰው። በ1672 ግን ብዙ ያልተማረው ቡንያን በእስር ቤት የሚጽፋቸውን መጻሕፍት ያነቡ የነበሩ ቡንያንን አስፈቱት። እርሱም ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት ይሠራቸው የነበረውን የያኔውን ሥራ ቀጠለ። በእጁ እየሠራ በአንደበቱና በሕይወቱ የኢየሱስን አዳኝነት እየገለጸ ጥቂት ዓመታት አስቆጥሮ እንደገና በክርስቶስ ምክንያት ሦስት መቶ ዓመታት ያስደነቀውን መጽሐፍ በእስር ቤት ሆኖ ደረሰ- መጽሐፉም «Pilgrim's Progress» ይሰኛል። በአገራችን ይህ መጽሐፍ «የመናኝ ጉዞ» በሚል ርእስ ተተርጉሞ፣ ያለፉትን ሠላሳ ዓመታት እየተነበበ አለ። ቡንያን የመናኝ ጉዞ ያለለት መጽሐፍ «ክርስቲያን» የተባለው ሰው የጥፋትን ዓለም ትቶ መውጣቱን፣ በጉዞውም የመረሩ ፈተናዎችን መቋቋሙን፣ በመጨረሻም ክርስቲያን ካሰኘው ክርስቶስ ጋር መገናኘቱን በመግለጽ የተጠቃለለ ነው።

ቡንያን የሞተው በ1688 ነው። በሕይወት ሳለ ግን 100,000

(Pilgrim's Progress) ታተመ። ይህም በሕይወቱ ዓለም በመጽሐ ፍ ቅዱሳዊ ትምህርቱ መዋጡን ተመልክቷል። እስከ ዛሬ ድረስ በጎትመትና በስርጭት በእንግሊዞች በቁጥር መጥቆ በየሰው ቤት የሚገኝ መጽሐፍ የቡንያን «የመናኝ ጉዞ» (Pilgrim's Progress) ነው።

ያለፉትን ሦስት መቶ ዓመታት ቡንያንን በሕጉ የገታ ዳኛ፣ አስሮ ያስቀረ እስር ቤት፣ ገድሎ የተወ ሞት የለም።

ውድ አንባብያን፣ የማያዛልቅ ተረት ቢሆንም፣ «ከእንጨት መርጠ ለታቦት፣ ከሰው መርጠ ለሹመት» እንዳሉ፣ እኔም የፊታችሁን ኃላፊነት መግለጽ ይረዳኝ ዘንድ ከእምነት አርበኞች ይህን ሰው መርጬላችኋለሁ። ቆራጡን ጆን ቡንያንን ሁሉ አልልም፣ ግን ፈለጉን ትከተሉ ዘንድ ይህን በማንበብ ላይ ትገኛላቸሁ። ቡንያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸም ቆርጧል፣ መቁረጡ፣ የምኞትን መንገድ አልዘረጋለትም፣ ክርስቶስን መስሎ ለመኖር ወስኗልና መተው፣ መወገድ፣ መታወር ምግቡ ሆነው አልፈዋል። እናንተም ነገን ስታስቡ ብድራታችሁ ይኸው ብቻ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም፣ የጠራችሁ ጌታ በአባቱ ፊት አያፍርባችሁምና ደስ ይበላችሁ

ሕፃንነት. . .ጣለኝ ወይስ አወደቀኝ?

የማወራችሁ ድርጊት ከተፈጸመ አሥር ዓመት አልፎታል። ከአፏ በወጣው ቃል ግራ ብጋባም፣ ኋላ ላይ ግን በመገረም የተ ደነቅኩባት ሕፃን ነበረች። ሰሎሜ አለማየሁ ትባላለች፣ በዕድሜዋ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ላይ ብሶታን ገለጸችልኝ። «ሽመልስ እኮ ቅድም አወደቀኝ፣» ብላ ደገመች። ይህም እኔን ግር አሰኘኝና «እመታልሻለሁ» እያልኩ ያሳየችኝን ስፍራ አሻሸሁላት።

አስከትዬም፣ «ሰሎምዬ፣» «አወደቀኝ» አይባልም፣ «ጣለኝ» ነው የሚባለው። ሌላ ጊዜ እንዲህ እንዳትይ እሺ!» አልኳት። እርሷ ግን

አላዳመጠችኝም። ከአባቷ ጋር ንትርክ ፈጥራ ወደ ሌላ ምልከታ፣ ወደ ሌላ ርእስ፣ ወደ ሌላ ጉዳይ ተላልፋለች።

እነርሱ የጋራ ጉዳይ እንደ ያዙ ሳስተውል፣ እኔ ፋታ አግኝቼ «ሽመልስ አወደቀኝ» ያለችውን ክስ አሰብኩ። እንዴት አለችው? ከማንስ ተማረችው?. . . የቃሉን በተለይም የቃለ እርባታውን ተመለከትኩ። ድሮ ድሮ የአማርኛ መምህሬ አድራጊ፣ ተደራጊ፣ አስደራጊ እያሉ ያስተነተኑኝን ዛሬ ፈለግኩት፣ በተለይም አድራጊን፤ እርሳቸው ከግሦች በስተፊት ላይ «አ» ሲቆም ግሡን አድራጊ ያደርገዋል ያሉኝን አስታወስኩ።

ለምሳሌ፣ «በላ» ከሚለው ግሥ ተነሥተን የራሱን የሰውዬውን መብላት ሳይሆን፣ ሌሎችን ማብላቱን ለመግለጽ «አበላ» ነው የሚሰኝ። ልክ እንዲሁ፣ ጠጣ ብሎ አጠጣ፣ ወዘተ... ሊባል ይችላል። በዚህም አካሄድ ሰሎሜ «ወደቀ» ከሚለው ግሥ ተነሥታ «አወደቀ» አለች- «ሽመልስ እኮ አወደቀኝ።» በዚች ሚጢጢ ዕድሜ ለካ እኔ ፈጽሞ ያላስተዋልኩትን፣ እርሷ ተረድታዋለች።

ይህን አስቤ እንደ ጨረስኩ የመነሻ ግራ መጋባቴ ፈጥኖ ወደ መደነቅ ተቀየረ። «አወደቀኝ አይባልም፣ ጣለኝ ነው» የተሰኘው፣ የእኔም ትምህርት ጊዜውን ጠብቆ መጪ እንጂ ለዚያን ጊዜ ጠቀሜታ እንደሌለው አጤንኩት። ሕፃኗ ሰሎሜ የሰዋሰው ትምህርት ሳትማር ሊባል የተገባውን ያኔ በትክክል አለች። እንኪያስ አብዛኛው ሕፃን ወይም ልጅ እንደ እርሷ ይሆንን? መልሱ አዎን ነው። በዚህ ምላሼ ወላጆች፣ ቤተ ክርስቲያንና መላው ኅብረተሰብ ለሕፃናት ትኩረት መስጠት ግድ መሆኑን ስለሚጠቁም፣ ሆን ተብሎ ከተካሄው ጥናታዊ ምርምር ልጀምር።

ምርምሩ በዓለም ላይ ኖረው ታሪክ ሠርተው ባለፉት ሰዎች ላይ አተኩሯል። አንዱ ባለ ታሪክ ሊዮናርዶ ዳቬንቺ ነው። በ1452 (እ.ኤ.አ) ነው ፍሎረንስ አጠገብ በምትገኘው በቪንቺ ከተማ የተወለደው። እርሱ ገና አሥራ አምስት ዓመት ሳይሞላው በጮርቃነቱ የሙዚቃ፣ የሂሳብና የሥዕል ፍቅር አደረበት፤ ያደረበትንም እየሆነው መጣ። ከዚህም የተነሣ ሥዕሎቹ ለአለፉት አምስት መቶ ዓመታት ለዓለም ሕዝብ እይታ በስፋት ቀረቡ። ከእነዚህ ውስጥ እነ «ዘ ላስት ሰፐር- የመጨረሻው ራት» እነ «ሞናሊዛ» ዋንኞዎቹ

ነበሩ፣ ይህ ሰው መሐንዲስ ነበር፣ ሙዚቀኛ ነበር፣ የቅርጻ ቅርጽ፣ የሂሳብና የካርታ ሥራም ጠቢብ ሆኖ ነው ያለፈው። ሊዮናርዶ ዳቬንቺን ለዚህ ያበቃውን ምሥጢር ለመግለጽ በ1475 ዓ.ም የተ ወለደውን ሚካኤል አንጀሎን ላስከትል። አንጀሎ «ሙሴ፣ ዳዊት፣ ጴጥሮስ፣ መስቀል የተሸከመው ክርስቶስ» የተሰኙትን ድንቅ ሥራ ዎችን ድንጋይ ፈልፍሎ በማበጀት እስከ ዛሬ ዓለምን ያስደነቀ ሰው ነው። ሥዕሎቹንም አስመልክቶ የብሪትሽ ሙዝየምን በጎብኚዎች ዘንድሮም የሚያጨናንቁት የእርሱ ሥራዎች ናቸው። በሥነ ምሕንድስና ሙያው አንጀሎ ለሮም ታላቅ ሲሳይም ነበር። እርሱንም ለዚህ ያበቃውን ምሥጢር ለመረዳት የሌላኛውን ተጠኚ የአልበርት አይነስታይን ታሪክ እንቃኝ። በ1879 የተወለደው አይነስታይን በርካታ ምጡቅ ሳይንሳዊ ምርምሮችን አጢኖ ለዚህ ትውልድ በጽሑፍ አበረክቷል፤ በሂሳብና በፊዚክስ የትምህርት ዘርፍም ግዙፍ ግኝቶችን ቸሯል። አይነስታይን «ፖለቲከኝነት በጥቂቱ ያገለግል ይሆናል። የታመነ የሂሳብ ስሌት ግን ለዘለቄታው ነው» የሚል ጽኑ አስተምህሮ ስለ ነበረው፣ ዛሬ እየመጠቀ ላለው ቴክኖሎጂ መሠረትን ጥሎ አለፈ።

የእነዚህ የተጠቃሾቹ አዋቂነት የት ላይ ቢመሠረት ነው ለዚህ የበቁት? የተሰኘው የጥናቱ ዋነኛ መልእክትና ጭብጥ በርካታ ዓመታት የፈጀ አድካሚ ሥራን አሠርቷል። በውጤቱም የሕጻንነት ዘመን አትኳሪነታቸው ለዚህ አብቅቷቸዋል የሚል ፋይዳ ተገኝቷ ል። ሦስቱም ለገጠማቸው ነገሮች ሁሉ ትኩረት ይሰጡ ነበር፤ ያዩትን ደጋግመው ይመለከቱታል። ሃያ ሠላሳ ዓመት የነበረውን ነባራዊ ነገር እነርሱ እንደ አዲስ ቆጥረው ዙሪያ ገቡን እያጤኑ ይመለከቱታል፤ ተመልክተውም ይተረጉሙታል። ከዚያም የነጠ ረ ቲዎሪ (ንድፈ) ያገኛሉ። እንኪያስ የጠቢብነታቸው ወይም የመጠቀ አሳብ እንዲያስቡ ያነበዛቸው ዋንኛ ምንጭ ከልጅነታቸው ጊዜ ጀምሮ የነበራቸው አትኳሪነት ነበር። ታዲያ አሁንስ ቢሆን ሕጻን ሆኖ አትኳሪ፤ ልጅ ሆኖ ዙሪያ ገቡን የማይመለከት ይገኝ ይሆንን? ምላሹ አይገኝም ነው። ይህን ደግሞ ለማረጋገጥ ከሕፃናት ዘንድ የተገኙትን ቁም ነገሮች በመጠቋቆም ልጠቅልል።

* * *

ከዕለታት በአንዱ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ የመረጣቸው ደቀ መዛሙርቱ የመበላለጥን ጥያቄ አንሥተው እርስ በርሳቸው ተ ሞጋገቱበት። እርሱም ሕፃን ጠራና በመካከላቸው አቁሞ፣ «ካልተ መለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም» (ማቴ. 18፡3) በማለት ጥያቄአቸውን መለሰ። እንደ ሕፃን መሆን ያለውን ትርፍም ገለጸ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ወላጆቻቸው ሕፃናቱን ጌታ እንዲዳስሳቸው አመጡለት፤ በዚህ ጊዜ በወላጆቹ ላይ ደቀ መዛሙርቱ ነቀፌታ አደረሱ። ጌታ ግን ተቆጪዎቹን ተ ቆጥቶ፣ «ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናት...» በማለት ሕፃናቱን አቀፋቸው፤ እጆንም ጭኖ ባረካቸው» (ማር. 10፡13-14)። ጌታ ለሕፃናት ያለው ስፍራ ይህ ነው።

በእነርሱም ዘንድ የተገኙት ቁም ነገሮች ደግሞ ተከታዮቹ ናቸው።

ሕፃናት ትልቅ ሰው ያላቸውን ምንም ነገር ያምናሉ፤ ያዘዛቸውንም ይፈጽማሉ። ይህም እምነት እንዳላቸው ይገልጻል፤ በእነርሱ ዘንድ ጥርጥር አይታሰብም።

እነዚሁ ሕፃናት አዲስ ገጠመኞችን ጊዜ ወስደው ያዩአቸዋል፤ ባዩትም ደስ ይሰኛሉ፤ አድናቂዎች ናቸው።

ሕፃናት ስለ መበደላቸው ስፍራ አይሰጡም፤ ፈጥነው ይቅር ባይ ናቸው። ይተዉታል፤ ይረሱታልም።

ይሉኝታ በእነርሱ ዘንድ የለም። የፈለጉትን ጥያቄ ለመጠየቅ ዝግጁ ናቸው። ይጠይቃሉም፣ መልሱንም ይናፍቃሉ፤ ሕፃናት ተ ማሪዎች ናቸው።

ሽረኝነት በሕፃናት ዘንድ አይገኝም። ቀጥተኛ አስተሳሰብና ግልጽነት ሕይወቶቻቸው ናቸው። «የተናገርኩት ነገር ይህን ያመጣብኛል» በሚል ሥጋት መደበቅ ወይም ማወሳሰብ አይቻ ላቸውም፤ ከእግዚአብሔር ቃል ለዚህ ጥሩ ምሳሌያችን ዮሴፍ ነው። እርሱ ሕልምን አለመ፤ ሕልሙ ስለ እርሱ ከፍ ከፍ ማለት፣ ስለ ወንድሞቹም ለእርሱ መስገድ የሚገልጽ ነበር። እንዳለመ ፈጥኖ ሄደ፤ ታላላቆቹን ሰብስቦ ሊሰግዱለት እንዳለ የሚጠቁመውን ታሪክ አጫወታቸው። የእርሱ ቀጥተኛ ፍላጎት ማለሙን ብቻ

መናገር ነበር፤ ዳሩ ግን በዘፍጥረት 37:5-11 እንደተገለጸው፣ ለወንድሞቹ ሕልሙም ሆነ ዓላማው አልተስማማቸውምና ሊያጠፉት ያደቡበት ጀመር::

ሕፃናት ዘንድ ቸልተኝነት አይከሰትም:: በቄላስይሰ 3:23 እንደተገለጸው፣ «ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉት» የሚለው ምክር በልጆች ዘንድ አሻሚነት ሳይኖረው የሚፈጸም ሕያው ቃል ነው:: ሕፃናት በታዘዙት ነገር ላይ ስንፍናን አይጠሩም፣ ተግተው መፈጸምን ያስቀድማሉ::

ተያይዞም በሕፃናት ዘንድ ማመቻመች (compromise) አይከሠትም:: ቀደም ብዬ እንዳነሣሁት፣ ሕፃናት ዘንድ መልሳቸውም ሆነ ጥያቄያቸው ግልጽና ቀጥተኛ ነው፤ አዎ ወይም አይደለም ይሉ ይሆናል፤ ግን ሁለቱም ሊሆን የሚችልበትን አቋራጭ መንገድ አይፈልጉትም::

* * *

በድግግም ሲነገር የሰማሁትን የልጅ ሥራ ልጥቀስ:: እናቱ ማንም ሰው መጥቶ «እናትህ አለች ወይ?» ካለ «የለችም፤ ገበያ ሄዳለች በል» በማለት አስጠንቅቃው ወደ መኝታ ክፍሏ ትገባለች:: እንዳለችውም ኋላ ላይ እንግዳ መጥቶ እናቱ መኖር አለመኖሯን ማሙሽን ቢጠይቀው፣ «እማምዬ ሰው ከመጣ ገበያ ሄዳለች በል ብላኛለች:: አሁን ደግሞ ስለ ተኛች፣ መጥራት አልችልም::» ብሎ አረፈው::

ልጆችን የሚዳኛቸው ፊት ለፊት ያዩት እውነታ ነው፤ እማኛ ቸውም እርሱ ብቻ ነው:: በእኔ ግምት ጌታን እነዚህ ሁሉ መልካም ነገሮቻቸው ናቸው ሕፃናትን አስወድዶ «እንደ ሕፃናት ሁኑ» ያሰኘው:: በመግቢያዬ እንዳነሣኋት ሰሎሜም ሆነ ሦስቱ ጠበብት የአትኳሪነትና የተመልካችነት ባሕሪያቸው የሚወደዱ ሀብቶቻቸው ናቸው፤ ተያይዞም ቅንነታቸው፤ የዘወትር ተማሪነታቸው፤ የመልካም ነገር ባለቤት አድርጎአቸዋል:: እነዚህን በጎ ነገሮች እያደ ረጉ እንዲዘልቁ እንክብካቤ የግድ ነው:: በዓለም ላይ ታላላቅ የተሰኙ የሳይንስና የጥበብ ሰዎች የታዋቂነታቸው መንሥኤ የልጅነት አታኳሪነት ሕይወት ከሆነ፣ በክርስቶስ ሆነው ካሉት የተወለዱት ሕፃናትማ በእግዚአብሔር ነገር አድገው ስፍራ ተሰጥቶአቸው ለወግ

ለማዕረግ ቢበቁ እንዴት ግሩም ነበር።

ከዚህም የሚበልጥ ታላቁ ተአምር

በአንድ ወቅት ሰዎች እግራቸውን በጨረቃ ላይ በማሳረፋቸው የዜና አውታሮች ሁሉ «ታላቁ ተአምር» በማለት ዘግበው ነበር። ዛሬም ውስብስብነት ያላቸው የሳይንስ ውጤቶች ሲከሠቱና ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ «ተአምር ነው» ይባልላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ተአምር ሲል ከዚህ በብዙ ይሻገራል፣ ይመጥቃልም። በሰው ልጅ ድካምና ጥረት፣ ፍልስፍናና እውቀት ፈጽሞ ሊከናወን የማይቻለውን እግዚአብሔር ብቻ አድርጎት ሲገኝ የተፈጥሮ ቋሚ ሕግጋት ሁሉ ተገልብጠውና ተሽረው አንድ ውጤት ሲታይ ያ ተአምር ይሰኛል።

ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በማደግ ላይ በነበረችበት ጊዜ የተ ቀበሉትን መልእክት ለማያምነው ዓለም ሲያደርሱ የቃሉን እውነተ ኝነት ያጸኑት በተአምራት ነበር። ከዚህ የተነሣ፣ በሮም አገዛዝ ሥር የነበረው ዓለምም በክርስትና ተጥለቀለቀ። ክርስትና ሥር እየሰደደ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ተጽፈው ሲጠናቀቁ፣ በተአምራት ቃሉን የማጽናቱ ጉዳይ እያሽቆለቆለ መጣ፤ «ለምን ይህ ሆነ?» ቢሉ፣ ሙሉ በሆነው በሕያው ቃሉ የጌታ መልእክት ወደ ሰ ዎች ስለ ደረሰ ቀዳሚው ምላሽ ነው። ይህ ሲባል ግን እግዚአብሔ ር ፈጽሞ ተአምራትን ማድረግ አቆመ ወይም ተወ ማለት አይደለም።

የተአምራት ስጦታ በአዲስ ኪዳን ተዘግቦ የምናገኝበት መጽሐፍ 1ኛ ቆሮንቶስ ነው፤ ይህም በምዕራፍ 12 ቁጥር 28 ላይ ይገኛል።

ዘመናቸውን በጌታ ሥራ የሚሳልፉት ሀሮልድ ማርቲን ዛምቢያ አገር ውስጥ የሆነውን እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፦

> «ወንጌል ፈጽሞ ያልደረሰበት ከዛምቢያ ክፍለ አገሮች ውስጥ የተረሳና የተዘነጋ መንደር ነበር። ከተሜዎች ብቅ አላሉበትም። በዚያ ታዲያ የጆሮው ታምቡሩ ተቀድዶ

ለዓመታት የደነቆረ ሰው ተገኘ። እንግዲህ ወንጌል እየሸረሸ ረ በዚያ መንደር ውስጥ ሲገባ፣ ያ ሕዝብ ለወንጌል ምላሽ ሊሰጥ በማይችልበት የሰይጣን አሠራር ውስጥ ተተብትቦ በባዕድ አምልኮ ተጠፍንጎ ለብዙ መቶ ዓመታት ኖሯል። ወንጌል የተሰበከ ዕለት እግዚአብሔር ቃሉን ሊያጸና የተ ጠቀመበት መንገድ ተአምር ነበር። ያ ሰው ሰማ። ደንቆሮነቱ ለሁሉ የታወቀ ነበርና፣ ተአምሩ ለሁሉም መገ ረምን አመጣ፤ ግርምታ ብቻ አይደለም፣ ለወንጌል ቃሉ ምላሽ ተሰጠ። ብዙ ሰዎች ዳግመኛ ተወልደው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ።

እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ገጠመኞች ወንጌል ፈጽሞ ባልተ ሰማባቸው ስፍራዎች ሊሆኑ ይችላል፤ ሲሆኑ ግን ሰባኪው ሁሉን ሊያደርግ እንደሚችል አያስገምትም፤ የተአምራት ስጦታ አለውም አያሰኝም። እግዚአብሔር ይህን በፈለገው ጊዜ በማንም ሊያደርገው ስለሚችል።

በዚህ ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች በሐዋርያት ጊዜ የተ ፈጸሙት ተአምራቶች ሁሉ ለምን በእኛ ዘመን አልተፈጸሙም፣ ይልቁን፣ «በእኔ የሚያምን... ከዚህም የበለጠ ይሠራል» (ዮሐንስ 14፡12) ያለው ጌታ ራሱ አልነበረምን? በማለት ሲጨነቁ ይስተ ዋላል። እርግጥ ነው፣ ጌታ በአገልግሎት ዘመኑ አሥራ አንድ ሰ ዎችን ደቀ መዛሙርት አድርጓል፤ ዛሬ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ብዙ ሕዝብን ለጌታ መንግሥት እያበቃችና ደቀ መዛሙርት እያደረገች ነው። ከዚህ የበለጠ ትሠራላችሁ ያላት ተስፋ እየተፈጸመ መሆኑን አንዘንጋ - ታላቁ ተአምር የሰዎች መዳን ነውና።

* * *

እርግጥ ነው፣ ተአምራት በተወሰኑ ሁነኛ ዘመኖች ውስጥ መከናወናቸውን ማረጋገጥ እንችላለን። በዘመነ ሙሴና ኢያሱ፤ የአሮን በትር እባብ ሆነች፣ ቀይ ባሕር ለሁለት ተከፈለ፣ እስራኤ ላውያንም በደረቅ መሬት በባሕሩ መካከል አቋረጡ፣ በምድረ በዳ መና ተመገቡ፤ ፀሐይም በኢያሱ ዘመን ቆመች። ይህን የመሳሰሉ ሌሎችም ሆኑ። ኋላ ኋላ ግን እነዚህን የመሰሉ አልተደገሙም፣

አልታዩምም። የኤልያስና የኤልሳዕ ዘመን እስኪመጣ ብዙ ዓመታት ያለ ምንም ተአምራት አለፉ።

እግዚአብሔር ምክንያታዊ ሥራውን በኤልያስና በኤልሳዕ ዘመን በተአምራት ገለጸ። ግን ይህም እስከ ነቢዩ ዳንኤል ድረስ ብዙ መቶ ዓመታትን ያለ ተአምራት አሳልፎ ዳንኤልን ከአንበሶቹ አፍ ሲያድነው ታየ። በዚያው ዘመን ሦስቱ ዕብራውያን ወደ እሳት ተጣሉ፣ ተረፉም፤ የተከበረው ንጉሥ ናቡከደነጾር እንደ ከብት ሆኖ ለዓመታት ሣር በላ። እንዲህ ከሆነ በኋላ፣ የተአምራት ድምፅ አሁንም ለብዙ መቶ ዓመታት ሳይከሠት እስከ ዘመነ ሐዋርያት ድረስ ቀጥለ። ከዚያ፣ ጌታ ሲመጣ አገልግሎቱም ሲቀጥል በውኃ ላይ ተራመደ፣ የሞቱ ሰዎችን አስነሣ፣ በጥቂት ዓሣና እንጀራ በሺህ የሚቆጠሩትን መገበ፤ ጳውሎስ በእፉኝት ተነደፈ፣ ግን ምንም አልሆነም። ጴጥሮስ የተጠረቀበት ሰንሰለቱ በገዛ ፈቃዱ ለቀቀው፤ የተከረቸሙትም የእሥር ቤት በሮች በራሳቸው ተከፈቱ። እነዚህን የመሰሉ ተአምራት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እናስተውላለን፤ ግን እነርሱም ቢሆኑ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ተጽፈው እየተጠናቀቁ ሲመጡ እየቀነሱ መሄዳቸው አይዘነጋም።

በእግረ መንገዱ ሦስት ሊታሰቡባቸው የሚገባቸውን ተአምር-ነክ ጉዳዮችን ከሀሮልድ ማርቲን ጋር በመስማማት ላነሣሣ። *ቀዳሚው ነጥብ፣ ብዙ ብዙ ትላልቅ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ተአምራትን በእጃቸው ሳይፈጽሙት ግን የእምነት ሰዎች ነበሩ፣* ለዚህ አብርሃምና ዳዊት ዋናችን ናቸው፤ መጥመቁ ዮሐንስም አለ፤ ለመጥመቁማ፣ «ዮሐንስ ምንም ተአምር አላደረገም» ተብሎ ተጽፎለታል (ዮሐንስ 10፡41)። ይህንኑ ሰው ጌታ፣ «በእውነት እላችኋለሁ በምድር ላይ ከተወለዱት ሰዎች ሁሉ ከአጥማቂው ዮሐንስ የሚበልጥ ከቶ የለም» (ማቴ. 11፡11) ማለቱን ልብ በሉ።

እናም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ ይህን ቋሚ ያልሆነውን ድርጊት እግዚአብሔር በፈቀደው በራሱ ጊዜ ብቻ ማስኬዱን ሲያረጋግጥ፣ በተጨማሪም ተአምራት ሁል ጊዜ በዕቅድና በዓላማ ላይ ተመርኩዘው እንደሚሆኑም ያስታውቀናል።

ሁለተኛው ነጥብ፣ የእግዚአብሔር ቃል የሚለንን በእምነት ታዝዘን እንድንኖር እንጂ፣ በምልክቶች ላይ እንዳንደገፍ በጽኑ

ይመክረናል። ጌታችንም ሆነ ጳውሎስ በትምህርታቸው ያሳሰቡን በእምነት እንድንኖር ብቻ ነው። ቃሉ፣ «የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም» (1ኛ ቆሮ. 5፡7) ብሏል። በእምነት አለመጠንከር፣ በጌታ ላይ አለመታመን፣ ለገዛ ስሜት ታማኝ መሆንና ተአምራትን ናፋቂ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔርን እናውቃለን ያሉት የጠየቁትን አስተውሉ፣ «መምህር ሆይ፣ አንተ ተአምር ስታደርግ ማየት እንፈልጋለን?» ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ፣ «ክፉና እምነተ-ቢስ የሆኑ የዚህ ዘመን ሰዎች ተአምር ለማየት ይፈልጋሉ» አላቸው (ማቴዎስ 12፡38-39)። በአንድ ወቅት ደግሞ ሰውየው ወደ እርሱ ቀርቦ «ልጄን ፈውስልኝ» አለው። ኢየሱስ ግን መልሶ፣ «እናንተ እኮ ተአምራትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ በቀር ምንም አታምኑም» (ዮሐ. 4፡48) አለው።

ጌታ በቃሉ ላይ ብቻ ልባችን እንዲያርፍ ይፈልጋል፤ የእምነታችን መሠረት ሕያው ቃሉ ብቻ መሆኑን እንድናውቅ፣ እንድናምንና እንድንኖርበት ይፈልጋል።

ሦስተኛው ነጥብ፣ ተአምር በጌታ የመምጫ ጊዜ ላይ ሊፈጸም እንደሚችል ማወቅና መረዳት ተገቢ ነው፤ ተአምራቱ ግን የሚሆኑት በእግዚአብሔር ሉይደለም። አሳሳች ተብሎ በተጠራው በዲያብሎስ እና እርሱ ባሳታቸው አቀንቃኞቹ ይሆናል። ጌታ በገዛ አንደበቱ እንዲህ አለ፣ «በዚያን ጊዜ... ሐሰተኞች መሢሖችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፣ እነርሱ ቢቻላቸውስ የእግዚአብሔርን ምርጦች እንኳን ለማሳሳት ታላላቅ ተአምራቶችንና ድንቅ ነገሮችን ያሳያሉ» (ማቴ. 24፡23-24)። በመጨረሻም፣ ይህንኑ የጌታ መልእክት ጳውሎስም ሲያጠነክረው፣ «...የዐመፅ ሰው የሚመጣው በሰይጣን ኃይል አሳሳች ተአምራትንና ምልክቶችን አስደናቂ ነገሮችንም በማድረግ ነው...» በማለት ይነግረናል (2ኛ ተሰ. 2፡9-10)። እንግዲህ የጌታ የሆንን እኛ ተአምራትን አስመልክቶ ልንገነዘብ የሚገቡን ቁም ነገራት እነዚህን የመሳሰሉትንም ነው።

ፈውስም ቢሆን እንደ ስጦታነት የተገለጠው በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡9 ነው። ከዚያ ቀደም ብሎ ግን ኢየሱስ «...ሕዝቡን ከበሽታና ከደዌ ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዘዋወር ነበር» (ማቴ. 9፡34)። ኋላም በሐዋርያት ሥራ ጴጥሮስ ሽባውን ሲፈውስ፣

ጳውሎስም በትኩሳትና በተቅማጥ ወደ ሞት የተጠጋውን እንደ ፈወሰው ሕያው ቃሉ ይገልጽልናል (ሐዋ. 2፡6-8፤ 28፡8-9)። እነዚህ ግን አሁን በአለንበት ዘመን አይስተናገዱም። እርግጥ፣ አልፎ አልፎ እግዚአብሔር ወድዶ ሲያደርገው የመስማት ወይም የማየት አጋጣሚ መኖሩ አይጎዳም፤ ይህን ማየት ግን በዚህ ዘመን ፈውስን አስመልክቶ ከሚዘራው የተሳሳተ ትምህርት ጋር ግጥጥሞሽ የለውም። «የታመመ ሁሉ ይፈወስ ዘንድ ይገባዋል፣» የሚለው የዘመኑ ግራ-ገብ አስተሳሰብ ትክክል አይደለም፤ የዚህም ማርከሻው በጳውሎስ ተረጋግጧል፤ በኤፌሶን በነበረበት ጊዜ ሐዋርያው ብዙ ሕሙማንን ፈውሷል፣ ጨርቁ ሳይቀር አገልግሎት ሰጥቷል (ሐዋ. 19፡12)። ኋላ ግን በበሽታ የተጠቃ ወዳጁን እንደ ቀድሞው ፈጥኖ ሊፈውሰው አልቻለም (ፊልጵስዩስ 2፡25-27)። ጢሞቴዎስም በሆዱ ሕመም በብርቱ ሲሠቃይ ጳውሎስ ሊፈውሰው አልቻለም (1ኛ ጢሞ. 5፡23)። ጥሮፊሞስም በታመመ ጊዜ በዚያው በሚሊጢን ነበር የተወው (2ኛ ጢሞ. 4፡20)። ራሱም ቢሆን ጳውሎስ በአገልግሎቱ የኋላ ጊዜያት ውስጥ እየታመመ ያለ ፈውስ እንደ ነበር የጌታ ቃል ይነግረናል (2ኛ ቆሮ. 11፡30 12፡5-10፤ ገላትያ 4፡4፣ 13)።

እንግዲህ የታመመ እና በደዌ ያለ ሁሉ ይፈወሳል ብሎ ማለት ልከኛ እሳቤ አለመሆኑን አጢኑልኝ። ሁሉ አይፈወስም፤ ኢየሱስም ሁሉን እንዳልፈወሰ ዮሐንስ ይነግረናል፤ ከብዙ ሕሙማን መካከል አንዱን መርጦ ፈወሰ፣ ሌሎቹን ግን ተወ (ዮሐ. 5፡1-8)።

ይህም የሚያስረዳው ሁል ጊዜ ሁሉን መፈወስ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ ነው። *ሌላው ፈውስን አስመልክቶ ያለው ግርግር ሁል ጊዜ አለመፈወስ ከበሽተኛው አለማመን ጋር የተያያዘ በማድ ረግ ማስተማር ነው።* ይህ ግን ልክ አይደለም፤ ብዙ የጌታ ሰዎች ያልተናዘዙት ኃጢአት ሳይቀር፤ በጌታ ላይ ያላቸው እምነት ሳይጎድል ግን በበሽታ ማቅቀው ኖረዋል፤ ሳይፈውሱም ሞተዋል።

በተለይ ምንም እምነት በጌታ ላይ ሳይኖራቸው የተፈወሱም አሉ። ለዚህ የቤተሳይዳው ሽባ ዋነኛው ነው (ዮሐ. 5፡13)። ፈውስ በሕመምተኛው እምነት ላይ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ብቻ የሚመሠረት ነው። ከዚህም የተነሣ፣ «እንደ ፈቃዱ

ይሁንልኝ» በማለት መጸለይን ችል ማለት አይገባም።

በዘመናችን ሁሉ ፈዋሽ የሆነ የሚመስልበት አጋጣሚም እየበ ረከተ መምጣቱ ሌላኛው መታረም የሚገባው ስሕተት ነው። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያንም እንኳ በሐዋርያት እጅ ፈውስ ሲፈጸም ታየ እንጂ፣ ሁሉም ሲያገለግልበት አልታየም፤ ከሐዋርያትም እንኳን የአገልግሎት ግንባር ቀደሞቹ ብቻ ናቸው ይፈወሱ የነበሩት (ሐዋ. 15፡12)።

ይልቅስ፣ መታመም ያለ ጉዳይ ነው፤ በተረገመች ምድር ላይ እየኖርን ከውድቀት በኋላ ለሰው የተረፈው ሐብት በሽታ መሆኑን እንገንዘብ። ጌታ ሲመጣ ግን «ሞት ወይም ኀዘን፣ ለቅሶ ወይም ሥቃይ፣ ከዚያ በኋላ አይኖሩም፤ ምክንያቱም የቀድሞዎቹ ነገሮች አልፈዋልና» (ራእይ 21፡4) የሚለውን ተስፋ በተስፋ መጠባበቅ የተ ሻለ ነው። አማኝ በሕመም ውስጥ ሲሆን በራሱ ፈቃድ የቤተ ክርስቲያኑን ሽማግሌዎች ጠርቶ ስለ ሕመሙ እንዲጸልዩለት ይገባል፣ ይህንንም መታዘዝ ተገቢ ነው (ያዕቆብ 5፡13-15)።

በመጨረሻም፣ ጌታ ተአምራትን ዛሬም ይሠራል፤ ግና ከሁሉም የሚበልጠው የተአምራቶች ሁሉ ቁንጮ እግዚአብሔርን በቃሉ ውስጥ እንደምናገኘው መገንዘብ ነው። እርሱን ማወቅና መረዳትም የሚገኘው በእምነት በፊቱ በመመላለስ ነው። በኃጢአት አረንቋ ውስጥ የወደቀውን ሰው ከገሀነም ፍርድ ሊያድነው የሚችለው ወንጌል ነው። ይህም ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ሲሰበክ መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ኃጢአተኛነት እየወቀሰ ለዳግም ልደት ያበቃቸዋል። ይህ ነው ታላቁ ተአምር፤ ይህ እንዲሆን አንትጋ!

መከረኝነት

ነጋ ይባላል። አቋሙ የሰጠ፣ ሰውነቱ የጠሰቀ ወንድም። ከንግድ ሥራ ኮሌጅ እንደ ተመረቀ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጠረ፤ በሥራው ትጉሕ ነበር። «ክርስቲያኖች ሁሉ በሥራ ገበታቸው ታማኝነታቸው እንደ ነጋ ከሆነ...» የሚለው አነጋገር የውይይት መነሻ ነበር፤ በሚያገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ወደ ክርስቶስ ሮጠው የመጡትን በማሳደግ ደቀ መዝሙር ሆኖ ደቀ መዛሙርት የማብዛት ፍሬውን ሲያስቡ፣ ዛሬም አብረውት ያሉ ወገኖች ይ ረኩበታል። በእድሜው ሠላሳ አራት ላይ የሚወዳትን ለማግባት ሲሰነዳዳ ነው ሆስፒታል መግባቱ የተሰማው፤ የሳምንት እድሜ አላገኝም፤ መቼም ስልክ አብሳሪም አርጂም መልእክት ደርሷል፤ በስልኩ ሁላችንም ለቀብሩ ታደምን፤ በዚያ ግን እኔ እና ወዳጆቼ እግዚአብሔርን «ምኑን አለን እንላለን?» አልነው፣ ፈራነው ዕ ቅዳችንን ሳያስጨርሰን ጣልቃ እንዳይገባ በልባችን ተማጸንነው። የዚያን ሰሞን አከራረማችን «ህልም ነው፤ እውን እውነት ነጋ ሞቶ-ቀበርነው!» የእርስ በርስ ድንጋጤአችን ሆነ። «ግን እውነት ለምን እግዚአብሔር...?

* * *

ዓለምሽት ናት ሌላዋ መደነቂያዬ። የፈካች ቡቃያ ናት፣ ብዙ ሩጫ፣ ብዙ ፍሬ ከፊት ለፊትዋ እንዳለ የተመሰከረላት እኅት ናት። በዘመድ አዝማድዋ መካከል እንደ አልማዝ ፈርጥ የደመቀች። የመድመቋ ምክንያት የክርስቶስ ፍቅር ነበር። በፍቅሩ ተሸንፋለች፤ ይህ የመረታቷ ውጤት ሁለንተናዋን ለጌታዋ መስጠት ሆነ፤ ብርሃንነቷና ጨውነቷ ዙሪያዋን ሁሉ አበራው፤ አጣፈጠው። ለክርስቶስ ተማራኪ በዛለት፤ ከቤቷ ወደ ጎረቤት፤ ከጎረቤት ወደ አካባቢው ቀበሌዋ ሁሉ ዘመተች፤ በዘመቻ ላይ ሳለች ነው ክርስቶስን አንድ ቀን ለአንድ ብኩን ሰው ያስተዋወቀችው። እርሱ ግን ብስራቱን ተቃወመው፤ አልተስማማም። በምትኩ እርሷነቷ ብቻ ማርኮት ለአጉል ነገር ተመኘት። እርሷ ግን ለሚጠፉት የሞት ሽታነቷን፣ ለሚድኑት ደግሞ የሕይወት መዐዛዋን አዘለቀች። ታዲያ «እምቢየው» የተባለው ሰው እያደር በቀል ሸተተ

ው፤ ወደ ተማሪ ቤታ እየሄደች ሳለ ተከተላት፤ ለሻይ ከጓደኞቿ ጋር አረፈችበት ድረስ መጣ፤ በአቁመ ልቡ በሳለ ስለቱ ወጋት፡፡ የዛኑ ቀን ማታ ላይ ነው ወደ ወደደችው ጌታ መሰብሰቢ የተ ስማው፤ «ዓለምሽት እኮ...» የሁሉም ጎዘን ቅጥ አጣ፣ ድንጋጤና ብርክ ሆነ፡፡ «ሊወስድ ከፈለገ፣ ባልጠፋ መንገድ ለምን እግዚአብሔ ር... ይህን መረጠ?» የብዙዎቻችን ጉምጉም ሆነ፡፡

* * *

በዚህ ጽሑፌ፣ «እግዚአብሔር እንደ ሰው ደክሞት የዓመት ሥራ ፈቃድ ወስዶ ተሰውሮ ነበር እንዴ?» የአሰኙኝን ገጠመኞቼን አብረን እንድንፈታው ነው ፍላጎቴ፡፡ ለምን የመረረ ሥቃይና መከራ ጌታን በትጋት በሚያገለግሉት፣ በሚወድዱትና በሚያፈቅሩት ላይ ይሆናል? ጥንቁቁ ኢዮብ ራሱ በደል እንዳይገኝበት ብቻ አይደለም፤ ምናልባት ልጆቼ እግዚአብሔርን አሳዝነውት ቢሆን ይል ነበር- መሥዋዕትን ዘወትር ስለ እነርሱ እያቀረበ፡፡ ሰርክ ይህን እያደረገ ሳለ የመከራ ጦርፍ ጊዜ ሳይሰጥ ጎረፈበት፣ ጦርፉ በምንም አልተ ገታም-ሙልጩን አወጣው፤ ምናልባትም መፍትሔ እንኳን ቢሆን ተብሎ ወዳጆቹ፣ ሚስቱም ጭምር መላ መላውን መቱ፡፡ እግዚአብሔር ግን በእርሱ ላይ ያነጣጠረውን የመከራ ዒላማ በድግግሙ አነጣጠረበት፣ አልሳተውም፣ ሁሉን አሳጣው፣ ራሱንም በቁሙ አፈረሰው፡፡

* * *

. . .በሦስት ጉዳዮች ሦስቱ ለምን? ለምን? ለምን አልኳችሁ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ከለምን? ይልቅ ቀድሞ «መቼ፣ እንዴትና በማን መከራና ሥቃይ ሆነ» ይላል፡፡ ለዚህም ምላሹ፡- መከራና ሥቃይ የሰው ልጅ የሕይወት ባልደረባ የሆነው ገና ከጠዋት ነው፡፡ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር እውነት ላይ ተ ጠራጣሪ ሆነው ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰይጣን መታዘዝን ሲመርጡ፣ ያንንም ባለመታዘዝ ሲያጸኑት፤ በዚያን ጊዜ፣ በዚያን ቅጽበት በሰው ዘር ላይ መከራና ሞት ከተፍ አለ፤ ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ፤ ከያኔ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ወደፊትም ሊዘልቅ ያኔ መከራ በሰው ጀመረ፡፡ በዘፍጥረት ሦስት እንደተመለከተው፣ የሰው ዘር ብቻ ሳይሆን፣ በሰው ጦስ ምድሪቱ ጠላትነት ለሰው

እንዲኖራት ሆነ። ሆኖ የማያውቀው እሾህና አሜኬላ አብቃይነት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በመርዶነት ለሰው ደረሰ፤ ምድርም ለመከራ ተዳረገች። ሰው በራሱ ከተሸከመው መከራ በተጨማሪም ፍጥረትም የመከራን መዋጮ በሰው ላይ ታደርግ ዘንድ የኃጢአት ውጤት አመጣው። በተለይ ክርስቶስን ማመን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን አስገኘ እንጂ፣ ከመከራ ነፃ አለማድረጉንም ልብ በሉ። ከዚህም የተነሣ ነው የመከራ ሕይወት ተካፋይነት ባለፉትና ባሉት ቅዱሳን ሕይወት ሳያቋርጥ የቀጠለው። ራሱ ጌታ ክርስቶስ በኢሳይያስ ሃምሳ ሦስት ላይ፣ «...እኛ ልንሸከመው የሚገባንን መከራና ሕማም እርሱ ተሸከመ፤ ይህም በእርሱ ላይ የደረሰበት ግርፋትና መከራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተላከ ቅጣት እንደ ሆነ አድርገን አሰብን» ተባለላት። እንደተተነበየውም ሆነበት። ጌታ ክርስቶስም ከመከራ ነጻ አልነበረም፤ ሐዋርያቱንም ብንመለከት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚዘክረው ኑሮአቸውና አሟሟታቸው አሰቃቂ ነበር።

መከራ ዓይነተ ብዙ ነው። በውጤቱ ሞት የሆነው ላይ ቅድሚያ ትኩረት ሰጠሁ እንጂ፣ የቁም መከረኞችም አሉ። እስቲ የወጣቷን የአልማዝን ታሪክ ላውጋችሁ፤ በአምስት የትዳር ዓመታት አስቴርንና ናትናኤልን ከትዳር ጓደኛዋ ታፈራለች። ኋላ ላይ አልማዝ ክርስቶስን በማመን ክርስቲያን ትሆናለች። እምነቷ ለአደባባይ ሲበቃ ትዳር ላላ፣ ፍቅር ረገበ፣ ጎበረት ወደመ። «እምነትሽን ካልተውሽ እፈታሻለሁ፣» የባል የዘወትር ማስፈራሪያ ሆነ። አቋሟ ስለ ጸና፣ ላለመብላትና ላለማደር ወሰነ-ለአንድ ዓመት ያህል። ይህንን ጉድ አልማዝ ታገሠች፣ ይብስ ብሎ ግን ታናሽ እኅቷን በሌለችበት አስገድዶ ደፈራት። አልማዝ ይሄኔ በቃት፤ እንዲህ ዓይነቱን የከፋ ተግባር መሸከምም አቃታት። ቤቷን ትታ፣ ትዳሯን ሰብራ ብን አለች። ይህ ከሆነ ደግሞ ዓመታት አለፉ። ዛሬ አልማዝ ያለ ቋሚ ገቢ ልጆቿን ለማሳደግና ለማኖር ደፋ ቀና ትላለች። ይህም የቋሚዎች መከራ ነው- «ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች»፣ የሚያሰኝ ለምን እንዲህ ሆነ የሚያስብል።

* * *

በመሠረቱ፣ ሰው ሁሉ ሟች ነው። ጌታ በመሀል ካልመጣ በቀር

ዛሬ በሕይወት ያለን ሁላችን በእርሱ ጊዜ መሰብሰባችን - መሞታችን አይቀርም። ታዲያ እኮ እግዚአብሔር ከብዙ የመውሰጂያ መንገድ አንዱ፡- በመከራና በሥቃይ በማሳለፍ ወደ ሞት ማድረስ ነው። እርግጥም፣ ያደርስለታል፤ ከ-አደረሰለት ደግሞ አስፈላጊ ነው፤... ታዲያ እንዳንዘናጋ ቅዱስ እግዚአብሔር መከራን ለሰው አላመጣም፤ ሰው ከመነሻው በራሱ ምርጫ አመጣው እንጂ። ይልቅ፣ እግዚአብሔር ከመከራና ከሞት ለዘላለሙ ነጻ የምንሆንበትን የአርነት ቀን አዘጋጅቶል፤ ዐቅዷልም። 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡55ን ለምን አናጤነውም! ይህን እያጤንን ከወዲሁ ለካስ ለዚህ ኖሯል? የሚያሰኝ በጎ ውጤትም ስላለው፣ መከራ እንዴት መከረንን አብረን እንይ። ለዚህ መረጃዬ ጴጥሮስ ነው በ1ኛ ጴጥሮስ 4፡12-16 «ወዳጆቼ ሆይ፣ እንደ እሳት በሚፈትን መከራ ውስጥ ስትገኙ ያልተለመደ እንግዳ ነገር እንደ ደረሰባችሁ አድርጋችሁ አትደነቁ... ክርስቲያን በመሆን መከራ የሚደርስበት ቢኖር ስለ ክርስቶስ ስም እግዚአብሔርን ያመሰግን እንጂ አይፈር...» ይላል። መከራ እንግዲያስ ዘርን እንደሚያበቅል የለማ መሬት ወይም አፈር ሊቆጠር ነው። በዚሁ አባባሉ በእርሱ ላይ የተዘሩትን ለፍሬ የሚያበቃ በመሆኑ። ቃሉ፣ «ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ ፍጹሞች ያደርጋችኋል» (1ኛ ጴጥ. 5፡19) ይላልና።

* * *

ሌላው ተደራቢ ጥቅም መከራ ወደ እግዚአብሔር መጠጊያ፣ እግዚአብሔርን ማስታወሻ መሆኑ ነው። የሰው ዝንጉነት የሰው ልጅ ድካም ነው። በዙሪያው ባሉት በተመቻቹ ሁኔታዎች ሲዋጥ ወይም የሰው ውክቢያ ሲበዛበት፣ እግዚአብሔርን ይረሳል። በክርስቲያንነቱም ሊፈጽመው የሚገባውን ግባዊ ሕይወት ይተዋል፤ በአዘናጊ የሕይወት መንበሽበሾች የተረሳው እግዚአብሔር በመከራ ጊዜ ሊታወስ ይችላል። መከራ ክርስቲያንን እየተቀረጸ ወደ ሕያው እግዚአብሔርና ወደ አሳቡ አድራሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣ ችሏልም።

* * *

ልጃቸው ዛሬ ሠላሳ ዓመቷ ነው። ሠላሳውንም ዓመት ያሳለፈችው ተሣሥራ በአልጋዋ ላይ ነው። ዛሬም እንደዚያው

አለች። ምንም ማድረግ ስለማትችል፣ ፍላጎቷን ሁሉ የሚሆኑላት እናት-አባት ናቸው፤ እነርሱ ስለ ልጃቸው ሲናገሩ፣ «እግዚአብሔር እኛን ለመቅረጽና ለክብሩ ለማቆም ያለፉትን ሠላሳ ዓመታት በልጃችን በኩል ወደ እኛ መጣ» ይሉለታል፤ ሽባነት ያውም የሌላ ሰው ሽባነት ሌላውን ቀርጾ ለምስጋና አበቃ። እንዲህ ከሆነስ፣ የመከራ ግቡ የእምነታችንን እውነተኛነት ማረጋገጫና ሰላም የሞላበትን የጽድቅ ሕይወት ማጽኛ ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡7፤ ዕብ. 12፡11)።

* * *

በቅርቡ በአንድ ክርስቲያን ወንድም ቀብር ላይ ለተሰበሰበው ኀዘንተኛ ቃለ እግዚአብሔር ያሰሙት መጋቢ የተናገሩት ትዝ ይለኛል፣ «ይህ ወንድማችን የዘመኑን ግማሽ በበሽታ ገፋው፤ በዚህ ሥቃይ ውስጥ ሆኖ ከመንፈሳዊ ኮሌጅ ተመረቀ። እያነከሰ ሰበከ፤ አስተማረም። ታዲያ እኛ በዚህ ሁሉ አገልግሎቱ «እግዚአብሔር አያልፈውም፣ አንድ ቀን ይፈውሰዋል» እንል ነበር። አሁን ግን «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህን እሰብክላችኋለሁ።» ከእናንተ አንዳንዱ ግን «ሳይፈውሰው ከሚገድለው ምን ነው» ትሉ ይሆናል። በሽታው እንደ ጀመረው ቢጨርሰው ለማለት ነው። የእኔ ምላሽ ግን «የሕይወት ምንጭ እርሱው ነው፤ ወሳጅም እርሱው ስለሆነ፣ ማን ከልክሎት ነው።» እግዚአብሔር በዕብራውያን 11፡36-37፣ «ሌሎች መዘባበቻ ሆነው ተገረፉ፣ ሌሎች በእግር ብረት ታሥረው ወደ ወህኒ ቤት ተጣሉ፣ በድንጋይ ተወገሩ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተገደሉ፣ የበግ፣ የፍየል ቆዳ ለብሰው ተንከራተቱ፣ ድሆችና ስደተኞች ሆነው ተንገላቱ» በማለት የምስክር ቃሉን ይሰጣል። ሊሆን ያለው ይሆናል ማለት ነው። በታላላቅ የእምነት አባቶች ይህ ከሆነ፣ በእያንዳንዳችን ላይ በገጠመን ወይም በሚገጥመን መከራ የሕይወት አረማመዳችን በጽድቅ ጎዳና እንኳ ቢሆን ፈጥኖ ደራሽ መልስ በሌለው በ «ለምን» ጥያቄ ውስጥ መዘፈቅ ላይኖርብን ነው። እግዚአብሔር እኮ ለኢዮብ ምንም ምላሽ አልሰጠውም። ኢዮብ ግን ሳይሰለች ጠያይቆት ነበር - «ለምን የተነሣ ሆነብኝ? በማለት።

ኋላ ግን ጭራሹኑ እግዚአብሔር ኢዮብን ጠየቀው። ለቀረበለት ጥያቄ የኢዮብ መልስ ዝምታ ነበር። የልዑሉ እግዚአብሔርን ሁሉ-

አዋቂነት፣ «ሉዓላዊነትና ሁሉን ቻይነት» በነገሮች ሁሉ ላይ ሲያስተውልና ሲገነዘብ፣ የቀደመውን «የለምን» ጥያቄና ንትረካ ትቶ መደነቅን «ሀ» ብሎ ጀመረ (ኢዮብ 38-42)። ከዚህ የተነሣ፣ ክርስቲያን በገጠመው ነገር ለምን? ለምን? ብሎ ከእግዚአብሔር ጋር ከመሟገት ይህ መቼ ያበቃ ይሆን? ብሎ ማጤን መልካም ይሆናል። የኢየሱስን ድርጊት እንዳንረሳ- ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ አለቀሰ፣ ስለ አልዓዛር ኀዘን የገባቸውንም ባየ ጊዜ እንዲሁ። ለምን ነበር ያለቀሰው? ለዚህ ምላሽ ማግኘት በውጤቱ ፍሬ ያፈራልና እናጢነው።

ወደ ተነሣሁበት ልመለስ። በጽሑፌ ውስጥ እንደ አነሣሣኋቸው ነጋ እና ዓለምእሸት ወይም የቅርቡን ተሸኚ የመሰሉ ገጠመኞች ገጥመዋችሁ «ለምን?» ብላችሁባቸው ይሆናል። ሁል ጊዜ ግን ይህን ከግምት አያስገቡ። የመከራ መንሥኤ ሰው ራሱ መሆኑን ተረዱ። እግዚአብሔር ሰውን ሊያሳቅል ገና ከመነሻው የወሰነለት አለመሆኑን አትዘንጉ። ክርስቲያን ስለ ሆናችሁ ከመከራ ነጻ የመሆን ዋስትና እንዳላችሁም አትቁጠሩ።

ሽክላውን እርሱ እንደ ወደደው እንደ ዐቀደው ይሠራዋልና እግዚአብሔር ያሰበውን እንዲፈጽምብን ሁሉን ለእርሱ እንተ ውለት።

ታዲያ አንዘንጋ፣ በዘመን መጨረሻ ላይ አለንና በቅርቡ እንዲህ ይሆናል፣ «እንባችን ሁሉ ከዐይናችን ላይ ይታበሳል፤ ሞት ወይም ኀዘን ወይም ለቅሶ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖሩም። ምክንቱም የቀድሞዎቹ ነገሮች ሥርዓቱ ሁሉ አልፏል» ይላልልናል፣ ይሆናልም (ራእይ 21፡4)።

ላጤነት እና ዘንድሮ

ላጤነትህ(ሽ) ዘንድሮም ቢጨምር ግላዊ አስተያየትህ(ሽ) ምን ይሆናል? ምላሹ በርካታ ነው። ጥቂቶቹን ልጠቃቅስ።

* * *

«ብቻዬን እንደ ሆንኩ አልገምትም። ዘንድሮ ከአጋሮቹ ጋር ያለኝ ጎብረትና ቤተ ክርስቲያኔ ላላገቡት የምትሰጠው እንክብካቤ ከሰው የተለየ ነገር እንደሌለኝ አስቆጥሮኛል። ይልቁኑም፣ ቤተሰብን ማስተዳደር ከባድ ይመስለኛል። ከእኔ ይልቅ በአንድ ወቅት ትዳር ይዘው ተፋትተው ወይም በሞት ተለይተው ላሉት ዳግም ላጤዎች ይጨንቀኛል።»

(በዕድሜው 33ኛ ዓመት ላይ ያለ ወንድም ምላሽ ነው)።

«ፍርሃት በእጅጉ አለብኝ። ባለማግባቱ ወላጆቼ፣ የአገቡ ወዳጆቼና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በምን ትጠብቂያለሽ?» ይጫኑኛል። ከዚህም የተነሣ «የተገኘውን...» ወደሚል ዝንባሌ አንዳንዴ እነዳለሁ። ከፍርሃቴ ነጻ ለመሆን የማላውቀውን ከምዘርፍ የተፈተነውን እንዳይ ዘንድሮ ራሴን አበረታታዋለሁ።

(በዕድሜዋ 30ኛ ዓመት ላይ ያለች እኅት ምላሽ ነው)

«ጓደኞቼ ሁሉ ሲያገቡ የተመለከተው ዐይኔ፣ «አንዳንድ እያሉ ሲዳሩ፣ አንቺ ግን የተተውሽ ነሽ» አለኝ። አንዳንዴ እራሴን ብቻ እያሰብኩ፣ ለራሴ ባይተዋር እየሆንኩ በአሳብ እዋጣለሁ፤ ተስፋም ሀብቱን ሁሉ ይዞ የኮበለለ ይመስለኛል።

«ከዚህ የበለጠ ቅር የሚለኝ ግን የቤተ ክርስቲያኔ መጋቢ በሁሌ ስብከቱ ባለትዳሮችን እያበረታታ ሲያስተምር እኔና መሰሎቼ በትምህርቱ አለመጎብኘታችንና አለመታሰባችን ያሳዝነኛል። እርግጥ፣ ዘንድሮም የማይቀር ነገር ቢኖር ቤተ ክርስቲያን የግብዣ ዝግጅቶችዋንና ኮንፍራንሶችን ስታዘጋጅ የጉልበት ሥራ ላይ ጥሪው ለላጤዎቹ መሰጠቱ አይቀሬ ነው ባይ ነኝ።»

(የ35 ዓመቷ እኅት ምላሽ)

«ዕድሜዬ 39 ነው፤ አላገባሁም። ሰዎቹ «አሁንማ የባንክ ገንዘብህ ደልቧል፤ ወጪ የለብህም፤ ሚስት አትል ድስት!» ይሉኛል። ተከራይቼ መኖሬን፣ በሆቴል መመገቤን፣ የስልክና የመብራት ሂሣብ መክፈሌን፣ ሁለት ወንድሞቼን ማኖሬን፣ የፍቅር ስጦታና መባዬን አለማስተጓጎሌን ከቁብ ሳያስገቡ እንዲህ ማለታቸው ቅር ያሰኘኛል። ታዲያ ዘንድሮ እነዚህን ማን አደብ ግዙ ይልልን ይሆን?»

(ለአርባ አንድ የቀረው ወንድም ድምጽ)

«ዕድሜዬ 31 ነው፤ ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች» የሚያሰኝ የቤት ልጅ ነኝ። «ከሞቱት በላይ፣ ከቆሙት በታች» የሚያሰኝ ማለቱ በክርስቲያን ቤተሰብ አድጌ ወደ ጌታ የመጣሁ ነኝ። ምንም ሌላ ልምምድ የለኝም። አንድ ቀን ወደ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ተጋበዝኩኝ። ሁሉም ያገቡ ናቸው። ጥናቱ እንዳለቀ ብዙዎች ምክራቸውን ለጋገሱኝ። «ለማግባት መዘግየት ጥሩ አይደለም» አሉኝ። ተስማማሁ። ግን አቀራረባቸው እንደ «ሚጢጢ ልጃቸው» ስለ ነበረ፣ በሸቅሁ። አለማግባት ማለት ከትልቅ አስተሳሰብ መጉደል ማለት አይደለም። ይህ አገማመት በብዙዎች ዘንድ ላጤዎችን ለታላቅ ኃላፊነት እንዳያበቃቸው አድርጎአቸዋል ባይ ነኝ።

(የእኅት «እንትና» መልስ)

«ላጤዎችን ከትልልቅ ጉዳዮች ማዕድ ዙሪያ ገለል ለማድረግ ከመፋጠናቸው በፊት በአግባቡ ይመልከቱን እላለሁ። ባለማግባታችን እንደ ሙሉ ሰው አንታሰብም። በክርስቶስ አካል ውስጥ ያሉ ብልቶች ሁሉ በሰውነታቸው ሙሉ ሆነው እርስ በርሳቸው ተገጣጥመው እንዲሠሩ መበጀታቸውን ይዘነጉታል፤ ባለማግባት ጉድለት ካለማ፣ ጳውሎስም ጉድ ፈላበት፣ ጌታም ጭምር። ስለዚህ በዘንድሮው ላጤነቱ ሙሉነቴን እያሰብኩ በጌታ ተደግፌ እዘልቀዋለሁ።»

(የ35 ዓመት ወንድም ምላሽ)

«ብዙ እኅቶቼ ክርስቲያን ወንድም አግብተው መልካም ልጆች ለማፍራት ይጓጓሉ። እኔም እንደ እነርሱ ነው የማልመው። በ18 ዓመት ዕድሜዬ ላይ ግን የጸለይኩትን አልዘነጋውም። «እግዚአብሔር ሆይ፣ በኑሮዬ፤ ጣጣ ሁሉ ላይ ኃላፊዬ አንተ ነህ፣ የሚበጀኝን አዘጋጅልኝ፣ እንዳስተውልም እርዳኝ» እለው ነበር። እናም ጌታ ባልን ቢያዘጋጅልኝ መልካም፣ ባላገባም ደግሞ በዚህ ሁኔታ እንድኖር ፈቅዷልና፤ ሁሉንም እሺ ባይ ነኝ...»

(ሦስት አሥሮችን ያስቆጠረች እኅት)

«በላጤነቴ ደስ ይለኛል። በዚህ ዓይነት ሕይወት ገና ጥቂት ዓመታት እመርቅበታለሁ። ለመንፈሳዊ ሕይወቴ ተገቢ ስንቄን

እየሰበሰብኩ ነው። የሰበሰብኩትን እያካፈልኩ ነው። እማራለሁ አገለግላለሁ። ወላጆቼ ግን ተመርቄ ሥራ መያዜን ብቻ መመዘኛ አድርገውት አግባ ይሉኛል። ለምን አገባለሁ? ዋጋ የሚያስከፍለውን ትዳር ከመኖሬ በፊት መገራት እንዳለብኝ ለምን ሰዎች አያስተውሉም? ከአምና ይልቅ ብዙ ልሠራ ቆርጫለሁ-»

(የ25 ዓመቱ ወጣት)

«ዕድሜዬ 28 ዓመት ከመንፈቅ ነው። ሦስቱ ጓደኞቼ አግብተው ወልደዋል። በትዳራቸው ደስተኞች ናቸው። በእርግጥም ናቸው። ከዚህም የተነሣ ባገባ የእነርሱ መልካም ዕጣ እንደሚገጥመኝ ነግረውኛል፤ እስማማለሁ። ግን «ጌታን አመስግን፣ የጌታ የሆነውን ነገር በሙሉ ልብህ የምትፈጽመው እንደ እኛ ሳትሆን ነው ይሉኛል።

«ድሮስ እላቸዋለሁ፤ ጳውሎስ በአዲስ ኪዳን የቱ ጋ ተጋቢዎችን ለጌታ ሥራ ሲያደፋፍር ታየ? የእኔ ቢጤዎቹን አይደል ለጌታ ሙሉ ነገር እንዳላቸው ያበሰራቸው። እውነት እኮ ማግባት ልብን ይከፍላል እላለሁኝ።»

(ልቡ ካልተከፈለበት ከሚተጋው ወንድም የተገኘ መልስ)

«ከስድስት ወር በኋላ 34ኛውን ዓመቴን እያያዘዋለሁ። የቤተ ክርስቲያኔን ሰዎች እንደ ቤተሰቤ እቆጥራቸዋለሁ። እነርሱም ቆጥረውኛል ብዬ አስባለሁ። ለማግባት መዘግየቴን አጠንክረው አያነሡብኝም። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ «መሸብህ» የሚል ድምጽ ይሰማኝና እደነግጣለሁ። ሰሞኑን ግን የተጽናናሁበት ነገር አለኝ። መጽናናቴም ዘንድሮን ያዘልቀኛል። ይኸውም «ጠቢብ ሰው በሌላው ነገር ሊያዝን አይገባውም፣ ባለው ግን ሊደሰት ይገባዋል» የሚል ነው። ዓይኖቼን በጌታ ላይ አድርጌ እዘልቀዋለሁ።

(ባለው ነገር ሊደሰት ከወሰነው ወንድም የተደመጠ)

* * *

ዘንድሮን አስመልክቶ የብዙ ላጤዎችን መልስ ሰማን። የእግዚአብሔር ቃልስ የሚያብራራው እንዴት ይሆን?

«ነገር ግን ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል፤ ያገባው ግን

ሚስቱን እንዴት ደስ እንደሚያሰኛት ያስባል፤ ልቡም ተከፍሏል። ያልተጋባ(ች)... በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ፤ የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንድታሰኘው ታስባለች» (1ኛ ቆሮ. 7፡32-36)።

* * *

አንድ ትኩረት ስለሚደረግባቸው ዓቢይ ጥቅሶች ያጠና ሰው በጥናታዊ ጽሑፉ እንዳስገነዘበው፣ በወጉ ትምህርት ያልተሰጠበትና ባለመጠቀስ ቀዳሚ ከሆኑት ጥቅሶች ውስጥ አንዱ ይህ 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡32-35 መሆኑን ያረዳል። ለምን ተተወ?

- መጋቢዎች ስላላገቡት ሽክም ስለሌላቸው?
- ባለማግባት ተጠርጣሪነት ስላለ?
- እንደሚሉት «ያላገቡ ቀልበ-ቢሶች» ስለሆኑ?
- ለጠንካራ ቤተ ክርስቲያን የባለትዳሮች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለሆነ?
- የጥቅሱን ሐቲት ማዘጋጀትና ሥነ አፈታቱንም ማቀናበር ስለሚከብድ? ይሆን ይሆናል።
- ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለታደምን ለእኛ የተወልን ሥራ ወንጌሉን ማብሰር፣ ማጥመቅና ማሳደግ ነው (ማቴ. 28፡19-20)።

ታዲያ ይህንን አደራ ለመፈጸም ለጌታ የሚመቸው ማን ነው?

- «በቅሌን ማቄን» ያልተተበተቡት፣
- ሁለት የተወደዱ ነገሮችን ይዘው ሚዛን ደፊውን ለመለየት ያልተቸገሩት፣
- እውቀታቸውንና ዝንባሌያቸውን ሁሉ ሙጥጥ አድርገው የሚቸሩት እነርሱ «እግዚአብሔርን በሙሉ ልባቸው ያገለግሉታል።» ያላገቡትን ላጤዎች ማለት ነው። እንኪያስ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ላይ ይሁን እግዚአብሔር ለዘንድሮ ልባቸው ያልተከፈለባቸውን ላጤዎችን ይፈልጋል።

ታዲያ ለመሰረግ የተመቻቸ ነገር ያላችሁ ደግሞ ሰርጋችሁን ማፋጠን አትርሱ።

ትጭጭት እና ዘንድሮ

ሁሉም የሕይወት ገጽታ የየራሱ ቅድመ-ዝግጅት አለው። ትዳር አንድ የሕይወት ዘርፍ ነው። በዚህ መንገድ ማለፍ የተገባው የትኛውም ሰው በዛሬ ዛሬ ሁሉን ነገር ከውኖ ዛሬ ሰርጌ (የጋብቻዬ ዕለት) ነው አይልም። ይልቁኑ፣ አስቀድሞ ይዘጋጃል፣ ይደራጃልም።

በዝግጅት ውስጥ የእናት አባቱን ፍልሚያ ተወጥቶ ለድል በበቃው ጉብል ታሪክ ልጀምር። በጊዜ ውስጥ በእኩል ፍቅር ካስተናገዳቸው ብዙ ሴቶች መካከል አንዲቷን ለመውደድ ራሱን ያዘጋጃል፤ «ምርጫዬ ነሽ» ከማለቱ በፊት ወደ ቤተሰቡ ይወስዳታል፤ እናትዬው አዩለት፣ ጠሏትም። በሌላው ጊዜ ልጅዬው ፈተናውን ማለፍ የሚችለው በወላጆቹ ልትወደድ የምትችል ጓደኛ ስትኖረው እንደ ሆነ አሰበ። ያንንም እንደ አንድ ተጨማሪ መስፈርት አድርጎ ወሰደው። ከወራት በኋላ ተሳካልኝ ብሎ በሌላው ቀን በሌላው ዓመት ሌላ ቆንጆ ይዞ ከተፍ አለ፤ እናት ዛሬም ምርጫው የሆነችውን ሴት ሲያዩ ፊት ነሷት። አትራራልህም፤ ፍላጎትህን አታውቅልህም፤ መልሳቸው ሆነ። ሌላ ድካም ለልጅዬው።

ኋላ ላይ መሳካቱ አይቀርምና ከብዙ ሙከራ በኋላ እናቱ የሚወዱለትን ልጅ አስተዋወቃቸው፤ ወደዷት፣ ችግሩ ግን አባቱ ደግሞ ልጅቱን ነቀፉ፤ ፈጽመውም ጠሏት፤ «አያገባትም» ብለው ወረፉ። በጋብቻ ቅድመ-ዝግጅት ላይ የተነጣጠረ ሳንካ። ወጣቱ ግን ተስፋ አልቆረጠም፣ ይህንንና ያንን ተቋቁሞ አንዲት ልጅ አጨ።

* * *

ግሪኮች በጽንሰ አሳብ ላይ ከመወያየታችን በፊት አወያዩን ርእስ በቅጡ እንወቀው ይላሉ። የየቃሉን ፍቺ አጢነው ከተስማሙ በኋላ ነው ውይይት የሚጀምሩት። እኔም በእነርሱ እምነት «ትጭጭት» ወይም «አጨ» ምን ማለት ነው? የሚለውን ላብራራ።

ደስታ ተክለ ወልድ በዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት «አጨ ቃል ኪዳን አሠረ፣ አብሮ ለመሆን ተስማማ» ሲሉት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ደግሞ፣ «ከጋብቻ በፊት ዘላቂ ኅብረትን ለመመሥ

ረትና እርስ በርስ ተግባብተው ለመኖር የሚያበቃቸውን ጓደኝነት ጀመሩ፣ ወይም ለመመሥረት ተስማሙ፣ ወይም ለዚሁ ተግባር ተመራረጡ» ይለዋል። እኒህ ትርጉሞች የዘንድሮ የትጭጭት መልእክቴን ያጎሉልኛል ብዬ እንደ ሁነኛ ፍቺ ተቀብዬአቸዋለሁና እናንተም ተቀበሉልኝ።

* * *

ማጨት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንግዳ ጉዳይ አይደለም፤ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን አነሣስተውታል። እስራኤልን እግዚአብሔር በድግግም «አጭሻለሁ» ይላታል (ኤር. 2:2፤ ሆሴዕ 2:21-22)። አዲስ ኪዳን ደግሞ በጳውሎስ አንደበት ቤተ ክርስቲያንን ለክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ንጽሕት ድንግል ለአንድ ወንድ እንደ ታጨች ያበስራል (2ኛ ቆሮ. 11:2)። ብሉይም አዲስም መመረጥና መለየትን፣ መወደድንም ያበስራሉ። የዚህ ምልልስ ተግባር በተዋደዱ በሁለት ግለሰቦች ሕይወትም ይቀረጻል።

ዳዊት ለሳኦል መልእክትን ሲልክ፣ «...ያጨኋትን ሚልኮልን ስጠኝ» (2ኛ ሳሙ. 3:14) ብሎት ነበር፤ ሰጠውም። ዮሴፍንም አስመልክቶ በማቴዎስ 1:24፣ «እጮኛውን ማርያምን ወደ ቤቱ ወሰዳት...» ይለናል። እንኪያስ ከጋብቻ በፊት ካሉት ቅድመ-ዝግጅቶች ውስጥ አንዱ ትጭጭት መሆኑን ይጠቁማል፤ ተስማምቶ ጓደኝነትን መጀመር። ያው የሕይወት ገጽታ ነው ዛሬ ያለው።

* * *

እስቲ በጋራ ሆነን ቅድም አንዲት ልጅ አጨ ወዳልኋችሁ ሰው ልመልሳችሁና በትጭጭት ወቅታቸው ምን ዋነኛ ጉዳይ ማወቅ አለባቸው? የሚለውን እንመልስላቸው፤ በምክር ፍጻሜአችን ላይ ደግሞ ሌሎችን የዚህንና መሰል ሕይወት ተጋሪዎችን «ጆሮ ያለው ይስማም» እንላቸዋለን።

ሁለቱ ጓደኝነትን ለመመሥረት የተስማሙት አንደኛው ወንድ ነው፤ ሌላኛዋ ደግሞ ሴት ናትና ይህ መሠረታዊ ልዩነት ነው። ሁለቱም ከተለያዩ ሁለት ቤተሰቦች የተገኙ ናቸው፣ የየራሳቸው ዘመድ አዝማዶች ያሏቸው፤ የሁለቱም አስተዳደግ ለየቅል ነው፤

ልምምዶቻቸውም አይገናኙም። ለየነገራቱ አድናቆታቸው ይለያያል፣ ልዩ ልዩ ስሜት አላቸው። ያው አንዱ ነገር እርሷን ያዝናናታል፣ እርሱን ደግሞ ያስቆዝመዋል፤ ሁለቱም ሕይወትን የሚመሩበት አቅጣጫ ግጥምጥሞሽ የለውም፤ ሁለቱም የእኔው እምነት ነው የሚሏቸው የየራስ መረዳቶች አሏቸው። እነዚህ ሁለቱ ናቸው ጓደኝነት የጀመሩት። ፍቅርም ይጠነክራል፣ ግጭትም ይጨምራል። ሁለቱም ገጠመኞች የጤናማ ግንኙነት ውጤቶች ስለሆኑ፣ መሆናቸው አይቀሬ ነው። ጓደኞሞቹ ከላይ የተነሡትን ገሃድ እውነታዎችን መካድ አይችሉምና መፍትሔው መጋፈጥ ብቻ ነው። ሁለቱም የልዩነቱን ምክንያቶች በገዛ ፈቃዳቸው አላመጡትም፣ ሆኖ ተገኘ እንጂ። ስለዚህ «ልንጋፈጠው ይገባል»ን መቀበል አለባቸው።

ሌላኛውን ሊታወቅ የሚገባውን ቁም ነገር ልዘክር። በአንድ ወቅት የሥነ-አእምሮ ጠበብት የሆኑት አማካሪ፣ «ጓደኞሞች በበለጠ እንዲፋቀሩ የምትረዷቸው እንዴት ነው?» ብሎ ወዳጃቸው ይጠይቃቸዋል። «አንተኑ ልጠይቅህ፣ ጥርስህን በጽኑ ታምመህ በነበረበት ጊዜ ስለ እነማን ታስብ ነበር?» «ስለ ሕመሜ ብቻ» መልሱ ፈጣን ነበር።

በዚህ ምላሽ ላይ ተንተርሰው ነበር የማፍቀር ጥበብን የገለጹለት። «ይህ ዓለም ባልተቋረጠ መከራ የተሞላ ነው፤ ሰው ሁሉ የየራሱ የሆነ ሁነኛ ችግር አለው፤ ብቸኝነት ጭንቁ ነው፤ የተስፋ መቁረጥ ዘር በውስጡ አለ፤ የእግዚአብሔርን አሳብ የመረዳት ድህነትም አለው። አለመሳካቶች ሁሌ መጣንብህ ይሉታል። ከእነዚህም የተነሣ በጎዘን የተመታ የሰው ልብ እንደ ጥርስ ሕመም ነው። ሕመም በሕክምናም ሆነ በሌላ ዘዴ ይታገሣል፣ ይተዋልም። የውስጥ አለመረጋጋት ግን አብሮ ይውላል፤ በምሽት አልጋ ላይ ይወጣል። ቅዠት ሆኖ አድሮ ስትነቃም «የሙጥኝ በዚህ ነኝ ይልሃል፤ ያስቸግርሃል።» ሁለት ጓደኞሞች ፍቅርን በማሳደግ ስኬ ታማ ወደ ሆነ የጋብቻ ሕይወት እንዲዘልቁ በትጭጭት ወቅታቸው ይህን ቀዳሚ እውነት አስቀድመው መቀበል አለባቸው። ሁለቱም የፍቅር ደሃ መሆናቸውን ማወቅ ይገባቸዋል።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ልዩ አድርጎ ነው የፈጠረው፤

ማንም ማንንም መሆን አይችልም። ይልቅ፣ ሁሉም እግዚአብሔር በቸርነቱ በውስጡ ያስቀመጠለት ክቡር መዝገብ አለው- ማፍቀር። ታዋቂው ደራሲ ጆን ፓውልና ዶክተር ዶብሰን «በጓደኝነት ጊዜ ከመፈቃቀር የሚያሸሽን ችግር» በተሰኘው ጥናታቸው፣ «ሁሉም ሰው በውስጡ ያልተፈለቀቀ ጽጌረዳ ነው» ይሉለታል። ጽጌረዳ እንዲጸድቅ ከተፈለገ፣ ሊመቻችለት የተገቡ መሠረታዊ ነገሮች አሉለት። በቂ የፀሐይ ብርሃን፤ ምቹ ለም መሬትና የዘወትር እንክብካቤ ያስፈልጉታል።

ይህ ከሆነለት፣ ፈጣን ዕድገት ያሳያል፤ በቅጠሉ ተሸፍኖ ያልታየው ጽጌረዳ ወቅቱን ጠብቆ ሲገለጥ፣ ለሁሉም ዓይን ማረፊያ ይሆናል። የሚጸድቀውም ለዚሁ ነው። ግን በትይዩ፣ ይህ ተክል አጓጉል ቦታ እንዲበቅል ይሆናል፣ ሳይመቸውም ይቀራል። ውጤቱ መቀጨጭ፣ መድረቅ፣ መውደምም ይሆናል። በውስጡ ሊገለጥ የነበረ ዕፁብ ጽጌረዳ እንደ ነበረው ማንም አያስብለትም፤ አልታየማ፣ የለማ። ልክ እንዲሁ ነው ይላሉ ፓውሎና ዶብሰን በጓደኝነት የትጭጭት ወቅት ላይ በሁለቱም ውስጥ በጋራ ሊገለጥ የሚገባውን ፍቅር ለመግለጥ ሁለቱም አንዳቸው ያንዳቸውን ሕይወት መኮትኮት፣ ማረምንና ማጥራትን ሁሌ ሥራዬ ብለው ሊይዙት ይገባል። እንደ ትጉሕ አትክልተኛ መሆን ሲቻል ጽጌረዳው ይፈለቀቃል፣ ይገለጣልም። «ጓደኛሞችን ይበልጥ እንዲፋቀሩ የሚ ረዱት እንዲህ ነው።» ለጥያቄው ምላሻቸው ይህ ነበር።

መቼም ዘንድሮ እና የመጪዎቹ ዓመታት ጥንድዬዎች በትጭጭት ወቅታችሁ በየዘርፉ ብስለትን ማየት ግዴታ ነው። ላብራራው። ለምሳሌ፣ **በአስተሳሰብ ወደ ብስለት** ማምራት አንደኛው የተሻለን አሳብ ይዞ ቢመጣ ተመካክሮ ግራ ቀኙን አይቶ ማሻሻልን፣ መቀየርን፣ መተውን ሲለማመድ ለጋራ ውሳኔዎቻቸው ተገዢዎች ሲሆኑ፣ የግልና የጋራ ኃላፊነቶቻቸውን ሲወጡ ሲታይ ብስለት በአስተሳሰብ ላይ ታየ ማለት ነው። **ስሜታዊ ብስለትም አለ**። ገጠመኞቻቸው በስሜት ማዕበል የሚነዳቸው ሆኖ ሳለ እርሱኑ ተ ቆጣጥረው፣ እርሱኑ ተሻግረው ማለፍ ሲችሉ በሁለቱም ሕይወት ብስለት ተከሥቷል ማለት ነው። ይህ ብቻ አይደለም፣ አግባብ በሆነ ጉዳይ ላይ ተራርመው፣ ተተቻችተው ለጊዜው ስሜታቸው ተጎድቶ

ግን የተቀባበሉ ሲሆኑ፣ ቅጥ-ያጣ ጎዘንንም ሆነ ገደብ-የለሽ ደስታን በመሸሸና በመቅረብ ሳይሆን፣ በውስጡ በመሆን በአግባቡ ማሳለፉ በጋራ ሕይወታቸው እየተከሠተ ሲመጣ ስሜታዊ ብስለት ተገለጠ ማለት ነው።

የማኅበራዊ አኗኗር ብስለታቸውም ሌላው ተፈታኝ ጉዳይ ነው። ይህ ወደ ሌሎች ሰዎች የመድረስ አቅማቸውን ይመለከታል፣ ከእነርሱም ጋር ጤናማ ግንኙነትን፣ ጓደኝነትንና የማፍራት ውጤት የማኅበራዊ ሕይወት ገጽታ ነው። የሁለቱ ጓደኛሞች የሕይወት አድማስ ቤተሰቦቻቸውና የቅርብ ጓደኞቻቸው ብቻ ሲሆኑ አይገባም። ሰፊ የሕይወት ልምምድን ከሌሎች ጋር መጋራትን ጓደኛሞቹ እያሳዩ ሲመጡ አደጉ ማለት ነው።

መጨረሻ ላይ አመጣሁት እንጂ፣ የሁለቱንም ሕይወት የሚያጣፍጠው ጨው **የመንፈሳዊ ሕይወታቸው ብስለት ነው**። ከመነሻው የተጫጨት በክርስቶስ የሆኑት ናቸው። የእነርሱ መልህቅ እግዚአብሔር ነው፤ የሕይወታቸውም ብቸኛ ባለሥልጣን የእግዚአብሔር ቃል ነው። እርሱ ይመክራቸዋል፣ ይመራቸዋል፣ ያግባባቸዋል፣ ያስተዳድራቸዋልም። በሕያው ቃሉ በየዕለቱ ሕይወታቸው ተገዘተውበት ሲኖሩ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ብስለት ወይም እድገት ታየ ይባላል።

ቀደም ሲል ምሳሌ ያደረግኋቸው ሁለት ወጣቶች በዚህ ምክር ከተስማሙ፣ ትጭጭት ዘንድሮ ሰምሮ ለመጪው ተሸጋገሩ ማለት ነው።

ያገሬ ሰው፣ «ጓደኛህ ሲመክር በእኔም ብለህ መስክር» ይል የለ። እንግዲህስ «ጆሮ ያለው ይስማ!»

የሠርጉ ማግስት... የምሥራች

«...ጫካ ውስጥ በጀርባዬ ተንጋልዬ በደም ተለውሼ አገኘኝ...» በሚለው በሉሊት ንግግር መጀመር ወደድኩ። «. .እንስራዬም እዚያው ጎኔ ተሰብራ፣ እንክትክታ ወጥቶ ነበር። የእንጀራ አባቱ ካበላሸኝ ሰው ጋር (ድንግልናዬን

ከወሰደው ሰው) በጎን ታርቆ በትንንሽ ገንዘብ ክብሬን (ድንግልናዬን) ባሸጠው በሳምንቱ እናቴ ሞታ ተቀበረች። የሙት ዓመቷ ሳይወጣ የእንጀራ አባቴ ላንዱ ዳረኝ። ያ የተዳርኩለትም ሰው ክብር የላትም በማለት ጀርባዬ እስኪተላ ድረስ ገርፎኝ መሐሉ የተቆረሰ ዳቦ አሸክመኝና ሰደደኝ...»

የሉሊት ብሶቷ አላለቀም። እኔ ግን ደራሲ በዓሉ ግርማ በአድማስ ባሻገር መጽሐፉ፣ ድንግልናዋን ያለፈቃድዋ ያጣችውን ልጃገረድ ያናገረበት ገለጻ ጥሩ ምሳሌ ስለሆነኝ ብቻ ነው የወሰድኩት።

እንደ እኔ አንባቢ አንድ ጥያቄ ሳያነሣ አይቀርም፣ «ከገሃዱ ዓለም እውን የሆነ ስንት ተመሳሳይ ገጠመኝ እያለ ለምን «ልብ ወለዷን ሉሊትን» መረጥክ? የሚል ይመስለኛል። ከተጨባጩ ሕይወት የሚሸሹ ሁሉ ልብ ወለድ ውስጥ መሸሸጋቸው ያለ ነው። የእኔ ግን ለመሸሽ ሳይሆን፣ እንዲህ ያለውን ርእስ ሲነካኩ አምላክ ከፈጠራቸው ይልቅ ደራሲ የቀረጻቸውን ገጸ-ባሕርያት መጠቀሙ ሸሽት ሳይሆን፣ ብልሃት ስለ መሰለኝ ነው።

ታዲያ ይህንን ጽሑፍ ሳዘጋጅ ልብ ወለድ ቢሆንም፣ «የገሃዱ ዓለም ነጸብራቅ ነውና» «ሉሊት ክብሯ ከተገሠሠ በኋላ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኟ ተቀብላ ቢሆን ኖሮስ...? እና ከዚያም «እግዚአብሔር ሰጠኝ...» ያለችውን ሰው ብታገባ «የማግሥቱ የምስራች...» የሚስተናገደው እንዴት ይሆን? አሳስቦኝ ነበር።

መቼም ትጭጭት ፍጻሜ ሲያገኝ ጋብቻን ነው የሚያስከትለው፤ በማግሥቱም የጫጉላውን ታሪክ፤ በሠልስቱ ደግሞ ቅልቅልን። አሁን አሁን በሠርግ ማግሥት ማለዳ ያለውን የምስራች እንድንመካከርበት መንደርደሪያውን ብቻ አመላክታለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ ድንግልን አስመልክቶ ፍቺ ሲሰጥ፣ «ወንድ ያላወቃት (ያልደረሰባት) ብላቴና ልጃገረድ» ይለዋል (ዘፍጥ. 24፡16)። እንዲህ ዓይነቷ ብላቴና በአግባቡ ለታጨችለት ወንድ ብቻ ነው የምትገባው። ሌላ ሊደፍራት ፈቃድ የለውም። እርሷም እሽኮ ለሌ ለማለት ኬላ አለባት። እንዲህ ቢሆን ጫን ያለ ቅጣት ሁለቱንም ይከተላቸዋል። ለዚህም ነው አምኖን የትዕማርን ክብር

ከመግሰሱ በፊት «በዓይኑ ፊት ጭንቅ የሆነበት።» ወንዱ ብቻ ሳይሆን፣ ሴቲቱም መከላከል ስትችል ወይም የድረሱልኝ ጩኸት ሳታሰማ ቀርታ ብትደፈር፣ የደፈራት ወንድ ጭምር በድንጋይ ተ ወግረው እንዲሞቱ ዘዳግም 22፡23-24 ያዝዛል።

እንዲህ ዓይነቶቹን የብሉይ ኪዳን ታሪኮችና ትእዛዞች፣ ማስጠንቀቂያዎች በአግባቡ ጨምቀን ትርጉም ብንሰጣቸው፣ እግዚአብሔር ለጋብቻ ክቡርነትና ቅዱስነት ምን ያህል ትኩረት እንደ ሰጠው እንረዳለን። ይህ እውነት ከጎሊና እንኳን ቢሰወር የሐ ዋን የአካል ክፍል ይመሰክር ዘንድ የድንግልና ምልክትን አስቀመጠ።

ታዲያ በታጨች ሴት ዘንድ በጋብቻዋ ማግስት ይህ ድንግልና ሲገኝ በእኛው ባህል የምሥራቹ ይቀልጣል። ባለምሥራቾቹም ይበዛሉ። ቀዳሚ የምሥራች፣ ለሙሽሪት ይገባታል፣ አቆይታዋለችና። ሁለተኛው የምሥራች በማለዳ ወፍ ሲንጫጫ ለወላጆችዋ የሚደርሰው ነው። በመልካም ሥነ-ምግባር፣ በእንክብካቤ ባያሳድጓት ለዚህ አትበቃምና የምሥራቹን ቆይቶ እንደ መጣ ደመወዝ ይቆጥሩታል። ከዚህ ደመወዝ ባለድርሻ ለመሆን የሚከጅሉ ሌሎችም አይጠፉም፣ ጎረቤቶች፣ ጓደኞች... ደስታውን ሊጋሩ ይቋምጣሉ።

ይህ ማለዳ አንዳንዴ ሌሊቱን የመሰለ የጨለመ መርዶ ሊያመጣ ይችላል። «ጀርባ እስኪቆረስ አስገርፎ መሐሉ የተቆረሰ ዳቦ አሸክሞ መስደድ...» «እርግጥ ይህ አደራረግ ተገቢ ነው ተገቢ አይደለም» የሚል ውዝግብ ማንሣት ርእሰ ጉዳዬ አይደለም። እስራኤላዊ ልጃገ ረዶችን አስመልክቶ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ይለናል። ድንግል እንደ ሆነች ስትናገር ከርማ ስለ ዋሸች ሴት የሚገባት ቅጣት አለ፤ በድንጋይ መወገር (ዘዳግ. 22፡20-21)። ድንግል ሆና ሳለ ያገባት ወንድ በሐሰት ቢያወራባት እርሱ ደግሞ ይገረፋል፣ መቶ የብር ሰቅል ይቀጣል፤ በዕድሜውም ሁሉ ሊፈታት አይገባውም (ዘዳግ. 22፡13-19)።

ብዙ ወጋችን ከእስራኤላውያን ጋር ስለሚመሳሰል፣ በኢትዮጵያውያንም ዘንድ ድንግልና በጣሙን ይከበራል። «የለም! ጠፋ!» ሲባል እንደ መርዶ ያስደነግጣል፣ አንገት ያስደፋል፤ ተገኘ

ሲባል በአንጻሩ ፌሽታ ይሆናል።

ባህሉ ጥብቅ ከመሆኑ የተነሣ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ሕይወት የሚኖሩትም መንፈሳውያን ይህን አልተላቀቁትም። እንዲያውም ጉራማይሌ እያደረጉ ወጉን ያደበዝዙታል፣ ትርጉሙን ያዛንፉታል።

ይህቺን አንቀጽ ማጠናከር ይጠበቅብኛል መሰል። ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በቤተ ክርስቲያን ከተዳሩ በኋላ ቀሪውን ነገር እንደ ወጉ ለመፈጸም ይነሣሉ። «የምሥራች» ለመድረስም ሲመጡ፡-

«ብር አምባር ሰበረልሽ)
ወንዱ ልጅሽ...!
... ኬላው ተሰበረ!
በእናት በአባቷ ቤት ሲከበር የኖረ!»

እንዳይሉ የምሥራቹ ክርስቲያናዊ፣ ዘፈኑ ዓለማዊ ይሆንባቸውና፡-

ድንቅ ነው የተሠራው (2)
የእኛ ጌታ ያደረገው...
* * *
ገረሰሰው የጠላትን ጦር
ጦሬ የምዋጋበት
* * *
ደስ ደስ ደስ ደስ ብሎናል
እግዚአብሔር ታላቅ ነገር አድርጎልናል...

በማለት ያዜማሉ፣ ይህን ጉራማይሌ ለመዜም ባህላቸውን ማለቱ አይደቀርም።

ለማንኛውም ከጥቂት ዓመታት በፊት እዚሁ አዲስ አበባ ሴት ልጃቸውን ለመዳር፣ ለመኪል የበቁ አንድ አዛውንት በሠርጉ ጥዋት ስልክ ይደወልላቸዋል። የደወለው የሙሽራው ሚዜ ነው።

«ሃሎ...! አባባ...ሃሎ እየመጣን ነው ጠብቁን»
«ለምን ልጅ! ምን ችግር አጋጠማችሁ?
«ችግር እንኳን አላጋጠመንም፣ አባባ

«... እና ደህና?»

«የምሥራች ይዘን ነው!»

ሥራ የላችሁም!? እኔ ሥራ አለብኝ...ልጆች ሥራ አለብኝ... አታገኙኝም::»

እርፍ::

አዛውንቱ አገልጋይ ልጃቸውን ተጠራጥረው ወይም ልጅቱ ንጹሕ ሳትሆን ቀርታ አልነበረም:: ልጃቸውስ በእርግጥ ድንግል ነበረች:: ግን አንድም እርሳቸው ከጉራማይሌው የባህል ቱማታ የተፈቱ ሆነው እንጂ:: ሁለቱም ደግሞ በየሰንበታቱ እግዚአብሔር አምላካቸውን ያመለኩባቸውን ዝማሬዎች ለወግ-ለባህልና ለታይታ ሊያድበሰብሷቸው አልወደዱ ይሆናል ብንልም ያስኬዳል::

እንደገና ወደ ሉሊትና ሉሊትን ወደሚመሳስሉ ብዙዎች ልመልሳችሁ:: ሌሊቱን በዓይነ ኅሊናችሁ እዩልኝ:: ውኃ ልትቀዳ በሄደችበት አለውዱታዋ ተደፍራ ነበር:: እንደ ገና ያለ ውዱታዋ ተድራ መከራዋ ከመቀጠሉ በፊት ኢየሱስ አግኝቷት ቢሆን ኖሮ?... እግዚአብሔር አበሳዋን ሽሮላት በቅድስና ኖራ በቤተ ክርስቲያን ብትዳር በማለዳው የምሥራች ሊጠበቅ ይሆን?... ወይስ ሰባራ ጉድፋም ልትባል ይሆን? ...ወይስ ሉሊት አሁን እኮ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነኝ አሮጌው አልፎአል ብላ...የምስራች ለመላክ ይዳዳት ይሆን?

* * *

ሉሊትስ ልብ ወለድ ናትና ለመከራከሪያ አትበቃ ይሆናል:: ነገር ግን ያለ ክርስቶስ በኖርንበት ዘመን በኃጢአት ወጎኒ ተጠፍረን ሳለ እንደ ማንኛውም ሥጋ ለባሽ በብዙ የተበላሸ ልምምድ ውስጥ የምናልፍ ቁጥራችን ጥቂት አይደለም:: ክርስቶስ ግን ከትቢያ ሊያነሣን ሲሻ ሞታችንን በሞቱ ለውጦ፤ መቃብራችንን ከፈተ፣ ከኃጢአት መቃብር አወጣን፤ አዲስ ሰው አደረገን፣ ለመንግሥቱም አበቃን:: «እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻለሁና» (2ኛ ቆሮ. 1፡12) ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ዋናው ድንግልና የጌታ ከመሆን ከዚህ ይጀምራል::

እንግዲህ ከአዲስ ልደት በፊት ድንግል ሆና ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥታ ቢሆን እሰየው! ክብሩ ለእርሷም፣ ለቤተሰቧም፣ ለቤተ ክርስቲያንም ነው! . . .ለዘያ ግን በቀደመው ኑሮ እንደ ሉሲት በግድ ወይንም በፈቃድዋ ድንግል ባትሆን፣ ዋነኛው ከእምነት በኋላ ያለው የቅድስና ኑሮዋ ስለሆነ፣ እንደ ሰባራ ገል መታየት የለባትም። ወይንም ደግሞ ወጉን ለማሟላት ሲባል የራሷን ጎሊና፣ ቤተሰቧንና ቤተ ክርስቲያኗንም እንድትሸነግል መገፋፋት የለባትም።

በተውነው የቀደመው ሕይወት ይህንን ሰው ያወቀውን ፀሐይ የሞቀውን ጉዳጉድ ለመሸፈን ሲባል ብዙ ነገር ይደረጋል፣ ወግ ነውና ቤተ ክርስቲያን ግን ከዚህ ወግ መላቀቅ የለባትም ወይ? ወጣቶቻችንስ ያልሆኑትን እንዲሆኑ ለምን እንገፋቸዋለን? ቅድስናን አጥብቀን «የምስራቹን» ጉራማይሌ ለምን አናፈዝዘውም?!

ለምን እንጽፋለን?

የጥያቄው ምላሽ እንደ መልካችን ሊለያይ ወይም ሊቀራረብ ይችላል። የአጻጻፍ ዘዴን በመማሬ እጽፋለሁ፣ ታሪክን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገሪያ በመሆኑ እጽፋለሁ፣ ጽሑፍ ስጦታዬ ሆኖ «ጻፍ ጻፍ ስለሚለኝ» እጽፋለሁ፣ እርካታዬ ስጽፍ ስለሆነ እጽፋለሁ፣ ለሰው ልጅ ሊደርሰው የሚገባ መልእክት ስላለኝ እጽፋለሁ፣ ወዘተ...ለ«ለምን ትጽፋለህ?» ጥያቄ ከሚቀርቡት መልሶች ጥቂቶቹ ናቸው።

ፈተና እንደሚያርም አስተማሪ «አንተ ልክ ነህ! አንተኛው ስተ ሃል» ብሎ መወሰን ቢቸግርም፣ ከምላሾቹ ሚዛን ደፊው «ለሰው ልጅ ሊደርሰው የሚገባ መልእክት ስላለኝ እጽፋለሁኝ» የሚል መልስ ከሰጠው ጋር ቆይታ እናድርግ። ቆይታውም «ክርስቲያን ጸሐፊ ለምን ይጽፋል?» ለሚለው ብቸኛ መልስ ከእርሱ ዘንድ ስላለ ነው።

ይህ «መልእክት» የተሰኘው ቁም ነገር ከየት ይገኛል? ለክርስቲያኑ ጸሐፊ ከአደመጠው ትረካ፣ ከአነበበው ጥንታዊና ዘመናዊ ጽሑፎች «እርግጥ ነው ወይም ትክክል ነው» ብሎ

ሳያመዛዝን ከተቀበለው የቅብብሎሽ ትምህርት፣ ከጎበረተሰቡ ጋር ሲኖር እያደረገው ካለው፣ ከጠቢባን መድበለ መረጃዎች፣ ወይስ ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል?

ለክርስቲያን ጸሐፊ የመልእክት መገኛዎቹ ከላይ ከተጠቀሱት አብዛኛዎቹ ሊሆኑ ይችላሉ። ግን ከሁሉም ቀዳሚ የመልእክቱ ዋንኛ ምንጭ በመንፈስ ቅዱስ የተደረሰው መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ፣ የመልእክቱ መገኛ እግዚአብሔር ብቻ ሊሆን ይገባል።

ምንጩስ ተገኘ፣ ከምንጩ በጽሑፉ ውስጥ ሊተላለፍ የሚገባው ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ዳርቻ ድረስ የተጻፉትን ማስተላለፍ ወይም ውስን መሆን? ምላሹ፣ ራስ ለሆነው መልእክት ቅድሚያ በመስጠት፣ የተቀሩትን መልእክቶች ሁሉ በሥሩ እንዲያድሩ በማድ ረግ ማስተላለፍ፣ ይህ የክርስቲያን ጸሐፊ የጸሐፊነቱ ዓርማ ሊሆን ይገባል።

ራስ የሆነውም መልእክት ሁለት ነው። አንደኛ፣ «ሰዎች ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተዋል። የተለያዩትን ደግሞ ሊያስታርቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኗል። እርሱ በጎቹ ለሆኑት ሁሉ ደሙን አፈሰሰ፣ ምትክም ሆኖ ሞተ። ከዚህም የተነሣ፣ ሰዎች ኃጢአተኝነታቸውን በመረዳት ክርስቶስን በማመን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመፍለስ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅን በመመሥረት፣ በክርስቶስ ጌትነት ሥር መኖር» የሚል ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ እርቅን መሥርተው ክርስቲያን የሆኑት እነርሱ ከመንፈሳዊ ሕፃንነት ወደ ክርስቶስ ማደግ አለባቸው የሚል ነው። እነዚህ ሁለት ነጥቦች ሳይነጣጠሉ ተደጋግፈው በመልእክትነት ለሰዎች እንዲደርሱ፣ ደርሰውም የሰውን ሕይወት እንዲቀይሩና እንዲያሳድጉም ያስፈልጋል።

እንግዲህ ይህ ዐቢይ መልእክት በጽሑፍ ሊተላለፍ ሲፈለግ፣ መልእክቱን ማስያዣና ማኖሪያ ዕቃ ያስፈልጋል። ይዘቱን ማስተ ላለፊያ ሲባልም የጽሑፍ ቅርጽ ለማለት ነው። በዘገባ ማሳለፍ፣ በምሳሌ መግለጽ፣ በመረጃዎች ማስደገፍ፣ በውይይት መጠቀም፣ ስንኞችን መቋጠር፣ ረጅም ወይም አጭር ክርስቲያናዊ ልብ ወለዶችን፣ ወዘተ...መድረስ ወይም ከእነዚህ አንዱን ወይም ሌላውን ለሥራው ተስማሚ የሆነውን በመምረጥ የመልእክቱ መያዣ

ወይም ማስተላለፊያ በማድረግ ማድረስ ይቻላል። ልክ ለሰውነታችን ጥቅም የሚሰጠንን ወተት አንዱ በብርጭቆ ሲጠጣው፣ ሌላው በኩባያ፣ ሌላው በሽክና ወይም በጮጮ፣ ወይም በዋንጫ ይጠጣዋል። መጠጫው ወተትነቱን አይቀይረውም። ተጠቃሚ ጠጪው ነው-ሰውየው። ጠቃሚው ወተቱ ነው - መልእክቱ። ሁለቱን የሚያገኘው መያዣየው ነው - ብርጭቆው - የጽሑፉ ቅርጽ።

መልእክቱ ሲደርስ ግን ዋናው ጥንቃቄ ለይዘቱ በመጨነቅ ሊሆን ይገባል።

ሀ. አሻሚ ወይም ድራቢ ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ ቃላትን በማስወገድ፣

ለ. ከአንቀጽ አንቀጽ ሽግግር ሲደረግ የአሳብ ተያያዥነትንና ተከታታይነትን በመጠበቅ፣

ሐ. በብዙ ቃላት የደረጁ (የታጀቡ) በርካታ ረዥም ዐረፍተ ነገሮችን መጠቀም መልእክቱን እንደሚያደበዝዝ አውቆ በመጠንቀቅ፣

መ. የሚተላለፈው መልእክት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለውን መጣጣም በእርግጠኝነት በመመዘን፣

ሠ. ለጽሑፉ ውበት የሚደረገው ጥንቃቄ መልእክቱን እንዳያፈዘውና ያለ መልእክት እንዳያስቀረው በማስተዋል፣

ረ. የሚተላለፈው ጭብጥ እንጂ ጽሑፉን ክርስቲያናዊ የሚያደርገው አልፎ አልፎ የእግዚአብሔር ስም በውስጡ መነሣቱ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስያሜዎች ጣል፣ ጣል ማለታቸው ብቻ አለመሆኑን በማጥራት፣

ሰ. በአጭር ጽሑፍ ውስጥ አንድ ወይም ሁለት መልእክቶችን ማስተላለፍ በቂ ሆኖ፣ ግን ምሉእነት የጎደላቸው የታጨቁ ልዩ ልዩ ቁም ነገሮች በአንዱ ጽሑፍ ውስጥ እንዳልተካተቱ አበክሮ በማጤን፣

ሸ. እጅ እንዳመጣ ሥርዓተ ነጥቦችን በጽሑፍ ውስጥ መደንሰር ሳይሆን፣ በተገቢ ቦታቸው መገኘታቸውን በመገንዘብ፣

ቀ. ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ጽሑፎች በልቅነት የሚጠቀሙበት

አባባልና ገለጻ በጽሑፉ ውስጥ አለመስተናገዱን መፈተሽ፣ ወዘተ...ይዘቱን በቅርጹ ውስጥ በማኖር የመልእክት ራስ ያልናቸውን ሁለት ዐቢይ ቁም ነገሮች በተገቢው ሁኔታ ሊያደርሱት ያስችላሉ።

* * *

አያይዘን፣ ክርስቲያናዊ ልብ ወለድ በቅርጽነቱ ይዘትን (መልእክትን) በማስተላለፍ ያለውን ጠቀሜታና ልንጠነቀቅበት ስለሚገባው ጥቂት እንበልና «ለዚህም ነው የምንጽፈው» በማለት መልእክቱ ይጠቅለል። በቅድሚያ ግን «በክርስቲያን ልብ ወለድ ጽሑፍ» ምንነት (ትርጉም) ላይ እንስማማ።

«ሕይወት በቁንጽል መልክ ፊት ለፊት በታየው ውጤት ላይ ብቻ ሳይመረኮዝም። በምትኩ ለውጤቱ ምክንያት ሊሆን ያሰቻለውን ፈትሾ በማውጣት «ለካ» ለዚህ ኖሯል! ማሰኘት ይጠበቅበታል። ውበትን ተላብሶ በእግዚአብሔር ቃልና በገጸ ባሕሪው በድርሰቱ ውስጥ በተሳለው ሰው ሕይወት ላይ በመመርኮዝ የቀረበ የፈጠራ ጽሑፍ እርሱ ልብ ወለድ ነው። ሁሌ ከዕውቀት የሕይወት ገጠመኝ ጋር ቁርኝት ያለው አንባቢም በሰው ሕይወት፣ በሰው ስም የራሱን ሕይወት የራሱን ስም እንዲያስተካክል የሚያግባባ የውጤት ጽሑፍ ክርስቲያናዊ ልብ ወለድ ጽሑፍ ሊሰኝ ይችላል። እንግዲያስ ይህን የጽሑፍ ቅርጽ መጠቀም ያለውን ጠቀሜታና ሊጠነቀቁለት የሚባውን ነጥቦች ላከታትል።

ጥቅሙ፦

1. ክርስቲያናዊ ልብ ወለድ የጥናት፣ የምርምርና የድካም ውጤት መሆን ስለሚገባው፣ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ተርጉሞ በትክክል ከገጸ-ባሕርያት ሕይወት ጋር በማጣጣም የሰዎችን እንቅስቃሴ በምክንያትና በውጤት አዋቅሮ መልእክቱን ለብዙዎቹ በጽሑፍ ማቅረብ መሆኑ፣
2. የሰውን ሕይወት ይወክሉልናል በማለት ስም ሰይመን የመ ረጥናቸው ገጸ ባሕርያት የሚመሩት ሕይወት በአንባቢያን ሲጤኑ የየዕለት ተዕለት ገጠመኞቻቸው በአብዛኞቹ ተ ደራሲያን ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑ፤ «የእኔ ነገር ወይም የእኛ ጉዳይ ነው» ማሰኘታቸው፣

3. አንዳንድ አንባቢያን ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸው መረዳት አነስተኛ ቢሆንም፣ በሕይወታቸው የሚለማመዱት ወይም ልክ ነው ብለው የተቀበሉት «እውነተኛ ነኝ» ባይ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን ስሕተትነቱ የጎላ ሲሆን፣ ጸሐፊው መልእክቱን ውበት አላብሶ እስከ ዳር ድረስ ተነብቦ እንዲያልቅ በማድረግ ከእውነት ጋር የማገናኘትና እንደ ጌታዬ «ጆሮ ያለው ይሰማ»ን ማድረሻ መሆኑ፣
4. መልእክትን በፈጠጠ መልኩ «ይህን ልል ነው የምፈልገው... ብታደርግ አድርግ ባታደርግ ወዮ!» በሚል ሁኔታ በማቅረብ ሳይሆን፣ አንባቢው ቁም ነገሩን በራሱ በጎ ፈቃድ ፈልጎ፣ አግኝቶም እንዲጠቀምበት አድራጊ መሆኑ፣
5. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምርበትን ስልት በመከተል ጸሐፊው ሊጠቀምባቸው የመረጣቸው ምሳሌዎችም ሆኑ ሰዎች ከተደራሲያኑ ሕይወት ቅርበትና ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖራቸው የቻሉ መሆናቸውን ተገንዝቦ የሚጠቁም መሆኑ፣
6. እየተላለፉ የደረሱን የሥነ-ቃል ዘርፎችን እንደ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ አባባሎች፣ ፈሊጦች፣ ወዘተ... በጽሑፍ ውስጥ መልእክት በማጉላት ኃይላቸው ጠንካራ የተሰኙትን ተገቢ ዎቹን በተገቢው ጊዜ መጠቀም መቻሉ ከጥቅሙ አኳያ የሚዘከሩ ናቸው::

ጸሐፊ ሊጠነቀቅለት የሚገባው

1. ጽሑፉ በጸሐፊው ተጽፎ መውጣቱን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፣ በሰዎች ሊነበብ የሚቻል መሆኑን መረዳት፣
2. ክርስቲያናዊ ልብ ወለድ ሁል ጊዜ ለክርስቲያኖች ጥቅም በሚውል መንገድ ብቻ መድረስ እንደሌለበት ማስተዋል፤ ጌታን ያልተረዱት ያላመኑት እንደሚያነብቡት ግምት ውስጥ በማስገባት እነርሱ ድረስ የሚደርስ መልእክት ይዞ በተነባቢነቱ ለውጤት ሊያበቃቸው ይችል ይሆንን ብሎ ማሰብ፣
3. ጽሑፍ ያለችግር የሚደርሳቸው «የከተማ ሰዎች ናቸው»

በሚል አሳብ አጻጻፉን «ለእነርሱ ይድረስልኝ» ከሚል ጠባብ ክልል ወጥቶ ጽሑፉ በየትም ስፍራ ሊደርስና ሊነበብ፣ መልእክቱም ያለ ችግር ሊደርስ መቻል አለመቻሉን ማስተ ዋል፣

4. ጸሐፊው አንባቢ ክርስቲያኖች ከኀብረተሰቡ ራሳቸውን አግልለው እንዳልኖሩ በመቁጠር፣ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ልብ ወለዶችን በማንበብ አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው ደራሲዎቹ በመልእክታቸው ሊያሳድሩት በሚፈልጉት ዓላማ ውስጥ በከፊል ወይም በሙሉ ሊገቡ ስለሚችሉ፣ ደግሞ የአጻጻፍን ስልት በድግግም ካነበቧቸው መጻሕፍት ውስጥ ስላስተዋሉ ክርስቲያን ጸሐፊ ከሥነ ምግባር አኳያ ከእግዚአብሔር አሳብ ውጭ የሆነውን አገላለጽ በመተው በምትኩ በአጻጻፍ ደረጃው ላቅ ያለ ጽሑፍ ማቅረብ መቻ ሉን መመዘን፣

5. «የምንጽፈው ልብ ወለድ ነው፣» በማለትም የእግዚአብሔር ቃል ሊለው ካቀደው መስመር ውጭ አለመሄዳችንን በእጅጉ መገንዘብ፣ ወዘተ፤ እነዚህን ከላይ የተነሡትንና መሰል ነጥቦችን በከፊልም ሆነ በሙሉ መጠቀምና መጠንቀቅ ለክርስቲያን ጸሐፊ፣ «የምትጽፉት ሁሉ ለማነጽ ይሁን እኛ ም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተ ማርን የምንሰብከው እርሱን ነው» (ቈላስይስ 1:28 ይህን ያስታውሰናል)። የ«ለምን እንጽፋለን?» ጥያቄም በዚሁ ቃል መልስ ያገኛል።

«እ ን ተ ራ ረ ም»

ቢሊግርሃም «መንፈስ ቅዱስ» የተሰኘውን መጽሐፍ ሲጽፉ የመጀመሪያ ምዕራፋቸው ባደረጉት የመግቢያ ጽሑፍ ልጀምር። «አምስተኛ ክፍል ያስተምር የነበረው መምህር ተማሪዎቹን «ስለ ኤ ሌክትሪክ ብርሃን ሊያስረዳኝ የሚችል ማን ነው?» በማለት

ይጠይቃል። በዚህ ወቅት ከተማሪዎቹ አንዱ እጁን በማውጣቱ መምህሩ ዕድሉን ሰጠው፡- ልጅየው ቆመ፣ ራሱንም አሻሸ፣ አቅማማና፣ «ማታ ቢሆን በደንብ አስታውሰው ነበር፣ አሁን ግን ተረሳኝ» አለ በቁጭት። በዚህ መልስ መምህሩ ቅር ተሰኘ። አንድ ተማሪ ብቻ ሊሞክር ተነሥቶ እርሱም በመርሳቱ አዘነ።»

የመምህሩ ኀዘን እኔና እናንተ ስለ «ሥላሴ» ተጠይቀን ወይም ስለ «መንፈስ ቅዱስ» ተጠይቀን በምንመልሰው መልስ ከተማሪው ተራ የምንገባ ሆነን የሚታዘንብን ጊዜ እንዳለ ቢሊግርሃም የዘንድሮን ነገር እያሰቡ ይጽፋሉ። ከክርስቲያኖች የሚጠበቀው «... በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ...»ን (1ኛ ጴጥ. 3፡15) መ ረሳቱንም ያሳስባሉ።

* * *

ወደ ቁም ነገሬ ልመለስ፣ አብዛኛው ምእመን ስለ «መንፈስ ቅዱስ» ያወራል። አንዳንዱ ጥምቀቱን፣ ሌላው ስጦታዎቹን፣ ሌ ላው ፍሬዎቹን፣ ሌላው ስለ የስድብ ቃል በመንፈስ ቅዱስ ላይ፣ ወዘተ... ብቻ ሁሉም ይናገራል። የሁሉም ንግግር እንደ እግዚአብሔ ር ቃል መሠረት ከሆነ እሰየው ነው፣ ግን እግዚአብሔር አሳቡን የገለጠበት ቃሉ ማመሳከሪያነቱ ተዘንግቶና ተረስቶ የየራሳችን ልሙጥ ገለጣ ሲኖር የእንተራረም ጥያቄ ከፍተኛ ስፍራ ይይዛል። ኋላ «መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?» ተብለን ተጠይቀን መልሳችን ተዝ ረክሮ መግለጽ ያቅተናል፤ እንደ ተማሪው ከመሆኑ ከማለት ለመዳን ጠንቀቅ ከወዲሁ ዋና ጉዳይ ነው።

በገጠመኞቹ ልቀጥል፤ ወዳጄ ነው፤ በብዙም እንቀራረባለን። «... ይህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ነው፤ አብና ወልድ የድርሻቸውን ፈጽመው ሁሉንም ኃላፊነት ለመንፈስ ቅዱስ ትተውለታል...» ይል ነበር በስብከቱ። እያደመጥኩ «ሥላሴ-ሦስትነት በአንድነት-አንድነትም በሦስትነትን በምን ተረድቶት ይሆን?... ኃላፊነት ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስ ከተሰጠ፣ በዚህ ዘመን አብና ወልድ ድርሻቸው ምን ይሆን?...» ስብከቱ ሁሉ ጥያቄ ሆነብኝና፣ ወዳጄን ግር ብሎታል ብዬ ወሰንኩ። እውነትም በ«መንፈስ ቅዱስ» አስተምህሮ ላይ ግር ብሎታል።

* * *

ሌላኛውን ሰውዬ ግን አላውቀውም። ይሰብክበት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በሕዝብ ጢም ብላ ሞልታ እንደ ነበር ነው የማስታውሰው። ትዝ እንደሚለኝ፣ ከሚተርከው ትረካ የተነሣ በታዳሚው ፊት ላይ ድንጋጤና ግርታ ነግሦ ይታያል። ስለ አንድ ሰው እንዲህ ይል ነበር፣ «...እግዚአብሔር በችግሬ ስላልደረሰልኝ እኔ እርሱን ከዚህ በኋላ አላመልክም...» አለ። ይህ ሰው ከችግሩ ሳይወጣ ሞተ፣ ለሞቱ ምክንያት መንፈስ ቅዱስን መስደቡ ብቻ ነው» ይላቸዋል። «እናንተም አታጉረምርሙ፣ ለምን? ለምን?» እያላችሁ መንፈስ ቅዱስን አትክሰሱ፤ በሥጋ መሞታችሁ ብቻ ሳይሆን፣ ለዘላለም ወደ ገሀነም ልትወርዱ ትችላላችሁ፣» ይል ነበር። እውን በእግዚአብሔር ቃል ስለዚህ ጉዳይ የተገለጸው እውነት ከሰውየው ማስፈራሪያ ጋር አብሮ ይሄድ ይሆንን? ምላሹ በፍጹም አይሄድም። እንኪያስ መታረም አለበት።

እስኪ ጥቂት መሠረታዊ እውነቶችን በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ላይ ቅዱስ መጽሐፍ የገለጠውን እንጨብጥ። ዘላለማዊነቱን አስመልክቶ ዕብራውያን 9፡14፤ ሁሉን አዋቂነቱን ደግሞ 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡10፣11፤ እግዚአብሔር ተብሎ መጠራቱን የሐዋርያት ሥራ 5፡3፣4፤ ስለ ፈጣሪነቱ ዘፍጥረት 1፡2 ገልጦታል። እነዚህ ጽኑ እውነቶች ናቸው። ተጨምሮም መንፈስ ቅዱስ ራእይ 2፡7፣ የሐዋርያት ሥራ 13፡2፣ እንደሚማልድ፤ ሮሜ 8፡14፣ እንደሚመርጥ፤ የሐዋርያት ሥራ 20፡28 እንደሚያዝን፤ ኤፌሶን 4፡30 ስጦታን እንደሚሰጥ እነዚህም ምስክሮቻችን ናቸው። ልናስብ ብንፈልግ፣ ያሰብነውንም ልንናገር ብንደፍር፣ ማሰባችንም ሆነ መናገራችን፣ ማስተማራችንም ጭምር ከእግዚአብሔር ቃል ፈር ሳይለቅ መሆን አለበት። እንኪያስ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ክርስቲያን የሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምክንያት ገሀነም ይወርዳል ከማለት ቆጠብ ማለት ተገቢ ነው።

እግር ጥሎኝ በአንድ ቦታ ተገኝቼ መተራረማችን ለመልካም ሆኖልኝ የተለያየንበትን ሌላውን «የመንፈስ ቅዱስ» ጉዳይ ላጫውታችሁና ልጨርስ። አንድ ወንድም ነው «እነርሱ እኮ...» እያለ ያጫውተኝ ጀመር፣ በውስጤ ይህ ወንድም መታረም አለበት

አልኩ። ትንሽ እንደ ቆየሁ ትዕግሥቱ አለቀና በሁሉ ፊት ስሙን ጠቅሼ «ቤተ ክርስቲያኒቱን የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ ናት ማለት አትችልም፣ ደግሞም መንፈስ ቅዱስን እነርሱ አሥረውታል መሰኘ ቱም ልክ አይደለም፣» በማለት አስተጋባሁ። «እንዴት! ለምን?» ተ ከታታይ ጥያቄው ሆነ። ከእርሱም ጋር አብረውት ያሉትም እንዲሁ ሞገቱኝ።

ምላሼ ጥቂት ነበር፣ ለቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ራስ ሆኖ እኛ ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ዳግም በመወለድ ብልቶች ሆነናል። ለዚህ ድንቅ ሥራ ማን አበቃን? መንፈስ ቅዱስ ነው፤ እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው፣ «ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል። ስለ ኃጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው» (ዮሐ. 16፡8-11)። መንፈስ ቅዱስ ልንወጣበት ከማንችልበት ከኃጢአት አረንቋ ውስጥ እንዳለን ገልጦልን መንገድ፣ እውነትና ሕይወት የሆነውን ክርስቶስን ብቸኛ የሆነውን መፍትሔ አሳየን፣ አመንን። እንኪያስ ማንም ሰው ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ ክርስቲያን መሆን አይችልም። ካልተቻለ ደግሞ፣ ከዚህ ውጭ የተደራጀች ቤተ ክርስቲያን ወይም ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ ለዘላለም ሕይወት የበቃ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ሊኖር አይችልም። እንግዲያስ መንፈስ ቅዱስን የሚቃወመው ማንኛው ነው? ማንም ሊኖር አይችልም። ይህ ለመጀመሪያው ጥያቄ ገለጻ ነው። አስከትዬም፣ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ተገኚ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይ፣ በሁሉ ላይ ባለሥልጣን፣ ተስተካካይ የሌለው ነው። መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ስለ ሆነ፣ እርሱን ተቃዋሚውም ሆነ አሳሪ ው ማን ነው? ክርስቶስ የሞተላት ቤተ ክርስቲያንማ አብራው ሠሪ ነች።

«እንዲህ ከሆነ ነገሩ፣ አለ ዓይን ዓይኑን አየው የነበረው ወንድም፣ «በዚህን ዘመን ትንቢት የለም፣ ልሳንም ቆሟል የሚሉት ምን ሊሰኙ ነው?» «እነርሱ በሮሜ 12-6-8፤ በአፌሶን 4፡11፤ 1ኛ ጴጥሮስ 4፡11፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 እና 28-30 ከተጠቀሱት በርካታ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች ውስጥ አንዱን ወይም

ሁለቱን የማይቀበሉ ናቸው። መቼም ልሳንም ሆነ ትንቢት ወይም የተቀረው ስጦታ ሁሉ በራሱ መንፈስ ቅዱስ እንዳልሆነ ማወቅ ደግሞ ማስተዋል ነው። ስጦታዎቹ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የተሰጡ፣ ያለ እኛ ድካም የተቸሩ ናቸው፤» ተግባባን።

በመጨረሻም፣ «እውነት እኮ ነው! እውነት እኮ ነው፣» የድግግም ቃላችን ሆነ። ባለማስተዋል ለዓመታት «የመንፈስ ቅዱስ አሳሪ፣ ተቃዋሚ፣ ወዘተ...» የተሰኙትን አጓጉል አባባሎች ለመተ ው ተስማሙ፣ ተስማማንም። የመንፈስ አንድነትን ይጠብቃል ይሉሃል ይሄ ነው - መተራረም እንደ ሕያው ቃሉ ሲሆን!

ውርጃ = መብት፣ ወይንስ ግድያ?

እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ነው። ለዚህም ነው የሰውን አካል ከምድር አፈር ካዘጋጀ በኋላ የሕይወት እስትንፋስ እፍ ያለበትና ሕያው ነፍስ ያለው እንዲሆን የፈቀደው።[1] ከዚህም የተነሣ ኢዮብ አለ፦ ሕይወትን የሰጠኝ ሁሉን የሚችል አምላክ እስትንፋስ ነው።[2] ስለዚህ ሕይወት የሰጪው አምላክ ንብረት ከመሆኑ የተነሣ፣ የሰውን ሕይወት መልሶ ለመውሰድ ብቸኛው ባለ መብት ፈጣሪ ሆነ። እንግዲህ ሰው ጣልቃ ገብቶ ሕይወትን ቢያጠፋ ራሱን በእግዚአብሔር ቦታ ማስቀመጡና መተካቱም አይደል!? ይህን መሰሉ ኃጢአት ደግሞ «ከበደል ሁሉ የከፋ ነው»። ለዚህም ነው የሕይወት ምንጭ አትግደል[3] ብሎ ትእዛዝ ያወጣው።

ሕይወት የሚጀምረውና በማኅፀን ውስጥ ህልውና የሚያገኘው የወንዱ ዘር ከሴቲቱ እንቁላል ጋር በተገናኘበት ቅጽበት ነው። ጅምሩ የተወሰነለትን ጊዜ ፈጽሞ እስከ ተወለደ ድረስ ያለማቋረጥ ሂደታዊ እድገት ይኖረዋል። እስከ ሠላሳኛው ቀን ድረስ የሠራ አካላቱ ቅርጽ ይይዛል። ጥቂት ቀን ሲታከልበት፣ የልብ ምቱም በወጉ ይታወቃል። አርባ አምስት ቀናት ሲያስቆጥር፣ የእጁ ክንድና የእግሩ ቅልጥም መጠነኛ እንቅስቃሴ ይኖራቸዋል። ስድሳኛው ቀን ሲጠናቀቅ ደግሞ አእምሮው ፈጣን እድገት ያሳያል፤ የእግርና የእጅ

ጣቶቹ የየራሳቸውን አሻራ ይይዛሉ። ሕፃኑ በዚህን መሰሉ የእድገት ሂደቱ ውስጥ የሚያጋጥመውን አደጋ መከላከል አይቻልም እንጂ፣ ጉዳት ቢገጥመው ሥቃይ ይሰማዋል። (ይህ ሁኔታ የውርጃውን ሙከራና አጋጣሚ ይመለከታል።)

* * *

የወንዱ የዘር ክሮሞዞምስ (ህብለ በራሄ) ከሴቲቱ አቻ ክሮሞዞምስ ጋር በተገናኘበት ቅጽበት የተጀመረ ይህ ሕይወት በፅንስነት የመኖርን ሂደት ገና እንደ ጀመረ፣ አልያም ሊዘልቅ ነው በተሰኘበት ጥቂት ወራት ወይም ደግሞ ለመወለዱ ብቁ በሚሆንበት ጊዜ ውስጥ የፅንሱ ሕይወት እንዲጨልም የሚደረግበት ሙከራ ዘርፈ ብዙ ነው። መቼም ወደ አለመኖር የማምጫ ጐዳናዎቹ በርካታ ቢሆኑም፣ ጥቂቶቹን እንደሚከተለው መዘርዘር ይቻላል። በማኅፀን ውስጥ ያለውን ሕይወት ለማፍረስ የማኅፀንን በር በማስፊያ መሣሪያ ተጠቅሞ ሽሉን በማወክ ለመቆራረጥ በሚረዳ መሣሪያ በመጠቀም ማውጣት። ሌላው ከዚሁ ጋር ተቀራራቢው አሁንም የማኅፀን በርን አስፍቶ አፈ ሰፊ ቧንቧ መሰል አካል በማስገባት ፅንሱን በመምጠጥ ስቦ ማስወገድ።

ጊዜው ገፍቶ ከሦስት እስከ አምስት የወር ክልል ውስጥ ሲገባ ደግሞ ክፍተቱ የተመቻቸና ብቁ ስለሚሆንም ጥርስ ባለው መሣሪያ ፅንሱን ቆራርጦ እንዲወጣ ማድረግ። በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የሕፃኑ ራስ ስለሚተልቅ ለማውጣት መሰባበር ይኖርበታል።

አካላቱ ሳይበተንና ፅንሱን በማጨንገፍ በሕይወት የሌለ ልጅን መውለድም ሌላው ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ ተግባራዊ እንዲሆን በእናቲቱ ሆድ ውስጥ ወደ ፅንሱ መርዛም ፈሳሽ በመርፌ በመላክ የሕፃኑን ጤንነት በማወክ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሕይወቱ እንዲያልፍ ይፈረድበታል። ኋላም ሙሉ በድኑ ይወጣል። ሌላው ያለመኖር ጎዳና ሕፃኑን እስከ ሕይወቱ እንዲወጣ አድርጎ ተገቢውን እንክብካቤ ነፍጎ በቸልተኝነት እንዲሞት መወሰን ነው።

* * *

ግን ወላዲቱ «እምዬ» በውላጇ ላይ ፈርዳ በዘሯ የምትጨክንበት ምክንያት ምን ይሆን? እርምጃ መውሰድስ ለምን አስፈለገ?

የመጀመሪያው «የይሆናል» ምክንያት ልጆችን በማሳደግ የሚኖረውን ኃላፊነት ላለመወጣትና የኑሮን ማሻቀብ ለመቆጣጠር ለተቀራራቢ ጉዳዮች ሲሆን፣ በሁለተኛነት የሚጠቀሰው ደግሞ ዘር ተቀባይዋ ሴትና ዘር አቀባዩ ወንድ የኃጢአት ጽዋቸውን ላለመጠጣት በመወሰን ከጋብቻ በፊት፣ ወይም በጋብቻ ውስጥ፣ ወይም መታመንን ባጎደለ ስርቆት የመጣን ፅንስ ከወላጆች፣ ከራስ፣ ከባል፣ ወይም ከእጮኛ ለመሰወር ኃጢአት ኃጢአትን ወልዶ በመፍትሔነት በውርጃ አማካይነት ነውርን በመሸፈን ራስን ነፃ ለማድረግ ነው።

ታዲያ እኮ መፍትሔ ተብዬዎቹ መፍትሔ ይምሰሉ እንጂ ተዛዝለው የሚያመጡት ችግር የትየለሌ ነው። መሐንነቱ፣ ያለወቅቱ መውለዱ፣ ከማጎፀን ውጭ መፀነሱ (የመኖር ተስፋ ባይኖረውም) ፣ በስሜት መዋዠቁ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ የግድያ ተጠያቂ መሆኑ፣ በመንግሥት ሕግም ሁኔታው ከተገለጠ አስወራጅም፣ የማስወረድ ተግባር ፈጻሚውም እስከ አምስት ዓመት የእሥራት ቅጣቱ (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 529 -530) ወዘተ... በእርምጃ ወሳጆቹ ላይ ሊከተል ይችላል። ሁሉም ክፉ ውጤቶች ናቸው።

* * *

በቅዱስ መጽሐፋችን ውስጥ ማስወረድን በተመለከተ የተገለጸ መመሪያ አለው ወይ? ምላሹ ፈጣን አይሁን እንጂ ለምን አይኖረውም። «ሥላሴ» የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ አንድም ቦታ አልተጠቀሰምና የሥላሴን ነገር አንቀበልም ማለት እንደማይቻል ሁሉ፣ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ እግዚአብሔር አሳቡን በገለጠ ቁጥር ከተሰበሰበው አጠቃላይ ትምህርት «ሥላሴ» በማያሻማ መልኩ እንደ ተገለጠ ሁሉ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር በማኅፀን ውስጥ እንዲቀመጥ በወሰነው ሕይወት ላይ ውርጃ መፈጸም በግድያ ስም የማይመዘገብበት ምክንያት አይኖረውም፣ ያውም «አትግደል»ን በመጣስ ሕግ ውስጥ። እንዴት ከተባባልን፣ በመረጃዎች እንዝለቅ፣ «እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጥሮታልና የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈሰሳል።»[4] ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በራሱ መልክ የፈጠረበት ዐቢይ ምክንያት ፈጣሪውን እንዲያመልክ፣ በምድር ላይም በሕይወት ኖሮ

እግዚአብሔርን እንዲያሳውቅ፣ በአመዛዛኝነቱ፣ በአስተዋይነቱ፣ በአዋቂነቱ ዓለምን እንዲያስከብር አስቦ ነው። አምላክ እስትንፋስን ለሰው ልጅ የሰጠው ለራሱ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲውል በመወሰን ነው። ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሰው ልጅ እንዲኖርለት ይፈልጋል። እንደ ፈጠረው ሁሉ፣ በራሱ ጊዜ ሕይወቱን ወደ ራሱ ይወስዳል። በዚህ ውሳኔውም ጣልቃ ገብነትን - ማስወረድን- እግዚአብሔር አምርሮ ይጠላል። ለምን? «አምላክ እኔ ብቻ ነኝ. . .የምገድልም ሕይወትንም የምሰጥ እኔ ነኝ» ብሏልና።[5]

* * *

ዳዊት በማኅፀን ውስጥ በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር የነበረውን ድርሻ ሲገልጥ፣ «ሁለንተናዬን የፈጠርህ አንተ ነህ፣ በእናቴ ማኅፀን አገጣጥመህ የሠራኸኝ አንተ ነህ...አጥንቶቼ በመሠራት ላይ እንዳሉ በእናቴም ማኅፀን በጥንቃቄ በመገጣጠም ላይ እንዳሉ፣ እዚያም በስውር በማድግበት ጊዜ በዚያ መሆኔን አንተ ታውቅ ነበር።»[6] አለ። ይህ የዳዊት የምስክርነት ቃል በማኅፀን ላለው ሕይወት ታላቁ ባለ ድርሻ እግዚአብሔር ብቻ ነው ይላል። ከዚህ ቀድሞ እርሱ በማኅፀን ውስጥ ሕይወትን ከማስቀመጡም በፊት እንኳ ስለ ሕፃኑ የወደፊት ሕይወት ሁሉን ያውቃል፣ ለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ኤርምያስን፣ ዮሐንስን፣ ኋላም ኢየሱስ ክርስቶስን በማስረጃነት ያቀርባል።

እግዚአብሔር ኤርምያስን አለው፣ «ገና በእናትህ ማኅፀን እንድትፀነስ ከማድረጌ በፊት መርጬሃለሁ፣ ከመወለድህም በፊት አንተን ቀድሼሃለሁ ለሕዝቦች ሁሉ ነብይ አድርጌ ሾሜሃለሁ።»[7] ይለዋል። ተመልከቱ፣ ይህ ሁሉ ዕቅድ የእናቱ ወይም የአባቱ አልነበረም፤ እነርሱማ ምን ያውቃሉ? ምንም።

መጥምቁ ዮሐንስ ሳይወለድ በፊት ስም ወጣለት- ዮሐንስ ተብሎ። በማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መሆኑን፣ ተወልዶም ለብዙዎች ደስታ እንዲሆንና ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር አምላካቸው እንደሚመልስም ተበሰረለት። ገና ሳይፀነስ እና እንደ ተባለውም ሆነ። በማኅፀን ውስጥ እንዳለ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ፣ ጊዜው ሞልቶ ሲወለድም ዮሐንስ ተብሎ ተጠራ፣ አድጎም ቀደም

ሲል የተወሰነውን የእግዚአብሔርን ሙሉ አሳብ ፈጸመ::[8]

* * *

ኢየሱስም «ኢየሱስ ተብሎ መጠራቱ፣ ታላቅ መሆኑ፣ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ መባሉ፣ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን መውሰዱ፣ በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም መንገሡ እናም መንግሥቱም መጨረሻ የሌለው መሆኑን» እግዚአብሔር በመልአኩ በኩል ከመፀነሱ በፊት አስቀድሞ ለማርያም ገለጸላት::[9] የተነገረለት አብዛኛው ተፈጽሟል:: ለፍጻሜዎቹ ሁሉ ዋንኛው ምክንያት የጌታ ኢየሱስ መወለድ ነበር እናም በሕይወት መኖር::

* * *

በእነዚህ ሦስት ታሪኮች እግዚአብሔር በእናት ማኅፀን ውስጥ ለፈጠረው ሰው ቀድሞ ዕቅድ እንዳለው ጽኑ ማረጋገጫዎች ናቸው:: ከዚህም የተነሣ፣ በራሳችን አካል ውስጥ እግዚአብሔር በሚያሳድረው ሀብት የመብቱ ባለቤትነት በእኛ ዘንድ ውስን መሆኑን እናስብ:: «ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው፣ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፣»[10] የጳውሎስ ቃል ነው:: ከዚህም የተነሣ፣ የውርጃ መብት የለንም:: የመግደል ሥልጣን የእግዚአብሔር፣ ሕይወትንም መስጠት የእርሱ ብቻ ነው::

ይልቅ ማስወረዱን በቸልተኝነት ማየት ከምን ይመጣል? የሚለውን ጥያቄ እንመለስበት:- ሁለት ምላሾች ይጠቀሳሉ:: አንዱ ያዕቆብ፣ «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል»[11] አለን:: ወደ እግዚአብሔር ባለመቅረባችን የእግዚአብሔርን ፍላጎትና የእርሱን አሳብ፣ ትክክለኛ ምሪቱን፣ የእርሱ የሆነውን ግልጽ ውሳኔ እንዳናውቅ እንሆናለን:: ውርጃ ግድ መሆኑን ዘንግተንም የዲያብሎስን አሳብ በማድመጥ ሽንገላውን እስከ «ካስወገድኩት ፅንስ ያስነቀልኩት ጥርስ ጐዳኝ» ድረስ እንሄዳለን:: ይሄ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ የሚወገድ የስንፍና መንገድ ነው - ቸልተኝነት::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሁለተኛውና ውርጃን በቸልተኝነት እንድናይ

የሚያደርገን «ባልንጀራችንን እንደ ነፍሳችን የመውደድን» ሕግ መሻር ይሆናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግጋትን ሁሉ ያሠረውና የጠቀለለው፣ «እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ ውደድ፤ ይህም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ እንድትወድ ያደርጋል»[12] በሚል ነው። ሌላውን ያለመውደዳችን ምንጩ ወይም በማጎፀን ስላለው ሕፃን የመግደል ውሳኔያችን መነሻው ፍቅርን ማጣት ነው። ባለመታዘዝ እግዚአብሔርን መጥላት፤ በሥልጣኑም መግባት። እነዚህ ሁለት ነገሮች በሕይወታችን እየገነኑ ሲመጡ፣ ለኃጢአት ያለን ስፍራ ዝቅተኛ በመሆን ቸልተኝነት በውሳኔዎቻችን ላይ ሊነግሥ ይችላል። በማጎፀናችን ውስጥ የተሸከምነውን ሕፃን ሳንወድ፣ ያላየነውን እግዚአብሔር እንወደዋለን ብንልስ ያዋጣልን?[13] አያዋጣም። ስለዚህም፣ ወላጆች ከማጎፀናቸውና ከአብራካቸው በሚወጣው ነፍስ ላይ የውርጃን ቅጣት የሚበይኑት ለምን ይሆን? ረጋ ብለን እናስብ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. ዘፍጥረት 1:7
2. ኢዮብ 33:4
3. ዘጸአት 20:13
4. ዘፍጥረት 9:6
5. ዘዳግም 32:39
6. መዝሙር (139:13፣ 15-16
7. ኤርምያስ 1:5
8. ሉቃስ 1:57-66
9. ሉቃስ 4:16
10. ሮሜ 12:1
11. ያዕቆብ 4:7
12. ማቴዎስ 22:37-40
13. 1ኛ ዮሐንስ 4:40

ዋቢ መጻሕፍት

1. Abortion by Dr. & Mr. J. C. Willke.
2. Children Things We Throw Away by Melody Green.
3. Moral Ethics by Herbert VandorWat.
4. The Sanctity of Human Life by Harold S. Martin.
5. The Crime of Being Alive by Sharon Bennelt.
6. The Abortion Attitudes for Action by Melody Green.
7. **የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ**

የወላጅ አባዜ!

ሊታዩ በሚችሉበት ስፍራ ላይ ተሰቅለው «የዚህ ቤት ራስ ክርስቶስ ነው»፣ «እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።» የሚሉት ጥቅሶች በጌጥ ተሸልመው በበርካታ ክርስቲያን ቤተሰብ ቤቶች ውስጥ ይገኛሉ።

እነዚህ ተነባቢ ተሰቃዮች በውስጣቸው አምቀው የያዙት እውነት ጠንካራ ነው፣ የመጀመሪያው የልጆች ራስ ሚስት ከሆነች፣ የሚስት ራስ ባል ከሆነበት ቤት ውስጥ የሁሉም ዋኛ መሪ፣ አስተዳዳሪና ተቆጣጣሪ ክርስቶስ መሆኑን የሚገልጥ ክቡር ቃል ነው። በትይዩም፣ ዘመዶቻችንም፣ ጎረቤቶቻችን መላው ኅብረተሰብ እና ሰይጣንም የምናመልከውን አምላካችንን የምንወደውን ጌታችንን ሊያቀልሉብን፣ ወይም ሊያጠራጥሩን፣ ሊያስክዱን የፈተና ጦራቸውን ሲሰብቁ፣ «እኛ ግን እግዚአብሔርን ከማምለክ» ወደ ኋላ አለማለትን ሁሌ ማብሰራችን ጀግንነት ነው።

* * *

ተንጠልጣዮቹ የጥቅስ ሥራዎች «ተናገሩ» ቢሰኙ የሚሉት ከዚህ ያልተለየውን ነው። የእነርሱ ፍላጎት ይህ ሆኖ ግን

የሰቀላቸው ኑሮ በአባዜ የተሞላ ቢሆንስ?

ቤተሰብ በኑሮውና በተግባሩ ይህንን ሳይገልጸው በተቀራኒው «የዚህ ቤት ራስ እኔው ነኝ...እኔም ቤቱም መሻታችንን እናመልካለን» ቢመሰክር፣ የዚያ ቤት ታይታ ነገሩና ተግባሩ እንደ ስምና ወርቅ አልተጣጣሙና ጥፋት ከፊታቸው ሊጠብቃቸው ይችላል።

መቼም የሁሉም ሕይወት በቅጡ የሚፈተነው በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ስለሆነ፣ ከሰው ጋር በምናደርጋቸው መስተጋብሮች አባት ከሚስት፣ ልጅ ከአባት ከእናት፣ ከቤተሰብ ከዘመድ አዝማድ፣ ከጎ ረቤት ከአጎራባች ጋር የሕይወትንና የኑሮን ገጠመኞች ይለዋወጣል። ታዲያ በየድንገቱ ልውውጥ፣ «ራስ ነህ» የተሰኘው ክርስቶስ በእኛ ሕይወት እርግጥ ራስ መሆኑ ይፈተናል፤ እናመልከዋለን የተባለለት እግዚአብሔርም መመለኩ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ይፈተሻል፣ «የፈረሱም የሜዳውም ይኸው» ብሒል በተግባር ውሎ፤ ክርስትናችን ሕይወታችን መሆኑ በአደባባይ ተፈትኖ የሚያልፍበት ወይም የሚወድቅበት ፈታኝ ወቅት ሰው ከሰው ጋር ሲኖር ብቻ ነው።

ክርስቲያን ቤተሰብ በኑሮአቸው ከሰቀሉት ጥቅስ ጋር ተዛማጅ ባይሆኑ፣ መፍትሔው ምንድን ነው? ከወላጆች ምን ምን ይጠበቅባቸዋል? ልጆቻቸው የክርስቶስን ራስነት የተረዱ፣ ያመኑ፣ የታዘዙ እንዲሆኑ ምን ያስፈልጋቸዋል? የዚህን መልስ ጠቅለል አድርጌ በየተራ ላቅርብና፣ እንደ ጌታ «ጆሮ ያለው ይስማ» ልበል።

* * *

ልጃችሁን በጎሊናችሁ ስላችሁ ከሕፃንነቱ እስከ ሙሉ እድገቱ ምን እንደሚመስል ማሰብ ካለባችሁ ልታስቡት የሚገባው ጢሞቴዎስን መሆን አለበት፣ በዕድሜ ለጋ በነበረው ጢሞቴዎስ ሕይወት ውስጥ ገና ከጥዋቱ ክርስቶስ በእርሱ ሕይወት በርቶና ደምቆ ታይቷል፣ ለድምቀቱና ማስመሰል ላልተቀላቀለበት እምነቱ ቀዳሚ አብቃይ፣ ኮትኳቾቹ ወላጆች ናቸው - ቤተሰቡ። ጳውሎስ እማኝነቱን ለእርሱ ሲሰጥ፣ «የክርስቶስ የታላቅነቱና የአዳኝነቱ የድካሙ ውጤት በአያትህ ሕይወት ተገልጦ ለአንተ ተላለፈልህ፤ በእናትህም ሕይወት ውስጥ ሥር ሰድዶ ይህ ሕይወት ለአንተ ተት

ረፈረፈልህ፣ ከእነርሱም ብርቱ ድካም የተነሣ የክርስቶስን አርማ ተሸከምክ» ይልለታል፤ ብላቴናው ጢሞቴዎስን። ወላጆች በክርስቶስ ያገኛችሁትን ንጹሕ እምነት ወደ ልጆቻችሁ ማስተላለፍ ይጠበቅባችኋል፤ የራሳችሁ ጢሞቴዎስ እንዲኖራችሁ።

ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ከትምህርት ሲመጡ ትኩረት በመስጠት የክፍል ሥራ ተሰጥቷቸው ከሆነ እንደሚገባ መሥራታቸውን ያዩላቸዋል፤ የቤት ሥራ ካላቸውም ግልጽ ያልሆነላቸውን በማስረዳት ያበረታቷቸዋል፤ ተግተው እንዲያጠኑም በየጊዜው ያስታውሷቸዋል። ግን ጎን ለጎን አብረው ያላስኬዱት ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የሰጠውን ምክር መዘንጋት ነው። እንደ ሁኔታውም መተው «...ዛሬ የምሰጥህን እነዚህኑ ትዕዛዛት ዘወትር አሰላስል፣ ለልጆችህም አስተምራቸው።» ይህ እውነት ስለ ቤተሰብ «እኔ እና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን» የማለቱ ማጽኛው መንገድ ነው።

የእግዚአብሔር የሆነው መመሪያ በራስህ ሕይወትና በልጆችም ሕይወት ውስጥ ቅድሚያ እንዲኖረው በማድረግ መትከል ዐቢይ ጉዳይ ነው። ወላጆች ከትምህርት ቤቱ የቤት ሥራና ክትትል ሊቀድምባቸው የሚገባ ተግባር ይህ ነው። በዚህ ጉዳይ የጠቢቡ ሰለሞን ምክርም «ልጅን እንዴት መኖር እንደሚገባው ብታስተምረው፣ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ከዚህ ፈቀቅ አይልም» (ምሳሌ 22፡6) የሚል ነው።

ወላጆች ሊገነዘቡት ከሚገባው ነጥብ ሌላኛው የልጆች የስብዕና ጉዳይ ነው። ጥንቃቄን በተሞላ መልኩ ስሜታቸው፣ አእምሮአቸው፣ አካላቸው፣ ማኅበራዊ እና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ፈርጅ ይዞ እንደሚገባ በማደግ ወደ ተደላደለ ሙሉዕነት እንዲደርስ መጣር አለባቸው። በልጆች ላይ የሚወሰድ የትኛውም ዓይነት የእርምት እርምጃ ልቡ ጥፋተኝነቱን ተገንዝቦ በጥፋቱም እንዲጸጸት አድርጎት የሚያልፍ መሆን ይገባዋል። ከዚህ የራቀ ሆኖ ልጆች በምሬት ሕይወታቸውን መምራት ቀጥለው መራሮች እንዳይሆኑ ወላጆች የልጆቻቸውን የዕድሜ ታናሽነት ከግንዛቤ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፣ ስፍራ በመስጠት ዛሬ ከመከሩት ልጅ ዛሬውኑ ፍጹምነትን ባለመጠበቅ፣ ወላጅ ባይሆን ነው የሚያሰኝ ግፍ

የሞላበትን ቅጣት በማራቅ፤ ለእኔ ግድ የላቸውም የሚያሰኙ አቆጥቋጭ አሳብን በመንቀል በምትኩ «ወላጆች ሆይ! በጌታ ኢየሱስ ሥነ-ሥርዓትና ምክር...ልጆቻችሁን አሳድጉ? ኤፌሶን 6፡4ን መታዘዝ በውጤቱ የተሟላ ስብዕና ያላቸውን ልጆች ያስገኛል።

* * *

ወላጆች በቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት አገልግሎት ፍሬያማና ሞገስ የተላበሰ፣ የተከበረም እንዲሆን ከሚረጋገጥበት መረጃዎች አንዱ የልጆቻቸው ሕይወት በራሱ እየጮኸ የሚሰጠው ምስክርነት ነው። ለወላጆቻቸው ያላቸው አክብሮት፣ ከእነርሱ ለወጣው ትእዛዝ ያላቸው ተገዥነት፣ ወላጆችን ተደማጭነትንና ተቀባይነትን በቤተ ክርስቲያናቸውና በየደረሱበት ስፍራ ሁሉ ማስገኘቱን ከወዲሁ በማስተዋል ለአስተዳደጋቸው መጠንቀቅ ተገቢ ነው። እንዲህ ዓይነት ልጆች ያሉት ለሽምግልና በቅቷልና። ቲቶ 1፡5-6 ታዲያ ይህ በአደባባይ የወጣ ትርፍ በቤት የጀመረው የቃል ትምህርትና የሕይወት ምሳሌነት ያስገኘው ውጤት ነው።

ወላጆች መውለድን እንጂ ማሳደግን፣ መብዛትን እንጂ መጥራትን፣ ከሕይወት ዕቅዳቸው ከአራቁ ለልጆቻቸው ሊሚሉላቸው የሚገቡትን መሠረታዊ አይቀሬ ጉዳዮችን ቸል ይሉባቸዋል፣ እንደ የሁኔታውም ይረሱዋቸዋል፤ ይህ ግድየለሽነት በምግባቸው፣ በልብሳቸው፣ በትምህርታቸው፣ ወዘተ...ከተገለጸ እንዲህ ዓይነቱ ወላጅ «ለቅርብ ቤተሰቦቻቸው ያውም ለልጆቻቸው አላሰቡምና እምነታቸውን የካዱ ሆነዋል፤ ከማያምንም ሰው ከፍተ ዋል» ይሰኛሉ (1ኛ ጢሞ. 5፡8)። ታዲያ የዚህ ሂደት ዕድገቱ ብቸኝነትና የበታችነት የሚሰማቸውን ልጆች ማብዛት ይሆናል። ለዚህ «ልምጡ መንፈሳዊነት» ትርጉም የለውም፤ «ክርስቲያን ነን» ማለትም ፈዝ ነው። ለዚህ መፍትሔው ወላጆች አቅሙ እስካላቸው ድረስ ለልጆቻቸው ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ መፈጸምን ቸል አለማለት ነው።

«የዚህ ቤት ራስ ክርስቶስ ነው» የሚል ልጅን አፍርቶ ለኃላፊነት ለማብቃት የወላጅ እውነተኛ ፍቅር አግባብ በሆነ በቅጣት የተሞላም መሆኑን በተግባር መግለጽ ነው፤ ያጠፋ ሁሉ መቀጣት አለበት። እግዚአብሔር እኛን ልጆቹን በተስተካከለ ሕይወት

እንድንመራ የፍቅር ቅጣትን በሕይወታችን በማድረግ አሳድጎናል፣ ያሳድገናልም። የሚወደድ ልጅ እንዲታረም መቀጣቱ ተገቢ ከሆነ፣ ልጆቻችንን እንወዳቸዋለን ማለታችንና በቁልምጫ ስም ሌት ተቀን መጥራታችን በብቻው ፋይዳ-ቢስ ነው። አጥፍተው ሲገኙ በመቅጣት ማስተማር የመውደድ መግለጫ ነው (ምሳሌ 22፡17)።

ግራ የሚያጋቡ ተግባሮችን ልጆች ሲያደርጉና ጥያቄ የሚፈጥር ሥራ ሲሠሩም ወላጆች እያመነቱ ምን መሆናቸው ነው? በማለት ማቅማማት ወይም እስኪነጋ በማለት መዘግየት በፍጻሜው በጎ ውጤት አያስገኝም። ካህኑ ዔሊ በልጆቹ ተግባራት ሁሉ ንዝህላል ሆነ። ለምን? እንዴት? ማለት ሲችል ተወው። አዶንያስ የዳዊት ልጅንም በተመለከተ ተመሳሳይ እርምጃን ወላጅ ዳዊት አደረገ። የሠረገሎችን፣ የፈረሶችን፣ ፈጣን ሯጮችን ሲያደራጅ ለምን ይሆን? ማለትን ቸል አለ። ውጤቱ ታዲያ አባቱን ከመንግሥቱ ለማሸቀንጠር መከራ ማድረግ ሆነ። ወላጆች በልጅነታቸው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አያገባንም ማለት አለመቻሉን ማወቅና ከልጆቻቸው ጋር የጠበቀ ወዳጅነትን ማፍራት «እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» የሚለውን ቃል ያጸናል።

ቤተ ክርስቲያንን ሙሉ ለማድረግ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን እንደ ወደደ ለእያንዳንዱ አማኝ እንዴት እንደ ደለደለው እናውቃለን። ሁሌም ስለ ስጦታዎቹ በመገረምና በመደነቅ ሲጠቅሙን ስንጠቀምበት፣ ስለ እነርሱም ስንናገር እንሰነብታለን። ግና ብዙ ያልተነገረላቸው የክብር ስጦታዎችም የልጅ ስጦታዎች ከእግዚአብሔር እጅ ለወላጆች ብቻ የተሰጡ አሉ። ስጦታ ከሆኑ ታዲያ አለአግባቡ አይያዙም፣ አይናቁም፣ አይደርሱም። ዳዊት ትኩረት እንዲደረግባቸው ወድዶ፣ «ልጆች ከእግዚአብሔር የሚገኙ ስጦታዎች ናቸው፤» አለላቸው (መዝሙር 27፡3)። ይህን መረዳትና ማመን የወላጆች የውዴታ ግዴታ ነው የሚል ቤተሰብን ለማብዛት የዚህ ቤት ራስ ክርስቶስ ነው።

* * *

ወላጅ እናት ሴት ልጇን ስትቀጣ በተደመጠው ቃለ ምልልስ ልጠቅልል።

«ከቤት ውጪልኝ!»

«ምን አጠፋሁ? እናት ዓለም... ደግሞ እኮ መሽቷል!»

«መምሸቱን አትነግሪኝም፣ የደከምኩት ክርስቲያን ትሆኛለሽ ብዬ ነበር?...ግን...» «ግን...ምን ምን ሳደርግ ስሆን እየሸኘን ሐዋርያው ጳውሎስ እንኳን...»

* * *

አላስጨረሰቻትም። ገፍትራ አስወጣቻት፤ ጎረቤቶቿ የዛሬን ትደር እያሉ ተለማመኗት። ግን ላትሰማቸው ወስና ወደ ጨለማው ሰደደቻት። ልጅቱ ከእናቷ በተለየች በዓመቱ አማላጅ ላከችባት፣ «እናት ዓለም ይቅር በዪኝ» የሚልን መልእክት አስጨብጣ። «የእርሷን ነገር አያሳየኝ፣» የእናትየው መልስ ነበር። በእኔ እምነት ከወላጆች የሚጠበቀው የፍቅር መለኪያ ይህ ሊሆን አይገባውም። ፍቅር ከልጆቹ ማንነት የተነሣ የሚፈልቅና የሚፈጠር መሆን የለበትም። ወላጆች ለልጆቻቸው ባላቸው ነገር በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነው ጊዜንና ሁኔታን አይቶ የማይንሸራተትና የማይቀያየርን ፍቅር በሕይወታቸው ውስጥ ሊያፈስሱላቸው ይገባል። በዚህም ዐመፀኝነት ኋላ ላይ ሊቀየር፣ ሊለወጥም ይችላል። ለዚህ ሁነኛው ምሳሌ የወላጅን ፍቅር አስመልክቶ የሉቃስ አሥራ አምስቱ አባት ነው። ወላጆች ልጆቻችሁን በማይለወጥ ፍቅር ውደዷቸው ከላይ የተጠቀሱት በተግባር ሲተረጎሙ በእርግጥ የእናንተ ቤት ራስ ክርስቶስ መሆኑ፣ እናንተና ቤታችሁም በእርግጥ እግዚአብሔርን እንደምታመልኩ እውን ይሆናል።

«ጥሎሽ»ን ጣለብኝ

እጮኛ ኖራው ለዓመታት ሳይጋቡ መቆየታቸው ከንክኖኝ «እስከ አሁን የምትወዳትን ልጅ አለማግባትህ ለምን ይሆን?» ብዬ ጠየቅኩ፣ ለመልሱ አላቅማማም። «አጉል ባህል ተጋረጠኝ፣ የጥሎሽ ዝግጅት ለዚህ አበቃኝ፣ ጭንቅ ሆኖብኝ» ነበር መልሱ።

እንዴት ጥሎሽ ይህን ሰው አስጨነቀ? ራሱ ጥሎሽ ምንድን

ነው? ከየት መጥቶ እንዴትስ ይስተናገዳል? መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይሆንን? መሠረታዊ ነገሮች የተሟሉለት ስለ ጥሎሽ ብሎ ወቅቱን ማሳለፍ ይገባው ይሆንን? ሥርዓት ሳይጠብቁ ጥያቄዎቹ በአእምሮዬ ሊስተናገዱ ፈለጉ። ዳሩ ግን የመክብብ 3፡11 «ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው» በከፊል መልስነት ፈጥኖ ከተ ፍ አለልኝ። ሁሉም በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ ሲያልፍ ውበቱ የተ ጠበቀ እንደሚሆን የጋራ ደስታን፣ የጋራ ሰላምንና ፍቅርን እንደሚያድል ተገነዘብኩ።

ግና እግዚአብሔር ለሥራ፣ ለጨዋታ፣ ለመተዋወቂያ፣ ለመተ ጫጨያ፣ ለመጋቢያ፣ ወዘተ...ጊዜን ሰጥቷል። የመተዋወቂያው ከመተጫጨያው፣ የመተጫጨያው ከመጋቢያው ጊዜ ጋር እየተ ቃየጡ፣ አንዱ በአንዱ ላይ ይተላለፋል፤ ይደረባል። ይህን ጊዜ ሊኖር የሚገባው ድምቀት በፍዘት፣ በረከትም በመጓደል ሊተካ ይችላል።

ወዳጄ ግን የሚለኝ «ላገባ የሚገባኝ ከ3 ዓመታት በፊት ነበር፤ ግን ተገቢውን የወርቅ ስጦታና አልባሳት በዓይነት በዓይነት ላሟላው አልቻልኩም። ዕቁቡም፣ ቁጠባውም ተሰባስቦ እወርቁ ጋ ደረስኩበት ስል፣ ከአምናው ተመን የዘንድሮው በሁለት እጥፍ ተ መንድጎ ይቀድመኛል። ተፍጨርጭሬ በደረስኩ ቁጥር እርሱ የሚሸሸኝ ከሆነ፣ መቼ ይሆን ጋብቻዬ?» ጸጥታ ሆነ።

* * *

«ይህን ጥሎሽ ደግሞ የምወዳት ልጅ ትፈቅደዋለች፡ የእርሷ ምርጫ ትክክለኝነቱ በገንዘቡ መጠን እንዲታሰብና፣ ቤተሰቧ እኔን በላቀ መልኩ እንዲቀበሉኝ ፈልጋለች። የእርሷን በቅጡ ባላውቅም፣ ወድጃታለሁና እኔ ደግሞ ለእርሷ ደስታ ነው ያለሁት። ይልቁኑ፣ አንድ ጊዜ ያጫወተችኝና ዛሬም ጎሊናዬን የሚያናውዘውን ልንገርህ። የእርሷ ወዳጆች አብዛኞቹ ሲያገቡ ሚዜ ሆና በጥሎሽ ምሽት ተገኝታ ክርክር ፈጥራ ነበር። አነሰ! ጎደለ! ጫማው ከቀሚሱ ጋር አልተግባባም፣ ወርቁ ሃያ አንድ ካራት አይደለም» እያለች በጭንቅ በተከማቸ ጥሎሽ ላይ አፊዛ ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ ሙሽራው የላካቸው ሙዜዎች «ይቅርታ ጠይቀው ዋስም ጠርተ ው» መመለሳቸውን ዘርዝራልኛለች። «አንተ ግን በምንም

እንዳትነቀፍብኝ፣ ይህ ቀረ ብለው እንዳይቆጡ፣ አልማዝ ሰርግ ላይ የተረሳውን ከአሁኑ እንድትገዛ፣ የከበቡሽ ጊዜ ቅሬታ ላስከተለው ወርቅ ፋክቱር እንድትይዝ፣ ኮቱ ከጉርዱ፣ ቦርሳው ከጫማው፣ በቀለም መጣጣማቸውን አገናዝብልኝ፣ እሺ!» ዓይን ዓይኔን እያየች ምላሹም። እሺ ነው! ያ እሽታ ዛሬም ድንጋጤዬ ነው።

* * *

ለማንኛውም አነሣሴ ጥሎሽ ምን ማለት ነው? ከሚለው ይጀምራል። ደስታ ተክለወልድ በአማርኛ መዝገበ ቃላታቸው፣ «ለልጃገረድ የሠርጉ ዕለት በዕድምተኛ በሠርገኛ ፊት የሚጣል ወርቅና ብር፣ ቀሚስና ኩታ፣ ካባና ጌጥ ስጦታ በየዓይነቱ...ሰጠ» ጥሎሽ ይባላል። ይላሉ። ሌላው ጸሐፊ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ደግሞ፣ «...ለሴት ልጅ ጫማ መጋለጫ ጥሎሽ የሚሆንን የጋብቻ ገንዘብ፣ የፍቅር ጥሎሽ የሚሆን የመወደድ ስጦታን ሰጠ» በማለት አስፍረዋል፤ ሁለቱ የቋንቋ ሊቃውንት ስለ ጥሎሽ የሚሰጡት ምጥን ፍቺ፣ «በሙሽሪት ቤተሰብ ፊት ልጅቱንና ቤተሰቧን መውደዱንና መምረጡን ለመግለጥ የሚቀርብ የሙሽራው ስጦታ» ሊባል ይችላል። ይህ ስጦታው እንደ ሁኔታው እናት አባትንም ማሽሞንሞንን ሊጨምር ይችላል። ትርጓሜውን አስከትሎ ሊቀጥል የሚገባውን ከማንሣት በፊት በሕንድ አገር «አቤት!» አሰኝቶ የነበረውን ለወንድ የሴት ቤተሰብ የሚሰጠውን የጥሎሽን ጉዳይ ላንሣ።

* * *

በአብዛኛው በሕንድ የአስተዳደር ክልል ኗሪ እናቶች አምጠው ሲወልዱ የሚታሰባቸው የምጣቸውን ጭንቅ ሳይሆን፣ የተወለደችው «ሴት» መሆኗን ሲረዱ የሚሰማቸው ኀዘን ነው፤ የሚያስመርራቸው። ሴትን መውለድ መርዶ ማርዳት ነው። አንድ ቤተሰብ ሁለት ሦስት ሴት ልጆችን እግዚአብሔር ከሰጣቸው፣ የባህላቸው የጥሎሽ ደንብ ያሸከማቸው ለሴት ልጃቸው ባልና ቤተሰብ ሕግ የደነገገውን ጥሎሽ መክፈል ይኖርባቸዋል። ይህም ራሳቸውን እንዲያማርሩ ያደርጋቸዋል። ጥሎሽ ያመጣውን መዘዝ ሕንዶቹ መፍትሔ ሰጠን ይላሉ። የተፀነሰው ሽል በማኅፀን ሳለ ወንድ ወይም ሴት መሆኑን መለየት በመቻል ይህ እውነት ነው። ተችሏልም። የሕንድ እናቶች የሕክምናው ውጤት ሴት

መሆኗን ከገለጠ፣ በጥሎሽ «ድህነትን» ከሚጠሩ፣ «ውርጃ ሊፈቀድ ይገባል» በማለት ይህን በሥራ ላይ ለማዋል ይራወጣሉ። ድርጊቱንም በየምክንያቱ ያደርጉታል። በጥሎሽ የመጣ መዘዝ ለሕይወት ጥፋት ሲዳርግ!

በአገራችን የሴት ቤተሰብ በአንዳንድ ስፍራ ጥሎሽ መጣሉ ቢታወቅም፣ በመተሳሰብ ነውና እንደ ሕንዶች አያሳስብም፤ ግን የጥሎሽ ጦስ በወቅቱ ላለማግባት የሚያስወስን ከሆነ፣ ይህ አቋም ሕይወትን ከማጥፋት ጋር አይቀራረብም ብላችሁ ነው? ቅድም የጥሎሽን ትርጉም ነው ያነሣሁት፣ አሁን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገጽታውን እናጢን። መቼም አዲስ ኪዳን የሚለው ብዙ ነገር ስለሌለ፣ መረጃዎቼ ሁሉ ከብሉይ ናቸው።

ዘፍጥረት 24፡53፣ «የአብርሃም ሎሌ ተልዕኮው እንደ ተሳካለት ሲያረጋግጥ፣ ለተመረጠችው ለርብቃ ከወርቅና ከብር የተሠሩ ጌጣጌጦችን፣ እንዲሁም ልብስ አውጥቶ ሰጣት፤ በተጨማሪም ለወንድምዋና ለእናትዋ በጣም ውድ የሆኑ ስጦታዎችን አውጥቶ ሰጠ» ይላል። ጥሎሽ መሆኑ ነው። ግን ማን ሰጠ? ለምን ተሰጠ? መልሱ ሰጪው ባል (ሙሽራው) የላከው መልእክተኛ ሳይሆን፣ አባትየው የላከው አገልጋይ ወይም ሎሌ ነው ስጦታውን የሰጠው። ያዘጋጀውም ራሱ ሎሌው ነው። የተሰጠበትም ዋንኛ ምክንያት ስኬ ታማኝነት ወይም መከናወን ስለ ገጠመው ብቻ ነው። ገጸ በረከቱንም የሰጠው ለርብቃ ብቻ ሳይሆን፣ ለቤተሰቧም ጭምር ነበር። ዛሬ ላይ ቆመን ይህን መሰሉን ጥሎሽ ነው የምንከተለው? ከተባለ፣ አይደለም ነው መልሱ። ጉዳዩም ለየቅል ነው። ስለዚህ በመታሰቢያነት አይዘከርም። ለወደዳት ለመረጣት ሙሽራው በሚዜው ነው የሚወሰነው። ሁለተኛውን ማስረጃ የምናገኘው በዘፍጥረት 34፡11-12 ነው። የሼኬም ጉድ። የያዕቆብን ልጅ ወደድኩ አለና ፈጠን ፈጠን ብሎ አስገደዳት፣ ክብረ ንጽሕናዋንም ደፈረ። ይህን ከፈጸመ በኋላ ወደ ዲናን አባትና ወንድሞች ሄደ። «አሳቤን ብትፈጽሙልኝ የምትፈልጉትን ሁሉ አደርጋለሁ፣ ለሙሽራዋም ጥሎሽ የፈለጋችሁትን ያህል ጠይቁኝ፣ እርስዋን እንዳገባ ፍቀዱልኝ እንጂ የፈለጋችሁትን ሁሉ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ» አለ። ሼኬም በዚህ ታሪክ ስጦታውን ጥሎሽ ብሎታል፣ ግን ከምን ተነሥቶ

የታሰበ ገጸ በረከት? ምላሹ ሁለት ነው። እርሷን የራሱ ማድረግና ሰላምን ከቤተሰቦቿ ጋር ለመፍጠር የሚሰጥ ስጦታ ነበር፣ ማባበያ ሊሆን የሚገባው። ግን ተዋውቀው፣ ተዋድደው ቢተጫጩና ወደ ጋብቻ ዓለም ለመምጣት በመስማማት ላይ ሆነው ይህን ስጦታ ሊያቀርቡ ቢታሰብ ጥሩ፤ ግን ሼኬም እንዳያት «ወደዳት»፣ ክብረ ንጽሕናዋንም ደፈረ፣ ይህ ጥሎሽ ግን የንጹሕ ፍቅር መግለጫ ስላልነበረ፣ የወንድሞቿ ውሳኔ በቀል ነበር። ሼኬምንና ቤተሰቡን መግደል። ገደሉም። እንግዲህ በዚህ መነሻነት ሊሰጥ የተገባውን ጥሎሽ አሁንም በእኛ ጊዜ ላይ ቆመን ካሰብነው ከምናውቀው የእኛ ጋር አይገጥምምና ይተው። እርግጥ ከነዓናዊው ሼክም በዘጸአት 22:16-17፣ «አንድ ሰው የአንዲት ልጃገረድ ክብረ ንጽሕና ቢደፍር ማጫ ሰጥቶ ያግባት፣ የልጅትዋ አባት ሊድርለት ቢፈቅድ ግን ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ካሣ ለልጅትዋ አባት ይክፈል» የተሰኘውን ሕግ መፈጸሙም ይሆናል።

ይልቅ፣ ንጉሥ ሳኦል ልጁን ሜልኮልን ለዳዊት ሊድርለት ሲፈልግ ቅድመ-ዝግጅቱን አስታውቆት ነበር። ጥሎሽ ለልጃገረዲቱ እንዲቀርብ፣ ጥሎሽ ግን ወርቅና የተትረፈረፈ ስጦታ ሳይሆን፣ የፍልስጥኤማውያንን ሸለፈት ነበር። ዳዊት የንጉሡን ልጅ ሊያገባ በመታሰቡ ደስ ስለ ተሰኘ መቶ ፍልስጥኤም ሳይሆን መቶ መርቆ ሁለት መቶውን ጨፈጨፈ። የሚገባውንም ጥሎሽ ሰጠ (1ኛ ሳሙ. 18: 24-27)።

ሳኦል ለዳዊት መልእክት ሲልክ፣ «ንጉሡ ስለ ልጁ ከአንተ የሚፈልገው ጥሎሽ. . .ይህ ነው» ካለ፣ በተወሰነ መጠን ሊቀርብ የሚችል ገጸ በረከት እንዳለ ጠቋሚነት ይኖረዋል። እንዴት? ምን ያህል? የታወቀ ነገር የለም። እነዚህን ውሱን የጥሎሽ ጥቅሶች ስንመለከት፣ መጽሐፍ ቅዱስ እርሱን አስመልክቶ የሰጠው ገለጻ የለም ማለት ነው።

ጥሎሽ ግን ሐብትን ስለሚይዝና ገንዘብን ስለሚያጣቅስ አፍቅሮተ ገንዘብን አስመልክቶ ቅዱስ መጽሐፍ «በእርግጥ ያለኝ ይበቃኛል የሚል ሰው ፍጹም መንፈሳዊነትን ስለሚያተርፍበት ሃይማኖት የሀብት ምንጭ ነው። ምክንያቱም ወደዚህ ዓለም ምንም ይዘን አልመጣንም፤ ከዚህም ዓለም ይዘነው የምንሄደው ምንም

ነገር የለም። የምንበላውንና የምንለብሰውን ካገኘን ይበቃናል። ሀብታሞች ለመሆን የሚፈልጉ ግን በፈተና ይወድቃሉ፣ ሰዎችን በሚያበላሽና በሚያጠፋ ከንቱና አደገኛ በሆነ በብዙ ምኞት ወጥመድም ይያዛሉ። ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው። አንዳንድ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት በመመኘት ከእምነት ርቀው ልባቸውንም በሐዘን ጦር ወግተዋል» (1ኛ ጢሞ. 6፡6-10) እንደሚያስከትል ግንዛቤ በመስጠት ልቀጥል። ጥሎሽ ሰ ዎችን ወደ ጋብቻ በጊዜው እንዳይደርሱ በማድረግና ከእርሱ ይገኛ ል ተብሎ የተሰጠበት ገንዘብ ባለመሰብሰቡ የጭንቅ መዘዝ ቢሆን፣ የዚህ ምንጭ ገንዘብን ከመውደድ ጋር የተያያዘ ስለሚሆን፣ ከእግዚአብሔር የሚያርቅ ጉዳይ ሆኗል። በአንጉል መልክ ከጥሎሽ ጀርባ አፍቅሮተ-ገንዘብ ሥር ከሰደደ፣ «የእነርሱ አምላክ ሆዳቸው ነው፣ አሳፋሪ የሆነ ነውር ነገር ለእነርሱ ክብራቸው ነው። አሳባቸውም የሚያተኩረው በምድራዊ ነገር ላይ ነው» (ፊልጵ. 3፡19) እንዳያሰኝ ማመዛዘን ከወዲሁ መልካም ነው።

እንኪያስ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ጥሎሽን አስመልክቶ ሊገነዘበው የሚገባው ቁም ነገሮች የእግዚአብሔር አሳብ፣ ፍላጎትና የቃሉ እውነት በኅብረተሰቡ ባህል መካከል በመስረግ እያሸነፈ መውጣትን ነው። አንድ ሕዝብ የራሱ መለያ ባህል አለው። ባህልነቱ ከሕዝብ ሕዝብ ባመጋገቡ፣ በአለባበሱ፣ በአዘፋፈኑና ወደ ጋብቻ በመድረስ፣ ወዘተ...ስልቱ፣ በመጠን በመጠኑ ይለያያል። ጥሎሽንም አስመልክቶ እንዲሁ ነው። «አንዱ ወገን የሴቷ ቤተሰብ ለባልየው እንዲጥል ሊያስገድድ፣ ሌላኛው ሁለቱም ተሞሻሪዎች በልውውጥ ጥሎሽን ይጥላሉ። አሁንም ደግሞ እንደማነሣው አግቢውም ለብቻው ጥሮ ጥሮ ጥሎሽ የሚሰጥበት ሲሆን፣ በአንዳንድ ክልል ደግሞ ጥሎሽ ጭራሹን አይታወቅም።

እንግዲህ ቅዱስ ቃሉ በብቸኝነት የሚመራውና የሚገዛው ክርስቲያን ሕዝብ በምድር ዘመኑ ሁል ጊዜ የክርስቶስ አሳብና ፍላጎት እንዲያሟላ ቃሉንም እንዲፈጽም ውክልናን (አምባሳደርነት) ከያዘ፣ ተጋቢዎች ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን እኩል ስፍራ ሊያጤኑት ይገባል። በክርስቶስ ሥራ እኩል ከሆኑ ደግሞ፣ አንዱ በአንዱ ላይ ሊጫነው መብት የለውም። በምትኩ ተጋጪ

የሆኑ ጎጅ ባህላዊ ገጽታዎችን በመጋፈጥና በመሻገር ትዳራቸው በራሱ ወንጌልን ገላጭ እንዲሆን የፍቅርም ግዴታቸው መሆኑን ሊ ረዱ ይገባል። ጥሎሽ መንፈሳዊ ሕይወትን በማኮስመን፣ ስጋትን በመፍጠር፣ ትዳርን ማፍዘዝ መቻሉ በሁለተኛ ደረጃ ሊታወቅ ይገባዋል። ደራሲ ወርቁ «በክርስቲያናዊ ጋብቻ» መጽሐፋቸው ላይ ጥሎሽን አስመልክቶ ሲጽፉ፣ «ጥሎሽ የመስጠት ባህል በአገራችን በኢትዮጵያ እጅግ ተስፋፍቶ ይገኛል። በአውሮፓውያን ጥሎሽ መጣል ሴቷን እንደ ሸቀጥ መግዛት ነው በማለት ያወግዙታል» ይላሉ። አስከትለውም፣ «...የጥሎሽ ወጪ ከሠርጉ ወጪ ጋር ሲደመር ገና ሥራ ይዞ ራሱን ለማደራጀት ለሚጥር ወጣት ከባድ ሸክም ነው። ብዙ ጋብቻ የሚጀምረው ለጥሎሽና ለሰርግ የብድር ዕዳ ውስጥ በመግባት ነው...ይልቁኑ፣ ተጋባዥ ሰዎች ጋብቻቸውን እንዲያደንቁላቸው ለጥሎሽና ሠርግ ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት በማባከን ለሚሠሩት ቤትና ለአስፈላጊ ወጪ እንዲውል ገንዘቡን መያዝ ተገቢ ነው» ይላሉ፤ «አንተ ግን ነገርህን ሁሉ በልክ አድርግ» (2ኛ ጢሞ. 4፡5) የሚለውን ከጠቀሱ በኋላ።

እንዲህ ከሆነ ደግሞ፣ ክርስቲያን ተጋቢ ጢሞቴዎስ ከተመከ ረበት ምክር ውጭ መሆን የለበትም። እኔ መቼም ለተወደደችዋ ለእርሷ ጥሎሽ ሆኖ የሚቀርብላት ራሱ ነው ብዬ ነበር በሕይወት መጽሔት በቁጥር 7 «ማግባት ለምን?» ላይ የጻፍኩት። የወደደ ለወደዳት ፍቅረኛው ራሱን ነው የሚሰጠው። እርሷም እንዲሁ። የተሰጣጡት ከምንም የተነሣ አይደለም። መሥዋዕትነት የሚጠይቅ ፍቅር በመፈጸም ነው። እርሱ ምስኪንነቱንም ገልጾ አቅሙን አሳይቶ ተቀራረቡ። ኋላም በተገለጠው እውነት የሁለቱ ያለ ጥሎሽ ወይም በልክ በሆነ ጋብቻ ለመጋባት ራስን ማቅረብና ማዘጋጀት ግድ ሆነ። ግልጽነትን የተላበሰ ትውውቅ ዘላቂ ነገር ያበጃልና የዚህ ውሳኔንና መተማመን ነገ ለሚጋቡት ሊተውላቸው ይገባል።

በጥሎሽ መዘዝ ሳያገቡ ላነካከሱት ኩርሺላ ቻንዲ የሰጡትን ምክር ልጥቀስ። ባለንበት መልካምን ማድረግ ተገቢ መሆኑን ኢየሱስ ክርስቶስ አበሰረ። በሰንበት «ከእናንተ መካከል አንድ በግ ያለው በጉ በሰንበት ቀን በጉድጓድ ውስጥ ቢወድቅበት ስቦ የማያወጣው ማን ነው?» (ማቴ. 12፡11) አስተማረ። ያወጡታል

እንጂ፣ መልሱ ነበር። አናወጣውም ብለው ሰንበት ተላልፎ ሌላው ቀን እስኪመጣ እንጠብቅ ቢባል፣ አንድ ችግር ከፊት ለፊት አለ። የሚያደፍጡትና ዙሪያውን ወጣ ገባ የሚሉ አውሬዎች በጉን የዕለት ሲሳያቸው በማድረግ ያለ መታሰቢያ ያስቀሩታል። ከዚህ የተነሣ፣ ከክፉ አውሬዎች መጠበቅና ለሰው ጥቅም መዋል አለበትና በጉ ይወጣል። ልክ እንዲሁ፣ በጥሎሽ መዘዝ የሚዋልል ጎጂ ባህል ከእግዚአብሔር አሳብ ያለፈ ገና ሁሌ ማንም የአቅሙን በመፈጸም እንዳይዘረጋ ሊያገባት ባለችው የነገ ሙሽሪት የተተበተበ የነገ ባህል ልክ እንደ በጉ በጉድጓድ ድንገት እንደ ወደቀ ይቆጠራል። ሰንበት ነውና መውጣት የለበትም ተሰኝቶ እንዳይቀር ግን መልካም ማድረግ ለሙሽራው ይገባልና። በጥሎሽ ጉዳይ ተጎድቶ እንዳይቀር ቶሎ ይውጣ።

ግን እናንተ በጥሎሽ መዘዝ ዕዳ ገብታችሁ በመክፈል ላይ ያላችሁ የተበዳሪ ተሳዳጁ የትናንት ሙሽሮች፣ እናንተ ነገ ለማግባት ደፋ ቀና የምትሉ የጥሎሽ አሳብ ነውዘኞች፣ እናንተም ልትሞሸሩ ያላችሁ ልጃገረዶች፣ እናንተ «ባህል መጠበቅ» የምትሉ ወገኖች ስለ ጥሎሽ የምትጨነቁ፣ ስለ መጋባት ብትማከሩ አይመረጥም?!

ጾታዊ መፈላለግ

እግዚአብሔር በወንድና በሴት ሕይወት ውስጥ ጠንካራ ጾታዊ መፈላለግን አስቀምጠ። መፈላለጉንም በጋብቻ ፈጸመው። ጋብቻ ሁለቱንም አንድ ሥጋ ስላደረገ፣ ፍቺን ፈጽሞ ተቃወመ። አንድ ሥጋ የመሆን ምሥጢርንም ለመጋባት ዋነኛ ምክንያት አደረገው።

* * *

በዚህ ጽሑፍ የሥጋ ተራክቦ ግራ ቀኙን ካልቃኙት ምንም መፍትሔ የላቸውም የሚያሰኙ ችግሮችን ሊፈጥር መቻሉን አመላክታለሁ።

አንደኛው፣ ጠንካራ ጾታዊ መፈላለግ ዕድሜ ሲገፋ ወይም ከተ ጋቢዎቹ አንዱ በበሽታ ተጠቅቶ ሲደክም ቀዝቀዝ ሊል ይችላል።

በዚህ ወቅት የተመሠረተው ጋብቻ እግዚአብሔር ከመነሻው አዋህዶ አንድ ያደረገው በመሆኑ፣ የዕድሜ መግፋትና በሽታ ሊለየው አይቻ ልም። ይልቁኑ፣ በዚህ የጋብቻ ሕይወት ውስጥ የትዳር ዕድሜው በረዘመ ቁጥር መረዳዳቱና መተሳሰቡ በሁሉም አቅጣጫ እያደገ የመግባባቱ መጠን በመንፈሳዊ፣ በማኅበራዊ፣ በአእምሮአዊ፣ በስሜታዊ፣ እና በአካላዊ ነክ ጉዳዮች ሁሉ ላይ የዳበረ ስለሚሆን፣ ይህን ከግምት ማስገባት ነው። (1ኛ ቆሮ. 13፡4-8 ይመልከቱ።)

ሁለተኛው፤ የሥጋ አንድነት ለማግባት ዋንኛው ምክንያት ከሆነ፣ የተጫጩ ወይም ለጋብቻ ቅድመ-ዝግጅት የሚያደርጉ ወጣቶች ዘላቂ የትዳር ሕይወታቸውን ከመጀመራቸው በፊት በጾታዊ የመፈላለግ ተራክቦ ላይ የሚግባቡ እንደ ሆነና እንዳልሆነ ከወዲሁ ለማወቅ ሩካቤ ሥጋ መፈጸም የለባቸውም ወይ? የሚል ነው። ጥያቄውን በብቻው አይተን እንመልስ ከተባለ፣ አዎን ተገቢ ነው የሚያሰኝ ምላሽ ላይ እንደርስ ይሆናል። በቅኝት የተሞላው መልስ ግን ይህ አይደለም፤ ያልሆነበትን ምክንያት ልዘርዝር፡-

ሀ. ምርጫችን ትክክለኛውን ወንድ ወይም ሴት መሆኑን ወይም መሆኗን ከወዲሁ ካረጋገጥን፣ በመረጥነው ሰው ሕይወት ውስጥ እርስ በርሳችን ያዋደደን የፍቅር ባሕርይ የማይታገሥ፣ ተስገብጋቢ፣ ተጠራጣሪ፣ ሥርዓተ ቢስ ባለመሆኑ፣ ይኸው ፍቅር ተጋቢዎቹ ሥርዓተ ሕይወትን በቅደም ተከተሉ እንዲያደርጉት ያደርጋቸዋል። በሰዎች ሁሉ ዘንድ እንዲታይ እግዚአብሔር የተወልን የፍቅር ባሕርይ ይህን እንድንሆን ያስገድደናል። ይህም ደንቡ ከጋብቻ በፊት የሥጋ ተራክቦ ዝሙት መሆኑን ያመላክታል።

ለ. እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አሟልተው በተመራረጡ ተጫጪዎች ሕይወት ውስጥ የሥጋ አንድነት በጋብቻ ውስጥ የሚያመጣው ውጤት መልካም ነው (ዘፍጥረት 1፡31)። እግዚአብሔር መልካም፣ መልካም፣ መልካም እያለ አምስት ቀናትን ካሳለፈ በኋላ፣ ሰውን ፈጠረ። እርሱም «እጅግ መልካም» ነበር አለለት። ይህ መልካምነት በጾታዊ መፈላለግና በሥጋ አንድነት ውስጥ የሚገኘውንም ሕይወት ይጨምራል።

ሐ. አንዳንዱ የተዋደዱ ሁሉ አይፋቀሩም፣ የተጫጩም የማይጋቡበት ጊዜ አለ። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የሥጋ ተራክቦ

ጉዳት ሊያስከትል የሚችለው ይህ አጋጣሚ ሊከሠት በመቻሉ ነው። በተለይ ራስን በመቻል ባልተደራጁ ተጫጪዎች ሕይወት ውስጥ ተራክቦው ለችግር የተጋለጠ ልጅን ያመጣል። በሴቲቱ ሕይወት ውስጥም የበታችነትን ስሜት ከወንዱ በበለጠ ይፈጥራል፤ ይልቁኑ፣ ስግብግብ ያልሆነውን ፍቅር ተስገብጋቢ በማድረግ የራስን ፍላጎት ቢያሟሉበት፣ የተዋደዱት ለነገ ያስቀሩት ምንም ነገር ስለማይኖር ተመቺነታቸውን ለማፍረስ ፈጣን ይሆናሉ።

ከእነዚህም በበለጠ፣ እግዚአብሔር ስለ ሰውነታችን እንዲህ አለን፣ «ሰውነታችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በውስጣችሁም የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆኑን ታውቁ የለምን? እንግዲህ እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ እንጂ የራሳችሁ አይደላችሁም...ሰውነታችን ለጌታ ኢየሱስ፣ ጌታ ኢየሱስም ለሰውነታችን ስለሆነ ሰውነታችንን ለዝሙት ማዋል አይገባንም» (1ኛ ቆሮ. 6፡19-13)። ይህ እውነት በሰውነታችን ላይ የእኛ ፈቃድና አሳብ በብቻው ሊሠለጥንበት እንደማይገባ ያስ ረዳናል። በምትኩ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ብልቶቻችን ለተቀደሰና ለንጹሕ ተግባር በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ማዋል ነው።

እንኪያስ እነዚህ ያነሣኋቸው ለመግባባትም ሆነ ለመጣጣም የሥጋ ተራክቦ ከጋብቻ በፊት አጓጉል መሆኑን ያመላክታሉ። ይልቅስ፣ በጋብቻ ጅምር ሕይወት ውስጥ የማያግባባ ችግር ቢከሰት፣ በሁለቱም በኩል በማቆጥቆጥ ላይ ያለውን ያሰማ ጎን ማግባባትን በማሳደግ መርታት ይቻላል።

ሦስተኛው፣ የሥጋ አንድነት በትክክለኛው መስመር በጋብቻ ተ ፈጻሚነት ኖሮት ባልና ሚስት በትዳር ሕይወት እየተመላለሱ በመ-ሐከላቸው አለመግባባት ነግሦ ንትርክና ብጥብጥ፣ ኩርፊያና ዝምታ እየበዛ አንድ አልጋ ላይ አድረው የተለያዩ የሚሆኑበት ጊዜ ቢበዛና የዚህ ችግር ዐቢይ ምክንያት የሥጋ አንድነት አለመግባባት ቢሆን፣ የእነዚህ ተጋቢዎች የወደፊት ተስፋ በእኛነታችን ምክንያት የተ በላሸውን በማረም ችግሩን መርታት ቀዳሚው መፍትሔ ለዚህ አባባል የተጋቡ ሰዎች የሥጋ አንድነትን በተመለከተ የገጠማቸውን ችግር ተብዬዎች ከመፍትሔያቸው ጋር ልጠቁም፦

ሀ. ብዙ ጊዜ የሥጋ አንድነት ከመፈጸሙ በፊት ሊሆኑ

የሚገባቸውን ቅድመ-ዝግጅቶች አለመረዳቱ ችግርን ይጋብዛል። በምሳሌ ላብራራ፣ ድርጊቱ ወደ ጫጉላ ቤት ሚዜዎች ሙሽሮችን ከሸኙ በኋላ የሆነ ነው። ሙሽሪት ወደ መታጠቢያ ቤት ገብታ ትጸዳዳለች፤ በአእምሮዋ «ሕልምና እውን ምን ዓይነት መጣጣም እንዳላቸው እያሰበች፤ ከባልዋ ጋር የሚኖራትን የፍቅር ሕይወት እያሰላች፣ ለድርጊቱም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሊዛመድ የሚችልላትን የከራረሙ ጥቅሶች እየፈተሸች ተውባ እንደ ጨረሰች፡ - ግር ባለ መንፈስ ከመታጠቢያ ክፍሏ ወጣ አለች፤ በተለይ ሙሽራው «ዘገየች» በሚል መንፈስ የድርጊት ሰው ለመሆን ተ መቻችቶ አድፍጧል። ዐይኖቹ እርሷን በመጠበቅ ተግተዋል። እናም እንደ ወጣች ተቀበላት፤ ለእንቅልፉ ደግሞ አልዘገየም፣ አሸለበ፤ እስከ ረፋዱም ተኛ። ይህ ለእርሱ ስግብግብ ስሜቱን ማርካት ቢሆንም፣ ለሙሽሪት ግን «መደፈር» ነበር። የዚህ ዓይነቱ ገጠመኝ በተጋቢዎች መካከል በተደጋጋሚ ሊመጣ ቢችል፣ የሴቲቱ የኋላ ኋ ላ ውስጣዊ ፍላጎቷ መለያየት ሊሆን ይችላል። ለዚህ ግን ጽኑ መፍትሔው መግባባት ብቻ ነው።

በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ትዳርን ለማጣፈጥ ባል ከፍተኛ ድርሻ አለው። ከድርሻው ዋንኛው የሥጋ አንድነት ከመፈጸሙ በፊት ሊሆኑ የሚገባቸውን ቅድመ-ዝግጅቶችን ጠንቅቆ ማወቅ፣ በእርሱም መኖርን መለማመድ፣ ሚስት የስሜት፣ የእውቀት፣ የእምነት፣ ወዘተ...ባለቤት መሆኗን በመረዳት አነሣሽ ተግባሮችን ማስቀደም ወሳኝ ነው። የተፍታታ የመዝናናት ስሜትን በመፍጠር፣ በአካል በመቀራረብ መደናነቅን ማሳደግ፣ ልበ ግብ የፍቅር ቃላትን መጠቀም እና የመሳሰሉትን በማድረግ የእግዚአብሔርን «እጅግ መልካም ነበር» መረዳት መፍትሔ ነው።

ለ. አንዳንዱ የሥጋ አንድነትን በመፈጸም ሂደት ላይ ባሎች ወቅቱ ሳይደርስ ዘርን ለማፍሰስ ይጣደፋሉ። ይህ በወንዶቹ ላይ በተ ደጋጋሚ ሲከሰት፣ በግላዊ ሕይወታቸው ውጣ ውረድን ይፈጥራል፤ ፍርሐት፣ ጭንቀት ወይም ያለመብቃት ክፉ ስሜት ይዘራል።

ይህን ግን፡-

1. ለረኾም ቀናት የሥጋ አንድነት ሳይፈጸም ቆይቶ ሲጀመር፣

ሊከሰት ይችላል።

2. በድንግልና ሕይወት ኑሮውን አሳልፎ ለግንኙነት አዲስ በሆነ ሰው ግንኙነት ላይ ተደጋጋሞ ሊከሰት ይችላል።
3. ለሚስቱ ያለው ታማኝነት በወንጀለኝነት ስሜት የተጠቃበት ለመገናኘት በሞከረ ቁጥር ይህን ዓይነት ችግር ሊገጥመው ይችላል።
4. ሚስትንም በስሜት ተነሣሽነት ቀርፈፍ የምትል መሆኗን ካለማወቅና በተመሳሳይ ሌሎች ምክንያቶች ሊከሰቱ መቻላቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው። ይህ ደግሞ የችግር ተብዬ ሥችን ተቃራኒ በመኖር በአብዛኛው ይስተካከላል።

ከሁሉም ከሁሉም፣ ከምንወዳት ሚስታችን የበለጠ የችግር ተካፋይ ስለማይኖረን፣ ከእርሷ ጋር በመመካከር መፍትሔ ውን በጋራ ማግኘት የመፍትሔ ቁንጮ ነው።

ሐ. በሥጋ አንድነት ዝግጅት ላይ ስንፈተ ወሲብ በወንድ ላይ ሊከሰት ይችላል። ይህ በሴቶችም ሕይወት ውስጥ ይከሰታል፤ ለዚህ ዓይነቱ ችግር ከመነሻ መፍትሔዎቹ በጥቂቱ፦

1. ጥንካሬን በምንመገበው ተመጣጣኝ ምግብ ማደራጀት፣
2. የአልኮል ሱሰኝነት ካለ ከነአካቴው መተው፣
3. የአሳብ ጫናን ቀስ በቀስ ማስወገድ፣
4. የጋብቻ አማካሪዎችንና ባለሙያ ሐኪሞችን ማማከር፣
5. ችግርን አፍኖ ለግንኙነት ፍላጎት እንደሌለው ሰው አለመምሰል፣ ወዘተ...መፍትሔ - ጠሪ ናቸው።

ባል ውጤታማ ሆነም አልሆነም፣ ለእርሱ ያላት ፍቅር ጽኑ መሆኑን በማብሰር ያንንም በተግባር በመግለጽ የመፍትሔ ቀዳሚ መሆን የግድ ነው።

መ. በሥጋ አንድነት ዝግጅትም ሆነ ተግባር ላይ የተሸሸጉ «ስውር ፍርሐቶች» መኖር። ነጥቡን በምሳሌ ላብራራ፦ ወንድየው በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላይ ባለቤቱን ቅር እንደሚያሰኝ ሳያገባትም በፊት ቢያብሰለስል፣ ሴቲቱም ባሌን አላስደስተውም በሚል ሥጋትን በውስጧ ያነገበች ቢሆን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የሚሰሙት፣ የሚያዩት፣ የሚያነብቡት ግነትን የተሞሉ

መሆናቸውን ባለመረዳት እነዚህኑ «አሜን» ብሎ መቀበል ችግርን ጋባኝ ነው። መፍትሔው እግዚአብሔር ይህን አጓጉል ከመነሻው አለመፍጠሩን በመፍትሔ የተፈጠሩ ሥጋቶችን በማውጣት ያለመታሰቢያ ማስቀረት ተገቢ ነው።

ሠ. በሥጋ አንድነት ጊዜ የተረጋጋ ስፍራና ሁኔታ ማጣት በባልና ሚስት ሕይወት ውስጥ ምቾቶችን ባለማምጣት ችግር ሊያመጣ ይችላል። ይህም በድግግም በተጋቢዎች ሕይወት ውስጥ ሊከሰት ይችላል። ለዚህ መፍትሔው ባልና ሚስቱ ችሎታቸውን ተጠቅመው ስፍራውንና ሁኔታውን በማመቻቸት ችግሩን ማቅለል ነው።

ማጠቃለያ፡-

ችግሮች እነዚህ ብቻ አይደሉም፣ ሞልተዋል፤ ዳሩ ግን ተጫጪ ዎችም ሆኑ ባለ ትዳሮች የሥጋ አንድነት ወቅት አንጣጣም ይሆናል ወይም አልተጣጣምንምና ከወዲሁ እንለያይ ወይም እንፋታ ሊሉ አለመቻላቸውን መረዳት ተገቢ ነው። እግዚአብሔር እኮ! አንድ ያደረገውን ችግር ሊለየው አይገባም፤ ተጫጪዎችም ሆኑ ባልና ሚስት ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን እንዳለ ነው፡- «ልባችንን በሰፊው ከፍተን ስሜታችንን እንደ ገለጥንላችሁ እናንተ ም ልባችሁን ከፍታችሁ ስሜታችሁን ግለጡልን» (2ኛ ቆሮ. 6፡13)። ይህ አካሄድ ከጋብቻ በፊትም ሆነ በ ኋላ ግልጽነት በመንፈሳዊ፣ በአእምሮአዊ፣ ማኅበራዊ፣ በአካላዊና በስሜታዊ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ሁለቱ ልባቸውን አስፍተው ሊተዋወቁ ይገባል።

የሠርጋችን ክቡር እሴቶች እና «አይረቤ» ባህሎች

ሠርግን ሳስብ አገሬን አስታውሳለሁ፣ በአግባቡ ለመረዳት አዲስ አበባን እጠራለሁ። አዲስ አበባን ያስመኘኝ ሁነኛ ናሙና መሆን ስለምትችል ነው። ለዚህ ደግሞ ዋቢዬ ሀዲስ አለማየሁ ናቸው። በታዋቂው መጽሐፋቸው «ወንጀለኛው ዳኛ» የአዲስ አበባ መገለጫ

የሆነችውን አዲስ ከተማን እንዲህ ይገልጿታል፡፡

«አንዳንድ ተመልካቾች» አዲስ ከተማ የኢትዮጵያ ናሙና ናት የሚሉት ስሕተት አይደለም፡፡ አዲስ ከተማ ትንሽ ኢትዮጵያ ናት/ አዲስ ከተማ በልዩ ልዩ የኢትዮጵያዊ ክፍሎች የተፈጠረው፣ የተሠራውና የተፈራው ሁሉ፣ ማለት ሰዉ፣ ሀብቱ፣ ባህሉ፣ ሥርዓቱ፣ ቋንቋው፣ እምነቱ፣ ይህ ሁሉ ባንድ ላይ የሚታይባት ትንሽ ኢትዮጵያ ናት/ አዲስ ከተማ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ሸቀጦች፣ ቤተ ክርስቲያኑ ከቤተ መስጊዱ፣ ቂሱ ከሼኩ፣ ክርስቲያኑ ከእስላሙ፣ ይሁዲው ካረመኔው ጋር ባንድ ላይ የሚታዩባት ትንሽ ኢትዮጵያ ናት/ አዲስ ከተማ መንዜው ከነባናው፣ ጅሜው ከነቡናው፣ ዶርዜው ከነሸማው፣ ከፊው ከነበርጩማው፣ አዲሱ ከነጨቤው፣ አፍሲው ከነቅቤው፣ ወለጌው ከነብረቱ፣ ጉራጌው ከነእንሰቱ፣ ጎጃሜው ከነማሩ፣ ትግሬው ከነክራሩ፣ ሌላውም ሁሉ እንዲሁ ለትርዕይት እንደ ተደራጀ በጥቂት በጥቂት እየተቆነጠረ ተመጥኖ የሚታይባት፣ ትንሽ ኢትዮጵያ ናት::

ከአገባባቸሁ አንቀጽ ላይ በቀዳሚነት «...በልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍል የተፈጠረ ሁሉ የሚገኝባት፣ ጥንታዊው ከዘመናዊው ጋር ጎን ለጎን የሚታይባት፣ ሁሉ ብሔረሰብ ከቋንቋውና ከባህሉ ጋር የሚተምባት፣» የሚሉትን በሦስት እምቅ ሐረጎች በመውሰድ ስለ ሠርግ ጉዳይ እናንብብ፡፡

የእኛ ብቻ ነው ያልነው ባህላዊ ሥሪት፣ አፍሪካዊ ሆኖ፣ የአፍሪካውያን ያልነው፣ ከሌላው አኅጉር የእነርሱም የሆነው ከሌላው ዘንድ ተገኝቶ የሁሉ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ አይሆንም አይሉበትም፣ ሊሆን ይችላልና፣ ለዚህ መዘክሬ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ኩሬያዊ ሳይሆን፣ ወንዛዊ መሆኑ ነው፡፡

ኩሬ ባለበት እንቅስቃሴ የለም፣ ኩሬ ተሻግሮ አያረግፍም፣ ተጓዥ የሆነው ወንዝ ግን ይንቀሳቀሳል፤ ሁሌም ስፍራውን ትቶ ይጓዛል፣ በሄደ ቁጥር ይዞት የመጣውን ውኃና አፈር ለሌላ እየገበ

ረ የሌላውን እየያዘ ይዘልቃል፣ ከዚህም የተነሣ መንቀሳቀስ ሀብቱ ነው። የሰውም ልጅ ታሪክ እንዲሁ ነው፤ በተለያዩ ሰዋዊና ተ ፈጥሮአዊ ምክንያቶች ሁላችንም እንቀሳቀሳለን። በእንቅስቃሴያችን ባህላችንን፣ ቋንቋችንን እና እምነታችንን ከሌላው ጋር እናነካካለን። የሠርግ ርእሳችንም እንዲሁ ነው።

* * *

መወራረስ እና መቀባበል የዓለሙ ሁሉ ቢሆንም፣ በየፊናችን በወረስነውና በተቀበልነው ውስጥ «የራሳችን ብቻ የምንለው አለን፤ እርሱም ሠርግ እና ሥርዓቱ ነው። በትርጉሙ፣ «ሊጋቡ ያሉ የተ ቃራኒ ጾታ ጉብሎች አንድ መሆናቸውን ለማኅበረሰቡ እወቁልን የሚሉበት የደስታ ቀን ሠርግ ተብሎ ይጠራል።» የደስታ ሰሞን በተባለው ሠርግ ውስጥ ደግሞ ሠርግን ያጀቡት ከባቢዎች አሉ። እንደ ባህሉ ልዩነት ቢኖርም። ሽማግሌ ወደ ወላጆቿ መላክ፣ ለጥየቃው የምላሽ ዝግጅት፣ ለልጅቱ እና ለወላጆቿ ስጦታ የማበርከቻ የጥሎሽ ቀን፣ ዕለተ ሠርጉ፣ የምሥራች የመባያ ማግስት፣ መልስ በእናት በአባቷ ቤት፣ የሁለት ተጋቢዎች የቤተ ሰብ የመቀላቀያ ቀን፣ ወዘተ...ተደማምረው ሠርግን ያሳድጉታል። ከዚህም የተነሣ፣ እነዚህን መጠቋቆም ይኖርብናል።

መቼም ቢሆን የውበት መነሻ እግዚአብሔር ነው። ከጠዋቱ ከመነሻው፣ የሰው ጅማሬ በሆኑት በአዳምና ሔዋን ሕይወት ውስጥ፣ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ይጣበቃል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ»ን በሰው ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር በጋብቻ አንድነት ጀመረው፣ ይህንንም አዘለቀው፣ ሲያዘልቀውም መዋለድን (ዘፍጥ. 1:27)፤ ኅብረትን (ዘፍጥ. 2:18)፣ ጾታዊ እርካታን (ዕብ. 13:4) በውስጡ አስቀመጠ፤ ይህ አንድ ሥጋ የሚያደርገው የጥምረት ታሪክ በጊዜ ውስጥ አጃቢዎችን አስከትሎ ማኅበራዊ ገጽታ እንዲኖረው ሠርግ የሰው ሥራ ሆኖ ተበጀለት።

በአገራችን ሠርግ ውበት አለው። እኔ ውበት ከምልለት ከሦስቱ አንደኛው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እየዘቀጠ፣ ኅብረተሰቡ ምሳሌነት ለኅደለው አኗኗር ራሱን እየሰጠ ባለበት ዘመን ውስጥ ያለን ይመስለኛል። መጋባት መውለድ፣ ልጆችን ማሳደግና ቤተ ሰብን መንከባከብ በብዙዎች ዘንድ ተራ እና ኋላ ቀር አመለካከት

የሆኑ ያህል በሕዝቡ ዘንድ አድረዋል። ከዚህም የተነሣ፣ የመገናኛ ብዙሀን እያደረሱልን ያሉላቸው ማስታወቂያዎች ሰዎች ተጋብተው በመኖር ጤናማ ሕይወትን በትዳር በመምራት ማጠንከር ሳይሆን፣ «ኮንዶምን» በመጠቀም ሁሉም ከሁሉ ጋር እንዲሄድ፣ እንዲዳራና እንዲዘሙት እያግባቡት ይመስለኛል። ይህ አካሄድ ደግሞ የእግዚአብሔር አሳብ የሆነውን የጋብቻ መንገድ ይጻረራል። አንዳንድ ደራሲያንም በየድርሰቶቻቸው ሊገልጹት የሚወዱት በጋብቻ መጽናትን «ፋሽኑ ያለፈበት» ሕይወት አድርገው ነው። እስቲ በሀዲስ የተሰኘው ልብ ወለድ በገጸ ባሕርያቱ ተጠቅሞ ያስተላለፈውን መልእክት እናጢነው፦

> «ወተት ለሰውነት ይጠቅማል፣ ይጠቅማልና ሁሉም ይፈልገዋል። የፈለገው ደግሞ ክፍያውን ይቻለው እንጂ በየወተት ማደያው፣ በየሱቁም ይሸምተዋል። አንዳንዶች ግን እንዲህ በቀላሉ ማግኘት ሲችሉ፣ ላም በቤታቸው አኑረው ከእርሷው ጋር ሲታገሉ ይገኛሉ። ቀለሟን ያዘጋጃሉ፣ እየቀለቡም ወተቷን ይጠብቃሉ፤ ከእርሷው ጋር ደፋ ቀና ይላሉ፣»

ካለ በኋላ የንጽጽሩ መቋጫ ጋብቻን ማርከስ ነው። ወንድ ሁሉ የሚያረኩ ለዓይን የሚያጓጉ ሴቶች ከከተማ ሞልተውለት ሳሉ ለምን ይሆን በቤቱ ከአንዲት ሴት ጋር የሚሰላች በማለት ላሚቱን ከሴቲቱ ጋር በማስተያየት ይኮንናል። ይህ አካሄድ በእግዚአብሔር የተዋቀረውን ጋብቻ የማውረድ ጥረት ነው። ለዚህ ጥረት ተገዳዳሪ የሚሆን መፍትሔአዊ አካሄድ ሠርግን በመሠረግ ማሳየት ነው። ሠርግ በሰው የተበጀ ሥርዓትም ቢሆን፣ የጋብቻን ክቡርነት፣ የቤተ ሰብን ታላቅነት በማወጅ ሁሌ ያገለግላል። ለኢትዮጵያውያን ይህ ውበት ነው።

ሁለተኛው ጋብቻን የቀደሱ ለመምሰል ያለጋብቻ በመኖር ብህትውናን (ብቸኝነትን) የሚያስፋፉትን በመውቀስ ውበትን ማጉላት ነው። የአዲስ ኪዳን አስተምህሮን በመታዘዝ የዘለቁትን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ለመቃወምና፣ ለስደት ለማብቃት «ስመ ክርስቲያን» የሆኑ ግለሰቦችና «ቤተ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች» ከቤተ ክርስቲያን ምሥረታ በኋላ ብዙ ጥፋትን በዓለም ላይ እንዳደረሱ

ታሪክ ይዘክራል። ብዙዎች መነሻችን ነው የሚሉት «... ስለ ጻፋችሁት ጥያቄ ሰው ከሴት ጋር በግብረ ሥጋ ባይገናኝ ወይም ሚስት ባያገባ መልካም ነው» የሚለው 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡1 ቅዱስ የጳውሎስ ምላሽ እና በራሱ የመሰከረው፣ «...ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሚስት ሳያገባ ቢኖር በወደድሁ ነበር» (ቁጥር 7) የሚለውን መልእክት ዐውዳዊ ፍቺ ባለመስጠት፣ «አለማግባትን የቅድስና ጎዳና! አለማግባትን ለመንግሥተ ሰማይ የመግቢያ ቅድሚያ ቀብድ በማድረግ ያስተምራሉ፣ ያውጃሉ። ብዙዎቹ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያናት ጳጳሳትና ቀሳውስቱ ያገቡ ዘንድ አይፈቅዱም፤ የግሪክ ካቶሊካውያኑ ደግሞ ለቀሳውስቱ ፈቅደው ለጳጳሳቱና ለፓትርያርኩ ከልካይ ናቸው። ይህ አካሄድ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፡-

በ270 ዓ.ም. አንቶኒ የብሕትውና ኑሮን በመጀመር፣

በ358 ዓ.ም. ባዝል የገዳምን ማኅበረሰብ በማጠናከር፣

በ540 ዓ.ም. ቤነዲክት የገዳምን አኗኗርንና ሕግን በመጻፍ በየጊዜው ብቻ መኖርን፣ ጋብቻን መኮነንና ዓለማዊ ገጽታ እንዲኖረው በማድረግ መስፋፋቱ በኢትዮጵያም አድጓል። ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አስተምህሮ ሊንደው የሚችል ጠቋሚ ሠርግ ነው። ሠርግ ባለበት የእግዚአብሔር የመጋባት ድንጋጌ እየተደጋገመ ይታወሳል፤ ባለማግባት ጎሊናቸው የታጠረ፣ እያገቡ ባሉት ተሠራጊዎች ይረታሉ፣ ይህ ሁለተኛው ውበት ነው።

ሦስተኛው የሠርግ ውበቱ ሁሉን በሥርዓቱ ላይ ማሰባሰቡ ነው፣ አገራችን የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ምድር ናት፣ ሁሉ እርስ በርስ ተሣሥሮ በፍቅር እንደሚኖርባት የሚረጋገጥበት ትክክለኛ መግለጫ ሠርግ ነው። የሠርግ ታዳሚዎች፡- የተጋቢዎች፣ የወላጆች፣ የዘመድ አዝማድ፣ የጎረቤቶች፣ ሁሉ ተጠሪ ናቸው። ተከብረው ተጠርተዋልና፣ ሁሉም አክብረው ይገኛሉ። በዚያም ተገኝተው ልዩነታቸውን ሳይሆን፣ አንድነታቸውን ይገልጹበታል። ሀዲስ ዓለማየሁ ስለ አዲስ ከተማ ናሙናነት እንደ ገለጹት፣ ሠርግም በናሙናነቱ አዋጅ ይላል። ለዚህ ሁነኛው ምሳሌ ባህላዊ በሆኑት የሠርግ ዘፈኖቻችን ላይ የሚታየው የመርገፍገፍ እንቅስቃሴ ነው፡- የአማርኛው፣ የትግርኛው፣ የኦሮምኛው፣ የጉራጊኛው፣ ወዘተ...ይዘፈናል፣ ለአማርኛው ዘፈን ሁሉ ተሳትፎ

ለኦሮምኛው፣ ሁሉም ይሳተፉሉ። አማራው የጉራጌውን ግራ ቀኝ ሲያሳምር፣ ጉራጌው የአማራውን እስክስታ እንደ ልቡ ያደርሰዋል፣ «ሁሉ የሁሉ» ይህ የሠርግ ሌላኛው ውበቱ ነው።

አስከትለን ደግሞ ሁሉ ነገር የራሱ የሆነ በጎ ጎን እንዳለው ሁሉ፣ አይረቤ የሚባሉለት ግርዶችም አሉበት። እናም ግርድ ብዬ የማምንባቸውን የሠርግ ምልከታ አራት ያህሉን በመጠኑ ላስከትል።

አንደኛው፣ «እባብ ግደል፣ ከነበትሩ ወደ ገደል» የሚል ምሳሌ አለን፣ እባቡ መወገድ አለበትና ገደል ይጣል፤ በትሩ ግን ማን ያውቃል ሌላኛውም እባብ ይመጣ ይሆናልና ለመከላከል እንዲችሉ ከእጅ ባይለይ ይሻላል። ልክ እንዲሁ፣ መጋባት በታወጀበት ከመጋባት እበልጣለሁ የሚል ሌላ አጃቢ ካለ አጃቢውን ለብቻው ነጥሎ ዋንኛውን መጠበቅ ተገቢ ነው። መጋባትን እግዚአብሔር የሠርግ ጣጣ ሳይፈጠር፣ ኃጢአት ወደ ዓለም ሳይገባ፣ አስቀድሞ ደነገገው፣ ይህንኑም ፈጸመው፣ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን የደረሱ፣ ደርሰውም ተጋብተው ለመኖር የሚያስችል መጠንና ዝግጅቶች ያሏቸው ተፈቃሪዎችስ ይጋቡ ዘንድ ከሰማይ መልእክት ለሰዎች ደረሰ። ያንን በመታዘዝ በተፈጸመም ጊዜ መጋባት እውን ሆነ። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ውሳኔ ነው። ይህ ውሳኔ በተጋቢዎቹ ዘንድ እውን እንዳይሆን አንዳንዱ ሠርግ አጥር በመሆን አስችግሯል።

«ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ፣» የሚለው ምሳሌያዊ አባባል ሁሉም ድሆች በሆኑበት ማኅበረሰብ ውስጥ ፈጽሞ አይሠራም፤ ጥቂቶች ሰማየ ሰማያትን አቋርጠው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ሊደርሱ እንደሚችሉ በማመን፣ ስለ ጽድቃቸውም ጭምር በገንዘብ ላይ ሊደገፉ የሚችሉ ሊኖሩ ቢችሉም፣ ኢትዮጵያ ግን በዓለም ውስጥ ካሉት አገሮች ውስጥ በድህነት ደረጃ የመጨረሻውን ተርታ ከያዙት ውስጥ አንደኛዋ አገር ነች። በተጋቢዎች ሕይወት ውስጥ ጥሎሽ፣ ሠርግ፣ መልስ፣ ወዘተ...ገንዘብ-ነክ ዝግጅቶች ሆነው በሠርግ ባህላዊ አካሄድ ውስጥ ይካተታሉ። መሠረታዊ የሕልውና ጉዳዮችን ለሚሟላት በምንጥርበት ሕይወት ውስጥ ቢቀርም፣ ለክፉ

የማይሰጥ በጎ ነገር ውስጥ ሠርግ አንዱ ነው።

ሁለተኛው አይረቤ፣ «ካልተሳፈሩበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ፣ ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ፣» የሚለው ዕምቅ ስንኝ ነው። እርግጥ፣ የዘንድሮዎቹ የአዲስ አበባ ታክሲዎች የጊዜ ክቡርነትን ሊገልጽ ያለውን ይህን የስንኝ ቋጠሮ እያፈረሱ እንዳለ ይገመታል፤ ቢሆንም፣ በጥንቱ አካሄድ የአባባሉን ዋና ነጥብ በብቻው አንሥተን ለአሠራረጋችን እናውለው፣ «ዘመኑን ዋጁት...» የአዲስ ኪዳን መልእክት ነው፣ ጥቅሱ ጊዜውን በመጠቀም፣ ለእግዚአብሔር ክብር እንድናውለው ያሳስበናል። እግዚአብሔር በእድሜያችን ላይ የሚያክላቸው ሰኮንዶች ሁሉ ለበጎ ግልጋሎት ይውሉ ዘንድ ይገባል፣ ሠርግ ሁለቱ ተሞሻሪዎች የሚያደምቁት ሥርዓት አይደለም፤ ሕዝብ እንጂ፤ ያ ሕዝብ ደግሞ ታዳሚ ሆኖ ለሠርጉ በተጠራ ጊዜ የሚጠበቅበት አብሮ መሆን ነው። አጃቢ ከሆነ መዋል፣ ካልሆነ ደግሞ የቀን እኩሌታውን አብሮ ማሳለፍ ይጠበቅበታል። በዚህ ቀን የሚባክነውን ጊዜ ለመጠቀም ትንሽ ምሳሌ ላንሣ። ሠርገኞች አምስት መቶ ሰው ጠሩ እንበል፤ ከዚህ ውስጥ 75 አጃቢ የሙሉ ቀን ዋይ ሆኖ 425ቱ ለቀን እኩሌታ የተ ሰበሰበ ይሁን። አንድ አጃቢ «ዘጥ ዘጥ» እያለ ለ10 ሰዓት ቢቆጠሩ 75ቱ በእያንዳንዳቸው በ10 ተባዝቶ 750 ሰዓት፤ 425 ለቀን እኩሌታ ያልንለትን ለአምስት ሰዓታት እንደሚዘገዩ ብንቆጥር፤ አጠቃላይ ብዜቱ 2125 ሰዓታት ይደርሳል፤ ይህ ከአጃቢዎቹ 750 ጋር ሲደመር፣ 2875 ሰዓቶች ሙጥጥ ብለው አልቀዋል። እነዚህ ሰዓቶች ወደ ሥራ ቢቀየሩስ? ወደ ንባብ ቢለወጡስ? ምን «ተአምር» ይሆን ነበር። ይህ ሲታሰብ የሰርግ ሌላው ግርድ የጊዜ ብክነቱ ነው።

ሦስተኛው አይረቤ ነጥብ፣ «የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል» የሚለውን አባባል ያስታውሰኛል። «አንተ ዝጋ፣ አንቺ ዝጊ» በሚል ሙግት የተተወ በር ቀማኛ ማስጎብኘቱ አይቀሬ ነው። ፉክክር በጤናማ አካሄድ ለበጎ ውጤት ተፈላጊ ማኅበራዊ ክስተት ነው፣ «የፉክክር ቤት...» ብሒሉ ግን ለቸልተኝነት፣ ለስንፍና፣ ለግድየለሽነት እና አርቆ ላለማየት የተደረገ ፉክክር ስለሆነ፣ ለጉዳት ሳይጥል አይቀርም። መማር የአስተሳሰብ ለውጥ በማስከተል በድርጊቶቻችን ላይ መገለጹ እውን የሚሆነው፣ እያንዳንዳችን ስለ

ሌሎች ሳይሆን፣ የእኔነታችን መኖር ስንችል ነው። ሠርግና ተ ሠራጊዎቹ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከልጅነት እድሜ ጀምሮ በዓይናችንም ሆነ በሕሊናችን ሲጓዝ የከረመው «እኔም ልፈጽመው» ወደ መጓዝ ጥፋትን በውስጡ በማዘሉ አደጋ አለው፤ የአደጋው የመነሻ ዋንኛ ጎዳና ፉክክሩ ነው። በአውሮፓና በአሜሪካ ሠርግና ተ ሠራጊ ሠርግን ሲያስቡ፣ የወዳጆች የአጭር ጊዜ መገናኛ ነው። በኢትዮጵያ ግን እንዲህ አይደለም፤ ሙሽሪት የወደፊት የሠርግ ዝግጅቷን የምትጀምረው በ10 ዓመት እድሜዋ ነው፣ (ይህ የእኔ ግምት ነው) በዓይነ ሕሊናዋ እየሳለች፣ ለእውነተኛው የሠርግ ዋዜ ማ እስክትደርስ ምላሷን ታገዝፈዋለች። ከዚህ በፊትም ያልነበ ረ ወደፊትም የማይሆን ሠርግ ታደራጃለች። ይህ አደረጃጀት በፉክክር ውስጥ ሾልኮ የወጣ ነውና ሁሌ አለመርካትን፣ አለመሳካትን ይጋብዛል፣ ጌታ (ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው ተ ሣነው) እንዳለው ዓይነት ቤተ ሠሪ ወደ መሆን ትመጣለች። ይህም ሌላው ግርዱ ነው። በአይረቤነቱ፣ ራስን አለመሆንን በማሳደግ ላይ ሊገነባ ያለ ሠርግ ቢቀርም ጉዳት የለውም።

አራተኛው፣ ከመጽሐፉ ቅዱስ የወጣ ድርጊት ሁሉ ሊታሰብበት ይገባል። ጸሐፊው ሉቃስ በቤሪያ ስላሉት ሲናገር፣ «በተሰሎንቄ ካሉት ይልቅ ቅን አመለካከት ያላቸው ነበሩ፣ ቃሉን በታላቅ ደስታ ተቀበሉ፣ የቃሉንም እውነተኛነት ለማረጋገጥ በየቀኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይመረምሩ ነበር» (ሐዋ. 17:11) ይላል። እናም አሁንም ግርድ ያልኩትን የመጨረሻ ገጠመኝ «ሠርግ ለማን አስፈለገ?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፣ በተለይ ጥሎሽን በመዘርዘር ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ያስተ ዋወቀው የዲና ክብረ ንጽሕና በተወሰደ ጊዜ ወሳጁ ክፍል ማጨያ ለማቅረብ መፈለጉን ይገልጻል። በዘዳግም 22:13-29 ደግሞ ያገባትን ሴት ድንግል አልነበረችም ብሎ አግቢው ቢከስ፣ ነገሩ እንዲጣራ ይደረጋል፤ እውነት ሆኖ ቢገኝ፣ ልጅቱ በአባቷ ቤት ሳለች አመንዝራለችና ትወገራለች። ይህ ባይሆን ግን፣ ወላጆቿ የድንግልና ምልክት የሆነውን የደም ጨርቅ ወስደው ለአገር ሽማግሌዎች ካሳዩ ሰውየው ይቀጣል፤ ለብላቴናዋም አባት አንድ መቶ ሰቅል ብር በጥሎሽ ይከፍላል። ሕይወቱ እስካለም ድረስ አይፈታትም።

በዚህም አካሄድ ድንግልና ዋጋ ያለው ጉዳይ መሆኑ ተጠቆመ፤ በ1ኛ ሳሙኤል 18፡12-27 ዳዊት የሳኦልን ልጅ እንዲያገባ ሲሆን የተጠየቀው የጫማ የጥሎሽ ንብረት ነበር። ጥሎሽ በብሉይ ኪዳን ለአባትና ለወንድሞች ይሰጣል፤ ይህም ልጂቱን በክብር ስለ መጠበቃቸው የምስጋና ስጦታ ነው። ከዚህ ፍንጭ በመነሣት ጥሎሽ ሊሆን የሚገባው ልጅቱ ድንግል ከመሆኗ የተነሣ ለእርሷና ለአሳዳጊዎቿ የሚቀርብ ገጸ በረከት ነው። ከዚህ ድንበር ያለፈ ጥሎሽ ሁሉ ልከኝነት አጠያያቂ ነው። አዲስ ኪዳን ጥሎሽን በተ መለከተ የከፈተልን ምንም ቀዳዳ የለም። ጥሎሽ በአዲስ ኪዳን ይኑር ቢባል ሊሆን የሚችለው በሕይወት ዘመን ሁሉ ሊገለጽ የተ ገባው «ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደደ» ባልም ሚስቱን በመውደድ የፍቅር ጥሎሽን እድሜ ልኩን ራሱን ማቅረብ ብቻ ነው። እንዲህ ከሆነ፣ የዘንድሮው ጥሎሽ ሰው በገዛ እጁ ከትከሻው ያዋለው የገዛ ሸክሙ ነው ማለት ነው።

ሁለተኛው፣ *ሠርግን ለትዳር ትልቁ ዋስትና እንዲሆን በመቁጠር መሠረግን* በብቻው የመምረጡ ጣጣ ነው። በአንድ ወቅት በሕይወት መጽሔት ላይ የተግባቡት ሁለቱ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ተሠረጉ። ዓለሙ ሁሉ ባልና ሚስት በማለት በዓይኑ ፈርሞላቸው ተለየ፣ ማታ ላይ ግን የጫጉላ ቤቷን በአካል አንድነት ሳይሆን ተፋጥጠው በማደር አነጉ፣ እንዲህ የመሆኑ ምሥጢር ወንድየው በአንድ ወቅት በመኪና አደጋ የወንድነት አቅሙ ከጥቅም ውጭ ሆኖ ነበር። ይህን በትውውቅ ዘመናቸው አልነገራትም፣ የፈለገው «አገባ» መባል ብቻን ነበር። በኢሳይያስ 4፡1 «ሰባት ሴቶች አንዱን ወንድ ይዘው ለምግብ ሆነ፣ ለልብስ፣ ራሳችንን ችለን እንተዳደራለን ባል የላቸውም ተብለን ከመሰደብ እንድንድን የአንተ ሚስቶች ተብለን እንድንጠራ ብቻ ፍቀድልን» ብለው ይለምኑታል ይላል ለመባል ያህል ብቻ።

መጽሐፍ ቅዱስ የባልና ሚስትን የተሣሠረ መቋጫ ያደረገው ሁለት የተዋደዱ፣ የተዋወቁ፣ በነገር ሁሉ የተስማሙ፣ ተጫጭተ ው፣ ለሥጋ አንድነት ሲበቁ መጋባት እውን ይሆናል። እርግጥ ነው፣ መተዋወቅ፣ መተጫጨት፣ በአደባባይ የሚታይ እንቅስቃሴ ስለሆነ፣ ተጋብተናል ባይሉንም፣ የሚዋደዱ ናቸው ወይም ሳይተ

ሳሰቡ አይቀሩም የሚለው የኅብረተሰቡ ለእውነት የሚጠጋ ግምት አለ። ይህ ግምት በእርግጠኝነት የሚቋጨው እግዚአብሔር ብቻ ተመልካች የሚሆንበት የሥጋ አንድነት ሲፈጸም ነው። ይህ ድርጊት፣ ፊሽካ ነፊዎች በሚገኙበት የጅምሩ አካሄድ አይከወንም፣ የሁለቱ ተፈቃሪዎች እግዚአብሔርን በማክበር፣ ለወገኖቻቸው በመጠንቀቅ፣ መልካም ምስክርነት በተላበሰ አካሄድ በራሳቸው የሚፈጽሙት ነው (ዘፍጥ. 2፡24፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡9-36)። ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን ይህንኑ ያጸናሉ። ይህ እንግዲህ ሰዋዊ የሆነውን የሠርግ ሥነ ሥርዓትን በመጠቀም መፈጸም፣ አልያም ያለ ሠርግ በመፈጸም ትዳርን በሠመረ መልኩ ማደራጀት ይቻላል። የሠርግ አይረቡ-ግርዱ ሠርጉ በራሱ ጋብቻ መስሎ መገኘቱ ነው። ይህም «ከፈረሱ በፊት ጋሪው» እንደ ተገሸረ ያስቆጥረዋል። እንግዲህ አትርሱ፣ ለውሸቱ ሦስት መረጃ፤ ለግርድ አራት ምስክር መጥራቱን ልብ በሉ!

ማጠቃለያ

«የሠርጋችን ክቡር እሴቶች እና አይረቤ ባህሎች» ሁላችን የኅብረተሰቡ አባላት ስለሆንን፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይመለከተናል። ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን፣ የራሳቸውን ደሴት ፈጥረው ከሌላው ሕዝብ ተለያይተው መኖር እንችላለን ቢሉ፡- ከከፋ ድጥ ላይ ይወድቃሉ። ይልቁኑ፣ ጌታ እንዲህ አለን፣ «ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም ውጪ እንድትወስዳቸው አልለምንህም...አንተ እኔን ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እኔም እነርሱን ወደ ዓለም ላክኋቸው...» (ዮሐንስ 17፡16-18)። ይህ መመሪያችን ነው፤ ካመኑት እና ከማያምኑት ጋር በአንድ ላይ እንድንኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ በዚያ የጨለማውን ሥራ በመግለጽ የብርሃን ልጅነታችንን ማወጅና የክርስቶስን ታላቅ የደኅንነት ሥራ መግለጥ ተገቢ ነው። «ከባህላችን በላይ ሊገኝ የሚገባው የእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ ብቻ ነው፣ እርሱ በማያሻማ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተገልጿል።»

በጎ ባህላዊ እሴቶችን ከኑሮአችን ጋር በማጣጣም፣ አፈንጋጭ የሆኑትን በቃሉ ማለዘብ፣ እና መቃወም በጌታ በመሆናችን የተሰጠን የዘወትር ሥራ ነው። ሐዋርያቱ እንዲህ አሉ፣ «ለሰው ከመታዘዝ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል» (ሐዋ. 5፡29)።

የጠንካራ ማኅበረሰብ መለኪያ

«አባዬ፣ እኛ በሥላሴዎች እናምናለን?»

«አዎን፣ አቡሽ፣ ግን ለምን ጠየቅኸኝ?»

«ት/ቤት ጓደኛዬ በሥላሴ አታምኑም ሲለኝ ጊዜ ነው።...ግን አባባ፣ ሥላሴ ምን ማለት ነው?»

«ሥላሴ....በአካል ሦስት፣ በመለኮት አንድ ወይም...ማለት ነው።»

«አልገባኝም፣ አባብዬ፣ በደንብ አስረዳኝና ሄጄ ልንገረው።»

«አቡሽ፣ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት አስተማሪ ያስተምርሃል... እርሱን ጠይቀው።»

* * *

«እማማ፣ አንቺ የወለድሽን ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን?»

«አዎ፣ ሁላችሁም የጌታ ልጆች ናችሁ።»

«ግን እንዴት ነው መሆን የቻልነው?»

«ከእኛ ጋር ትጸልያላችሁ፣ ትዘምራላችሁ. . .በቃ።»

«ታዲያ ኃጢአተኛነታችሁን ተረድታችሁ ንስሐ ስትገቡ እግዚአብሔር ልጆቹ ያደርጋችኋል ለምን አለ?»

«ምን አውቃለሁ. . .»

* * *

ለጠንካራ ቤተ ክርስቲያን አንዱ መለኪያው ልጆችን በእግዚአብሔር ቃልና በመልካም ምሳሌነት ማሳደግ መቻል ነው። ቤተ ክርስቲያን ለሕፃናት፣ ለልጆችና ለወጣቶች ከምትሰጠው ዘላቂ ዕቅድ፣ ጥንካሬዋ ሊበሰር ይችላል።

በተመሳሳይ ግን፣ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ተጠቃሚ ሕፃናት፣ ልጆችና ወጣቶች መንፈሳዊ ትምህርትን በሳምንት ውስጥ ካሉት ቀናት በአንዲቱ፣ ከዚያም ደግሞ በተወሰኑት የሰዓት ዝግጅቶች ላይ ብቻ ተወስነው ይማራሉ። ታዲያ ከተቀሩት በርካታ ቀናት ለሕፃናቱ ማን አለን ከተባለ፣ ወላጆች ከተባለ ትክክለኛ መልስ ነው።

* * *

ሁሉን አዋቂው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሰንበት አስተማሪው፣ ለወጣቶች አስተባባሪ፣ ወይም ለሌላ ኃላፊነቱን ሳይሰጥ፣ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ልጆችን እንደ ጌታ አሳብና ፍላጎት፣ እንደ እርሱ ምኞት እንዲያሳድጓቸው ወላጆችን አዘዛቸው? (ዘዳግ. 6፡6-7፤ ኤፌ. 6፡4) እንዲህ ከሆነ፣ የአቡሽ አባት እና የሚሚ እናት ለተጠየቁት ጥያቄዎች የመመለስ ወይም የመገኘት ኃላፊነት ነበረባቸው።

ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው በሳል ጥያቄ እንደሚጠይቋቸው ባለማወቅ፣ ወይም በልጅነት ዕድሜያቸው ልጆች የጌታን ነገር ማስተዋል እንደሚኖርባቸው ባለመገንዘብ ወይም እንደ «ማሚ» የጌታን አሳብ በትክክል ባለመረዳት ወይም ባለመኖር የልጅና የወላጆች ግንኙነት በርቀት ይሆናል።

* * *

ልጆች የቤተ ክርስቲያናት ደጃፍ ከመርገጣቸው በፊት ባሉት ዓመታት ከመወለድ እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ቅርባቸው እናታቸውና አባታቸው ናቸው። ብዙ የሕፃናትን አስተዳደግ ያጠኑ ጠበብቶች የጥናታቸው መደምደሚያ «በዚህ የዕድሜ ክልል በልጆች ሕይወት ውስጥ ወላጆች የሚያሳድሩት ገንቢም ሆነ አፍራሽ ተጽዕኖ በዘላቂ ሕይወታቸው ያንኑ ተከትሎ ይዘልቃል» ይላሉ። አባባላቸው፣ «ልጅን በሚሄድበት *መንገድ* ምራው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ከዚያ ፈቀቅ አይልም» (ምሳሌ 22፡6) ከሚለው *ጋር* ይስማማል። ወላጆች በልጆቻቸው ሕይወት ውስጥ በቂ የግንባታ *ሥራ* ከመጀመራቸው በፊት ግን ለመገንባት ብቁ መሆናቸውን ከወዲሁ ማስተዋልና ራሳቸውን መመዘን ይጠበቅባቸዋል። አይቀሬው መመዘኛ ክርስቲያንነታቸው ነው። ኃጢአተ ኝነታቸውን ተረድተው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከመንፈስ ቅዱስ ተወልደው የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽ መሆናቸውን በቅጡ ማወቅ አለማወቃቸው፣ የእግዚአብሔር ቃል ብቸኛ የሕይወት መመሪያ፣ የማይሻሻልና የማይለወጥ መሆኑን የተረዱ መሆን አለባቸው።

* * *

መቼም የራሳችንን ክርስቲያንነትና የሚጠበቅብንን ኃላፊነት ተ

ረድተን ወደ ልጆቻችን ሕይወት ስንዘምት በሂደቱ ውስጥ እንቅፋቶች አይታጡም፣ ከእንቅፋቶቹ አንዳንዱ «እኔ እኮ ደካማ ክርስቲያን ነኝ። ከልጆቼ ጋር በነገሮች ሁሉ መጨዋወትን ከያዝን፣ «ለካ እንዲህ ናት! በሚል ግምት ውስጥ እንዳልወድቅ ልጠነቀቅ ይገባል፣» የሚል በራስ ያለመተማመን ጫና ልጆችን በተገቢው ሁኔታ ላለማሳደግ አንድ እንቅፋት ነው። ሁለተኛው ጋሬጣ ራስን መናቅ ሳይሆን፣ ልጆችን መናቅ ነው። በዚህ ዕድሜያቸው ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛውን ነገር ለማወቅ አይችሉም፤ ስለዚህ እስኪያድጉ እጠብቃለሁ ማለት። ሁለት ዓመቱን ያልሞላ ሕፃን እንኳን ከወላጆቹ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ስለ እግዚአብሔር ግምታዊ እውቀት አለው። ይህ ደግሞ ጥቂት ዕድሜ ሲጨምር ሕይወቱን ለጌታ እስከ መስጠት የሚያደርሰው ስለሚሆን፣ ሕጻናትን ዝቅ አድርጎ ማየት ተገቢ አይደለም።

ሦስተኛው እንቅፋት፣ ከፊል እውነትን ብቻ ለልጆች ማድረስ ነው። ለምሳሌ፣ «ሲጃራ ብታጭስ ጭሱ ጭንቅላትህ ውስጥ ገብቶ ትነድዳለህ፣» ማለት የሲጋራን ጎጅነት በመግለጽ ማሳየት እውነት ቢሆንም፣ የወላጆየው ማጠቃለያ ግን ውሸት ነው። ሲጃራ የሚያስከትላቸውን ጠንቆች ለልጁ በመግለጽ ዕድሜ ያሳጥራል፣ የሳንባ ካንሰር ያመጣል፣ ወዘተ...ቢባል በቂ ነው።

አራተኛው ጋሬጣ፣ የወላጆች ጽኑነት ማጣት ነው። «ዛሬ ጸሎት አናደርግም፤ ሁላችንም ስለ ደከመን፣ ወደ መኝታችሁ ሂዱ፣ የዛሬ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ቤተ ክርስቲያን ከተማራችሁት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ፣ ዛሬ አይኖረንም፣ ወዘተ...» በተሰኙ ምክንያቶች በልጆች ፊት ወስነን እናደርገዋለን ያልነውን የዕቅድ መርጎ ግብራችንን በየጊዜው የምንለዋውጠውና የምንሸረው ከሆነ፣ በውጤቱ ልጆቻችንም ሲያሻቸው ያሻቸውን የማድረግን ነገር ይዘው ያድጋሉ። እውነቱ ግን፣ የዕለት እንጀራችንን ሳናስተጓጉል ከመመገባችን የተነሣ በሕይወት እንዳለን ሁሉ፣ ጸሎትንና የጌታን ቃል ለመንፈሳዊ ሕይወታችን በዘላቂነት መጠቀም ተገቢ ነው።

የመጨረሻ ያልሆነ፣ ለዚሁ ጽሑፍ ግን እንደ መጨረሻ እንዲቆጠር የፈለግኩት ሊታረም የሚገባው ጋሬጣ፣ «ቴሌቪዥን መመልከት እኮ ኃጢአት ነው፣ ልብ ወለድ ማንበባችሁ ያረክሳችኋ

ል፣ ይህንንና ያንን ብታደርጉ፣ አትድኑም» የመሳሰሉትን አስደንጋጭ መልእክቶች ወደ ልጆች በድግግም ማድረስ ነው። መጥፎ ፊልሞችን አትመልከቱ፣ የምታነቡትን ምረጡ፣ ወይም ምክር እየጠየቃችሁ ማለት ሲቻል፣ የማይቻልን ግላዊ ውሳኔን በልጆች ሕይወት ውስጥ ማሳደር ጉዳቱ ሚዛን ደፊ ነው። እንግዲህ ከአንድ እስከ አምስት የጠቀስኳቸው ወላጆች ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ ሊጠነቀቁበት የሚገቡ ናቸው።

ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ለሕፃናት፣ ለልጆችና ለወጣቶች በምትሰጠው ሰፊ ስፍራ ትገለጣለች በማለት ከመነሻዬ ላይ ተናግሬ ነበር። ይህ የቤተ ክርስቲያን ጥረቷ ፍጹምና ሙሉ የሚሆነው ግን ወላጆች ለልጆቻቸው ከጌታ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ እንደሚገባ ሲወጡ ነው። ስለ ጌታ መጨዋወት በየጊዜው እንደሚፈለግ ውኃ ጥም ነው። የትናንቱ ለዛሬ በቂ ነው ብለው ወላጆች ቸል ሊሉት አይገባም። የነፍስን ጥምና ረሃብ በየጊዜው ማርካትና ማጥገብ የወላጆች ድርሻ ነው። ወላጆች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ኃላፊነት በትክክል ከተወጡ፣ ጠንካራ ቤተሰብ ለጠንካራ ቤተ ክርስቲያንና ለጠንካራ ኅብረተሰብ መሠረት ይሆናሉ።

ለተመራቂዎች ሁሉ

በ1803 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) እንዲህ ሆነ፣ አንዲት አነስተኛ ጠረጴዛ በውስጧ የያዘችውን ብርና ወርቅ እንዳጨቀች ተሰረቀች። መጥፋቷ በፖሊስ እንደ ተሰማ፣ የአውስትራሊያ (የሲዲኒ) ፖሊሶች የተጠናከረ ክትትል ጀመሩ። ክትትሉ ፍሬያማ አልነበረም። የጠረጴዛዋ ደብዛ ጠፋ፤ መርማሪዎቹም ታክተው አሰሳውን ቸል አሉ።

አንድ ምሽት ግን በዮሴፍ ሳሙኤል እጅ ላይ አንዲት የወርቅ ቤሳ በመገኘቷ ዮሴፍ ተያዘ። መያዝ ብቻ አይደለም ወደ ዘብጥያም ወርዶ ይመረመር ጀመር። በምርመራው የዮሴፍ የሁልጊዜ ቃል፣ «ቁማር ስጫወት ያገኘሁት ነው፤ ሰክሬ ስለ ነበር የሰጡኝን ሰዎች በውል አላውቃቸውም፣» የሚል ሆነ። ፍርድ ቤቱ ግን ተከሳሹ፣

«እኔ አልሰረቅኩም» እያለ ቢወተውትም፣ «ሌባው እርሱ ነውና ይሰቀል» ብሎ በየነ።

የስቅላቱን ፍርድ የሚያስፈጽመው ማርሻል ፕሮቦስት አዲስ ገመድ አስመጥቶ በሕዝብ ፊት «ንጹሕ ሰው ነኝ!» እያለ የሚጮኸውን ሰው አንጠለጠለው፤ ያ አዲስ ገመድ ግን ተተለተ ለና ተሠቃዩን ሰው ከመሬት አኖረው። ማርሻል ፕሮቦስት ዮሴፍ በመትረፉ ተበሳጭቶ፤ «መገደሉ አይቀሬ ነው!» በማለት በሦስት የተገመደ ገመድ እንዲያቀርቡ ወስኖ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲሰቀል አዘጋጀው። ሕዝቡ፣ «ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ነውና አትስቀሉት፣» እያለ ዳግመኛ እንዳይሰቀል ቢማጠንም፣ ሰውየው በተሸረበው በአዲሱ ገመድ ተሰቀለ፤ የወርቅ ቤሳ የተገኘበት የተ ሠቃዩ ሰው ገመዶች ግን እየተረተሩ ዳግመኛ ዮሴፍን ለምድር አበቁት። ሕዝቡ በደስታ ሲቃ ተዋጠ። ያ ሰውም ተርፎ ቁልጭ ቁልጭ ይል ጀመር። ሰቃይ ማርሻል ፕሮቦስት ግን የመንግሥትን ሕግ አስፈጻሚ ስለሆነ፣ ዳግመኛ ድንጋጤ ወረረው፤ አሁንም ግን አቋሙን ባለመቀየር ለሦስተኛ ጊዜ፣ «አሰቅዬው! አንጠልጥዬው አርፋለሁ፣» በማለት በመውደቅ አቅም ያጣውን «ወንጀለኛ ተብዬ» ለሦስተኛ ጊዜ ሰቅሎት መለስ አለ፤ ወዲያው ሕዝቡ «በሆታ! ተ ረፈ! ተረፈ!» ብሎ እልልታውን አቀለጠ። እውነትም ዮሴፍ ለሦስተ ኛ ጊዜ ከገመዱ አምልጦ ኖሯል።

* * *

ያን ሰሞን ታዲያ በሲዲኒ ከተማ የሕዝቡ ሁሉ ንግግር፣ «እግዚአብሔር እውነተኛ ዳኛ ነው፣» የሚል ሆነ። ከራርሞ ግን የሕዝቡ ምስክርነት ሳይለወጥ፣ የተሠቃዩ ቃል ግን ታጠፈ። ዮሴፍ ሳሙኤል በየመጠጥ ቤቱ በተገኘ ቁጥር «እኔን ገመድ አይዘኝም» እያለ ማቅራራት ጀመረ። ይህ ቀረርቶ ያልጣማቸው ጓደኞቹ፣ «አንተ ሰው ያኔ ያተረፈህ እግዚአብሔር ነውና፣ እርሱን ዛሬም አመስግን እንጂ እንዲህ አትበል» ቢሉትም፣ ዮሴፍ ግን፣ «ብልሐቴ አዳነኝ፣ ዛሬም ገመድ አይችለኝም» እያለ መዘበቱን አዘለቀው።

ይህን ጊዜ፣ «ብልሐትህ ካዳነህ፣ እስቲ ዛሬ በዚህ ልጥ ሞክር» ብሎ አሮጌውን ቀጭን ልጥ ተመልካቹ ሰው ጣለለት። ወዲያውን ዮሴፍ በቤቱ ጣራ ላይ ገመዱን ሸብ አድርጎ አንገቱን አስገባ።

የቆመበትንም በርጨማ በገዛ እግሩ መታ፤ ገመድ አይችለኝም ባዩን ገመዷ ተሸከመችው፤ አሮጌ ልጧ ሳትበጠስ ቀረች፤ ዮሴፍም በዚያው ሞተ።

* * *

ይህን አስደናቂ ታሪክ በዚህ ጽሑፍ የማንሣቱ ምክንያት «ልዑል እግዚአብሔር ብቻ» መሆኑን ለማሳሰብ ጥቂት ነጥብ መነሻ ስለሆነኝ ነው።

ልዑል የሆነው እግዚአብሔር ያድናል፤ ይገድላልም፤ ትሑታንን ያከብራል፤ ትዕቢተኞችንም ይቃወማል፤ ፈቃዱን ይፈጽማል፣ የሚከለክለውም የለም፤ አሳቡን ለሰዎች ሲል አይቀየርም፣ በሁሉም ላይ ሥልጣን የእርሱ ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ አጋጣሚ ወይም እኛ በሰዋዊ አነጋገር እንደምንለው «ዕድል» የሚባል ዕጣ ፍጹም የለውም። እርሱ አሳቡን እንደ ታላቅነቱ እየፈጸመ ሰዎች ከገዛ አሳባቸው ይነቁ ዘንድ ይረዳቸዋል። ከማንቂያው የእርዳታ እጆቹ አንዱ በዮሴፍ ሳሙኤል የተፈጸመው ታሪክ ነው። ድርጊቱ የሚያስጨብጠን ቁም ነገር «የሚመካ በእግዚአብሔር ብቻ ይመካ» የሚል ነው።

መቼም «ተመክቶ እንድንመካም መሠረትን የጣለ ብርቱ ሰው ይፈለግ» ከተባለ በቶሎ ወደ ሕሊናችን ከተፍ የሚል ሰው የጌታ የሆነው ጳውሎስ ነው። እርሱ ሰውዬ ቀድሞ የሚመካበት እልፍ ነገሮች ነበሩት፤ በስምንተኛው ቀን የተገረዘ፣ ትውልደ እስራኤል፣ ያውም ብንያማዊ፣ የጠራ ዕብራዊ፣ እንከን የለሽ ፈሪሳዊ፣ ስለ ሃይማኖቱ ቀናተኛ፣ ሕግን በመጠበቅ ያለ ነቀፋ ነበር። እርሱ ግን እነዚህ ሁሉ የሚያስመኩም ቢሆኑ፣ ከእነዚህ ሁሉ በላይ ግን መመኪያስ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ማወቅ ነው» አለ (ፊልጵስዩስ 3፡7)። ይህም በሕይወቱ እውነት ሆኖ እንዲጸና በስተ ኋላው የነበረውን እየረሳ ከጌታው ጋር እስኪገናኝ ከፊቱ ብዙዎች በጨለማ ሆነው፣ ስለ ጨለማ ሲያወሩ፤ ለዓለም፣ ለፈቃዳቸውና ለዲያቢሎስ ደስታ ራሳቸውን ሲሰጡ አስተዋለ። ለዚህም ወንጌልን ይዞ ከጠላት ኃይል ሊያድናቸው እንደሚገባ ወስኖ ወደፊት ተራመደ፣ ተራምዶ ሰዎችን ሊያጠምድ፤ በክርስቶስ የሆኑትን ደግሞ የጌታ ጽኑ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ለማገዝ የፊቱን አየ፣

ያየውንም ለመፈጸም ልዑል የሆነው እግዚአብሔር እንዲረዳው በጉልበቱ ተንበርክኮ ጸለየ፣ የጸለየው «ክርስቶስ በእምነት በልባቸው እንዲኖርና የእነርሱ ሥርና መሠረት በፍቅር የጸና ይሁን» በማለት ነበር (ኤፌ. 3፡14)።

እንኪያስ፣ ደስ ለተሰኙት ለዘንድሮዎቹ ተመራቂዎች እንደ ወንድምነቱ የምላቸው «የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክቴ» በጌታ ዘንድ ብዙ ተቀብላችኋልና ብዙ ይፈለግባችኋል፣ ያን ብዙ ለወገኖቻችሁ በፍቅር ሳታካፍሉ አትቅሩ፣ ሁሌ የሚያስመካ ነገር ቢኖር ለዚህ ያበቃችሁ እግዚአብሔር ብቻ ይሁን። «እርሱ ልዑል ነውና እናንተን ለማገዝ ችል አይልም። በ1803 በሰዎች አመለካከት ብቻ ተወስኖበት የተሰቀለውን ዮሴፍ ሳሙኤልን አስቡ፤ ፈረዱበት፣ ግን በተአምራቱ አተረፈው። ኋላ ታበየ፣ በውጤቱም ሰው ሁሉ መተረቻ አድርጎት አለፈ። ተመራቂዎች እንዳይተረትባችሁ ተጠንቀቁ! ያም በእርሱ በመመካታችሁ ይገለጽ። ደግሜም እላለሁ፣ ብዙ በመቀበላችሁ በጸጋው መከፈል ለሚችል የፍቅር ዕዳ እንኳን ጌታ አደረሳችሁ።

(መታሰቢያነቱ፦
በየጊዜው ትምህርታቸውን ዳር ለሚያደርሱ
ተመራቂዎች ነው)

«በመለኮታዊ ራዕይ ሲያል ሲገለጽ» በሚለው መጽሐፍ ላይ የቀረበ ትችት

ይህን መጽሐፍ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት በየገበያው አየሁት እንጂ አላነበብኩትም፤ ዘንድሮ ግን ሰባኪው እርሱኑ እየጠቀሰ ስብከቱን ስለ ጨረሰ አግራሞት ተፈጠረብኝ። መገረሜ ሰባኪው ከእግዚአብሔር ቃል አስበልጦ መጽሐፉን ለመረጃነት መጠቀሙ አንዱ ሲሆን፣ ሌላው አድማጩ ከሕያው ቃሉ ጋር ሳያመሳክር «እውነት ነው» ባለው ማጽናቱ አስደነገጠኝ። ከዚህም የተነሣ፣ በማግስቱ ገዝቼው ከሽፋን ሽፋን አጤንኩት፣ አነበብኩት፤ በመጨ

ረሻም «እኔስ ዝም አልልም» በማለት ብዕሬን አነሣሁ።

* * *

በአነሣሴ ላይ ግን ወዳጆቼ ጌታቸው በለጠና ላዕከ ታፈሰ የሚሰጡኝን ምክር ለመታዘዝ አቅም አልነበረኝም፤ እነርሱ «የአንድን ነገር ጠንካራ ጎን አስቀድመህ ከዚያ ሊስተካከል የሚገባውን ደካማ ጎኑን በማስረጃ በማስደገፍ ብትናገር ወይም ብትጽፍ፣ ሚዛናዊነት ያለው ሥራ ይሆንልሃል» ይሉኛል። ይህን ምክር በመታዘዝ ሰነባብቻለሁ፤ በዚህኛው ላይ ግን ምክሩ ደፈ ረሰብኝ። ከዚህም የተነሣ አካሄዴ «ቀና ሲታጣ ይጋለጣል ጎባጣው» ሆኖብኛል፤ እናም እርሱኑ እነሆ፡- ከጀርባው ሽፋን ስጀምር ሰዎች ስለ መጽሐፉ አስተያየት ሰጥተውታል። በመሠረቱ አስተያየቱ መጽሐፉ እንዲነበብ ይጋብዛል፤ ያስተዋውቃል፣ ያሸጠዋልም።

ከዚህም የተነሣ፣ ዶ/ር ዓለማየሁ ኃ/ገብርኤል፡-

«ይህ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘቱን የለቀቀ አይደለም...ላመነውም ሆነ ላላመነው ሊሰጥ የሚችለው ጥቅሙ በቀላሉ የሚታይ አይመስለኝም...ስለ ሲያል እርግጠኝነት ሰዎች እንዲገባቸውና ወደማይመለሱበት ሳይሄዱ ምርጫቸውን በጊዜ እንዲያስተካክሉ ደራሲዋ ልምዷን አካፍላለች። መጽሐፉ በሁሉም ሰው ሊነበብ የሚገባው ነው።» ይሉለታል።

አሳታሚው የሕይወት ሥነ-ጽሑፍ አገልግሎትም ደግሞ *«...የክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት እጅግ በቀረበበት በዚህ የመጨረሻ ዘመን እንደዚህ ያሉ ታምራዊ መጽሐፍት የምጽአቱን መድረስ ጠቋሚዎች ናቸውና ጌታን በክብር ለመቀበል እንዘጋጅ» ይልለታል።*

በእኔ እምነት ዶክተሩም ሆኑ አሳታሚው አጋንነው ከማስተ ዋወቃቸው የተነሣ፣ መጽሐፉን ሸማቾች እንደ ጣፋጭ ኬክ ተ ሻምተውበታል፤ ይህን ሸሚያ ማረጋገጥ የሚቻለው በጎትመቱ ድግግም ነው።

የመጀመሪያው እትም በ1992፣ ሁለተኛው እትም በ1993፣ ሦስተ ኛው እትም በ1994፣ አራተኛው እትም በ1996 ዓ.ም ታተመ፣

እንዲህ የተቸበቸበው መጽሐፍ ግን ሰዎችን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አላገጣጠመም፤ ይልቁኑ፣ አዛባ፣ አሳሳተም ለዚህ አባባሌ ታገሡኝ እንጂ መረጃዬን አካትታለሁ።

* * *

ወደዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ገጾች ስንገር የገጠመኝ ግራ ገብ ቀዳሚ ጉዳይ አለ። እርሱም መጽሐፉ በመታሰቢያነት የተሰጠበት መግለጫ ነው፤ በመሠረቱ መታሰቢያ ሊሆን የሚገባው በየጊዜው ስማቸው እንዲታወስ ለተፈለጉ ስመ-ጥር ሰዎች (ዛሬ በሕይወት ከሌሉ)፣ አልያም በመጽሐፉ ዝግጅት ጋባኾነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች፣ አልያም የቅርብ ተፈቃሪ ለሆነ ሰው ወይም ሰዎች «ለእነከሌ» በማለት ይለገሳል። ይህ መጽሐፍ ግን መታሰቢያ ሆኖ የተሰጠው ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ነው (ለእግዚአብሔር መሆኑ ነው)፤ በውኑ ሕያው እግዚአብሔር መታሰቢያ ያስፈልገዋል? ወይስ እግዚአብሔር እና ሟች ሰዎች በእኩል መፈረጅ ጀመሩ? ይህን ተርጓሚው ወይም ደራሲዋ ሊያስቡበት የተገባ የተጣረሰ አካሄድ መሆኑን ልብ ሊሉ ይገባል። እንደ እነርሱ አባባል ግን «እግዚአብሔር ሞቷል።»

ወደ መጽሐፉ አጠቃላይ ጭብጥ ስገባ፣ (እ.ኤ.አ) 1996 ኢየሱስ ወደ ሜሪ ኬ. ባክስተር ይመጣና፣ «ወደ አንቺ የመጣሁት የማሳይሽንና የምነግርሽን እንድትጽፊና እንድትነግሪ ለዚህ ምክንያት ተወልደሻል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ የታመኑና እውነተኞች ናቸው። ያንቺ ጥሪ ሲያል እንዳለና እኔም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ወደ ዓለም ተልኬ የሰውን ልጆች ሁሉ ከዚህ ሥቃይ ለማዳን እንደ ሆነ ለዓለም እንድታሳውቂ ነው፣» በማለት ለ40 ቀናት ነፍሷን ከሥጋዋ እያወጣ ሲያል እያደረሰ ያመላልሳታል። በዚህም የገሀነምን ምሥጢር ይገልጽላታል (ገጽ 5ን ይመልከቱ)። በዚህ የ40 ቀን የምልልስ ጉብኝት የመጀመሪያ ቀን ላይ፣ «ልጄ ሆይ! በመንፈስ ወደ ሲያል ውስጥ እወስድሽና ዓለም እንዲያውቃቸው የምፈልጋቸውን ብዙ ነገሮች አሳይሻለሁ፤ ብዙ ጊዜም እታይሻለሁ፣ መንፈስሽንም ከሥጋሽ አውጥቼ በርግጠኝነት ወደ ሲያል እወስድሻለሁ፤ በዓይንሽ የማሳይሽንና በራእይ የምታያቸውን ሁሉ በመጽሐፍ እንድትጽፊያቸው እፈልጋለሁ» (ገጽ 7) በማለት ወደ

ሲያል አብረው ይገባሉ።

* * *

አሁን ደግሞ እየገቡ በየጊዜው ሆኑ የተባሉትን ክንውኖች መጥ ኜ በ3 ልመድባቸው፦

ምድብ አንድ

የሲያል ገጽታ፦

- ሲያል በሰው ቅርጽ የተበጀ ስፍራ ነው (ገጽ 12፣ 22፣ 49፣ 63፣ 76፣ 80፣ 101)።
- አካባቢው የጠነባና የገማ ከመሆኑ የተነሣ ለበሽታ ያጋልጥ ነበር (ገጽ 9)።
- የገማው ጠረን፣ የበሰበሰ የሥጋ ሽታን የያዘ ሆኖ በተ ዝለግላጊ እባቦች ተሸፍኗል (ገጽ 63)።
- ሙታን ይሸታሉ፣ የሰቆቃ ኡኡታ ያለማቋረጥ ያሰማሉ (ገጽ 14፣ 63)።
- የሲያል እሳት ኃጢአተኞችን እንጂ ሰይጣንንና አጋንንቱን አያቃጥላቸውም (ገጽ 61)።

ምድብ ሁለት

ሴቲቱና ገጠመኝ ተብዬዎቹ፦

- ኢየሱስ ያስጐበኛት ከነበረችው ሴት በመሰወሩ በዲያብሎስ ቁጥጥር ሥር ለመዋል በቃች (ገጽ 65)።
- የጎብኝዋ ነፍስ በሰንሰለት ታሰረች፣ በእሳቱ ተቃጠለች፣ አጽሟም በትል ተሞላ (ገጽ 67፣ 102)።
- ከእሳት ወደ ውኃ፣ ከሙቀት ወደ እርጥበት ተሻገረች (ገጽ 68)።
- ኢየሱስ የሲያልን አሠቃቂነት እንድታውቂው ይህ መሆን ይገባዋል በማለት አስረዳት (ገጽ 68፣ 108)።
- ለሴቲቱ ኢየሱስ የሚመለስበትን የመጨረሻ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ልጆችና ስለ አውሬው ልጆች ምንነት ገለጸላት (ገጽ 82፣ 91)።

ምድብ 3

ቃሉን የተጻረሩ «የኢየሱስ» እንግዳ ትምህርቶች፡-

- «ጻድቃን በእምነት ይኖራሉ፣ ፈዘኞችና የማያምኑ መሪ ያቸው በእሳት ባሕር ውስጥ ይሆናል ተብሎ ተጽፏል፣» በማለት «ኢየሱስ» መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለ ጥቅስ ይናገራል (ገጽ 15)።
- በኢየሱስ አምኖ የዳነ በኃጢአት ምክንያት ደኅንነቱን እንደሚያጣ ኢየሱስ ያስተምራል (ገጽ 17፣ 32፣ 25፣ 33፣ 41፣ 43፣ 49፣ 88፣ 103፣ 114)።
- በጉብኝቱ ለሲያል የበቁ ሰዎች መኖራቸውን በማወቁ ኢየሱስ የመረረ ለቅሶ ያለቅሳል (ገጽ 22፣ 77)።
- የሲያል መከራ የሚበቃው መቼ ነው? ለሚለው ጥያቄ ኢየሱስ ማብቂያውን አባቱ እንጂ እኔ አላውቀውም በማለት ይመልሳል (ገጽ 27)።
- ኢየሱስ በጸጋ ሳይሆን፣ በሥራ መጽደቅ እንዳለ ትምህርት ይሰጣል (ገጽ 25፣28፣30፣124)።
- ኢየሱስ አምነው ከካዱኝ ጭራሹን ያላወቁኝ ይመረጣሉ በማለት ያስተምራል (ገጽ 43፣70)።
- ኢየሱስ ዛሬውኑ ጥሩኝ እንጂ የምትወዷቸውን ሁሉ አድንላችኋለሁ የሚል ተስፋ ይሰጣል (ገጽ 48)።
- ኢየሱስ «ቅዱስ የጦር ኃይል» የሚባሉ አገልጋዮችን በሥራ ላይ ከተሰማሩት ሠራተኞች፣ እመቤቶች፣ ወንደላጤዎች፣ ያላገቡ ሴቶች፣ ከትምህርት ቤት ሕፃናት እንደሚገነባ ትንቢት ይናገራል (ገጽ 81)።
- ኢየሱስ ሰይጣን ወደፊት የሚታሠረው የቅዱሳን ጸሎት ጠንካራ ከሆነ ብቻ መሆኑን አስተማረ (ገጽ 92)።

* * *

እነዚህን ያህል መግለጫዎች ከመጽሐፉ ከነቀስኩኝ፣ ለተዘረዘሩት ለሦስቱም ክፍሎች አጠቃላይ ቅኝቴን አስከትላለሁ።

በ1960ዎቹ በሰፊው ይሰራጩ ከነበሩት በራሪ ጽሑፎች ውስጥ አንዱ «አርባ ስምንት ሰዓት በገሀነም» የሚለው በብርሀኑ ከበደ

የተተረጎመው የጆርጅ ሌየክስ ራእይ ትርጉም ነበር። በ1970ዎቹ ደግሞ «ክርስቲያኑን ዓለም ያሸፈተው» ጽሑፍ በናይጄሪያ፣ ሌጎስ «ለአማኑኤል አሞፅ» ተገለጸልኝ ያለው «የዲያብሎስ እና የገሀነም ምሥጢር» በሚል ርእስ በካሴት እና በጎትመት ወረቀት ሲናኝ የከ ረመው ጽሑፍ ነበር። በእነዚህ የጎትመት ውጤቶች «ዲያብሎስን ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል» የተሰኘ አስተምህሮ እንዳይኖሩ አስገንዝቧል። እናም ዲያብሎስ ተፈራ፣ ተከበረ። ስለ ልዑል እግዚአብሔር ሳይሆን፣ ስለ ዲያብሎስ ተዘከረ፤ «ዲያብሎስን ተ ቃወሙ ከእናንተም ይርቃል» ያልተጻፈ ያህል ተረሳ። በ1990ዎቹ ደግሞ «በመለኮታዊ ራዕይ ሲያል ሲገለጥ» የሚለው መጽሐፍ የቀድሞዎቹን ስፍራ ያዘ። መቼም ቢሆን እግዚአብሔር ቃሉን ያከብራል፤ እንደ ቃሉም ይሠራል። በዚህ አኳያ፣ በሦስት ክፍል ከጠቋቀምኩት ውስጥ የተዛነፉትን መግለጫዎች በቃሉ መሠረት ሲፈተሽ የዕብራውያን ጽሑፍ «ለሰው አንድ ጊዜ መሞት የተገባ ነው፣ ከሞተ በኋላም ፍርድ አለበት» (ዕብ. 9:27) ይላል። ሐዋርያው ዮሐንስ በምዕራፍ 5:28-29፣ «በመቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካም የሠሩ [በክርስቶስ ያመኑ] ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል» ይለናል። የፍርዳቸውንም ውሳኔ ማቴዎስ በምዕራፍ 25:34-41 ሲገልጽ፣ ጻድቃንን፣ «እናንተ አባቴ የባረካችሁ ኑ፣ ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ ያዘጋጀሁላችሁን መንግሥት ውረሱ... እናንተ የተረገማችሁ ከእኔ ራቁ ለሰይጣንና ለተከታዮቹ መላእክት ወደተዘጋጀው ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ» በማለት በዓለም የታሪክ መዝጊያ ላይ ፍርድ ይከናወናል።

ይልቁኑ፣ ይህ ከፊታችን ሊሆን ስላለው ፍርድ ሐዋርያው ጳውሎስና በ2ኛ በተሰሎንቄ ምዕራፍ 1:7-10 ሲናገር፣ «አሁን መከራ ለምትቀበሉትም ከእኛ ጋር እረፍትን ይሰጣችኋል፤ ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ ከኃያላን መላእክቱ ጋር ከሰማይ በሚወርድበት ጊዜ ነው፣ ከሰማይ የሚወርደውም በሚንበለበል እሳት ነው፤ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታችን ለኢየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል። እነርሱ ከጌታ ፊትና

ከኃያል ክብሩ ተለይተው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ...» ይለናል። እነዚህ የተሳሰሩ መልእክቶች የሚያስገነዝቡት ሰዎች ሁሉ እንደ ሞቱ አይቀሩም፣ ለፍርድ በትንሣኤ ይነሣሉ፤ በክርስቶስ ያመኑ ለእግዚአብሔር መንግሥት ለዘላለም ሕይወት ይበቃሉ፣ ያላመኑበት ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው ለገሀነም ቅጣት ለዘላለም ቃጠሎ ተላልፈው ይሰጣሉ። ይህም በኢየሱስ ይሆናል፤ ከዚህ በማለፍ ግን ኢየሱስ ከትንሣኤ በፊት ሰዎችን ለእሳት በማብቃት የገማ፣ የከረፋ፣ የሰቆቃ ስፍራን፣ በሰው አካል ቅርጽ በማዘጋጀት አሰቃቂ ፍርድን እንደ ጀመረ ቃሉ አይነግረንም፤ ፍንጭም አይሰጠንም። በትይዩ፣ ምናልባት አንዳንዶች «ይህ እኮ በሀብታሙ ሰውና በአልአዛር ተከሥቷል» ይሉ ይሆናል። ይህ ግን የማይገጣጠም መሆኑን ክፍሉን ገልጦ ማንበብ በቂ ነው። ኢየሱስ ሥራውን በዘላለማዊው ዕቅዱ መሠረት እንደ ቃሉ እየሠራ እንዳለ የዮሐንስ ወንጌል በሙላት ያስረዳል። ከዚህ የተነሣ፣ ኢየሱስ ለ40 ቀናት የሜሪ ኬ. ባክስተርን ነፍስ ከሥጋዋ እያወጣ፣ የሲያል ጉብኝት እና ትውውቅ ሲያካሂድ መክረሙ፣ ሴቲቱ በዲያብሎስ ተ ይዛ ሥጋዋ በእሳት መቃጠሉ፣ አጥንቶቿ በትል ተሞልተው መሠቃየቷ፣ «የሲያልን መራራነት እንድትቀምሰው፣ ከዚያም የተነሣ በሕይወት ያሉ ሰዎች የገጠማትን በመስማት ገሀነም እንዳይገቡ ይረዳል» የሚሉ ገለጻዎች፣ ሰዎች ገሀነምን በመፍራት ብቻ ክርስቲያን ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚጠቁም የስሕተት ትምህርት ነው። በክርስቶስ የሆንን ሁላችን ክርስቲያን የሆንነው እርሱ አስቀድሞ ስለ ወደደን ከፍቅሩ የተነሣ እንጂ፣ ሲያል ከፊታችን አለ በሚል ስጋት አይደለም። ሐዋርያው ዮሐንስ 1ኛ ዮሐንስ 4:9-10፣ «በልጁ አማካይነት ሕይወት እንድናገኝ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታል በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር ምን ያህል እንደ ሆነ ለእኛ ተገልጧል፤ ፍቅር ማለት እንዲህ ነው፦ እኛ እግዚአብሔ ርን ስለ ወደድነው ሳይሆን፣ እርሱ ስለ ወደደንና ኃጢአታችንን እንዲደመስስ ልጁን ስለ ላከልን ነው» በማለት የዳግም መወለዳችን ምሥጢር «ከእግዚአብሔር ጥሪ እና ከእርሱ ፍቅር» የተነሣ መሆኑን ያስረዳናል። ከዚህ እውነት አንጻር፣ ሰዎችን በገሀነም አስፈራርተን እመኑ አንልም፣ በዚያም የሚሆነውን ለማወቅ

አንጓንም፤ ቃሉ ስለ እግዚአብሔር እንድናውቅ እንጂ፣ ስለ ዲያብሎስ እና ስለ ሲያል እንድንፈላሰፍ አልፈቀደም (ገላ. 1:69)።

* * *

ከሁሉም ከሁሉም፣ በመጽሐፉ ውስጥ የሚያስገርመው ዝርዝር ለወይዘሮ ሜሪ ኬ. ባክስተር የተገለጸው ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አለመሆኑ ነው። «ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍላቸው ወደ ልዩ ወንጌል፣ ልዩ መንፈስ እና ልዩ ክርስቶስ የሄዱ እንዳሉ ይገልጽላቸዋል» (2ኛ ቆሮ. 11:4)። በዚህም የሆነው እንዲሁ ነው፣ «40 ቀናት ነፍሷን በሲያል ያስነበኝ የነበረው ልዩ ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔርን ሕያው ቃል ሽሯል፣ ቀይሯልም። በፍርድ ወቅት ኢየሱስ ጎጥኣንን ይበቀላል፣ እርጉማን በማለትም ወደ ተዘጋጀላቸው የቅጣት ስፍራ ይሰድዳቸዋል» (2ኛ ተሰ. 1:7-10፤ ማቴ. 25:41)። ከዚህ ውጭ ግን የሚሆነውን ሁሉ የማያውቅ ሆኖ በሲያል ጉብኝቱ ማዘን ደግሞም አምርሮ ስለ እነርሱ ማልቀሱ እንግዳ ጉዳይ ነው።

«ልዩው ኢየሱስ» በዮሐንስ 3:16፣ «በልጁ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ አይጠፋም»፤ እንዲሁም ኤፌሶን 2:8-9 «እናንተ የዳናችሁት በእምነት አማካኝነት በጸጋው ነው፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ በእናንተ ሥራ የተገኘ አይደለም፣ ማንም ሰው እንዳይመካ ይህ ስጦታ የተገኘው በሥራ አይደለም» የሚለውን ጽኑ የደኅንነት ሥራ በመገልበጥ፣ ሰው በሥራው ሊጸድቅ እንደሚችል፣ ክርስቶስ ጠርቶት ያመነም፣ በሆነ ምክንያት የዘላለም ሕይወቱን እንደሚያጣ ያስተምራል። «ልዩው ኢየሱስ» ኢየሱስን አምነው ከካዱት ይልቅ ከመነሻው ያላወቁት እንደሚሻሉ ያስረዳል። ለነገሩ ለገሀነም መብቃት መሻሉ ከምኑ ላይ ይሆን? ይህ ኢየሱስ ስለ ሲያል ማብቂያው መቼ እንደ ሆነ አለማወቁን በመግለጽ አብን ጠይቁት በማለት የመረታት ገለጻ ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ከመሆኑ የተነሣ የማያውቀው እንደሌለ ያስተምራል።

«ልዩው ኢየሱስ» እንደ አንዳንድ ገድላ ገድሎች፣ አንተ እመን እንጂ የምትወዳቸውን ሁሉ አድናለሁ (ገጽ 48) በማለት «ጉቦ» ወይም ማጓጊያ ሲያቀርብ ይሰማል፣ ቃሉ ግን እንዲህ አላለም።

በመጽሐፉ የመጨረሻ ገለጻም «ልዩው ኢየሱስ» ትንቢትን ይናገራል። መጨረሻው ዘመን ወንጌልን ለዓለም ለማድረስ ቅዱስ ኃይል ያደራጃል፣ ሠራዊቱ የሚሰበሰበው ከቤት እመቤቶች፣ ከወንደላጤዎች፣ ካላገቡ ሴቶች፣ ከሕፃናት እንደ ሆነ ይናገራል፤ (ገጽ 81)። ይህ የጌታ ቃል እንግዳ ትምህርት ነው። አዲስ ኪዳናችን እያንዳንዳችን የክርስቶስ አምባሳደሮች መሆናችንን በማስረዳት፣ ሰዎችን ሁሉ በወንጌል እንድንደርስ ታዝዘናል (ማቴ. 28፡19-20)። ይህንንም ፍቅሩን የተረዱት ሁሉ የሚፈጽሙት ተግባር ነው፣ «ልዩው ኢየሱስ» ግን ይህን አጠበበው፤ የቤት እመቤቶች፣ ወንደላጤዎች፣ ያላገቡ ሴቶች፣ ሕፃናትም ጭምር የተለየ መለኮታዊ ችርነት የተደረገላቸው ይመስላል። ሌላውን ሁሉ ያለምክንያት በማስወገድ «ሠራዊትን» ወደፊት ሊያደራጅ ተነበየ።

* * *

መልእክቱን ባጠቃልል ሳይሻል አይቀርም፤ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 7፡24-27፣ «ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የሚያውለው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራውን ብልህ ሰው ይመስላል፤ ዝናብ ዘነበ፣ ጎርፍም ጎረፈ፣ ነፋስም ያንን ቤት ገፋው። ይሁን እንጂ ቤቱ በዓለት ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም፤ ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራውን ሞኝ ሰው ይመስላል። ዝናብ ዘነበ፣ ጎርፍም ጎረፈ ነፋስም ነፈሰና ያንን ቤት መታው፣ ገፋው ቤቱም ወዲያውኑ ወደቀ፤ አወዳደቁም እጅግ የከፋ ሆነ» በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን ማስጠንቀቁን ልብ የሚል ልብ ይበለው። ፈለጉን የተከተለው ጳውሎስ በገላትያ 1፡6-8፣ «ከክርስቶስ ጸጋ እንዲህ ፈጥናችሁ መለየታችሁና ወደ ሌላ ወንጌል መሄዳችሁ ያስደንቀኛል። ይህንን ያልሁት ግራ የሚያጋቡአችሁና የክርስቶስን ወንጌል ለመለወጥ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች ስላሉ ነው እንጂ ወንጌልማ በመሠረቱ አንድ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክም እንኳ ቢሆን እኛ ከሰበክንላችሁ የተለየ ሌላ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» ማለቱን ልብ የሚል ልብ ይበል። እንግዲያስ ለመድረስ፣ ለመተርጎም፣ ለማስመስገንም ሆነ ለማተም ከመፋጠናችን በፊት፣ መልእክቱ ከሕያው ቃሉ ጋር ይስማማልን?» እንበል።

ቀልባችን አጋንንት ላይ ያልሰፈረበት ምክንያት

ከስሜታዊነት ነጻ ሆኖ ለቃሉ ታማኝ በመሆን «አጋንንትን የማስተናገዱን» አካሄድ በአግባቡ የገለጹት የግሌ ወዳጅ ሮበርት ቲም ናቸው። ብዙዎች አጋንንትን ማውጣት ያስፈለገበትን፣ አወጣጡን፣ ደግሞም አገባቡን፣ ምን ብለው እንደ ጻፉ አንብቤ ያለሁ፣ ሄደው ሄደው ዳር ሊደርሱ ሲሉ የቃሉን ሳይሆን የራሳቸውን በማለታቸው ብዙዎቹን ቸል ብያቸዋለሁ።

* * *

ጥንቁቁ ጸሐፊ ሉቃስ በወንጌሉ ውስጥ አርባ ሦስት ጊዜ በመደጋገም አጽንኦት የሰጠበት ጉዳይ «የእግዚአብሔር መንግሥት» ነው። በሃያ አራቱም ምዕራፎቹ በግልጽና በስውር ስለዚህ መንግሥት ባሕርይ፣ ስለ ተጠቃሚዎቹ፣ ስለ አመሠራረቱ፣ ስለ አመጣጠኑ፣ ስለ መተላለፉ ሁሉ በወግ በወግ ዘርዝሯል። በዝርዛሮውም መንግሥቱ እየመጣች ስለ ነበር የንስሐን ጥሪን በመሃላቸው ስለ ተገኘች መግዛትን፣ ተቃውሞ ስለ ገጠማት መቋ ረጧን፣ ስለምትመጣም ጥበቃን አብራርቶበታል።

እንግዲህ አጋንንት የማውጣት አስፈላጊነት ምላሽ በእግዚአብሔ ር መንግሥት በመሀል ከመገኘት ምሥጢር ጋር ለማገናዘብ፣ ቀድሞ መሠረትን የሚጥልልኝ የተስፋዎች ሁሉ የመጀመሪያው የሆነው ዘፍጥረት 3:15 ነው። «በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነት እንዲኖር አደርጋለሁ፤ የእርሷ ዘርና የአንተ ዘርም ዘወትር ጠላቶች እንደ ሆኑ ይኖራሉ፤ የእርስዋ ዘር የአንተን ራስ ይቀጠቅጣል፣ አንተም የእርስዋን ዘር ተረከዝ ትነክሳለህ» ይላል። ይህ ቃል ኪዳን በሰዎች ታሪክ ውስጥ ተገላጭ ሆኖ ምላሹ ሙሉዓት ሊያገኝ የቀ ረበበት ዘመን የመጪሁ ወደዚህ ዓለም መምጣት ነው፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መፀነስ፣ መወለድ፣ ማደግ፣ አገልግሎትን መጀመርና ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ጋር መፋለሙ ትኩረት ተሰጪው ነጥብ ነው። ፍልሚያው ያመጣበት ሁነኛ ጉዳይ እውነተኛ፣ ወቅታዊ እና በወሳኝ ምላሽ የሚገለጥ ስለ ነበር፣ የመልእክቱ አጽንኦት በተአምራቱ ተገልጾ ታየ፤ በነቢዩ እንደ ተጻፈውም፡- «*በዚያን ጊዜ ዕውሮች ይያሉ፣ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ አንካሳዎችም*

እንደ ሚዳቋ ይዘላሉ፣ መናገር የማይችሉ ድዳዎች ይዘምራሉ» (ኢሳ. 35:5-6) ተብሎ እንደ ተጻፈው ሆነ።

ይህ ድርጊት በምስክሮች ሁሉ ፊት በኢየሱስ እጅ ተከወነ። የኢየሱስ ልዑልነት በተፈጥሮ፣ በሞት፣ በበሽታ፣ በመናፍስት ሁሉ ላይ ገነነ። ይህንንም ያስተዋሉት በአንድነት የሰጡት ምስክርነት «ጋኔኑም ከወጣለት በኋላ ድዳው ሰው ተናገረ፣ ሕዝቡም እንዲሁ ያለ ነገር በእስራኤል ከቶ ታይቶ አይታወቅም» እያሉ ተደነቁ (ማቴ. 9:33) የሚል ነበር።

ይህ አካሄድ ግን ከመሪዎቹና ከሕዝቡ አንቀበልም ባይነት የተነሣ እንቅፋቶች ገጥመውታል። ሕዝቡ በተለያየ ወቅትና ቦታ ኢየሱስን ወደ ክልላቸው እንዳይደርስ ተከላከሉ፤ በየጎጡ የቤተ ክህነቱ ዋነኞች አገልግሎቱን በመንቀፍ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ቀዳሚ ሆነው፣ በፊት ለፊት ተቃወሙት፡፤ ኢየሱስ የመጣበት ዓላማ የተዛነፈ እንዲመስልም ጣሩ። የዚህ ጥረታቸው ድንበርም ኢየሱስ በዚያ በአጋንንት እሥራት ውስጥ የነበሩትን ነጻ እያወጣ መዝለቁን ላለመቀበል፣ አጋንንትን በአጋንንት ኃይል እንደ ሚያወጣ ተነጋገሩበት፣ «እርሱ አጋንንትን የሚያስወጣው በአጋንንት አለቃ አማካኝነት ነው፤» (ማቴ. 9:34) በማለት ፈሪ ሳውያኑ ተናገሩ። ለዚህ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ምላሽ ይቅርታ ስለማያገኘው በደል መግለጽ ነበር፡-

> «ስለዚህ ሰው የሚያደርገው ማናቸውም በደል ወይም የስድብ ቃል ሁሉ ይቅር ይባልለታል። እላችኋለሁ፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሰው ግን በደሉ ይቅር አይባልለትም። በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሰው በደሉ ይቅር ይባልለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ ግን በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም» (ማቴ. 12:31-32)፤

በማለት አገልግሎቱን ለማዋረድ፣ ላለመቀበልና ለማስወገድ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በማየት በተአምራት አመልካችነት እየመጣች ባለችው የእግዚአብሔር መንግሥት የሚነግሠው ኢየሱስ መንግሥቱን ላይመሠርት፣ እርሱም ላይነግሥ እንዳለው

ታየ። ይህም ንጉሥነቱ ሳይሆን፣ ሞቱን ሊያመጣ እንደሚችል ተገለጠ፤ እናም የእግዚአብሔር መንግሥት መሢሑን አክርረው ከመቃወማቸው የተነሣ ፈዘዘች።

በዚህ የኢየሱስ ገለጻ ሰይጣን ሰይጣንን የሚያወጣው ከሆነ፣ መንግሥቱ መለያየቷን ልታውቁ ነው የሚገባው፤ ይልቅስ፣ በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ ኢየሱስ የበላይ የሆነበት ዋና ምክንያቱና አጋንንቱንም ማስወጣት ያስፈለገው «የእግዚአብሔር መንግሥት» ለመምጣቷ ምልክት እንደ ሆነ ነገራቸው።

«እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች ማለት ነው» (ማቴ. 12፡28) አላቸው። ይህም የኢየሱስን አምላክነት፣ ብቸኛ መሢሕነቱን እና ሁሉን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሠሪነቱን አወጀ። ኢየሱስ ከአጋንንት እሥራት ነጻ ማውጣቱ ያ የተጠበቀውና ሊቀበሉት የተገባው እርሱ ብቻ መሆኑን ለመግለጽ፣ እንዲሁም እንደ ቃል ኪዳኑ የዳዊት ዙፋን የባለቤትነቱ ምንጭ እርሱ መሆኑን በመጠቆሙ ተአምሩ ፍሬያማ ነበር።

ሐዋርያውም በገላትያ መልእክቱ 4፡4 የገለጸው ቁም ነገር፣ «ጊዜው ሲደርስ» እግዚአብሔር አንድ ልጁን መላኩ ነው፤ የጊዜው መድረስ መገለጫ ከሆኑት አንዱ በዘመናት ሁሉ ውስጥ በሁሉ ላይ ኢየሱስ ያለውን የሰይጣንን ሥራ በማፍረስ መገለጥ ነበር። ይህም አጋንንት ከያዙአቸው ሰዎች ሁሉ በሥልጣኑ በማስለቀቅ ሊገለጥ ስለ ተገባው ይህን ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ፈጸመው።

የእግዚአብሔር መንግሥት መባቻነቱንም በአግባቡ ለማብሰር፣ መሢሕነቱንና ሕያውነቱን ለማሳየት የተልዕኮ ባለቤት ያደረጋቸውን አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት (የአስቆሮቱን ይሁዳንም ጭምር) በእስራኤላውያን ሁሉ ዘንድ እየደረሱ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቷን እያበሰሩ በአጋንንት የታሰሩትንም ነፃ እያወጡ እንዲዘልቁ ላካቸው።

> *«አሥራ ሁለቱን ጠርቶ አጋንንትን የማውጣትና ደዌን ሁሉ የመፈወስ ኃይልና ሥልጣን ሰጣቸው፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ለሰው ሁሉ እንዲነግሩ በሽተኞችን እንዲፈውሱ ላካቸው» (ሉቃስ 9፡12፤ ማቴ. 10፡1) ይላል።*

እነርሱ የመሢሑን መምጣት የሚገልጸውን ብስራታዊ መልእክት አጋንንትን በማውጣት አደረሱ፣ ተመልሰው በእስራኤል ሁሉ ለመድረስ ቁጥራቸው ትንሽ ስለ ነበር የመልእክት ለውጥ ሳይኖር ሌሎች ሰባ ደቀ መዛሙርት ተመርጠው ድውያንን እንዲፈውሱ፣ መንግሥቱ ቀረበች እንዲሉና አጋንንትን ከሰዎች እንዲያወጡ ታዘዙ (ሉቃስ 10፡1)። እንደ ተላኩትም፣ ውጤታማ ሆነው ሲመለሱ የእነርሱ የደስታ መሠረት አጋንንት እየታዘዙ መውጣታቸው ብቻ ሆነ፤ ይህ ግን ለላካቸው እንደ ምልክት እንዲያገለግል የተፈለገ ጉዳይ እንጂ ዋነኛ አለመሆኑን፣ *«ነገር ግን ስማችሁ በሰማይ መዝገብ ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ እንጂ አጋንንት ስለ ታዘዙላችሁ አትደሰቱ» (ሉቃስ 10፡20) በማለት የተሻለውን አሳየቸው።*

በዚህም በክርስቶስ የዳግም ልደት ባለቤት መሆን ብቻ ከሁሉ እንደሚበልጥ መግለጹ ነው። የማንም ስም በሕይወት መጽሐፍ መገኘቱ የሚያስገኘው ውጤት አለ፣ ዲያብሎስን የማሸነፍ አቅምን፣ በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ እና የመሞላቱ ሀብትን (ዮሐ. 4፡4፤ ኤር. 5፡18)፣ ቃሉን የመረዳት ምሥጢርን (ዮሐ. 8፡32) ያሰጣልና፣ እውነተኛ ደስታስ በዚህ ሊሆን እንደሚገባው አስረዳቸው፤ በዚህም አጋንንትን ማስወጣት ምራቂ እንጂ ዋና አለመሆኑን በመግለጽ አኮ ሳመነው።

ጌላም ቤተ ክርስቲያን እየደረጀች ለመሄድ መሠረቷን በምታጠናክርበት ወቅትም የቃሉ እውነተኛነት ጽኑ መሆኑን፣ የክርስቶስም የደኅንነት ሥራ ብቸኛ መፍትሔ መሆኑን እስኪወጣ ድረስ እግዚአብሔር ተአምራቱን በሐዋርያቱ መግለጹን አዘለቀ፤ *«እኔ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኔን የሚያስረዱት ነገሮች እኔ በመካከላችሁ ሳለሁ በትዕግሥት የፈጸምኳቸው ሥራዎች ናቸው፤ እነዚህም ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች ተአምራትም ናቸው፤» (2ኛ ቆሮ. 12፡12) በማለት ጳውሎስ ተፈላጊነታቸው ለዚህ ብቻ እንደ ነበር ገለጸ።*

እንግዲህ አሳቤ እንዳይበተን እስካሁን ለማለት የፈለግኩትን ሰብሰብ ላድርግና ልቀጥል።

ሀ. የዘፍጥረት 3፡15 ቃል ኪዳን ሊፈጸም እንዳለው ለመግለጽ

አጋንንትን አስወጣ፣ አስወጡም።

ለ. በኢሳይያስ 35:5 የተጠበቀው አድራጊ መሢሕ መምጣቱን ለማስተዋወቅ ሰዎች ከአጋንንት እሥራት ወጡ።

ሐ. ማቴዎስ 12:28 የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቱን ለማሳወቅ ሰዎች ከአጋንንት እሥራት ነጻ ወጡ።

መ. 2ኛ ቆሮንቶስ 12:12 የሐዋርያቱ መልእክት ሰማያዊ መሆኑን ለማሳወቅ ከአጋንንት ነጻ ማውጣት አስፈለገ።

ሠ. ሉቃስ 10:20 የደስታ ጣራ ዳግም ልደት እንጂ፣ ከአጋንንት ነፃ ማውጣት አለመሆኑን ለመግለጽ አጋንንት አወጡ።

* * *

አጋንንት በማውጣት ጉዳይ ላይ ቀልባችንን ሊወስዱ የማይገባቸው ተከታታይ ጉዳዮችን እነሆ፦

በሉቃስ 4:16-21 ያለው መልእክት ሲመጣን ኢየሱስ ጥቅሉን ተርትሮ ያነበበው ክፍል በኢሳይያስ ስለ እርሱ የተጻፈ ክፍል ነበር፤ «... መልካም ዜናን ለድሆች እንዳበስር ሾሞኛል፤ ለታሠሩትም መፈታትን፣ ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅና የተጨቆኑትንም ነጻ እንዳወጣ ልኮኛል» ካለ በኋላ፣ ጠቅልሎ ተቀመጠ። «እነሆ ይህ አሁን ሲነበብ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ» አላቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ «ዛሬ ተፈጸመ» ካለለት ጉዳይ አንዱ በአጋንንት ለታሠሩት መፈታትን መስጠቱ ነው። በነቢዩ የተባሉለት ሁሉም በአገልግሎት ወቅት በሙሉዓት ተከናውኗል፤ ፈጻሚው እርሱ መሰከረ፤ ኋላም ሐዋርያቱ እርሱን ወክለው የፈጸሙት ተመሳሳይ ሥራ በኢየሱስ ስለ ኢየሱስ ብቻ ሊገለጽ የተገባው መሆኑን ያስረዳል።

* * *

በሉቃስ 7:18-23 ያለው ደግሞ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን በመጠርጠር የገዛ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ኢየሱስ በመላክ፣ «ይመጣል የተባለው መሢሕ አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ?» በማለታቸው፣ የሰጠው ምላሽ እኔ እንዲህ ነኝ ማለቱን በመተው፣ በዚያው ሰዓት፣ «ሰዎችን ከልዩ ልዩ በሽታና ደዌ ፈውሶ ርኩሳን

መናፍስትንም አስወጣ፣ የብዙ ዕውሮችንም ዓይን አበራ።» ከዚያም ለመልእክተኞቹ ያያችሁትን ንገሩት አላቸው፣ በዚህ ድርጊቱ የኢየሱስ ሁነኛ መልእክት በነቢያት እንደ ተጻፈው፤ የመሢሑን ማንነት የሚገልጹትን ተአምራት እርሱ ብቻ እየፈጸመው እንዳለ አመላከተ። የእርኩሳን መናፍስት መውጣትም ለዚሁ ጉዳይ ተፈላጊ መሆናቸውን አጣቆመ።

* * *

ማርቆስ 3:11-12 እንዲሁም **ሉቃስ 4:35ን** በጥምረት ብንመለከት፣ ርኩሳን መናፍስት ኢየሱስን ባዩ ሰዓት በፊቱ እየተ ደፋ፣ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» እያሉ በሚጮሁበት ጊዜ እንዲወጡ ሳያዛቸው፣ በምትኩ የእርሱን ማንነት እንዳይገልጹ በብርቱ ያስጠነቅቃቸዋል። ከዚህ ስፍራ የሚጠበቀው ቁም ነገር በሁሉ አቅጣጫ ገናናነቱን በመግለጽ፣ በአለማውጣቱም ሥራውን ከዳር የሚያደርስ ብቸኛ እርሱ መሆኑን፣ ሊወጣላቸው የተገባቸውን ደግሞ ከአጋንንቱ ጋር ውዝግብ በመፍጠር እና ሕመምተኛውን ለከፋ ጉዳት በማድረስ ሳይሆን፣ «ዝም ብለህ ከእርሱ ውጣ!» በማለት ምንም ጉዳት ሳያደርሱ እንዲለቁ ማድረጉም በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ «በሥልጣንና በኃይል ርኩሳን መናፍስትን ያዝዛል እነርሱም ታዝዘው ይወጣሉ።» አሰኝተውለታል። እናም ኢየሱስ በአገልግሎት ዘመኑ ርኩሳን መናፍስትን እንዲህ አስተናግዷቸዋል ማለት ነው።

በማቴዎስ 12:43-45 ያለው ክፍል ሲጠን ደግሞ፣ ርኩሳን መናፍስትን ከአንድ ሰው ማውጣት በብቻው በቂ አለመሆኑን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ፣ በትምህርቱም ከአጋንንት አሥራት ነጻ የወጣው ሰው በክርስቶስ በመሆን የዳግም ልደት ባለቤት ካልሆነ፣ ያ ሰው ዳግም ከእርሱ በወጡት አጋንንቶችና ሌሎችም ታጉረውበት ሊያሠቃዩት እንደሚችሉ ነገራቸው። ሲጨርስም፣ «በዚህ ዘመን ሰዎችም ላይ የሚሆነው ይህንኑ የሚመስል ነው» በማለት ደመደመ። ይህም የሚነገረን ቁም ነገር፣ ከአጋንንት እስራት ሰዎችን ነጻ ለመውጣት ከማተኮር፣ ክርስቶስ ለሰው ልጆች የመጣበትን፣ የሞተበትን ብስራት በኃይልና በሥልጣን መግለጽ ብቸኛው ጉዳይ እንደ ሆነ ያበስራል። ጳውሎስ በሮሜ 1:16፣ «እኔ በወንጌል ቃል አላፍርም ምክንያቱም የወንጌል ቃል በመጀመሪያ

አይሁዳውያንን ቀጥሎም አረማውያኑን ሰዎች ሁሉ ማዳን የሚችል የእግዚአብሔር ኃይል ነው» በማለት፣ ሁሌም የሚቀድመው በአጋንንት ላይ መሠልጠን ሳይሆን፣ በወንጌል የምስራች ቃልና በእግዚአብሔር ኃይል ላይ መቆምን ያሳውቃል። ይህ ሲሆን በአጋንንት የታሠሩ ሰዎች ቢኖሩ ያለ ጉዳት፣ በዝምታ ለቅቀው ወጥተው ለእግዚአብሔር ልጅነት በበቁት ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ፈጥኖ ይሠራል።

* * *

በሉቃስ 8፡26-39 የሚተነትንልን ቁም ነገር በአጋንንት እሥራት ተይዞ የነበረው ሰው በክርስቶስ ነጻ መሆኑና እርሱን ለመቀበል መፈቀዱን ይናገራል።

ታማሚው ድኖ ራሱን እንዳወቀ የጠየቀው ጥያቄ፣ «እባክህ ልከተልህ» የሚል ነው። የኢየሱስ ምላሽ፣ «ወደ ቤትህ ሂድና እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ ተናገር» የሚል ነበር። የተፈዋሹ ምላሽ ታዛዥነት ስለ ነበር፣ «ኢየሱስ ያደረገለትን ትልቅ ነገር በከተማው ሁሉ መናገሩን» (ቁጥር 39) ያበስራል።

ይህ ሰው የሆነለት ተአምር ያረማመደው የክርስቶስ ተከታይ ወደ መሆን ነበር - ወደ መዳን። የደኅንነት ምሥጢር በሰው ውስጥ ሲከሠት ደግሞ ተከታይነትን እንጂ ሽሽትን አይጋብዝም። ከዚህም የሚጠበቀው ዐቢይ ጉዳይ የሰዎች ጥረትና ጉጉት ከአጋንንት እሥራት ሰዎችን በመፍታት እዚያው ጋ ለመቆም ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ኃይል የሚሰጠው ሥራ ለዳግም ልደት ምክንያት ሊሆን የተገባው መሆኑን ማስመር ነው። ከዚህ ውጭ የሆነ ነጻነት ውሎ አዳሪ ባርነትን ስለሚወልድ ፋይዳ - ቢስ ነው።

እንግዲህ ለጊዜውም ቢሆን እንዲህ በማለት ላጠቃልል። ትኩረታችን፦

ሀ. በዋናው ጉዳይ ላይ እንጂ፣ በምራቂው ላይ አይሁን። ዋናው የሰውን ሙት መንፈስ ሊቀሰቅስ የሚችለውን የክርስቶስ የጸጋ ወንጌል መስበክ ነው። ያ ሲሠራ እግዚአብሔር መበርከቱን አት ረፍርፎ ለወደዳቸው ሁሉ ያደርሳል (ሮሜ 1፡16)።

ለ. ክርስቶስ ራስ የሆነላት ቤተ ክርስቲያንን በማነበር ሳለች የምትጠባበቀው ዐቢይ ነገር ሁከትን፣ ጩኸትን፣ አልያም ቅጡን

አጥቶ የሚያሳክረውን «የመንፈስ ሥራ» መመልከትን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ልዑልነት በሁሉ ላይ ተገላጭ ሆኖ እርሱ በገዛ ፈቃዱ እንደ ፍላጎቱ እንደ ዓላማው ሁሉን ሊፈጽም መቻሉን ማመን ነው። እናም በአጋንንት የተያዙ ወደ ጉባዔ ብቅ ቢሉ፣ ገንዘቡ ሊያደርጋቸው ከወደደ ቃሉ ልባቸውን አፍርሶ በጸጥታ ያለ ሐሰት ገንዘብ ሊያደርግ መቻሉን ማመን ተገቢ ነው።

ሐ. የእግዚአብሔር መንግሥት እና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ምስስል ያላቸው ቢመስሉም፣ አንድ አለመሆናቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ሉቃስ እስራኤላውያን የሚጠባበቁትን መንግሥት መምጣትዋን ያስተውሉ ዘንድ ድውያን ተፈወሱ፣ ሰዎች ከአጋንንት እሥራት ነጻ ወጡ፣ እነዚህ ግን የመጣላቸውን መሢህ በማስወገድ ሰቀሉት። እነሆ፣ መንግሥት ተላለፈ፣ ከመተላለፉም የተነሣ ያኔ ለመምጣቱ ምልክት የሆኑ ዛሬም በምልአት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉ እንዳለ ይሁን ቢባል ዓላማውን እና ምክንያቱን ያሳክራልና ሁለቱን በአግባቡ መለየት ተገቢ ነው።

ሔዋን የቀየሰችው መንገድ

የስሕተት ትምህርት በተነሣ ቁጥር የማስታውሰው አንድን ሰው ብቻ ነው፣ ሔዋንን። እርሷ ለስሕተት ትምህርቶች ሁሉ ቁንጮ ናት። የእርሷ ጥፋት በዘመናት ውስጥ ዓይነቱን ሳይቀይርና ሳይሻሻል ቀጥሏል። ይህን ጊዜ፣ «በውኑ ሔዋን ምን ፈጸመች?» የሚል ጥያቄ ይነሣል። ይህ ጥያቄ መልስ ይሻል። ሔዋን የፈጸመችው የጌታን ሕያው ቃል በገዛ ፍቃዷ ጨመረች፣ በራሷ አሳብ ቃሉን ቀነሰች፣ እንደ ፍላጎቷ በቃሉ ላይ ማሻሻያ አደረገች። መቼ? ድሮ ድሮ። እንግዲህ ይህ ብቻ ነው እርሷን ከስሕተት ጅማሬ ጋር የሚያሳስበኝ፡- በሚከተለው መረጃ ልል የፈለግኩትን ይመልከቱልኝ።

- እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡-
- «... ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካሙንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፣ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን

ትሞታለህ...» (ዘፍጥ. 2፡17)።

* * *

- ለሔዋን ከፈታኙ ይህ ጥያቄ ተከተለ፡-
- «...ሴቲቱንም በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት...» (ዘፍጥ. 2፡1)።
- በጥያቄው መሠረት ሔዋን የሰጠችው ምላሽ የሚከተለው ነው፡-

  «ሴቲቱም በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፣ ነገር ግን ከገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ እግዚአብሔር አለ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም...» (ዘፍጥ. 3፡2)።

ንጽጽሩን እንቀጥል፤ እግዚአብሔር ባዘዘው በቃሉና እርሷ በመለሰችው ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት እንመልከት፡-

ሀ. እግዚአብሔር ዛፊቱን በእጃችሁ አትንኩት አላለም፤ እርሷ ግን አለች። ይህም በቃሉ ላይ መጨመሯን ያረጋግጣል።

ለ. እግዚአብሔር ዛፊቱን ሲያስተዋውቅ፣ «ክፉውንና መልካሙን ያስታውቃል» ብሎ ነበር፤ እርሷ ግን ይህን ተወችው፤ ይህም ከቃሉ እንደ ቀነሰች ያረጋግጣል።

ሐ. እግዚአብሔር እንዳይበሉ ያዘዛቸውን ዛፍ አካባቢ አልገለጠም፤ እርሷ ግን በገነት መካከል ካለው በማለት ቃሉን እንዳሻሻለች ያረጋግጣል።

እንግዲህ ሔዋንን የሚያስነቅፋት እግዚአብሔር በማያሻማ ሁኔታ አሳቡን በቃሉ ሲገልጽላት፣ ከእርሷ የሚጠበቀው መታዘዝና እግዚአብሔርንም ማመን ወይም አለመጠራጠር ነበር። እርሷ ግን በእግዚአብሔር መልእክት ላይ ጨመረች፣ ቀነሰች፣ እንዲሁም አሻሻለች። ይህ አሠራር ነው ጥንትም ዛሬም የስሕተት ትምህርትን በዓለም ላይ እያስተናገደ ያለው፡- መፍትሔው ቀላል ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል እግዚአብሔር እንዳለው መረዳት፤ ማለትና ማድረግ ብቻ ነው።

* * *

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከሆኑት ውስጥ ዮሐንስ በሁለተኛው መልእክቱ ይህን ጽኑ ማሳሰቢያ አስከተለልን፡- «በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የማይኖርና ከእርሱም ርቆ የሚሄድ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የለም፤ በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የሚኖር ሰው ግን

አብና ወልድ ከእርሱ ጋር አሉ» (2ኛ ዮሐንስ 9)። ዮሐንስ ይህን ዋንኛ የሐሰት አስተማሪዎችን የመለያ መስፈርት ለሁል ጊዜው ሲሰጠን፣ በዘመኑ፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሥጋ አልተ ገለጠም» በማለት የሚያስተምሩ መናፍቃን ገጥመውት ነበር (ቁ. 7)። ግና ክርስቶስ ስለ ራሱ ምን አስተማረ? የዚህን ምላሽ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ነው የምናገኘው። በ1ኛ ዮሐንስ 2፡23፣ «ወልድን የሚክድ አብ የለውም፣ በወልድ የሚያምን በአብ ያምናል» ይላል። ይህን ጥቅስ ያስመረጠኝ የስሕተት አስተማሪ ዎች፣ ሁሉም ማለት ይቻላል፣ የሚናኙትና የትምህርታቸው ማዕ ከል የሚያደርጉት «ኢየሱስ ክርስቶስ» ነው። ክርስትና ገና አንደኛ መቶ ዓመቱን ሳያከብር ኖስቲስቶች፣ «አምላክ ርኩስ በሆነው ዓለም ሥጋ ለብሶ በሰው ውስጥ በማደር በአካል አይገለጽም» በማለት ቃሉን ሽረው ተነሡ፤ ሥጋ መልበሱን፣ ፍጹም ሰው ሆኖ በምድር የመመላለሱን ታሪክ ሐሰት ነው በማለት የራሳቸውን የማሻሻያ መመሪያ አጸኑ።

* * *

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመንም «አርዮስ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት አንቋሸሸ፣ ካደም።» አትናሺየስ ግን ልክ እንደ ዮሐንስ እስከ ፍጻሜው ተቃወመው፤ በቃሉም እውነት ረታው። ጳውሎስ አርዮስን ስለ ወከሉት ሐሰተኞች እንዲህ በማለት ማስጠንቀቂያውን ያጠናክራል፣ «...ይህንንም ያልሁት ግራ የሚያጋቡአችሁና የክርስቶስንም ወንጌል ለመለወጥ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች ስላሉ ነው እንጂ ወንጌልማ በመሠረቱ አንድ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መላእክትም እንኳ ቢሆኑ እኛ ከሰበክንላችሁ የተለየ ሌላ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን...» ይላል (ገላትያ 1፡7-8)።

ገለጻዬን በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን እንዴት በሔዋን የተጀመ ረው ጥፋት ሂደቱን ቀጥሎ በ1ኛ ዮሐንስ 4፡1 መሠረት፣ «ወዳጆች ሆይ፣ በዓለም ላይ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት ስለ ተነሡ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ይልቅስ...መርምሩ» ያለበትን በሁለት የተለያዩ እምነቶች ላይ ፍተሻ ላድርግ፣ እናንተም ዳኙ፡-

መጽሐፍ ቅዱሳውያን	ርእሰ ነገር	በቃሉ ላይ መቀነስ፣ መጨመር ወይም ማሻሻል ያደረጉ ካቶሊካውያን
66ቱን መጻሕፍት ብቻ የሕይወትና የተግባራቸው መመሪያ ያደርጋሉ (2ኛ ጢሞ. 3:16-17፤ ዘዳግ. 12:32)	መጽሐፍ ቅዱስ	በ66ቱ መጻሕፍት ሳይወሰኑ ሌሎች መጻሕፍትን ይጨምራሉ፣ የሽማግሌዎችን ወግ የሕይወት መመሪያ ያደርጋሉ፣ ለቤተ ክርስቲያን የጎላ ሥልጣን ይሰጣሉ (ማቴ. 15:1-9)
መጽሐፍ ቅዱስን ደራሲው መንፈስ ቅዱስ ሊተ ረጉምላቸውና ሊያብራራላቸው እንደሚችል ብቻ ያምናሉ (1ኛ ዮሐ. 2:27፤ ሮሜ 15:4፤ ዮሐንስ 14:26)	የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም	የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም የሚሰጡት ወይም የሚወስኑት የቤተ ክርስቲያኒቱ ጳጳስ ወይም ቤተ ክርስቲያኒቱ ብቻ ነች።
ወደ እግዚአብሔር አብ የመቅረቢያ ሁነኛ መንገድና አማላጅ ክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ ያምናሉ (ዮሐ. 14:6)።	ወደ አብ አድራሽ እና አማላጅ	ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በጌታ እናት በኩል፣ በመላእክትና በቅዱሳን ሰዎች በኩል ሊቀርቡ እንደሚችሉ ያምናሉ።
እግዚአብሔር ባዘጋጀው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ የዘላለም ሕይወትን ያስገኛልን ያምናሉ (ሮሜ 3:24፤ ኤፌ. 2:8-9፤ ሮሜ 10:4፣10)።	የዘላለም ሕይወት	የዘላለም ሕይወት በእምነት ብቻ ሳይሆን፣ በመልካም ሥራ ሊገኝ እንደሚችል ያምናሉ።
ደኅንነት የሚጸናው ክርስቶስ በሠራው ሥራ ብቻ መሆኑን ያምናሉ (ዮሐ. 3:16፤ ሮሜ 5:18፤ ዮሐ. 5:24)።	ዋስትና	የደኅንነት የመጽናት የአለመጽናት ጉዳይ ዛሬ ሊረጋገጥ አይችልም ይላሉ። ሰው ከሞተ በኋላ ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር እንድትደርስ በሕይወት ያሉ ዘመዶቹ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያወጣቻቸውን ሕግጋት ተግባር ቁርባንና ምጽዋትን፣ አማላጅነትን በማስፈጸም ዋስትና እንደሚገኝ ያምናሉ።

መጽሐፍ ቅዱሳውያን	ክፍል ሁለት ርእሰ ነገር	በቃሉ ላይ መቀነስ መጨመር ወይም ማሻሻል ያደረጉ የመጠበቂያ ግንብ «የጅሆቫ እምነት ተከታዮች»
እግዚአብሔር በመለኮት አንድ በአካል ሦስት መሆኑን ያምናሉ፣ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ (ማቴ. 3:13-17፣ 28:19፣20፤ 2ኛ ቆሮ. 13:14)	እግዚአብሔር	ይሖዋ አንድ አምላክ ነው በሦስት አካል አይታወቅም፣ የሥላሴ ትምህርትም ከሰይጣን ነው በማለት ያምናሉ።
ሰው የማይጠፋ ዘላለማዊ ነፍስ አለው (ዘፍጥ. 1:26፤ 5:1፤ ኢዮብ 32:8፤ 1ኛ ቆሮ. 11:7	ዘላለማዊነት	ሰው የሚጠፋ ነፍስ አለው፤ ይህችም ነፍሱ ከአካሉ ተነጥላ አትኖርም።
ኢየሱስ አምላክ ነው፣ የሥላሴ ም አንድ አካል ነው (ዮሐንስ 1:1፤ ቄላ. 1:15-19፣ 20፤ 1ኛ ዮሐ. 5:7-8)።	ኢየሱስ ክርስቶስ	ኢየሱስ አምላክ አይደለም፤ ይልቅ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው የመጀመሪያው ፍጡር ነው።
ክርስቶስ ኢየሱስ በአካል እንደሚመለስ ያምናሉ (1ኛ ተሰ. 4:16-17፣ ማቴ. 24:30፤ ራእይ 1:7)	ለኃጢአት የተከፈለ ዋጋ	የክርስቶስ ሞት፡- ሰው በሥራው ደኅንነቱን ይፈጽም ዘንድ እንደሚችል የተዘጋጀለት መንገድ እንደ ሆነ ያምናሉ።
የክርስቶስ ሞት ለሰው ልጅ ኃጢአት የተከፈለ ፍጹም ዋጋ መሆኑን ያምናሉ (ሮሜ 3:24፤ 2ኛ ቆሮ. 5:20)።	ትንሣኤ	ክርስቶስ መለኮታዊ መንፈስ ሆኖ ተነሥቷል እንጂ በአካል አልተነሣም።
ክርስቶስ ከመቃብር ሞትን ድል ነሥቶ የተነሣው በአካሉ ነው (ዮሐ. 20:24-29፤ ሉቃስ 24:23)።	የኢየሱስ መመለስ	ክርስቶስ በማይታይ ሁኔታ በ1914 ዓ.ም ወደ ምድር ተመልሷል፣ አሁን ምድርን በመግዛት ላይ ይገኛል።
የዘላለም የቅጣት ስፍራ ለኃጢአተኞች ተዘጋጅቷል፤ (ማቴ. 5:22፤ ሉቃስ 13:24-28፤ 2ኛ ጴጥ. 2:17፤ ራእይ 14:9-11)።	ገሀነም	ገሀነም ወይም የዘላለም የመቃጠል ቦታ የለም፣ ይልቅ እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ደረጃ ያልደረሱ ሰዎች በንነው/ተንነው/ ዳግመኛ ላይታሰቡ ይጠፋሉ።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ለምሳሌ ያህል የተወሰዱ ናቸው። ከእነርሱ ሌላ ብዙ ብዙ እንዳሉ መገንዘብ ይኖርብናል። ያዕቆብ በመልእክቱ በምዕራፍ 1:25 ላይ፣ «...ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹም ሕግ /ቃሉን ማለት ነው/ ተመልክቶ በእርሱ የሚጸና እርሱንም ሰምቶ የማይረሣና በሥራ ላይ የሚያውለው ሰው በሥራው የተባረከ ነው» በማለት የቃሉን ዋነኛነት ያረጋግጥልናል። እንግዲህ እነርሱ የቃሉ ደራሲ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ይህ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ሲገልጥልንና ሲያስተምረን በእኛ ውስጥ አድሯል። ስለዚህ በትሑት መንፈስ ቃሉን ተግተን እናጥና፣ በቃሉ እንደ ተጻፈ፣ «...ማንም በዚህ ቃል ላይ አንዳች ነገር ቢጨምር... ማንም በዚህ የትንቢት መጽሐፍ በተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል...» ወዮለት ብሏል (ራእይ 22:18-19)። እንግዲህ ጌታ እንዳለው፣ «መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ» (ራእይ 2:7)።

የሥነ ፍጻሜው ቅኝት

ከአዲስ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ የጸሐፊው ስም ያልተጠቀሰበት መጽሐፍ የዕብራውያን መልእክት ነው፤ ባይጻፍበትም፣ በርካታ መረጃዎች ጸሐፊው ጳውሎስ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ፤ እኔም እንዲሁ እላለሁ። ዕብራውያን በጳውሎስ ከተጻፈ፣ በአዲስ ኪዳናችን አሥራ አራት የጳውሎስ መልእክቶች አሉን ማለት ነው።

በእነዚህ በርካታ መጻሕፍት ውስጥ የተላለፈው አንኳር መልእክት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካልነቷ አባላቷ ሁሉ ያላቸውን በረከቶች ያውቁት ዘንድ፣ ያላቸውን ኃላፊነት ይረዱት ዘንድ፣ እና በፊታቸው ያለውን ጽኑ ተስፋ ይጠብቁት ዘንድ ያስገነዝባል።

ክርስቲያኖች የሚጠብቁትና የሚጓጉለት ጽኑ ተስፋ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ነው።

ጳውሎስ፣ «...እኛ በሕይወት የምንገኝ ጌታን በአየር ላይ

ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን፤ ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ» (1ኛ ተሰ. 4፡14-18) በማለት ቤተ ክርስቲያንን ያበስራል።

ሊፈጸም ያለው ይህን የመሰለ ተስፋ ሆኖ ሳለ፣ ለምን ይሆን በርካታ ክርስቲያኖች ስለ መጨረሻው ዘመን የማያሳስባቸው? ምላሹ ሁለት ነው። የዘባኞች ተጽዕኖ በአማኞች ዘንድ መስረጉ አንዱ ነው። «ዘባኞቹ ኢየሱስ ይመጣል ተብሎ ተስፋ ተሰጥቶ አልነበረምን? ታዲያ የት አለ? የቀድሞ አባቶቻችን ከሞቱበት ጊዜ አንሥቶ ሁሉ ነገር ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እንደ ነበረው ነው» ይላሉ (2ኛ ጴጥ. 3፡4)። ሁለተኛው፣ ቃለ እግዚአብሔርን በአግባቡ ካለመረዳት የተነሣ የተዛቡ አመለካከቶችን መኖር ትኩረት ሳይሰጡ አልቀሩም። በመጨረሻም፣ የእግዚአብሔርን የመርሐ ግብር አፈጻጸም አለመረዳት የሚያጓጓውን የኢየሱስን ክርስቶስን መገለጥ ቸል ያሰኘዋል።

* * *

በሁለተኛነት ያነሣሁትን የተዛባ ምልከታ በጥቂቱ ላብራራው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ አንዳንዶች ወደ እርሱ ይሄዳሉና፣ የአማኝ ሞቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው ይላሉ። ይህ እሳቤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። አንድ በክርስቶስ ያለ ሰው በሥጋው ሲሞት መንፈሱና ነፍሱ ዘላለማዊ ናትና ወደ ፈጣሪዋ ትመለሰላች፤ ሥጋው ግን በምድር ይቀራል፤ ይህም በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡16-17፣ «ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል፣ በክርስቶስ አምነው የሞቱትም አስቀድመው ይነሣሉ...» በማለቱና፣ ኢየሱስ «...እኔ ባለሁበት እንድትኖሩ እንደ ገና መጥቼ እወስዳችኋለሁ» ማለቱ፣ እናንተ ወደ እኔ ትመጣላችሁ የሚል ፍቺን አይዝም፣ ቀጥተኛው ትርጓሜ እኔ ወደ እናንተ እመጣለሁ ማለት ነው። ከዚህም የተነሣ፣ ሞትና ዳግም መመለስ ግንኙነት የላቸውም።

ሌሎች ደግም፣ «የመንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ መምጣት ዳግም ምጽአቱ» ነው ይላሉ። ይህ ኢየሱስ ያስተማረውን ትምህርት ይጣ ረሳል። ራሱ «አጽናኝ እንዲመጣ እኔ ብሄድ ይሻላችኋል» ብሏል። ይህ ግን ራሱ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ በመሆን መምጣቱን አያሳይም፤ ይልቅስ፣ ስለ ኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት በዓለ ሃምሳ

ከሆነ በኋላ ፊልጵስዩስ 3:21፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4:81፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 4:16፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:51 ተጽፎ ይገኛል። ዳግም መምጣቱ በበዓለ ሃምሳ ዕለት ቢፈጸም ኖሮ፣ ኋላም ስለዚህ ጉዳይ ባልተነገረን፣ ባልተጻፈም። የቀሩት ደግሞ፣ «የኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም መደምሰስ የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ነው» ይላሉ። እርግጥ፣ የኢየሩሳሌም የመደምሰስ ታሪክ ብዙ ትንቢቶችና የአዲስ ኪዳን አስተምህሮዎችን በአግባቡ እንዲጤኑ ረድቷል-ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም አለቀሰ፣ ያለቀሰው ያለ ንስሐ በድንዳኔ የመዝለቋን ታሪክ አይቶ ነበር፤ «ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርም» እንዳለውም፣ በጊዜው በታይተስ መሪነት ቤተ መቅደሱ እንዲፈርስ፣ ሕዝቡም እንዲበተን ሆኗል። ይህ ሆነ ማለት ግን ኢየሱስ ዳግም ከያኔ ጀምሮ መጣ ማለት አይደለም። በዮሐንስ 21:21-23፣ እንዲሁም በራእይ 22:20፣ «ኢየሱስ...በቶሎ እመጣለሁ» አለ። ዮሐንስ እነዚህን መልእክቶች የጻፈው ከ70 ዓ.ም በኋላ በዘጠናዎቹ አጋማሽ ላይ ነበር፤ በ70 ዓ.ም ላይ ቢሆን ኖሮ፣ የጌታ ዳግም የመምጣቱ ታሪክ ባልተጻፈ ነበር።

የተዛቡ አመለካከቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም፣ በእውነት ላይ ተጫምቶ መነሣት ተገቢ ስለሆነ፣ በጥንቃቄ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ለመመስከር ሦስት ወገኖችን ላሳያችሁ።

ለዚህ ሁነኛ ጥቅሴ 1ኛ ቆሮንቶስ 10:32 ነው። «...አይሁዳውያንንም ቢሆን፣ ግሪካውያንንም ቢሆን፣ የእግዚአብሔርም ቤተ ክርስቲያንን ቢሆን ማንንም አታሰናክሉ።» ሦስቱ ወገኖች እነዚህ ናቸው። አይሁዳውያን፣ እስራኤላውያን፣ ግሪካውያን (አሕዛብ)፣ እኛ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጻቸው ስለ አይሁዳውያን የተበተኑ፣ የተሰደደዱ፣ የታወሩ ሕዝቦች መሆናቸውን ይዘክራል። ለዚህም ጽኑ መረጃው ዘዳግም 28:58-68 እንዲሁም ሮሜ 11 ነው።

እስራኤላዊ ያልሆነውን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ አሕዛብ (ግሪካውያን) በማለት ይጠራቸዋል።

በሦስተኛነት የሚያነሣው ክፍል በክርስቶስ ሥራ የተመሠረተችውን ቤተ ክርስቲያንን ነው። በእርሷ ውስጥ ያደሩት እስራኤላውያን ወይም አሕዛብ ብቻ አይደሉም፣ ሁለቱንም በአንድነት

በክርስቶስ በመጥራት ታገለግላለች።

እንኪያስ ስለ ሥነ ፍጻሜ ስንነጋገር እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ሦስቱን ክፍሎች ለየብቻ እንደሚያስተናግዳቸው የየራሳቸው ሁነኛ ቃል ኪዳንና የየራሳቸው ጅማሬና ፍጻሜ እንዳላቸው መረዳት ተገቢ ነው። ይህም የአንዱን ለሌላው ላለማወራረስና ላለመቀየጥ ይረዳናል።

ለምሳሌ፣ ከሦስቱ የመጨረሻውን ቤተ ክርስቲያን አንሥተን ብንመለከት፣ ሁለት የስም አንድነት ያላቸው ቤተ ክርስቲያናትን እናያለን፤ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያንና ሐሰተኛ ቤተ ክርስቲያን። የእውነተኛዋ መለያዋ አንድ ነው፤ ክርስቶስ እንዳለው የገሀነም ደጆች የማይቋቋሟት፣ በዘመናት ውስጥ በመዝለቅ ሳትጠፋ የኖረች፣ የቃሉን እውነት በመታዘዝ የምትኖር የትኛዋም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እርስዋ እውነተኛ ናት።

ሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የእውነተኛዋን ቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ መንገድ ይዛ ትጓዛለች። መሠረቷ ክርስቶስ አይደለም፤ ትምህርቷ ወግና ቅይጥ ነው፤ በሕያው ቃሉ ላይ መጨመር፤ መቀነስም ሆነ ማሻሻል የዘወትር ተግባሯ ነው። 1ኛ ጢሞቴዎስ 4:1 ላይ እንደተገለጸው፣ «በኋላኛው ዘመን አንዳንድ ሰዎች አሳሳች መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት በመከተል ሃይማኖትን ይክዳሉ» ይላቸዋል። ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስ በ2ኛ ጴጥሮስ 2:1-3:18 ምንነቷን ገልጧል፣ ጳውሎስም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ እንደ ነበር ሲያብራራ፣ ሁለት ዓይነት ወንጌል፣ ሁለት ዓይነት መንፈስ እና ሁለት ኢየሱስ እንዳለ በ2ኛ ቆሮንቶስ 11:4 ዘክሯል። ከዚህም የተነሣ፣ የመጨረሻውን ዘመን የምናጤነው ሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን እንዳለች በመረዳት ነው፤ ይህች ቤተ ክርስቲያን ለሐሰተኛው ክርስቶስ ራሷን የምታዘጋጅና ብዙዎችን የምታስት ነች። ሁሉንም ማስተናገድ ትችላለች፤ ተከታዮቿ ብዙ ናቸው። እንኪያስ የመጨረሻው ዘመን እንደ ቀረበ የምንረዳው ይህ ምልክት በዓለም ዙሪያ እየገነነ ሲመጣ ነው።

በትይዩ፣ ሥነ-ፍጻሜን ለመቃኘት የዓለምን ሁኔታ መመልከት ሌላው ጉዳይ ነው። የዓለም ፖለቲካ አካሄድ፣ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሂደቶች በወጉ ይመረመራሉ። የዓለም መንግሥታት

ጎብረታቸውን በማጠናከር ዓለምን በፈለጉት አቅጣጫ ይመሩ ዘንድ እየጣሩ ነው። በስምምነታቸው ጦርነትን አጥፍተው ሰላምን ለማስፈን፣ መለያየትን አስወግደው አንድነትን ለማምጣት ይጥራሉ፤ ነገር ግን የጥረታቸው አቅጣጫ እየገነነ ሲመጣ፣ ለዚህ ሁነኛ መፍትሔ ሐሰተኛው ክርስቶስ ይሆናል። እርሱ በልዩነት ምክንያት የመጣውን ግጭት ወደ አንድነት የማድረስ መፍትሔን ይዞ ይመጣል። በልዩነትም አንድነት ሊኖር እንደሚችል አግባቢና አዕምሮአዊ መንደርደሪያን ይሰጣል፤ ይህን አሠራር ሁለተኛዋ ዓይነት ቤተክርስቲያን ተሳታፊ በመሆን ታራምዳለች።

ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ በሆነው አካሄድ ዓለም በማቴዎስ 24 ላይ እንደተገለጸው፣ በብዙ ጦርነቶች፣ የምድር ነውጦች፣ ቸነፈሮች መዝለቋ ሁነኛ መረጃ ይሆናል። በዚህ ጽሑፍ ቅኝት እነዚህን በአጭሩ ለማስተዋወቅ እሞክራለሁ።

ከ1970 ወዲህ ታላላቅ ስድስት ጦርነቶች በዓለም ላይ ተካሂደዋል። የቬትናም፣ የፎክላንድ፣ የሊባኖስ፣ የኢራንና ኢራቅ፣ የአፍጋኒስታንና የባሕረ ሰላጤው ጦርነቶች ከፍተኛዎቹ ናቸው። በተለይም የ1991 የባሕረ ሰላጤው ጦርነት በዓለም ላይ ከተካሄዱት ጦርነቶች ሁሉ የመጠቀ እንደ ነበር ተዘክሯል።

የመሬት ነውጥንም በተመለከተ የቅርቡ «የዓለም አልማናክ» እንደ መዘገበው፣ እስከ ዛሬ በዓለም ላይ ከተመዘገቡት 577 ታላቅ ነውጦች ውስጥ 38 የሆኑት በያዝነው ክፍለ ዘመን እንደ ሆኑ አስታውቋል። በትይዩም፣ ከታላላቆቹ ውጭ አናሳ ነውጦች የተ ባሉትን ከ12ኛው ክፍለ ዘመን እስከ ዛሬ የሆኑት በምሳሌነት ሲጠኑ ምን ያህል እንደ ሆኑ መገንዘብ ይቻላል።

በ12ኛው ክፍለ ዘመን 84 የመሬት ነውጥ፣ በ13ኛው ክፍለ ዘመን 115 የመሬት ነውጥ፣ በ14ኛው ክፍለ ዘመን 137 የመሬት ነውጥ፣ በ15ኛው ክፍለ ዘመን 174 የመሬት ነውጥ፣ በ16ኛው ክፍለ ዘመን 258 የመሬት ነውጥ፣ በ17ኛው ክፍለ ዘመን 378 የመሬት ነውጥ፣ በ18ኛው ክፍለ ዘመን 640 የመሬት ነውጥ፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን 2119 ሆኗል። በ20ኛው ክፍለ ዘመንም በጥቂቱ ብናይ፣ ከ1950 እስከ 1975 ባለው እንኳን በመሬት ነውጥ ጊዜ 625,700 (ስድስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ) ሕዝቦች

ሲያልቁ፣ አንድ ሚሊዮን አሥራ አምስት ሺ አምስት መቶ ሕዝቦች የነውጥ ተጠቂዎች ሆነዋል። እንግዲህ ምን ያህል እየመጠቀ እንደ ሄደ ተገንዘቡ።

ቸነፈርም እንዲሁ ነው። ኤድስ በቸነፈር ጎራ ለመመደብ የሚችል የፍጻሜው የጥፋት መንገድ ነው። የዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት (እ.ኤ.አ) ከ1987 እስከ 2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 100 ሚሊዮን ሕዝቦች በኤድስ ሊለከፉ መቻላቸውን ከወዲሁ አርድታ ል። የታይም መጽሔት፣ «እስከ ዛሬ ያልሰማችሁት ጉድ?» በተሰኘ ው ዓቢይ ርእሱ፣ «በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሆኖ የማያውቅ ፈጣን ወራሪ ቸነፈሩ ኤድስ ብቻ ነው፣» በማለት ያብራራል። ለቸነፈሩም መንሥኤ ከሆኑት አንዱ የግብረ ሰዶማውያን (የወንድ ለወንድ ተ ጋቢዎች) ልቅነት በዓለም ላይ በመብትነት ደረጃ እየተስፋፋ መሄድ፣ የጌታን በቶሎ ዳግም መመለስ ለክርስቲያኖች የሚያስረዳ ይመስለኛል።

አሁን ደግሞ በአጭሩ የእስራኤልን ሁኔታ ላብራራላችሁ። በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ከአብርሃም መጠራት ጀምሮ እየሰፋ የምናገኘው ሕዝብ እስራኤል ነው። ይህ ሕዝብ የዓለምን ታሪክ አቅጣጫ ይዞ እንደ እግዚአብሔር መርሐ ግብር መንዙን መለኪያ በመሆን ያሳያል። ከዚህም የተነሣ፣ በመነሻነት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለይቶ ቀርጾ፣ እንደሚመች በማድረግ ለዓለም ሕዝቡ ታማኝ የጌታ ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ ለይቶ ኃላፊነትም ሰጥቶ ያዘልቃቸው ዘንድ ፈለገ። ይህንንም በሕዝቡ መካከል አደረገ፤ በምትኩ ግን ዐመፀኝነት፤ ባዕድ አምላኪነት ተግባራቸው ሆነ፤ በዚህም የሚሆንላቸውንና የሚሆንባቸውን በዘሌዋውያን 26 ላይ ገለጸ፤ ያንንም ሆኑ።

የእስራኤል እምቢተኝነት በብሉይ ኪዳን ሲገኝ፣ እግዚአብሔር እንደ ቃሉ ለባዕዳን ገዢዎች አሳልፎ በመስጠት ቀጣቸው፤ ከምድራቸውም አስወገዳቸው፤ ተመልሰውም በተረጋጉ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ሌላ ዓመፅ አደረጉ። ይኸውም ሊያድናቸው የመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን በመቃወም ሰቀሉት። የዚህም ውጤ ት በ70 ዓ.ም የቤተ መቅደሱ መፍረስ፣ የከተማዋ መደምሰስ፣ የሕዝቦቿ አገር-የለሽ በመሆን መበተን ሆነ። እግዚአብሔር ከዚያን

ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ይጠቀም ዘንድ ወደደ። የእስራኤል የሂደት ጣሪያ የሚሰበስባትን በመፈለግ፣ ሰላምን የሚዘራባትን በመመኘት፣ በዓለም ላይ ገናና ሆና የበላይ የሚያደርጋትን በማሰስ፣ ቤተ መቅደስ የሚሠራላትን ለማመቻቸት ስትጥር ያኔ የመጨረሻው ሰዓት የዳግም ምጽአቱ ወቅት እንደ ደረሰ መለየት ይቻላል። እናም ይህን ዘመን በዚህ መፈተሽ ተገቢ ነው።

እነዚህ ከላይ ያነሣኋቸው ነጥቦች የሚያሳዩን አንድን ቁም ነገር ነው፤ እርሱም እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ፊት ስለ ሠራነው ሥራ በግላችን መልስ የምንሰጥ ስለሆነ፣ ፍሬያማ መሆናችንን ዛሬ እንመርምር (ሮሜ 14:12)። ጳውሎስ እንዲህ ይመክረናል፣ «ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በምንም ነገር አትናወጡ፣ ለጌታ ሥራ የምትደክሙት በከንቱ አለመሆኑን አውቃችሁ ሳታቋርጡ ዘወትር የጌታን ሥራ ለመሥራት ትጉ» (1ኛ ቆሮ. 15:58)። ይህን ቃል ሥራችን እናደርገው ዘንድ ይገባል። የእግዚአብሔር ሰዓት ሲሞላ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣቱ አይቀርም፤ እኛ ግን ተግተን የሰጠንን አደራ እንፈጽም።

ዋቢ መጻሕፍት

Dolan, D. *Holy War for Promised Land*. Nashville, TN, Thomas Nelson Publisher, 2000.

Dyer, C. H. *The Rise of Babylon*, Wheaton, Il., Tyndale House Publishers, 1991.

Evans William. *The Great Doctrines of the Bible,* Moody Press Chicago, 1949.

Goetz William R. *Apocalypse Next,* Moody Press Horizone House Publisher, 2001.

Walvoord John F. *The Return of the Lord,* Zondervan Publishing House, 1995.

ገናን አናግንነው!

አሜሪካኖች የገናን ዛፍ ማስጌጥ የጀመሩት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ነው። ከዛሬ መቶ እና መቶ ሃምሳ ዓመት እነርሱን ቀድመው የገናን ዛፍ በማድረግ ብዙ መቶ ዓመታትን ያስቆጠሩት ግን ጀርመኖች ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ ወደዚህ ደረጃ የደረሱት ኢየሱስን ብለው ሳይሆን፣ ችግራቸውን አስበው ነው-ቅዝቃዜን፣ ውርጭን፣ አጓጉሉን ረኻም የክረምት ወራትን። በዚህ የርጥበት ወቅታቸው ያሏቸው አረንጓዴ ቅጠላ ቅጠሎች ሁሉ ይወድማሉ፤ ያለ መታሰቢያም ይጠፋሉ። በዚህ ቀውጢ የአየር ጠባይ ያንን ጽኑ ውርጭ ተቋቁሞ የሚወጣ አንድ የዛፍ ዘር አለ።

ታዲያ ጀርመኖቹ ለዚህ ዛፍ መትረፍ ዋንኛው ምክንያት ሊያጠፉት የሚመጡትን መንፈሳዊ ኃይላትን የመቋቋም ችሎታው እንደ ሆነ ገመቱ። ሌትና ቀን ሳያቋርጥ የሚሸከረከረውን ክፉ መንፈስ ከተቋቋመው፣ እኛንና ቤተሰባችንን ሁሉ ይህ ዛፍ ከክፉ ሊጠብቀን ይችላል በማለት ዝንጣፊውን ወደ ቤታቸው አስገቡት፣ እንደ መታመኛም፣ እንደ መኩሪያም ይቆጥሩት ጀመር። ቀስም እያሉ ይህንን ዛፍ አስጌጡ። መነሻ ነገሩ ይህ የሆነለት ዛፍ፣ የኢየሱስ ልደት በየዓመቱ ሲመጣ የጥድ ዝንጣፊ ከውጭ ወደየቤቱ እየገባ እንደ ጀርመኖችና እንደ አሜሪካኖች እኛም ዘንድ እየተዘወተረ ከረመ። አሁን እኔ ልጠይቀው የፈለግኩት የገና ዛፍ በውኑ ከጌታ ልደት ጋር ያገናኘው ሁነኛው ጉዳይ ምንድን ነው? መቼም ክርስቲያኖች ነንና ባህልንም ታሪክንም አጢኖ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ማድረግ እንዳለብን አስቀድሜ ለራሴው የዓመት ሥራ ሰጥቼዋለሁ። ይህንንም ማሰቤ እንደ ልማዱ «ገና» ሲመጣ እንዳልሳሳት ብዬ ነው! እናንተም አስተውሉት።

መቼም የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ተጠቅመን የኢየሱስን ልደት ልንዘክር ብለን ከወራት መካከል ነጥቀን የምናወጣው ታኅሣሥን ብቻ ነው፤ እርሱም ከያዛቸው ቀናት ውስጥ ሊሸኘው የቀረበውን የመጨረሻውን ነው ለኢየሱስ የልደት ዕለት የምንመድበው።

ከወዲሁ በዚያን ዕለት ስጦታዎች መለዋወጥ፣ በእነርሱ

መደናነቅ፣ ጣፋጭ ምግቦችን መገባበዝ፣ እንዲሁም «በገና ጨዋታ አይቆጠም ጌታ፣» «ጌታ ተወለደ፣» «*Happy Chrismas*»፣ «*Merry Christmas*» የሚሉ የካርድ ዓይነቶችን መለዋወጥ፣ የገናን ዛፍ አቆነጃጅቶ፣ ከረሜላዎችን ወሻሽቆ ዕለቱን ማሰብ፣ ደቃቅ አምፖሎችንም ብልጭ ድርግም ማድረግ ዓመት በዓመት የሚጠበቅ ትእይንት ነው።

* * *

በኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመምጣት ምክንያት ግን ዕለቱንና ወራቱን የሰቆቃ ወቅት ማድረጉንም ልብ እንበል። መላእክቱ፣ «በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድርም እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ሰዎች ሁሉ ሰላም ይሁን» በማለት ሲያበስሩንና ሲያመሰግኑ፣ ከወራት ወይም ከዓመት በኋላ በቤተልሔም ያሉ እናቶች ሁሉ «ወዮ» ብለው አለቀሱ፤ በምድር ሰላም ሳይሆን ሁከት ሆነ፣ ሄሮድስ በዕለቱ ከተወለዱት ጀምሮ ወደ ኋላ በመመለስ እስከ ሁለት ዓመት የደረሱትን ሕፃናት ሁሉ ፈጀ። በዚህም ምክንያት በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ሆኗል፣ ግና በምድር የኀዘንና የጨለማ ወቅት ነበር።

* * *

ይህ ብቻ አይደለም፣ ኢየሱስ የተወለደ ዕለትም ነው ማርያም ለመውለድ የምጥ ጣር የገጠማት፤ ኢየሱስም ፍጹም ሰው ነበርና ማልቀስ የጀመረው የዚያኑ ዕለት ነው፣ ከኃጢአት በቀር ሰው የሆነው እርሱ ሊለፋ የጀመረበት ዕለት ያ ቀን ነው። መነሻው፤ ኢየሱስ በደጅ ጥናት በተገኘ ስፍራና ምቹ አልባሳት ሳይኖርለት የመከራን ጽዋ «ሀ» ብሎ «የገና» ዕለት ተያያዘው። አማኑኤል የሁል ጊዜ ስሙንም ያኔ ያዘ፤ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ»። «ገና» የደስታ ሳይሆን የኀዘን፣ የብርሃን ሳይሆን የጨለማ በሆነበት ዕለት እግዚአብሔም ከእኛ ጋር ሆነ።

ኢየሱስ በገና ዕለት ሰው ቢያለቅስ አልቅሶበታልና የሰው ችግር ይገባዋል፤ ኢየሱስ ያልተመቻቸ ሕይወት ገጥሞታልና ነገረ ዓለሙ ዝብርቅርቅ ሲል መያዣ መጨበጫን ሰው ሲያጣ ሊያረጋጋው ሊያግዘው ይችላል፣ በሰዎች መካከል ተገኝቷልና።

ለኢየሱስ የተገባው ስም አማኑኤል ከሆነ፣ የገና በዓል ሊከበር የሚገባው በዓመት 365ቱንም ቀናት ነው። ማለቴ በየቀኑ ገና ሊሆን ነው የተገባው፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የማይሆንበት የቀናት ብዛት 364 ነው ካላልን በቀር፤ አማኑኤል በአማኑኤልነቱ ሁሌ «ገና» ሆኖ እንዲያልፍ ፈቃዱ ነው። የዓመቱ ሰው ብቻ ያድርገን ብለን ካሰብን ግን የገናን ገናነት የመረዳታችን አቅም ዝቅ ብሏል።

የገናው ባለቤት በሦስት ዋንኛ ነገሮች ክርስቲያኖች አማኑኤ ልነቱን እንዲረዱት ይፈልጋል።

አንደኛው፣ የገና አምላኪዎች ሳንሆን፣ ጌታን ብቻ ለማምለክ ልንሰባሰብ እንደሚገባን ማወቅ ለሁሉ ያሻዋል። በማቴዎስ 18፡19-20፣ «ከእናንተ ሁለቱ በምድር ላይ ማናቸውንም ነገር ለመለመን በጸሎት ቢተባበሩ በሰማይ ያለው አባቴ ይፈጽመዋል፣» ምክንያቱም «ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት ስፍራ እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ» እንደ መሪ ጥቅስ ይወሰዳል። በአገራችንም ሆነ በዓለም ዙሪያ ያሉት ቤተ ክርስቲያናት መቼ ጢም ብለው ይሞላሉ ተብሎ ቢጠየቅ፣ ሁሉም ዘንድ አንድ ዓይነት መልስ እንደምታገኙ ማወቅ ተገቢ ነው፤ የገና ዕለት። ግን ለምን በዓመት አንድ ቀን በዚያን ዕለት ብቻ እንድንሰባሰብ ሆነ? ምላሹ አሁንም አንድ ነው፤ ዓለም በሙሉ ከሰው ጋር ሊሆን የመጣውን ኢየሱስን በመተው የቀን አምላኪ፣ የበዓልና የሥርዓት አድራጊ ስለሆነ ነው። ይልቁኑ፣ ክርስቲያኖች ሁላችን በየጊዜው መሰባሰባችንን ጌታ ፈልጎታል።

ሁለተኛው፣ የገናችን መገለጫ ፍቅርን የጋራችን በማድረግ መኖርን መለማመድ ነው። ኢየሱስ የተራቡትን ስላጠገቡ ሰዎች፣ የታመሙትን ስላስታመሙ ወዳጆችና ቤት የለሾችን የመሸባቸውን እንግዶችን ያስተናገዱትን ሰዎች፣ «ያደረጋችሁትን ሁሉ ለእኔ እንዳደረጋችሁ ነው» (ማቴ. 25፡40) አላቸው።

ታዋቂው ሊዎቶልስቶይ በድርሰቱ እንዲህ ጽፎ እንደ ነበር ይታወሳል። ሰውየው በእንቅልፍ ውስጥ ሳለ በሕልሙ ኢየሱስ ወደ እርሱ መጥቶ፣ «ዛሬ ወደ አንተ ቤት እመጣለሁና ተዘጋጅተህ ጠብቀኝ» የሚል መልእክት ተወለት። ሰውየውም ልክ እንደ ነቃ ኢየሱስን ሊያስተናግድ ሥራ ጀመረ፤ ቤቱንም አዘጋጅቶ ጨረሰ።

ግን ከአሁን አሁን ደረሰ ሲል አጓጉል ሰዎች ወደ ቤቱ እየመጡ ልቡን አደከሙት። ጠዋት ላይ ጠኔ ሊጥለው የነበረ አንድ የጃጀ ሽማግሌ ወደ እርሱ መጣ፣ ምግብ አቅርቦ አስተናግዶ ሸኘው። ቀትር ላይ ደግሞ የታረዘች ሕመምተኛ ሴት መጣችበት የሚያስፈልጋትን ሁሉ አደረገላት፣ ሸኛትም። ሊመሻሽ ሲል ደግሞ አባቱን ድንገት ያጣ ሕፃን ረዳት ናፍቆ አለቃቀሰበት፤ እንባውን ጠርጎ አለባበሰና ረዳው። በዚህ ሁሉ እንደ ሕልሙ ኢየሱስ ሳይመጣ መሸ። ኋላ ላይ ተሰላችቶ አንቀላፋ፣ ተኛም፤ ኢየሱስ ግን በሌሊት ወደ እርሱ መጣና፣ «በቤትህም መጥቼ ስለ አስተናገድከኝ አመሰግንአለሁ» አለው። «መቼ መጣህና?» የሰውየው ፈጣን ጥያቄ ነበር። ጌታ ግን በማለዳ ረዳት እንደሌለው ሽማግሌ፣ በቀትር በሕመምተኛ ሴት ተመስዬ፣ ኋላም ወላጅ-አልባ ልጅ ሆኜ ወደ አንተ የመጣሁት እኔ ነበርኩ አለው። እንግዲህ ገና ገና ሆኖ በየዕለት ሕይወታችን ተገለጠ ሲባል ይኸው ነው።

ይህንኑ አሳብ ትንሽ ላሳድገው። የኢየሱስን ልደት አስመልክቶ ታዋቂው ጸሐፊ ሄንሪ ቪንዲያክ «ሌላው ሰባ ሰገል» በማለት ከደ ረሰው ድርሰት ገጸበረከት ለኢየሱስ ለማቅረብ አንድ «ሌላ» የሩቅ ምሥራቅ ሰው ብዙ ገጸ በረከት ይዞ ገሰገሰ። ቢገሰግስም ግን ቤተ ልሔም የደረሰው ዘግይቶ ነበር። ያዘገየውም ጉዳይ በየመንገድ ሊ ረዱ የሚገባቸው ሰዎች እየገጠሙት ለኢየሱስ ሊሰጥ ካዘጋጀው ስጦታ አንድ አንድ እያለ ሲሰጥ ነው። ሲደርስ ግን «ወላጆች» ኢየሱስን ይዘው እንደ ሸሹ አወቀ። ተስፋ ሳይቆርጥ የሄዱበትን አቅጣጫ ይዞ ተከተለ። አሁንም በመንገዱ የሚረዱ ሰዎች እየገጠሙት ለኢየሱስ ካዘጋጀው ስጦታ እየሰጠ፣ በመጨረሻ ኢየሱስን አይሁዳውያን ሊሰቅሉት በዝግጅት ላይ ሳሉ ኢየሩሳሌም ዙሪያ ደረሰ...ያኔ በእጁ የቀረችው አንዲት የአልማዝ ጌጥ ብቻ ነበ ረች። ጠቢቡ ሰው ይህንንስ ለማንም አልሰጥም ለኢየሱስ ነጻ ማውጫ ይረዳኛል ብሎ ወደ መሠቀያው ተጣደፈ.... በጥድፊያው መሃል አንዲት ምስኪን ልጃገረድ አስቆመችው።

ሁሉን አጣሁ፤ ከዚህ በኋላ ሕይወቴ ሁሉ ከንቱ ይሆናል፤ መፍትሔው ሴተኛ አዳሪነት ብቻ ነው አለች፤ በአሳቡ ዋዠቀ፤ ከፊቱ ኢየሱስ አለ-ሊሰቀል፤ አጠገቡ ልጃገረዲቱ አለች-ዘማዊ

የምትሆን። ወሰነና አልማዙን ተጠቀሚበት ብሎ ሰጣት። በዚያን ቅጽበት መሆኑ ነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ ይህንን ሰው «በችግሬ ደረስክልኝ» ሲለው የሰማው። «መቼ ጌታ? እንደ ሮጥኩ፣ በእናትህ እቅፍ እያለህ አገኝሃለሁ ብዬ እንደ ተንከራተትኩ፣ ይኸው በስቅለትህ ደረስኩ። መቼ በችግርህ ደረስኩልህና? መቼ እስከ ዛሬ ዓይንህን አየሁ?» «ኢየሱስም፡- ተርቤ አብልተኸኛል፣ ተጠምቼ አጠጥተኸኛል፣ ታርዤ አልብሰኸኛል፣ ታምሜ ጠይቀኸኛል፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብለኸኛል፣ ታስሬ ጎብኝተኸኛል» አለው። ሰውየው ግን፣ «ጌታ ሆይ፣ መቼ ተርበህ አየሁና አበላሁህ? መቼ ተጠምተህ አየሁና አጠጣሁህ? መቼ ታርዘህ አይቼ አለበስኩህ? መቼ ታመህ ወይስ ታሥረህ አይቼ ጠየቅኩህ?» የድግግም ጥያቄው ሆነ። ጌታ ግን፣ «ከእነዚህ ለአንዱ እንኳን ያደረግከውን ሁሉ ለእኔ እንዳደረከው ነው» ሲል ይመልስለታል።

አያችሁ፣ ሁለቱ ደራሲዎች በድርሰታቸው ኢየሱስ ከእኛ የሚጠብቀውን ፍቅር ገለጡለት። ማን ያውቃል ዕብራውያን 13:12 በእኛ ላይ ቢፈጸምስ? እንዲህ የሚለው፡- «እንግዳ ተቀብሎ ማስተናገድን አትርሱ፤ ምክንያቱም እንደዚህ እንግዶችን እየተቀበሉ በማስተናገድ አንዳንድ ሰዎች ሳያውቁ መላእክትን ተቀብለው አስተናግደዋል።» እንዲህ ከሆነ እውነቱ በቤቱ ማስተናገድ የሚገባኝ፣ ተስፋ የሌለውን፣ ችግረኛውን ሊሆን ነው።

ሦስተኛው የገና ቁም ነገር፣ ኢየሱስን ከፍ ከፍ ከማድረጉ ላይ ነው። ኢየሱስ አለ፣ «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛ ል፣ እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው።» ይህ በየግል ሕይወታችን በየዕለቱ ሲፈጸም ሁሉም ገና ለእኛ ሆነ ማለት ነው። ሰላማችን፣ ግንኙነታችንና አንድነታችን ከጌታ ጋር የጠበቀ ሲሆን፣ ያያዝነውን የእርሱን እውነት ምሥጢር አድርገን ውለን አናድርም። በያለንበት እንተነፍሰዋለን፣ ያን ጊዜ በሰማይና በምድር ሥልጣን ያለው ኢየሱስ ከበረ ማለት ነው። ያ ነው ልደት።

እንግዲያስ፣ ከጌታ ጋር አብረን በመተሳሰባችን፣ አብረን ፍቅር በመጋራታችንና በአንድነት የአዳኝነቱ መልእክት የተገለጠበትን ዘር በመዝራታችን ገና ገና ሆኖ ይገለጣል። በዓመት ጉዳይ ሳይሆን፣

በዕለት ሕይወታችን ነው የጌታ ልደት ትርጉም ያለው የሚሆነው፤ እርሱ ሁሌ ከእኛ ጋር አብሮን አለና። እንግዲያስ፣ ኢየሱስን እንጂ ገናን አናግንነው።

«ዝምታ ወርቅ አይደለም!»

«መናገርን» በተመለከተ እኔ እና ካሽ ዲክቴል አንድ ዓይነት አቋም አለን። «የሰዎች የማሰብ ደረጃ በሚናገሩት ይመዘናል፣» እንላለን። የምንናገረውን ለማሰብ፣ ያሰብነውን ለማደራጀት እና ለሌላው ለማስተላለፍ የቃል ሀብት ወሳኝ ነው። የምናስበው በውስጣችን ባደሩት ቃላት ነውና፣ እነርሱን ተጠቅመን ከተናገርን በሰው ልጅ ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጠው እምቅ ጉልበት ሥራ ላይ ዋለ ማለት ነው።

ይህ ግን በተግባር ይገለጽ ዘንድ ዓይኖቻችን ለመናገር «ዳዴ» ከሚሉት ሕጻናት ላይ ሊያርፍ ይገባል። «እነዚህ እምቦቃቅላዎች የአገር ብቻ ሳይሆኑ የዓለምም ሀብት ናቸው። በጎ ነገር ሁሉ ከእነርሱ ሲነሣ፣ አልያም ለዘለቂታው ለእነርሱ ሊጠፋ ይችላል።»

ከእነርሱ እንዴት ሊጠፋ እንደሚችል የእኔና የካሽ ዲክቴልን ገጠመኞች እናካፍላችሁ።

* * *

ሰላም ወደ መዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤት ከመግባቷ በፊት በአቅሟ ግራ የገባትን ሁሉ ትጠይቃለች፤ ወላጆቿ ደግሞ ለጥያቄዋ ለአፍታም ሰንፈው አያውቁም፤ ሁሌም ወደ እርሷ የመገንዘብ ደረጃ እየወረዱ ይመልሱላታል፤ ሲያሰኛቸውም ይጠይቋታል። ከዚህም የተነሣ ሳይሆን አይቀርም፣ የሰላም ሕይወት «መጫወት፣ ማውራት፣ ማውራት፣ መጫወት» ሆነ። የመዋዕለ ሕፃናትን ደጃፍ በረገጠች ዕለት ደግሞ ከእድሜ እኩዮቿ ጋር መቦረቅን ተያያዘች፤ ክፍልም ውጭም ብዙ አድማጭ አገኘች። ከቀናት ባኋላ ግን ያውም የመዝሙር መምህሯ፣ «ዝም በይ ሰላም!» ብላ ጮኸች። ሰላም ኩምሽሽ አለች፣ በእኔ ግምት ያ ቀን የሰላም ጨዋታን አቆመ፤ ሰላም ስጋት በፈጠረው ዝምታ ተዋጠች፤ ወላጆቿን እንደ ቀድሞው

መጠየቁን ትታ ደብተሯን ብቻ ተመልካች ሆነች፤ ሰላም ዛሬ አድጋለች ግን ፈሪ ነች።

* * *

ጂሚ ሁለተኛ ክፍል ሳለ የገጠመውን ካሽ ዲክቴል ያወጉዋች ኋል። እናቱ በአሜሪካ «ወቅታዊ የፖለቲካ ትንታኔ» አቅራቢ ከሆኑት ሴቶች አንዷ በመሆኗ በየሄደችበት ጂሚን ከእርሷ አትለየውም። ከዚህም የተነሣ፣ ብዙ ነገር አይታል። እክፍል ከጓደኞቹ ጋር ሳለ «በተራ ወሬነት» «ትላንት እኮ! ከኒውዮርክ ከንቲባ ጋር ምሳ በላን» ይላቸዋል። የሰሙት ረኻርም ሳቅ ይስቃሉ። «ውሸታም!» ይሉታል፤ ጂሚ ግራ ቢጋባም፣ በሌላው ቀን «ትናንት ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ተገኝተን ዋይት ሀውስን ጎበኘን» ይላቸዋል። ጓደኞቹ ከመሳቅ አይታቀቡም፤ ያፌዙበታል። ይህን ወሬ የሰማችው መምህሩ ባትስቅም ጠረጠረችው፤ «አትዋሽ! መዋሸት ኃጢአት ነው!» ብላ ገሠጸችው። እውነት በተናገ ረ ያልታመነው ሕጻን ዛሬ አድጎም ተጠራጣሪ ነው።

* * *

አቡ ዘንድሮ የአሥረኛ ክፍል ተማሪ ነው። ሕፃን ሳለ መምህራቸው በሁሉም ላይ ትወስድ የነበረውን ቅጣት ያስታውሳል፣ «የመተኛት ሰዓት» በተባለው ክፍለ ጊዜ ቀድማ የምትተኛው መምህሯ ነበረች። ስትተኛ እንቅልፍ ይሏት ጥርግ ይላል። እነርሱ ደግሞ ለመተኛት ይሞክራሉ፣ ግን ብዙዎቹ አይተ ኙም፤ ይጫወታሉ፣ ይሳናተላሉ፣ ድምጻቸው ይወጣል፣ እናም መምህሯ ከእንቅልፏ ትነቃለች። እንደ ተነሣች ገላ የሚያበልዝ ቁንጥጫዋ በሁሉም ላይ ይደርሳል። ሴቲቱ በጥርጣሬ የተኙትንም ጭምር ትመዘልጋለች። አቡ ከያኔ ጀምሮ መጫወቱን ተወ፣ ሊጫወቱ በሞከሩት ሁሉ ላይ ሊመጣ ያለውን በማሰብ መስጋቱ ጨመረ፤ ይህ የታወቀው ደግሞ ባለፈው ዓመት ጤና ከማጣቱ የተነሣ ሐኪሙ በውትወታ ብዛት የተረዱት ነው። እንደ መንሥኤ «የሕፃንነት መከራው በሽታው ሆኗል» ያሉት።

* * *

ካሽ ዲክቴል ስለ አራቱ ረባሾችም የሚሉት አላቸው። ሐዋርድ፣ ዲክ፣ ፖል እና ዲፍ በየክፍል መምህሮቻቸው «አስቸጋሪዎች»

በሚል ስም ተፈርጀዋል። ያስቸገሩት «መምህሮቻቸው ያላዩትን በማሳየታቸው፣ ያልተረዱትን በመጠየቃቸው፣ አዳዲስ መረጃዎችን አምጥተው በክፍል ውስጥ በማወያየታቸው» ነበር። ለእነዚህ አስቸጋሪዎች ዕጣ ክፍላቸው በከንቱ መቅረት መሆኑን አስቀድመው አረዷቸው፤ ይህ ቢሆንም የኮሌጅ መግቢያ ፈተና በተዘጋጀ ዕለት ግን ከመቶ ሃያ ጓደኞቻቸው ጋር በጋራ ፈተናውን ተፈተኑ፡- በውጤቱ አራቱ ብቻ ከፍተኛውን ውጤት አገኙ፤ እናም ዛሬ አንዱ ሚኒስቴር፣ ሌላኛው ዶክተር፣ አንዱ የታሪክ ፕሮፌሰር፣ ሌላኛው ታዋቂ ጋዜጠኛ ሆነው ፍሬያማ ሥራ እየሠሩ ነው። በንግግር ራስህን መግለጥ ለፍሬ ያበቃል ማለት እንዲህ ነው።

* * *

ሻሮን ታዋቂ ጋዜጠኛ ናት፤ በኮሌጅ ሳለች ግን የእንግሊዝኛ መምህሯ «A» ያገኘችበትን ፈተና «B» አድርጌአለሁ ይሏታል፤ ምክንያታቸውንም ሲገልጹ፣ «ጥግ ይዘሽ ትቀመጫለሽ፣ አትጠይቂም፣ አትወያዪም፣ ተሳትፎም የለሽም፤ ለተሻለ ደረጃ ለመብቃት ፍላጎት ካለሽ፣ ተሳታፊ ሁኚ» ብለዋት ነበር። ሻሮን በመምህሯ አልበሸቀችም፣ የኋላ ታሪኳን ግን ፈተሸች፤ ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ በየክፍሏ ከገጠሟት መምህሮቿ ብዙዎቹ «ዝም በሉ! ማስታወሻውን ከጥቁር ሠሌዳ ገልብጡ! ጸጥታ! የምናገረውን ስሙ!» የሚሉ ነበሩ ከእነርሱ ምክርና ትእዛዝ የተነሣ «ለጭምትነት» እንደ በቃች ተረዳች። ሻሮን ዛሬ ለ«B» ያበቃትን ለመቋቋም በጥረት ላይ ነች።

* * *

እነዚህን ምስክሮች ለአንዱ ነጠላ ጉዳይ ስንል ያቀረብንላችሁ ናሙናዎች ናቸው። መምህራን ሕፃናትን ይናገሩ ዘንድ በማድረግ ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ጥያቄያቸውን ያቀርቡ ዘንድ ሊያበረታቱ ይገባል። በየሰዉ የቋንቋ እድገት እና የማሰብ አቅም ተሣሥረው የሚጓዙ ጥንዶች ናቸው፣ ሊለያዩ አይገባም፣ «ዝምታ ወርቅ ነው፣» በሚለው አሳሳች የታሠሩ ሁሉ ይህን አባባል ሊያርሙ ይገባል። ዝምታ የሚያመጣው ውጤት ባዶነት ነው፤ ባዶነትን በሁሉም ዘርፍ። ከዚህ የተነሣ፣ የመምህራን ድርሻ ትልቅ ነው። ከመምህራንም በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ኃላፊነትና አስተዋጽኦ የትልቅ ትልቅ ነው።

ቃሉን ማን ተጋፋው?

ገጠመኞች (ልምምዶች) ሁሉ ለሕያው ቃሉ ባለሥልጣንነት መገዛት፣ በእርሱም መጥራትና መፈተሽ አለባቸው፤ በእርሱ በቃሉ ያልጸኑ፣ ያልተረጋገጡ ልምምዶች ሁሉ ሊወገዱና ሊተዉ ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በነጠላ ጥቅስ ወይም በተወሰኑ ምዕራፎች ላይ አለመወሰኑ ለዚህ ትልቅ መርጎ ነው፤ በመጽሐፍ ያለች እያንዳንዷ ቃል ለብቻዋ ለክርስትና ሕይወት መመሪያ አለመሆኗን ከወዲሁ ማወቅም ሌላው ትልቅ መርጎ ነው። እናም ሁል ጊዜ ይህ መልእክት በመጀመሪያ የተደረሰላቸው እነማን ናቸው? ከዚያ አስከትሎ ለእኛ ያለው ዋንኛ ትምህርት ምን ይሆን? በቅደም ተከተል ማስኬድ ግድ ነው።

ለምሳሌ፣ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ብንመለከት ቀዳሚ መልእክቱ ሽግግር ነው፤ ሽግግር ከየት ወዴት? እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ሊሠራ ያቀደውን ከድምዳሜ አድርሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንዳቀባበለ (እንዳሸጋገረ) ያሳውቃል፤ ለዚህች ቤተ ክርስቲያንም የተሰጠው ኃላፊነትም ብሩህ ሆኖ እንዲዘልቅና ዋንኛ አስተምህሮዎችም እንዲታወቁ የጳውሎስ መልእክቶች ግንባር ቀደም በመሆን ተጽፈዋል።

ይህን ግን በመተው በተወሰኑ ምዕራፎች ላይ በመቆም መርጎ ይውጣ ቢባል፤ ስሕተት ሠሪ፣ ጥፋት አምጪ ይሰኛል። ለዚህ አባባል የሐዋርያት ሥራን በመውሰድ በአንድ ርእሰ ገዳይ ላይ እናውጋ፣ በልሳን ላይ።

አትኩሮት የሰጠነውን ርእስ ስናጤን ብዙዎቻችን አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ (ሐዋ. 11:26) ከመባላቸው በፊት እንደ ነበረ በእግረ መንገዱ አንዘንጋ፦ እንግዲህ ትምህርቱን አንድ ብለን በመጀመር አሥራ ሁለት ተከታታይ ነጥቦችን እነሆ፦

አንደኛ፣ በጴንጠቆስጤ በዓል ጴጥሮስ መልእክቱን ለእስራኤላውያን ብቻ ነበር ያደረሰው (ሐዋ. 2:5፣14፣22፣36፣12)። በዚያም የተገኙት አይሁዶችና ወደ ይሁዲነት የተቀላቀሉት ናቸው።

ሁለተኛ፣ ከአንድ መቶ ሃያ ደቀ መዛሙርት ውስጥ አሥራ

አንድ ሐዋርያት ብቻ ነበሩ በልሳን የተናገሩት (ሐዋ. 2፣7፣14)። ከመቶ ሃያዎቹ የተወሰኑት ሴቶች ነበሩ። ሴቶች ደግሞ በጉባኤ ይናገሩ ዘንድ ተከልክለዋል (1ኛ ቆሮ. 14፡34)። በወቅቱ ጴጥሮስ ሰብኮ የዳኑት ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች በልሳን አልተናገሩም።

ሦስተኛ፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም ሆነ በሌሎች ቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ አንድም ጊዜ አማኞች ልሳን እንዲሰጣቸው ሲጸልዩም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ ሲማጸኑ አናገኝም፣ ከጴንጠቆስጤ በዓል ቀድሞም ሆነ ኋላ ይህ አልተፈጸመም፤ ይልቅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ቃሉን በድፍረት ያለ ፍርሃት እንዲሰብኩ ጸልየዋል፤ ጸሎታቸውም መልስ አግኝቷል (ሐዋ. 4፡29-31)።

አራተኛ፣ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት የተደመጡት ልሳናት ሁሉም ቋንቋቸውን በሚያውቁት ዘንድ ሊደመጡ የቻሉና ሰዎች ተረድተው ገብቷቸው ምላሽ የሰጡባቸው ነበር። የማይታወቅ የድምጽ ድግግም ወይም ትርጉም-የለሽ ቋንቋ አልተናገሩም (ሐዋ. 2፡8-11)።

አምስተኛ፣ የሕግ ዘመን-መስተዳድር ሲጀምር በሙሴ ድንቅና ተአምር እግዚአብሔር አድርጎ እንደ ነበር፣ የዘመነ ጸጋ መስተዳድርም በቤተ ክርስቲያን ሲቀጥል ይኸው ተአምር በኢየሱስ ክርስቶስና በሐዋርያት ሆነ (ዘዳግ. 18፡15-20፤ ማርቆስ 16፡15-18፤ 2ኛ ቆሮ. 12፡12)። ከዚያም የተነሣ ሰዎች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉት ከተሞች በሽተኞቻቸውንና በርኩሳን መናፍስት የሚሠቃዩትን ያመጡ እና ሁሉም ይድኑ ነበር (ሐዋ. 5፡12፣16)። በዚያን ጊዜ ልሳንም ስጦታ ሳይሆን፣ ይህ የጸጋ ዘመን መጀመሪያ አመልካች ምልክት ነበር። ለምን? ቢሉ አይሁዶች ምልክት ይሻሉና (1ኛ ቆሮ. 14፡22፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡22)። ምልክትን መሻታቸው ብዙም አያስገርምም። በሕዝብነት ሳይታወቁ በምልክትና በድንቅ ተመሥርተዋልና። ለእኛ ግን እንዲህ አይደለም።

ስድስተኛ፣ በሐዋርያት የተከወኑ ምልክቶችና ድንቆች ዋኛ ዓላማቸው ለአይሁዶች ነበርና ሐዋርያት ዘመናቸውን በፈጸሙ ጊዜ የእነርሱም አገልግሎት አብሮአቸው ተካትቷል (1ኛ ቆሮ. 1፡22፣ ዘጸአ. 4፡30ን ይመልከቱ)። በእስራኤል እግዚአብሔር ለመጠቀም

ያቀደውን መርሐ ግብር ሲተው የምልክት ስጦታዎችንም ተወ፤ ይህም በሐዋርያት እንኳን ኋላ ላይ ሳይፈጸም ቀረ (ሐዋ. 19፡11-12፤ ከ1ኛ ጢሞ. 5፡23 እና 2ኛ ጢሞ. 4፡20 ይመልከቱ)። ጳውሎስ የሚወደውን ጢሞቴዎስን ከሕመሙ መፈወስ አልቻለም። እንግዲያስ ሐዋርያት ባሉበት ጊዜ እንኳ ምልክቶች አገልግሎታቸውን ካሽቀለቀሉ፣ ዛሬስ? ዛሬማ ሐዋርያት የሉም። ከ12 ሐዋርያትም ሌላ ሌላ ሊኖር አይችልም (ራእይ 21፡14)።

ሰባተኛ፣ በመንፈስ ቅዱስ በድግግም መሞላት በሐዋርያት ሥራ 2፡4 ኋላም በሐዋርያት ሥራ 4፡8፤ 31፤ 7፡55፤ 9፡17 እንዲሁም 13፡52 ተከናውኗል፤ በዚህ ሁሉ ልሳን መናገር አልነበረም። ክርስቲያን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል፤ ግን ሁሉም ክርስቲያን በልሳን አልተናገረም (1ኛ ቆሮ. 12፡14-31)። ሁሉ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ታዝዟል (ኤፌ. 5፡18)፣ በልሳን እንዲናገር ግን አልታዘዘም።

ስምንተኛ፣ የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉ ጊዜ በልሳን አልተናገሩም ነበር (ሐዋ. 8፡15-17)።

ዘጠነኛ፣ መንፈስ ቅዱስንና ኢየሱስን አንድ ዓይነት ዓላማ እንደሌላቸው በመቁጠር መጠመቅ፣ አጥማቂ፣ የእሳት ጥምቀት የተሰኙትን ነጥቦች፣ አለአግባቡ መተርጎም ስሕተትን ይጋብዛል (1ኛ ቆሮ. 3፡16)።

አሥረኛ፣ ልሳናትን በሁለት ቦታዎች ብቻ ነው ለመነሻ መረጃነት ሆነው የምናገኘው፣ ይኸውም በሐዋርያት ሥራ 2 እና 10 ላይ ነው። የመጀመሪያው ለአይሁዶች፣ ሁለተኛው አሕዛብን እግዚአብሔር እንደ ተቀበላቸው ለማሳወቅ ልሳን በምልክትነት አገለገለ፤ ይልቁኑ፣ በቆሮኔሊዮስ ዙሪያ የሆነው የሥልጣን ምልክትነት ጴጥሮስ እግዚአብሔር እንዴት በክርስቶስ አሕዛብን እንደ ደረሰ የታየበት ምልክት ነበር።

አሥራ አንደኛ፣ ልሳናት ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን በመቀጠል ላይ በነበረችበት የመጀመሪያው ወቅት ላይ ነው የተገለጸው (ሐዋ. 2፡10፤ 19) እና በ1ኛ ቆሮቶስ ላይ። መቼም ልናውቅ የሚገቡን አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፈውልናል። እናም እኛ ቃሉን አምነን እንድንኖር ታዘዝን (ሮሜ 1፡17)። በ20ኛው መቶ

ከፍለ ዘመን ግን ሰዎች ምልክትንና ድንቅ ነገራትን በማየት ለመኖር በመጓጓት እግዚአብሔርን የማመናቸው መሠረት እርሱን ከማድረግ የተነሣ የስሕተት አሠራር እያጥለቀለቀ ይታያል። ልምምዶች ሁሉ በጌታ ቃል ሊመሠረቱ ግድ ነው።

አሥራ ሁለተኛ፣ የልሳን ታሪክ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ታይቶ የተዋወቅንበት ጊዜ በጥንቷ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ብቻ ነበር፣ ማለትም ከመቶ ዓመተ ምሕረት በፊት ከዚያ እስከ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዓመተ ምሕረት ድረስ አልተከሰተም። ከወዲሁ ግን ባለፉት ሰባና ሰማኒያ ዓመቶች ጀምሮ ልሳን በየቦታው የሚታይ ሆኗል። ይህ ለምን ሆነ? ምላሹ በአሥራ አንደኛው ነጥብ ላይ ተሰጥቶታል። ልሳን ስሜታዊነትን፣ ተጨማሪ መገለጥን በመያዝና ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ በሆነ ሁኔታ ይስተናገዳል። ይህ ከፍተኛ ጥንቃቄን ይጠይቃል። ልሳን በዚህ ዘመን በሁሉ ዘንድ ተከሥቷል - ሙስሊሞች፣ ሂንዱዎች፣ በአጋንንት እሥራት ውስጥ ያሉ ሁሉ ይጠቀሙበታል። እንግዲያስ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡9 በመመልከት በዘመን ፍጻሜ ላይ መኖራችንን እናስተውል። እናም ለሕያው ቃሉ ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ተገዥዎች ለመሆን ቃሉን እንወቅ፣ ደራሲው መንፈስ ቅዱስም በእኛም ውስጥ አለና ይመራናል፤ ቃሉንም ያስተምረናል።

መግባባት የፍቅር መሠረት

ዚክን የጠየቅኋት ጥያቄ አንዲት ነበረች፤ «የተጫጨም ሆነ ተጋቢዎች ወዳጅነታቸውንና ፍቅራቸውን እያሳደጉ የሚሄዱት በምንድን ነው?» ምላሿ፣ «በመግባባት» የሚል ነበር፤ የእርሷን መፍትሔ እኔም ሆንኩ ሴልዋን ሁስም ተቀብለነዋል። ሴልዋን ሁስ «እግዚአብሔር እንዳቀደው ያለ ጋብቻን» የጻፉ ሰው ናቸው።

በጽሑፌ መግባባት ምን ማለት ነው? ለምንስ ያስፈልጋል? ደግሞስ እንዴት ስኬታማ ይሆናል? በመጠየቅ እኒሁኑ በትክክል እመልሳለሁ።

የመግባባት ፍቺው «ሳይጋጨ በመስማማት፣ ወይም ተጋጭተ ው በመስማማት ወይም ያልተስማሙም ለመስማማት ወደ አንድ አሳብና ወደ መቀባበል መድረስ» ማለት ነው።

ይህ መግባባት ያስፈለገበት ሁነኛ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ጋብቻን ሲመሠርት በተጋቢዎች ሕይወት ውስጥ ይህ ተገልጾ ፍሬያማነታቸው ለተፈቃሪዎቹ፣ ለቤተሰባቸው፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለኅብረተሰቡ ይትረፈረፍ ዘንድ መግባባት የጌታ ፈቃድ ሆነ፤ አስፈለገም። የዚህም የመግባቢያ የሕይወት ዘርፎች በተጋቢዎች የመንፈሳዊ፣ የማኅበራዊ፣ የአካላዊ፣ የአእምሮአዊና የስሜታዊ ጉዳዮች ሁሉ ላይ እየተቀባበሉ እርስ በርስ በመደጋገፍ በመዋዋጥ ሲቀጥሉ ይገለጻል።

እንኪያስ የተጣመሩ ተጋቢዎች የትዳራቸው ብቸኛ ምሰሶ ሀብት፣ ዝና፣ እውቀት፣ ውበት፣ ወዘተ... ሳይሆን፣ «መግባባት» ብቻ ነው፤ ይህም ስኬታማ /ውጤታማ/ የሚሆነው ሦስቱን ጠንካራ መርኖዎች ሲከተል ነው። ተጋቢዎች ማውራት ሳይሆን መናገርን፣ መስማትን ሳይሆን ማዳመጥ፣ መደናገር ሳይሆን መ ረዳት የዘወትር ሕይወታቸው ሲሆን፣ መግባባት በጽኑነት እግሩን ተክሎ ማለት ነው።

* * *

እስቲ አጠር አጠር አድርጌ ሦስቱንም ላብራራቸው። ብዙ ሰው ያወራል እንጂ አይናገርም፤ ማውራት ያለ አሳብ፣ ያለ ዓላማ፣ ያለ ፍሬ በከንቱ አፍን መክፈት ነው፤ ይህ አይፈለግም፤ መናገር ግብ ሊኖረው የሚችል ዓላማ ይዞ ፍሬ አሳቡን ለማቅረብ የሚከፈት አንደበት ነው።

ተጋቢዎች ማንነታቸውን የሚገልጹት የትኛውንም አሳብ በአግባቡ ለወዳጃቸው ሲናገሩት ነው። ሐዋርያው፣ «...እውነትን በፍቅር እየተናገርን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር እናድጋለን» አለ (ኤፌሶን 4፡15)፤ ይህም በፍቅር እውነትን ከተጫጨበት፣ ከዚያም የአካል አንድነት ፈጽመው ከተጋቡበት ጊዜ ጀምሮ እድገትን ማሳየት ግዴታው ነው።

እርግጥ፣ የትውውቅ ዘመን ላይ የንግግሩ ክልል፣ «ዛሬን እንዴት ዋልሽ?» ወይም «ሥራህ እንዴት ነውን?» እልፍ አይል

ይሆናል። ኋላ ግን የንግግር ምልልሱ ሰዎች ስለ ሰዎች የተናገሩትን በመናገር ላይና በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ አስተምህሮ ዎች ላይ ያተኩራል፤ ይህም ሲያድግ በጽንሰ አሳቦች ላይ መወያየትንና ሚዛናዊ የውሳኔ ጉዳዮችን በማንሣት መነጋገር ይከተ ላል። እንዴት «ጋብቻን ጋብቻ የሚያደርገው በሁሉ ነገር ተ ስማምተን ለአካል አንድነት መብቃታችን ነው፣ ወይስ ሠርግ መሠ ረጋችን?» «ክርስቲያን የመሆናችን ምሥጢር ምንድን ነው? ልንሆነው የሚገባው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንዴት ይገለጽ?» ይህ የንግግር ወይም የመግባቢያ ሁነኛ በር ነው፤ ራስን ያስመለክታል፤ መተዋወቅንም ያሳድጋል። ለምን? ቢሉ፣ በውስጡ ስሜታችንና ፍላጎታችን ይገለጣል፣ በግልጽም የምንወደውንና የምንጠላውን ያለ ቅሬታ ወደ ማሳየት ያመጣል። ይህም በንግግር ሕይወታችንን በግልጽና በታማኝነት ለምንወደውና ለምንወዳት አጋራችን ማሳየት የዘወትር ተግባርም ፍሬያማ ይሆናል፤ ጠቢቡ በምሳሌ 25:11፣ «በወቅቱ በትክክል የተነገረ ቃል በብር ላይ እንደ ፈሰሰ የወርቅ ጌጥ ውበት ይኖረዋል» ይልለታል። ያዕቆብም በምዕ ራፍ 3:2-10 ያጸናው ይህንኑ ነው። እንኪያስ ንፋስን እንደ መጎሰም ያለ ወሬን ሳይሆን፣ በፍቅርና በዓላማ መናገር የመግባባት ደጃፍ ነው።

* * *

ሌላው የመግባቢያ ዘርፍ ደግሞ መስማትን ሳይሆን፣ ማድመጥን መከታተል ነው። መቼም ጆሮ ያለው ፍጡር ሁሉ ወደ ውስጥ ያገ ኘውን ድምጽ ሁሉ ያለ ፈቃድ ያስገባል፣ ለእነዚህም ውሱን የሆነ ምላሽ ይሰጣል፤ ወይም አይሰጥም። በትይዩ ግን፣ አንድን ነገር ብቻ እያብላላ፣ እያነጻጸረ፣ በማመዛዘን ለምላሽ የሚያዘጋጅበት እርሱ ማድመጥ ይባላል፤ ተናጋሪ ይህን የመሰለ አድማጭ ካላገኘ፣ ድካሙ ሁሉ ከንቱ ነው። ማድመጥ ጥረት ይጠይቃል፤ ከዚህም የተነሣ፣ ሰነፎች ለማውራት እንጂ ለማድመጥ ፈቃደኞች አይደሉም። ሕያው ቃሉ በምሳሌ 18:13፣ «መልስ ከመስጠትህ በፊት አድምጥ፣ አለበለዚያ ሞኝና የተናቅህ መሆንህን ታሳያለህ» ይላል። ያዕቆብ በ1:19 ለማድመጥ ንቁ መሆንን ያበረታታል፤ ደግሞስ ማን ያውቃል? ለሰው አንድ አፍ እና ሁለት ጆሮዎች

እግዚአብሔር ያደርገለት ንግግሩ ምጥን ሆኖ በአግባቡ እንዲያደምጥለት ይሆን? እንጃ!

ግና በትክክል ላለማድመጥ ለተፈቃሪዎችና ለተጋቢዎች እንቅፋት በፊልጵስዩስ 2፡3 «ያለ እኔ ማን አለ» በሚል መንፈስ ተከላካይ ለመሆን መዘጋጀት ትልቁ እንቅፋት ነው። ሌላው፣ ለምላሻችን የሚረዳንን የተናጋሪያችንን አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የድምጽ አወጣጥ፣ የቃላት አሰካክ፣ ስፍራ ሳይሰጡ ነጠላ መልእክቱን ብቻ መከታተል የማድመጥ ተደራቢ መሰናክል ነው። ይህንን ሥራዬ ብሎ ማረምና ማድመጥ ለመግባባት ጽኑ መሠረት ነው።

* * *

ሦስተኛውና የመጨረሻው፣ መደናገር ሳይሆን መረዳት ነው። ተጋቢዎቹ የንግግራቸውና የማድመጣቸው ሁነኛ ውጤት ስኬታማ የሚሆንበት ዳርቻ አንዱ ሌላኛውን ሙሉ ለሙሉ ተረድቶ ሊያስተላልፈው ያለው መልእክት ገብቶት ለትክክለኛ ምላሽ ሲበቃ ነው። ያም አንዱ ሌላውን በመላት የሚረዳው ሐዋርያው እንዳለ ሁለቱ «... በአሳብ፣ በፍቅር፣ በመንፈስ፣ በዓላማ እየተስማማችሁ ደስታዬ ሙሉ እንዲሆን አድርጉ...ን» በፈቃደኝነት ሲታዘዙ ነው (ፊልጵ. 2፡2)። ይህ አባባል እስካሁን ልል የፈለግኩትን ሁሉ የሚቋጭልኝ ቃል ስለሆነ፣ በዚሁ አበቃለሁ። ሁሌ አሳባችንን በንግግር ከመግለጽ አናፈግፍግ፤ ወደ ጆሮአችን የሚደርሰውን መልእክት እናድምጠው፤ ተናግረንና አድምጠን በመረዳት እንስማማ። እንኪያስ፣ ይህ የመግባባት የሕይወት መመሪያ ሲልዋን ሁሉም ሆኑ እኔና ባለቤቴ ዚክ እንዳልነው፣ ለተጫጨትም ሆነ ለተጋቡት አለኝታ ይሁንላቸው፤ ጆሮ ያለውም ያድምጠው!

2000ም እንደ 1900!

ለዛሬው ጽሑፌ ዋንኛ መግቢያ ላደርገው የሚከተለውን ጥቅስ መርጫለሁ፤ እንዲህ ይላል፦

«ከአንድ ምንጭ ጣፋጭ ውኃና መራራ ውኃ ሊወጣ ይችላልን? ወንድሞቼ ሆይ፣ የበለስ ዛፍ የወይራ ፍሬ

ሊያፈራ ይችላልን? ከመራራ ውኃ ጣፋጭ ውኃ ሊገኝ ይችላልን?» (ያዕ. 3፡11)። ያዕቆብ የፈለገው ምላሽ፣ «አይቻ ልም» የሚል ነው።

* * *

በየወሩ እየታተመ የሚወጣው «ቤተሰብ ነክ» ጉዳዮችን የሚያስተናግደው የ«Washington Watch» *2000* ዓ.ም. የመጀመሪ ያው ወር ላይ *1900* ዓ.ም በገባ ጊዜ አቀባበሉ ምን እንደሚመስል ዘክሮልናል።

እ.ኤ.አ የዛሬ *100* ዓመት የዓለም ሕዝብ እንደ ዘንድሮው *2000* ሽርጉዱን አብዝቶ ነበር፤ ሺህ ዘጠኝ መቶ በኢኮኖሚ ማደግ፣ በዕ ውቀት መጥለቅለቅ፣ በሰላም መኖር፣ ከበሽታ መላቀቅ፣ ሊሆኑ እንዳላቸው ገና ከዋዜማው ሲገልጹና ሲጽፉ ቆዩ። ያ የተጠበቀው *1900* መጣ፣ ዓለም በደስታ ተዋጠች፣ ልክ እንደ ዘንድሮው ያኔም የመጀመሪያው ወር የመጀመሪያው ቀን ይልቁንም *1899* ተሻግሮ *1900* የሚገባበት የመሸጋገሪያው ስድስተኛ ሰዓት በፈንጠዝያ ተ ዋጠች።

* * *

መቼም በአብዛኛው እንደሚታወቀው፣ የሰው ልጅ ያለ ምግብ ብዙ ወራት፣ ያለ ውኃ ጥቂት ቀናት መኖር ይችላል፤ ያለ ተስፋ ግን ለአንድ አፍታ አይኖርምና ተስፋ እንጀራቸው ሆኖ በእልልታ ተቀበሉት። ሲቀበሉት በእርግጠኝነት ምኞታቸው ጣፋጭ ውኃ ሊጠጡ፣ ጣፋጭ ፍሬም ሊበሉ ነበር። ዳሩ ግን በዘመኑ ውስጥ ያልተስተዋለ ነገር ነበር። ዘመኑን ሲቀበሉ ያልተስተዋለውን እነሆ፡- ጆሴፍ ስታሊን የ*21* ዓመት ልጅ ሆኖ በትፊሉስ ዩክሬን ይማር ነበር፤ ቤኒቶ ሙሶሎኒ የ*17* ዓመት የተማሪ አስተማሪ ሆኖ ያገለግል ነበር፤ አዶልፍ ሒትለር ደግሞ የ*11* ዓመት ልጅ ሆኖ በብራና ይማራል፤ ዛሬ ደግሞ በስፋት የምንዘክራት በ*1900* ማርጋሬት ሳንገር የ*20* ዓመት ወጣት ሆና በኒውዮርክ የሕክምና ሙያዋን ታጠናክር ነበር።

እነዚህ አራት ወጣቶች በ*1900* መግቢያ ላይ በሕይወት ተገኙ። አዲሱም ዘመን አብሮ ተቀበላቸው። የታሪክ መዘክርነት ስለቀደሙት ሦስት ሰዎች ሲጽፍ እንደ እስታሊን፣ ሙሶሎኒና ሒትለር የእልፍ አእላፍ ንጹሐን ደም አላግባብ ያፈሰሰ እስከ ዛሬ

አልተነሣም ይላል።

እንኪያስ በ1966 ዓ.ም የሞተችው የማርጋሬት ሳንገር ታሪክ እንዴት ነው? ጀረድ ግራንት ታሪኳን ፈልፍሎ እንደ ጠረዘው፣ ሴቲቱ «የቤተሰብ ምጣኔን» በማስተማር ወላጆች ያለ ችግር ልጆቻቸውን እንዲያሳድጉ፣ ልጆችም የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲያድጉ፣ «ስለ ቤተሰብ መቆርቆር» ዋንኛ ጉዳይ መሆኑን አስተማረች። ተቀባይነቷም አደገ፤ አከታትላ ስለ ሕዝብ፣ በተለይም ስለ ሴቶች፣ መብት ተቆረቆረች፤ ሥቃይ-አልባ ግድያን (Euthanasia)፣ ዘር ማምከንን (Sterilization)፣ ውርጃን (Abortion)፣ እና እንደ ተወለደ የመግደልን (Infanticide) መርሐ ግብሮችን አጠናክራ ማራባትን ቀጠለች። ይህም የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተዳምሮ ሁሉም ለናዚ መርሐ ግብር አገልግሎትን በሥነ ሳይንስ ስም ሲያስኬድ የማርጋሬት ሥራ በአሽዊትዝ (Auschwitz) የስድስት ሚሊዮን አይሁዳውያን እልቂት ረዳት በመሆን ቆመ። የማርጋሬት ሳንገር የቤተሰብ ጥበቃ ዓላማ በአዘጋጆቸው መሠረ አካሄድ በ1942 የድርጅቷን ስም በማሳደግ የአሜሪካ የፌዴሬሽን መንግሥት «የቤተሰብ ጥበቃ» በማለት የአሜሪካ ግዛቶች ሁሉ በአንድ አሳብና ፈቃድ እንዲያራምዱት መንግሥትን ጣልቃ አስገባች፤ አስከትላም ሥልጣኗን ለዶ/ር አሊን ጉተማቸር አሻገረች። ይህ ሰው ስለ እርሷ በድግግም ሲመሰክር፣ «ሁላችንም ወይዘሮ ማርጋሬት ሳንገር በቀደደችልን ጎዳና ላይ የምንረማመድ ሰዎች ነን፣ ፈለጓን ልንቀይረው አንዳዳም፣» በማለት ያላትን ራእይ እያመሰገነ ይመሰክራል። የሚዘከርላት ሲፈተሽ ግን እውነቱ እንዲህ ነበር፦ «ሴቶችና አዲሱ ትውልድ» በሚለው መጽሐፏ፣ ሳንገር «ልጅን ባመት ባመት የሚፈለፍሉ እናቶች ጨም ረው ማርገዛቸውን ካወቁ ፈጥነው ማስወረዳቸው ለቤተሰባቸው ምሕረትንና ፍቅርን እንደ ፈጸሙ ያስቆጥራቸዋል...» ትላለች። ከዚህ የተነሣ ድርጅቱ በዓለም ላይ ውርጃን በማስፈጸም እርዳታን ለሚያደርጉ ዛሬም ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ ይገኛል።

ሳንገር ስለ ነጻ ፍቅር ስታስተምር፣ ልጆች ያለ መከልከል በነጻነት ፍላጎታቸውን መፈጸም አለባቸው፣ ለአካለ መጠን ባይደርሱም እንኳ ወሲብ-ነክ ጉዳዮችን መለማመድ ይችላሉና የዘር ማፍሰስ (masturbation)፣ የወሲብ ልምምድን፣ የተመሳሳይ ጾታ

ግንኙነትን በማበረታታት የበረከቱ ጽሑፎችን በልጆች ነጻነት ስም ዘርታለች፤ አዘራሯም የክርስትናን ትምህርት በማንቋሸሽና በመንቀፍ እንደ ነበር ተጽፎበታል።

ማርጋሬት ሳንገር የመጀመሪያ ጋዜጣዋን ስታሳትም ጽሑፉ «የሴት ዐመፅ» ይሰኝ ነበር። በዚህ መልእክቷ ከካፒታሊዝም ይልቅ አብልጠን ልንዋጋው የሚገባን ክርስትናን ነው ይላል፣ የክርስትና ትምህርት የሴቶችን ክብር ገፍፏል፣ የበታች አድርጎ ለድርብ ጭቆና አብቅቷቸዋል በማለት ደስኩራለች። ሁሉም የተቃውሞ ቃታውን በክርስትና ላይ እንዲስብ አመቻችታለች። እስከ ዛሬም ድርጅቱ ማስታወቂያዎችን፣ ጽሑፎችን ከዚህ ዓላማ አኳያ በማንሣት የእግዚአብሔርን አሳብ ይቃወማል።

ማርጋሬት ሳንገር እንደ ተቀሩት የዘመኗ ሰዎች መልካም የሚመስለውን በማር የተለወሰውን መርዝ ለሕዝብ በማድረስ ሌላዋ አራተኛ ሰው ናት፤ ያኔስ የነበሩት ዘመነኞቿ ስታሊን፣ ሙሶሎኒንና ሒትለር በዓይን ታይተው ሊቆጠሩ የማይችሉትን ሰዎችን ጨፍጭፈው እኩይ ሥራቸው ያኔውኑ አበቃ፣ የሳንገር ያልተቋረጠ ግድያ ግን ዘመኑን ሙሉ ሞልቶ ለ2000 ዓመት መቀበያ ደረሰ። ደርሶም ቀጠለ፣ እንኪያስ መላው ምንድን ነው? «ወንድሞቼ ሆይ፣ የበለስ ዛፍ የወይራ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን?... ከመራራ ውኃስ ጣፋጭ ውኃ ሊገኝ ይችላልን?» ፈጽሞ አይቻልም። ልክ እንዲሁ፣ በኃጢአት ከተበከለው የሰው ልጅ ተስፋ የሚያሰጥ ነገር ሊገኝበት አይችልም። ይህን ሁሉ ስል እውቀትን፣ ሥልጣኔን፣ ለሰው ልጅ ሊጠቅሙ የሚችሉትን ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎችን በመጥላት ወይም በመካድ አይደለም፣ እግዚአብሔር ለሰው በሰጠው ማስተዋል መጠን ቁሳዊ ውጤቶችንና ሥራዎችን ሰው ለሰው ሊያስገኝ ይችላል። ዳሩ ግን የማንነትን ጥያቄ፣ የመንፈሳዊ ሕይወት ጉዳይን፣ ከእውነተኛው ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኘት ምሥጢርን፣ ሰው በሥልጣኔው ሊያገኘው አይችልም።

ከክርስቶስ ጋር በመታረቅ የእግዚአብሔር አሳብ መረዳትን ሰው እስካልተረዳ ድረስ፣ እልቂትን እንጂ ጽኑ ተስፋን የሚዘራ ማንም የለም። መፈናፈኛ ያጣና ተስፋው ጭልጭል የሚልበት ሕዝብ ሁልጊዜ ያረፈ እየመሰለው ዓመትን በመቁጠር ይባትላል፤ ውጤቱ ግን እንደ 1900 መግቢያ ነው። ጽኑስ ተስፋ እግዚአብሔርና

እግዚአብሔር ያዘጋጀው መድኃኒት ነው። እርሱም በሰዎች መካከል የተገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ከዚህ ውጭ 1900 እና 2000 ለውጥ የሌላቸው ናቸው።

የቀባሪው ጣጣ

«ቀባሪ አታሳጣኝ» የብዙ ሰዎች የጸሎት አጀንዳ ነው። ጤነኛ ውም፣ ሕመምተኛውም የሞቱን ቀን እያለመ ይህንን ይደጋግመዋል፣ ከመደጋገሙ የተነሣ፣ ዳር ሆኜ አባባሉን ልፈትሸው ቆም አልኩኝ።

ከሩጫ፣ ከግርግር፣ ከሁካታ የሕይወት አኗኗር ዘይቤ ለአፍታም ቢሆን ቆም ብሎ ነገሩ ልክ ይሆንን? ብሎ ለማገናዘብ እረፍት ማድ ረግ መፍትሔን ያስከትላል፣ እረፍትን ያመጣል እንጂ፣ መዋተትን አይጋብዝም። እናም የኑሮ ዘይቤ የሆነውን ልፈትሸው ሁ፣ሁ... አልኩኝ።

በፍተሻዬ የብዙዎቹ ጸሎት የመመለሱን ጉዳይ ብጠራጠርም፣ በየቀብሩ ቦታ ግን በድኑን ተከታትሎ ወደ መቀበሪያው ጉድጓድ የሚቻኮለው ሕዝብ በርክቶ አገኘሁት፣ በሚቹ የሕይወት ዘመን ያልታሰበ፣ ለዓመታት ያልታየ፣ በችግሩ እና በጣሩ ሰዓት ያልነበ ረ ሁሉ፣ ከቅርበኞቹ የቤተሰብ አባላት ጋር ተደማምሮ-እየተከዘ፣ እያለቀሰ፣ እየታዘበ ለ«የቀባሪ አታሳጣኝ» ልመና መልስ ሆኖ ይገኛ ል። እኔም በአጀቡ መካከል ሆኜ እንደ ገጣሚ መንግሥቱ ለማ «ምን አለ! ሚች ቀና ብሎ የልቡን ተናግሮ ቢመለስ!» በማለት ተ ከዝኩኝ፤ እንደ ሆነም ቆጥሬ ደነገጥኩ፤ ከድንጋጤው ኋላ ግን ምን ለውጥ በቀባሪዎች ዘንድ ሊፈጠር እንደሚችል ለመገመት ሞከርኩኝና ግጥሙን አስታወስኩ።

«ዝም ያለው ዘመዴ እኔ ሳጣጥር
ሞተ ቢሉት መጣ አልቅሶ ሊቀብር።
እኔ ሙቼ ሳለ ይህንን ስላየሁ
በመንፈስ ነድጄ ተቃጥዬ ጨስሁ።
በልቤ እንደ ደረሰ የእግዚአብሔር ፈቃዱ

ሆኖ ተነሥቼ እነርሱ ሲያረግዱ፡፡
እንዲህ እንዲህ አልኩኝ አልቃሽ ተብዬውን
ታምሚ ነበረ ሳጣጥር ማዘን፡፡
አሁን ክንዱ ክንዱ ቀኝ እጁ ቢሉኝ
ከሞትኩኝ በኋላ ምንም አይገባኝ፡፡
ይህን ተናግሬ አንጀቴን አርሼ
ወደ መጣሁበት ሄድኩኝ ተመልሼ፡፡»

ይህ ቆይታዬ ይህንን እንጉርጉሮ ጨምሮ በጽኑነት ያስጨበጠኝ ትልቅ ቁም ነገር «የቀባሪ አታሳጣኝ» ጸሎት ሳይሆን፣ የኢየሱስ ክርስቶስን «ሌሎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው» ያለለትን ፈትሾ እውነቱ በሕይወት ሳሉ በጎውን መፈጸም የለውጥ ሁሉ መሠረት መሆኑን መረዳት ብቸኛ ቁም ነገር ሆነልኝ፡፡ ዛሬ ላይ በአጠገቤ ያሉትን በችግሬ እንዲደርሱ እንደ ተመኘሁ በችግራቸው ልደርስ፣ ለሕይወት የደረሰልኝ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ ለተገባቸው የተልዕኮውን ታላቅ መልእክት በሕይወት ሳለሁ ማቅረብ እንዳለብኝ ተረዳሁ፡፡ የክርስቶስ ምክር ከሞት ኋላ ሳይሆን፣ ከሞት በፊት እንደ ተገባ ቆይታዬ ገልጦልኝ፣ ለሌላ መገረም አሸጋገረኝ፡፡

ከቀብር ተመላሽ ሆኜ ሳዘግም ቅጥር ግቢውን ሐውልቶች ከመልእክቶቻቸው ጋር ገዝፈው ተኮልኩለውብታል፡፡ እይታዬ በአርባ አምስት ዓመቱ ሰው ሐውልት ላይ ሆነ፡፡ በጉዛዜው ይሁን ወይም በቤተሰቦቹ ፈቃድ ለይቼ ያልተረዳሁት መልእክት በሐውልቱ ላይ ሰፍሯል፡፡

«...መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬን ጨርሻለሁ፣ ሃይማኖትን ጠብቄያለሁ» (2ኛ ጢሞ. 4፡7)፡፡

ይህ ጥቅስ በነጠላ ጥቅስነቱ ብቻ ሊሰጥ የሚችለው ፍቺ ነጠላ የሆነ፣ ተስፋንና የድል ውጤትን ይመስላል፤ የቀዳሚ ተናጋሪው የሐዋርያው ጳውሎስ የሕይወቱ ዐቢይ ጉዳይ ሲጤን ግን ሊያስተ ዛዝብ የሚችል መልእክት አለው፡፡ ጳውሎስ የኢየሱስ በመሆኑና የእግዚአብሔርን ፍቅር ከክርስቶስ የማዳን የመሥዋዕትነት ሥራ በማግኘቱ ሕይወቱን ለጌታው አሳልፎ ሰጠ፣ ታላቅ የሆነውን ተልዕ ኮ በመንፈስ ቅዱስ የመለወጥ ጉልበት ተማምኖ፡- «ኃጢአተኞች ለሆንን ለእኛ ክርስቶስ ሞቶልናል» በማለቱ ብዙ ጊዜ ታሠረ፣ ተገ

ረፈ፣ ተወገረ፣ ተራበ፣ ተሠቃየ፣ ይህ ሁሉ ሳያንስ ይህን ለጢሞቴዎስ በጻፈለት ጊዜ የሮማ መንግሥት ሊሠዋው መዘጋጀቱን ተረዳ። ጳውሎስ የሆነውን ሁሉ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ሲያስብ ያለ ነቀፋ መልካም የሆነውን ገድል በአግባቡ ተጋድሏል፤ ከዓለም፣ ከሰይጣንና ከሥጋው ጋር ተፋልሟል፣ እናም አሸንፏል፤ በዘመኑ ሮጧል፣ ሩጫውንም በማሸነፍ አጠናቅቋል፤ ለሕያው ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ አብሪነት ያገኘውን ያልተሸቀጠ እውነት በመጠበቅ ሃይማኖትን ጠብቋል። ይንንም በሞቱ ዋዜማ ላይ ቆሞ አስተላልፏል። ይህ ነው እውነቱ የእኔ የሐውልቶች ቅኝት ግን በዚህ ወግ ውስጥ ያልተገኙ፣ ጭራሹኑ የጳውሎስን ፈለግ የተከተሉትን ሁሉ በማሳደድ ዕድሜያቸው የነጠፈ ሁሉ ተጽፎላቸው በማየቱ «አይ! የቀባሪ ጣጣ» አልኩኝ። በጉብኝቴም ለያስገርሙኝ የቻሉትን ሁሉ ለቃቅሜ ከመካነ-መቃብሩ ቅጥር ወጣሁኝ። ወጥቼ ያብከነከነኝ «ከአባቱ» የሚለው ጥቅስ ነበር፦

«የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፣ በአንተ ደስ ይለኛል» (ሉቃስ 3፡22) ይላል።

ይህ የተባለው በአንድ ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየው ለጋ ሕፃን ነው። ለለጋው ሟች ሉቃስ 3፡22ን ያልጠቀሰ ሌላ ጽሑፍ ሰፍሮ ቢሆን ግድ የለኝም። የወንጌል ጥቅሱ ግን የሚናገረው ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር አብ የመሰከረለት እውነት ነው። ምስክሩም ጽኑ ነው። ጥቅሱ ከጌታ በቀር ለማንም ሊነገርለት አይችልም፤ እርሱ ነው የአባቱን ፈቃድ ሊፈጽም የመጣ፤ መጥቶም ሲጨርስ «አባት ሆይ...የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኩህ» (ዮሐ. 17፡4) ያለ ብቸኛው እርሱ ነው። እንግዲህ ይህን የ«ቀባሪ አባት ጣጣ» ምን ይሉታል።

መቼም «ቀባሪ አታሳጣኝ» የሕዝብ የጸሎት አጀንዳ ነው። እርሱ ቆም እንድል አስገድዶ ይህን አስገነዘበኝ። ብዙ ሐውልቶች በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባሎችን በላያቸው ተሸልመው ቆመዋል፤ ሐውልቶቹን ያቆሟቸው፤ ጥቅሳ ጥቅሶቹንም ያሰፈሯቸው፤ ከሟች ኋላ የተገኙ ሰዎች ናቸው፤ ቀባሪዎቹ የነገ ተረኞቹ፤ እነዚህ ሰዎች ለሟቾቹ አግባብነት የጎደለውንና አልፎ አልፎ አግባብ የመሰሉ ተስፋ-ነክ ቃላትን ሲቀሽሩ፣ ስለ ራሳቸው አስበው ይሆን? መቼም ከሞት በኋላ ለፍርድ ሁሉም በሕያው እግዚአብሔር ፊት

ይቆማል። አንዱ ቃሌን ለምን አልታዘዛችሁም ሲሆን፤ ሁለተኛው የላክሁላችሁን መድኃኒት ኢየሱስን በሕይወት ሳለችሁ ለምን አላመናችሁበትም? ማለቱ አይቀርም። እናም ለመጪው ይግባኝ- የለሽ ጥያቄ መልሱ አሁኑኑ ሊሰጥ ይገባል። ይህን ለአፍታ ከሁካታው ወጥተን ቆም በማለት በአግባቡ ከመለስን፣ «ቀባሪ አታሳጣኝ» የጸሎት አጀንዳ መሆኑ ይቀራል። ከሞት በኋላ በአጉል ተስፋ ከመጀቦን፣ ዛሬ ለእውነቱ መገለጥ የተሻለ ምርጫ ነው።

«ሰዶማዊነት...»

«እርሱን በማንበብ የልጅነቱን ወራት አስታውሶ በትዝታ ስሜት ውስጥ የማይዋልል የለም»

የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ

ዓርብ ጎዳር 6 ቀን 1950 ዓ.ም

ይህ ሁነኛ አስተያየት የተቸረው «መስከረም» ለተሰኘው የታደሰ ሊበን «የአጭር ልብ ወለድ» መድብል ነው። የልብ ወለድ ሥራው ወጥነት ኖሮት ቀዳሚ በመሆን ለሕዝብ የተዋወቀው የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ወዲያው ተበረታቶ ሌሎች ስድስት አጭር ልብ ወለዶችን በዚያው ዓመት አድርሶ እንደ ነበር ሥራው ይመሰክራል።

የጻፈው ሁለተኛ መጽሐፍ «ሌላው መንገድ» ይባላል። በውስጡ ከተሠሩት ሥራዎች አንዱን ነቅሼ ሳወጣ፣ በገጽ 55 ላይ «አንድ አጋጣሚ» የተሰኘ ጽሑፍ ይገኛል።

ይህ ሥራ «ሰዶማዊነት ይውደም» ለምልለት ጽሑፍ መነሻ ሆኖ ኖል። ከአርባ ዓመታት በፊት በወሲብ የተመሳሳይ ጾታ ተፈላላጊነት የታወቀ መሆኑ፣ ጉዳዩ በደራሲው ዘንድ አሳሳቢ ሆኖ «እንጠንቀቅ» የማለቱ ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ፣ በግርድፉ ታሪኩን አሳውቃች ኋለሁ፡- «እኔ» እያለ የሚናገረው የታሪኩ ዋንኛ በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተቀጥሮ መሥራት ሲጀምር ገና ሁለት ዓመቱ ሲሆን፣ እድሜው ሃያ አንድ ነበር።

ይህ ወጣት አንድ ቀን የባንክ ደንበኛቸው በሆነው ሰው ዓይን ውስጥ ይገባል፤ እንዲታይ ያደረገው ሁነኛ ምክንያት አካላዊ ቁመናው፣ ውበቱ እና አለባበሱ እንደ ነበር መጽሐፉ ይገልጻል። የወሲብ ጥቃት ሊፈጸምበት የነበረው ይህ ወጣት በገዛ አንደበቱ ስለ ቁመናው እንዲህ ብሏል፦ «...ቀጥ ያለ አፍንጫ፣ ትክክል የሆኑና ንጣታቸው በረዶ የመሰሉ ጥርሶች፣ እጅግም ያልወፈሩ እጅግም ደግሞ ያልሳሱ መለስተኛ ከንፈሮች፣ ቅንድቦቼ ትክክል መሆናቸውና መጥቆራቸው ሰዎች ተኩሏል ወይም ተከርክሟል አሰኝተው የሚያወሩላቸው ፀጉሬ፣ ግንባሬ፣ ጉንጮቼ፣ ጆሮዎቼ፣ እምንም ዘንድ ያልተዛቡት በጠቅላላው የሠራኝን እጅ ረቂቅነት አጉልተው የሚያወሱ ነበሩ። ለሴቶቹም የማይችሉት ፈተና ነበርኩኝ...» (ገጽ 55)።

ይህ ገጽታ ያለው ወጣት በ1942 ዓ.ም ሊተዋወቀው ጥረት ከሚያደርገው ሰው ጋር ይገናኛል። በዕለቱ ወጣቱ አለባበሱን ራሱ ሲገልጸው፦ «ወደ ሥራ ለመሄድ ስወጣ በጣም አምሬ በመስከረም ወር ከሌሎች ቀደም ብሎ የፈነዳ አደይ አበባ ወይም ፀሐይ በተለይ በእርሱ ላይ ብቻ ፈንጠቅ ያለበት ጽጌሬዳ መስዬ ነበር፤ ይህም ደግሞ እውነት ነበር። ኮቴ አሁን እንኳን ያኔ ለብሼው የተነሣሁት ፎቶግራፍ እቤት አለኝ። ድሮ ፈረንጆች የሰይጣን ቆዳ ከሚሉት ጨርቅ የተሰፋ ሱሪዬ ለኮቱ የሚስማማ ዳለችማ ገበርዲን፣ ሸሚዜ ነጭ አሚዶ በሚሉት ነጭ ዱቄት የተተኮሰ፣ ጫማዬ ቡና መልክ፣ ከረባቴና የእግር ሹራቦቼ ደግሞ በልብሶቼ መልክ ግጥም የሆኑ ነበሩ» (ገጽ 57)።

ከላይ የተላለፉት ሁለቱ ገለጻዎች ሲጣጣሙ ሊሰጠን የሚችለው ፍቺ፦ ቁመናው ያማረ ነው፤ የሚያደርገው ሁሉ የሚቀበለውና ድምቀት ሰጥቶ ለሚያየው ሁሉ እንኳን ሴትን ወንድን ሊያነሆልል የሚችል መሆኑን ያሳውቃል። ይህ ወጣት ነው በአንድ ወንድ የተ ፈቀረው፤ አፍቃሪው ለወጣቱ ሁሉን ሊያደርግለት እንደሚችል፣ በጎደለው ሁሉ አስፈላጊውን ገጸበረከት ሊያዘጋጅለት እንዳለው ያሳውቀዋል፤ በዘበኛ በጥብቅ በሚጠበቀው ጭር ባለው ቤቱ ውስጥ ጋብዞም ሁሉን ያቀርብለታል፤ ቀስ በቀስ አንዲትን ሴት በመጠጋጋት፣ በመነካካት፣ በመዳሰስና በመሳም ሊፈጠር

የሚችለውን የወሲብ ቅድመ- ዝግጅት በወጣቱ ላይ ይሞክራል፤...

ደራሲው ታደሰ ሊበን እነዚህን ሁኔታዎች «አንድ አጋጣሚ» በሚለው ሥራው ውስጥ አዋውጦ፡- በዘመኑ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ዎች በጎብረተሰቡ ውስጥ ሊታዩ እንዳሉ፣ እንደ ታዩም በማስጠንቀቂያነት «ጆሮ ያለው ይስማ፣ ዓይን ያለውም ይይ» በማለት በስልታዊ ገለጻ ሥራውን ይደመድማል።

* * *

ዛሬ እኔ ደግሞ በ1942 ዓ.ም ተፈጸመ ከተባለበት 50 ዓመት በ ኋላ የተመሳሳይ ጾታ ወሲባዊ ግንኙነት አሳስቦኝ፤ እናም «ዝምታ» መፍትሔን ስለማይጠራ፣ አንድም በዓለም ዙሪያ ያሉ «ስመ ቤተ ክርስቲያናት» በዚህ አካሄድ ላይ ያላቸውን የዘንድሮ አቋም በማሳወቅ፣ አንድም ሰዶማዊነት በእግዚአብሔር ቃል ሲፈተሽ ምን ምን ልከኛ መልእክት እንዳለው ለመግለጽ ተነሣሣሁ።

አንድ የአገሬ ምሳሌያዊ ንግግር አለ፤ «ወርቁ ከዛገ ብረቱ ምን ይሆን?» ይላል። ከማዕድናዊ ባሕሪው የተነሣ ወርቅ አይዝግም፤ ብ ረት ግን ሊዝግና ሊበላሽ ይችላል። እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ ያለውን በብረት የተመሰለውን ዓለም ብርሃን በመሆን ጨለማን እንዲገልጡ ክርስቲያኖችንና ቤተ ክርስቲያንን አኑሯል። እነዚህ እንደ ወርቅ የተመሰሉት በሰዶማዊነት ላይ ዝገት ሊታይባቸው ከሆነ «ጮክ» ብዬ እንደ ታደሰ ሊበን «እንጠንቀቅ!» ማለቴ ተግባሬ ይሆናል።

በቅድሚያ፣ «የስመ አብያተ ክርስቲያን»ን እንቅስቃሴ በግርድፉ እንዲህ አቀርባለሁ፡-

* * *

የተባበሩት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን «United Church of Christ» (እ.ኤ.አ.) በ1970 ዓ.ም ሰዶማዊ የሆኑ ሰዎችን ለቅስና አገልግሎት ሾመች።[3]

* * *

በኤፒስኮፖል ቤተ ክርስቲያን «Episcopal Church» በ2.4 ሚሊዮን ተከታዮች ዘንድ መከፋፈልን ያመጣ ርእሰ ጉዳይ፡- ሰዶማዊ ቄሶች አይሾሙ፤ በዋናነት፣ የሰዶማዊነት (የወንድ ለወንድ

ግንኙነት) እና የሌዝቢያን (የሴት ለሴት ግንኙነት) እንቅስቃሴ አራማጆች ቸል የማይባሉ በተከታይነት ያወዛገቡ ክርክሮች ነበሩ።[4]

* * *

በአሜሪካን የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን «Pesbyterian Church (U.S.A)» (እ.ኤ.አ.) በ1997 ዓ.ም በጥቅሉ 2.7 ሚሊዮን በሚደርሱት አባሎቻቸው ዘንድ የቤተ ክርስቲያኑ መሪ አባላት በሕጋዊ ትዳር የተጣመሩ፣ አልያም ላጤ የሆኑ፣ አልያም በብትውና ለመኖር የወሰኑ ብቻ ሊሆኑ ይገባል በማለት ወሰኑ። ይህ ውሳኔ ግን ተቃውሞን በሰዶማዊ እንቅስቃሴ አራማጆች ዘንድ አሳድሮ ሰፊ የአመለካከት ልዩነት ሰፈነ።[5]

በርካታ የተባበሩት ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን «United Methodist Church» አገልጋዮች (እ.ኤ.አ.) በ1997 ዓ.ም በበተነት በራሪ ወ ረቀት ላይ «ሰዶማዊነት ግላዊ ነጻነት በመሆኑ፣ መሪዎች የቅጣት ጅራፍን ይዘው ወደ መኝታ ቤታችን አይምጡ፣ ያለ ጣልቃ-ገብ ክልከላ የሌለው የነጻነት ስፍራችን መኝታ ቤታችን፣» በማለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቅጣትን እንዳይበይኑ ወሰኑ።[6]

እነዚህ አራት ያህል ናሙናዎቼ በወርቅ የተመሰሉት ምን ያህል በሰዶማዊነት ጉዳይ ዝገት እንዳጠቃቸው ይጠቁማል። አስከትዬ ዘርዘር አድርጌ የምገልጸው የወንድና የሴት ግንኙነት መሠረታዊ አካሄድን፣ በሶዶማዊነት ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻን እና ሶዶማውያን የሚያነሷቸውን ክፍሎች ልከኛ ዳኛ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ምን ሊሆን እንደሚገባው ነው። በመጨረሻም፣ «የጆሮ ያለው ይስማ» መልእክቱን አሰምቼ እደመድማለሁ።

መልእክተ አንድ

> «ነገር ግን ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ በዚህ ምክንያት ሰው አባትና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል፣ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ... እንግዲህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው» (ማር. 10፡6፣9)።

ኢየሱስ በዚህ ንግግሩ ያጸናው መሠረታዊ እውነት የዘፍጥረት 1:27 እና 2:24 መለኮታዊ የወንድና ሴት ግንኙነት ነው።።።

እግዚአብሔር ከመነሻው ሰውን ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠረ። ይህም ከአዳም ውድቀት በፊት ጀምሮ ለዘላቂነት ሩካቤ ሥጋ ሊፈጸም የተገባው በወንድና በሴት መካከል ብቻ መሆኑን አስተማረ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከመነሻው ጀምሮ ሊሆን የተገባው ግንኙነት ከዚህ ውጪ እንደማይሆን በትምህርቱ የደነገገበት ይህ መነሻ በሌሎች ክፍሎችም ውስጥ ተስፋፍቶ ተገለጸ። እውነቱ ያለ ለውጥ የተገለጠባቸው ስፍራዎች በማቴዎስ 19:4-6፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 6:16፣ እንዲሁም በኤፌሶን 5:31 ላይ ታየ። ይልቁኑ፣ የጳውሎስ መልእክት በኤፌሶን 5:31 ላይ አድጎ፣ የባልና ሚስት ግንኙነት እንደ ክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ዓይነት መሆኑን አብራራ። ለዚህም ምሳሌነት ብቃቱ የባልና የሚስት ግንኙነት ልክኛ ፣ ተፈጥሮአዊ፣ ዘላቂ እና በመዋለድ ሕያውነትን ማግኘው መንገድ በዚሁ ብቻ መሆኑ ጸና። ይህ በምንም ዓይነት በተመሳሳይ የጾታ ተጋሪዎች ዘንድ አይገኝም።

ይልቁኑስ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽኑ መልእክቶች ሰዶማዊነትን በመኮንን ብቻ ሳይሆን፣ አግባብነት የጎደላቸውን ልክኛ የሚመስሉ የሩካቤ ግንኙነቶች በታቀደላቸው መሠረት እንዲፈጸሙ ይመክራሉ፣ ይገልጻሉም። አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት፣ በተለይም ዘሌዋውያን፣ በትዳር ውስጥ ያልተፈጸሙትንና በትዳር ውስጥ ሳሉ ታማኝነት የጎደለው መተላለፍ በዝሙትነቱና በርኩስነቱ በመግለጽ በእስራኤላውያን መካከል ሊገኝ የተገባውን የቅድስና መለኪያ ያጸናል።

መልእክተ ሁለት

የሰዶማዊነት ነውሮች የፈጸመባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንና ይህንን እንደ ልክኛ አካሄድ የሚሄዱበት እና የሚከላከሉበትን ምክንያት እያስተሳሰርኩ ላመላክት፦

ዘፍጥረት 19:1-29

«... ሕዝቡ ሁሉ ቤቱን ከበቡት፣ ሎጥንም ጠርተው እንዲህ አሉት፦ በዚህ ሌሊት ወደ ቤትህ የገቡት ሰዎች ወዴት ናቸው? እናውቃቸው ሩካቤ እንፈጽምባቸው ዘንድ ወደ እኛ አውጣቸው።... ሎጥም ይህን ክፉ ነገር አታድርጉ፤ እነሆ፣

ወንድን ያላወቁ ሁለት ሴቶች አሉኝ፣ እነርሱን ላውጣላችሁ...» (ዘፍጥ. 19፡4-9) አላቸው።

ይህ ክፍል በቅጡ የሚናገረው ለሰዶምና ለጎሞራ ጥፋት ምክንያት የሆነው የሕዝቡ በሁሉ ዘርፍ መረን-የለሽ መሆን ነው። ይልቁኑ፣ ወደ ሎጥ ቤት የገቡትን ሰዎች ለመገናኘት መወሰናቸው የእግዚአብሔር ቅጣት በእነርሱ ላይ እንዲወድቅ አድርጎታል።

ሶዶማውያኑ ግን ይህንን አይቀበሉም። የሰዶምና የጎሞራ መጥፋት እንግዶችን በአግባቡ ባለማስተናገድ የመጣ እንጂ፣ የምስስል ጸታ ድርጊትን ለመፈጸም በተደረገ አይደለም ይላሉ፣ (ሕዝ. 16፡49-50) «እነሆ፣ የእኅትሽ የሰዶም ኃጢአት ይህ ነበረ፡- ትዕቢት፣ እንጀራን መጥገብ መዛለልና ሥራ መፍታት... እንዲሁም በፊቴ ርኩስ ነገር አደረጉ አጠፋኋቸው።» ማለቱ ከሶዶማዊነት ክስ ነፃ ያደርጋል በማለት ይከላከላሉ።

ይህ መከላከል ግን ዕረፍትን በሙሉነት አይሰጥም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአግባቡ እንግዶችን አለመቀበልና አለማስተናገድ አንድም ጊዜ በርኩሰት ተፈርጆ አይታወቅም። ይልቅስ፣ ሕዝቅኤል 16፡50 ለሰዶም ጥፋት ዋንኛው በፊቱ ርኩስ ነገር መፈጸማቸው መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም፤ ያም ርኩሰት በዘሌዋውያን 18፡22፣ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ፣ ጸያፍ ነገር ነውና» በማለት ሲያስጠነቅቅ፤ ይሁዳም በቁጥር ሰባት፣ «እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ... በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል» በማለት አዲስ ኪዳን ጽኑውን ልከኛ እውነት ያስረዳል።[8]

ዘሌዋውያን 18፡22፤ 20፡13

«...ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ፣ ጸያፍ ነገር ነውና...»

«ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል፤ ፈጽመው ይገደሉ፤ ደማቸው በላያቸው ነው» (ዘሌዋ. 20፡13)።

እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ሰዶማዊነትን በግልጽ ይኮንናሉ፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከሌላው ሕዝብ ተለይተው በቅድስና ይኖሩ ዘንድ የሙሴ ሕግ የሆነው ይህ ድንጋጌ በመሐከላቸው

በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆን ይደነገጋል። ሰዶማውያኑ ግን ይህን የሚያጣጥሉት ሕጉ ለእስራኤላውያን የተሰጠ ስለሆነ፣ ክርስቲያኖችን ሊገዛ አይችልም በማለት ነው። ይህንኑ ሲያጠናክሩትም፣ ክርስቲያኖችን ሊገዛ አይችልም በማለት ነው። ይህንኑ ሲያጠናክሩትም፣ «ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ሆኖ» ሁላችንን ከሕግ እስራት ነፃ አውጥቶናል። ነጻነቱም የሶዶማዊነት ልምምድን ማድረግ ባለመንቀፍ ሊገለጽ ይገባዋል» ይላሉ።

የእግዚአብሔር ቃል ግን ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ መሆኑን ቢገልጽም፣ በአዲስ ኪዳን በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የክርስቶስ የሕይወት ሕግ በሥራ ላይ ሊውል እንደሚገባው ተጽፏል። ያም በአዲስ ኪዳን ሙሴ ለቅድስና አኗኗር የደነገጋቸው ደንቦች ጠንክ ረው ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ በሮሜ 1:26-27፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 6:9-11 እንዲሁም 1ኛ ጢሞቴዎስ 1:9-10 የሚያስተምሩት እግዚአብሔር ከመነሻው ያለውን የዘፍጥረት 2:24 ቃል በመሆኑ፣ አሁንም ለሶዶማዊነት የቀና መንገድ በዚህ የለም።

> «...ሰውነታቸውንም ደስ ባሰኙ ጊዜ ወስላቶች የሆኑ የከተ ማው ሰዎች ቤቱን ከበቡ በሩንም ይደበድቡ ነበር ባለቤቱንም ሽማግሌውን... እንድንደርስበት ሩካቤ እንድንፈጽምበት አውጣልን አሉት። ባለቤቱም... ይህን ክፉ ነገር እባካችሁ አታድርጉ አላቸው... ሰዎቹ ግን ነገሩን አልሰሙም...» (መሳፍንት 19:22-26)።

ይህ ገለጻ በትረካው ከሰዶምና ከጎሞራ ጋር የተቀራረበ ነው፤ ድርጊቱን ጸያፍ ያደረገው ሽማግሌውን ለመገናኘት ወንዶቹ ፈልገው መምጣታቸው ነው። ለመስተናገዱ የገቡበት ቤት ባለቤት ልመናውን የሚያቀርበው ልታደርጉ ያሰባችሁት «ክፉ ነገር» በመሆኑ አትፈጽሙ የሚል ነው። ሰዶማውያን ግን ይህን ክፍል ሲያቀሉት፣ ቤቱን የከበቡት ሰዎች ሰዶማዊ ግንኙነትን ለመፈጸም የመጡ አለመሆናቸው የሚረጋገጠው ባለቤትየው የሰውየውን ቁባት ባወጣላቸው ወቅት ሳይቃወሙ ከሴቲቱ ጋር ተገናኙ። ይህም «ያለ ፈቃደኝነት መደፈርን» ብቻ ይገልጻል፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ወንድየውን ካልሰጠኸን ብለው ባከረሩ በማለት ይከላከላሉ።[11]

የእግዚአብሔርን ቃል ስናይ ግን ልናስተውል የሚገባን ቁም

ነገር አጠቃላይ የመሳፍንትን ዘመንና ይፈጽሙ የነበሩትን ድርጊቶች ነው። ይህም «ሁሉም በፊታቸው ደስ የሚያሰኛቸውን ብቻ ያደርጉ ነበር» በመባል ተገልጿል። የሕዝቡ ሰውነታቸው በጥጋብ ሲነሣሣ ሊፈጽሙ የፈለጉት በአግባቡ ሊፈጸም የተገባውን ወሲባዊ ግንኙነትን ሳይሆን፣ ተቃራኒውን ነበር።

*1*ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፡-

«ዳዊትም ለሳኦል መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች፣ ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው።»

«የሳኦል ልጅ ዮናታን ግን ዳዊትን እጅግ ይወድድ ነበር።»

«...እየተላቀሱም እርስ በርሳቸው ተሳሳሙ፣ ይልቁንም ዳዊት እጅግ አለቀሰ።» (*1*ኛ ሳሙ. 20፡41)

«...ወንድሜ ዮናታን ሆይ፣ እኔ ስለ አንተ እጨነቃለሁ፣ በእኔ ዘንድ ውድህ እጅግ የተለየ ነበረ፤ ከሴት ፍቅር ይልቅ ፍቅርህ ለእኔ ግሩም ነበር» (2ኛ ሳሙ. *1*፡26)።

አራቱ ተከታታይ ገለጻዎች እርስ በርስ ይደጋገፋሉ፤ ሊሉ የሚወዱት በዳዊትና በዮናታን መካከል የጠለቀ ወንድማዊ የሆነ የጓደኝነት ፍቅር አለ የሚል ነው። ከዚህም የተነሣ እርስ በርሳቸው ይተሳሰባሉ።

ሰዶማውያኑ ግን ይህን አይረዱም፤ አይቀበሉምም። ይልቁኑ፣ የሚሉት ነጥብ ሁለቱ ሰዎች ሰዶማውያን ነበሩ። ከዚህም የተነሣ ዳዊት ስለ ዮናታን የሚገልጸው ገለጻዎች የተራክቦ ግንኙነት በመሐላቸው ያሉ ሰዎች የሚሆኑትንና የሆኑትን ነው በማለት ለጉዳያቸው ዋቢ ያደርጉታል።[12]

ጤናማው የመጽሐፍ ቅዱስ አቅጣጫ ግን፡- በሰዎች መካከል የወዳጅነት መጠጋጋትና መቀራረብ ምን ጊዜም ሊኖር የሚችል መሆኑን ያስረዳል። የያዕቆብና የልጁ የቢንያም፣ የኢየሱስና የደቀ መዝሙሩ የዮሐንስ ቅርርብ፣ በዳዊትና በዮናታን ላይ ከታየው ጋር አቻ ነው። ሰዶማውያኑ ግን እነዚህን የመሳሰሉትን ግንኙነቶች የዘነጉ ይመስላሉ።

ማጠቃለያ

ለ«ሰዶማዊነት ይውደም» «የጆሮ ያለው ይስማ» መልእክቴን በሮሜ 1፡24-32 ባለው መልእክት ላይ አደርጋለሁ፤ እንዲህ ይላል፡- «...ሰዎች ይህን በማድረጋቸው ምክንያት እግዚአብሔር ለአስነዋሪ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸው እንኳ የተለመደውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባልተለመደ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶቹ የተለመደውን የግብረ-ሥጋ ለመገናኘት በብርቱ ተመኙ፤ ስለዚህ ወንዶች ከወንዶች ጋር አሳፋሪ ነገርን ፈጸሙ...» በማለት ሐዋርያው ጽፏል። ይህ ተነባቢ ክፍል ሰዶማውያን የእግዚአብሔርን ጽኑ ሕግ መተላለፋቸውን ያረጋግጣል። የዚህ መተላለፍ ጦስ ደግሞ እግዚአብሔር ሕግ መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፤ የዚህ መተላለፍ ጦስ ደግሞ፡- እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ በመፍጠር ያዘጋጀውን የጋብቻ ቤተሰባዊ ስንስለት ያጠፋል፤ የዚህ መጥፋት ደግሞ ለግለሰብ፣ ለቤተሰብ፣ ለኅብረተሰብ እና ለአገር ልማትን ሳይሆን ውድቀትን፣ ክብረትን ሳይሆን ውድመትን ይጋብዛል። ሶዶማዊነት ከእግዚአብሔር መለኪያነት ጋር አለመግጠም በመሆኑ፣ ለትስስራዊ ሕይወት ጨለማን በማስፈን ንክኪው የበዛ ችግር ይጋብዛል፤ ከዚህም የተነሣ ጽኑ መፍትሔን በማጤን ለዚያም መገዛት ይገባል፤ ያም ከእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ከሆነው አሳብ ጋር መጣጣም ነው።[13]

ታደሰ ሊበን በመጽሐፉ ያነሣሣው የሶዶማዊነት መግለጫ ዛሬ በአገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ መሄዱ እሙን ነውና፣ የክርስቶስ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ድምጿን ከፍ አድርጋ፣ «አምላክን ለመገናኘት ተዘጋጁ» ልትል ይገባል።

የግርጌ ማጣቀሻ

1. ታደሰ ሊበን፣ <u>ሌላው መንገድ</u>፣ ገጽ 55።
2. ታደሰ፣ ገጽ 57።
3. Larie Good Stein, "<u>I Can be Fully Myself Gay and Christian,</u> p.24.

4. Good Stein, p.24.
5. Good Stein, p.42.
6. James V. Heidinger, Gay & Sex, p.30.
7. Homosexual & the Bible - Bad News of Good News.
8. Derek Kidner, Genesis: an Introduction and Commentary, p.137.
9. Holy Bible, Romans 10:4.
10. Charles C. Ryrie, The End of the Law, p.124.
11. Dr. Walter Wink, "Homosexuality and the Bible, p.19-21.
12. Robert Williams, Just as I am.
13. The Bible and Homosexuality-Family research council, p. 3-24.

የሴቶች ድርሻ

በጎብረተሰቡና በቤተ ክርስቲያን

ይህ ጥናት የርእሱን ጠቋሚነት በመግለጥ ይጀምራል፤ «ሴቶች» የሚለው ቃል ስለ አንዲት ሴት ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ብዙዎ ዎች ተናጋሪ ነው፡፡ «ሴቶች» በማለቱ ከወንዶች ነጥሎ እነርሱነታቸው ላይ የበለጠ አጽንኦት ለመስጠት እንደ ፈለገ ያስ ረዳል፤ እኒህ ሴቶች የተልዕኮ ባለቤት ስለሆኑ፣ «ድርሻ» ኖሮአቸዋል፤ ድርሻ፡- ተካፋይነትንና ተጠያቂነትን የማጣቆም አቅም አለው፤ አጠቃላይ የሰውን ልጅ ከግምት የሚያስገባ ቃል ደግሞ «ጎብረተሰብ» ነው፤ የሰዎች በጎብረት (በጋራ) መኖር፡- በዚህ ውስጥ የሰዎችን እኩሌታ የሚወስዱት ተ ጠሪዎች ሴቶች ናቸው፡፡ ጎብረተሰብ የአንዲት ጀምበር ውጤት ሳይሆን፣ የዘመናት የትውልዶች ሰንሰለታዊ ጉልህ ፍሬ ነው፡፡

ከዚህም የተነሣ፣ የዚህ አካል ሆነው ኅብረተሰብን ኅብረተሰብ ያሰኙትን ሴቶች ማጥናት ተገቢና የጋራ ጉዳይ መሆኑን ያረጋግጣል። ኅብረተሰብ ወንድ አይል ሴት፣ ሕፃን አይል አዛውንት፣ የተማረ አይል ያልተማረ፣ ዘር አይል ጎሳ፣ ሁሉን አቅፎ ተጓዥ ሀብት ነው። በዚህ የኅብረተሰብ አካል ውስጥ ሌላ ዘርፍ አለ፤ በክርስቶስ የተጠሩ ለዳግም ልደት የበቁ አማኞች፤ እኒህ አማኞች በኅብረት ሆነው የተሰጣቸውን ተልዕኮ ይፈጽማሉና «ቤተ ክርስቲያን» ተብለው ይጠራሉ። ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን ካሰኟት ዋንኞቹ ተጠሪዎቿ ወንዶችና ሴቶች በአንድ መገኘታቸው ነው። ይህ ደግሞ የሴቶች ድርሻ በኅብረተሰቡ ውስጥ በሙልዐት፣ በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን በሰፊው ተጠሪ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

እንግዲህ መነሻችን በፍንጭ ሰጪ ርእሰ ጉዳይ ምንነት ላይ ከተንደረደርን፣ በተከታታይ ልንመለከታቸውና ልናጤናቸው የተገቡትን መሠረታዊ ነጥቦች አብረን እንምከር።

አንድ፡- ርእሱ መነጋገሪያ መሆን ለምን አስፈለገው?

ሁለት፡- ሴቶችና ሀገራዊ ግንዛቤ መነጋገሪያ መሆን ለምን አስፈለገው?

ሦስት፡- ሴቶችና ድንበር-አለፉ ግንዛቤ?

አራት፡- የሴቶች ድርሻ በኅብረተሰብ ውስጥ

አምስት፡- የሴቶች ድርሻ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

ስድስት፡- ሴቶችና የእግዚአብሔር መንግሥት

ሰባት፡- ማጠቃለያ

ከማጠቃለያ ውጭ ስድስቱ ተከታታይ ርእሰ ጉዳዮች ተሳሳሪዎች ሆነው አንዱ በሌላው ላይ እየተገነባ ወደ ተፈለገው አቅጣጫ ያጓጉዘናል። በየርእሶቹ ቀድመን ልናስተውል የሚገባን መሪ ሀሳብ ይኑረን ካልን፣ የጥናቱ መብራት ኤርምያስ ምዕራፍ 1 ነው። ኤርምያስ ሰማያዊ ተልዕኮ አለው፤ መመሪያው፣ «...እንግዲህ እንድትነቅልና እንድታፈርስ፣ እንድታጠፋና እንድትገለባብጥ፣ እንድታንጽና እንድትተክል በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ዛሬ

ሾምሁህ» ይላል። ይህ ቃል በውስጡ ሁለት ተልዕኮዎች ይዟል፡- ቀዳሚው በሰው ልጆች አኗኗር ውስጥ የእምነትና የአኗኗር መሠረት ሆኖ ከደማቸው ጋር የተቀላቀለ የሚመስለውን አጉል ትምህርት፣ አጉል ፍልስፍና ሁሉ እንዲያፈርስ፣ እንዲያስወግድ ታዟል፤ ከዚሁ ኃላፊነት ጎን ለጎን ሌላው አቻው ተልዕኮ፡- በፈረሰበት ቦታ ሌላ ግንባታ፣ በተነቀለበት ስፍራ ሌላ ተክላ መሆኑ ነው፤ ይህ ሌላው ተግባር በትክክለኛው እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና አተገባበር ላይ መሠረት መጣል ነው።

1) ርእሱ ለምን ተተኪ አጀንዳ ሆነ?

ርእሰ ጉዳዩ መነጋገሪያ መሆን ለምን አስፈለገው? መነጋገሪያ የሆነበት ምክንያት አጀንዳው፡- ትናንት የነበረና ዛሬም ነገም ሊኖር እንደሚችል መታመኑ በበቂ መልስነት ያስጠራዋል።

የሰው ልጆች ባሉበት ስፍራ ሁሉ ሰውን ሰው ያሰኙትና ሰው የሆኑት ሴቶች በዚያ አሉ፤ ሊመገቡ፣ ሊለብሱ፣ ሊጠለሉ፣ ሊኖሩ፣ ሊወልዱና ሊዋለዱ፣ ሊሠሩና ሊያሠሩ፣ በግላዊና በማኅበራዊ ኑሮ ሁሉ ውስጥ ይገኛሉ፤ ይኖራሉም። መኖራቸው ነው መነጋገሪ ያነታቸው፤ ሕልውናቸው ነው መወያያ አጀንዳ የሚያደርጋቸው።

እነርሱን ከወንዶች አስለይቶ መነሺያና መጠቆሚያ የሚያደርጋቸው ደግሞ፡- ከልዩነት ማደግ የተነሣ በሰዎች ሁሉ ዘንድ ሊባነንበት፣ ሊነቃበት የሚገባ ነጥብ መኖሩ በአንድ ወገን፤ በትይዩም ባለማወቅ ወይም ባለማስተዋል ሴቶች የዘነጓቸውን ወይም የተዋቸውን ለማመልከት መነሣቱ ጉዳዩን መነጋገሪያ እንዲሆን ያደርገዋል የሚል እምነት ይኖረኛል።

ይህን ደግሞ ለማረጋገጥ እና ተገቢ እርምጃ ለመውሰድ፡-

ሀ. በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክልሎች ይሁንኝ ባልተባለ የሥራ ጉብኝቶች በመገኘት ግንዛቤን በማዳበር፤

ለ. ከአብዛኛው ቤተ እምነቶች በከፊሎቹ በመገኘት የሴቶችን ድርሻና አስተዋጽኦ በግርድፉ በማጥናት፤

ሐ. በሴቶች ላይ የተጻፉ ሀገራዊ ዐውደ ጥናቶችንና ጽሑፎችን በመመልከት፤

መ. በቅድመ-መሰናዶ የትምህርት ፕሮግራሞች በተለይም በእቴጌ መነን (በየካቲት 12 የመሰናዶ ትምህርት ቤት) ተማሪዎች በሴቶች ጉዳይ ላይ የጻፏቸውን ጥናቶች በመፈተሽ፤

ሠ. ሀገራዊ አመለካከቶች፣ አባባሎች፣ መዝገበ ቃላዊ ፍችዎች ሴቶችን በተመለከተ ያቆሙትን ድንጋጌ በማጤን፤

ረ. ሀገራዊ ያልሆኑ ድንበር-አለፍ የምርምር ጽሑፎች ሴቶች በጎብረተሰቡና በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ የከተቡትን መመልከት ይህን ርእሰ ነገር መነጋገሪያ ወይም ተተኳሪ አጀንዳ እንዲሆን አብቅቶታል።

እንግዲህ ርእሳችን እንጉዳይ ወይም የጅብ ጥላ ሆኖ ድንገት በቅሎ የታየ ሳይሆን፣ በአጠገባችን የኖረ እንደ ነበር ልብ ማለት ተገቢ ነው። እናም በአግባቡ ሊጠና በመገባቱ እንደ ጸሐፊነቱ «ጆሮ ያለው ይስማ! ያነበበም ያስተውል» እላለሁ።

2) ሴቶችና ሀገራዊ ግንዛቤ

ሀገራዊ መዝገበ ቃላት ሴትን በተመለከተ ሊሰጡ የሞከሩት ትርጓሜ በሴት ማንነትና ድርሻዋ ምን ሊሆን እንደሚችል በሚከተለው ትንታኔ ውስጥ ይመልከቱ፡-

ትንታኔ 1. ከሣቴ ብርሀን ተሰማ፡- በ1951 ዓ.ም እንደ ጻፉት፣ «ሴት ማለት፡- የተፈጥሮ ባሕርይዋ ቀዳዳና ስንጥቅ የሆነ እንስት፣ በፍጥረታ ከወንድ አባላዘር የዘር አካል የሚሆን ዘርን ተቀብላ ልጅን የምትወልድ የወንድ ረዳት» (ገጽ 291) በማለት ይተረጉሟታል።

ይህ ትንታኔ አጽንኦት የሚሰጠው፣ አካላዊ መለያንና የሴትን ወላድነት በማመልከት መገታት ነው።

ትንታኔ 2፡- ደስታ ተክለወልድ በየካቲት 17 ቀን 1956 ዓ.ም እንደ ጻፉት፣ «ሴት ማለት፡- ሚስት፣ የወንድ ጣምራ፣ ሁለተኛ ባልተቤት፣ የቤት አስተዳዳሪ 1ቆሮ 7፡2-4 «ነገር ግን ከዝሙት ለመጠበቅ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ትኑረው እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት...ሚስት አካልዋ የራስዋ ብቻ አይደለም፤ የባሏም ነው፤ (ገጽ 1209)

ይህ ትርጓሜ፡- የትዳር ምንነትን በማብራራትና ሴት ለወንድ

ያስፈለገችበትን መሠረታዊ ምክንያት በመግለጽ «ባል-ተኮርና ቤተ ሰብ-ተኮር» ድርሻዋን ይገልጻል።

ትንታኔ 3. ፖለቲካዊና ማኅበረሰባዊ መዝገበ ቃላት በ1978 ዓ.ም እንደ ጻፈው፣ ሴቶች፡- የዜግነት፣ የእናትነትና የሠራተኛነት መብታቸው መረጋገጥ በዋናነት ተጠቃሽ ነው። ይህን ለማስከበርና ለሕፃናት ደህንነት መጠበቅ፣ ለሰላም፣ ለዲሞክራሲና ለብሔራዊ ነፃነት መረጋገጥ መታገልና መደራጀት፤ ሴትን ሴት ሊያደርጋት ይችላል። ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ1911 ዓ.ም ጀምሮ፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ የሚከበረው ማርች ስምንት የሁልጊዜ የማንቂያ ደውል ይሆናል» (ገጽ 138-9) ይላል።

ይህ ትርጓሜ በማርክሲዚም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት የተገኘ ጭምቅ መልእክት ሲሆን፣ በይዘቱ ሴቶችን ከማኅበረሰባዊ የሕይወት ገጽታና አኗኗር አካያ ሊተረጎም እንደሚገባ ያመላክታል።

ትንታኔ 4. በ1993 ዓ.ም የአማርኛ መዝገበ ቃላት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር እንዳዘጋጀው፡- ሴት ማለት እንስት፤ ከወንድ የተለየ የተፈጥሮ ምልክቶችና ባሕርያት ያሏት ሰው፤...በማለት (በገጽ 134) ይተረጉማል።

ይህ ፍቺ ከወንድ በተለየ የተፈጥሮ አካላዊ ምልክቶች ላይ ከማተኮር ባሻገር፣ ከወንድ የተለዩ ባሕርያት ወራሽ በመሆን መለያ እንዳላት አመላክቷል፤ በትይዩም በፍቺው «ሰው» በማለት ሙሉ ስብዕና ያላት መሆኗንም አረጋግጧል።

ሀገራዊ ግንዛቤ አመላካች ይሆናሉ ተብለው የተመረጡት እነዚህ መጻሕፍት በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀመጡ መሆናቸውን ልብ ማለት ተገቢ ነው።

በዚህም ካለፉት 50 ዓመታት ወዲህ የተዘጋጁ መዝገበ ቃላት ከፊሎቹ ባዘጋጁት ሊቃናት ስም የተሰየሙ ሲሆኑ፣ ከፊሎቹ ደግሞ በቡድን ከመዘጋጀታቸው የተነሣ የወል ስያሜን ይዘው ቀርበዋል፤

አቅርቦቱ፡-

ሀ. ዓመታት በጨመሩ ቁጥር የግንዛቤ መዳበርን በማመልከት ስለ ሴቶች የተሰጡ ሀገራዊ እይታዎች አድማሰ-ሰፊ የመሆን አቅምን አዳብረዋል።

ለ. በየጊዜው የተሰጡ ፍቺዎች ከግል ጠባብ መረዳት አኳያ ብቻ የሚታዩ ሳይሆን፣ አዘጋጆቹ የጎበረተሰቡ አባላትና ነዋሪ ሰዎች ከመሆናቸው የተነሣ የብዙዎችን ውክልና ይዘዋል።
ሐ. ርእሰ ጉዳዩን ከግል ወደ ማኅበር፤ ከማኅበር ወደ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ እይታ በማጣቀም፡- ሰዎችን ሁሉ በተሳሰረ (በተያያዘ) ሁኔታ መረዳት ተገቢነቱን አሳይተዋል።
ከዚህ ቀጥሎ ከመዝገበ ቃላት ትንታኔ በመውጣት ሐቃዊ የመኖር እይታን ከሀገራዊ ትውፊቶች አኳያ በማጤን ሴቶችን ጎበረተሰቡ እንዴት እንደሚረዳቸው ከምሳሌያዊ አነጋገሮች በመነሣት እንገምግም፡-

«ሴት ለቤት፣ ወፍጮ ለዱቄት» (ለውጥ-የለሽ ኑሮ)
«ሴትና መሬት የማይችሉት የለም» (ያለ ርኅራኄ መተው)
«ሴት በማጀት፣ ወንድ በችሎት» (ለአደባባይ አለመብቃት)
«ሴት ታውቅ፣ በወንድ ያልቅ» (ለውሳኔ መገደብ)
«ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ፣ የት አለ ንግዱ» (ተጠራ-አልባነት)
«ሴት በዛ፣ ጎመን ጠነዛ» (የሥራ ፈትነት መንሥኤ)
«ሴት ካልወደደች ቋንጣ አትጠብስም» (አድሏዊ ግንዛቤ)
«ሴት ካልዋሸች፣ ባልዋን ትወልዳለች» (የግብታዊነት መንሥኤ)
«ሴት የወደደ ገሀነመ እሳት ወረደ» (ለዳግም ሞት አብቂ)
«ሴት ያፈቀረ ጉም የዘገነ» (እምነት-አልባ)
«ሴት ያመጣው ጠብ አይበርድም» (የብጥብጥ መነሻ)
«ሴትና ቁስ ቀስ» (አጥፊነት ሕይወት)
«ሴትና በቅሎ እንደ ገሪዋ ነው» (አስተዋይ-አልባ ሕይወት)
«ሴትና ፈረስ የሰጡትን ይቀምስ» (መንሥኤ-አልባ ተገዢነት)

ከላይ የተዘረዘሩት አባባሎች የተወሰዱት ብርሀነ ገ/ጻድቅ ካዘጋጃቸው ከ6790 የምሳሌያዊ አነጋገሮች ስብስብ ገጽ 31፣ 1992 መጽሐፍ ነው። በቅንፍ ውስጥ ያሉት መግለጫዎች የዚህ ዝግጅት ማብራሪያዎች ናቸው። 16ቱ አባባሎች ምሳሌያዊ ንግግሮች በመባል የሚጠሩ ናቸው፤ ምሳሌያዊ ንግግር በባሕርይው ግጥማዊ በመሆኑ ዜማ አለው፤ በዜማነቱ አይረሴ ነው፤ በአይ

ረሴነቱ ያለፉትን በርካታ መቶ ዓመቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ ነግሦ ኖሯል፤ ይኖራልም። መኖር ማለት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብል እየተቀበለ ማቀበልን ያመላክታል፤ ኅብረተሰብ በሥነ ቃል ዘርፎች በርካታ ጠቀሜታ ያላቸውን ርእሰ ጉዳዮች እንደ ማስተ ላለፉ መጠን፣ አሉታዊ አፍራሽ ተጽዕኖዎችን በ «እሽታ» የማስረፅ አቅምም አለው፤ ከዚህ አኳያ ከላይ የተዘረዘሩትን ምሳሌያዊ ገለጻ ዎች ሲመዘኑ ውስጠ መልእክታቸው በሴቶች ላይ አሉታዊ ተ ጽዕኖን በማሳደር በኅብረተሰቡ እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን በጎ አቅም ያጠፋል ወይም ያዳክማል፤ ከዚህ ባሻገር የሴትን ልጅ የአኗኗር ስብዕና በማጉደል፤ የተፈጥሮና የዜግነት መብቷን ያደበዝዛል። ከዚህም የተነሣ ድርሻን ለማወቅ ከጎናቸው የሚቆሙት የኅብረተሰቡ እኩሉ ተካፋይ ወንዶችና ሴቶች ራሳቸው የስብዕናን ምንነት በመፈተሽ እየሠሩ ሊተጉበት የሚገባ ተ ልዕኮ እንዳለው ማወቅ ቀዳሚ ሥራ ነው።

በዚህ አቅርቦት «መንፈሳውያን» ለሆኑ አንዳንድ አማኞች ይህን መነጋገር «ዓለማዊነት» ወይም «አይመልከቱ» ጉዳይን ያስተናገድን ተደርጎ እንዳይቆጠር በቅድሚያ ራሳችንን እንድናይ አግባባለሁ።

ሁላችንም የኅብረተሰቡ ውጤቶች ነን፤ ወላጆቻችን ባደጉበት አቅጣጫ አሳድገውናል፤ እነርሱንም የእኛ አያቶች፣ ዘመድ አዝማዶችና በዙሪያቸው ያሉት ሁሉ የየበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተ ዋል። በዚህ የጋራ የመዋጮ ሕይወት ተገንብተን ያደግንና የኖርን ሌሎችን በማኖር የራሳችንን አሻራ የምንተው የዘንድሮዎቹ እኛም አስተውለን ወይም ሳናስተውል ባለን ገሪ የትውፊት ሕይወት ቤተ ሰባችንን እንመራለን፤ እንመራለንም፤ በዚህ ጊዜ ነው ያልታረሙ ሊስተካከሉ የተገባቸው የግንዛቤ-አዋኪ የመሆን አቅም የሚኖራቸው።

በማስተዋል «የቆምንበትን» ራሳችንን ማኅበራችንን በመፈተሻ ቀጣይ ተግባራዊ እርምጃ ምን ሊሆን እንደሚገባ ያመለክታል፤ ይህን ተመልክተው ምላሽ ሊሰጡ የሞከሩ ኢትዮጵያውያን ብዙዎች ናቸው፤ ከክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል፤ ከክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ሥራዎች ባሻገር በቅርቡ በሰው ደግ ጌታቸው ካሳ ተጽፎ

ለንባብ የበቃው «የበደል ውርስ ይቅር» መጽሐፍ በሴቶች ጉዳይ ላይ አነጣጥሯል፤ በውስጡ፡- አሉታዊ ተጽዕኖዎችን እየገለጠ፣ ልከኛን ድርሻ ለማመልከት ጥሯል፤ በዚህ ዝግጅት ምጥን አጣቋሚ ነጥቦችን ለማስተዋወቅ እሞክራለሁ።

መጽሐፉ በጥገኝነት የተዋቀረ ትዳር መሠረት የሌለው መሆኑን በማሳየት «ወፍ ለጎጆዋ አለማነሷን» በማመላከት የትዳር ዋስትና ባልና ሚስት (በወንድና ሴት) የጋራ ኃላፊነት መጽናቱን ያስተዋውቃል (ገጽ 35)።

«ወልደው ካልሳሙ ዘርተው ካልቃሙ» የሚለው የአዛውንትን አነጋገር በመቃረን በፍቅር ልከኛ ትርጓሜ ባለመውለድም መኖር መቻሉን በማብሰር የሴት ጸጋ መውለድ ቢሆንም እንኳ፣ ለመውለድ የማያበቁ የጋራ ችግሮች ቢከሰቱ በሌላው ሕይወት በአስተማማኝ ሁኔታ መመራት መቻሉን ያረጋግጣል (ገጽ 42-9)።

የባል ለውጥ ሳይሆን፣ የፍቅር ጽናትና የመግባባት ተጠሪነት ተፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የጎበረተሰቡን አሉታዊ አመኔታ ለመቀየር ጥረት ያደርጋል፤ በዚህም «እርቀ ጥል ጓዳ በመግባት ይቁም» የሚል መፍትሔን ይጋብዛል (ገጽ 58)።

ትንታኔው በመዝለቅ ሽማግሌዎች (ድሮም ባልና ሚስት ይደባደባል»፣ «የባል በትር የቅቤ ንጥር» ነው በማለት በልዝቡ የሚቀርቡበት አቀራረብ «መሸምገል መሸንገል» ሊሆን መቻሉን በማሳየት፤ ለሴት ልጅ ያለውን አመለካከትና አቀራረብ መቀበል ወሳኝ መሆኑን ያበስራል (ገጽ 61)።

ትዳርም ምሥጢር ሆኖ የተዘጋ የመቃብር መገለጫ ሳይሆን፣ በገሀድ የሚነበብ ከተዘጋ መቃብር ሕያው ሰዎች ተነሥተው አዋጅ የሚሉበት ዓለም መሆኑን ደራሲዋ የድሮን ሰው ከዘንድሮ ጋር ታስተያያለች። «ድሮ ምሥጢር እንደ ተከደነ ይቀራል ወደ መቃብርም ተያይዞ ይገባል፤ የዘንድሮ ሰው ግን ፊኛው የጠበበ ስለሆነ አትናገር (አትናገሪ) ያሉት (ያሏት) ሁሉ (ያፈተልክበታል)፤ ያፈተልክባታል» (ገጽ 113)። ዝም በሉ አትበሉን፤ ባልንጀራን በሚወድ ፍቅር እያደመጣችሁን፤ ተገቢ እንክብካቤ አድርጉ በማለት ጎበረተሰቡን ለጎበረተሰቡ ትገልጣለች።

«የበደል ውርስ ይቅር» እንደ ስሙ በውርስነት ጎበረተሰቡ የተ

ቀበላቸው አፍራሽ ግንዛቤዎች መቀየር፣ መለወጥ፣ በበጎ መተካት እንዳለባቸው ያመላክታል። እግዚአብሔር ለነብዩ ከሰጠው ተልዕኮ አንዱ ማፍረስና መንቀል ሲሆን፣ በፈረሰበት መገንባትን በተነቀለው መትከልን ወዲያው ወዲያው ለማድረግ መነሣት የሴቶች ድርሻን በጎበረተሰቡና በቤተ ክርስቲያን ሊኖራቸው የተገባውን አቅጣጫ ምን እንደ ነበር ያረጋግጣል፣ ያመላክታል።

በደልን በውርስነት ከሚያሻግሩት ሀገራዊ ገጽታዎች አንዱ ሕግ ነው፤ የፍትሐብሔር ሕግ በ1952 ጸድቆ ሲወጣ በውስጡ የደነገጋቸው መብቶች ለወንድ አድልተው ሴትን ያገለሉ እንደ ነበር ይታወቃል፤ ይህን ለማሻሻል ከ1968 ጀምሮ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የየጊዜው ድካም ለውጥን እያመጣ እንደ ሆነ መገንዘብ ይቻላል፤ በመሠረቱ በሕጉ ላይ መሻሻልን ማየት፣ የጎበረተሰቡን አስተሳሰብ በእኩል ደረጃ ይቀይራል ማለት አይደለም።

በተያያዥነት ተዛዝለው ከመጡት ሴት አግላይ ሀገራዊ ሕጎች ውስጥ ጥቂቱን ብንመዝን፣ የቤተሰብ ኃላፊነት፣ የልጅን ስም መሰየም፣ አባትና እናት በሌሉበት የልጅ ሞግዚት ከወንድ ወገን መምረጥ፣ የመኖሪያ ሥፍራ መወሰን፣ የቤት ሠራተኛ የመቅጠር መብት፣ የጋራ ሀብትን የማስተዳደር መብት፣ ሁሉ የተሰጠው ለወንድ ነው።

ይህ ሕግ በ1952 ተዘርዝሮ ወጣ እንጂ፣ በጎበረተሰቡ ልብና በገዢዎች ፈቃድ ላይ ግን ቀድሞም ባልተጻፈ ሁኔታ እንደ ነበር መገመት ተገቢ ነው፤ ከዚያም በኋላ ላለፉት 46 ዓመታት እዚህ ግባ የተባለ ማሻሻያ ሳይኖረው መክረሙ ሴቶች ድርሻቸውን ባንነው ተግባራዊ እንዳያደርጉት አድርጓቸዋል።

3) ሴቶችና ድንበር - አለፍ ግንዛቤ

ሀገራዊ ግንዛቤን በተመጠነ ሁኔታ አይተናል፤ ቀድመን ያነሣናቸው ምልከታዎች በኢትዮጵያ ብቻ ተከልሎ ያለ ጉዳይ ባለመሆኑ አስፍተን የሴቶችን ድርሻ በልከኛው ስፍራ ለማኖር ዓለም አቀፍ እይታን ገጣጥመን መናበብ ይኖርብናል።

የዓለም ሉተራን ፌዴሬሽን የወንጌል ተልዕኮና ልማት ክፍል

ባዘጋጀው መጽሐፍ የድንበር-አለፋን የሴቶች ምንነት አስፍሯል፤ ለዚህ ዝግጅት አጋዥ የሆኑትን ነጥቦች ለውይይት ያግዝ ዘንድ ማነሣሣት ተገቢ ይሆናል።

ሀ. በዓለም ያሉትን በአብዛኛው ከተናጋሪነት ይልቅ በተገዢነት መመልከት (androcentrism)። ይህ አስተሳሰብ አሉታዊ ተጽዕኖን በጎብረተሰቡ አምጥቷል፤ በትንሣኤው በመገኘት ቀዳሚ የዐይን ምስክር የነበረችው መግደላዊት ማርያም ሆና ሳለ፣ 1ቆሮ 15፡5-6 ላይ ጳውሎስ፣ «ለኬፋም ታየ፣ በኋላም ከ500 ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ» በማለት ሴትን ያላቀፈ መምሰሉ አነጋግሯል።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከነበሩትም አንዱ፣ «ሴቶች የክፋት መግቢያ በሮች ናቸው፣» በማለት ጽፏል። ይህ የሚያመለክተው ሴቶችን ብቻ የኃጢአት ምክንያት ማድረግ ነው። በትይዩ፣ የቋንቋ ቃላት አገልግሎት ባሰያየም ለወንዶች ያጋደለ መስሏል፤ «Human kind» የሚለውን ቃል «mankind» በሚለው፣ «Chairperson» የሚለውን ቃል «Chairman» በሚለው ቦታ በመተካት ለአገልግሎት ማዋልን መርጧል። በመሠረቱ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀምም «ወንድሞችና እኅቶች» በ«ወንድሞች» መተካቱን ልብ ማለት ተገቢ ነው።

ለ. የገነነ ማጠቃለያ (Over generalization)። በጾታዊ ትንታኔ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን በሴቶች ላይ ሊያመጣ እንደሚችል ላመላከተበት ነጥቡ ምሳሌን ያነሣው «አስር ሚሊዮን ሴቶች ተሰብስበው ባሉበት አንድ ብላቴና ወንድ ተገኝቶ» ዜና ሲሠራ፣ በወንዱ ጾታ ማቅረብን የፈረንሳይኛ ቋንቋ ይመርጣል። የማቴዎስ 14፡21 ዘገባም አምስት ሺህ ወንዶች እንደ ተመገቡ ከተናገረ በኋላ፣ ሴቶችና ልጆች እንዳልተቆጠሩ ይናገራል። ይህ አጻጻፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ችግር ሳይሆን፣ አገላለጹ የአይሁዶች ባህላዊ አገላለጽን መሠረት ያደረገ መሆኑን ልብ ማለት ተገቢ ነው፤ አይሁዶች ሴቶችን ዝቅ አድርገው ያያሉና።

ሐ. የጾታ አቀባበልን (Sex Appropriateness) በተመለከተ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የሠርግ የጥሪ ካርዶች ሴቲቱን በመጠን አሳንሰው ወንድየውን አርዝመው የመግለጣቸው መንስኤ ከዚህ የጾታ አቀባበል ጋር ተያይዞ ቀርቧል፣

ብዙ ጊዜም እናቶች ለሥራ ፍለጋ በወጡ ቁጥር፣ «ልጆች አሉሽ? ሥራ ስትጀምሪ የልጆችሽን ነገር ምን ታደርጊዋለሽ?» የሚለው ጥያቄ በቤተሰብ ጉዳይ ወንድን የማይመለከት በማድረግ ሴቶችን ለተገደበ ኃላፊነት ያዋላቸው ይመስል፤ «ቤት ያለ ሴት» የሚለውም ግንዛቤ ከዚሁ እይታ ጋር ተያያዥነት አለው፤ በኢትዮጵያ ቴሌ ቪዥን የምንመለከታቸው የሳሙና ማስታወቂያዎች ሴቶችን አጣቢ ዎች ወንዶችን የፀዳ ለባሾች አድርጎ ማቅረቡም የዚሁ ገጽታ ነው።

መ. ጾታዎችን ማበላለጥም (Sexual dichotomism) ሌላው የሰፋ ልዩነት መንሥኤ መሆኑን የዚሁ ጉዳይ አጥኚዎች አብራርተው፣ «ወንዶች» አስበው ውሳኔ የሚሰጡ፣ ሴቶች ደግሞ ስሜታውያን በመሆናቸው የተደላደለ አቅም እንደሌላቸው በማመን፣ መበላለጥን መፍጠር በዓለም አቀፍ ደረጃ ጫናን እንደሚፈጥር ታውቋል። (HWF documentatation The Gospel Transforming Cultures, 1999 P. 158-9)

በተጨማሪም፣ ከክርስትና አስተምህሮ ጋር የረባ ንክኪ የሌ ላቸው የዓለም ሕዝቦች ሴቶችን በተመለከተ የሚያምኑትና የሚተ ገብሩትን አካሄድ *«የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና ሓገል ጋዮቿ»* በሚል ርእስ ዶክተር መለሰ ወጉ ያጣቆማቸውን ነጥቦች አብረን እንመልከት (ገጽ 113-130)፦

የእስልምና እምነት ተከታዮች ሚስቶቻቸውን በፈለጉበት ጊዜ «ውጪ» የሚል ቃል ብቻ በመተንፈስ ያለ ሀብት ንብረት መለመላዋን የመላክና የመፍታት መብት አላቸው።

የሒንዱ ሀይማኖት ተከታዮች ሴቶች የወንዱን ብልት ያመልኩ ዘንድ ያደርጓቸዋል።

በአፍሪካ አንዳንድ ሀገሮች ልጆችና ሴቶች የወንዶች ባሪያ ሆነው ያገለግላሉ።

በአይሁድ ታልሙድ እንደተጻፈውም፦

ለምኩራብ ክብርን ለመስጠት ሴቶች ቶራን (የሕግ መጽሐፍን) ማንበብ የለባቸውም።

ከመቶ ሴቶች ምስክርነት የአንድ ወንድ ምስክርነት ይበልጣል።

ሴት በወንዶች መካከል ተገኝታ ድምጽዋን ማሰማት ውርደት ነው።

ማኅበር በ10 ሰው ይመሠረታል፤ አንዲት ሴት ከዘጠኝ ወንድ

ጋር በተገኘችበት ግን አይመሠረትም፤ ዘጠኝ ብቻ ናቸውና።

ማንኛውም አይሁዳዊ፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ሴት፣ ውሻና አሕዛብ ሆኜ እንድወለድ ስላላደረግኸኝ አመሰግንሀለሁ፣» ብሎ ይጸልይ፤ በማለት ተንትኗል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ጠቋሚ ሀሳቦች ግምት ውስጥ በማስገባት የምንገነዘበው ቁም ነገር፣ ችግሮችን ለመፍታት መዘጋጀት ሙሉ አቅምን በመስጠት ተገቢ ግንኙነትን ለመመሥረት ይረዳናል፤ ግንዛቤያችን ሳይጠብ ሁሉን-አቀፍ ለማድረግ ምስክራችን በሰው ልጆች ሁሉ ላይ፣ በተለይም በዓለም ባሉ ሴቶች ሁሉ ላይ፣ መሆን አለበት። እነዚህን መገንዘብ ትክክለኛውን የሴቶች ድርሻ ለማወቅና ለማሳወቅ ይረዳናል።

4) የሴቶች ድርሻ በኅብረተሰቡ ውስጥ

ኅብረተሰቡ ወንድን ከሴት፣ ትንሽን ከትልቅ፣ የተማረን ካልተማረ፣ ልጅን ከአዋቂ፣...ሳይለይ በአንድ ላይ አገጣጥሞ የሚኖር ስብስብ ነው። ይህ ስብስብ ዛሬ የተገኘ (የተመሠረተ) ሳይሆን፣ ዘመናትን በትናንት ውስጥ አካትቶ ዛሬን በወቅቱ ትውልድ መጪውንም በመገንዘብ የሚያስረክበው ያለው ማኅበር ነው።

ኅብረተሰብ እርስ በርሱ የሚጋመድበት፣ የሚተሳሰርበትና የሚቀባበልበት የራሱ ታሪክ አለው፤ ይህን ደግሞ በመተግበር የኅብረተሰቡ እኩሌታ ኃይል ሴቶች ናቸው። እኒህ ኅብረተሰብን ኅብረተሰብ የሚያሰኙ ሰዎች ከወንዶች ጋር ተካክለው ኃላፊነታቸውን የሚወጡባቸው በርካታ የጋራ ተግባራት አሏቸው፤ ከተፈጥሮአቸው ማንነት የተነሣም በወንዶች የማይከወን የራሳቸው ማንነቶችም አሏቸው፤ ይወልዳሉ፤ ያጠባሉ፤ በሴትነት ወጋቸውም ለዘለቄታው ይኖራሉ።

የሴቶች ድርሻ በሰዎች መካከል ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ሴቶች ራሳቸውን ማወቅ አለባቸው፤ ወንዶችም ሴቶች ሊያበረክቱት የተገባቸው ኅብረተሰባዊ ድርሻ እንዳላቸው መረዳት አለባቸው፤ ኅብረተሰብም ለኅብረተሰብነት የበቃበትን የሴቶች ዋነኝነት በትክክል መረዳት እና ተገቢ ስፍራቸውን መስጠት የግድ ነው።

ተገቢውን ስፍራ ለመስጠት በሀገራዊ የአኗኗር ስልት፣ ባህል፣

ወግ፣ እምነት፣ ትምህርት፣ ያሰረፁትን አሉታዊ እና አዎንታዊ ገለጻዎችን መፈተሽ ግድ ይሆናል። ይህ ሲጣራ፣ ድርሻን በኅብረተሰብ ውስጥ የመወጣት ኃላፊነት በቀላሉ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

በቀዳሚ ሁለት ምዕራፎች የተነሡት የግንዛቤ እውነታዎች የት ላይ እንዳለን ካመላከቱን፣ የእነርሱን አሉታዊ ይዘት በማሻሻል፣ በመቀየር እና በበጎው በመተካት መሥራት ሴቶች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ያደርጋል።

ይህን የበኩል ድርሻ እንዳይወጡ ከአንድ መቶ ዓመት በፊት በምዕራቡ የዛሬ ሥልጡን ሀገራት ውስጥ የተደረገውን ወይም የነበረውን አመለካከትና አስተሳሰብ ለመመዘን እንሞክር። ያኔ፦

ሴቶች ድምጽ የመስጠት መብት አልነበራቸውም።

ሴቶች የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም አይችሉም።

ሴቶች ከቤት ውጭ ምንም ዐይነት ሥራን አይሠሩም።

ሴቶች በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ተቀጥረው ቢገኙ ለእኩል ሥራ እኩል አይከፈላቸውም።

ሴቶች ከፍተኛ ትምህርት የመማር መብት አይሰጣቸውም።

ሴቶች በስፖርት ውድድሮች አይሳተፉም።

ሴቶች በፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ አይገቡም።

ለሴቶች ጸታዊ ትንኮሳ ምላሽ አይሰጥም።

ሴቶች ስለ ሴቶች ሕይወትና አኗኗር የበኩላቸውን ምንም እንዲሉ አይፈቅድም።

እኒህ ምጥን «አሉታዊ» አቋሞች ሴቶች በእግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም የመጡበትን ተልዕኮ አላስፈጸማቸውም፤ ይፈጽሙ ዘንድ ግን ያለፉትን በርካታ ዓመታት መወያየት፣ መመካከር፣ በግልጽ ተገቢ የሆነውን እርምጃ ለመውሰድ መቻል ዛሬ ላይ እኒህ ሁሉ ትክክለኛ ስፍራቸውን እንዲይዙ አድርጓቸዋል። ከዚህም የተነሣ ሴቶች ገደብ ያላለፈ ድርሻቸውን መወጣት ችለዋል፤ ይህን ወደ ሀገራዊ ሁኔታ ለማምጣት ሲታሰብ አግባብ በሆነ ለውጥ-አምጪ ምክክሮች እና ትብብሮች ላይ ሁሉም የኅብረተሰቡ አካል ተካፋይ ሊሆንባቸው ይገባል፤ አማኞች የተለዩ ሳይሆኑ የኅብረተሰቡ አባላት ናቸውና፣ የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይኖርባቸዋል፤ በኢትዮጵያ ዛሬ ላይ ቆመን ዙሪያ ገባውን ስንመለከት፦

ሴቶች በቤተሰባዊ ሕይወት በወንዶች አይታገዙም፤
ሴቶች አድካሚ ሥራዎችን መሥራታቸው አልታየም፤
ሴቶች ተሰሚ እንጂ ተደማጭ አይደሉም፤
ሴቶች የመወሰን አቅማቸው በገደብ ነው፤
ሴቶች ለኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ተጋላጭነታቸው ከግምት አይገባም፤
ሴቶች ለወለዷቸው ልጆች የባሎች እገዛ የላቸውም፤
ሴቶች ያፈቀሩትን የመጠየቅ አቅም የላቸውም፤
ሴቶች በወላጆቻቸው እና በትምህርት ቤት የእኩል መብት ተጠቃሚ አይደሉም፤
ሴቶች ለሴቶች ያላቸው ግንዛቤና በትምህርት ቤት የእኩል መብት ተጠቃሚ አይደሉም፤
ሴቶች ለሴቶች ያላቸውን ግንዛቤ አልተመጣጠነም።

እኒህና መሰል ተጨማሪ ጉዳዮች በሀገር ውስጥ በአግባቡ ተ ሠርቶባቸው ለውጤት መብቃትና፣ ለውጤት የተገባቸውን ድርሻ ሊከውኑ ይችሉ ዘንድ ኅብረተሰቡ ሊነሣሣ ይገባዋል፤ ድርሻን ለመወጣት መብቃትና፣ ለውጤት የተገባቸውን ድርሻ ሊከውኑ ይችሉ ዘንድ ኅብረተሰቡ ሊነሣሣ ይገባዋል፤ ድርሻን መወጣት የሚችለው በመፈክርና በአቋም መግለጫ ሳይሆን፣ በኅብረተሰቡ አጠቃላይ የአስተሳሰብ ለውጥ ሲመጣ ነው።

አንድ ባል ወይም ወንድም ሚስቱን ወይም እኅቱን ጠጋ ብሎ ድስት ወይም ሳህን ሲያጥብላት ቢገኝ፣ «እረዳት» ወይም «ረዳኂት» ብሎ ይናገራል፤ ልኩ ግን ድስትና ሳህን ማጠቡ የገዛ የሕይወቱ ክፍል ሆኖ ያለ መካሪ ዘካሪ በሥራው ውስጥ ተገኝቶ ሲኖር ማየትና ይህንንም ብዙዎች እያደረጉት ሲኖር መመልከት የአስተ ሳሰብን ለውጥ ያመለክታል።

ሴቶች የድርሻቸውን የመፈጸም አቅም ይኖራቸው ዘንድ የአስተ ሳሰብ ለውጥ በፈጠሩት የመደብ ክፍተቶች ላይ መጠጋጋት ወይም መቀራረብን ማምጣት የሁሉም ኃላፊነት ሲሆን፣ ለውጥ ይኖራል፤ ኅብረተሰብ በኑሮ ውስጥ በቀያቸው መድቦ ምድቡ የልዩነት መንሥኤ መሆኑንም ተቀብሏል። ወንድን ከሴት አልቆ፣ ቀጭንን ከወፍራም አሽሎ፣ ሀብታምን ከድሀ ለይቶ፣ ብሔርን ከብሔር ከፍና ዝቅ አድርጎ ማሰብን «አሜን» ብሎ ተቀብሎታል፤ ይህን ቅበላ

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀራራቢ ምስስሎሽ አለው። ምስስሎሹን የበለጠ በመረዳት ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለቱንም በእኩል ዐይን በእኩል መብት (ዕድል) ውስጥ በማሳለፍ ማቀራረቡ መሠረታዊ ድርሻን የመወጣት አቅም ነው፤ በተያያዥ ትምህርት፣ በቅርርብ ግልጽ ውይይት፣ መቀባበልና አስፍቶ መረዳት፣ መፍትሔ ናቸው።

በኅብረተሰቡ ውስጥ ሴቶች የድርሻቸውን መፈጸም እንዲችሉ ጽንፈኛ የሆኑ ሃይማኖታዊ ትንታኔዎችን ባግባቡ ይለዝቡ ዘንድ ማድረግ ሌላው የድርሻቸውን በአግባቡ እንዲፈጽሙ የሚያስችል ሁነኛ አቅጣጫ ነው።

በዓለም ላይ ያሉ በርካታ የእምነት እንቅስቃሴዎችን ለጊዜው በመተው በአይሁድ አማንያንና በክርስቲያኖች ዘንድ የጋራ የሆነው «ወንድ-ተኮር» አስተሳሰብ ወንድ ለእግዚአብሔር የቀረበ ወይም እርሱን መሳይ፣ ሴትን ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ በሁለተኛ ደረጃ የምትታሰብ የሚያደርግ ማኅበራዊ አመለካከት በሁሉም ዘንድ በስፋት አለ። እግዚአብሔር ከመለኮታዊ ፈቃዱ አኳያና ከማኅበረሰቡ የነበረ እሴት አኳያ ዕቅዱን ይፈጽማል፤ ከዚህም የተነሣ ሣራን ሳይሆን አብርሃምን፣ ዲናን ሳይሆን 12ቱን ወንዶች፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ዲያቆናትን የሰየመበት የወንድ መረጣ የራሱ የሆነ ትርጓሜ ያለው መሆኑን ባለመገንዘብ፣ የተቀረው የወንዱ ዓለም የተለየ ዕይታን፣ ዕድለኝነትን ከእግዚአብሔር የተ ወሰነ ያህል ቆጥረው ራሳቸውን ያገዝፋሉ፤ ሴቶቹም በትይዩ ለእግዚአብሔር ያለመቅረብና ያለመመረጥ ውሳኔ በማድረግ ሃይማኖታዊ ገለጻዎችን ያቀርባሉ። በጋብቻ ሕይወትም የወንድን የማፍቀር አቅም የዘነጉ፣ የሴቶችን የመገዛትና ለወንድ አምባገነናዊ ባሕርይ ሁሉ ተገዢ ሆና የምትኖርበትን ግንዛቤ አኑሯል።

ይህ በኅብረተሰቡ ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥን አስገኝ ማለት የሚቻለው ግንዛቤው እግዚአብሔር ወንድንና ሴትን ካየበት አኳያ የወንድ ቀዳሚ ኃላፊነትን በመፈጸም የሚመጣን ማኅበራዊ ለውጥን ተግባራዊ በማድረግ ነው።

ይህን ለውጥ ለማምጣት ግን ጽንፈኛ በመሆን ከልክ ያለፈ «ወገነ ሴት» መሆን አይገባም። «Womens Voices Feminist Visions» መጽሐፍ በገጽ 489 የዓለም አማልክት ሁሉ ቀዳሚዎቹ ሴቶች መሆናቸውን

ዘግበዋል፤ ዘገባው ልክ ሊሆን ይችላል፤ ጽንፉ ግን እግዚአብሔርም በሴት ሊገለጥ ይገባል የሚለው ዝንባሌ ግን አግባብ አይደለም።

በሴቶች ጉዳይ ላይ ያለን ግንዛቤ የበለጠ ያግባባን ዘንድ በዓለም ላይ በቀደመው የጥንት ዓለም የነበሩትን እንስት አማልክት በከፊል መተዋወቅ ተገቢ ነው።

የግብፆች የሰማይ ንግሥት የብርሃን እናትና የታህታዩ ዓለም አምላክ ሀቶር (Hathor) ትባላለች።

የአሦራውያን (Assyrian) የሕይወት ምንጭ፣ መልካም እረኛ፣ የመራባት እናት፣ የፍትሕ ዋንኛና የሰማይ ንግሥት አስታሬት (Astaret) ትባላለች።

የሁሉም አማልክት እናት፣ የምድርና የጨረቃ እመቤት አኑ (Anu) ትባላለች።

ስካንዲኒቪያንን (Scandinavian) ለሕይወት ያበቃች ፈሪጅ (Freyia) ትባላለች።

የሀዋልያ (Hawalilian) ፈጣሪ፣ የሁሉ እረኛና መሪ ሀውማ (Haumea) ትባላለች።

የዩሩባ የናይጀሪያውያን (Yourba Nigerian) የፍቅርና የመራባት ምንጭ አዱዳ (Odudua) ትባላለች።

የመሰጶጣሚያን (Mesopotamian) የፍትሕ፣ የመሬት፣ የፍጥረት ሁሉ አምላክ አሼራ (Assherah) ትባላለች።

የሂንዱ (Hindu) አምላክ፣ ሕይወትን መስጠትም ማጥፋትም የምትችል ካሊ (Kali) ትባላለች።

የግሪኮች እናት ጠባቂ፣ የ12ቱ፣ የግሪክ አማልክት ሁሉ እናት የሥርዓተ-ሕዝብ መሪ እና የምድር ለምነት ተቆጣጣሪ ድሚትር (Demeter) ትባላለች።

ለቬትናማውያን የሕይወት መገኛ፣ ሕዝብን ተንከባካቢና ጠባቂ፣ የለምነት ሁሉ ምንጭ ፖኢኖ ኖጋር (Poino Nogar) ትባላለች።

ከላይ በከፊል የተዘረዘሩትን ማወቅ መልካም ነው። የጎበረተሰብ ለውጥ ሚዛናዊነት ይኖረው ዘንድ የጥንቱ ዓለም ለሴቶች በጎ ዕይታ እንደ ነበረው ይጠቁማል። እርግጥ ነው፣ አማልክቱ ዐይን ኖሯቸው አላዩም፣ ጆሮ ኖሯቸው አልሰሙም፣

እግር ኖሯቸው አልሄዱም፣ እናም የሚታመኑባቸው እንደ እነርሱ መሆናቸውን ልብ ማለት ተገቢ ነው (ኢሳ. 44-46)። በትይዩ፣ አጉል ጽንፍነቱ በእነዚህ ላይ በመመሥረት የትውልድ ቅብብላዊ ሰንሰለት በምሥራቅ እና በምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ለማርያም የሚሰጠው ስፍራ ኢየሱስን በሚሸፍን መልክ ላይ መድረሱ አሳሳቢና አስደንጋጩ አፍራሽ የታሪክ ዕይታ ነው።

እንግዲህ ሴቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ መኖራቸው አይቀሬ ነው፤ ጡት አጥብተው ማፋፋታቸውም ወንዶች የማይጋሯቸው መገለጫቸው ናቸው። ሴት በሚስትነት ሕይወቷ ውስጥ የፍቅር መነሻና መደምደሚያ መሆኗ የኑሮ ድርሻዋ ነው።

ይህቺን ሴት ለኅብረተሰቡ መሠረት ከሆነው የቤተሰብ ሕይወትን አካሎ ሴቶች ሁሉ ሊሆኑት የሚችሉትንና ድርሻቸው ሆኖ ሊተገብሯቸው የተገቡትን ውጤታማ ኃላፊነቶች (ከጥበብ) መጽሐፍ ምሳሌ 31 ላይ በመዘርዘር ማየት ይቻላል፦

ቤተሰብ በተደላደለ መሠረት ላይ እንዲቆም ዘላቂ ጥረትን አድራጊ ነች (ቁ. 12)።

ኃላፊነትን በግሏ በመወጣት የሠራተኛነት ሕይወት ኑሮዋ ነው (ቁ. 13)።

ኅብረተሰብን ለመጥቀም የሚያግዝ አስተዋጽኦ ሁሉ ቸል አትልም (ቁ. 14)።

ልማት የድህነት መግደያ መሆኑን አምና መሬትን በአግባቡ ትጠቀማለች (ቁ. 16)።

መኖሯ ትርጉም ያለው ይሆን ዘንድ ጊዜዋን ለፍሬያማ ሥራ ታውላለች (ቁ. 18)።

ድሆችን በማገዝ ራሳቸውን የሚያኖሩበትን አቅም ታጎለብታለች (ቁ. 20)።

ዕደ ጥበብ በሙያነቱ የኅብረተሰቡ መገልገያ ይሆን ዘንድ ሠርታ ታሠራለች (ቁ. 22)።

ኢኮኖሚን በማሳደግ፣ ሀገርን ለማሳደግ ጥረቷን ታሳድጋለች (ቁ. 24)።

ያላትን ዕውቀት ሁሉ በተገቢው ስፍራ በመጠቀም ጥበበኛነትን

ታመጣለች (ቁ. 26)።

ለእግዚአብሔር መገዛትንና ማክበርን የኑሮዋ ቀዳሚ ጉዳይ ታደርጋለች (ቁ. 30)።

ሰለሞን ጥበብን ከእግዚአብሔር በመጠየቁ በዙሪያው የሚከወኑትን ጥቃቅንና ዐብይ ተግባሮች ሁሉ በአስተውሎት ይመለከታል፤ በዘመኑ የተማራቸውንና ለሰዎች ጥቅም ሊተላለፉ የተገባቸውን እውነቶች ሳይቆጥብ አስተላልፏል። በዚህ መሠረት፣ የሴቶች መሠረታዊ ሕይወት በማኅበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ የአንዲት ሴትን አኗኗር በሞዴልነት በማቅረብ አሳይቷል።

5) የሴቶች ድርሻ በቤተ ክርስቲያን

ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሕይወቱን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ በትንሣኤ የክርስትናን መሠረት ጣለ፤ በዚህም ለዘላለም ሕይወት የተጠሩ (የታጩ) ሁሉ ይድኑ ዘንድ እግዚአብሔር ብቸኛን መንገድ አዘጋጀ። ያ የድል፣ የነፃነት ሕይወት ምንጭ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ ሊሄድ ሲዘጋጅ የመጨረሻውን የአደራ መልእክት ለተከታዮቹ ሰጠ፦ «ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃቸኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ. 28፡19-20፣ አ.መ.ት.) አለ። ይህ ትእዛዝ ሴቶችን ያቀፈ መርኅ ነው። ይህ በአግባቡ ተፈጻሚ እንዳይሆን ለመንደርደሪያነት አሻሚነት ያላቸውን ክፍሎች ለመተንተን በመሞከር የበለጠ የሴቶችን ድርሻ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማሳየት ይረዳል፤ ከዚህም የተነሣ፣ ሁለት የመልእክት ክፍሎችን በስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ስልት እንመልከት፦

«ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ»ን ትእዛዛዊ ቃል የምናገኘው በ1ኛ ቆሮንቶስ 14:34-36 ላይ ነው፤ ይህ አባባል ከተዛማጁ አውዳዊ ፍቺው አኳያ ካልተጤነ፣ ሴቶች ምንም ዐይነት ድርሻ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይም እንደ ሁኔታው በማኅበረሰቡም ውስጥ ሊኖራቸው እንደማይችል ያመለክታል። ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ

አጠናን ግን ልከኛን ትርጓሜ ለማግኘት በወቅቱ የነበሩት የተ ጻፈላቸውን ሴቶች ማንነት፣ ባህላዊ ፍቺ ግምት ውስጥ በመክተት ትኩረት የተገባውን ጥቅስ ወይም ምዕራፍ ከቅርብ እና ከሩቅ ዐውዱ አኳያ ማጤን የግድ ይለዋል።

ይህን እንደ መስፈርት ወይም መለኪያ ተጠቅመን ከመዘንን፣ የዚህን ጥቅስ አጠቃላይ ጠቋሚ ፍቺ ማወቅ እንችላለን።

ይኸው የቆሮንቶስ መጽሐፍ ከዚህ ክፍል ቀድሞ 11፡15 ላይ ሴቶች በጉባኤ ምክክር ድምጽ አውጥተው እንደሚጸልዩ ተናግሯል። ይህ የሚሰጠው አጋዥ ፍቺ የሴቶች ድምፅ በጉባኤ እንዳይሰማ አለመታገዱን ነው።

ይህ ግን በብቻው በቂ መልስ ስላልሆነ፣ የሚከተሉትን አማራጭ ትርጓሜዎች አብረን እንመልከት፡-

ምዕራፉ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም አስቀድሞ አውርቷል፤ ሁከትና ሥርዓት-አልበኝነት መታረም እንዳለበትም አውጇል፤ ከዚህ የተነሣ፣ ትንቢት (ቃለ እግዚአብሔር) ሲነገር ጥያቄ በመጠየቅና በመንሾካሾክ የሚያስቸግሩ ሴቶችን ለማስተካከል የተጻፈ ነው።

በምዕራፉ ውስጥ «መናገር» ተብሎ የተረጎመው ቃል በግሪኩ «ላሌኦ» የሚል ነው፤ ትርጉሙ ተራ ንግግርና ጫጫታን ያመለክታል፤ ለመምከርና ለማስተማር የሚደረግ ንግግር ግን «ሌጎ» የሚል ቃል ለብቻው አለው። ከዚህም የተነሣ፣ ሴቶች እንዳያስተምሩ መከልከልን ሳይሆን፣ እንዳይረብሹ ማገድን ይመለከታል።

በግሪክ «ጎኔ» የሚለው ቃል ሴት ወይም ሚስት ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፤ በዚህ ዐውድ «ጎኔ» ሚስትን በማመልከት በጉባኤ ባላቸውን ከአጠገቡ ሆነው መጠየቃቸውን ትተው በቤታቸው እንዲጠይቁ መምከሩ ነው።

በምኩራብም ሆነ በቤተ መቅደስ ሴቶችና ወንዶች ተለያይተው ይቀመጣሉ። ሴቶች ከበስተኋላ ራቅ ብለው በመቀመጣቸው ጮክ ብለው ጥያቄ የመጠየቅ ጥረት አድርገው ስለሚሆን፣ ይህን ለማ

ረም የተሰጠ ድንጋጌ ነው በማለት መፍታት ይቻላል።

2. በተያያዥ፣ «ሴት እንድታስተምርና በወንድ ላይ እንደትሠለጥን አልፈልግም፣» የሚለው የ1ኛ ጢሞ. 2፡11-15 መልእክትም ሌላኛው አነጋጋሪ ክፍል ነው።

ይህም በተገቢው የሥነ አፈታት ስልት መተርጎምና ወደ ተሻለ ግንዛቤ መድረስ ይቻላል። ጳውሎስን በመነሻነት በመውሰድ ማስተማርን በተመለከተ ከሴቶች ጋር የተያያዘ አገልግሎት ሰጥቶ ነበረ ወይ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፤ ሰጥቷል፤ በሐዋርያት ሥራ 18፡18፤ ሮሜ 16፡4 ላይ የምናገኛት ጵርስቅላ ባሏን አቂላን በመርዳት አብራው የተጓዘች ሴት ነበረች፣ ስሟ ብዙ ጊዜ አቂላን በመቅደሙ በአጻጻፍ የወንድ ስፍራን ይዛ ወንድን አገልግላለች። በብሉይ ኪዳን ትምህርት ታዋቂ የነበረውን አጵሎስን አስተምራለች። ይህቺን ሴት በሚመለከት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዘመኗ ሰፊ አገልግሎት እንደ ነበራት ይገልጻል።

ከጳውሎስ ጋር በወንጌል ሥራ የተጣመዱ ሴቶችን ስንፈልግ፣ ኤዎዲያንና ሴንጢክን እናገኛለን (ፊልጵ. 4፡2)፤ ሊዲያም ሌላዋ ተጠቃሽ ሴት ነች (ሐዋ. 16፡14)፤ ይህቺን ሴት ኢውኪቢዮስ የተባለ ታሪክ ጸሐፊ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀዳሚ ስፍራ እንደ ነበራት ጽፎላታል። በወንጌል ሥራ የተጋች በመሆኗ መታሰሯ የሚነገርላትና ከጳውሎስም ቀድማ በጌታ የነበረችው ዩሊያን (ሮሜ 16፡7) ሌላዋ ሴት አገልጋይ ነች። እነዚህ ሁሉ ጳውሎስ 1ኛ ጢሞ 2፡11-15 ለጢሞቴዎስ ከመጻፉ በፊት የነበሩ ሴቶች ናቸው።

ይህን በመንደርደሪያነት በማንሣት፣ በቀጥታ ወደ ክፍለ ዐውዱ ስንመጣ ልናገኘው የምንችላቸው አማራጭ ትርጓሜዎች ይኖራሉ፤ መኖሩ ደግሞ ለመቀራረብ የተሻለውን ለመገንዘብ ያስችላል።

ክፍሉ ተቃዋሚ ትምህርት በመያዝ የእኛ ነው ልክ በማለት የሚያውኩ ሴቶችን የሚያርም ነው። በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡5-7 ላይ መናፍቃዊ ትምህርት መጥቷል፤ ይህን ደግሞ ሴቶች እየተቀበሉት ነው፤ ከዚህም የተነሣ፣ ማስጠንቀቂያው ተሰጥቷል።

ወንጌል ነፃነትን በብዙ ዘርፍ እንደ ሰጠ ማመን ሌላኛው ነጥብ

ነው። በጊዜው የነበሩ ሚስቶችም ባሎቻቸው ላይ ተነሥተው ሳያምፁ አልቀሩም፤ ወንድ እና ሴት በግሪክ ባል እና ሚስት ተ ብሎ ተተርጉሟል።

ክፍሉ ከፍ ብሎ ስለ ጌጥ መናገሩ መልእክቱን ከቤተ ክርስቲያን በማውጣት በባልና ሚስት የቤት ውስጥ ግንኙነት ላይ የሚያተኩር ነው። ማስተማር በዘመኑ ክርስትና አዲስ በመሆኑ፣ ይህ ድርሻ ለሐዋርያት ብቻ የተሰጠ ነበርና፣ ሴቶች በዚህ ኃላፊነት ቀዳሚ እንዳይሆኑ ታስቦ ሊሆን ይችላል።

በእነዚህ አስቸጋሪ በመሰሉ ክፍሎች ውስጥ ብርሃን እንዲፈነጥቅባቸው ከሆነ፣ አስከትለን ማጤን ያለብን የሴቶች ሁነኛ ድርሻ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ሊሆን እንደሚገባው ማየት ነው።

«ክርስትናና ሴትነት» በመነሻ ገጹ በዓለም ላይ ከሚገኙ ሃይማኖቶች ሁሉ እንደ ክርስትና ለሴቶች ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጥ ሃይማኖት አንድም የለም (ገጽ 2) በማለት እውነቱን ግልጥ ያደርጋል። አከታትሎም፣ ክርስትናና መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተ ምሩት ስለ ሴቶች የተሳሳተ እምነት ያለውን የወንድ አመለካከት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለሴቶች ያለውን የከበረ ሀሳብ ማብራራቱን ያበስራል። በተያያዥም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር የተመላለሰበትን ሕይወትና አገልግሎት በዝርዝር ሲጠና አድምቆ የሚያሳየው እግዚአብሔር ለሴቶች ያለውን ትልቅ ዓላማ እና በተሳትፎ የሚመጡትን ኃላፊነታቸውን ወይም ድርሻቸውን ማሳወቅ ሆኖ ይገኛል።

አጠቃላይ ቅኝትን በመመልከት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ 540 ሴቶች፣ ስለ 324 እናቶች፣ እንዲሁም ስለ 401 ሚስቶች የሚናገር መጽሐፍ መሆኑ ደግሞ እነርሱነታቸውን በአግባቡ በዙሪያ ገቡ እንድናጠና ይረዳናል። እርዳታውም በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖራቸውን ስፍራ ይገልጻል፤ ገላትያ 4፡4 ኢየሱስን አስመልክቶ፣ «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተ ወለደውን...ልጁን ላከ፣» በማለት የዘመን ፍጻሜንና የኢየሱስን ከሴ ት መገኘት መነሻ ያደርግበታል፤ የተወለደውንም ሕፃን የዘር ሐረግ

ሲያስቆጥር ሉቃስ ዓለም አቀፍ ዕይታ ያለው ጸሐፊ ትውልዱን ከማርያም አንጻር ማተት ይጀምራል (ሉቃስ 1፡31-32፤ 2፡7)፤ የትውልዱ ዝርዝርም ውስጥ ወቅቱ ከሚፈቅደው የባህል እሴት ጋር ሊጋጠሙ የማይችሉትን አራት ሴቶች አካትቶ ይገኛል፤ ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት፣ እና የንጉሥ ሰለሞን እናት ቤርሳቤ (ማቴ. 1) በወንዶች ብቻ ሲቆጠር የነበረ የቀደመ የትውልድን ሐረግ አይሁዳዊው ማቴዎስ የጣሰበት መሠረታዊ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ (በታላቋ መሲሐዊት ጎብረተሰብ ውስጥ) ሴቶች ሙሉ ተቀባይነትና ድርሻ እንዳላቸው ለመግለጽ ነው።

በመሠረቱ፣ ታሪክን ነቅሶ አተያይቶ አመሳክሮ እርግጡን የጻፈው ጸሐፊው ሉቃስ በወንጌሉ ውስጥ በርካታ ሴቶች የነበራቸውን አስተዋጽኦ ገልጾአል፤ በዚህም ወንጌሉ «የሴቶች ታሪክ ወንጌል» በመባል ተጠርቷል። ሉቃስ ያየበትን ዐይንና ትንታኔ እንደ አይሁዶች የጠበበ፣ እንደ ትምክህተኛ ወንዶች ወንድነቱን ያገዘፈ ዝርዘራን ሳይሆን፣ ከአካባቢ ባለፈ ዕይታ ዓለም አቀፋዊ ተልዕኮን ከግምት በማስገባት በዓለሙ ሁሉ ሴትን በተመለከተ ያለውን እኩይ ልማድና ባህልን በእውነቱ ለመገልበጥ የተደረገ ሥራ መሆኑን ልብ ማለት ይቻላል።

ይህም ደግሞ ኢየሱስ በትምህርቱ ሁሉ ገለጻዎቹ እነማንን የመነሻ መንደርደሪያ እንዳደረገ ማጥናት የበለጠ በቤተ ክርስቲያን ሴቶችን የምናይበትን ግንዛቤ በመለወጥ ያሳድጋል።

ኢየሱስ፦

የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር ለመግለጽ ጠፍቶባት በፍለጋ ስላገኘችው የወርቅ ባለ መሀለቅ አስተማረ (ሉቃስ 15፡8-10)።

ስለ ይቅርታ ሲያስተምር በድንጋይ ተወግራ መሞት አለባት የተባለችውን ሴት መሠረት በማድረግ አስተማረ።

ስለ መንግሥተ ሰማይ ምንነት ሲገልጥ፣ አንዲት ሴት ወስዳ ከሦስት መስፈሪያ ጋር የለወሰችውን እርሾ አመሳክሮ ዘረዘረ (13፡33)።

የክርስቶስ ፍቅርን ጥልቀትና የምስራችን የማድረስ ኃላፊነትን

ሲገልጥ፣ «ከሳምራዊቷ ሴት» ጋር በመነጋገር አብራራ (ዮሐ. 4፡1-42)።

ቤተ ክርስቲያንንም በትክክል ለመግለጽ፣ «የክርስቶስ ሙሽራ» በማድረግ ሴትን ተመራጭ አደረገ (ኤፌ. 5፡22፤ ራዕይ 22፡17)።

ከላይ የተዘረዘሩትን ውሱን መሠረታዊ መንደርደሪያዎችን ከግምት ካስገባን፣ አስከትለን በኢየሱስ የሕጻንነት ዕድገት ውስጥ እናቱ የአይሁድነት ባህልንና ወጉን በማስተማር በመቅድሚ በሦስት ዓመት አገልግሎቱ በርካታ ሴቶች ተከትለውት፣ ተገልግለውና አገልግለውት ማለፋቸው፣ በመስቀል ጉዞውና በመስቀል ላይ ጣሩ፣ በመቃብሩ ዙሪያ እና በትንሣኤው ገድል የቅርቦቹ ሴቶች ሆነው መገኘታቸው ዕይታችንን በማሳደግ ከኢየሱስ እርገት በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጋራ እና በተናጥል እንድንመለከት ያስገድደናል፤ ጳውሎስ፡-

ፌቤን... እርስዋ ለብዙዎች ለእኔም ለራሴ ደጋፊ ሆነች (ሮሜ 16)።

ሊዲያ... ልቧን የመክፈቷ ውጤት በቤቷ ቤተ ክርስቲያንን አስገኘ (ሐዋ. 16)።

ጥቂት ያይደሉ ሴቶች ከጳውሎስና ሲላስ ጋር ተባበሩ (ሐዋ. 17)።

በአያትህ በሎይድ በእናትህ በኤውንቂ ያለው እምነት በአንተ ዘንድ ተገኘ (1ኛ ጢሞቴዎስ)።

የዮሐንስ ማርቆስ እናት ቤትን የአገልግሎት ማዕከል አደረገች (ሐዋ. 12)።

በወንጌል ስርጭት ወቅት ሴቶች በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚፈጽሙት ሥራ ድርሻቸው እንደ ነበር (እነዚህ) ምጥን ጠቋሚ ክፍሎች ያስረዳሉ።

ሴት ከዳግም ልደት የተነሣ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነችበት ቅፅበት ጀምሮ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈሳዊ ዕድገት እየጨመረች በሄደች ቁጥር ልትተገብራቸው የሚገቡትን ሦስት መሠረታዊ ድርሻዎቿን «ክርስትናና ሴትነት» የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ማሳየቱ ለዚህ ዝግጅት ተመራጭ አድርጌዋለሁ፡- ሴትነቷ፣

ሚስትነቷ፣ እናትነቷ፤

በሴትነቷ፡- ከእግዚአብሔር ጋር ግኑኝነት ሊኖራት ይገባል በትሕትና፣ በተገዢነት፣ በአፍቃሪነት።

በሚስትነቷ፡- ከባሏ ጋር ግንኙነት ሊኖራት ይገባል-በታዛዥነት፣ በአክብሮት፣ በታማኝነት።

በእናትነቷ፡- ከልጆቿ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖራት ይገባል፤ በፍቅር በርኅራኄ፣ በአስተማሪነት።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ከእግዚአብሔር ዐይኖች አኳያ ከወንድ እኩል መፈጠሯ፣ የእግዚአብሔርን አምሳልነት በእኩል መጋራቷ፣ እኩል የሞራል ብቃት ያላት መሆኑ፣ እኩል የጸጋው ተካፋይ መሆኗ፣ እኩል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የምትቀበል መሆኑ፣ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃላፊነትን በማወቅ ድርሻዋን ከወዲሁ መወጣት እንዳለባት ያበስራል፤ እግዚአብሔር ተመልካች ሴቶችን ሳይሆን፣ ተሳታፊ ሴቶችን ፈጥሯል።

6) ሴቶችና የእግዚአብሔር መንግሥት

የእግዚአብሔር መንግሥት ይዞታን በሰው ልብ ውስጥ እግዚአብሔር እያሰፋው የሚገለጥበት የሕይወት መገለጫ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት የእግዚአብሔር ሕዝብ አኗኗር በግልና በጋራ በበጎ ሥነ ምግባር ታንጾ የሚኖርበት ዓለም ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ዋስትና ያለው የአማኝ የደኅንነት ሕይወት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት በቤተ ክርስቲያንና በማኅበረሰብ ውስጥ በመገኘት ኃላፊነትን በትክክል የመወጣት እንቅስቃሴ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት ዓለም ሁሉ ከእርግማን የሚወጣበት የነገው የኢየሱስ የነጋሢነት መጻኢ መስተዳድር ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት መገለጫዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምንነት በትክክል ይገልጣሉ፤ እነዚህ ደግሞ ተግባራዊ ሆነው ልከኛ ፍቺአቸውን የሚያገኙት እግዚአብሔር ወንዶችም ሴቶችም በጥቅሉ የመሲሐዊቷ ኅብረተሰብ አባላት እጅ ለእጅ ተያይዘው በዓለም ውስጥ በመገኘት ተገቢ ድርሻቸውን ሲወጡ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 13 ውስጥ በርካታ ምሳሌዎችን

በማንሣት የእግዚአብሔር መንግሥት ምንነት በማያሻማ ሁኔታ ገለጣት፤ መንግሥቱ ትናንት ነበረች፣ ዛሬም በመሀከላችን አለች፣ ነገ በሙልዐት ተልዕኮዋን አተልቃ ትመጣለች። በትናንቱ መስተዳደሯ ውስጥ ሴቶች ድርሻ ነበራቸው፤ በዛሬው የብርሀንና የጨው መገለጫቸው ድርሻቸው እንደ ተጠበቀ አለ፤ በነገው የኢየሱስ የነጋሢነት ዓለም ውስጥ ከእነሙሉ ክብራቸው በዚያም አሉ።

ከዚህም የተነሣ፣ የንጉሥ የካህንነት ተግባራቸውን በአግባቡ እየፈጸሙ፣ የክርስቶስ የአምባሳደርነት ተልዕኳቸውን በድል እየተወጡ ዛሬን ኖረው ለነገ የሚሻገር ሥራ ይጠበቅባቸዋል።

ማጠቃለያ

ይህ ዝግጅት የተዛባ አመለካከት ያላቸው የቀናውን ይይዙ ዘንድ፤ በዕንቅልፍ ዓለም ውስጥ ገብተው አልነቃ ያሉ ባንነው ይነቁ ዘንድ ታቅዶ መዘጋጀቱን ልብ እንድንል እንፈልጋለን።

ይህን ደግሞ በአግባቡ ለመጨበጥ፣ ለሴት የተሰጠውን አሉታዊ ሰዋዊ ፍቺ በመሻር እግዚአብሔር ከፈጠረበት፣ ከዓለመበት አኳያ ቅድሚያ መስጠት ዋንኛ ሆኖ ተገኝቷል፤ ከዚህም የተነሣ ሀገራዊና ድንበር-አለፍ ግንዛቤዎችን በማጤን ሴቶች በጎበረተሰቡና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመገኘት ሊፈጽሙት የተገባውን ሁሉ ዛሬ ያጤኑት ዘንድ ማግባባት ቀዳሚ ተግባሩ ሆኗል።

እርግጥ፣ ዝግጅቱ «ሁሉ በሁሉ» ሆኖ የመጠቀ ጥናታዊ ሥራ አይደለም፤ ቢሆንም ያነጋግር ዘንድ፣ አቅጣጫ ያጣቁም ዘንድ ተፈልጓል። ይህንም በውስጡ እንዳለ አሳይቷል፤ እናም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወንዶችን ከሴቶች ቀላቅላ በምትሄደው ጉዞዋ እንደ ምሳሌ 6 እና 30 እንዳሉት ገብረ ጉንዳኖች ሁሉም የየግል ኃላፊነቱን፣ ሁሉም የጋራ ኃላፊነቱን ሳይዘገይ በመወጣት ጨለማውን ዓለም በብርሀን፣ አልጥም ያለውን ግራገብ ጎብረተሰብ ጨው ሆኖ በማጣፈጥ እንደርስለት ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ማንቃት የዝግጅቱ ተልዕኮ ነው። ማጠቃለያውም ይኸው ነው።

ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍት

Berchi (በርቺ) The Journal of Ethiopian Women Lawyers Association, Vo1-q No2, Summer 2001.

Culture and Change. Ethiopian Women Challenging the Future, IIRR 2003, Nairobi, Kenya.

Diana K. Iry, Pjil-Exploring Gender Speak. McGraw-Hill,2000.

Verta Taylor & Noney. Feminist Frontiers. McGraw-Hill 2001.

Jean E, Syswerda. Women of the Bible. Zondervan, 2002.

The Shepherd's Stuff. Published by World Map, 1993.

Susan M. Shaw. Women's Voices, Feminist Visions McGraw-Hill, 2001.

አልማዝ ተምትሜ፡- የጾታ አድልዎ ምንነትና አመሠራረት፡፡ SOS ***2006.***

ከእንቁ የከበረች፡- የልባም ሴት ባሕርያት፡፡ ኤስ ኣይ ኤም፣ *1998* ዓ.ም፡፡

ታሪኳ ጃርሳ፡፡ የሴቶች አገልግሎት፡፡ ኤስ ኣይ ኤም፣ *1991* ዓ.ም፡፡

መለሰ ወጉ (ዶ/ር)፡፡ የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ፡፡ ብርሀንና ሰላም፣ *1997*፡፡

ብርሃኑ ገ/ጻድቅ በፍቃዱ፡፡ የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት *1992*፡፡

የሰው ደግ ጌታቸው፡፡ የበደል ውርስ ይቅር፡፡ *1997* ዓ.ም፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች፡፡ ኤስ ኣይ ኤም፣ *1998* (እ.ኤ.አ)

አምሳሉና ዳኛቸው፡፡ የአማርኛ ፈሊጦች፡፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ *1979* ዓ.ም፡፡

ክርስትናና ሴትነት፡፡ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፣ *1996* ዓ.ም፡፡

ግርማና ወርቁ፡፡ ሣቅ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ሰብለ ወንጌል በላቸው፡፡ ሴቶችና አገልግሎታቸው፡፡ *1998* ዓ.ም

ይሁዳ 17-25

17. እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ! የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ከዚህ በፊት የተናገሩትን ቃል አስታውሱ::

18. እነርሱ፣ «በመጨረሻው ዘመን ከእግዚአብሔር ፈቃድ የራቁ የገዛ ራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ፌዘኞች ይመጣሉ» ብለዋችሁ ነበር::

19 እነርሱ ሰውን የሚለያዩ፣ የሥጋን ምኞት የሚከተሉ፣ መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ሰዎች ናቸው::

20. እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፣ ከሁሉ በላይ በተቀደሰው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ:: በመንፈስ ቅዱስም ኃይል ጸልዩ::

21. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በምሕረቱ ወደ ዘላለም ሕይወት እንዲያደርሳችሁ በመጠባበቅ ራሳችሁን በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ጠብቁት::

22. ለሚጠራጠሩ ሰዎች ርኅራኄ አድርጉላቸው፤

23. አንዳንዶችን ከእሳት አውጥታችሁ አድኑአቸው፤ ሌሎችን በፍርሃት ራሩላቸው፤ ሆኖም በኃጢአት የረከሰውን ሰውነታቸውን የነካውን ልብስ እንኳ ሳይቀር ጥሉ::

24. እንዳትወድቁ ሊያደርጋችሁና ነቀፋ የሌለባችሁ አድርጎ በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችል፣

25. እርሱ ብቻ መድኃኒታችን ለሆነው አምላክ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከጥንት ጀምሮ፣ አሁንም፣ ለዘላለምም ክብርና ግርማ፣ ኃይልና ሥልጣንም ይሁን! አሜን:: [አ.ት. (የታረመ) 1997]

***

ዐውደ ትንቢት - ድምፀ ቤዛ:- ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ካስተ ላለፈችው የቀደሙ መልእክቶቿ አንዱ የዘላለም መንግሥቱ የትሮይ ፊረስን ነበር *በ1992 ዓ.ም* በቁጥር *5* ላይ የዘረዘረችው፤ በትንተናዋም የግሪክ ሀገራት በሆኑት በትሮይና በእስፓርታ ሰዎች መካከል ጠብ ነበር፤ ትሮይ ግን አይበገሬ ሆና ለብዙ ዘመናት ጸንታ የኖረችው ከነበራት ግንብ የተነሣ ነበር፤ ዙሪያዋን በከበባት ወደር-የለሽ ቅጥር ተከልላለች፤ ግንቡ ማንም ሾልኮ እንዲገባ አላደረገም፤

መግቢያ በሮቿ በአደፈጡ ወታደሮቿ ይጠበቃል፤ የተዘጋው ሲከፈት አይታይም፤ በትሮይ ግን የእስፓርታውያን ልዕልት ተ ማርካ በቤተ መንግሥት አለች፤ እርሷን ለመመለስ ያልተቆፈ ረ ድንጋይ አልነበረም፤

ሀገሪቱን ሊማርክ፣ ሊያሸንፍ ያለው የእስፓርታ ጦር ሁልጊዜ ሙከራ ያደርጋል፤ ስኬት ግን የለም።

በአንድ ወቅት ግን የጦርነት ወሬ መወራቱ ቆመ፤ ሀገሪቱንም ለተከታታይ ዓመታት ልገዳደርሽ የሚሏት ስፓርታውያን ትእኩ ሳውን ትተው ስሟን የሚያገን፣ ኩሩነቷን የሚገልጽ ዝና ይናኙላት ያዙ።

ውሎ አድሮ ስሟን ያገንላት የነበረው የእስፓርታ መንግሥት ለሀገሪቱ ስጦታን መላኩ እና ያ ስጦታም ወደ ግንቡ እየተጠጋ መድረሱን መንግሥቱ አወቀ። የሚመለከታቸው ልዑካን ተልከው ባነጋገሩ ጊዜ፣ ስለ መንግሥቱ ጽኑነት፣ ምሳሌነት እንዲሁም በትሮይ ላለችው ጣዖት የተላከ ከእንጨት ሙሉ ለሙሉ የተሠራ ፈረስን እንዲያደርሱ መላካቸውን አረጋግጠው በየገዛ ፈረሳቸው ሸምጥ ጋልበው ተመለሱ።

ፈረሱን ወደ በሩ ባስጠጉት ጊዜ ግን ከግዝፈቱ የተነሣ የሚገባ አልሆነም፤ ቁመቱ ከበሩ፣ ከግንቡም ከፍ ብሏል፣ የጎኑም ስፋት ሙሉ በር ቢከፈት እንኳ አያስገባውም።

ከዚህም የተነሣ፣ ምክክር ተደርጎ «ስጦታው» በመግባቱ ላይ የትሮይ ባለሥልጣናት ተሰማሙ፣ በሩን ነቅለው ጎኑን አስፍተው፣ ግንቡን ነድለው አስገቡት፣ ወዲያውም እጅ በእጅ ግንቡ ተሠርቶ በሩም እንዲገጠም ተደረገ።

ስለ ታላቁ ስጦታ ፈረሱን ከከተማው መሀል በማቆም ሕዝባዊ ደስታ ሆነ።

***

ታላቂቱ የትሮይ ከተማ ግን የዛንለት ነዳ አደረች፤ ታላቅነቷም የዛን ዕለት አበቃላት። ለካስ ስጦታ ላኪው በፈረሱ ሆድ ውስጥ ጦሩን ጭኖ ወታደሮቹን አኑሮ አስገብቷል፤ ሁሉ ባንቀላፉበት ሰዓት ከፈረሱ ሆድ ወጥተው ቤተ መንግሥቱን ተቆጣጠሩ፣ ከተ ማዋን አጋዩ፣ በሩን አስከፍተው ሩቅ የመሰለትን አስገቡ፣ ለ10

ዓመታትም ፍዳ አሳየአቸው፤ ጠላት አልሸነፍ ያለውን ሁሉ በስልት ሊቋቋመው ይሞክራል፤ ያንንም ያደርጋል፤ ቅጥርን ማስፈረስና መግባት።

ዛሬ ውጫዊ ውበት ባላቸው ትላልቅ ስጦታዎች፡- ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መንፈሳዊ ገጽታ ባላቸው ነገሮች ብዙ ነገር ሊፈርስ እንደሚችል ይህ ገለጻ አመላክቷል፤ ይሁዳ፡- ይህንኑ ነው እያለ ያለው።

***

ታላቁ የቻይና ግምብ ቢያንስ ሦስት ጊዜ በጠላት ተደፍሯል፤ ለመደፈሩ ምክንያቱ ደግሞ ቻይናውያን ናቸው። የቻይና ወታደሮች በገንዘብ ተታለሉ፤ አደረጉትም። ቄርዝቢ፣ «*ጠንካራ መከላከያን የሚወስነው የጠንካራ ሰዎች መኖር ነው*» ይላሉ። ይህ ገለጻ በመንፈሳዊ ውጊያም ላይ ተመሳሳይነት አለው።

***

ቤተ ክርስቲያን አሸንፋ ለመዝለቅ ከፈለገች በውጊያ ላይ መሆኗን በማወቅ የታማኝ ወታደር ኃላፊነት በመወጣት መዝለቅ አለባት። የኤፌሶን መጽሐፍም ሆነ የይሁዳ መልዕክት፣ «የዲያብሎስን ሽንገላ ለመቃወም» (ኤፌ. 6፡11) የጦር ትጥቁን በሙሉ በመታጠቅ በዘመቻው ላይ መገኘት ግድ ነው ይላል፤ ይሁዳም በቁጥር 24፣ «*እንዳትወድቁ፣ እንዳትሸነፉ* የሚያደርግ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር አለ» ይላል።

ይሁዳ ጦርነቱ፡- በዋናነት ከሐሰት ትምህርቶችና ከአስተማሪዎቻቸው ጋር መሆኑን አረጋግጧል፤ የሐሰት ትምህርትና ሰባኪዎቻቸው የመናፍቅ ትምህርት እና መናፍቃን ተብለው ይጠራሉ።

መናፍቅ፡- ስሪተ ቃሉ መንፈቅ ነው፤ ግማሽ ማለት ነው፤ መንፈቀ ለሊት፣ መንፈቀ ዓመት እንደምንል፤ ኪዳነወልድ ክፍሌ እና ከሣቴ ብርሀን ተሰማ፡- መናፍቅ፡- ሙሉ እውነትን ያልተቀበለ፣ በትምህርቱ ሁሉ ግማሽ እውነት፣ ግምሽ ውሸትን አቃይጦ የያዘን ገለጻ ሁሉ **<u>መናፍቃዊ ትምህርት</u>** አስተላላፊዎቹንም **<u>መናፍቃን</u>** እንደሚባሉ ያብራራሉ።

በይሁዳ መጽሐፍ ውስጥ ሾልከው የገቡት ሙሉ ለሙሉ የዚህ ባሕሪ ተካፋዮች የሆኑ ሰዎች ናቸው። የትምህርታቸውም ይዘት፡-

- ✓ ሙሉ ለሙሉ እንዳይካድ፣ እውነት በውስጡ አለበት፣
- ✓ ሙሉ በሙሉ እንዳይታመንበት፣ ውሸት በውስጡ አለበት።

ይህን መሰል ይዘት የያዘውን ትምህርት ወደ ክርስቶስ ማኅበር ማስገባት፣ በዚያም እግሩን ተክሎ ለዘመናት እንዲቆይ ማድረግ ከመናፍቃኑ አካያ ጉልህ ጥቅም አለው።

በመሠረቱ፣ የቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ መኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ በእርሱ አምሳል የተፈጠሩ የሰው ልጆች በምድር ላይ ሲኖሩ ትርጉም ያለውን ሕይወት እንዲኖሩ እና እንዲያልፉ ታደርጋለች።

ቤተ ክርስቲያን፦

* የመኖርን ትርጉም በትክክል ትገልጻለች።
* የሰውን ዘላቂ ስብዕና በማያሻማ ሁኔታ ታስተምራለች።
* ሰው በዚህ ምድር ብቻ ሳይሆን፣ በሚመጣውም ዓለም ዘላቂ ኑዋሪ መሆኑን ታብራራለች።
* ሰዎች እንስሶች ባለመሆናቸው ግብ-የለሾች አለመሆናቸውን ታረጋግጣለች።
* የሰው ልጆች በሚያደርጉት ምንም ጥረት መፍትሔ-አልባ የሆኑበትን ኃጢአትንና የኃጢአትን ምንነት ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ በመታመን የነጻነት ድልን በማወጅ ሕዝብን ከእስራት ትፈታለች።
* ሰላም፣ ፍቅር፣ መተሳሰብ በምድር ላይ እንዲነግሥ የእግዚአብሔር መንግሥት (የእግዚአብሔር ፈቃድ) እንዲጸና ጸንታ ትታገላለች።

***

ሾልከው በየጊዜው ወደ ክርስቶስ ማኅበር የሚገቡ መናፍቃዊ ግንዛቤዎች ግን እነህን ሁሉ በማሸመድመድ እግዚአብሔር ፈቃዱ በክርስቲያኖችና በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት እንዲፈጸም ያዘጋጀው ዕቅድ እንዲላላ እና እንዲፈርስ በማድረግ፣ እውነቱ እንዲቀየጥ እንዲሁም ያለ ዓላማ እንዲኖር በማድረግ ጉዳትን ያደርሳል፤ ይህ እንደ ውጤት ለእነርሱ ለመናፍቃኑ ጥቅም ነው።

***

በርካታ ክርስቲያኖች እና ቤተ ክርስቲያናት ሾልከው ስለሚገቡ መናፍቃዊ ትምህርቶች ያላቸው ግንዛቤ የተገደበ ነው።

ለእነርሱም መናፍቅነት፦

⇒ «ኢየሱስ ፍጡር ነው» ብሎ ማስተማር፣

⇒ «ሥላሴ ሰው-ሠራሽ የሰይጣን ፈጠራ ነው» ማለት፣

⇒ «ሃይማኖቶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የማድረሻ አማራጮች ናቸው» የሚል ትምህርት፣

⇒ «ድነት በሥራ አማካኝነት» ይገኛል የሚል ሰበካ፣

⇒ «የዳኑ ስለማይጠፉ እንደ ልባቸው ይኑሩ» የሚል ትምህርት እና የመሳሰሉትን

ብቻ በማነፍነፍ፣ በቤተ ክርስቲያን መኖር አለመኖራቸውን በማድፈጥ፣ በመጠባበቅ መጽናትን ወይም እነርሱን ተቋቁሞ ማለፍን ብቻ የታማኝ «አርበኛነት» ሥራ አድርገው ያምናሉ፤ ይቆጥራሉም። እነዚህ ሁሉ መታረም፣ መገሠጽ፣ መወገድ ያለባቸው መናፍቃዊ ትምህርቶች ናቸው። በእነርሱ ላይ ጽኑ እርምጃ መውሰድ ግድ ነው።

ሾልከው ስለሚገቡ አስተማሪዎች እና ትምህርቶች ስንነጋገር ግን ከዚህ ይሰፋል፤ ከዚህ ይልቃል።

ይሁዳ በቁጥር 3፣ «... በማያዳግም ሁኔታ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አንድ ጊዜ ስለ ሰጠው እምነት በብርቱ እንድትጋደሉ ለመምከር ልጽፍላችሁ ግድ ሆነብኝ» ሲል፣ ግንዛቤው እግዚአብሔር በምድር ላይ በቤተ ክርስቲያን (በክርስቲያኖች) አማካኝነት እንዲፈጸሙ የፈለገው ተልዕኮ ዳር እንዳይደርስ የሚያደርጉትን በሙሉ ማለቱ እንደ ሆነ ልብ ማት ተገቢ ነው።

ቁጥር 17 እና 18 የክተት ጥሪው፦ ወደ ክርስቶስ ቁመት በማያደርሱ ምንም ነገሮች ላይ ትኩረት በመስጠት መፋለም ነው።

***

- ግብ ያለው ሕይወት መኖር፣ ክርስቶስ የሄደበትን ዱካ መከተል እና የእግዚአብሔር የሆነውን ሀሳብ መፈጸም፦ የተወሳሰበ ጉዳይ

አይደለም፤ የሚከብድና የሚያስጨንቅ ኃላፊነትም አይደለም፤ ይልቅስ፡- የልዑል እግዚአብሔርን ማንነት ባለመረዳት፣ የሰው ልጆችን አቅምና ዳርቻ ባለማስተዋል በሚመጡ ወጥመዶች መያዝ በጦርነቱ ውስጥ ተሸናፊ በማድረግ፤ ወደ ኋላ በመጎተት ያለ ፍሬ ስለሚያስቀር፣ ልብ መግዛት ተገቢ ነው። እና ይሁዳ፡-

«እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ! የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ከዚህ በፊት የተናገሩትን ቃል አስታውሱ። እነርሱ፣ «በመጨረሻው ዘመን ከእግዚአብሔር ፈቃድ የራቁ የገዛ ራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ፌዘኞች ይመጣሉ» ብለዋችሁ ነበር **(ቁ. 17፣ 18)** ይላል።

በቁጥር 5 ላይ፣ «ይህን ሁሉ አስቀድማችሁ የምታውቁት ቢሆንም... ላስታውሳችሁ እወዳለሁ» በማለት፡-

- ⇒ ሰዶምና ገሞራን፣
- ⇒ የመላእክትን ዐመፅ፣
- ⇒ የቆሬን ዐመፅ እንደ ገለጸልን ሁሉ፣ «አሁንም ሐዋርያት ከዚህ በፊት የተናገሩትን ቃል አስታውሱ...በማለት መልእክቱን የሚጽፍበትን የመጨረሻው ዘመን መገለጫ» እንደ ሆነ ያረጋግጥላቸዋል።

ቅድሳን መጻሕፍት፡- ለሰው ልጆች፣ በተለይም ለክርስቲያኖች፣ የዘመን መጨረሻ የጀመረው የእግዚአብሔር ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚያ ወዲህ ባሉት ጊዜ ያትም ሆነ ወደፊት በሚመጣው ዘመን፡-

- ✓ ሌላ መድኃኒት አይመጣም፤
- ✓ ሌላ መልእክት አኖርም፤
- ✓ ሌላ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው ማንነት የሚረዳ ቅንጣት መገለጫ አይወጣም።

ሁሉ ነገር ተጠቃሎ በሰዎች መካከል በተገኘው፣ ፍጹም ሰው ሆኖ በመምጣት እግዚአብሔርን በገለጸው በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሟል፤ እርሱ በመሠረተው መሠረት ላይ አማኞች በተናጠልና በጋራ ሕንፃው ፍጻሜ እንዲያገኝ ይሠራሉ።

***

አንርሳ፣ ሁሉም ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚጻረር ትምህርት እንዳለና የትምህርቱም ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን በመምታት ላይ የሚያነጣጥር መሆኑን ተናግረዋል።

- ✓ ጳውሎስ፣ 1ኛ ጢሞ. 4፣ 2ኛ ጢሞ. 3 ላይ፣
- ✓ ዮሐንስ፣ 1ኛ ዮሐንስ 2፡18-4፡1-6 ላይ፣
- ✓ ጴጥሮስ፣ 2ኛ ጴጥ. 3፡3 ላይ

ይሁዳም ሐዋርያ ባይሆንም በመልእክቱ ያሳሰበው መናፍቃዊ ትምህርቶች ከየትም ይምጡ፣ በውጤታቸው ግን ክርስቲያንን ያደክማሉ፣ ያፈዛሉ፣ ወደ ኋላ ይጎትታሉ፣ ጠልፈው በመጣል ያለ ፍሬ ያስቀራሉ። ከዚህም የተነሣ፣ መቃወም፣ መታገል እና ሁሉን አጥርቶ ማየት ተፈላጊ ነው።

***

10ኛ ክፍል ሳለሁ፡- በዕድሜ የከበሩ ምናልባትም ጡረታ ሊወጡ አምስት ዓመት ብቻ የቀራቸውን የአማርኛ መምህሬን አስታውሳለሁ። እርሳቸው ለማኦ ሴቱንግ ትምህርትና ለዲያሌክቲካል ቁስ አካላዊነት የሁሉ ነገር መነሻነት እጃቸውን ሰጥተው ነበረ፤ ከዚህም የተነሣ፣ ክርስትና ላይ ያነጣጠረ ትምህርትን መስጠት ሥራቸው ሆኖ ቀጠለ።

መጽሐፍ ቅዱስን ማንም ዘወር ብሎ እንዳያየው፣ «ሴት ለባሏ ትገዛ»ንና በየመጽሐፉ ባሪያ እና የመሳሰሉት መግለጫዎችን ሁሉ በመልቀም፣ መጽሐፉ የጨቋኞች ድርሰት መሆኑን በማስተማር አማርኛን ረሱ።

አንድ ቀን ከመግባታቸው በፊት በጥቁር ሰሌዳው ላይ «ባርነትን ስትቃወም አንተ ራስህ የኃጢአት ባሪያ ሆነህ እንዳትገኝ» የሚል ጽሑፍ ጽፌ ጠበቅኋቸው።

መልእክቱ ለሚያደንቋቸው ተማሪዎች እና ለራሳቸውም ጭምር ስለ ነበር፣ ትንሿ ልቤ ደነገጠች፤ በክፍለ ጊዜው አልቀሩም ገቡ፤ አነበቡት፤ ማን ጻፈው? ስላሉም እኔው በሰፊው ሕዝብ ተጋለጥኩ፤ ሰውየው ተቆጡኝ፣ ግን ደግሞ ዕድል ሰጡኝ፣ «የሚቀጥለውን ክፍለ ጊዜ ለአንተ ሰጥቻለሁ፣ የጻፍካትን

ታብራራለህ» አሉኝ ደስ አለኝ፤ አልከፋኝም።

የዛን ጊዜ በምስራች ድምፅ ሬድዮ «ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ» በማለት ያስተምር የነበረው አቶ ሰለሞን አባተ የትምህርት ቤ ታችንን የክርስቲያን ጎብረት ያስታጥቅ ስለ ነበረ፤ በጊዜው አዘጋጅቶ የሰጠውን ጽሑፍ በደንብ አንብቤ ተማሪ ጓደኞቼ ፊት እና ጋሽ ገላው አጠገብ ቆሜ ገለጻ ሰጠሁኝ።

ያኔ ባደረኩት እስከ ዛሬ የማልረሳው ነገር፦

⇒ ደስተኛ ነበርኩ፣

⇒ ድፍረት ነበረኝ፣

⇒ ሰውን እግዚአብሔር ፈጠረው እንጂ ዝግመተ ለውጥ አልነካውም በማለቴ ረክቼ ነበር።

⇒ የኃጢአት ባሪያ ማለትም ኢየሱስን አለማመን መሆኑን አብራርቼ ነበር። ዛሬ ላይ ቆሜ ያለፈውን ትናንት ከ25 ዓመታ በኋላ ስመለከተው፣ በጊዜው ያንን አቅምም፣ ጸጋም፣ ማስተ ዋልም የሰጠኝ ጌታ መሆኑን አልዘነጋም። ይህ ድርጊቴ ከቁጥር የማይገባ የሚመስል ነው፣ ግን አስተዋጽኦ ነበረው። ሁሉም ክርስቲያን ባለበት ተመሳሳይ አቋም ቢወስድ ትርጉም ያለው ሥራ ሊሠራ ይችል ይሆን? ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ፤

ያኔ ነበር፦

«አዲስ ሰው ሆንኩኝ አዲስ ፍጥረት
ከቶ ላይገዛኝ ኃጢአት ወይ ሞት» የሚለው ዝማሬያችን
«ማርክሲስት ሆንኩኝ ሌሊኒስት
ከቶ ላይገዛኝ ኤምፔሪያሊስት» ተብሎ በየቀበሌው ኪነት የሞቀው።

⇒ ***ትኩረት መስጠት፣ ምላሽ ማዘጋጀት፣ ወቅቱን ጠብቆ ምላሽ መስጠት የሐሰት ትምህርቶችን አቅም ይገታል።***

***

ሸማግሌው ከባሕር ዳርቻ አይጠፉም፤ የባሕሩ ማዕበል በየሰዓቱ እየተነሣ ብዙ ዓሣዎችን ወደ ደረቁ አሸዋማ ዳርቻ ይወ

ረውራቸዋል፤ ዓሣዎቹ በደረቁ ምድር ላይ ከቆዩ ይሞታሉ፡- ሽማግሌው ይህን ልብ ስላሉ፣ አንዳንድ ዓሣ ወደ ባሕሩ ቢመልሱ አያሌ ዓሣዎች እንደሚያተርፉ አመኑ እናም ይህንን በየጊዜው ያደርጉ ጀመር።

አንድ ወጣት ግን ይህን ድርጊታቸውን ተመልክቶ ስለ ነበር፣ «አባት ለምን ይደክማሉ? የእርስዎ አንዳንድ ዓሣ ወደ ባሕሩ መወርወር ዓሣዎቹን ከእልቂት አያተርፋቸውም እኮ፣» ይላቸዋል።

የሽማግሌው መልስ፣ «ልጄ አንድ ዓሣን እንኳ ወደ ባሕሩ መመለስ የአንድ ዓሣ ዕድሜ በማርዘም ልዩነት ያመጣል፣ ይህንን ማድረጌንም እቀጥላለሁ» አሉት።

ልክ እንዲሁ ብዙ ነገሮች ተስፋ አስቆራጭ ቢመስሉም፣ <u>ይሁዳ</u> ግን <u>**ተዋጉ**</u> ማለቱን አላቋረጠም።

ሐዋርያቱ ያሳሰቡት ክርስቲያኖችን የሚቋቋም ፈተና ሁል ጊዜ፣ በየትኛውም ዘመን አለ። ከዚህ የተነሣ፣ አማራጭ የሌለው መፍትሔ መቋቋም ብቻ ነው።

***

በቁጥር 19 ላይ ሾልከው ለመግባት የሚጥሩት እና የገቡት፣ «...መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ሰዎች ናቸው» ይላል፣ ይህ ማለት ደግሞ፡- ባለመወለድ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና የእርሱን መለኮታዊ መገለጥን ፈጽመው አያስተውሉም። እነርሱ ፍጥረታዊ ሰው ስለሆኑ፣ ዓለማዊ፣ ምድራዊ ሰዋዊና ሰይጣናዊ የሆነውን ፍላጎት ብቻ የሚያስተናግዱ ናቸው፤ ከዚህም የተነሣ፣ መለኪያቸው ሰው እንጂ፣ እግዚአብሔር አይደለም።

ሁላችንም በአንድ ወቅት እንደ እኒህዎቹ ሰዎች ነበርን፣ ግን እግዚአብሔር የልዩነት ምክንያትን በሕይወታችን ውስጥ በማኖር እርሱን እንድንረዳ፣ ከአጎጉል አመለካከታቸውም እንድንጠበቅ ተመከርን።

> ይሁዳ በቁጥር 20፣ *«እናንተ ግን... ከሁሉ በላይ በተቀደሰው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤ በመንፈስ ቅዱስም ኀ ይል ጸልዩ።»* አለ።

<u>እናንተ ግን</u> የሚለው ሐረግ ንጽጽርን አመልካች መግለጫ ነው።

በክተት ጥሪ ውስጥ የተካተቱ በሙሉ፣ በጦርነት ላይ ሳሉም አኗኗራቸው በተቀደሰው እምነታቸው ራሳቸውን ማነጽ ነው፤ ይህንን በማድረግ መትጋት ኑሮአቸው መሆን አለበት፤ ራሳቸውን ለማነጽ በቀዳሚነት ለየግላቸው የተተወላቸውን ኃላፊነት መወጣት ግዴታቸው ነው፤ በማኅበር ሲሆኑ ለቤተ ክርስቲያን በተሰጧት አስተማሪዎች፣ መጋቢዎች፣ መካሪዎች ሥር ሆነው ተግተው መማር ይጠበቅባቸዋል። ቢያንስ እሑድን በአጥቢያቸው ተገኝተው «ሳይቻኮሉ» ከጌታ ያገኙትን ኅብረት መፈጸም አለባቸው። ለማነጽ እና ለመታነጽ መትጋት ይህ ነው፤ በተያያዥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መጸለይ አቅምን በማግኘት በጦርነቱ ውጤታማ ያደርገናል።

ከ10 ዓመት በፊት አንድ መጽሔት አዘጋጅ ነበር፤ በዚያን ጊዜ በማዘጋጅበት ጊዜ አንድ ዜና መጣልኝ፡- በስካንዲኔቪያን ትላልቅ የገበያ ማዕከላት፡- እንደ ደንበል፣ መርካቶ፣ ይርጋ ኃይሌ እና ጌቱ ኮሜርሻል የመሳሰሉ አዳራሾች-በእሑድ ቀን ለሕዝቡ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች በአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ክፍት ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ መወሰኑን የሚገልጽ መግለጫ በመገናኛ ብዙኀን ተነገረ። ይህን ሕዝቡም ሰማ፤ ይህ በሆነ በማግስቱ ግን ወደ መንግሥታቸው ምክር ቤት ስፍር ቁጥር የሌለው ተሰላፊ ከተማውን አቋርጦ ደረሰ፤ የያዙት ቅስት፣ «እሑድ የጌታ ቀን ነው፣ ዕረፍት አድርገን ራሳችንን የምንመዝነው ለአንድ ቀን ነው፣ ክርስቲያኖች ይህንን በመቃወማችን ምንም ዐይነት ተጽዕኖ ሊደረግብን አይገባም፣ በእሑድ ኮሌጅ ከመግባት በጌታ ቤት መገኘት ምርጫችን ነው፣ መንግሥታችን የሀገሩን ዜጎች አግልሏል፣» የሚል ነበር።

***

አማኞች ይህን ተቃውመው ለመውጣታቸው በርካታ ምክንያቶች ነበሯቸው፤ ዋንኛው የማንም ሕይወት ተያያዥነት አላት፤ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖን ውሎ አድሮ የሚያመጣ ውሳኔ መሆኑን፣ <u>በቤተ ክርስቲያን</u> በእሑድ ቀን ሊገኙ የተገባቸውን ወገኖች ከፍሎ የሚያስቀር ምንም ዐይነት እንቅስቃሴ ከራርሞ በሌላው ተቃዋሚ እና ፈላጊ <u>ክፍል ውስጥ በቀላሉ</u>

መሸጎጥን እንደሚያመጣ መገንዘብ፣ ከሁሉም በላይ ቤተ ክርስቲያን ያላትን አንድነት ፍቅር እንዲሁም ሰዎችን ወደ ክርስትና ለማምጣት የመጋበዝ አቅሟን እንደሚያፈዘው መረዳት እና ከሁሉም በላይ የዓለምን ሥርዓት ባለ መከተል የሾለኩ ስሕተታዊ አሠራሮችን ሊያመጡ የሚችሉትን በድፍረት መቋቋም ከወዲሁ ተገቢ መሆኑን አውቀዋል።

የስሕተት ትምህርቶች ተከላካይ እስካጡ ድረስ እየተስፋፉ ይሄዳሉ፤ እያንዳንዱ አማኝ 24 ሰዓታት በየቀኑ ይጠቀምበት ዘንድ ተሰጥቶታል። ከእነዚህ ሰዓታት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ከማን ጋር ውለን፣ ከማን ጋር ተገናኝተን፣ በማን ደጃፍ ተምረን፣ ሠርተን እንደምንገባ የምናውቀው እያንዳንዳችን ነን።

መቆያ ስፍራችንን እንለውጣቸዋለን ወይም ይለውጡናል። ምን ጊዜም ክርስቲያኖች እውነተኛ ደቀ መዝሙር ሆነው ግብ ያለውን ሕይወት እንዲመሩ ጌታ ይፈልጋል።

<u>በዘመናት ውስጥ ሾልከው የገቡ የሐሰት አመለካከቶች</u> ሁሉ ቸል ተብለው <u>በተተዉበት ስፍራ ሁሉ</u> ክርስቲያኖች ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም አቅቷቸው «አቅመ ቢስነትን» የኑሮአቸው መለያ አድርገውታል፤

⇒ ክርስቲያኖች፦ የክርስቶስ መሆናቸውን ለመግለጽ ፍላጎት ያጡበት ስለ ክርስትናቸው ምላሽ ሊሰጡበት የሚያበቃ ዕድል በእጃቸው ላይ ሲቀመጥ የሚሸሹበትና የሚያፍሩበት ሁኔታ በብዙዎች ዘንድ እየሰፋ ሄዷል።

⇒ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትም የእሑድ ታዳሚዎችም ልባቸውና አካላቸው በተራራቀበት ሁኔታ «መጥቶ የሄደ» ዓይነት ውሎን ሲፈጽሙ ይታያል፤ በርካታ ቸልተኝነቶች በአማኞች ሕይወት ውስጥ ከተገለጹ የእነዚህ መሠረታዊ ምክንያት ወይም መነሻ <u>የሐሰት ትምህርቶች እርሾ ቦክቶ መጋገሩ ነው</u>።

የሐሰት ትምህርቶች፦

- ጽድቅን ይቃወማሉ፣
- ግዴለሽነትን ያንጸባርቃሉ፣

- ታማኝነትን ይቀንሳሉ፣
- ለራስ ቅድሚያን ይሰጣሉ፣
- በማኅበራዊ ኑሮ ስም ከጌታ ጋር የሚቆዩበትን ጊዜ ይቀንሳሉ፣
- መንፈሳዊነት ምራቂ ወይም ተከታይ «ባጣ ቆየኝ» ኑሮ ያደርጉታል፤
- እንደ ዜጋ የተሰጣቸውን ሀገራዊ አቅም አይገልጡም፣
- እንደ ሁነኛ ቤተሰብ ትዳራቸውን በቅጡ አይመሩም።

እነዚህን የመሰሉ አቋሞች በአንዱ በሰው ውስጥ ገብተው አይታዩም፤ ትናትናና ዛሬ ተያይዘው ባሉበት ግንዛቤ «በምንም አይደል» ማዳበሪያ ጸንተው የበቀሉ ናቸው።

***

የሥራ ባልደረባዬ የገጠመውን የአውቶቢስ የጉዞ ታሪክ ተርኮልኝ ነበር። ባለፈው ዓመት «ዲጂታል ካሜራውን» ከመጣበት ከክፍለ ሀገር አውቶቢስ ላይ ትቶ ወረደ፤ ከቤቱ ደርሶ መጣሉን ባወቀ ጊዜ ኀዘን ተጫነው፤ በሳምንቱ ግን አንድ ሰው ስልኩን አግኝቶ ከደወለ በኋላ ካሜራውን ማግኘቱን ነግሮት ሊሰጠው ቀጠረው። ጓደኛችን «ምስጋናውን ደረደረለት፣ መረቀው፤ እንደዚህ ዐይነት ክርስቲያን በዘመኔ አልገጠመኝም፤» ብሎ አመሰገነ፤ ተገባብዘው በመጨረሻ ለማንኛውም ስምህን ልወቅ ባለው ጊዜ፣ «አቡድልአዚዝ» እባላለሁ ነበር ምላሹ። ከክርስቲያን ይጠበቃል ያለለት ሥነ ምግባር ከሌላ በተሰማ ጊዜ ደነገጠ። ዛሬ ክርስቲያኑ የሚመሰገንበት እያነሰው የሚወቀስበት ከበዛ አቅምን ያሳጣ አንድ ጠንቅ አለ፤ ያንን ማ ረም ተገቢ ነው።

***

በርካታ አማኞች የዲቪ (DV) ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን በተ ዘጋጁበት እና ሁሉን ጨርሰው አሜሪካ የገቡበት ታሪክ ሲፈተሽ ንጽሕናን መሠረት ያደረገው በቁጥር ትንሽ ነው። ከDV ውጭ አሜሪካ ለመግባት የሚፈልጉ በርካቶቹ፡- ኬንያ፣ ሱዳን፣ የመን ወይም እዚያው አሜሪካ ተቀምጠው የሚሞግቱበት የፍርድ ቤት ሥርዓት፡- የአብዛኞቹ «ጌታ ራሱ ዋሽልኝ እኔም ጸጋን» አበዛላች

ኃላሁ ያላቸው እስከሚመስል የደረሰበት ሁኔታ እንዳለ፤ ብዙዎች ይናገራሉ። በጌታ ነን ላሉ ወንድሞች እና እኅቶች ምን ነው ይህ ምርጫቸው ሆነ?!

***

ይሁዳ፣ ማንም መንፈሳዊ እንደ ሆነ ራሱን የቆጠረ፣ ማንም ግብያለው ሕይወት እኖራለሁ ብሎ እንደ ክርስቲያን የሚኖር፣ ማንም በቁጥር 22 እና 23 ላይ እንደ ዘረዘረው፡-

⇒ «ለሚጠራጠሩት ርኅራኄን በማሳየት ወደ ሩጫው መንገድ ወደ ትክክለኛው መልሱአቸው።»

⇒ ከእሳት ተናጥቀው መትረፍ የሚገባቸው ካሉ አስፈላጊውን ውሳኔና መሥዋዕትነት ክፈሉ።

⇒ «የረከሱ እና የወደቁ ካሉ በሥራቸው ሳትተባበሩ ግን ኃጢአታቸውን ገልጾ በማሳየት እና በመግለጽ ወደ ሕይወት መልሷቸው» ይላል።

***

የእንቁራሪት በላተኞች፡- እንቁራሪትን ቀቅሎ ለመብላት ውሃውን አፍልተው በትልቁ ድስት እንቁራሪቶቹን መዘርገፍ የዝግጅቱ መጀመሪያ ነው፤ ይህ በሆነ ጊዜ ግን ከተዘረገፉት 3/4 ኛዎቹ ፍሉ እንደ ነካቸው ተፈናጥረው በመውጣት ድስቱን ባዶ አደረጉት።

ሆዳሞቹ ሰዎች ግን ያደረጉት የሚመቻቸውን ሰፊ ገንዳ በማዘጋጀት ያለ ችግር በሚዋኙበት ታላቅ ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ አኖሩአቸው፤ አሁን የዘለለ የለም። ቀጥለው በላተኞቹ የታላቁን ገንዳ ውሃ ሊያስተውሉት በማይችሉበት መጠን ቀስ ቀስ እያሉ ወደ ለብታ፣ ከዚያም ወደ ፍል ውሃነት አሻገሩት፤ በዚህ ሂደት ውስጥ ያመለጠ እንቁራሪት አልነበረም፤ ለመብል የደረሰ ቅቅል እንጂ፤ እንግዲህ፡- ሕይወታችን በሐሰት አስተማሪዎችና በትምህርታቸው ተጽዕኖ ውስጥ አለ ወይስ ለክተት ጥሪው ታዳሚ በመሆን የታማኝ ወታደርን ሚና እየተጫወትን ነው? ውጤታማ እንድንሆን ካህን መሆናችንን ማወቅ፣ ካህን ከሆንን ደግሞ ፍርሀትን አሸንፈን መቆም አለብን በማለት የይሁዳን መልእክት እጨርሳለሁ።

የሚሊኒየሙ መርዶ እና ብሥራት

ሀ) የጥናቱ መንሥኤ

«የኢትዮጵያን ባይብል ባፕቲስት ቸርች ፌሎሽፕ (Ethiopian Bible Baptist Church fellowship) ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በጎብረቱ ሥር ለታቀፉት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት መሠረታዊ ዕውቀትን ሊለግሱ የሚችሉ ዐውደ ጥናቶችን ማካሔድ ጀምሯል፤ ይህ ጅምሩ እጎትማማች ቤተ ክርስቲያናት ጎብረታቸውን የበለጠ ያጐለብቱ ዘንድ ረድቷል፤ በአጠቃላይ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በየጊዜው በሚያቀርቡት ትምህርቶች ተጋባዥ እና አጋዥ በመሆን ተጠቀመዋል፤ ጎብረቱንም አግዘዋል።

ይህ ጎብረት በ1999 ዓ.ም ካቀዳቸው ዝግጅቶች ውስጥ አንዱ ፦ ይህ ዓመት እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር 2000 ዓመተ ምሕረት ስለሚሆን፣ ይህን የሁለት ሺህ የምሕረት ዓመትን ለመቀበልና በተከታዩ መባኢ ዓመታት ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ተልዕኮ በአግባቡ ዳር ለማድረስ እርስ በርስ መተሳሰብ ተፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህም የተነሣ፣ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዘመን አቆጣጠሩ ከአውሮፖውያን የተለየ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ የ2000 ዓመት ምሕረትን አቀባበል ሀገራዊ እና አፍሪካዊ በሆነ አኅጉራዊ ደረጃ አዘጋጅቷል፤ በዝግጅቱም ሀገርን ማስተዋወቅ እና ዘላቂ ችግሮቻችንን መቅረፍ ቀዳሚ አጀንዳው ሆነውለታል።

የኢትዮጵያን ባይብል ባፕቲስት ቸርች ፌሎሽፕ (EBBF) ደግሞ ዓመትን ከሌላ ዓመት በማስበለጥ ወይም በማሳነስ ሳይመለከት፣ ቤተ ክርስቲያናትን ለየራሶቻቸው አጥቢያዎች፣ በተሻገረም ለመላው የኢትዮጵያ ጎብረተሰብ፦ የሚሊኒየሙ ዝግጅት የዘነጋውን (ያፈዘዘውን) የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትን በትክክል በማሳየት ሕዝብ ሁሉ ክርስቶስን ያልቀው ዘንድ፣ ክርስቲያኖችም በጌታቸውና በአዳኛቸው ይታመኑ እና ይደገፉት ዘንድ ይህን ጥናት ማቅረብ አስፈልጎታል።

ከዚህም የተነሣ፣ ዝግጅቱ «ኢየሱስ» - ተኮር በመሆን፣ ያለፉትን 2000 ዓመታትን እና የመጪውን የአንድ ሺህ ዓመት አካሄድ ለመጠቆምና ለማመላከት ይሞክራል፤ በዚህም የዛሬ ሰባት ዓመት አውሮፖውያኑ 2000

ዓመት ምሕረትን እንዴት ተቀብለው እንደ ነበር? የኢየሱስ ማንነት በ2000 ዓመታት ውስጥ እንዴት እንደ ነበር? ኢትዮጵያውያን 2000ን ስንቀበል አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባው ዐቢይ አጀንዳ ምን ሊሆን እንደሚገባው? እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ በቀጣዩቹ ሺህ ዓመታት ምን እንደሚመስል ይህ ጥናት በግርድፉ ያሳያል።

በመነሻነት ቀዳሚ ምዕራፍ ግን «የሚሊኒየሙን ሰው» በማስተዋወቅ ላይ ቤተ ክርስቲያናት ከወሰዱት የአቋም ምሳሌያዊ መግለጫ ይጀምራል።

ለ) የሚሊኒየሙ ሰው

እ.ኤ.አ. በመስከረም 2000 ዓ.ም ታትሞ የነበረው መረጃ የዚህ ዝግጅት ዋቢ ነው፤ አዘጋጁ ክሌመንት በርናባስ ሊል የፈለገው መሠረታዊ ነጥብ ለኢትዮጵያውያኑ የ2000 አክባሪዎችም ተመሳሳይ ጭብጥ አለው፤ ዐቢይ አሳቡና «ስሙኝ» የሚለው ጆሮ ኖሯቸው ሊያደምጡ ለሚችሉ በዓለም ላይ ላሉ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያናት ነው፤ ከዚህም የተነሣ ጭብጡ መላውን ዓለም ሳይመለከት መላውን ክርስቲያን ግን እንዲህ ይላል፦

የዓለም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል (World Council of Evangelicals /WCE) በሚሊኒየሙ ዋዜማ ላይ ተሰብስቦ «የሚሊኒየሙን ብቸኛ ሰው» ለመምረጥ ይመክራል፤ ምክሩም ተሳክቶለት አንድን ሰው በተመራጭነት ያቀርባል።

ይህንንም ለማስተዋወቅ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በዋናው ጽ/ቤት እንዲገኙ ከተደረገ በኋላ፣ ጉባኤው በሦስት አንጋፋ የካውንስሉ መሪዎች በጸሎት ይከፈታል፤ በማስከተልም የካውንስሉ ዋና ጸሐፊ «የሚሊኒየሙን ሰው» ለመምረጥ በርካታ ሰዎችን ካውንስሉ ሲያጣራ መክረሙን ዘርዝሮ ከብዙ ውጣ ወረድ በኋላ አንድ ሰው መም ረጣቸውንና ይህም ሰው ከጥቂት ደቂቃ በኋላ በመድረኩ ላይ ቀርቦ እንደሚታይ ያሳውቃል።

ከዚህ ማስተዋወቅ በኋላም የተጋባዥ ሕዝብ ጆሮው ቆመ፣ ዓይኑ ተኮረ፣ ጉጉቱ በየሰከንዱ እየናረበት ሄደ፤ ማን ይሆን በዓለም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል ታላቅ ሥራን በመሥራት ለዚህ ትልቅ ዕድል የበቃ? ሁሉም በዚህ ሲቃ ውስጥ ተወጥሮ ባለበት

አንዳንዱ ታዳሚ፡- የሚሊኒየሙ ሰው የሚመጣበትን ሊሞዚን መኪናን በዐይነ ኅሊናው ሲገምት፣ የተቀሩት የለበሰው ወደር-የለሽ ልብስና የዋጋውን ወድነት ከራሱ ጋር ሲያነጻጽር፣ ሌላው ያሉትን ዲግሪዎች ብዛት እየቆጠረ ሳለ፡- ሰውየው ከአህያው ጋር በመድረኩ ላይ ታየ፤ ሰውየው ባለ አህያ ነው፤ በዚህ ጊዜ ዋና ጸሐፊው ድምፁን ከፍ አድርጎ «የሚሊኒየሙ ሰው ይኸውና!» ብሎ ጮኸ፤ አጨበጨበም፤ የተሰማው የጭብጨባ ድምቀት ግን የእርሱና የካውንስሉ አባላት ድምፅ ነበር፤ በጉባኤው ያለው የአንዱም እጅ አልተዘረጋም፤ አላጨበጨበም።

ከአህያው ወርዶ የቆመው ሰው ግን የለበሰው መናኛ ልብስ ሲሆን፣ የእግሩ መጫሚያም የገጠሩ ጥልፍልፍ ነበር፤ ከመድረኩ የቅርብ ርቀት ያሉት ሰውየውን «የዓሣ ሽታ አለው፣ በልብሱም ላይ የደረቁ የደም ነጠብጣቦች አሉበት» ይሉ ነበር።

ሰውየው ግን ወደ መድረኩ መካከል መጥቶ ቆመ፡- በዚህ ጊዜ አብዛኛው ታዳሚ «ይህን ሰው አስወግዱት÷ ከዐይናችን አርቁት÷» እያለ መጮህ ጀመረ፤ በጩኸት ይህን የሚሉት ሁሉ በእውነተኛ ቁጣ ውስጥ ሆነው «ተቀለደብን» ይሉም ነበር።

ይኸው «የሚሊኒየሙ ሰው» ብሎ ያስተዋወቀው ዋና ጸሐፊ ግን በቁጣቸው ጣልቃ ገብቶ ማረጋጋት ጀመረ፤ ቀስ እያለ የገነፈለውን ቁጣ አቀዝቅዞ «በሠራነው ምርጫ እና ውሳኔ ላይ ቅሬታ ከምን የተነሣ ኖራችሁ?» በማለት ጠየቃቸው። ከምላሾቻቸው ጥቂቱን እነሆ፡-

«ሰውየው የመጣው ከገሊላ ናዝሬት ነው።»

«በሰውየው የዘር ሐረግ አመጣጥ ላይ ያለው ጥያቄ አልተመለሰም።»

«ክርስቲያን ሆኖ አናውቀውም፤ ስለ መለወጡም የሰማነው አስገራሚ ምስክርነት የለንም።»

«በመደበኛ ትምህርት ቤት ገብቶ አልተማረም።»

«ለሥነ መለኮት ግንዛቤው ምንም ዐይነት ደህራ የለውም።»

«አናጢ ስለሆነ የሚተዳደረው ወንበር ጠረጴዛ ሠርቶ ነው።»

«ለመጓጓዣው መናኛ መኪና እንኳ የለውም።»

«መኖሪያ ቤት የሌለው ጐዳና ተዳዳሪ ነው።»

«ዕድሜው 33 ዓመት ከመንፈቅ ብቻ ነው::» «ከዚህም የተነሣ፣ ምንም ዐይነት ልምድ ባለማካበቱ የፖለቲካ መሪዎችንም ሆነ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በአግባቡ ሊረታ፣ ሊያሳምንና ሊያግባባ ፈጽሞ አይችልም::»

«ከዚህ ሁሉ በላይ፣ የማንም ቤተ ክርስቲያን አባል አይደለም::»

«በዘመኑ በገዛ እጁ መጽሐፍ አልጻፈም፣ የምርምር ጽሑፎችንም ለኅብረተሰቡ አላቀረበም::»

«በሁሉ ነገር ሴጣ (simple) ሰው ነው::»

«ብዙውን ጊዜ የሚገኘው ከድሆች፣ ከበሽተኞች እና ከታወቁ ነው ረኞች ጋር ነው::»

«ወደዚህ ሲመጣ ከነበረበት ሰፍራ ይዞ የመጣው የድጋፍ ደብዳቤ ዎች (Recommendations) የሉትም::»

«በአስተምህሮው ብዙዎች ይጋጨታል፤ በሰዎችም መካከል መለያየትን ይፈጥራል::»

«የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚወሰኗቸው ውሳኔዎች ላይ ቅሬታውን (ተ ቃውሞውን) በማሰማት ይታወቃል::»

የሚሉ ምላሾቹ በዋናው ጸሐፊው ተመዝግበው፣ በመጨረሻ የዓለም የወንጌል አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ውዝግቡን በአግባቡ ከአደመጠ በኋላ፣ ያለምንም ተቃውሞ «በማንም የማይፈለገው የሚሊኒየሙ ሰው» የሚል ዘውድ በራሱ ላይ ጭነው ዳግመኛ እንዲሰቀል በአንድ ድምፅ ወሰኑ::

እናንተ በዚያ ስፍራ ተገኝታችሁ ቢሆን ድምፃቻሁን ለማን ትሰጡ ነበር? «ኢየሱስ የሚሊኒየሙ ምርጥ ሰው» ለሚለው ወይስ «ኢየሱስ በማንም የማይፈለግ የሚሊኒየሙ ሰው»? ልብ በሉ፣ ውሳኔያችሁ ዛሬ ኢየሱስን የተ ረዳችሁበትን መረዳትና የምትኖሩበትን ኢየሱስ-ተኮር የሕይወት ምንነትን ይመለከታል:: (*Light of Life*- September 2000, page 69-70)

ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም፣ ክርስቲያኖችንም እንደ አማኝ እንደ ዜጋ እና በዚህ ዓለም እንዳሉ እንደ አንድ አባል አድርገው ራሳቸውን ቆጥረው ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጡትን ትክክለኛ ስፍራን ቢመዝኑ ጥሩ ነው።

መርዶ ሆኖ ሚሊኒየሙን ከቤተ ክርስቲያን አኳያ የሚያስደነግጠው ኢየሱስን በማግለል ሰው-ተኮር አቋምና አስተሳሰብን በማስተናገድ ላይ ካለን ሚሊኒየሙን በብቻው ተቀብለን ልናስተናግደው እንችላለን፤ በመስተንግዶው ውስጥ ግን «እንግዳው» የለም፤ ወይም ለዘለቄታው አይኖርም።

ይህ ለሚሊኒየሙ መርዶ ነው፤ ምኒልክ አስፋው ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም ባቀረበው ሚሊኒየም-ተኮር ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ክርስቲያኖች እና ቤተ ክርስቲያናት የኖረባቸውንና ሊኖርባቸው የሚችሉትን ተግዳሮቶች ሁሉ ልብ ብለው ማጤን አለባቸው» ብሏል። እንደ አቅራቢው አባባል፣ ድኅረ-ዘመናይነት በግቡ-ቢስነቱና በአምላክ-የለሽነቱ በጥቅሉ ዓለምን፣ በጠበበ ደረጃ ደግሞ ክርስቲያኖችን ከአማኒነት (theism) ወደ አምላክ-ኾነት (deism)፣ ከዚያም ወደ ኢአማኒነት (a theism) በመጨረሻም ወደ ምንምነት (nothingism) የሚያደርስ እንቅስቃሴ ነው ካለ በኋላ፣ ይህ አካሄድ ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ዓለምን ሸፍኖ ቤተ ክርስቲያናትንም እያንገዳገደ መምጣቱን በቀዳሚነት ያረዳናል። በተያያዥ ደግሞ፣ የእስላማዊነት እንቅስቃሴ መስፋፋት ሀገራችንንም ሆነ መላውን ዓለም እየሸፈነ መምጣቱ፣ ይልቁኑ የኢትዮጵያን ሚሊኒየም በመቀበል ላይ ያለን እኛ ን ሊያሳስበን ይገባል በማለት እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ አውሮፓ የክርስቲያን አኅጉር፤ ኢትዮጵያም የክርስቲያን ሀገር በመባል ትጠራ ነበር። ይህ ግን በአውሮፓም ሆነ በኢትዮጵያ በሚያስደንቅ ፍጥነት ተቀይሯል፤ ካለ በኋላ እስልምና ተስፋፋ፣ ሃይማኖትነቱን፤ የሚስፋፋውም እምነቱን ከመስበክ ባሻገር የተለያዩ ጫናዎችንም በመፍጠር መሆኑን ያረጋግጣል። ከዚህም የተነሣ፣ ቤተ ክርስቲያናት በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው፤ ትኩረታቸው ለምን የሙስሊሞች ቁጥር ይጨምራል በማለት ሳይሆን፣ ክርስትና አድማሱ እንዳይሆን የተገታው ከምን የተነሣ ነው? ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መልስ መስጠት የግድ ነው፤ ይህን ቸል ማለት «ኢየሱስን ዳግመኛ ለመስቀል» መዘጋጀት ነው፤ ከዚህም የተነሣ የመርዶው እውነትነት አሌ አይሰኝም።

እንደ ምኒልክ አስፋው አሳሳቢነት ሦስተኛው ብርቱ ጉዳይ ብሔረተኛነት ነው፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ጠባብነት ብዙ አሉታዊ አሻራን ትቶብን እንዳለ አለ፤ ይኸው አካሄድም ወደ ክርስቲያኖች በመዝለቅ ይህን እኩይ ዘር ለማስወገድ እንደ መጣር፣ በምትኩ ዘሩን ለመዝራት ዋንኛ ወይም ቀዳሚ ሆነው ተገኝተዋል። በዚህም የክርስቶስ መንግሥት ከነገድ፣ ከቋንቋ፣ ከወገን፣ ከሕዝብ ሁሉ የተዋጁትን ሁሉ በአንድነት ይዛ እንደምትኖር ተረስቷል። በተ ያያዥ የመንፈሳዊ ሕይወት እንጭጭነት በበርካታ ወንጌላውያን አማኞች ዘንድ መኖርና በምሳሌነት ሊጠሩ በተገባቸው የባፕቲስት አጥቢያዎችም ሰፍኖ መገኘ ቱ በርካታ ክርስቲያኖች ምክንያታዊ ሳይሆኑ፣ ስሜታዊ መሆናቸውን ያ ረጋግጣል።

ኢየሱስን «በሚሊኒየሙ የማይፈለገው ብቸኛ ሰው» ብለው ያስወሰኑበት ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ ከላይ የዘረዘሩት አፍራሽ ሕይወት ውስጥ ውለው በማደራቸው የመጣባቸው አደጋ ነው። ከዚህ ጥፋት ለመትረፍ በተከታዩ ሚሊኒየም ክርስቲያኖች ሁሉ ሊያስቡባቸው የሚገቡ በርካታ ሥራዎች አሏቸው፦ አማኞችን የጌታ ደቀ መዛሙርት ማድረግ፣ የየወቅቱን አፍራሽ አስተሳሰብ መለየት፣ የሠለጠኑ መሪዎችን ማፍራት፣ የወንጌላውያን አማኞች ሁሉ ኃላፊነት ነው። ይህን ባለማድረግ መዘግየት 2000 እንድንቀበለው ቢያደርግም፣ ሌሎች 2000 ተግዳሮቶችን ሳንቋቋማቸው እንድንቀር ሊያደርግ ስለማያስችል፣ ቁርጠኝነት የግድ ነው።

ይህን ቁርጠኝነት ልናመጣ የምንችለው በተቀበልነው በእኛ ሚሊኒየም ውስጥ ገዝፎ ጎልቶ የሚታየው ማን ነው? የሚለውን ከልብ ስንመልስ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ፣ «የዛሬ ስምንት ዓመት አውሮፓውያን 2000 እንዴት ተ ቀበሉት? እኛስ የኢትዮጵያን ሚሊኒየምን ለመቀበል ምን እያደርግን ነው?» ለሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠት ግድ ይሆናል።

ሐ) የዛሬ ሰባት ዓመት

የዛሬ ሰባት ዓመት ዓለሙ ሁሉ «ሽር ጉድ» ሲልለት የነበረ ዓመት ነበር፤ ጃንዋሪ 1 ቀን 2000 ዓመተ ምሕረት፤ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር የተሰፈረለትን የጊዜ ቆጠራ ተንተርሶ 2000 ሊመጣ ሲል ኢትዮጵያዊያኑን ጨምሮ መላው የዚህች ምድር ኑዋሪ ያን ዓመት ሊያየው ጉዋጉዋለት።

እርሱን ቀድሞ ግን አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ዓመታት አልፈው ነበር። ይኸው 2000 ግን ከሁሉ ተለየ። ድርሳናት ዓመቱን ለመቀበል የጠፋው ጊዜና ገንዘብ «የትየለሌ» እንደ ነበር ጽፈዋል፤ እርግጥ በሺህ ዓመት አንድ ጊዜ በሚመጣ የሺ ዓመት - ዓመት ውስጥ መገኘት ልዩ ስሜትን፣ ልዩ ምኞትንና ጉጉትን በማንም ውስጥ ይፈጥራል፤ መፍጠሩም ተገቢ ነው።

መሠረታዊው ጉዳይ ግን፡- ለምን 2000 ከ1569 ወይም 1823 ወይም ከ1981 በተለየ መንገድ ሊታይ ተገባው? ይህስ ከታሪክ አኳያ፣ ከፖለቲካዊ ገጽታ አኳያ፣ ከሀይማኖታዊ ደሀራና መሰል ከሆኑ ዋንኛ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነቱ ምንድን ነው? እነዚህን መመለስ የዚህ ዝግጅት ትኩረት ነው።

ከዚህም የተነሣ፣ ይህ አቅርቦት ዐበይት ነጥቦችን ከዛሬ ሰባት ዓመት ያለፈ ታሪክ ጋር በማስተያየት (እ.ኤ.አ) በ2007 ላይ ቆሞ ያለፈውን 2000ን ያያል፤ እንዲሁም ከራሳችን ሀገር በራሳችን አኳያ በመቃኘት በ 2000 ላይ ቆመን ፈጥኖ የደርሰውን የእኛን የኢትዮጵያውያን 2000ን ይመዝናል።

መ) 2000 በምዕራባውያን

የአሜሪካውያኑ የከተሞች ከተማ በሆነችው ኒውዮርክ (New york) 2000 ዓመተ ምሕረትን ለመቀበል ከልክ ያለፈ ዝግጅት ተደርጎ ነበር። በዚያው ዘመን በእንግሊዝ ሎንደን (London) ለሚሊኒየሙ መታሰቢያ ለማኖር 1.2 ቢሊዮን ፓውንድ አውጥታለች። በአውስትራሊያ ሲዲን ደግሞ ሁሉን የሚያሳትፍ ከዚህ በፊት ከተከናወኑት ክንውኖች የበለጠ የ"fireworks party" ተካሂዶ ነበር፤ በአየርላንድ በማርች 1999 ይከበር የነበረውን የቅዱስ ፓትሪክን ዕለተ ቀንን (St. Partick's day) ከ2000 ክብረ በዓል ጋር በማመቻቸት ከምድር ወገብ የሰሜን ክልል ላሉት ሀገራት የዓለም አቀፍ ኤግዚብሽን አዘጋጅተ ው ነበር።

የኒውዝላድ ፕሮጀክት ደግሞ የፒራሚድ ቅርፅ ያለው ታላቅ «ማማ»ን ሠራች፤ ማማው በአናቱ ላይ የሰዓት መቁጠሪያ ቢኖረውም፣ አጠቃላይ ገጽታው፣ ብሔ ሮችን፣ ባህላዊ እሴቶችን፣ ሀይማኖታዊ ጭብጦችን፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን የሚገልጹ ምስሎች ተቀርጸውበታል፤ እኒህንም ማንም ያለመከልከል እስከ 3000 ዓመተ ምሕረት የሚመለከታቸው ሆነው ተዘጋጅተዋል።

ጣሊያንም ሀገራት ሁሉ ዘላለማዊ ከተማ 'eternal cty' የሚሏትን ሮምን 30

ሚሊዮን ጎብኚዎች ይመለከቷት ዘንድ ቅድመ-ዝግጅቱን በ2000 መግቢያ ላይ አጠናቅቀው ነበር።

***

መስተንግዶው በተጀመረ ጊዜማ «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል እንጂ» የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት «ሰው በእንጀራ ብቻ ይኖራል» በሚልም ተተክቶ ነበር።

የኤደን በርጉ ባልሞራል ሆቴል (Edinburgh's Balmoral Hotel) ሚሊኒየሙን ለሚቀበሉ ጥንዶች የሦስት ቀን ውሎ 8,5000 ፓውንድ አስከፍሎም ትርፍ መስተናገጃ ታጣ። በሮም በሚገኘው ቪላ ላኩፖላ (Villa la coupola) ሆቴል የብሩኒ ሡልጣን ለአንዲት ቀን የከፈሉት 67,000 ፖውንድ ነበር፤ ይህ በኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ይሆናል (1,139,000)።

በሚሊንየሙ ወቅት ከመኝታ ክፍል ውጭ ሆኖ ሰማዩንና አካባቢውን መቃኘት፣ በዚያም ሆኖ በመመገብ ዘና የሚያስብሉ ሆቴሎች ዋጋቸው የትየለሌ ተወድዶ ነበር።

በመጨረሻዎቹ የዲሰምበር 31,1999 የመጠናቀቂያ ሰዓት መድረሻ ላይም፦ በየሀገሩ ልዩ ልዩ ምኞት ይተገበር ጀመረ፦ ሚግ 25 ተምዘግዛጊ በራሪዎችን በመያዝ አቅመኞች ከ80,000 ጫማ በላይ መጠቁ፤ የስኮትሽ 2000ን ተቀባዮችማ ፉጂ (FuJi) ላይ ሚሊኒየሙን ተቀብለው እንደገና ኩክ ደሴቶች (Cook Islands) ላይ በመገኘት ይህን ሚሊኒየም ለ2ኛ ጊዜ ለማክበር ጥረት አደረጉ፣ ተሳካላቸውም።

ሌላው ካምፓኒም ሰዎች ሁለት ሚሊኒየምን ከሚቀበሉ ሦስት ሚሊኒየምን በሕይወት ዘመናቸው ይቀበሉ ዘንድ ለማድረግ ተዘጋጁ፤ በሱፐር ሶኒክ ኮንኮርድ በመጠቀምም ከምሥራቅ ጫፍ ወደ ምዕራብ ጫፍ ተተኮሱ፣ በዚህም 2000ን ሦስት ጊዜ በ3 የተለያዩ ሀገራት ተቀበሉት።

እርግጥ፣ በደፈናው 2000 ዓለሙ ሁሉ ሲበላበት፣ ሲጠጣበት፣ ሲዘፈንበት ብቻ አልኖረም፤ ይልቁኑ በበርካታ ሀገራትም ልማት ተካሂዷል።

በእንግሊዝ፦ ለንደን ታላቁን ወንዝ ቴምስ (Thames) የሚያቋርጥ ሁለት ግዙፍ ድልድይ ለሚሊኒየሙ ይደርስ ዘንድ ተመቻችቶ ተጠናቋል። በካርዲፍ (Cardiff)

75,000 ተቀማጭ ተመልካችን የሚያስተናግድ ስታዲየም ተሠርቷል፤ በግላስኮ ው ሁለት ትላልቅ የሕፃናት መንደሮች ተቋቁመዋል፤ እነዚህ በናሙናነት በእንግሊዝ ሀገር የታዩ ናቸው። ልክ እንዲሁ፣ በሌሎች ሀገሮች ተመሳሳይ ሥራ መሠራቱ አሌ አይሰኝም። ከሰባት ዓመት በኋላ በኢትዮጵያም የእኛው ሚሊኒየምን ለማክበር ስንዘጋጅ፤ አዲስ አበባ በስፋት ታድሳለች፤ መንገዶች፣ አደባባዮች፤ ሆቴሎች የሚሊኒየሙ የመታሰቢያ አዳራሽ፣ ሀውልቶች፤ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን ሀገራችን ተክላለች።



2000ን መቀበል ፈንጠዚያን ከልማት ጋር ብቻ ይዞ እንደ መጣ መገመት ስሕተት ላይ ይጥላል፤ ይልቅስ፣ በተያያዥ የሥልጣኔ ምጥቁነት አደጋንና ጥፋትንም አመላክቶ ነበር፤

የኮምፒዩተር (Computer) ውስብስብ መረብ መስመር ይዞ እስከ ዲሴምበር 31 ቀን 1999 መሄዱ አላጠረጠረም፤ በዚሁ ቀን ከዕኩለ ሌሊት በኋላ ግን በዓለሙ ሁሉ ያሉት የኮምፒዩተር መረቦች ዓመት ቁጥራቸውን መቀየር አለባቸው፤ ሁሉም የተቀመሩት ለእያንዳንዱ ዓመት ሁለት ቤትን ይዘው ነው 73፣ ለ1973፤ 96፣ ለ1996፤ አሁን ግን ሰዓቱ ሞልቶ 1999 ሲጠናቀቅ 00 ይከተላል። በዚህ ቁጥር ደግሞ ጥቅም የሚሰጡት ኮምፒዩተሮች አልተስተካከሉም፤ ወይም ተ ገቢውን ያደርጉ ዘንድ አልደረጀም፤ ይህ ደግሞ የተሠሩትን ሥራዎች፣ ሊሠሩ ያላቸውን ዝግጅቶች፤ የሰማይ የምድር ግንኙቶች ሁሉ ላይ ሊገመት የማያስችልን መዛነፍ ያመጣሉ፤ መዛነፉ ደግሞ «የዓለም ፍጻሜን»ም ጨምሮ ድንገት ሊያስከትል ይችላል። እናም ይህን አስጊ ውጤት ለመቅረፍ 750,000 የዌብ ሳይት መረቦች በሰፊው ዘመቻ ላይ ተወጥረው ነበር። ከዚህም ዘመቻ የተገኘውን አመላካች ወጤት በጥቂቱ እናመላክት፦

መብራት-ነክ መስመሮች በመረጃ መዛነፍ የተነሣ ይጠፋሉ፣ በመጥፋቱም በጥቅሉ በሰው ልጆች ላይ አጠቃላይ ጉስቁልና ይመጣል። አንድ አሜሪካዊ እንደ ጻፈው፣ «**በርካቶች ቅዝቃዜን ባለመቋቋም ይሞታሉ፤ በረሃብ ይጠቃሉ፣ ወንጀል ይበዛል፤ 70% አሜሪካውያን ወይ ሥራቸውን ያጣሉ ወይ ገቢያቸው ያሽቆለቁላል።**»

በሆስፒታሎች የሚያገለግሉ ሕመማንን የሚያግዙ፣ የሚቆጣጠሩ፣ በርካታ ረዳት ሰጪ መረብ-አቀፍ የሕክምና አገልግሎትና መገልገያዎች የሚሊኒየሙ አቆጣጠር በመለየቱ፦ «ታማሚዎችን ወደ ሞት ሊያጣድፉ፣ ወይም በሽታቸውን ሊያባብሱ

ይችላሉ» በማለት ገልጸው ነበር። ዓለም አቀፍ አገልግሎት የሚሰጡ በተለይ ባንክ ቤቶች ወደር በሌለው ኪሳራ ውስጥ እንደሚወድቁ በወቅቱ ይታተም የነበረው የ'Sunday Times'ም አረዳ። ይህ ጥናት በግምት ላይ ብቻ ተመሥርቶ **«ይሆን ይሆናል» የሚል ሳይሆን፣ 2000 ቆጠራውን ሲጀምር በእርግጥ የሚፈጸም አደጋ መሆኑን እወቁት»** ይል ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ የሚፈጠረውን ቀውስ ለመቋቋም እንዲቻል የአሜሪካ መንግስት የ50 ቢሊዮን ዶላር የመጠባበቂያ ብር አዘጋጀቶ ነበር። ኒውክለር በመወንጨፍ ዓለምን የማጥፋት ሥራውን ሊጀምር እንደሚችል በማመን የአሜሪካ እና የሩሲያ የጠፈር ሳይንቲስቶች የጋራ የሆነ የመረጃ ልውውጥን ሥራ መሥራትም ጀመሩ።

በእንግሊዝ ሀገር የሚገኘው የሶፍት ዌር ሥልጠንም ሚሊኒየሙን «ቀውስ» በማለት ጠራው፤ ለዚህ ጥሪው ምክንያቱ ተሳሳሪ ችግርን በመፍጠር የሚመጣው ጦስ «በዓለም ታሪክ ውስጥ ተመን-የለሽ ጥፋትን ለመጀመሪያ ጊዜ በማምጣቱ የከፋ ይሆናል» በማለት ቀውስ የሚለውን ስያሜውን «ትክክል» ብሎት ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ የእንግሊዝ ካምፓኒ ዎች፣ ትላልቅ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሁሉ በቅድመ-ዝግጅቱ ላይ እንዲተጉ ተገደዱ።

ከላይ እየተዘረዘሩ ያሉትን «መባኢ ጥፋቶች» ከመገንዘብ አኳያ በርካታ ሀገራት፣ በተለይም አሜሪካውያን፣ ለድንገተኛ ጥሪው ምላሽ ለመስጠት በየከተሞቻቸው የምግብ ክምችትን፣ የንጹሕ ውኃ ዝግጅትን፣ የሕክምና አቅርቦትን በየአካባቢያቸው አዘጋጁ፤ አንዳንዶችም በከተማ ያሉትን ንብ ረቶቻቸውን በመሸጥ ወደ ገጠር መሄድንና በዚያ ማሳለፍን መርጠው ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው፤ ከኖሩበት ቀዬ ወጡ።

በሀገረ አሜሪካ ያሉ በርካታ ኢትዮጵያውያንም ሰላማዊ ሆኖ ይህን ሚሊኒየም የሚሻገረው የአፍሪካ አኅጉር በተለይም «ለማርያም እንደ አሥራት በተሰጠችው» እና «እጆቿን ወደ እግዚአብሔር በመዘርጋት» ቃል «ተገባላት» በተባለችው ኢትዮጵያ አውሮፓውያን 2000ን በዚያ አሳልፈው ከሚያልፉ ወደ ሀገራቸው መመለስን በመምረጥ መጥተው ነበር።

ሠ) የዓለም ፍጻሜ

ክፍለ ዘመኖች በተጠናቀቁና ሌላው በተጀመረ ቁጥር ከሁሉ ቀድሞ የሚታሰብ የጋራ ግንዛቤ «ፍጻሜ-ዓለም ሊሆን ነው» የሚል ነው።

ይህ እምነት ግን የበለጠ ገዝፎ የሚወጣውና በገሀድ የሚታየው የአንድ ሺህ ዓመት መደምደሚያ ላይ ነው። ሚሊኒየም ሦስት ዜሮዎችን አስከትሎ ሲመጣ የዓለም ታሪክ የሚዘጋበት ዓመት፤ መጋረጃውም ዳግመኛ ሳይከፈት የሚቀርበት የድምዳሜ ዘመን መሆኑን ያመኑ እና ያሳመኑ ብዙዎች ነበሩ።

እርግጥ፣ የዓለም ፍጻሜ «በዚህ ዓመት ይሆናል» ብለው ብዙዎችን ሲያስጠብቁ የነበሩ የተለያዩ እምነቶች ነበሩ፤ የ19ኛው ክፍለ ዘመን ቁስ በጻፈው ድርሳኑ «የዓለም ታሪክ በ1847 ይደመደማል» ብሎ ነበር፤ በመናፍቃን ጎራ የሚፈረጁ ሌሎችም የዓለም ታሪክ በ1874 ፍጻሜ ያገኛል ካሉ በኋላ፣ ዓመቱ ያለ ምንም ልዩነት በማለፉ ወደ 1914፣ ወደ 1915፣ ኋላም 1975ን እያስረገጡ ተከታዮቻቸውን አደርጅተው ነበር። በ1970ዎቹ የተጻፈው የሄል ሊንዲሴይ (Hailindisey) *'The Late Great Planet Earth'* መጽሐፍ **«ፍጻሜ ዓለም እስራኤላውያን የገዛ መንግሥታቸውን ከመሠረቱበት ከ1948 በመጀመር በአንድ የትውልድ የዘመን ክልል መካከል ባለው ዓመት ይፈጸማል» ብሎ ነበር።**

አሜሪካዊው ኤድጋርም በ1988 ከሴፕቴምበር 11-13 ባለው የቀናት ክልል ውስጥ «የዓለም ታሪክ የሚደመደምበት 88 መሠረታዊ ምክንያቶች» የሚል መጽሐፍን ለዓለም አቅርቦ ነበር።

በኢትዮጵያም «**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ኢትዮጵያ» በመባል የሚጠሩት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም በ1967 መስከረም ሁለት ከሥልጣን በወረዱ ጊዜ በርካቶች በገዳም ውስጥ ራሳቸውን ደብቀው የነበሩ ባህታውያን ወደ ከተማ ብቅ በማለት የዓለም ፍጻሜ በዚያው ዓመት እንደሚሆን አሳውቀው ነበር።**

እኒህና በርካታ አድምጡን አንብቡን ያሉ ትንቢት መሰል ንግርቶች ሁሉ ግምቶች ሆነው ቀርተዋል፤ ይህን መሰል አካሄድ ግን በተሻለ ሁኔታ ጎልቶ የመጣበትና የሥነ ፈለግ ጠበብቶች በተቀራራቢ ግንዛቤ በ2000 ፍጻሜ ዓለም በእርግጠኝነት እንደሚሆን ተናግረው ነበር።

በተለይም ሥነ ከዋክብት ተመራማሪዎች ሜይ 2000ን በተመለከተ የፕላኔቶች «የመቀራረብ እና በአንድ መስመር» ላይ የመዞር ያህል የሚጠጋጉበት ወቅት ይሆናል፣ ይህ ሲሆን ደግሞ በምድር የሕዋ ጉዞ ላይ ተጽዕኖን ያሳድራል፤ ከዚህም የተነሣ፣ እልፍ አእላፍን የሚጨርስ የምድር ነውጥ ይፈጠራል። በትይዩም ለመዳን የማይችሉ የበሽታ

መንሥኤዎች ወደ ሰዎች በመድረስ ለሰቆቃ ይበቃሉ በማለት በሚሊኒየሙ ላይ ተነበዩልን::

ሌሎቹ የሥነ ፈለግ ጠበብትም በዲሰምበር (December) 31,1999 ፕሎቶ ከሌላ የሰማይ አካል ጋር ይገናኛል፤ በመቀራረብም ሊላተሙ ይችላሉ፤ ይህም በምድር ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ወጤት «ሁሉንም ዝም ጭጭ በማድረግ የሰው ልጅ ታሪክ ድምዳሜ ይሆናል» ብለዋል::

***

በትይዩ እምነትን በተመለከተ:- በ2000 ሁሉም እንደየገዛ ፈቃዱ በሚሊንየሙ የሚሆነውን ሁሉ ሰብኳል፣ ጽፏል፣ አሳይቷል:: ከዚህም የተነሣ፣ ከአሜሪካ ሕዝብ 20 በመቶው በ2000 የዓለም ፍጻሜ ሊሆን እንደሚችል አምኖ ተቀምጧል::

አልቃይዳን የመሰሉ ፅንፈኞችም በተረዱበት ጎዳና በመዝለቅ ጥፋትን ለዓለም እንደሚያመጡ በመገመትም ከፍተኛ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ተቋሞች ሁሉ እንዲጠበቁ በወቅቱ መመሪያ ወጥቶ እንደ ነበረም መገንዘብም ተገቢ ነው::

የስኮትላንድ ኤፍ ቢ አይ (FBI) « ሚሊኒየሙን ሄደን ለመቀበል ጊዜው መጣ» በማለት ራስን በራስ የማጥፋት ዝግጅትን እንዲያደርጉ ተከታዮቻቸውን ያስተምሩ ስለ ነበሩ፣ መንግሥት ይህን ለመቆጣጠር እንዲሁም ሽብርተኞች በአጥፋቶ መጥፋት ስልት በየቦታው ጥቃት ሊፈጽሙ እንደሚችሉ በመረዳት ያልተቋረጠ ጥበቃ እንዲደረግ ታውጆ ነበር::

በለንደንም በተለይ የ 'Millennium Dome' በመባል የሚጠራው ስፍራ ላይ ጥቃት እንዳይፈጸም ከፍተኛ ጥበቃ፣ በአሜሪካም በስሜን ምዕራብ በሚገኙት ግዛቶች በተለይም ኩክስ (Kooks) ተብለው የሚጠሩት በሚገኙ በት ሁሉ ከፍተኛ ጥበቃ ይደረግ ዘንድ ተደነገገ፤ እስራኤልም በኢየሩሳሌ ምና በዙሪያዋ ባሉ ስፍራዎች ሁሉ ላይ በሚሊኒየሙ የመቀበያ ወቅቶች ላይ ከፍተኛ ጥበቃ ታደርግ ዘንድ ራሷን አዘጋጀች፣ አደረገችም::

እኒህ ሁሉ በተያያዥነት የሚመጣውን አደጋ መጠን ለመግታት እና ለማጥበብ የተደረጉ ናቸው::

በተያያዥ፣ ሚሊኒየሙን አስታኮ የብዙዎችን ቀኝ እጅ ያገኘው **«የአስተሳሰብ ለውጥን ራሳችን ለራሳችን፣ራሳችን ለጎረቤታችንና ለሰው ልጆች**


ሁሉ ማምጣት እንችላለን» የሚለውን የሥነ ልቦና ዝግጅት ግንዛቤ በምንቀበለው 2000 ላይ ደርሰን ቀጣዩን የ3000 ዓመት ጉዞን «ሀ» ብለን የምንጀምርበት ቦታ ይሆናል፤ በዚህም የሰው ልጅ ክብር፣ ጥንቃቄና ፍቅር የሚገባው ፍጡር መሆኑን ማመን ያስፈልጋል» የሚለው ቅቡል አስተሳሰብ መፃኢው ዘመን ተስፋ የሞላበት እና ተግባራዊ ለውጥ የሚታይበት ይሆናል የሚለውን ግንዛቤ በብዙዎች ዘንድ አኑሮ ነበር።

በዚህ ትይዩ፣ ሌላው እንቅስቃሴ «2000 ዓመተ ምሕረትን ለመቀበል እዚህ ድረስ ያስገዘን ታሪካችንን፣ ገድላችንን እና ሰዎቻችን በማስተዋወቅ ነገን ለብሩህነት እናብቃ» «የሚለው የአሜሪካውያኑ የኋይት ሀውስ (White House) የውሳኔ ቃልም በሥራ ላይ ውሎ ነበር፤ በሳይንስና በሥነ ጥበቡ ዘርፍ መንሥኤ የሆኑትን ማሳየት፣ በተያያዥም ቋንቋዎችን፣ ብሔረሰቦችን፣ በእኩል ዐይን የማየት ተገቢነትን ለማስተዋወቅም ዝግጅት ተደርጎ ነበር።

በእንግሊዞች ዘንድም «ኢኩሚኒካል (ecumenical) እንቅስቃሴን በማሳደግ 2000ን መቀበል ይበጀናል የሚል መርኅም በአዲሱ ሚሊኒየም ጸድቆ መመሪያ ወጣለት፤ **«ለምድር ከበሬታን እንለግስ፣ በላይዋ የሚኖሩትን የሰው ልጆች እናፍቅር፣ ሰላምን ለማስፈን የቀደመን በደል ሁሉ ይቅር በማለት እንዘለቅ፤ በዚህም መሠረት ላይ ቆመን ሚሊኒየሙን በመቀበል እንኑር»** ይላል።

ይህ መርኅ፡- ልቅ ከመሆኑ በቀር ምኞቱ በጎ ነው፤ በውስጡ ግን እግዚአብሔርን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ጣልቃ የሚያስገባ ምንም ስፍራ የለውም፤ እንዴት እና በምን ስልት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችልም የሚያሳይ ምንም ክፍተት የለም፤ ይህን መርኅ ግን ዓለሙ ሁሉ ወዶት ሻማውን አድምቆ አብርቶለታል።

በዚህም ቢሆን በዚያ፣ የተዘጋጀው፣ የታለመው፣ ሁሉ መስመር መስመሩን እየያዘ የተጓዘለት፣ የተሰጋለትም 2000 መጥቶ ሄዷል። እንኪያስ በ2000 ጃንዋሪ 1 ምን ተፈጸመ? እንዴትስ አለፈ? እነዚህ ጥያቄ ዎች የዝግጁቱን አጠቃላይ አቅጣጫ ያሳያልና ተከታታዮቹን ክፍሎች ልብ ገዝተን እንከታተላቸው።



ከሰባት ዓመት በፊት ተጠብቆና ተከብሮ በነበረው ተናፋቂ እና አስፈሪ

ቀን የሆነ ምንም አዲስ ነገር አልነበረም።» የቆጠራው መደብ ልክ እንደ 1999 አራትነቱን እንደ ጠበቀ ነበር፤ የምሽትና የንጋቱ ሰዓቱም ምንም አልተዛነፈም፣ የሁለት የፍጻሜ ቁጥሮች ዜሮዎችን አበዛ ካልተባለ በቀር 2000 እንደ ማንኛውም ዓመት ነበር።

ጃንዋሪ 1 እንደ ማንኛውም ቀን ፀሐይ ወጥታበት ጠልቃበታለች፣ ወንዞች አቅጣጫቸውን ይዘው ከመፍሰስ አልታቀቡም፣ የሰማይ አዕዋፍ እንደ በረሩ ውለዋል፣ የባህር ውስጥ ዓሣዎችም መዋኘታቸውንና የዕለት ሥራቸውን አላቋረጡም፣ ሕፃናት በቀኑ ተወልደውበታል፤ አደጋዎች እንደ ወትሮው በቀኑ ተፈጽመውበታል፣ ሰዎች በቀኑ ሞተውበታል፤ በጃንዋሪ አንድ ለፍቅር እጅ የሰጡ፣ ቃል የተገባቡ፣ የተጋቡም ነበሩበት። እንኪያስ፣ እንደ ወትሮው ሁሉ ይህ ሁሉ በዕለቱ ከተከናወነበት፣ ሰዎች ዓመቱን እንዲህ የጠበቁበት ምክንያት ምን ነበር?

መቼም የዘመን ቆጠራ እንዴት እንደ ተጀመረ እቅጩን መናገር አይቻልም፤ ቢሆንም፣ የቀደሙ ሰነዶችና በመከናወን ላይ ያሉ ሥራዎችን በማገጣጠም አንድን አጣቋሚ ምንጭ ማውጣት ይቻላል።

ዘመናዊነት ባልሰፈነበት በጥንቱ ዘመን የሰው ልጅ የጊዜ መስፈሪያዎቹ የሰማይ አካላት ናቸው በፀሐይ፣ በጨረቃ አጠቃላይ ሥርዓት ላይ በመመርኮዝ ንጋት፣ ረፋድ፣ ቀትር፣ ምሽት ተብሎ ይፈረጅ ነበር፤ ይህ ዛሬም አለ።

በትይዩ ግን፣ በምዕራቡ ዓለም ላለው የዛሬ ቆጠራ መንሥኤ የሆኑት ግን ዕብራውያን ናቸው። እነርሱ የቆጠራቸውን አንድ የጀመሩት በቅዱሳን መጻሕፍት ከተመዘገበው የፍጥረትን አመጣጥና የሰውን ልጅ ታሪክ በማገናዘብ ዛሬ ላለው ዓለም መነሻ አኖሩለት፤ በአቆጣጠራቸውም በ19ኛው ዓመት ላይ አሥራ ሦስተኛውን ወር በማከል ዘለቁ፣ ይህ ግን የአምስት ዓመት ልዩነትን በመያዙና ሌሎች ተወሳሳቢ ችግሮች ስለ ነበሩበት፣ ክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በስፋት ሊያለግል አልቻለም።

በጁሊየስ ቄሳር (100-4 ዓ.ዓ) ዘመን ግን የዘመን ቆጠራው አካሄድ መጠነኛ መሻሻሎች ተደርገውበት እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ክርስቶስ

ልደት በኋላ እንዲቀጥል ተደረገ። እርሱም ቢሆን ግን ከፀሐይ ሥርዓተ ዓመት አካሄድ በ13 ቀን ወደ ኋላ ይቀር ነበር። ይህን ደግሞ ለማረም ርዕሳነ ሊቀ ጳጳሳት ግሪጎሪ (ጎርጎሪዎስ) 13ኛ (1502-1885) አሥር ቀኖችን ከቆጠራው አስወጡ። ከዚህም የተነሣ፣ 1582 በያዘችው ኦክቶበር 4 ላይ ቆሞ 5ን ማስከተልን ትቶ ካሌንደሩ በቀጥታ ከ4 ወደ 15 ዘለለ፤ ይህም በሥራ ላይ ዋለ፤ ይህ በጊሪጎሪያን (ጎርጎሪዮስ) ስም የሚጠራው የዘመን ስሌት ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትን ሙሉ ለሙሉ አላገኘም ነበር፣ በተለይም በእንግሊዞች ዘንድ እስከ 1752 ድረስ ድጋፍ አጥቶ ኖረ።

«እኒህን የመሰሉ የቆጠራ እርግጠኝነት በታጣበት አካሄድ 2000ን ነቅሶ በተለየ መንገድ ማክበር አስፈላጊ አይደለም፤» በማለት ሰነዶችን አዛምደው የሚሞግቱ ብዙዎች አሉ። እዚህም ኢትዮጵያ የእኛ ባልነው የ2000 ቆጠራም ላይ ውዝግብ አለ። ይህን ለመገንዘብ የመሠረት ስብሐት ለአብን «ትውፊታዊ ዘመንና ታሪኩ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አመበ» ገጽ 29-101 መመልከት በቂ ነው። እንዲህም ቢሆን ግን፣ ተከባሪው 2000 የላቲኑን ምህፃረ ቃል A.D Anno Domini ን የ«በጌታ ዓመት» ማለት ወጣ።

ሚሊኒየሙ በዓለም ላይ በልዩነቱ በታወቀ የምድር ነውጥ፣ ወይም ዕለተ የኮከብ መውደቅ ወይም ደግሞ «የሕዳር በሽታ፣ አልያም የታኅሳስ ግርግር» ብለን እኛ ጊዜን በምንለይበት መለያ አይታወቅም፤ እውቅናን አግኝቶ ያለው «በጌታ ዓመት»ነት ነው፤ «ጌታን» መነሻ ያደረገ ቆጠራ ነው፤ የዛሬ 2000 ዓመት በተወለደው ሕፃን በኢየሱስ ምክንያት ዓመቶች እየተቆጠሩ ተ ከማችተው እዚህ ደርሰዋል።

ይህ የያኔ ሕፃን በያኔው ይዞታ የዛሬውን ዘመን ያስቆጥራል ማለት አስቸጋሪ ነው። ያደገው በናዝሬት ነው፤ የተገኘውም በገሊላ ነው፤ በዚህ ለተከታታይ 30 ዓመታት ሲኖር ማንም አላወቀውም፤ እርሱም የሌሎችን ቀልብ የሚስብ ምንም ነገር አላደረገም፤ ለሞቱ ሦስት ዓመታት ሲቀሩ ግን አስተምሯል፣ በሰዎች መካከል ተገኝቶ ፍላጎታቸውን ሞልቷል።

በዚህም በየክፍለ ዘመኑ የተነሡ ሁሉ በጋራ የሚሰሙትን መልእክት አስገኝቷል፤ የሩሲያው ፊዶር ዶስቶቪስኪ ይህን ሰው ሲዘክረው ያለለትና የጻፈለት፣ «...እርሱን የመሰለ ሰው ይህች ዓለም መቼም ቢሆን አታገኝም...» የሚል ነበር።

በየዘመኑ የነበሩ በርካታ ሰዎች ለ2000 ቆጠራ መንሥኤ ለሆነው

«ሰው» ይህን መሰል ግንዛቤ አላቸው። ለምን ይሆን ግን ወደዚህ የማጠቃለያ ነጥብ የደረሱት? ለምላሹ አብረን እንዝለቅ፡- ታሪክን ለማጥናት በተነሣን ቁጥር ቁጥሮች ዋንኛ መገልገያዎች ሆነው ይገኛሉ፤ ለዚህም መነሻንና መድረሻን ለማወቅ የግድ ይላል፤ ለዚህ የታሪክ ጉዘት ደግሞ ቅድመ እና ድኅረ በማለት ወደ ፊትና ወደ ኋላ መሄድ ግድ ነው። የልደቱ ዓመት ዓለሙን ሁሉ አያይዞ፣ አግባብቶና አቀናጅቶ ሥራውን ያሠራዋል።

በመሠረቱ፣ በዘመኑ ጽፎት የተወው ምንም መጽሐፍ የለም፣ ባይጽፍም እርሱን በተመለከተ ግን ለተከታታይ ሳይቋረጥ ለሁለት ሺህ ዓመት መጻሕፍት ተጽፈውለታል፣ ተጽፈውበታል፤ ግለ ታሪኩን የያዙት የወንጌል ክፍሎች ሙሉ ለሙሉ ወይም በአብዛኛው ከ2000 ቋንቋዎች በላይ ተተ ርጎመው ተሰራጭተዋል፤ እርሱንም በተመለከተ ካለፉት 50 ዓመታት በበለጠ ባለፉት አምስት ዓመታት ብቻ ስፍር ቁጥር የሌላቸው «እርሱን-ተኮር» ድርሳናት ተጽፈው ተገኝተዋል።

- በዘመኑ የሳለው ሥዕል፣ የአቀናበረው ግጥም፣ የደረሰው ሙዚቃ የለም። በትይዩ ግን፣ የሰውን ሁሉ ሕይወት የሚለውጡ መዝሙሮች፣ ግጥሞች፣ ፊልሞች፣ እና በርካታ የጥበብ ሥራዎች እርሱን በተመለከተ ላለፉት 2000 ዓመታት ለዓለም ቀርበዋል። ይልቁኑ፣ በስሙ የተዘጋጀው ፊልም ከ500 በላይ ቋንቋዎች በመተ ርጎም (አማርኛንም ጨምሮ) ዓለም እየተመለከተው ነው፤ ይህም በዓለሙ የፊልም ታሪክ ውስጥ ብቸኛ ያደርገዋል።
- በዘመኑ የጦር ሠራዊት አዘጋጅቶ አያውቅም፤ የታጠቁ ለዓመፅ የተነሡ ታጣቂዎችንም ለእርሱ ክብር አላደራጀም፤ እልፍ አእላፍ ሕዝቦች ግን ለእርሱ ፈቅደው ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል።
- ተጉዞ በዘመኑ ከሀገር ሀገር፣ ከአኅጉር አኅጉር አልተዘዋወረም፤ የ ረዘመ ጉዞ አደረገ ቢባል የሄደው እዚያው ከዚያው የሆነውን «የናዝሬት-ኢየሩሳሌም» ሊሆን ይችላል፤ ከዚህ ቢቀር ራሱን ያስተዋወቅ ዘንድ ያደ ረገው ሀገራዊ ምልልስ አልነበረውም፤ ያለፉትን 2000 ዓመታት ግን በዓለም ውስጥ ክርስቲያን በመባል እርሱን የሚከተለው ቁጥር እስከ ዛሬ ድረስ ከፍ እንዳለ አለ።
- በዘመኑ «ከዚህ ከታወቀ ትምህርት ቤት» ትምህርቱን አጠናቀቀ ተብሎ አይታወቅም፤ በመደበኛ ትምህርት ቤት አልገባም። ዳሩ ግን፣ በሺህ

የሚቆጠሩ ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ትምህርት ቤቶች በስሙ ተቋቁመዋል።

- ከሰዎች ጋር ያሳለፋቸው ዓመታት ሦስት ተኩል ብቻ ነበሩ፤ በእነዚህም ቢሆን እንቅስቃሴውን ገድቦ በትንሿ ፓለስቲና ብቻ አገለገለ። ከዚያ ማግስት ጀምሮ ግን ትምህርቱ በሳተላይት በመደገፉ፣ በሬድዮ፣ በቴሌቪዥንና በመሰል መገናኛ መስመሮች ሁሉ እየተሠራጨ ይገኛሉ።
- በዘመኑ «ከመንደር-አለፍ» ሆኖ ሳይታወቅ የኖረው ሰው ዛሬ ዓለም አቀፍ አገልግሎት በሚሰጡት እንደ «ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ» (Encyclopedia Britannica) በመሰሉት መዝገበ መረጃዎች ላይ እርሱን በተመለከተ በ30000 ቃላት ተጽፎለት ይገኛል። በእርግጥ፣ ዶስቶፍስኪ ስለዚህ ሰው እንደዚያ ለማለት በቂ ምክንያት ነበረው ያሰኛል።

ረ) ኢየሱስ

በግርድፉ የተተረከለት ሰው ኢየሱስ በመባል ይታወቃል። በዘመኑ ስመ ሞክሼዎች ኖረው ሳይሆን አይቀርም፤ እርሱን ከሌሎች ለመለየት «የናዝሬቱ ኢየሱስ» መለያው ነው።

የናዝሬቱ ኢየሱስን በተመለከተ ፈላስፋው ሩሴል «ኢየሱስ በምድር ላይ የነበረ ሰው ነው ማለት ተገቢ አይደለም፤ ለዚህም አባባሌ ምክንያቱ አሳማኝ መረጃዎች አለመኖራቸው ነው» በማለት ጽፏል። የእርሱን ግንዛቤ የሚጋሩ በርካቶች እስከ ዛሬ አብረውት አሉ።

የብዙዎቹ የጋራ አቋም፣ «ኢየሱስን በተመለከተ አለ የሚባለው ሰነድ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህ መጽሐፍ ደግሞ በብቻው ማረጋገጫ በመሆን ኢየሱስ በዓለም ታሪክ ውስጥ በእርግጥ እንደ ነበረ አድርጎ ለማስቆጠር አይበቃም፣» በማለት ለመጽሐፉ ቅድሚያ አይሰጡም።

የእነሩሴል እና የመሰሎቹ የግንዛቤ አቅም በእርግጥ እንደሚሉት ኢየሱስን ከሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያወጣው ይሆንን? የመጽሐፍ ቅዱስ ጥንታዊ ቅጅዎች ከምንም፣ ከማንም የጥንት ቅጅዎች የበለጠውን የያዙ ናቸው፤ 25,000 በላይ ሲኖሩት፣ የሆሜርና ኤልያድ ከ643 ያልበለጠ መሆኑን ልብ እንበል።

ከ45 ዓመት ጥንቃቄ ከተሞላበት ጥናት በኋላ፣ አጥኚዎች የሰጡት ምስክርነት ከ4000 ዓመታት በላይ የጊዜ መጠንን የያዘው የመጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ ኪዳን ገለጻ በየዘመኑ የያዘውን ጉዞት ጠብቆ ዛሬ በእጃችን ላይ ሲደርስ፡- ያስመዘገበው ታሪክ «እንከን-አልባነትን» ነው። የሥነ ቁፋሮ አጥኚዎች ያሰፉትን

2000 ዓመታት ከዚያም ቀድሞ የነበረውን ዘመን አካትተው አጥንተው በየጊዜው የሰጡት ምስክርነት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተዘረዘሩት መረጃ ዎች ሁሉ ከሥነ ቁፋሮ ውጤት ጋር ሰምና ወርቅ ሆነው መገኘታቸውን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጻሕፍትን በውስጡ በመያዙ 66 የተለያዩ አጀንዳዎች እንደ ያዘ መገመት ስሕተት ነው። ይልቅስ፣ 66 መጻሕፍትን እንደ አንድ ቅጽ መቁጠር የግድ ነው፤ ከ40 በላይ ደራሲያንን ያካተተ በእነርሱም መካከል የብዙ ሺህ ዓመታት ርቀትና ክፍተት የኖረው፣ በየጊዜው የነበሩት ጸሐፊዎች በጊዜ፣ በቦታ፣ በባህል፣ በቋንቋ የማይቀራረቡ ግን ደግሞ ያልተጋጩ፣ ያልተጣረሱ አንድን መልዕክት የያዙ ሆነው ተገኝተዋል። ጄ. አይ. ፓከርም፣ «የየዘመኑ ቋሚ ተአምር» ብሎታል። መጽሐፍ ቅዱስ መፃኢውን ዘመን ለመግለጽ በውስጡ በርካት ትንቢቶችን ይዞ የሚገኝ መጽሐፍ ነው፤ እነዚህን የተ ፈጸሙ እና ሊፈጸሙ ባላቸው የትንቢት መልዕክቶች ላይ ያለመፈጸም ወይም አጠራጣሪ ሆነው በመገኘት ጥያቄ ያስነሡ የመፃኢ ዘመን ገለጣዎች አንድም ስፍራ የለም። ሁሉም በእውነትነታቸው ጸንተዋል።

ክፍት አእምሮ ላለው ጎብረተሰብ ይህ ጭብጥ በራሱ አቅጣጫን ሊያሲዝ ያስችላል። በመሠረቱ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በርካታ ተቃውሞች በመነሣት ሊያጠፉት ወይም ሊያደበዝዙት ቢሞክሩም፣ እስከ 2000 ዓመተ ምሕረት ድ ረስ መጽሐፉ ከ2200 ቋንቋዎች በላይ በመተርጎምና በመሠራጨት ያለ መሆኑን ልብ ማለት ተገቢ ነው።

በተያያዥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በግለሰቦችና በማኅበረሰቡ ሕይወት ውስጥ በመግባት ሕዝባዊ ሊሆን የሚችል የሥነ ምግባር ልክኝነትን ማምጣቱ ሰዎች በምድር ላይ በመኖር ትውልዱ ቀጣይ እንዲሆኑ አብቅቷል።

የ17ኛው ክፍለ ዘመን የታሪክ ጠበብት «John Richared Green>> «ታላቅ ለውጥ በሕዝባችን ዘንድ የሆነበትን ክፍለ ዘመን ለማወቅ ከፈለግን፣ የማወቂያ መንገዳችን አንድ ብቻ ነው፤ ያም እንግሊዞች «የመጽሐፉ ሕዝቦች» ተብለው በተጠሩበት ጊዜ ነው... ያም መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤ ሕይወታቸውን የለወጠላቸው ሰዎች የዛን ጊዜ ለበጎ ሥራና ለለወጥ ተነሣሡ፣ ከተነሡት አንዱ **ዊሊያም** (William Wilberforce) **ነው፤ እርሱም የሰውን ልጅ ክቡርነት በማሳወቅ የባሪያ ፍንገላ ዘመንን አስቆመ። ሌላዋ ኤልሳቤጥ** (Elizabeth) **ነች፤ ሴቶች በእስር ቤት የሚፈጸምባቸውን ግፍና መነወር በአደባባይ በማሳወቅ እስር**

ቤቶች ለእርምተ ጥቅም ብቻ እንዲውሉ አስደረገች። ሎርድ ሻፍትበሪም (Lord Shaftebury) በድሆች ላይ የሚፈጸመውን ግፍ በመቃወም ሰልፍ ወጣ፣ ደጋፊዎ ቹም በአደባባይ የሀሸሽ ስውርና ግልጽ ንግድን፣ ልጆችን ለዝሙት ሥራ ማቅ ረብን፣ የሕፃናት ብዝበዛን በመቃወም ታገለ። ቶማስ በርናርደም (Thomas Barnando) በዘመኑ ብቻ ለ60000 ወላጆ-አልባ የጎዳና ልጆች መጠለያን በማዘጋጀት ተ ምረውና ሠርተው ጎብረተሰቡንና ራሳቸውን እንዲጠቅሙ አደረገ። እነዚህ ተ ጠቃሾች ሁሉ የመጽሐፉ ሰዎች ናቸው ፦የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ሕይወታቸውን የለወጠላቸው ሰዎች።

በኢትዮጵያም መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሰዎች ደርሶ ተመሳሳይ ለውጦችን በማምጣት ሀገራዊ ፋይዳ መገኘቱንም መገንዘብ ተገቢ ነው። ከዚህ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ቀድሞ በነበሩት በ15ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመኖች ውስጥ ጉልህ ታሪክን ትቶ ያለፈውን እስጢፋኖስንና ተከታዮቹን ማንሣት የመጽሐፍ ቅዱስን ጉልበተኝነትና ለዋጭነት ሊገልጽልን ይችላል። እስጢፋኖስ ጎብረተሰቡ ለሥራ መነሣት አለበት፤ ሥነ ምግባሩ ልከኛ ሆኖ ለተከታዩ ትውልድ ምሳሌነት ያለውን አኗኗር ማስረከብ ይኖርበታል፣ ገዳማት የትምህርት ማዕከላት በመሆን ዕውቀትን መጠበቅና ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል በማለት አስተማረ። ይልቁንም፣ እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ ብቻ ሊጸና ይገባዋል በማለቱ ከካህናትና ቀሳውስት ጋር ተጋጨ።

ግጭቱ እያደገ በመሄዱም፣ አፄ ይስሐቅ ዘንድ ቀርቦ ተወነጀለ፤ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥን የጠሉ እና የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክትን ቸል የሚሉ ሰዎች ተሰባስበው፤ «ይህ ተከሶ የመጣው ሰው መተተኛ ነው። ቃሉን እውነት አድርገው እንዲቀበሉት በመተት የሰውን ልብ ወደሱ ያዞራል፤ እርሱ በእጁ ከነካው ማንም ቃሉን ቸል የሚል የለም...» በማለት ትርምስ ፈጠሩ። እነርሱን ብቻ በማድመጥ የሚያምናቸው አብሮአቸው ወገነ፤ ንጉሡ ግን ለሚከሱህ ምላሽ ስጥ ባለው ጊዜ፣ «እነዚህ ሰዎች የሀገራችን ትምህርት ያልሆነ ታስተምራለህ? በማለት ነው የሚጠሉኝ «እውን የዚህች ሀገር ትምህርት ምንድን ነው? እንዴትስ ሆኖ የሌላ ይሆናል? በክርስቶስና በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ እንደ መጽሐፉ ማስተማር ክፋቱ ምንድን ነው?» በማለት መለሰ። ንጉሥ ይስሐቅም ከሳሾቹ መልስ ለጥያቄው እንዲሰጡ ዕ ድል ሰጣቸው፤ ምላሻቸው ግን ጭብጥ-አልባ ሆኖ ማደናገርና ማምታታ ስለ በዛበት፣ «እናንተ ልታስተምሩ ሳይሆን ልትማሩ ይገባልና ደብራችሁን

ለእስጢፋኖስ አስረክቡ» ብሎ ወሰነ።

ይህ ውሳኔ በመጽሐፉ ሕይወታቸው የተለወጡ ሰዎች ሕይወት መገለጫ ነው፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ከግል አልፎ ጎብረተሰቡ ይሰማው ዘንድ ግድ ስለ ነበረ፣ ኢትዮጵያዊው እስጢፋኖስ ንጉሡን ወደ ትግራይ ስመለስ ማዕቀብ እንዳያደርጉብኝ ለመኖርና ለማስተማር የሚያስችል ዋስትና ይሰጠኝ ብሎ መጠየቁን የፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ መጽሐፍ አክሎ ያብራራል።

«...የሚሰብከው እንደ ሐዋርያት የወንጌል ትምህርት ነውና ተቀበሉት፤ እኛም ትምህርቱን ወደነዋል፤ ...ሊከተለው የሚወደውን ሁሉ አትከልክሉ...» በማለት አውጆለት እንደ ነበር ይታወቃል።

እንግዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዚሁ መልክ እያደገ፣ ፈተናዎችን እየተቋቋመ፣ የሰዎችን ሕይወት እየለወጠ የመዝለቅ አቅም ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ መልእክት ሚሊኒየሙን ከመቀበል ጋር ተያያዥ በመሆን መልእክቱ ጎልቶ ይወጣ ዘንድ ማድረግ የ2000 የዝግጅት አካል መሆን አለበት።

ሰ)የዛሬ 2000 ዓመት

የኢየሱስ ክርስቶስ ግለ ታሪክ በወንጌላት ከመስፈሩ በፊት ኢየሱስ በሰዎች መካከል ተገኝቶ በተለይ ሲያስተምርና ሲያገለግል በነበረበት ጊዜ የአድማጮቹና የተለያዩ የጎብረተሰብ ክፍሎች ምላሽ ምን ነበር? በጊዜው ብዙዎች፣ «ይህ መልካም ሰው ነው» ሲሉ፣ ሌሎች «ሕዝቡን የሚያሳስት ሐሰተኛ ነው» (ዮሐ. 7÷12) በማለት የየወገናቸውን አቋም ያሳድጉ ነበር (ዮሐ. 7÷43)። በሕዝቡ መካከል በመገኘት መንፈሳዊውን ትምህርት የሚለግሱት የሕግ መምህራን ደግሞ «ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ሊሆን አይቻልም» ሲሉ፣ የተቀሩት «ኃጢአተኛው» (ዮሐ. 9÷16) በማለት በኃጢአት መርከሱን ያሳወቁ ነበር። በተለይም በፊልጶስ ቂሣሪያ በነበረበት ጊዜ የሕዝቡ ግንዛቤ በመለያየት ከፍቶ ነበር፤ አንዳንዶች «መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት ተነሥቶ መጣ» ሲሉ፣ ሌሎች «ኤልያስ ወይም ኤርምያስን» በመጥቀስ እርሱ ነው ይሉ ነበር (ማቴ. 16÷14)።

መጻሕፍትንና ፊልሞችን ብናጤን የምናገኘው ውጤት ከጥንቱ ጋር ተቀራራቢ ወይም አንድ ዐይነት ሆኖ ነው፤ በዋዜማው ተጽፎ የነበረው «The Holy Blood and the Holy Grail>> መጽሐፍ የሚተርከው ኢየሱስ ለነፃነት ተዋጊ ከመሆኑ ሌላ፣ በምድር ላይ ጋብቻን ፈጽሞ፣ ዘርን አትርፎ እንደ ሰው ኖሮ እንደ ሰው ማለፉን

ያረዳል። በእ.ኤ.አ. በሚሊኒየሙ ማግስት ተጽፎ የነበረው «The Davinci Code>> ደግሞ በጌታ ራት ላይ በጎኑ ያለው የሚወደው ደቀ መዝሙር ሳይሆን፣ ሴቲቱ መግደላዊት ማርያም መሆኗን በመግለጽ ኢየሱስ ከእርሷ ጋር የፍቅር ግንኙነት እንደ መሠረተ በየጊዜውም ያቀርባት፣ ይስማት እንደ ነበር በማስረጃ አስደግፎ የሚላቸውን ነጥቦች ያነሣል፤ ይልቁኑ ኢየሱስ የመጣው ስለ ሰዎች ኃጢአት ምትክነት ሳይሆን፣ ራሱ ለራሱ ኖሮ፣ ኅብረተሰቡን የሚቀሰቅስ ትምህርት አስተ ምህሮ ለመሄድ ነው፤ ይልቅስ መለኮታዊ ገጽታን የሰጡት በኒቂያ በንጉሡ ፖለቲካዊ ስውር አጀንዳ የተታለሉ መሪዎች ናቸው፤ የያኔው አጀንዳ ዓለምን ለማስተዳደር የታለመ እንደ ነበረ በመተንተን በኢየሱስ ክርስቶስና በክርስትና ላይ ይስቃሉ።



ይህ መሳለቅ ግን የዛሬ 2000 ዓመት በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ ነበረ ማወቅ ተገቢ ነው፤ እርግጥ ኢየሱስ ፍጹም ሰው ነበረ፤ ነውም፤ በሰዎች መካከል ሲገኝ አገኛኘ ቱ፣ አደራረጉ፣ አኗኗሩ፣ አሟሟቱ ሳይቀር እንግዳ ጠባይ የለውም። የዘር ሐ ረጉ በሰዎች የተሞላ መሆኑን ለመግለጽ ትወልዱ ወደ ኋላ 40 ዝርዝርን በወንጌሉ አስቀምጦለታል።

ማንነቱን በተመለከተ አራቱ ወንጌላት ተገቢውን መረጃ ባለመጣረስ ጽፈዋል፤ ይህ ዝግጅት በዚህም ሚሊኒየም ኢየሱስን በትክክል ይገነዘበው ዘንድ የሰነድ ቀዳሚ በሆኑት ወንጌላት ላይ በመመርኮዝ ጥቂት ነጥቦችን ያነሣል።

ሸ) አካላዊ ሕይወቱ

ማርያም የእርግዝናዋ ወራትን ስትጨርስ የመጀመሪያ ልጇን ወለደች (ሉቃስ 2÷7)፤ ይህንንም ሕፃን እንደ አይሁድ ሥርዓት በስምንተኛው ቀን አስገረዘችው (ሉቃስ 2÷21)፣ ከዚያም ልጅ እንደሚያድገው አደገ፤ ይህንንም በሉቃስ 2÷16 ላይ ሕፃን በማለት ይጠራዋል፤ ኋላም (ሉቃስ 2÷43) ልጅ /ብላቴና/ ብሎ ዕ ድገቱን ያሳውቃል፤ ይህንንም በአንድ ምዕራፍ ውስጥ አስፍሮ ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሕፃን ... «ወሬ ቆመች አልለገመች» እየተባለለት በመዳህ መሄዱን በኋላም በእግሩ እንዲቆም ወላጆቹ ጥረት አድርገዋል፤ እንደ ሀገሩ ሕፃናት ወተ ትን ከእናቱ ጡት፣ ከፍ ሲልም እየተጋተ፣ ሲዘልቅም ምግብን እንዴት መብላት፣ እንዴት በመፀዳጃ ቤት መጠቀም እንዳለበት እየተዋወቀ ያደገ ነው፤ በአደገ ቁጥር ጡንቻዎቹ መልክ መልክ ሲይዙ፣ ሰውነቱ ሲደረጅ፣ ድምፁ

ሲቀየር፣ ከልጅነት ወደ ወጣትነት ከዚያም ወደ መሉ ሰውነት መምጣቱ ሁሉ አካላዊ ሕይወቱ ነው።

ሰው ስለሆነ እንደ ሰው ምግብ አስፈልጎታል (ማቴ. 21÷18) የሚጠጣውንም እንዲሁ ሽቷል (ዮሐ. 4÷7)። ኢየሱስ ረኻቡን ጉዞ ተጉዞ ደክሞት ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ ማረፍን ተመኘ (ዮሐንስ 4÷6)፣ በመሸም ጊዜ ይተኛ ዘንድ ግድ ሆነበት (ማቴ. 8÷24)፣ በአካሉ መድከሙ እንዳለ ሁሉ፣ ማሰብና ትኩረት መስጠት በእርሱ ዘንድ እንደ ነበሩ ሉቃስ 23÷26 ያሳውቀናል።

በሞቱም ሰዓት በተሰቀለበት በጦር ወጉት፣ በዚህም ጊዜ ደምና ውኃ ከጐኑ ፈሰሰ (ዮሐንስ 19÷34)። ይህ ሁሉ በእርግጥም ኢየሱስ በአካላዊ ሕይወቱ ፍጹም ሰው መሆኑን ይናገራሉ።

ቀ) አዕምሮአዊ ሕይወቱ

ኢየሱስ በአካላዊ ሕይወቱ ገደብ እንደ ነበረው ልብ የምንለው ተወልዶ በአየር ላይ መቶ ሜትር ለመዝለል፣ ወይም በአንዱ በሁለት እግሩ ሁለት የተራራቁ ዛፎች ላይ ለመቆም ባለመሞከሩ ነው። ልክ እንዲሁ አእምሮአዊ ሕይወቱን በተመለከተ ማወቁ ከትንሽ ወደ ትልቅ እየዳበ ረ የመጣለት ሰው ነው። በሉቃስ 2÷52፣ «በእውቀትና በጥበብም ያድግ ነበር» ይለናል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ተርበው ያሉትን ሕዝቦች በተመለከተ ጊዜ የጠየቃቸው፣ «ስንት እንጀራ አላችሁ?» የሚል ነው (ማር. 6 ÷38)። ልጁ በአጋንንት እየተሠቃየ ያለውን አባት ያለው፣ «ይህ ከያዘው ስንት ዘመን ነው?» የሚል ነበር (ማር. 9÷21)። ወዳጁ ከሞተ ከአራት ቀን በኋላ ቢታንያ ሲደርስ የጠየቀው ጥያቄ፣ «በድኑን በየት አኖራችሁት? (ዮሐ. 11÷34) የሚል መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። በዚህም ኢየሱስ ሆን ብሎ እያወቀ ለመጠየቅ ያህል የሚያነሣቸው ጉዳዮች ሳይሆኑ፣ ትክክለኛውን መረጃ ያውቅ ዘንድ ያደረገው የእአምሮአዊ ሕይወቱ ምንነት ነው፤ በዚህም እንደ ሰው መኖሩን ያረጋግጣል።

በ) ስሜታዊ ሕይወቱ

ኢየሱስ ዘርፈ ብዙ በሆኑ ስሜት ገላጭ ጉዳዮች ሁሉ ላይ እንደ ማንኛውም ሰው ሆኗል፤ በቅርቡ ያሉትን ወዳጆቹ (ጓደኞች) (ዮሐ. 15÷15) ብሎ ይጠራቸዋል፤ ከበርካታ ቤተሰቦች ውስጥ ለይቶ አላዛርን፣ ማርያምንና ማርታን ይወዳቸዋል (ዮሐ. 11÷5)፤ የተቆጣበት ጊዜም ነበረው፤ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ እርሱ እንዳያደርሱ ሲከለክሉ ኢየሱስ በዚህ ደስ አልተሰኘም (ማር. 10÷14)

ሀገራዊ በሆነ ጉዳይ ሔሮድስ ሕገወጥ ሆኖ ሲገኝ፣ ማንነቱን ለመግለጽ «ቀበሮው» (ሉቃስ 13÷32) በማለት ገለጸው፤ ሐሰተኛ ነቢያትንም ነጣቂ ተኩላ ዎች (ማቴ. 7÷15) አላቸው፤ ፈሪሳውያንን «ተናዳፊ እባቦች» መሆናቸውን በመግለጽ «እውርነታቸውን» (ማቴ. 23÷17) ልስን መቃብሮች (ማቴ. 23÷27) እና ግብዞች (ማቴ. 23÷29) ብሎታል። በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ሲሸጡ እና ሲለውጡ ባገኛቸው ጊዜ ተቆጣ፣ ሊገበያዩበት ያቀረቡትን ሁሉ ገለባበጠ (ማቴ. 21÷12-13)። በሌላም ጊዜ ኢየሱስ ጥልቅ ኀዘን ገጠመው፤ ኀዘኑም ኢየሩሳሌ ምን በመመልከት ጥፋት ከፊታ እንዳለ መገንዘቡ ነበር (ሉቃስ 19÷41)። ደንቆሮና ዱዳ የነበረውን ባገኘም ጊዜ ማዘኑን (ማር. 7÷34)፣ የሚመራቸው አጥተው በድንግዝግዝና ባለመረጋጋት ያሉትን በማየት መተከዙን (ማቴ. 9÷36)፣ መልካሙን ዜና በሰማ ጊዜ ደስ መሰኘቱን (ሉቃስ 10÷21) ስለ እርሱ ያስተዋወቁን ወንጌላት ይናገራሉ። እነዚህ ሁሉ መረጃዎች ኢየሱስ በስሜታዊ መገለጫዎች ሁሉ ሰው መሆኑን ያስረዳሉ።

ተ) መንፈሳዊ ሕይወቱ

ኢየሱስ ከክፉ መንፈሳውያን ኃይላት ጋር ውጊያ ነበረበት። በአገልግሎት መነሻው ላይ አርባ ያህል ቀናትን ያሳለፈው ከዲያብሎስና ከአጋንንቱ ጋር በመፋለም ነው (ማቴ. 4)። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ «በሁሉ ነገር ተፈትኗል (ዕብ. 4÷15) በማለት ያረጋግጣል፤ ይጸልይ ነበር፤ በወንጌላቱ ሀያ አምስት ያህል ስፍራዎችና ሁኔታዎች ላይ መጸለዩን ይዘረዝራሉ። ከዚህም በመነሣት፣ በጸሎት የተሞላ ሕይወት እንደ ነበረው መገንዘብ ይቻላል፤ ወደ አምልኮ ስፍራዎችም በየቅዳሜው በመሄድ ያመልክ ነበር (ሉቃስ 4÷16)፣ መጽሐፍ ቅዱስንም በማጥናት ይተጋ ነበር።

ከላይ የተዘረዘሩትን የኢየሱስን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ሕይወት ስንመለከት ልናስተውል የምንችለው ዐቢይ ጉዳይ፡- ኢየሱስ ልዩ ፍጡር አልነበረም፣ መንፈስ ወይም በሥጋ የተሸፈነ ሌላ ግኝት አይደለም፤ እንደ እያንዳንዳችን የነበረ ሰው ነው። የኢትዮጵያውያን 2000 ዓመተ ምሕረት ይህን የኢየሱስን ሰው መሆን መገንዘብ አለበት ።

ሚሊኒየሙና ተተኳሪው ነጥብ

በትዳር ዓለም ውስጥ ያሉ ባልና ሚስት የጤና ሕክምናን አዘውትረው

ሊያደርጉ ይችላሉ። ከዚህም የተነሣ፣ ሚስትየው በሚሰሟት እንግዳ ስሜቶች ላይ በመመሥረት የተለያዩ ምርመራዎችን፣ ሽንትንም ጨምሮ፣ አደረገች። ከቆይታ በኋላ፣ ሐኪሙ እንግዳ ባልሆነ ስሜት፣ «አርግዘሻል» አላት። በዚህ ወቅት ባልና ሚስቱ ተቃቅፈው ደስታቸውን ተገላለጹ።



በተመሳሳይ ቀን፣ ሁለቱ ወጣቶች የደራ ጨዋታቸውን እያወኩ ልጅቱ ተራዋ ደርሶ ከሐኪሙ ጋር አሳለፈች፤ የታዘዘችውንም የምርመራ ጎዳናዎች ሁሉ ሄደች፤ ሽንትንም ጨምሮ፤ ሐኪሙ ከአፍታ በኋላ፣ በደመነ ገጽታ «አርግዘሻል» አላት፣ በምላሹ ደነገጠች፣ መግቢያ አጣች፣ ግራ ተጋባች፤ ከጓደኛዋ ጋር ለእርግዝና የሚያበቃ አስተማማኝ ተራክቦ እንዳላደረጉ ታስባለች፣ ግን ውጤቱ ይህ ነበር።



የኢየሱስን እናት በተመለከተ ግን ታሪኩ ልዩ ነበር፤ እርሷም «አርግዘሻል» ተ ባለች፤ የተባለችው ግን በሐኪም አልነበረም በገብርኤል እንጂ፤ በምላሹ፣ ለተ ባለው ነገር ያስደነቃት ዐቢይ ጉዳይ «ድንግልናዋ» ነበር። «ድንግል እኮ ነኝ!» ኢየሱስ ከወንድ ጋር ማርያም በፈጸመችው ግንኙነት የመጣ ሰው አይደለም፤ እርግጥ አወላለዱ እንደ ማንኛውም ሕፃን የእናቱን ማህፀን አስከፍቶ የተወለደ ነው። ሲፀነስ ግን በድንግልና ሆነ። ይህ ነው ተአምር፤ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ያሉ ተጋቢዎች፣ ወይም ከትዳር ውጭ በመጣ እርግዝና የየሰዎች ስሜት የተ ለያየ ቢሆንም እንኳ፣ ሁነቱ ተፈጥሮአዊ እንጂ፣ ተአምራዊ አይደለም።

ተአምር ግን ምንድን ነው? በዚህ ባለንበት ዓለም ምንም ነገር ሳይንሳዊ የሆነውን ሕገ ተፈጥሮ በመሻር ከተከናወነ ብዙዎች ክንውኑን ለመቀበል ይቸገራሉ፤ «መረጃ ያስፈልጋል፤ ሊደገምና ልንሞክረው ይገባል» ይላሉ። በትይዩ ግን፣ ሳይንቲስቶቹ ራሳቸው «ተአምር መኖሩን የማይቀበል ተመራማሪ ምርምሩ ጎደሎ ነው» ብለውም ያብራራሉ።

እንግሊዛዊው ሳይንቲስት ፕሮፌሰር ስር ኖርመን አንደርሶን «የፊዚክስ፣ የኬሚስትሪ፣ የሕክምና ወይም በተለያየ የሳይንስ የምርምር ሥራ ላይ የተከማቹ ሰዎች ሁሉ ያልተጠበቀ፣ እንግዳ ነበር፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሆኑ ምክንያቱንና ውጤቱን እንዴትና ለምን ብለን እንዳንጠይቅ እያስገደዱን ነው፤ ከዚህም የተነሣ እኒህም መኖራቸውን ከግምታችን መክተት ሥራችንን ሙሉ ያደርገዋል» ይላሉ።

ሲ. ኤስ. ሊዊስም (C. S. Lewis) «የትኛውም ጠበብት ተአምራትን ከጥናቱ ውጭ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ከሆነ የረባ ምንም ውጤት አያመጣም፣ ጊዜውን በማባከን ላይ ስላለ

የሚያልመውን የውጤት መቋጫ እርግፍ አድርጎ ትቶ የራሱን አልባሌ ኑሮ ሊጀምር ይገባዋል» በማለት ጽፈዋል።

በትይዩ፣ «በተአምራት ማመንና ተአምርን መጠበቅ የጅሎች የአኗኗር ስልት ነው» በማለት እነ ሰር ኬሄዲ በ "All in the Mind" በሚለው መጽሐፋቸው መዘርዘራቸው አይካድም።

በዋናነት ግን እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ሁሉ በአግባቡ ይሄዱ እና በዘላቂነት ይንቀሳቀሱ ዘንድ ሕገ ተፈጥሮን ደንግጎላቸዋል፤ እንደዚህም ቢሆን ግን እርሱ መብቱ በእጁ ነው፣ ሌላን አሠራር ሌላን ሕግ በፈለገው «ሁነት» ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ማድረግ ይችላል፤ ይህ ልዕልነቱ ተአምራትን ለሁል ጊዜ ያኖራል።

በእግዚአብሔር ዘንድ ተፈጥሮአዊ ሕግም ሆኑ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሕጎች ልዩነት የላቸውም፤ ፈቃዱን መፈጸሚያ ይሆናሉና። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዕብራይስጥ በተጻፉትም ሆነ በግሪክ ቋንቋ በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የእንግሊዝኛው ቃል ተአምር "Miracle" የሚለውን ቃል አናገኝም፤ ይልቅስ፣ ተአምራትን በሰፋ መልክ እንገነዘብ ዘንድ «በድንቃ ድንቅ» (ሐዋ. 2÷43) መገረም፣ መደመም ያለበትን ክንውን ገላጭ ሐረግ፣ እንዲሁም በምልክቶች (ሐዋ. 8÷6) የሆኑት ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን አመላካች በመሆን ተመዝግበው እናገኛቸዋለን። ከዚህም በመነሣት፣ የማርያም ድንግል ሆና ሳለች ኢየሱስን መፀነሷን በመገረምና በመደነቅ በአግባቡ ስፍራ ሰጥተን ልናጠናው ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ከዚህም የተነሣ በሚሊኒየሙ ሊተኮርበት የተገባው የኢየሱስ አወላለዱ ወይም አመጣጡ በሁለት ስፍራዎች በአግባቡ ተዘርዝሯል፤ አንዱ ማቴዎስ ነው፤ በመንግሥት ሥራ ላይ በመገኘት የግብር ሂደቱን ይቆጣጠራል፤ ሌላው ሉቃስ ነው፣ በታሪክ ዘጋቢነትና በሕክምና ሙያ ተክኖ ጎብረተሰቡን ያገለግላል። እኒህ ሁለቱ ምን ብለው ነበር?

ሉቃስን እናስቀድም፦ ሉቃስ 1÷26-38 ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ናዝሬት ተላከ። ናዝሬት በገሊላ ክፍለ ሀገር የምትገኝ ከተማ ናት። መልአኩ የተላከው

ማርያም ወደምትባል ወደ አንዲት ድንግል ነው። እርስዋ ከዳዊት ዘር ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው የታጨች ነበረች። መልአኩም ወደ እርስዋ መጥቶ «አንቺ ጸጋን የተሞላሽ፤ ሰላም ለአንቺ ይሁን፤ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» አላት።

እርስዋም በመልአኩ አነጋገር በጣም ደንግጣ «ይህ ምን ዐይነት ሰላምታ ይሆን?» ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት÷ «ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ፤ እነሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። በእስራኤልም ላይ ለዘላለም ይነግሣል፤ መንግሥቱም መጨረሻ የለውም።»

ማርያም መልአኩን «እኔ ድንግል ነኝ፤ ታዲያ ይህ ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል?» አለችው።

መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ÷ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል እግዚአብሔር ኀይል በአንቺ ላይ ይሆናል፤ ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ሕፃን ቅዱስ ነው፤ የእግዚአብሔርም ልጅ ይባላል። ዘመድሽ ኤልሳቤጥ እንኳ መኻን ስትባል ኖራ አሁን በስተእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፤ ከፀነሰችም እነሆ ስድስተኛ ወርዋ ነው። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።»

ከዚያም በኋላ ማርያም፣ «እነሆ፣ እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ፤ አንተ እንዳልህ ይሁንልኝ» አለችው። በዚህ ጊዜ መልአኩ ተለይቶአት ሄደ።

እርሷም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም እንደ ደነገጠች ሉቃስ ይገልጻል፤ መደንገጧ ተገቢ ነው፤ መልአኩ አንድም ሰውን እያነጋገረ፤ አንድም በመልእክቱ የሚነገራት በማህፀኗ የሚኖረው ወንድ መሆኑን፤ ስሙም ኢየሱስ ተብሎ መጠራቱን ያስረዳታል፤ ይህ ድንጋጤን ይፈጥራል፤ አብልጦ ግን ይህ ሁሉ ድንግል በሆነች ሴት ሕይወት ውስጥ መሆኑ የበለጠ ሊያስደነግጥ ችሎአል፤ በዚህ ድንጋጤ ውስጥ ላለችው ሴት ግን መልአኩ፡- ያረጀችው ሴት ኤልሳቤጥ ካረገዘች ስድስት ወር እንደ ሆናት በማብሰር፣ እግዚአብሔር ተአምርን እንደሚያደርግ የዘመዷን መረጃ ያነሣላታል፣ ማርያምም የእግዚአብሔርን መልእክት ተቀበለች።



ማቴዎስ ደግሞ ከዮሴፍ በኩል በመቆም ለዛሬ የኢትዮጵያ 2000 የዘመን ቆጠራ መንሥኤ የሆነውን ኢየሱስን ያነሣል፡- እንዲህ ሲል (ማቴ. 1÷18 - 25)::

ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ሁኔታ እንዲህ ነው፡- እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳለች ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች:: እጮኛዋ ዮሴፍ ደግ ሰው ስለ ነበር ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት አልፈለገም፤ ስለዚህ በስውር ሊተዋት አሰበ:: ይህን ነገር ሲያስብ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ተገልጦለት እንዲህ አለው፣ «የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ! እጮኛህ ማርያም የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ እርስዋን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ:: እርስዋ ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ስለሚያድን ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ::»

ይህም ሁሉ የሆነው እግዚአብሔር በነቢይ እንዲህ ሲል የተናገረው እንዲፈጸም ነው፣ «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙም «አማኑኤል ተብሎ ይጠራል::» አማኑኤል ማለት «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው» ማለት ነው::

ዮሴፍ ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ባዘዘው መሠረት እጮኛውን ማርያምን ወደ ቤቱ ወሰዳት:: ይሁን እንጂ ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ዮሴፍም የተወለደውን ሕፃን ስም «ኢየሱስ» አለው::



በአይሁዶች የትዳር አደረጃጀት ላይ ሦስት ደረጃዎች አሉ፤ ቀዳሚው «ወቅተ ግንዛቤ » ይባላል:: የነገ ተጋቢዎች ልጆች ከሆኑ፣ የሚያድጉበትና በቅርብ ርቀት የሚተያዩበት የጊዜ ክልል ነው:: እርሱን ተከትሎ «ወቅተ ትጭጭት» ይኖራል:: ይህ የነገ ተጋቢዎቹ በምስክር ፊት ቃል የሚገቡበት ሲሆን፣ ሁለቱም ባልና ሚስት በሚል ስም እየተ ጠሩ፣ ግን ከየቤተሰቦቻቸው ጋር የሚኖሩበት ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ጊዜ ነው፤ ማቴዎስ የሚተርከው በዚህ የጊዜ ክልል የሆነውን ነው:: ይህን ወቅት ቀጥሎ የሚመጣው «ወቅተ ጋብቻ» ነው፤ ይህም አብሮ በመኖር ይደመደማል::

ማርያምን በተመለከተ፡- በወቅተ ትጭጭት «አርግዛ» ተገኘች፤ ዮሴፍ ይህን መረዳት የሚኖርበት፡- ሴቲቱ ከሌላ ወንድ ጋር ተኝታለች በማለት ነው። ከዚህም የተነሣ፣ ማርያም ለፍርድ በሰዎች ፊት ቀርባ ከምትዋረድ እርሷን በስውር መተው የተሻለ እንደ ሆነ አመነ፤ ለዚህም ቢያንስ በሁለት ምስክሮች ፊት የተዋዋሉበትን ወረቀት ከእነርሱ ጋር ሆኖ መቅደድ ነው።

በዚህ ዝግጅት ሰዓት ላይ ግን መልአኩ ጣልቃ ገባ፤ ለእርሱም የማርያም አርግዞ መገኘት የእግዚአብሔር እጅ እንዳለበት እና እርሱ እንደ አሰበው አለመሆኑን ገልጦ አሳየው። ማቴዎስ፣ ዮሴፍ የመጀመሪያ ልጇን እስክትወልድ ድረስ ምንም ዐይነት የሩካቤ ግንኙነት አለማድረጉን አስረዳ። በሌሎች የወንጌል ክፍሎችም፡- ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ ማርያምና ዮሴፍ አብረው በመኖር ልጆችን እንዳፈሩ አሳወቀ (ማር. 6÷3)። የማቴዎስ ዙሪያ ገብ ዘገባ ግን ማርያም በድንግልናዋ ኢየሱስን ፀነሰች የሚለውን እውነት ማብሰር ነው።

ለዘመናት ግን ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ መልእክቶችን በመቀበል ከመትጋት ለምን? እንዴት? መቼ? በማለት የማያቋርጥ ውዝግብ ውስጥ ለመግባት ይናፍቃሉ። ለማመን ሳይሆን ለመከራከር፣ ለመቀበል ሳይሆን ለመቃወም የሚበረቱ ብዙዎች ናቸው።

የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥልጣንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ ተገቢውን መረጃ ማርያምን፣ ዮሴፍንና ኢየሱስን በተመለከተ ሰጥቷል። በትይዩ ግን፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ የተለያዩ እምነቶች ስለ ተመላኪዎቹ ያላቸው እምነት አስገራሚ እንደ ሆነ ጥቂት ምሳሌዎችን በማንሣት እንመዝን፡-

የቡድሃ እናት ልጇን እንዴት እንደ ወለደች ተጽፎላታል። እርሷ አለች እንደሚባለው፣ «በሆዷ ነጭ ዝሆን ከስድስት ጥርሶቹ ጋር ከገባ ከአሥር ወር በኋላ ቡድሀን ወለድኩት በማለት ተናግራለች።

ሂንዱይዝምን በተመለከተ፡- የተመላኪው (Divine Vishnu) አመጣጥ ለማስረዳት እርሱ ሰው ሆኖ ከእናቱ ማህፀን ከመወለዱ በፊት ዓሣ ነበር፣ እንቁራሪትም ሆኗል፤ ድብ ሆኗል፣ ኋላም አንበሳ ሆኖ ተለውጧል። ከዚህ በኋላ ነው በዳቪሉ ማህፀን አድሮ ሰው ሆኖ መወለዱን የምንሰማው።

የግሪኮች አማልክት እናት የሆነችው ፐርሲዩስ (Perseus) ዚየስ ንጉሡ ከሰማይ ከሚወርደው ዝናብ ጋር አብሮ በመምጣት ዋንኛው እንደ ሆነና የታላቁ አሌክሳንደር አባት ከሆነው ከፊሊፕ መቀዶኒያ ሚስት ጋር የተሳሰረ ግንኙነትን በተለያየ መልክ በማምጣት፣ ለእስክንድር መምጣት ምክንያት መሆኑን ትናገራለች።



በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የኢየሱስ ፅንሰት ልዩ ነው፤ በአዲስ ኪዳናችን ከላይ የተጠቀሱትን የሚመስሉ ተረታ ተረቶችን አልያዘም፤ ይልቅስ፣ እንደ ሰው የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑን ያስተ ዋውቀናል፤ ማንም ሊገነዘበው በሚችለው መንገድ። ይልቅስ፣ ሳይንሳዊ በሆነው ትንታኔ በመሄድ ስለ **ህብለ በራሄ** (Chromosomes) ብናጤን፣ ወንዶች x እና y የተባሉ **ህብለ በራሄዎች** ሲኖራቸው፣ ሴቶች x እና x የተባሉ አሉላቸው። "y" ወንድ እንዲሆን ምክንያት ነው፤ ይህ ደግሞ በማርያም በብቻዋ ያለ ወንድ ግንኙነት ሊፈጠር አይችልም፤ ይሁን ቢባል እንኳን ልትወልድ የምትችለው ሴ ት እንጂ ወንድ አይሆንም፤ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራ አብዝቶ ይገለጥ ዘንድ ግን «ወንድ» ልጅ ተወለደ።

ቅድመ - 2000

በአይሁዶች ዘንድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ትልቅ ስፍራ አላቸው፤ በዙሪ ያቸው ያሉት ኃያላን ሀገራትም ሆኑ በውስጣቸው የሚገኙት ተግዳሮታዊ አስተሳሰቦች ሳይጫኑዋቸው በመጽሐፎቻቸው ላይ ብቻ ታምነው ይኖራሉ።

የሙሴና የነብያት መጻሕፍት ለአይሁዳውያን አፈታሪኮች አይደሉም፤ ጊዜያዊ መፍትሔንም ጥለው እንደሚሄዱ ተረቶች አልነበሩም፤ በልሙጡም የእነርሱን ማንነት ብቻ የሚተርክ የታሪክ መጽሐፋቸውም አይደሉም፤ ከዚህ ሁሉ ያለፈ፡- እምነታቸውንና ምግባራቸውን የቀረጹበት የሕያው እግዚአብሔር ቃል ነው፤ ከዚህም የተነሣ ይታዘዙታል፤ ያጠኑታል፤ ሊመጣ ያለውንም ሁሉ በመጠባበቅ ይኖሩበታል።

እግዚአብሔር በአጠቃላይ ከሰው ልጆች ጋር በሀገር ደረጃ ከአይሁዳውያን ጋር ሊሠራ ያለውን እያገናዘቡ ይጽናኑበታል። ከዚህም የተነሣ፣ አንድን መሲሕ ይጠባበቃሉ፤ ተጠብቆ የሚመጣውም በነብይነቱ፣ በካህንነቱ እና በንጉሥነቱ ይገለጥ ዘንድ ይፈልጋሉ (ዘዳግ. 7÷6)።



አንድ ቀን ግን እንዲህ ሆነ፣ ቅድመ - 2000ው ድኅረ-ክርስቶስ ሆኖ ተገኘ። ኢየሱስ፣ እግዚአብሔርን በሚያመልኩበት በአጥቢያቸው በሚገኘው ምኩራብ ተገኝቶ ቁጭ አለ። እንደ ደንቡ፣ እንግዳ ሲኖር ወይም አስተማሪ በመካከል ሲገኝ፣ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ፈትቶ ዘርግቶ ያነብ ዘንድ ይጠበቅበታል። በዚህ መሠረት፣ ኢየሱስ ግብዣውን ተቀብሎ የመጣለትን አላነበበም፤ ዘመነ ክርስቶስ መሆኑን የሚያሳውቀውን በመጽሐፋቸው በነብዩ አማካኝነት ተጽፎ የነበረውን ክፍል ነጥሎ በማውጣት እንዲህ ሲል አነበበ፦ «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል» (ሉቃስ 4÷18-19)።

ይህን እያነበበ ሳለ፣ አድማጮቹ ትንቢቱን ያውቁታልና ተስፋን ይይዛሉ፤ ነገንም ይጠብቃሉ፤ እንዲህም እያሉ ከአራት መቶ ዓመታት በላይ እየተቀባበሉ ቆይተዋል፤ ከዚህም የተነሣ የእንግዳው እስከዚህ ድረስ ማንበብ የሚጠበቅ ነው። ዳሩ ግን፣ የተጠበቀው እንዳልተጠበቀ፣ ተስፋ የተደረገበት ተስፋ እንዳልተደረገበት የሚመስል እንግዳ ቃል ተከትሎ መጣ (ሉቃስ 4÷20-21)። ኢየሱስ «መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ በምኩራብም የነበሩት ሁሉ ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር፤ እርሱም **ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ**» አላቸው።

ይህ የ«ተፈጸመው» እውነት ሲታወጅ፣ ወዲያው ተቃርኖ (ተቃውሞ) አብሮት መጣ። ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያን በየገዛ መንገዳቸው የተረዱበትን አረዳድ ይዘውና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ይዞታ ባለመልቀቅ መንፈስ ተነሣሥተው ኢየሱስን ተቃዋሚ በመሆን ግንባር ቀደሙን ክፍል ተያያዙት። ይህ አጓጓዝ እየበረታ ሲመጣ ለእነርሱና ለመሰሎቻቸው ይኖሩበት የነበረውንና እያደረጉ ያሉትን በመግለጽ ኢየሱስ ላይ «ልብ» ይኖራቸው ዘንድ መከራቸው።

በዮሐንስ 5÷39-40 ላይ የተጻፈልን ማስታወሻ እንዲህ ይላል፣ «እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።» በማለት በገዛ መጽሐፋቸው ተጽፎላቸው የነበረውን የመዝሙረ ዳዊት ክፍልን ገለጠላቸው። ዮሐ. 15÷25፣ «ነገር ግን በሕጋቸው በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ

የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ተቃውሞአቸው ሊሰቅሉት እስከ መወሰን ደረሰም፤ ኢየሱስ ያገኛቸው የነበሩትን ሕግን ከሰጣቸው ከሙሴ ጋር በማገናኘት ዮሐ. 5÷46-47 «... ሙሴን ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?» አላቸው።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ኢየሱስን በተመለከተ ዘርፈ ብዙ የሆነውን አኗኗሩን ሁሉ ያበሰረ መጽሐፍ ነው። ግልጽነትን ተላብሶ ለሚዘረዘረው ሕይወቱ የልደቱ ስፍራ እንኳን እንዳያሳክር፣ በሁለት ስፍራ የሚገኙትን ቤተልሔሞች እንኳን ለይቶ አኑሯል፤ ቤተልሔም በይሁዳ አለ፤ ቤተልሔም ከዛብሎን 70 ማይልስ ወደ ሰሜን ርቆም ሌላ ሞክሼ ይገኛል። ነብያት ግን በሚክያስ 5÷2 «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣«አንቺ በኤፍራታ ምድር የምትገኚ ቤተልሔም ሆይ! ምንም እንኳን አንቺ ከይሁዳ ከተሞች ያነስሽ ብትሆኚም፣ አወጣጡ ከጥንት ዘመናት በፊት የሆነ የእስራኤል መሪ የሚሆን መስፍን ከአንቺ ይወጣልናል» በማለት ለይተው አኖሩ።



እንዲህም ቢሆን ግን፣ በየዘመኑ ተቃዋሚዎች ሳይታጡ እስከ 2000 ዓመተ ምሕረት ተደርሷል። በቅርቡ አንድ ተማሪ፣ «ኢየሱስ በቤተልሔም ይሁዳ መወለዱንና ከዳዊት ቤተሰብ ጋር የተገናኘ ተቆጣሪ መስመር እንዳለው ባወቀ ጊዜ ራሱ በራሱ ተነሥቶ፣ «እኔ ነኝ ክርስቶስ» አለ እንጂ፡- እርሱ እርሱ አይደለም በማለት ዲስኩር ሰጥቷል። እርሱ ግን እርሱን ቀድሞ በሄነሪ ሊዶን የተጻፈውን መሠረት ጣይ መጽሐፍ አላነበበም፤ መጽሐፉ ትንቢት-ተኮር የሆኑ 332 የብሉይ ኪዳን ኢየሱስ አመልካች መልእክቶች እንዴት በትክክል የዛሬ 2000 ዓመት በተወለደው ኢየሱስ ላይ ማ ረፋቸውን ያረጋግጣል። በዝርዝር ሂደቱም የሞቱን የመጨረሻ ቀናትና ሰዓታትን በተመለከተ እንኳን የተጻፉለት መልእክቶች የሚያስገርሙ መሆናቸውን ልብ በሉ፤ በተከታዮቹ እንደሚተው፣ እንደሚካድ፣ በ30 ብር እንደሚሸጥ፣ በመስቀል መከረኝነቱ አጥንቶች እንደማይሰበሩ፣ በልብሱ ላይ ዕጣ እንደሚጣጣሉ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ተተነበዩ፣ ሆኑም።

ክርስትናን ልዩ የሚያደርገውም ይኸው ነው፡- መሠረቱ የሆነው እግዚአብሔር ልዑል አምላክ ስለሆነ በጊዜ ውስጥ ያቀደውን ፕላን ዳር

ያደርሳል፤ ከእነዚህም ዐብዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜው ሲደርስ ከሴት መወለዱና በሕይወት ዘመኑ ሰማያዊ ሕይወት-ለዋጭ ትምህርቶች ወደ ኅብረተሰቡ ገብተው ዓለምን ይለውጡ ዘንድ ማድረጉ ነው። ከዚህም ባሻገር፣ በሞቱ እና በትንሣኤው መፍትሔ-የለሽ ሆኖ በኃጢአት አማካኝነት የፈረሰውን ድልድይ በራሱ መግጠም እና መሸጋገሪያ መሆን ነው።»



ሌላው ክርስትናን ላለፉት 2000 ዓመታት ልዩ አድርጎ ያዘለቀው መሠረታዊ ነጥብ ኢየሱስ እውነተኛ የሚታይ ምሳሌ ሆኖ መሄዱ ነው። 1ኛ ጴጥ. 2÷21፣ «የተጠራችሁት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአል» በማለት ምላሽ ሰጪ መልእክትን ትቶልናል። በምድር ሲኖርም ዮሐንስ በ8÷50 እንደ ገለጸልን፣ «እኔ የራሴን ክብር አልፈልግም» በማለት ሊያከበረው የተገባውን እግዚአብሔርን በትክክለኛው መገለጫው ይገነዘቡት ዘንድ ያደርግ ነበር። በዙሪያው ያሉትንም ሲመክር እውነተኛ ክርስትና-ተኮር ሕይወት በሉቃስ 22÷21 እንደሚነበበው «ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን... እኔ በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ሰው ነኝ» በማለት ያስታውቃቸው ነበር። ይልቁኑ፣ እርሱነቱ ብቸኛ ምሳሌ መሆኑን ሲያበስር፣ «ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነው» (ማቴ. 11÷29) በማለት እርሱን ራሱን የእምነትና የተ ግባር መፈተሻ አድርጎ አሳየ።

ይህ ማንነቱ ነው የዕብራውያን ጸሐፊን፣ «እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ጸንተን እምነታችንን (ሃይማኖታችንን) እንጠብቅ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም» (ዕብ. 4÷14-15) በማለት እንዲጽፍ የተገደደው። **እንኪያስ ክርስትና ማለት የክርስቶስ ሕይወትና አኗኗር ነው**፤ እንግዲህ ቅድመ 2000 ከድኅረ-ልደቱ ጋርና አኗኗሩ ጋር ማየት የተፈለገው መነጣጠል ስለማይቻል መሆኑን ልብ በሉ።

«የተመሰከረለት ሰው»

ታሪክ ታሪክ ሆኖ እንዲመዘገብ፣ እንዲታመንና እንዲተላለፍ ከተፈለገ የሚባልለት ዐቢይ ጉዳይ በሐቅ ላይ በተመሠረቱ መረጃዎች መረጋገጥ አለበት፤ ለዚህ ደግሞ የሚቀርቡ ምስክሮች ዐይነት ብዙነት እና «አቋመ አንድ» መሆን የታሪኩን ዘገባ «እውነት ነው» ብሎ ለመቀበል ያመቻቻ ል። ይልቁንማ፣ ዐይተው፣ አድምጠው ምስክር ለመሆን የበቁማ «የሚመሰክሩለትን ሰው» ለማመን ለመከተልም መሠረት-ጣይ ይሆናሉ።

በዚህ ክፍል ሊዘነጋ የማይገባው «የሚሊኒየሙ ሰው» በዘመኑ በነበሩ በመንግሥት ባለ ሥልጣናት፣ በተቃዋሚ ኃይላት፣ ጠላት ሆነውበት በቆሙ ሰዎች፣ በተከታዮቹ ደግሞም ራሱ ለራሱ የሰጡት እማኝነት ምን ነበር፤ ይህ ዝግጅት ይህን መጥኖ ያቀርባል።



ሀ. የጠላቶቹ ምስክርነት፡- ከሮማዊው ገዥ ከጲላጦስ መጀመር መልካም ነው። ከኢየሱስ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ፣ «እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም» (ዮሐ. 18÷38) በማለት በኢየሱስ ላይ የተመሠረተው ክስ መሠረት-አልባ መሆኑን የገለጸ ቀዳሚ ሰው ነው። በተያያዥ፣ የዚህ ሰው ሚስት ጲላጦስ በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ መልእክተኛ በመላክ፣ «ስለ እርሱ (ስለ ኢየሱስ) ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚህ ጻድቅ ሰው ላይ ምንም አታድርግ» አለችው። ለዚህም ውዝግብ መንሥኤ የሆነው ይሁዳ የአስቆሮቱው ስለ ኢየሱስ ሲመሰክር፣ «ኢየሱስ እንደ ተ ፈረደበት አይቶ ተጸጸተ፣ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌ ዎች መልሶ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ» (ማቴ. 27÷3-4)። በተያያዥ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ እንኳን በጐኑ ከተሰቀለው «በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው ይህ ግን ምንም ክፋት አላደረገም ብሎ ገሠጸው» (ሉቃስ 23÷39-41) በማለት የኢየሱስ ጠላቶች የሆኑት ሁሉም ስለ መከረኛው ሰው ማንም ሳያስገድዳቸው ይናገራሉ። በመጨረሻም፣ በመስቀል ሥራው ኃላፊነቱን ይፈጽም የነበረው ሮማዊ መቶ አለቃም በስተመጨረሻ ያረጋገጠው ምስክርነት፣ «... ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበረ...» (ሉቃስ 23÷47) በማለት እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

ምስክርነት ከኢየሱስ ብርቱ ተቃዋሚዎች መስማት እንዴት ግሩም

ነው!

ለ. <u>የተከታዮቹ ምስክርነት፡-</u> ቀዳሚ የማደርገው የተርሴሱን ሳኦልን ነው፣ ኋላ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በመባል የታወቀውን፤ እርሱ ሰው በትምህርት ዘለቅት ከመሆኑ ባሻገር፣ የብሉይ ኪዳን ሕጎችና ሥርዓቶችን ሁሉ በአግባቡ ተረድቶ የሚያስረዳ ፈሪሳዊ ሰው ነበር። በዘመኑ በብርቱ ኢየሱስን ጠልቶ ተከታዮችን በማሳደድ «የጽድቅ» ተግባር በሚለው ዘመቻ ላይ ፊት አውራሪ ሆኖ የወጣ የጊዜው «ጀግና» ነበር።

«ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት...» (ሐዋ. 9÷1) ወጣ ከማለት ባሻገር ይህ ጉዳይ «መንግሥታዊ ወይም ቤተ ክህነታዊ ፈቃድ» ለማግኘት በክርስትና መንገድ ያሉትን ሰዎች ወንዶችንም፣ ሴቶችንም ቢያገኝ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት የሚያስችል ደብዳቤ ይጻፍለት ዘንድ ጠየቀ (ሐዋ. 9÷2)። ይህን ያደርግ የነበረ ሰው ኋላ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገናኝቶት ክርስቲያን ከሆነ በኋላ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ በማለት መመስከር ጀመረ፡- «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» በማለት ጻድቅነቱን መስከረ። የዕብራውያን ጸሐፊም፣ «ቅዱስና ያለ ተንኰል የሆነ ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባል» (ዕብ 7÷26) በማለትም ተጨማሪ ምስክርነት አከለለት።

ከተከታዮቹ ግንባር ቀደም የሆነው ጳውሎስ ቀድሞ ሲቃወመው ኋላ ላይ ደግሞ በመከተል ስለ ተገነዘበው እውነት ተገቢ የሆነውን መሥዋዕትነት በደስታ ሲቀበል እናስተውላለን። በ2ኛ ቆሮንቶስ 11÷23፣ «እንደ ዕብድ ሰው እላለሁ እኔ እበልጣለሁ በድካም አብዝቼ፣ በመገረፍ አብዝቼ በመታሰር አትርፌ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ...» እያለ፣ እውነት ዋጋ የሚያስከፍል ከመሆን ባሻገር ሌሎችም ይገንዘቡት ዘንድ መሠረት ጣይነቱን ያስቀምጣል፤

ሐ. <u>የልብ ወዳጆቹ ምስክርነት፡-</u> ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሦስቱን በበለጠ ቅርበት ይከታተላቸው ነበር- ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን። እነዚህ ሦስት ሰዎች በአገልግሎቱ የ3 1/2 ዓመታት ውስጥ ከአጠገቡ

አልራቁም፤ ያውቃቸዋል፤ ያውቁታልም፤ ከዚህም የተነሣ፣ በየመጻሕፍታቸው ኢየሱስን አስመልክቶ የምስክር ቃላቸውን ጽፈዋል።

ጴጥሮስ፣ በ1ኛ ጴጥ. 1÷19 ላይ፣ «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና ዕድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ» ይላል። 1ኛ ጴጥ. 2÷22ም፣ «እርሱ ኃጢአት አላደረገም ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም...» የሚል እማኝነቱን ያውጃል።

ዮሐንስንም በተመለከተ፦ በጌታ የተወደደ መሆኑን ለማጽናት በዮሐ. 21÷7 ላይ «ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን «ጌታ እኮ ነው» ሲለው ይገኛል፤ ዮሐንስ የኢየሱስን ንጹሕነትም ሲመሰክር፣ «በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነፃል» (1ኛ ዮሐ. 3÷3) በማለት ስለ ኢየሱስ የቅርቡ መስካሪ ሆኖ ይቆማል።

በእኛም ዘንድ ቢሆን የቅርብ የምንላቸው ወዳጆቻችን ስለ እኛ ደካማነትና ጥንካሬ መናገር ይችላሉ፣ ቀርበው ዐይተውናልና ሊሉ የሚችሉትን ሁሉ በአግባቡ አንሥተው መግለጽ አይሳናቸውም። በኢየሱስ ዘንድም ይህ እውነት ሆኖ አገልግሏልና እርሱን በቅርበት የሚያውቁት ሁሉ «በእርሱም ኃጢአት የለም» (1ኛ ዮሐ. 3÷5) ሲሉ አውጁ።

<u>መ. የራስ ምስክርነት፦</u> ኢየሱስ ስለ ራሱ ለመናገር ወደ ኋላ አላለም። በዓለም ታሪክ ውስጥ ስለ ራሱ «ንጹሕ» መሆን በእርግጠኝነት የተናገረ እና የጻፈ እስከ ዛሬ አልተገኘም። በእግዚአብሔር የተወደዱት የብሉይ ኪዳን ሰዎችም እንኳን ስለ ራሳቸው የመሰከሩት «ነውረኛ» መሆናቸውን ነው። ንጉሥ ዳዊት «ኃጢአትን ፈጸምኩ» (2ኛ ሳሙ. 24÷10)፣ ነብዩ ኢሳያስ፣ «ከንፈሬ የረከሰብኝ» (ኢሳ. 6÷5) ይላል ኢዮብም ራሴን አዋርጄ በአመድ ላይ ተቀምጬ እናዘዛለሁ (ኢዮብ 42÷6) በማለት ነውር በእነርሱ ዘንድ እንዳለ ያረጋግጣሉ።

በአዲስ ኪዳን አማኞችም በማንም ዘንድ ፍጹምና እንዳልተገኘ ለማሳወቅ፣ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም

በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐ. 1÷8) በማለት የሰው ልጆችን ታሪክ ይደመድማል።



ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ስለ ራሱ እንዲህ ይላል፣ «የላከኝም ከእኔ ጋር ነው እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተ ወኝም» (ዮሐ. 8÷29)። ደቀ መዛሙርቱ ምን ብለው መጸለይ እንዳለባቸው ሲጠይቁት ከነገራቸው ቁም ነገር አንዱ፣ «እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን» (ማቴ. 6÷12) የሚለው ዋንኛው ነው። እነርሱ በደለኞች መሆናቸውን ያውቁ ዘንድ ገለጸላቸው፤ በዚህ አስተምህሮ እርሱ ሳይሆን እነርሱ ማንነታቸው ምን እንደሚመስል በመግለጽ፡- እርሱ በምንም ዐይነት በደል እንደማይከሰስ አስተማረ። ዲያብሎስም እርሱን በምንም ዐይነት ነውር ውስጥ ባለማግኘቱ ኢየሱስ፣ «...የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣል፣ በእኔ ላይም አንዳች የለውም» (ዮሐ. 14÷30) በማለት ስለ ራሱ መሰከረ።

ሠ. <u>**የእግዚአብሔር አብ ምስክርነት፡-**</u> የኢየሱስ ጠላቶች ስለ ንጽሕናው አረጋገጡ፣ ተከታዮቹ አመኑበት፣ የቅርብ ወዳጆቹ ስለ እርሱ በገሀድ መሰከሩ፣ ኢየሱስም ስለ ራሱ በማያሻማ ሁኔታ አሳወቀ። በዚህ ዝግጅት የእግዚአብሔር አብን ምስክርነት ደግሞ ማጠቃለያ በማድረግ እንመልከት። ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ እና በተራራ ላይ ሳለ በከበረ ወቅት እግዚአብሔር ተናገረ፤ ንግግሩ በሚወደው ልጅ በኢየሱስ ላይ ነበረ፡- አስቀድሞ፣ «የምወድህ ልጄ አንተነህ በአንተ ደስ ይለኛል» (ሉቃስ 3÷22) አለለት። ኋላም «...በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት» የሚል ድምፅ መጣ (ማቴ. 17÷5)።

እነዚህ አዋጆች እግዚአብሔር የዛሬ 2000 ዓመት ወደዚህች ዓለም ያመጣው ኢየሱስ ነውር-አልባ ፍጹም ሰው መሆኑን ያበስራሉ። ከ2000 ዓመት በኋላ የሰዎች ግንዛቤ የተዛባ ሆኖ ቢገኝ፣ ሊስተካከል ወይም ሊገራ የሚችለው «በርካቶች» ስለ ኢየሱስ ያሉትን በማስተዋል ነው።

እግዚአብሔር «እርሱን ስሙት» ያለበትን ምክንያት ማወቅ ተገቢ ነው፤ ከዚህም የተነሣ፣ ኢየሱስ «እኔ...ነኝ» ያለባቸውን ዐበይት ጭብጦችን እንናበብ፡-

1. «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም፤...» አላቸው (ዮሐ. 8÷12)። ሰዎች በመሠረታዊ የማንነት ጥያቄያቸው ላይ መፍትሔ ለማግኘት መደናቆር የለባቸውም፤ መንከራተት የለባቸውም፤ ኢየሱስ፡- በመንፈሳዊ ጉዳይ ላይ፣ በሥነ ምግባር መለኪያ ላይ፣ ወዘተ... መኖር የተገባውን ሁሉ ገልጦ አሳይቷል፤ ያም በእነዚህ ሁሉ ላይ ብርሀን ሆኖ በመምጣት ነው።

2. «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምን ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም» (ዮሐ. 6÷35)። ኢየሱስ ስለ ምድራዊ ምግብ አልተናገረም፤ እርሱነቱን የገለጸው ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት፣ ራሳቸው በራሳቸው መንገድ የሚሞክሩት መንፈሳዊነት የማይሳካ መዋተት መሆኑን በማሳየት በእርሱ መታመን ነፍስን የሚያጠግብ ምግብና መጠጥ መሆኑን አሳወቀ።

3. «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም...» (ዮሐ. 14÷6)። ማንም በገዛ መንገዱ ወደ እግዚአብሔር አይደርስም፤ በኃጢአት አማካኝነት የተቋረጠው ግንኙነት ሰውን ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ስለ ለየው፣ ሰው በራሱ ጥረት የሚሞክረው የግንኙነት መስመር ሁሉ ወደ ሕያው እግዚአብሔር አያደርሰውም፤ ከዚህም የተነሣ፣ ኢየሱስ የዚህ መሠረታዊ ችግር መፍትሔ እርሱው መሆኑን በማብሰር «እኔ ነኝ» ይላል።

4. «እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» (ዮሐ. 15÷1-5)። ሰዎች በዙሪያቸው በተከበቡት የአኗኗር ስልት ላይ ተመሥርተው ይኖራሉ፤ ያ ኑሮ ግን እርካታን፣ አያስገኝም ወይም የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ሥራ አያሠራም፤ ከዚህም የተነሣ፣ ከዋናው ጋር መገናኘት አማራጭ የሌለው የዕረፍት ስፍራ ይሆናል፤ ለዚህም «ኢየሱስ እኔ ነኝ» በማለት ያበስራል።

5. «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያው የሆነም የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም» (ዮሐ. 11÷22)።

የሰው ልጆች ከዚህ ምድር ኑሮ ባሻገር ሕይወት እንዳለ ያምናሉ፤ ለዚህም ሰው በውስጡ ያለው የገዛ መንፈሱ ተስፋን እስከ ማዶ ባሻገር

ይጠብቅ ዘንድ ያስገድደዋል፤ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከምድራዊ ሞት ባሻገር ሕይወት እንዳለ አስተምረዋል። ኢየሱስ ደግሞ የትንሣኤና የሕይወት መገለጫ መሆኑን ያበስራል፤ በአማኞች ዘንድ ትንሣኤ የሚከወን ዘላቂ ተስፋ ነው፤ ያም «እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል እንባዎችንም ሁሉ ከዐይኖቻቸው ያብሳል ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ኀዘንም ቢሆን ወይም ምሬት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም» (ራዕይ 21÷4) ይለናል። ይህም ሁሉ በኢየሱስ ይፈጸማል። ቀጣዩም ምዕራፍ የትንሣኤውን ምንነት አብልጦ ያሳያል።

ትንሣኤውና «ሰው-ተኮር ቶሪዎች»

የዛሬ 2000 ዓመት ከተከናወኑ አስደናቂ ኢየሱስ-ተኮር መገለጫዎች ውስጥ አንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው፤ መነሣት፤ ሕያው መሆን ነው። እልፍ አእላፍ ሀይማኖቶችን ክርስትና የሚለያቸው በኢየሱስ ሕያውነት ነው - በትንሣኤው።

እስከ ዛሬ ድረስም ለ2000 ዓመታት ባልተቋረጠ ድል የቀጠለው ኢየሱስ ሞትን ያሸነፈ ፍጹም ሰው ከመሆኑ የተነሣ ነው። እንዲህም ቢሆን ግን፣ ትንሣኤውን በሞት ለመደምደም ሰዎች በየጊዜው ተነሥተ ው፡- ኢየሱስ አለመነሣቱን ለማረጋገጥ ሰነድ አለን ብለዋል፤ በዚህ ዝግጅት አለን የሚሉትን አመልክቹ፡- በቀጣይነት የትንሣኤን እርግጠኝነት አስምሬ እደመድማለሁ።

የመጀመሪያው «ሰው-ተኮር ቶሪ»

«መቃብሩ ባዶ አልነበረም፤ እስከሬኑ በዚያ ነበር» የሚል ነው፤ ይህ ግን የአዋጪነት ምንጭና ፍንጭ የለውም፤ ምክንያቱም ቢያንስ አምስት ያህል ሰዎች በእሑድ ጠዋት መቃብሩ ቤት በመድረስ አይተዋል፤ አይተ ውም ያረጋገጡት አካል በዚያ አለመኖሩን ነው። ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 2÷23 ሲጽፍ፣ «እግዚአብሔር አስቀድሞ ባቀደው ባወቀው አሠራር መሠረት ለእናንተ ተላልፎ ተሰጠ እናንተም፣ በዐመፀኞች እጅ እንዲሰቀልና እንዲሞት አደረጋችሁት፣ እግዚአብሔር ግን... ከሞት አስነሣው» ይለናል። ለሞቱ ምክንያት የሆኑት ክፉ ሰዎች ዐመፀኞች ናቸው። የኢየሱስ ትንሣኤ የሐሰት ቃል ከሆነና በድኑ በመቃብሩ ከነበረ፣ ሊያደርጉት የሚገባው መሠረታዊ ሥራ መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ

አንሥተው «ተነሣ» ከመባሉና የምስራቹ ቃል እንደ ሰደድ እሳት ከመሸጋገሩ በፊት ሁሉን እያሳዩና እያስጎበኙ ዜናውን በገለበጡ ነበር፤ ይህ ግን ስላልተቻለ፣ ይህን መከላከያ መንገድ መከተል አልቻሉም።

ሁለኛው «ሰው-ተኮር ቶሪ»

«የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ፈጥነው የገቡት ወደ ተሳሳተ የቀብር ቤት ነው» የሚል ነው። ይህ ቶሪ ከ1907 በኋላ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ብዙዎች ማለት የሚፈለጉትን ሊተነትኑ ሞክረዋል። ዳሩ ግን፣ ይህ ወደ የትም የማያደርስ በአጭር ቀሪ አመለካከት ነው። የመቃብሩን ስፍራ ቀድመው የተመለከቱት ከቀብሩ ከ36 ሰዓታት በኋላ እንጂ፣ ከ36 ወራት በኋላ አልነበረም። ስለ ጎብኚዎቹ ማርቆስ በ15÷47 ሲተርክ «መግደላዊት ማሪያምና የዮሳ እናት ማርያም ኢየሱስን የት እንደ ቀበሩት ይመለከቱ ነበር» ይላል። «ይመለከቱ» የሚለው ገለጻ ስፍራውን ከሌላው ሁሉ ለይቶ ለማወቅ ጉጉትና ጽኑ ፍላጎት እንደ ነበራቸው ያረጋግጣል። በተ ያያዥ፣ ሉቃስ 23÷55፣ «ከገሊላ ኢየሱስን ተከትለው የመጡ ሴቶች ከዮሴፍ ጋር ሄደው መቃበሩን አዩ አስከሬኑም እንዴት እንደ ተቀበረ ተ መለከቱ» ይላል። ከዚህም በመነሣት፣ በእርግጥ ወደ ተሳሳተ ስፍራ እንደ ገቡ ቢገምቱ፣ ሊጠይቁት የሚችሉት ሰው ነበራቸው - ዮሴፍ የገዛ መቀበሪያውን ለኢየሱስ ያደረገው አይዘነጋውም። በተያያዥም፣ በእሑድ ጠዋት በድኑን ሽቱ ለመቀባት ያቀዱ ሰዎችም ስለ ነበሩ፣ ሁሉን በትክክሉ ዐይተውና ተገንዝበው የተመለሱ መሆናቸውን ልብ ማለት ተ ገቢ ነው።

ሦስተኛው «ሰው-ተኮር ቶሪ»

«በድኑን ባልታወቀ ሰው ወይም ሰዎች ተሰርቋል» የሚለው ነው። በጊዜው በድንን የሚሠርቁ ሌቦች ነበሩ። እነዚህ ሌቦች ግን ስርቆትን በከፊል አይፈጽሙም፤ በምንም ምክንያት የተገነዘበትን ትልቅ ጨርቅ ፈትተው ጥለው ልሙጥ በድን ብቻ አይወስዱም። ለሌቦች ዋጋ የሚያወጣላቸው በሽቶ የተቀመመው የመገነዢያ ልብስ ነው። እርሱን ትተው ሥጋውን ቢወስዱ የክስረት ክስረት ይሆንባቸው ነበር፣ ከዚህም የተነሣ አላደረጉትም።

አራተኛው «ሰው-ተኮር ቶሪ»

«የሮማውያን ባለሥልጣናት በድኑን አሸሸተዋል» የሚል ነው። ይህ መላ «ሮማውያን ምን ሊጠቀሙበት ይህን ያደርጋሉ?» የሚል ጥያቄን በቅድሚያ ያስነሣል። እሺ ይሁን ወስደው አርቀውታል ቢባል፣ የትንሣኤው ዜና የተሰማው ወዲያው በመሆኑ፣ በኢየሱስ ተከታዮች የምስራቹ ዓለምን እስኪያናጋ ድረስ የዘለቀው በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው። በእርግጥ፣ ሮማውያን በድኑን ወደ ሌላ ስፍራ ሰውረውት ቢሆን ኖሮ፣ «ይህ የተሳሳተ ዜና ሲሰራጭ ዝም ብለው ባልተቀመጡ፤ ይልቅስ፣ ተከታዮቹን ለማዋረድና ጸጥ ለማሰኘት «ይኸው በድኑ ብለው» ባጋለጡ ነበር፤ ይህን ግን አላደረጉም።

አምስተኛው «ሰው-ተኮር ቶሪ»

«የአይሁድ የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት በድኑን አሸሸተዋል» የሚለው ነው።፣ የቤተ ክህነቱ ሰዎች ኢየሱስን (መሲሑን) በተመለከተ የተጻፉትን ትንቢቶች መገንዘብ ስለሚችሉ፣ ይህን ያደርጉ ይሆናል ብሎ መጠርጠር አስቸጋሪ ነው። እንዳላደረጉ ማረጋገጥ የሚቻለው ግን የኢየሱስ ትንሣኤ ከታወጀ በኋላ መጠነ-ሰፊ ተከታዮች ለኢየሱስ እንደ አደሩ በተመለከቱ ጊዜ ያደረጉት እርምጃ ያሸሹትን በድን በማምጣት በመረጃ ማስደንገጥ ሳይሆን፣ የኢየሱስን ተከታዮች ማሳደድ፣ መግደልና ወደ እስር ቤት መጣልን ነው፤ ይህ ደግሞ ጥላቻቸውን ያስረዳል።

ስድስተኛው «ሰው-ተኮር ቶሪ»

«የኢየሱስ ተከታዮች በድኑን አሸሸተውታል» የሚል ነው። ይህ ዕይታ መነሻ ሊኖረው ይችል ይሆናል። ዳሩ ግን፣ በድኑን በትጋት ይጠብቁ የነበሩ የሮማ ወታደሮች መልዐኩ ወርዶ መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ ባንከባለለ ጊዜ ታላቅ የምድር ነውጥ ተፈጥሮ ስለ ነበር ጠባቂዎቹ መልአኩን በመፍራት ተንቀጥቅጠው እንደ በድን ሆነው ነበር (ማቴ. 28÷2-4)።

ከመቃብሩ በራፍ ላይ ያለው የመዝጊያ ድንጋይ ሲነሣ የተረጋገጠው መረጃ በውስጡ ምንም በድን አለመኖር እና ማንም ሊያየው በሚችል ሁኔታ ሁሉን ግልጽ አድርጎ ማኖር ነበር። ይህም በመሆኑ ነው የሆነው ሁሉ የሚመለከታቸው ካወቁ በኋላ አዲስ ሐሰታዊ ዕቅድ የወጣው፡- «የካህናት አለቆች ከሽማግሌዎች ጋር ተሰብስበው ከተማከሩ በኋላ ለወታደሮቹ ብዙ ገንዘብ ሰጡአቸውና እንዲህ አሉዋቸው «እኛ ተኝተን

ሳለ ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት» ብላችሁ ለሕዝቡ ንገሩ ይህን ነገር ገዥው የሰማ እንደ ሆነ እኛ ጉዳዩን አስረድተን በእናንተ ላይ ችግር እንዳይደርስባችሁ እናደርጋለን» (ማቴ. 28÷12-14) አሉዋቸው። በዚሁ መሠረት፣ «ወታደሮቹ ገንዘቡን ተቀብለው ልክ እንደ ተነገራቸው አደረጉ» (ማቴ. 28÷15)።

ይህ መንገድ ብዙዎችን ከሞትና ከቅጣት አትርፎ ይሆናል፤ አመዛዛኝ አእምሮ ላለው ግን ጉዳይ አጣብቂኝ ጥያቄዎችን ሊያስነሣ ይችላል። ሮማዊ ወታደር በጥበቃ ሥራ ላይ ሆኖ ተኝቶ ከተገኘ ይገደላል። የኢየሱስ በድን ጠባቂዎች ደግሞ በገዛ አፋቸው ተኝተን ነበር ለማለት አቅማቸው አይፈቅድም፤ ሲተኙስ ከወታደሮች አንድ ወይም ሁለት ይተኛ ይሆናል እንጂ፣ እንዴት ሁሉም ይተኛሉ?

ደግሞስ ተኝተው ከሆነ፣ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ድንጋዩን ሲያነሡ፣ በድንኑ ፈታትተው መገነጢያውን እዚያው ሲተዉ፣ እንዴት ምንም ኩሽታ አልነበረም? ይህም፡- የዋህነት ነው፤ ደግሞስ ሁሉ ተኝተው ከሆነ፣ እንዴት ደቀ መዛሙርቱ ሰረቁት ለማለት በቁ? ይልቅስ፣ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ለመስቀል ጉዞ ከጀመረ በኋላ ፈርተው የተደበቁ ተከታዮቹ ነበሩ። ዮሐንስ እንደሚነግረን፣ «በዚያኑ ቀን እሑድ ማታ ደቀ መዛሙርቱ አይሁዳውያን ባለሥልጣኖችን በመፍራት በራፎቹን ዘግተው በቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር» (ዮሐ. 20÷19)። ከዚህም የተነሣ፣ በድን ለመስረቅ ምንም አቅም አልነበራቸውም። አቅም ብቻ ሳይሆን፣ ድፍረትም አልነበራቸውም። እንደው አቅምን ቢያገኙም፣ ቆፍጣና የሮማ ወታደሮች አድፍጠው ይጠብቃሉ፤ መቃብሩ ታትሞ ታሽጓል፤ በየቃፊሩ ጠባቂዎች አሉ፤ ይህን ሁሉ ሊቋቋም የሚችል ድፍረት ኖሯቸው ቢሆንማ፣ ባላሰቀሉትና ባላስያዙትም ነበር።

በትይዩ ደቀ መዛሙርቱ በድንኑ ሊሰርቁ የማይችሉበት ዋና ነጥብም አለ። እነርሱ ከኢየሱስ ጋር 3 ዓመት 1/2 አሳልፈዋል። በዚህም መሠረታዊ ሕይወት-ለዋጭ ትምህርቶችን ከጌታ አግኝተዋል፤ አንዱ ትምህርት ለመንግሥት መታዘዝ፣ ሕግና ደንብን ማክበር፣ እንዲሁም አለመስረቅ ነው፤ ከዚህም የተነሣ አያደርጉትም። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 15÷14-15 ላይ፣ **«ክርስቶስ ካልተነሣማ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት ደግሞም ክርስቶስን**

አስነሥቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለ መሰከርን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነናል» በማለት የትንሣኤው እርግጠኝነት በማወጅ ያጸናል። ይልቅስ፣ ደቀ መዛሙርቱ ከትንሣኤው ማግስት ጀምሮ የነበራቸው አቋም በሐዋ. 5÷29 ላይ ተገለጸ፤ እርሱም «ጴጥሮስና ሐዋርያቱ «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባናል» የሚልን አዋጅ ማውጣታቸው ነው።

ሰባተኛው «ሰው-ተኮር ቶሪ»

«በመሠረቱ ኢየሱስ እኮ! አልሞተም» የሚል ነው ዮሐንስ ግን የጻፈው እንዲህ በማለት ነው፣ «... ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም...» (ዮሐ. 19÷34) ይላል። እንደ ቶሪ አቅራቢዎቹ፣ «ኢየሱስ በሰመመን ውስጥ ነበር፤ ይህንንም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ግንዘቱን በፈጸሙ ጊዜ አላስተዋሉም፤ ቀብረው ሲመለሱ ግን የቀብሩ ስፍራ ቅዝቃዜ እንዲሁም የታሸበት የተቀመመ ሽቱ ከሰመመኑ እንዲቀሰቀስ አድርገውት ስለ ነበረ ተነሥቷል ይላሉ። ይህ አካሄድ በዘላቂነት እንዳይሄድ የሚያደርጉ የራሱ ሕፀያች አሉት። **<u>አንደኛው</u>**፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከመዋሉ ቀድሞ የደረሰበት ግርፋትና ደብዳባ አቅሙን አሳጥቶታል፤ በመስቀልም ላይ ተሰቅሎ ለበርካታ ሰዓታት ተንገላቷል፤ ይህ ሁሉ ከሆነበት በኋላ መሞቱን ለማ ረጋገጥ ጐኑን በጦር ተወግቷል፤ መርማሪዎችም መሞቱን አረጋገጠዋል፤ ይህ ሁሉ በሆነበት ገሀድ ገጽታ ላይ ኢየሱስ ባይሞት እንኳን ከሰመመኑ ሲነቃ የተገነዘበትን ፈትቶና ተነሥቶ ያን ግዙፍ የመዝጊያ ድንጋይ ገፍቶ አስወገደ ማለት እውነታን እንደ መካድ ያስቆጥራል። **<u>ሁለተኛው</u>**፣ **<u>«</u>**ገፍቶ አስወገደ ወጣ እንበል»፣ በወጣ ጊዜ ግን የሚገናኘው ከሮማ ወታደሮች ጋር ነው፤ እነርሱ ሲያዩት ለተገቢው ክፍል ያስረክቡታል፤ ያንንም ደግሞ ያሳውቃሉ፤ ግን አልተደረገም። **<u>ሦስተኛው</u>**፣ ኢየሱስ በእርግጥ መሞቱን ቅዱሳት መጻሕፍት አረጋግጠዋል፤ በዙሪያውም ያሉ ሰዎች ተመሳሳይ ምስክርነትን ሰጥተ ዋል። ከዚህም የተነሣ፣ ቶሪው ቶሪ ሆኖ ይቀራል።

ይልቅስ፣ የትንሣኤውን እርግጠኝነት የማረጋገጫ ዐቢይ መረጃዎችን በጋራ እንመልከት፡- ይህን ማጥናት ደግሞ የ2000 ዓመትን የክርስትናን ጉዞ እና የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት አጉልቶ በማሳየት የኢትዮጵያውያን

ሚሊኒየም ትርጉም ሊሰጥ የሚችልበትን አቅጣጫ ያሲዘናል።

የትንሣኤ መረጃዎች

ለትንሣኤው በርካታ ምስክሮች አሉ። **መጽሐፍ ቅዱስ ራሳቸውን የቻሉ የተጻፉ ስድስት የትንሣኤው ምስክሮችን ያቀርባል።** እኒህም ከትንሣኤው ጀምሮ ለተከታታይ አርባ ቀናት ከሆኑት ውስጥ ይመደባሉ። ኢየሱስን «አትንኪኝ» ላላት ለማርያም ተገለጠላት (ዮሐ. 20÷14-18)። ለመግደላዊት ማርያም ታየ (ማቴ. 28÷8-9)፤ ባለማመን ጸንተው ከነበሩት አንዱ ለሆነው ለገዛ ወንድሙ ለያዕቆብ ታየ (ዮሐ. 7÷5፤ 1ኛ ቆሮ. 15÷7፤ ገላ. 1÷19)። ለበርካታ ዓሣ አጥማጅም ታይቷል (ዮሐ. 21÷1-14)። ለአዋቂዎችና ለጠቢባንም ታይቷል (1ኛ ቆሮ. 15÷8)። ለተ ጠራጣሪዎችም ታይቷል (ዮሐ. 20÷24-28)። ኢየሱስ በአትክልት ሥፍራ፣ በቤት፣ በመንገድ ላይ፣ ከከተማ ውጭ፣ በባህር ዳርቻ፣ በተራራ ላይ በተለያየ ጊዜ እና በተለያየ ቦታ የትንሣኤው ምስክሮች ይኖሩት ዘንድ ሆኗል።

ኢየሱስ ለጥቂት ሰዎች በመታየት ብቻ አልቀረም፤ ከ500 በላይ ለሆኑ ሰዎችም ታይቷል (1ኛ ቆሮ. 15÷6)። ይህ በድግግም የሚታየው ኢየሱስ ግን መንፈስ አልነበረም፤ የማይጨበጥ የማይዳሰስ አልነበረም፣ አብሮ በልቷል ጠጥቷልም (ሉቃስ 24÷30፤ ሐዋ. 10÷41፤ ዮሐ. 20÷21)።

⁎ የደ ቀመዛሙርቱ ሕይወትና አኗኗር ተለወጠ

ኢየሱስ በተለያዩ ስፍራዎችና ጊዜዎች ለተለያዩ ሰዎች በአካል መታየቱና ከእነርሱ ጋር መነጋገሩና መመገቡ የትንሣኤው ትልቁና ቀዳሚው መረጃ ነው። በተያያዥ ግን ሁለት የሚሆነው መረጃ የደቀ መዛሙርቱ አስገራሚ የሆነ የሕይወት ለውጥ መከሰት ነው። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ተጠራጣሪ ነበረበት፣ ከሀዲ እና ፈሪ ነበረበት፣ በየጊዜውም ኢየሱስን ለመገንዘብ ችግር የነበረባቸው፤ ይልቁኑማ ተሰቅሎ ከሞተ በኋ ላ ሞራላቸው ደቀቀ፡- በርን መዝጋት እና መሸሸን ወደ ቀደመ ሙያም መመለስን ሥራቸው አደረጉ። ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ በተለይም ከሳምንት በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱ ከተደበቁበት ወጡ፤ በአደባባይ ላይም ተገኙ፤ በድፍረትም የኢየሱስን መነሣት ከማብሰር ባሻገር፣ ኢየሱስን ይተርኩት ጀመር። ጴጥሮስ ቀድሞ ኢየሱስን የካደ፣ አላውቀውም እያለ የማለ

(ማቴ. 26÷69-70)፣ ኋላ ግን «ጴጥሮስና ዮሐንስ በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩአቸው ጊዜ መጽሐፍን የማያወቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተ ውለው አደነቁ» (ሐዋ. 4÷13) ይላል። ይህ በሕይወታቸው የታየውን ለውጥ ያስመለክታል። **ለውጥ፣ የቀደመን አስተሳሰብና አመለካከት እግዚአብሔራዊ በሆነ እውነት መተካት እና በዚያም ለመኖር ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት ነው።** ይህ ለውጥ የሚነገር፣ የሚሰበክ፣ የሚታይ፣ የሚተ ገበር ነው፤ ይህን መመዘን ወይም ማምጣት የሚቻለው በኢየሱስ **ሕያውነት ወይም የትንሣኤ መሠረት ብቻ ነው።**

3. ክርስትና በዘላቂነት እንደ ሰደድ እሳት የሚስፋፋ ዕድገት ኖረው። ይህ በሦስተኝነት የሚዘከረው ነጥብ፡- የክርስቶስን ሕያውነት በተከታዮች ኑሮ እና ምስክርነት ባልተዳረሰበት ሀገር ሁሉ ተቀባይነትን እያገኘ መዝለቁን ያረጋግጣል፤ የእግዚአብሔር ቃል ይህ መስፋፋት በጥቂት ዓመት ውስጥ ተግባራዊ ከመሆኑ የተነሣ፣ የክርስትና ጠላቶች «...እነዚህ ዓለምን ሁሉ ያወኩ ሰዎች አሁን ደግሞ ወደዚህ መጥተዋል..» በማለት በተሰሎንቄ ወንጌል እንዳይዛመት ጥረት አደረጉ (ሐዋ. 17÷6)። የትንሣኤ ው ኃይል ግን ተሰሎንቄን አልፎ ወደ ቤሪያና አቴና ፈጠነ፡- ይህ ፍጥነት በአራተኛው ክፍለ ዘመን ክርስትና የሮማ መንግሥት እምነት ይሆን ዘንድ አስገደደ።

ጴጥሮስ በመነሻ ስብከቱ አጽንኦት የሰጠበት ጭብጥ በ2000 ዓመት ሙሉ አለመዘንጋቱ ዋናው ነጥብ ነው። የእርሱም ምስክርነት በሐዋ. 4÷10 ላይ ተቀምጧል፣ «ይህ ሰው ድኖ በፊታችሁ የቆመው እናንተ በሰቀላችሁትና እግዚአብሔር ከሞት ባስነሣው በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደ ሆነ ለእናንተና ለሁላችሁ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን» ያለለት እውነት እስከ ዛሬ ዘልቋል፤ ይቀጥላልም።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 15÷4 ላይ ስለ ወንጌል፣ ስለ ክርስቶስ የሰጠው ድንጋጌ በዕውነትም የዛሬ 2000 ዓመት በኢየሱስ ልደት እግዚአብሔር ከሰው ጋር የሆነበት ተአምራዊ ድርጊት በዘመናት ሁሉ ውስጥ እውነት መሆኑን ማወጅ ነው። ይህም የመጪውን የ1000 ዓመት ዝግጅት ወይም ቅበላ ያመቻቻል። የእግዚአብሔር ቃል፣ **«በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈው ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ»**

ይላል።

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅዱ በማንም አይሻርም፤ ሆኗል ይሆናልም፤ ለዚህ አገልግሎት ደግሞ እግዚአብሔር የተልዕኮው ተባባሪ አድርጎ የእርሱ የሆኑትን ሁሉ ጠርቶ ኃላፊነትን ሰጥቷል፤ ይህን ኃላፊት በግልና በጋራ መፈጸም የሚሊኒየሙ መገለጫ ሊሆን ይገባዋል።

ማጠቃለያ

ይህ ዝግጅት በውስጡ መርዶም የምስራችም አለበት። ይህን ጎዘን እና ይህን ደስታ መገንዘብ፣ ተገንዝቦም የተግባር ሰው መሆን የዚህ ጽሑፍና የ Ethiopia Bible Baptist Church Fellolwship ራእይ ነው።

ዝግጅቱ በቀዳሚ የመግቢያ ጽሑፉ የዓለም የወንጌላውያን ካውንስል ኢየሱስን «የሚሊኒየሙ ታላቅ ሰው» አድርጎ ቢያቀርበውም፣ በዚያ ከየአጥቢያ ተወክለው የመጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች «በምንም መልኩ አይመጥንም» በማለት፣ «ኢየሱስ በማንም የማይፈለግ የሚሊኒየሙ ሰው» ብለው እንዳስወገዱት ልብ ማለት ተገቢ ነው። ቤተ ክርስቲያን የሞተላትንና መሠረት የሆናትን አግልላ በሌላ ጉዳይ ላይ እንዳተኮረች ይህ መልእክት ያረዳል፤ ዘመናት በተቆጠሩ ቁጥር የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ብርሃንና ጨው እያደረገች ጌታዋን ታከብር ዘንድ ግድ ይሆናል። ይህ የሚሊኒየም ዝግጅት ደካማ ጎናችንን አርመን በቀናው መንገድ ላይ መሄድን እንመርጥ ዘንድ ይመክረናል።

በትይዩም፣ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበረውን የኢትዮጵያውያን የ2000 ዓመት ዝግጅትን ጎብረተሰቡና መንግሥት የ2000 የምሕረት ዓመት ምክንያት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በዋነኝነት በማካተት ኢየሱስ ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት አለባቸው፤

ብዙዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአት መፍትሔን ብቻ በመስጠት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ መንገድ መሆኑን ያስታወቁ ይሆናል። ኢየሱስ ግን፣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ከሰዎች ጋር፣ ሀገሮች ከሀገራት ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያስተ ማረና የመከረ፣ እውነተኛው የሰላም፣ የፍቅርንና የዕድገትን መሠረቶች ሁሉ በኑሮውና በትምህርቱ ያስቀመጠ ፍጹም ሰው እና ፍጹም አምላክ የሆነ ልዑል ነው።

ከዚህም የተነሣ ኢትዮጵያውያን ለላቀ ዕድገታችን፣ መተሳሰባችንና ፍቅራችን መልሕቅ ሆኖ ሊያኖረን የሚያስችለውን «ኢየሱስን ከሚሊኒየም ዝግጅታችን አውጥተን ደፋ ቀና ብንል፤ ውጤቱ «ሩቅ አሳቢ፣ ቅርብ አዳሪ» ሆኖ መቅረት ነው።

በመጨረሻም፣ ዝግጅቱ በአብዛኛው ትኩረት ያደረገው የዛሬ 2000 ዓመት በቤተልሔም በመወለድ «እግዚአብሔር ከሰው ጋር» የሆነበትን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የዘከረ መልእክት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት አማኞች የወንጌልን ምሥጢር በመግለጥ የኢየሱስ አዳኝነትን በማብሰር ሁላችን ወደ ክርስቶስ ቁመት ለማደግ እንበረታ ዘንድ ነው። በትይዩም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም ዛሬም ለዘላለምም ያው መሆኑን ለማብሰር ነው (ዕብ. 13÷8)፤ አሜን።

እንግዲህ በኢትዮጵያውን ሚሊኒየም፣ የመጨረሻው መጨረሻ ማጠቃለያዬ፡- ሀገራችን ሚሊኒየሙን ለመቀበለ በርካታ ዘርፈ ብዙ ሥራ ዎችን ሠርታለች፣ በዚህም ልትመሰገን ይገባታል። ብሔር ብሔ ረሰቦች ተከባብረው እንዲኖሩ፣ በእምነት ልዩነት መናቆር ሳይሆን መቻቻ ልን፤ ድህነትን በሥራ መተካት፣ ሥነ ፍጥረትን በመንከባከብ፣ ቀጣይ ሥራን መሥራት ሁሉም እንዳለበት ተዘክሯል፤ ለተግባራዊነቱም ሁኔታ ዎች ተመቻችተዋል። ከዚያም ባሻገር፣ የኢትዮጵያን ሚሊኒየም በሀገር ደረጃ እና በአፍሪካ ደረጃም ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ጥረት ያደርጉትን ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶችን ማመስገን ተችሏል።

በቀዳሚነትም መንግሥት «ልዩ የሆነውን የሚሊኒየሙን የወርቅ ኒሻን» ለሼኽ መሐመድ አል-አሙዲ ሸልሟል፡ በጳጉሜ 6 ቀን 1999 ዓ.ም በልዩ ዕትሙ ሚሊኒየም-ተኮር ርእሱን ያስተናገደው አዲስ አድማስም ለሕዝብ ምላሽ በጠየቀበት መጠይቅ የሚሊኒየሙ ምርጥ መሪ በማለት አፄ ቴዎድሮስን፣ አፄ ምኒልክን፣ አፄ ኃይለ ሥላሴን በቅደም ተ ከተል አስታውቆ፤ የሚሊኒየሙ አትሌት በማለትም፣ ኃይሌ ገብ ረ ሥላሴን፣ አበበ ቢቂላንና እንዲሁም መሠት ደፋርን በተከታታይ አስተናግዷል። ፕሮፌሽናል ምሁራንንም በተመለከት ፕሮፌሰር ቅጣው እጅጉ፣ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅንና ዶ/ር አክሊሉ ለማን የሚሊኒየሙ ምርጥ ምሁራን በማለት አሳውቋል። ደራሲያንንም በተ

መለከተ ሎሬት ጸጋዬ ገመድህንን፣ ሃዲስ አለማየሁንና ከበደ ሚካኤልን አከታትሎ በማብሰር ደስታውን ገልጿል።

የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በርካታ እይታዎችን በአደረጀበት በመስቀል አደባባይም የሺው ዓመት የኢትዮጵያ መሪዎች በማለት አፄ ኃይለ ሥላሴን፣ ኮሌኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን፣ ፕሬዝዳንት መለስ ዜናዊን፣ ፕሬዝዳንት ነጋሶ ጊዳዳንና ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስን በምስል በማስደገፍ አስተዋውቆናል።

እኒህ ሁሉ የኢትዮጵያን ሚሊኒየም በአግባቡ ለማየት ያግዘን ዘንድ የተከናወኑ ክንውኖች ናቸው።

የዚህ ዝግጅት አቅራቢ ግን የዛሬ 2000 ዓመት ሰው በመሆን በሰዎች መካከል በመገኘት ዘርፈ-ብዙ ስለ ሆኑት የሰው ልጅ ችግሮች ጽኑ መፍትሔን የሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስን በቀዳሚነት ክርስቲያኖች፣ በተ ከታይም ከእነርሱ ብርሀንነትና ጨውነት የተነሣ ሀገራችንን፣ አኅጉራችንንም ጭምር በምስራቹ ቃል ለማላቅ መነሣት ተገቢ መሆኑን አውጃለሁ።

ከዚህ ቀደም በጸሐፊው የተዘጋጀ መጽሐፍ፡-

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡- የጥንቱ እና የመካከለኛው ዘመን

በዝግጅት ላይ ያለ፡-

የዕብራውያን መልእክት ትምህርት